

ከመስከረም እስከ መስከረም

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከመስከረም 2018 ዓ.ም እስከ መስከረም 2019 ዓ.ም ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

ቅጽ 9 VOL 9

ከመስከረም እስከ መስከረም

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከመስከረም 2018 ዓ.ም እስከ መስከረም 2019 ዓ.ም ያደረጓቸው ንግግሮችና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ክፍል

ISBN 978-99990-1-482-3

ISBN 978-99990-1-482-3
Copyright © 2026 Office of the Prime Minister – Ethiopia
ጥቅምት 2019 ዓ.ም. ታተመ

ማውጫ

ክፍል አንድ - የአማርኛ ንግግሮች እና መልዕክቶች

የጅግጅጋ ኮሪደር ልማት ጉብኝት ---------- 1

የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካ፣ የጎዴ ነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ ፕሮጀክቶች እና

የኦጋዴን የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት ማስጀመርያ ----------6

ፕልስ አፍ አፍሪካ ሚዲያ ስራ ማስጀመሪያ----------12

በክረምት በጎፈቃድ መርሃግብር በሀላባ እና ከምባታ ዞኖች የተገነቡ

ሞዴል የገጠር መንደሮችን ማስረከብ ---------- 16

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለማው ስማርት የፍርድ ሥርዓት ----------27

በምስራቅ ሸዋ ዞን የስንዴ ምርት ሥራዎች ጉብኝት----------30

የታደሰውን የፋሲል ጊቢ ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------34

የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ኢንስቲትዩት ጉብኝት ----------39

በመደመር መንግሥት እይታ፣ የዘርፎች እመርታ - ለብልጽግና

ፓርቲ መሪዎች የተሰጠ ስልጠና ----------45

በመደመር መንግሥት እይታ፣ የዘርፎች እመርታ - ክፍል 2 ----------68

20ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል----------94

የምሁራን ሚና ለሀገር ብልጽግና ጥናታዊ ፅሑፍ----------98

የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፍያ ግንባታ ማስጀመርያ---------- 127

በደቡብ ምዕራብ ክልል በጉራፈርዳ ወረዳ የገጠር ኮሪደር ጉብኝት----------135

የደንቢ ሎጅ ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------138

የአይሻ-2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ምረቃ ሥነ-ስርዓት ----------145

የሸበሌ ሪዞርት ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------150

የብላቴ ወንዝ ሰፋፊ የፍራፍሬ ልማቶች ጉብኝት----------153

የመከላከያ ሠራዊት የልዩ ዘመቻዎች ዕዝ 65ኛ ዓመት የምስረታ በዓል----------157

በድሬዳዋ የተደረገ ጉብኝት----------161

በቁንድዶ ተራራ የተደረገ ጉብኝት---------- 166

በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ናሲአል ዋሻ የተደረገ ጉብኝት---------- 168

የኒዒን ሌ ፓልም ሎጅ ምረቃ ሥነ-ስርዓት ----------171

የአዲስ ስፖርት ፓርክ ምረቃ ሥነ-ስርዓት ----------177

አርማወር ሐንሰን የምርምር ተቋም----------181

አሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ----------185

የቱሪዝም ጸጋ ለሀገር ብልጽግና ----------190
የመሶብ አንድ ማዕከል ተንቀሳቃሽ አውቶቡስ አገልግሎት ስራ ማስጀመሪያ----------197
የቶዮ ሶላር ኢነርጂ ሁለተኛው ምዕራፍ ምረቃ ሥነ-ስርዓት ----------201
የማህበራዊ ልማት እመርታ ለሀገር ግንባታ ፎረም----------206
በሁዋጂያን ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የተደረገ የፋብሪካዎች ጉብኝት----------215
የ2018 ዓ.ም ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ----------217
በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሱሉልታ ወረዳ የስንዴ ማሳ ጉብኝት----------223
በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የቀረበ ሃሳብ----------227
የገላን ጉራ የኢንዱስትሪ መንደር ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------232
የጎዴ የዩሪያ ማዳበሪያ ማምረቻ ግንባታ ፕሮጀክት ጉብኝት----------238
'የመረጃ ሉአላዊነት ለፖሊሲ ነፃነት' ጉባኤ----------240
የላፍቶ ሆስፒታል ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------245
በምሥራቅ ቦረና የስንዴ ልማት ክላስተር ጉብኝት----------249
የነገሌ ቦረና ገዳ አውሮፕላን ማረፊያ ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------250
የእንጦጦ-ቀጨኔ መድኃኔዓለም የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ምረቃ ----------253
የቢሾፍቱ አየር መንገድ ግንባታ ጉብኝት ----------258
የ2018ዓ.ም አረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር---------- 263
የ2018 ዓ.ም የክረምት የበጎ ፈቃድ ዘመቻ ማስጀመሪያ---------- 269
ዲጂታል ለልህቀት ጉባዔ ----------273
ከእንጦጦ እስከ ቀበና የወንዝ ዳርቻ ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------283
በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን የልማት ስራዎች ጉብኝት----------287
የአርባ ምንጭ የኮንፈረንስ ሪዞርት ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------289
ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የአውሮፕላን ማረፊያ ምረቃ ሥነ-ስርዓት ----------299
ሀገራዊ ምክክር የማስጀመሪያ ሥነ-ስርዓት---------- 305
የ2018ዓ.ም የአንድ ጀምበር ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር----------314
የባህር ዳር ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን
ማረፊያ አዲሱ ተርሚናል ምረቃ ሥነ-ስርዓት----------316
ሞጆ ዘመናዊ የሎጂስቲክስ ማዕከል ማስፋፊያ የመጀመሪያ ምዕራፍ----------320

መልእክቶች

የ2018ዓ.ም አዲስ ዓመት መልእክት----------324
እንኳን ለመስቀል በዓል አደረሳችሁ!----------326
እንኳን ለኢሬቻ መልካ በሰላም አደረሳችሁ!----------327
እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ!----------328
እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን!----------331
እንኳን ለ130ኛው የዐድዋ ድል በዓል አደረሳችሁ!----------334
እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል አደረሳችሁ፤ አደረሰን!----------335
እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል አደረሳችሁ፤ አደረሰን!----------338
እንኳን ለ85ኛው የጀግኖች አርበኞች በዓል አደረሳችሁ!---------- 341
እንኳን ለ1447ኛው የዒድ አል አድሐ በዓል አደረሰን፣ ----------343
እንኳን ለ1501ኛው የነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) የመውሊድ በዓል አደረሳችሁ----------345
የ2019ዓ.ም አዲስ ዓመት መልዕክት----------346

ክፍል ሁለት - በአፋን ኦሮሞ የተደረጉ ንግግሮች እና መልእክቶች

“Namoota ofiif aarsaa ta’anii Baalee bareedduu tiksanii
dhalootatti dabarsaa jiran kabajuu fi dhufanii ilaaluun
hedduu nama gammachiisa.”----------351
“Jaalalli Walloorraa Maddu, Itoophiyaa maraaf gahaadha!”---------- 355
“Gaafa carraa argannee ummata bulchinu, ummata
boossiisuu osoo hin taane, kadhannee mana ijaarree
, namoota dadhabaa gargaaruu danda’uun
carraa guddaadha” ----------358
Sirna Jalqabsiisa Ijaarsa Piroojektii Induustirii
seenaa keenya duraanii kan eegedha”----------362
“Wal-jaallannee, waliin dhaabbannee of jijjiiruu,
biyya jijjiiruu ni dandeenya.”----------376
Sirna Eebbaa Piroojektii Misooma
Bu’uraa Jallisii Qeexoo----------385
“Haroon Dandiifi naannoonsaa hiika seenaa
gadifagoo kan qabuufi seenaa keenya duraanii kan eegedha”----------393
“Cimnee Hojjennaan, Badhaadhina Guutummaatti
Dhugoomsuu Dandeenya!”----------398

“Gadaan quufaa-gabbina kan jedhu jecha
qofaa ta’ee hin hafu. Dhugaatti hiikamee,
quufnee, gabbannee buluuf halkanii-guyyaa ni hojjenna.”----------406
“Dachiin Booranaa, dachii Arsii fi Baalee fakkaatte.
Kana arguu kootti gammachuu jechaan ibsuu
hin dandeenyetu natti dhagahame.” ----------410
Giddugala Aadaa Booranaa ----------412
Booranni ummata aadaa fi seenaa keenya
rakkoo yeroo dheeraa keessatti kuunsee
tursuu danda’eedha---------- 417
Piroojektii Bishaanii ----------421
Gahee siiviil sarviisiin jireenya ummata keenyaa
fooyyessuu keessatti qabu ---------- 427
Ergaa Kabaja Ayyaana Irreecha Malkaa ---------- 432

ክፍል ሶስት - በሲዳምኛ የተላለፉ መልእክቶች

Fooliisho ontte - Sidaamignuni Sa’inno sokka ---------- 435

ክፍል አራት - በእንግሊዝኛ የተደረጉ ንግግሮች እና መልእክቶች

The World Atomic Week International Forum (WAW-2025) ---------- 437
24th COMESA Summit of Heads of State and Government ----------439
State Banquet for Malaysian Prime Minister ---------- 441
PM address at G20 ---------- 443
PM speech on economic rise at G20 ---------- 446
State Banquet for Indian PM ---------- 448
Prime Minister’s Remark at the 39th AU Summit ---------- 450
Remark at 80th year anniversary of UN ---------- 455
Opening Address at the “Ethiopia Delivers” Summit ---------- 455

ክፍል አምስት - በአረብኛ የተላለፉ መልእክቶች

Arabic Statements ----------467

መግቢያ

መሪዎች በዘመናቸው የሚገቡት ቃልና የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች ለሀገራቸው ያላቸውን ተስፋና ርዕይ፣ የማከናወን ጥበባቸውንና ለሕዝባቸው ያላቸውን ወገናዊነት ያመላክታሉ። ቃል ኃይል አለው፤ ይህንን የተረዱ አርቆ አሳቢ መሪዎች ቃልና ርዕያቸውን እንደ ዘር ዘርተው፣ በትናንት ስኬት ላይ እየገነቡ፣ ስህተትን እያረሙና አዲስ እሴት እየጨመሩ ወቅቱን ጠብቀው የብልጽግና ፍሬ ያጭዳሉ። መጻሕፍትና የታሪክ ድርሳናትም የመሪዎችን ቃልና ክንውኖች በመሰነድ ርዕይ ከተግባር ጋር ያለውን ቁርኝት ለታሪክ ምስክርነት ያስቀምጣሉ። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በየዓመቱ ተዘጋጅቶ ለአንባቢያንና ለትውልድ የሚታተመው «ከመስከረም እስከ መስከረም» ተከታታይ መጽሐፍ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ንግግሮችና መልዕክቶች ስብስብ ነው። ይህ 9ኛው ቅጽ የቀደሙትን ቅጾች አብነት በመከተል የተዘጋጀ ሲሆን፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመስከረም 2018 ዓ.ም እስከ መስከረም 2019 ዓ.ም በተለያዩ ሀገርኛና የውጭ ቋንቋዎች ያደረጓቸውን ቁልፍ ንግግሮችና ያስተላለፏቸውን አቅጣጫ ጠቋሚ መልዕክቶች አጠቃልሎ ይዟል።

ከታዳሽ ኃይልና የቱሪዝም መዳረሻዎች ማስፋፊያ እስከ አውሮፕላን ማረፊያና ዘመናዊ የሎጂስቲክስ ማዕከላት ግንባታ፣ ከከተማ ኮሪደር ልማት እስከ ተምሳሌት የገጠር መንደሮች፣ ከኢንዱስትሪ መንደሮች እስከ የግብርና ልማት ሽግግር መስኮች፣ ከሰው ሠራሽ አስተውሎት እስከ የመረጃ ሉዓላዊነት የተደረጉ ጉብኝቶች፣ ምርቃቶችና ስራ ማስጀመሪያዎች ሀገሪቱ ከመጀመር ባለፈ ማከናወኗን፣ ከማጠናቀቅም ባለፈ ዘላቂነትን ማረጋገጧን ያመላክታሉ። በሁለትዮሽ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች የተደረጉ ንግግሮችም ብሔራዊ ክብርንና ጥቅምን ያስቀደመ፣ በትብብር ላይ የተመሠረተ አጋርነትን ያንጸባርቃሉ።

ይህ ወቅት ሀገራችን ከ10.2 በመቶ በላይ እድገት ያስመዘገበችበት፣ ከ50 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የተሳተፉበትን ሀገራዊ ምርጫ ያካሄደችበት፣ አለመግባባትን በግጭትና ጦርነት ሳይሆን በምክክር የመፍታት ባህልን ያጸና አካታች ሀገራዊ ምክክርን እውን ያደረገችበት፣ ከሕዳሴ ግድብ ስኬት ማግስት የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታን ያስጀመረችበት፣ አዳዲስ የትብብር በሮች የተከፈቱበትና የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም የሚያረጋግጡ ብሩህ ተስፋዎች በየዘርፉ በጉልህ የታዩበት ነው። ይህ መጽሐፍ አንባቢያን ህልውናን ከክብርና ከነጻነት፣ ቃል መግባትን ከማከናወን ጋር ያጣመረውን የአመራር ጥበብ እንዲመለከቱ ያስችላል፤ ለተተኪው ትውልድም የሀገር ግንባታ ስንቅ ይሆናል።

መልካም ንባብ!

ክፍል አንድ
የአማርኛ ንግግሮች እና መልዕክቶች

የጅግጅጋ ኮሪደር ልማት ጉብኝት

መስከረም 22፣ 2018ዓ.ም

ዛሬ በጅግጅጋ ከተማ ነው የምንገኘው። ጅግጅጋ ከጥቂት ጊዜ በፊት መጥተን የመጎብኘት እድል ነበረን። አሁን ያየነው ጅግጅጋ ከዚህ ቀደም ካየነው ጅግጅጋ በእጅጉ የተለየ ነው። ስልሳ ኪሎ ሜትር ገደማ መንገድ ከተማ ውስጥ ተገንብቷል፤ ወደ አስር ኪሎ ሜትር የሚጠጋ እግረኛ መንገድ ተገንብቷል፤ አስር ኪሎ ሜትር የሚጠጋ የባይስክል መንገድ ተገንብቷል፤ በስፋት ተተክሏል በብዙህ ሺዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ቤቶች ተገንብተዋል፤ መብራት በስፋት ከተማ ውስጥ ተስፋፍቷል።

ዛሬ ፕሬዚዳንቱ እንደነገረኝ ሪፖርት ባለፉት ጥቂት ዓመታት የጅግጅጋ የመብራት አጠቃቀም አራት እጥፍ አድጓል እና በመብራት ፣ በመንገድ ፣ በእግረኛ መንገድ ፣ ባይስክል መንገድ ፣ በቤቶች ግንባታ ፣ ቤቶች ግንባታ በብዙህ ሺዎች ነው የተገነባው እንዳያችሁት በጣም ከተማው ተሻሽሏል አድጓል። የኮሪደር ማልማት ያለው ስራ፣ ስራ በመፍጠር የጭስ አልባውን ኢንደስትሪ በማነቃቃት የሰዎችን የአኗኗር ዘይቤ በማሻሽል እየተጫወተ ያለው ሚና በጣም በጣም ከፍተኛ ነው።እዚህ ጅግጅጋ ላይ ያየነው ለውጥ በአዲስ አበባ ከምናውቀው ለውጥ በምስራቁ የሀገራችን ክፍል ምናልባት በጣም ትልቁ ከተማ እና ትልቁ ስራ ሊሆን ይችላል፤ ይሄ በጣም በጣም ተስፋ ሰጪ ነገር ነው።

የከተማ የማሰዋብ ስራ መገንዘብ የሚያስፈልገው በሚቀጥሉት አስራ አምስት ሃያ ዓመታት ቢበዛ፣ አብዛኛው የማህበረሰብ የመኖሪያ ስፍራ ከተማ ይሆናል። ከተማን ስናዘምን ለልጆቻችም የሚመጥን፣ የሚመች ሀገር እየሰራን ነው ማለት ነው። ከተማን በእቅድ ካልሰራን ደግሞ በአንድ አካባቢ በጥግጊት የሚኖርበት ገሃነም ሊሆን ይችላል። ብዙ ጊዜ እቅድ የሌለው ከተሜነት አሰፋፈር ስርዓታችን ከመጠጥ ውሃ ጋር ፣ ከመብራት ጋር ፣ ከመንገድ ጋር ፣ ከሸንት ቤት ጋር ያለው ችግር ይታወቃል። ከተሞቻችን ካልጠፋ ቦታ በወግ እና በቅጡ በዕቅድ ባለመገንባታቸው ብዙ ቦታ የችግር መንስዔ ሲሆኑ ይታያል። ከተሜነት የሚያስፈልገው ለተሳለጠ አገልግሎት ነው፤ በቅርበት ሁሉን ነገር በምቾት ለማግኘት ነው። የልጆች ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማትና የመንግስት ተቋማት ሌሎች የመንግስት አገልግሎቶች መብራት መንገድ ለማግኘት እንጂ የተጨናነቀ ኑሮ ለመኖር አይደለም።

በዚህም ምክንያት ጅግጅጋ ላይ የተሰራው ስራ ፣ ሃረር ላይ፣ ድሬዳዋ ላይ የተሰራው ስራ በምስራቁ ክፍል የሚያመላክተው ምንድን ነው? ሰዎች ወደ አንድ ከተማ ብቻ ከመጉረፍ

በየአካባቢያቸው የእነሱን ባህል ፣ የእነሱን ታሪክ ፣ የእነሱን መልክ ፣ የእነሱን ጂኦግራፊ አቀማመጥ ፣ የእነሱ መልከዓ ምድራዊ ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ የከተማ አመሰራረት ዘዴ ከተከተልን ፣ ሰዎች በየአካባቢያቸው ስለሚኖሩ አንድ ከተማ ላይ መሰብሰብ ባህሪው ይቀንሳል እና ከተማን ስናዘምን የምንሰራው ነገ የልጆቻችንን መኖሪያ ነው።

ታድያ እንደዚህ ያለውን ድንቅ ስራ ለምንድን ነው አንዳንዶች የማይቀበሉት? በተለይ ራቅ ካሉ አካባቢዎች ያለን እንደሆነ በቃ ለአፍሪካ ለኢትዮጵያ ያ የጨቀየው ያላማረው ነገር በቂ ነው ብለው የሚያስቡ ሀገራት ግለሰቦች ቡድኖች ብዙ ጊዜ በደስታ አያዩትም። አንደኛ እነሱም ላይ ጥያቄ እየመጣባቸው ነው፤ እንኳን እናንተ አፍሪካ እንዲህ እያደረገ ነው እና ለምን አትሰሩም የሚባል ጥያቄ አለ ፤ በሌላ መንገድ ደግሞ ለእኛ በቂ ነው ብለው የማሰብ ችግር አለ። ለእንደዚህ አይነቱ ጆሮ መስጠት አያስፈልግም። ለእኛ የሚበጀንን የሚያስፈልገንን የሚጠቅመንን እኛ ነን የምናውቀው። የሚበጀንን የሚያስፈልገንን ከእኛ በላይ ለዜጎቻችን የሚያስብ፣ ከእኛ በላይ ለሀገራችን የሚቆጭ ከእኛ በላይ የእኛን ልማት የሚጠብቅ ሀይል አለ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ያማ ቢኖር ለረጅም ዓመታት እንዲህ ሆነን ባልቀረን ነበረ።

ይሄ ጭስ አልባው የሚባለው የቱሪዝም ዘርፍ ደግሞ አሁን እንኳን በሀገር ደረጃ ውጤቱ እየታየ ነው ያለው። እንግዲህ ሰምታችሁ ከሆነ ጅግጅጋ ላይ ሰላሳ ገደማ ሆቴሎች እየተገነቡ ናቸው፤ ይሄ ገበታ ለሀገር ስራችን ምናልባት በሶስት ወር፣ አራት ወር ሊመረቅ ይችላል። የገበታ ፕሮጀክት መቼም በየከተማው እያመጣ ያለው ተጨማሪ እሴት በጣም የሚገርም ነው። አሁን በሱማሌ ክልል ውስጥ በእንደዚህ ያለ ጽዳት፣ በእንደዚህ ያለ የመሬት አቀማመጥ ስራ፣ በእንደዚህ ያለ ስፋት እንኳን ሆቴል ቀርቶ ሰፈርም አይገኝም። እያመጣ ያለው እሴት ሲቪሊቲ ነው። የአኗኗር ዘዬ፣ የአገነባብ ዘዬ፣ አንድ ሰው ምን አይነት የኑሮ ደረጃ ቢኖር ምቹ እና ተገቢም እንደሆነም ጭምር ትምህርት እያመጣ ነው ያለው። ይህ ቦታ ሲጠናቀቅ በዚህ ከባቢ ያሉ የጎረቤት ሀገራት ካለምንም ጥርጥር እዚህ መጥተው መገልገላቸው አይቀርም እና ገበታ እዚህም፣ አርባ ምንጭም፣ ጅማም፣ ጎርጎራም በየቦታው የሚታየው ትላልቅ እሴት ነው በአካባቢ ላይ እያመጣ ያለው።

ይሄን በሱማሌ ተደግሞ በማየቴ በጣም ደስ ብሎኛል። የሱማሌ ክልል በዚህ ስፋት፣ በዚህ ልክ ትላልቅ ስብሰባ ሊካሄድበት የሚችል ብዙ ነገር በውስጡ የያዘ ቦታ ማየት ቀላል ነገር አይደለም። ይሄ ነገር በተቀመጠለት እቅድ መሰረት ተጠናቆ ለምርቃት እንደሚበቃ ምንም ጥርጥር የለውም። ሰማንያ፣ ሰማንያ አምስት በሙቶ የሚሆን ስራው አልቋል። አሁን የማሰማመር ስራ ነው የቀራቸው፤ ከጥቂት ወራት በኋላ ተመልሰን

እንደምናስመርቅ ተስፋ አደርጋለሁ። በድምሩ በሱማሌ ክልል ዛሬ ያየናቸው የመሶብ ፕሮጀክት ጅማሯቸው፣ የኮሪደር ስራቸው፣ የገበታ ስራ ከዚያም ውጭ ያሉ በርካታ የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ የሆስፒታል ስራዎች በድምሩ ሱማሌ አካባቢ የመነቃቃት ምልክት ያሳያል። ዛሬ ባየሁት ሁኔታ ምናልባት ከባህርዳር፣ ከአዳማ፣ ከሃዋሳ ውጭ ጅግጅጋን የሚተካከል ከተማ ብዙ በሀገር ደረጃ ያለ አልመሰለኝም፤ በተለይ በቤት ግንባታ ብዙ ክልሎች መማር ያለባቸው ጅግጅጋ ላይ የሚሰሩ ቤቶች ጽድት ያሉ ናቸው እና ከአራት/አምስት ከተሞች መካከል አንዷ ሆነች ማለት ነው፣ ወይም ከአስር ትላልቆቹ አንዷ ሆነች ማለት ነው፤ ይሄ ቀላል ነገር አይደለም።

የዛሬ ሁለት/ሶስት ዓመት ይሄን ማየት አይቻልም እና በጣም አስደማሚ ስራ ነው የተሰራው። ለዚህ የሱማሌ ክልል ህዝብ አመራሮች በዚህ ስራ የተሳተፉ ሰዎች በሙሉ ምስጋና ይገባቸዋል። የመጨረሻው መልዕክቴ በተለይ ለፕሬዚዳንቱ፣ ለካቢኔያቸው አሁን በሰራነው እና በተገኘው ውጤት አይደለም እርካታ ሊሰማን የሚገባው፤ ባለፉት ዓመታት ለምንድን ነው ይሄንን ሳንሰራ የቆየነው ብለው መጠየቅ አለባቸው። ሰሞኑን ጓደኞቼ ጋር ስናወራ የአራት ኪሎውን ቤተ መንግስት እና ዙሪያውን ብቻ ከሁለት ዓመት በፊት ሶስት ዓመት በፊት የነበረውን ሁኔታ አንስተን እንወያይ ነበር። አራት ኪሎ ከአደባባዩ ወደ ሸራተን መውረጃው ፍሬንድሺፕ ክፍል ሁለት፣ ፍሬንድሺፕ አንድ፣ ሳይንስ ሙዚየም የተሰራበት ያው የሚታወቅ ነው ምን አይነት ሰፈር እንደነበረ። የቤተ መንግስት ጋራዥ ብዙ ቆርቆሮዎች የጥበቃ ቤቶች የነበሩበት ነው።

ከግቢ ገብርኤል ጀምሮ ደግሞ ጓሮ ጓሮውን ሲኬድ በጣም የሚያስፈራ የሚባል ሰፈር ነው። ለኑሮ ፍጹም ያልተመቸ ከፍተኛ ለድህነት መገለጫ የሆነ ሰፈር ነው። አዋሬ በተደጋጋሚ ስናፈርስ ታውቃላችሁ የሚመስለውን ነገር፤ አዋሬ ደግሞ በጣም የሚያሳዝን ሰፈር ነው። በጥቅሉ አራት ኪሎ የሚባለው ቤተ መንግስት 360 ዲግሪ የተከበበው ከፓርላማ ውጭ የአብርሆት ላይብረሪን ጨምሮ ከፓርላማ ከተሰራበት ውጭ በጣም የመጨረሻ ድህነት፣ የመጨረሻ ችግር፣ የመጨረሻ የቆሻሻ ምልክት ሰፈር የነበረ ነው። እንዴት ነው ሶስት መቶ ስልሳ ዲግሪ በቆሻሻ እና በድህነት ተከበን እዚያ ግቢ ውስጥ ተቀምጠን ሀገር እየሰራን ነው ብለን የምናስበው የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ለረጅም ጊዜ እዚያ ቤት ውስጥ ስንቀመጥ በቅርብ ርቀት ያሉ የእኛን ጎረቤቶች ህይወት መቀየር ሳንችል እዚያ የተቀመጥንበትን ጊዜ በመቁጠር ብቻ ሀገር እየመራን ነው ብለን ማሰብ አስቸጋሪ ነው።

አሁን በኢትዮጵያ ደረጃ ምንም ችግር የሚባል ጠፍቷል ሁሉ ተገንብቷል የሚል መመጻደቅ ተገቢ አይደለም፤ ገና ብዙ ስራ ይጠበቅብናል። ቢያንስ ግን በምንኖርበት ሰፈር ውስጥ

ያሉትን ከባቢዎች በሙሉ ከነበሩበት ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ አሻሽለናል። ጅግጅጋም ሲመጣ ይሄው ነው፣ ጎንደርም ሲኬድ ይሄው ነው፣ ሀረርም ሲኬድ ይሄው ነው፣ አሶሳም በልኩ ይሄው ነው ፣ አርባ ምንጭም ይሄው ነው። ነገር ግን በየቦታ ያለን አመራሮች መጠየቅ ያለብን ነገር፤ አሁን የተገኘው ድል ለምን ትናንት መሆን አልቻለም መቆጨት ነው ያለብን። ይበልጥ ለመትጋት ይበልጥ ለመስራት ይበልጥ ለመልፋት እንጂ የእርካታ ምንጭ መሆን የለበትም። በእርግጥ በማንኛውም ሰው ዓይን እና መለኪያ ዛሬ ያየነው ነገር ሳቢ ነው ፤ በጣም ደስ ይላል ። ለውጡ በተለይ አምና ካቻምና ለመጣ ሰው በጣም ደስ ይላል። ግን ያ ደስታ የእርካታ ምንጭ ሆኖ ነገ ልንሰራ የሚገባንን ስራ የሚከለክል ከሆነ ጥፋት ነው። እና እኔ ያለኝ መልዕክት ጅማሯችን ጥሩ ነው፤ በትጋት በልፋት በእኛ ሀብት፣ በእኛ ድካም የዜጎቻችን ህይወት የአኗኗር ዘዬ ለመቀየር እያደረግነው ያለው ጥረት በጣም ተስፋ ሰጪ ነው። ነገር ግን ከሚጠበቅብን ደግሞ በጣም ሩቅ ስለሆንን ሳንረካ ልፋት ጨምረን ልፋት ጨምረን ስራ ጨምረን ሀገራችንን እንስራ ነው። አሁን በከተማ ስራዎቻችን ምንም ጥርጥር የለውም በአፍሪካ ምልክት እና ምሳሌ ተደርገን ተወስደናል። በቅርቡ በስንዴ ዓለም አቀፍ ሽልማት እንዳገኘን ይታወሳል አሁን ደግሞ ሰሞኑን በደረሰኝ ዜና በአረንጓዴ ዐሻራ እንደዚሁ ዓለም አቀፍ የተባበሩት መንግስታት ተቋም ኢትዮጵያ ሽልማት አግኝታለች። በኮሪደሩም እንደዚሁ ብዙዎች ለመማር ጥያቄ ያቀርባሉ መጥተው ይጎበኛሉ፤ ለብዙ የአፍሪካ ሀገራት ምሳሌ የሚሆን ስራ ተጀምሯል፤ ተጀምሯል ነው ከተሞቻችን መድረስ የሚገባቸው ቦታ አልደረሱም።

ይሄንን ስራችንን አይተው ሊያጣጥሉ የሚሞክሩ ሀገራት እና አንዳንድ ቡድኖች ደግሞ የእናንተን ስራ ስሩ ይሄን ለእኛ ተዉልን፤ ይሄ ሀገር ባለቤት አለው፣ ህዝብ አለው፣ እራሱን የሚወድ፣ እራሱን የሚያከብር፣ መለወጥ የሚፈልግ ህዝብ እና መንግስት አለው፤ ለእኛ ተዉልን ስራችንን ነው መልዕክቴ። እና ተባብረን በርትተን እንስራ የጀመርነው መንገድ በጣም ተስፋ ሰጪ እና ውጤታማ ነው አስደሳች ስራ ነው! ሳንታሰር፣ ሳንቆም፣ በርትተን ብንለፋ የበለጠ ያማረ የተዋበ በብዙዎች ዓይን የሚደነቅ እና የሚመሰገን ሀገር ለመስራት እድል አለን ብዬ አስባለሁ በጣም ጥሩ ስራ ነው።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ጅግጅጋ


Calub Natural
Gas Inauguration

የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካ፣ የጎዴ ነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ ፕሮጀክቶች እና የኦጋዴን የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት ማስጀመርያ

መስከረም 22፣ 2018ዓ.ም

ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣
ክቡር የፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ፣
የክልላችን ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ሙስጠፊ ሁመር፣
ክቡር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ፣
ውድ ወንድሜ አልሃጅ አሊኮ ዳንጎቴ፣
እንዲሁም የቻይና ወንድማችን እና ለዚህ ኢንቨስትመንት ከሩቅ ምስራቅ የመጣው ወንድማችን ጁ ጎንሸን የሲጂል ፕሬዚዳንት እና ዋና ሰብሳቢ፣
የተከበራችሁ ሚንስትሮች የሀገር ሽማግሌዎች እዚህ ስፍራ የተገኛችሁ ኢትዮጵያዊያን፣
በየቤታቹ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ ትላልቅ ነገር ለመጀመር፣ የጀመርነውን ለመጨረስ፣ የኢትዮጵያን ልክ ለማስተካከል ወደ ሚገባን የብልፅግና ማማ ለመውጣት በምናደርገው ጥረት ሁሉ መከናወን የሰጠን፣ የተናገርነው እንድንተገብር የረዳን ፈጣሪያችን እጅጉኑ የተመሰገነ ይሁን ።

ዛሬ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሌላ ትልቅ አነቃቂ፣ አመርቂ፣ ለኢትዮጵያ ብልፅግና መሰረት የሚጥል ስራዎች የምናስጀምርበት ዕለት ነው። ይህንን ስራ የስኬቶቻችን ማብሰሪያ፤ የማንሰራራት መሻታችን ማብሰሪያ አድርገን እንወስደዋለን ምክንያቱም እያንዳንዱ ስኬት ተሰናስሎ የኢትዮጵያን ማንሰራራት እውን ማድረግ እንዲችል ስለሆነ ዋና ትልሙ፤ ይህ ቀን ለኢትዮጵያዊያን ታላቅ ቀን ስለሆነ ለመላው ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሁም የኢትዮጵያ የልማት እውነተኛ አጋሮች እንደ አሊኮ ዳንጎቴ እና እንደ ጁ ያሉትን ጨምሮ እንኳን ደስ ያላቹ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እወዳለው!

ሁለት ሺህ አስራ ሰባት እና ሁለት ሺህ አስራ ስምንት ልክ እንደ መቶ ዓመት የሰፋ የአንድ ወር ጊዜ ለኢትዮጵያዊያን አምጥቷል። በሁለት ሺህ አስራ ስምንት ዋዜማ ህዳሴ የሚባል የንጋት ብስራት የተበሰረበት እጅግ ከፍተኛ የሆነ ለአፍሪካ በሙሉ የሚያነቃቃ እና የሚያበረታታ የኃይል ፕሮጀክት አስመርቀን አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አሁን እዚህ ቦታ ያስጀመርናቸውን እና ወደ አስር ቢሊየን ዶላር የሚጠጋ ኢንቨስትመንት በሶማሊ ክልል ለማስጀመር እና ለማስመረቅ ስለተገናኘን እንኳን ደስ አለቹ ለማለት እወዳለው!

ዛሬ ለሶማሌ የብልፅግና ፀሀይ ወጣላት፤ ይህ በሶማሌ የታየ ብርሃን በመላ ኢትዮጵያ እስኪረጋገጥ እያንዳንዱ ዜጎቻችንን ካሉበት የድህነት አረንቋ አውጥቶ ወደሚገባቸው የብልፅግና እና የልማት ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ እኔ እና እናንተ የሚጠበቅብን መትጋት፣ መትጋት፣ መትጋት፣ መስራት እና መጨረስ ብቻ ነው። እኛ እንጀምራለን ፤ እኛ ተግተን እንሰራለን ፤ እኛ እንጨርሳለን። ተግተን ጀምረን እንድንጨርስ ግን ተግተው የሚተቹ፣ ተግተው የሚዋሹ ደግሞ ያስፈልጋሉ። እነሱ ይዋሻሉ እኛ እንሰራለን፤ እነሱ ያወራሉ እኛ እናከናውናለን በስራዎቻችን ሁሉ ኢትዮጵያን ከፍ እናደርጋለን።

በስራዎቻችን ሁሉ ብልፅግናን እናረጋግጣለን ይህ እስኪሆን ድረስው የማንተኛ መሆኑን በድጋሚ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መግለጥ እወዳለው። በቅርቡ በጉባ ህዳሴን ስናስመርቅ 'ህዳሴ ተመርቋል ሌሎች ከፍ ከፍ ያሉ ፕሮጀክቶች ሜጋ ሜጋ ፕሮጀክቶች እስከ ሰላሳ ቢሊየን ዶላር የሚጠጉ ኢትዮጵያ ውስጥ ይጀመራሉ' ብዬ ስናገር እንዲሁ ለመናገር ብቻ ያልኩ የመሰላቸው አሉ። የሰላሳውም ቢሊየን ዶላር ኢንቨስትመንት ልክ ዛሬ እንዳያችሁት ሙሉ በሙሉ ተጠንቶ ዝግጅት ተደርጎበት የሀብት ምንጭ ተለይቶ ካለምንም ጥርጥር በሚቀጥሉት አምስት እና ስድስት ዓመታት የሚፈፀሙ ፕሮጀክቶች ይሆናሉ።

ከነዚህ ውስጥ አንደኛው የሶስት ነጥብ አምስት ሚሊየን ቶን ማጣሪያ ዛሬ እዚህ ያስጀመርነው እንዲሁም እጅግ ግዙፍ የሆነ የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ ከዛ በተጨማሪ ደግሞ ከካሉፕ ወደዚህ ከመቶ ኪሎሜትር በላይ ጋዝ ትራንስፖርት የምናደርግበት መስመር ሶስት ፕሮጀክቶች እዚህ ጎዴ ላይ ያሉ ሲሆን ካሉብ ላይ ደግሞ የመጀመሪያው ሂደት የጋዝ ፋብሪካ ዛሬ ስራ ይጀምራል። ሁለተኛው የጋዝ ፋብሪካ አስራ ሁለት እጥፍ ከአንደኛው የጋዝ ፋብሪካ የሚበልጥ ዛሬ ይጀመራል። የአንድ ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል፣ አንድ ሺህ ሜጋ ዋት ሲባል ከህዳሴ ከሚያመነጨው ከግማሽ በላይ ዛሬ በካሉብ የኃይል ማስጀመሪያ ፕሮግራም ይኖረናል። እነዚህ ሲደመሩ እንዲሁ አስር ቢሊየን ዶላር ይጠጋል። በቅርቡ የተፈራረምነው የኒውክሌር ፕላንት ከአምስት እስከ ሰባት ቢሊየን ዶላር ይፈጃል።

በቅርቡ እንዲሁ ፕሮግራም የምናስጀምረው የወርቅ ማጣሪያ እና የብር ማተሚያ ፕሮጀክቶቻችን በአዲስ አበባ ላይ ስራ የጀመሩ ሲሆን እነሱም እንደአስፈላጊነቱ የሚገለጥ ይሆናል። የኤርፖርት ስራችን ወደ አስር ቢሊየን ዶላር የሚጠጋ ፕሮጀክት ይሆናል፣ የሀውስ ሲጨመር ሰላሳው ተጠናቀቀ ማለት ነው። ዛሬ የምናስጀምረው የማጣሪያ ፕሮጀክት ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም፤ በአስራ ዘጠኝ ሀምሳ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር በአሰብ ወደብ አካባቢ አምስት መቶ ሺህ ሜትሪክ ቶን ማጥራት

የሚችል ማጣሪያ ኢትዮጵያ ገንብታ ነበር። ከአራት ዓመት በኋላ አስራ ዘጠኝ ስልሳ ሶስት ዓመተ ምህረት ወደ ስምንት መቶ ሺህ ሜትሪክ ቶን አሳድጋ ነበር። አለመታደል ሆኖ ወደብ ስናጣ ቢያንስ ማጣሪያው የኢትዮጵያ ሀብት ኢንቨስትመንት ስለሆነ ወይ ወደ አዋሽ ወይ ወደ ድሬዳዋ መምጣት ሲገባው ሪማጣሪያው እዛው ቀልጦ ቀረ። ይህ ጉዳይ ሀገር ወዳድ ለሆኑ ኢትዮጵያዊያን የሚያስቆጭ የሚያንገበግብ ጉዳይ ነው።

ወደብ ላይ ኢንቨስት አድርገን፣ ኤርፖርት ላይ ኢንቨስት አድርገን፣ መንገዶች ላይ ኢንቨስት አድርገን እነዛን እንኳን ማጣት ሳያንሰን በብዙ ሀብት የተገነባ ማጣሪያ ደግሞ ለኢትዮጵያ ብቻ የሚያገለግል ማጣሪያ በቆመበት እንዲበላሽ እና እንዲጠፋ መደረጉ እጅግ የሚያስቆጭ ተግባር ስለሆነ ያ ቁጭታችንን በምሬት፣ በለቅሶ፣ በሀዘን ሳይሆን እንዲህ በተግባር በመስራት መወጣት ሰላለብን እዚህ ቦታ ዛሬ ያስጀመርነው ማጣሪያ ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊየን ሜትሪክ ቶን ማለት እዛ አሰብ ካጣነው ቢያንስ አራት እጥፍ ማለት ነው። መበቀል በተግባር ማለት እንደዚህ ነው። ስምንት መቶ ሺህ ሲጠፋ ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊየን አድርጎ መስራት ማለት ነው።

እዚህ ሶማሌ ክልል ሽማግሌዎች አንድ ታዋቂ አባባል አላቸው ስለ ሞኝ ሰው ሲናገሩ ከዛፍ ላይ ያለውን ፍሬ ለመቅጠፍ በእጁ የያዘውን ጣፋጭ ፍሬ እንደሚጥል ሞኝ ልጅ ነው የሆነው። ገና ለገና ኢትዮጵያን ለማስተዳደር፤ ኢትዮጲያን ለማልማት ያላትን ፍሬ እየበተንን ሳይሆን እየሰበሰብን መሆን አለበት። ያ ደግሞ የሚሆነው ከትላንትና ጋር በጥቅሉ ሳንጣላ ስንቀር ነው።

ትላንትና ውስጥ መልካም ስራ ሲኖር ፈልቅቀን የምንጠቀም የምናሳድግ፤ ትላንትና ውስጥ ስንክሳር ስህተት ሲኖር የምናርም ከሆነ ማጣሪያ የሚያክል ነገር እንደዋዛ ጥለን አንመጣም። ይህንን አይነት ጥፋት ዳግም ላለመፈፀም ኢትዮጵያዊያን ካለንበት መነታረክ ካለንበት መባላት ወጥተን እንደዚህ ባለው ትላልቅ ስራ የኢትዮጵያን ስም ማስጠራት የኢትዮጵያን ከፍታ ለልጆቻችን የተሻለች ሀገር መስራት ለሁላችን የሰርክ ስራ መሆን ይኖርበታል።

ኢትዮጵያዊያን መንቃት አለብን ድፍን ዓለም ለኢንቨስትመንት የምትመች፣ አመርቂ እድገት ያላት፣ ተስፋ ያለት ሀገር እያሉ በከፍተኛ ጉጉት ከእኛ ጋር ሊሰሩ በሚሹበት፣ በሚጠይቁበት በዚህ ጊዜ መላ ኢትዮጵያዊያን ዐይናችንን ገልጠን በማየት በትብብር፣ በትግግዝ፣ ሰላምን በማምጣት በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያን ብልፅግና ማረጋገጥ ስለምንችል በዚሁ መንፈስ በትብብር አብረን እንድንሰራ። በተደጋጋሚ እንዳሳሰብኩት

ዛሬም ከአደራ ጭምር ላሳስባቹ የምወደው ነገር የኢትዮጵያ ብልፅግና የማይቆም ስለሆነ፣ የጀመርነውን መጨረስ የማይቆም ስለሆነ የግመሉ ጉዞ በውሾች ጩኸት የማይደናቀፍ ስለሆነ ጊዜያቹሁን ጉልበታቹሁን ከምታባክኑ ከግመሉ ጋር ተባብራቹሁ ሩጫችሁን እንድታፋጥኑ በዚሁ ታላቅ ቀን በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም ላሳስባቹ እወዳለው።
ህልማችን ሩቅ ነው፤ ተስፋችን የሚጨበጥ ነው!

የምግብ ሉዓላዊነት በኢትዮጵያ ውስጥ እናረጋግጣለን፤ የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ማዳበሪያ በእጅጉ አስፈላጊ ቢሆንም ቅድም በነዴ አካባቢ ስንንቀሳቀስ እንዳያችሁት ትላልቅ ወንዞች ከረምት ከበጋ የሚፈሱበት እንደዚህ ያለው አስደማሚ ሜዳ ትንሽዬ ማሽን እና ማዳበሪያ ቢያገኝ እንኳን ኢትዮጵያን ቀጠናውን ሊመግብ ስለሚችል የሶማሌ ክልል አመራሮች ቀን መጥቶላችኋል፣ ጊዜ መጥቶላችኋል፤ እድል አግኝታችኋል ይህ እድል ሳይባክን በአንድ ልብ፣ በአንድ መንፈስ ተባብረን የሶማሌን ክልል ለሶማሌ ብቻ ሳይሆን ለምስራቅ አፍሪካ የሚተርፍ ልማት ያለበት ክልል እድናደርግ አደራ ልላቹ እፈልጋለው።

ክቡር አቶ ሙስጠፌ እና ካቢኔያቸው እንኳን ደስ ያላችሁ! ታላቅ ታሪክ ነው በሶማሌ ክልል፤ ላለፉት መቶ ዓመታት ተደምሮ አስር ቢሊየን ዶላር ኢንቨስት አልተደረገም ኢትዮጵያዊያን ናቸው ልማት ይገባቸዋል ሁለተኛ ዜጋ አይደሉም፤ አጋር አይደሉም፤ የሀገር ምሰሶ ናቸው ብሎ ብልፅግና ስለሚያምን እንደዚህ ያለውን ኢንቨስትመንት ስላመጣ ጠብቃቹ ከፍሬ እንድታደርሱት፣ ሰላማችሁን እንድትጠብቁ፣ እነዚህን ኢንቨስተሮች እንድትንከባከቡ እኛን አምነው ስለመጡ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል በሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ሁሉ ከጎናቸው እንድትቆሙ አደራ እያልኩ፤ ክቡር አቶ ሙስጠፌ ከዛሬ ጀምሮ የሶማሌ ክልል ፕሬዚደንት ብቻ ሳይሆኑ የእነዚህ ስድስት ፕሮጀክቶች የቅርብ ጠባቂ ስለሆኑ እያንዳንዷ ሀብት ሳትፈስ ለቁም ነገር እንድትሆን፣ እኛን አምነው የመጡ ባለሀብቶች ደግሞ ትርፋማ እንዲሆኑ፣ ደስተኛ እንዲሆኑ ከእኛ ጋር ይበልጥ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የእርሶን ኃላፊነት እንዲወጡ በአክብሮት ላሳስቦ እወዳለው።

መላው ኢትዮጵያዊያን እንኳን ደስ አላቹ!

ታላቅ ቀን ነው፤ የታላላቅ ስራዎች ጅማሮ ነው! ይህ ጉዳይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ወንድሜ አል ሀጅ አሊኮ ዳንጎቴ ስላመንከን ሀብትህን ፣ እውቀትህን ፣ ገንዘብህን እኛ ጋር ለማፍሰስ ስለፈቀድክ በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም ያለኝን ክብር እና ፍቅር ወዳጅ፣ ኢትዮጵያን የሚያምን ሆኖ በቻይና መንግስት ድጋፍ እንደዚህ ያለውን ትላልቅ ኢንቨስትመንት ከእኛ ጋር ሊሰራ ስለመጣ እጅግ ደስተኛ መሆናችን ያለንን ፍቅር እና

ስገልፅልህ በታላቅ ደስታ ነው። እንዲሁም ወንድማችን ጁ ከሩቅ ምስራቅ ኢትዮጵያን ወዳጅ፣ ኢትዮጵያን የሚያምን ሆኖ በቻይና መንግስት ድጋፍ እንደዚህ ያለውን ትላልቅ ኢንቨስትመንት ከእኛ ጋር ሊሰራ ስለመጣ እጅግ ደስተኛ መሆናችን ያለንን ፍቅር እና አክብሮት ልገልፅላችሁ እወዳለው።ለሁለቱም ባለሀበቶች ላረጋግጥላቸው የምፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ በመንግስት ደረጃ ሙስና ቦታ የለውም፤ አንድም ብር ባልተገባ መንገድ ላልተገባ ሰው አታውሉም። ሀብታችሁ ሙሉ በሙሉ የሚውለው ለታለመለት አላማ ብቻ ሲሆን የእኔ እና የጓደኞቼ ስራ እናንተን እና ህዝባችንን በንፅህና ማገልገል ስለሆነ ከሙስና ነጻ ብቻ ሳይሆን በጣም ፈጣን አገልግሎት እየሰጠን የምናስደስታችሁ መሆኑን በድጋሚ ቃል ልገባላቹ እፈልጋለው።

ይህ ፕሮጀክት እንዲሳካ በጣም በርካታ ወገኖች ከፍተኛ ትብብር እና ስራ አድርገዋል። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ለማመስገን እወዳለው በቀድሞ የትራንስፖርት ሚንስቴር ዳግማዊት ሞገስ ይህ ጉዳይ ተጀምሮ እስኪያልቅ ልክ እንደ ድሮ በታማኝነት ሀገሯን ለማገልገል የሚያስደንቅ ብቃት እና ቁርጠኝነት ስላሳየች በእናንተ ፊት እንዳመሰግናት ይፈቀድልኝ። ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ ፣ ሚንስቴር ዴኤታዎች ፣ የማዕድን ሚንስቴር አባላት እስካሁን ያሳያችሁት ትጋት የሚያስደንቅ ነው ሰራው እስከሚጠናቀቅ በዚሁ መንፈስ እንድትቀጥሉ አደራ ልላቹ እወዳለው። የሶማሌ ክልል ፕሬዝደንት የካቢኔ አባላት እና ማህበረሰቡ ይህንን ልማት በከፍተኛ ደስታ ተቀብሎ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ በመቻላቸው ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል። እነሱንም ማመስገን እፈልጋለው። መላው ኢትዮጵዊያን የአፋር ወንድሞቻችን፣ የኦሮሚያ ወንድሞቻችን ፣ የትግራይ ወንድሞቻችን ፣ የአማራ ፣ የቤኒሻንጉል ፣ የጋምቤላ ፣ የሀረሪ ወንድሞቻችን ፣ በደቡብ ፣ በሲዳማ ያሉ ወንድሞቻችን ሁሉም ለሶማሌ ለወጣው ፀሀይ እንኳን ደስ ያላቹ ማለት እፈልጋለው።የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ውስጥ በሁሉም ፕሮጀክቶች ትላልቅ ሼር ባለቤት ስለሆነ ለኢንቨስተር እየሰጠን ሳይሆን ከኢንቨስተሮች ጋር በጋራ፤ ማዳበሪያውም ግማሽ የሚተካከል ሀብት የእኛ ነው፣ በማጣሪያው፣ በክሪፕቶው በሁሉም ኢትዮጵያ የሚገባትን ያህል ድርሻ ይዛ አብራ ስለምትሰራ መላ ኢትዮጵያዊያን እንኳን ደስ ያላቹ ዛሬ ጀምረናል ጨርሰን ደግሞ እናሳያቹዋለን።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ሶማሌ ክልል



ፐልስ ኦፍ አፍሪካ ሚዲያ ስራ ማስጀመሪያ

መስከረም 27፣ 2018ዓ.ም

የተከበራችሁ የኢዜአ ቦርድ አባላት፣ የኢዜአ ማኔጅመንት አባላት፣ እዚህ በዚህ ታሪካዊ ቀን የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ለዚህ ቀን አበቃችሁ!

የሰው ልጅ ስሪት በተለይም ጭንቅላት እንደ ነጭ ወረቀት ነው የነገሩትን የሚያደምጥ፣ ያደመጠውን ደግሞ አስላልቶ የሚያንጸባርቅ ነው። በትርክት፣ በንግግር ሰው ይሰራል፤ ማህበረሰብ ይሰራ፣ ሀገር ይሰራል፣ አጎጉር ይሰራል፤ በዚሁ ንግግር ግለሰብ ይፈርሳል፣ ማህበረሰብ ይፈርሳል፣ ሀገር ይፈርሳል የኢትዮጵያ ምስቅልቅል ውጤት የገነባነው ትርክት ውጤት ነው። እንዳንተማመን፣ እንዳንግባባ፣ እንዳንከባበር፣ እንዳንተጋገዝ፣ በጋራ እንዳንቆም ያደረገን ትርክት ነው። አፍሪካም እንዲሁ ትልቅ ሳለች ትንሽ መስላ እንድትታይ፣ በቅርጽ አንሳ፣ አቅሟ አንሶ፣ የመፍጠር አቅሟ አንሶ እንዲታይ የተሰራበት ዋነኛ ምክንያት በትርክት ጭንቅላትን ለመመገብ የአፍሪካ ሀገራት የነበራቸው ዝግጁነት ውስን ስለሆነ ባለፉት ሰባት ዓመታት ሰፋፊ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ተሰርተዋል።

ኢቢሲ ኢቲቪን ብትወስዱ በአፍሪካ ትልቅ የሚባል መሰረተ ልማት ገንብቷል። ፋናን ብትወስዱ እንዲሁ ሰፋፊ ስራ ተሰርቷል። አቢኤን፣ የአማራ ሚዲያ በመሰረተ ልማት ደረጃ በጣም ሰፋፊ ግንባታዎች አድርገዋል። ኢዜአ ሰማንያ ዓመቱን ካከበረ ጥቂት ጊዜ ሆኖታል፣ ሰማንያ ዓመት ሙሉ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ወደ አፍሪካ ማደግ አለመቻሉ አግባብ አልነበረም አግባብ አለመሆኑን መክሰስ ሳይሆን ግን ሰርተን መቀየር ያስፈልግ ነበር።

አሁን ፐልስ ኦፍ አፍሪካ በዚህ ሁኔታ መቋቋሙን አቅላችሁ እንዳታዩ በጣም የቀለለ ጅማሮ ቢመስልም በጥቂት ዓመታት ውስጥ በአፍሪካ ቀደምት ታዋቂ ከሆኑ ሚዲያዎች አንዱ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ለዚያ ምክንያቱ ደግሞ የትርክት ግንባታ በሀገራት ሲጀመር ከሀገር ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ ጉዳይ ነው። የቻይናው ሚዲያ፣ አሁን በቅርቡ የህንዶች ሚዲያ፣ በአውሮፓ ምናውቃቸው የአውሮፓ ሚዲያዎች፣ የአሜሪካ ሚዲያዎች፣ የአረብ ሚዲያዎች እያደጉ የመጡት ከሀገራት እድገት እና ከአቅም ጋር በቀጥታ ይያያዛል። ሁላችሁም እንደምታውቁት ተስፋ አደርጋለሁ እንደምታምኑት ኢትዮጵያ እያንሰራራች ነው፤ ተነስታለች። የዚህ አምስት/ ስድስት ቢበዛ አስር ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ ድሮ ከምናውቀው ታሪክ ጋር በፍጹም አይመሳሰልም። የዛሬ አስር ዓመት ያለችው ኢትዮጵያ በአፍሪካ በብዙ ነገር ግንባር ቀደምት ነች፣ ያኔ ትርክት መገንባት የመሻት ጉዳይ ሳይሆን ሀላፊነት ሆኖ ይመጣል። ያደገችው ቻይና ከእራሷ አልፋ የዓለምን

ትርክት ለመገንባት እንደሰራችው፤ እያደገች ያለችው ህንድ ከእራሷ አልፋ የዓለምን ትርክት ለመገንባት እየሰራች እንዳለችው፤ ሀብት ያላት ኳታር አልጀዚራን እንደገነባችው ሁሉ እኛም ኢኮኖሚያችን እያደገ ሲሄድ በአፍሪካትርክትውስጥ ጉልህ ስፍራ መጫወት ሀላፊነታችን መሆኑ አይቀሬ ጉዳይ ነው።

ለምን የተባለ እንደሆነ ወደኋላ መለስ ስንል በታሪካችን የአፍሪካ ከፍተኛው አደጋ የነበረው ከውጭ እየመጡ ያሉ በዝባዥ ሀይሎች አፍሪካን እንዳይበዘብዙ መከላከል ነበር። በዚህ ጊዜ ግንባር ቀደም ሆና ከዓደዋ ታላቁን ብስራት ያሰማችው በልጆቿ ደም በልጆቿ አጥንት በከፍተኛ ተጋድሎ ለብዙ የአፍሪካ ሀገራት ነጻነት ደውል ብስራት የተሰማው ከዓደዋ ነበር። ያኔ ለመከላከል፣ ያኔ እንዳንበዘበዝ የነበረው ተጋድሎ ላለፉት በርካታ ዓመታት በቆየንበት መንገድ መቆየት አልነበረበትም። ከተከላከልን በኋላ መልማት ነበረብን፣ ከተከላከልን በኋላ መበልጸግ ነበረብን፣ በዚያ ውስጥ አፍሪካዊ ወንድሞቻችን ካለ ምንም ጥርጥር ከኢትዮጵያ ያንን ተግባር ይጠብቃሉ። እና ዛሬ ጊዜው ደርሶ ከእራሳችን ተሻግረን የአፍሪካ ድምጽ ለመሆን እና አፍሪካ ምድረ ቀደምት መሆኗን፤ አፍሪካ በከርሰ ምድር ሀብት ከፍተኛ ሀብት ያላት አኅጉር መሆኗን፤ በብዙ ወጣቶች የተሞላች አኅጉር መሆኗን፤ ለመፍጠር የሚያበቃ ጭንቅላት ያላቸው ወጣቶች ያሉበት አኅጉር መሆኗን፤ አሁን ባለው የኢንዱስትሪ አብዮት ለመማር ከውጭ እውቀት ለመገብየት እንደ ከዚህ ቀደሙ አስቸጋሪ ባለመሆኑ ከእስያ ቀጥሎ ምንም ጥርጥር የለውም በመጪው ዘመናት አፍሪካ ታላቋ አኅጉር ትሆናለች።

ይህ በሚሆንበት ሰዓት አርፍደን በብዙ ጉዳይ እንደጀመርነው በዚህም ጉዳይ አርፍደን እንዳንጀምር ከእኛ ተሻግረን የአፍሪካን ትልቅነት፣ ሀብታምነት፣ የማድረግ አቅም ነገር ግን ስንሰበሰብ አፍሪካዊያን ሲደመሩ፤ እየተከፋፈልን በተገዛንበት መቶ ዓመታት ምንም አላመጣንም፤ ሰብሰብ ብለን ብንሰራ ደግሞ ለውጥ ልናመጣ እንደምንችል ይሄ ሚዲያ በብዙ ያስተምራል የሚል እምነት አለኝ። ሚዲያ አሰራሩን በሚመለከት አሁን ባለው የሚዲያ ዘመን ብዙ ሀብት የሚጠይቅ አይደለም፤ ፐልስ አፍ አፍሪካ ከበቂ በላይ መሰረተ ልማት ገንብቷል። አሁን የሚያስፈልገው በጣም ውስን አንከር እና በጣም ብዙ ተመራማሪዎች መገንባት ነው። ለምሳሌ ቅድም ያየናቸው ዜና አቅራቢዎች ለድፍን አፍሪካ ከሚሆኑ አንድ ሰው ለምዕራብ አፍሪካ፣ አንድ ሰው ለምስራቅ አፍሪካ፤ አንድ ሰው ለሰሜን፣ አንድ ሰው ለደቡብ ተመድቦ ከጀርባው በርከት ያሉ ተመራማሪዎች ኖረው፣ በምርምር ላይ መሰረት ያደረገ መረጃ ፕሮዲዩስ ማድረስ ከቻለ ምንም ጥርጥር የለውም በአፍሪካ ቀዳሚ ይሆናል።

የተለመደው የኢትዮጵያ የዜና አቀራረብ ባህል አሁን አይሰራም። ለምሳሌ የውጪ ሚዲያዎችን እያጣቀሱ ማቅረብ ሳይሆን ከውጪ ሚዲያዎች ጋር እኩል ዜና ማቅረብ ያስፈልጋል፤ ያ ደግሞ እንዲሆን በጣም ብዙ መንገዶች አሉ በቀላሉ መረጃን ማሰባሰብ፣ መተንተን ይቻላል፤ ቀድሞ መረጃን ማቅረብ ሲቻል ተወዳዳሪ እየተሆነ ይኼዳል። እና ወጣቶች እንድታበዙ፣ የጀመራችሁት ነገር ፍሬያማ እንዲሆን ተግታችሁ እንድትሰሩ፣ ከስራ ከትጋት ውጪ ውጤት ስለማይኖር በብዙ ጥረት ለአፍሪካ ግንባር ቀደም ሚዲያ እንድታደርጉት አደራ እያልኩ፤ እዚህ ቦታ የተቀጠራችሁ ወጣቶች ታሪካችሁ በእጃችሁ እና ከፊታችሁ ነው ያለው ቀደምት የሚዲያ ሰዎች እዚህ የምታዮአቸው በጊዜያቸው ብዙ የተጉ፣ ብዙ የሰሩ፣ አሁን ላለው ወጣት ደግሞ ልምዳቸውን ለማካፈል ከእኛ ጋር የሚገኙ ግለሰቦች አሉ። እናንተም ነገ በታሪክ ውስጥ ስማችሁ ጎልቶ የሚጠራ፣ በስራችሁ የምትታወቁ እንድትሆኑ ከፈለጋችሁ ትጋት ያስፈልጋል፤ ከስራ ውጪ፣ ከትጋት ውጪ ውጤታማ መሆን አይቻልም!

ስራችሁን አትለማመዱት፣ አትቻሉት፣ በቅተናል አትበሉ!

በየቀኑ መማር፣ በየቀኑ መትጋት ያስፈልጋል፤ ከልምምድ ወጥተን ሁልጊዜ የምንማር እንድንሆን፣ የምናድግ እንድንሆን፣ በአፍሪካ የምንፈለግ እንድንሆን አበክራችሁ እንድትሰሩ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ፐልስ ኦፍ አፍሪካ እንደተባለውም የአፍሪካ ድምጽ ነው፣ የአፍሪካ ምስል መገለጫ ነው፣ የአፍሪካ ባህል መገለጫ ነው፣ የአፍሪካ ሀብት መገለጫ ነው፤ ኢትዮጵያ አንሰራርታ አፍሪካ የምታንሰራራበትን መንገድ አብረን ካልሰራን በቀር ብቻችንን ማደግ ስለማንችል ከአፍሪካ ወንድሞቻችን ጋር በሁሉም ነገር በትብብር እና በመደመር፣ በጋራ እንድንቆም ፐልስ ኦፍ አፍሪካ ሚናውን እንደሚጫወት ከአደራ ጭምር ላሳስባችሁ እወዳለሁ። እንኳን ደስ አላችሁ ታላቅ ቀን ነው እንኳን ደስ አለን።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ



በክረምት በጎፈቃድ መርሃግብር በሀላባ እና ከምባታ ዞኖች የተገነቡ ሞዴል የገጠር መንደሮችን ማስረከብ

መስከረም 28፣ 2018ዓ.ም

ዛሬ በጣም አስደሳች ቀን ነው፤ ለእኔ እና ከእኔ ጋር ያሉ ወንድሞቼ።

ያው እንደሚታወቀው በሀገር ደረጃ ብልጽግናን ማረጋገጥ አለብን ስንል በቤተሰብ ደረጃ እያንዳንዱ ዜጋ ከነበረበት የኑሮ ዘዬ ወደተሻለ ደረጃ ማደግ አለበት ማለት ነው። የእኛ የብልጽግና ትርክት እያንዳንዱን ዜጋ፣ እያንዳንዱን ቤተሰብ፣ እያንዳንዱን መንደር ካልነካ የተሟላ ሊሆን አይችልም፤ የተሟላ የሚሆነው በገጠርም በከተማም፣ በከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉትንም አጅ አጠሮቹንም የሚያቀራርብና ወደ መካከለኛ የሚያመጣ መሆን አለበት።

በከተማ የከተማ ኮሪደር ብለን ላለፉት አራት/አምስት ዓመታት የእጅ አጠር ሰዎች ቤት እያፈረስን መንደሮች እንደቀየርን ይታወሳል። ለምሳሌ እኛ አዋሬ አካባቢ በጣም በጣም ዝቅተኛ የሚባል የአኗኗር ዘዬን የሚኖሩ ዜጎቻችንን በአካባቢው ለመቀየር፣ ቤት ገንብተን ለመስጠት ሞክረናልና ያ ልምምድ በግል ሀብት ያላቸው ሰዎች፣ ጉልበት ያላቸው ወጣቶች፣ መርዳት የሚፈልጉ ሰዎች ታክለውበት በከተሞች አካባቢ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ቤቶች ተሰርተዋል። አዲስ አበባ ብቻ በጣም በርካታ ቤቶች ፈርሰው ተገንብተዋል ተጠግነዋል።

ያ በከተማ ላይ የሰራነው ስራ ወደ ገጠር ካላመጣነው በቀር በከተማ ብቻ ሰርተን ብልጽግናን ልናረጋግጥ አንችልም!አብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አሁንም ገጠር ውስጥ ስለሚኖር ገጠሩን መቀየር ያስፈልጋልና የተሻገረ ገጠር ከነበረ፣ ከነበረው የኑሮ ዘዬ ከፍ ያለ ገጠር መፍጠር አለብን የሚል ትልም ነው የነበረን። ለዚያ ዘንድሮ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በአምስቱም ዞኖች ስራ ተጀምሯል። በሀላባ፣ በከንባታ፣ በስልጤ፣ በሐዲያ እና በጉራጌ ዞን፤ በአምስቱ አካባቢ እኛ ሞደል ቤቶች እንሰራለን።

የምንሰራቸው ቤቶች ቀደም ሲል እንዳያችሁት አንዱ፣ የአንዱ ቤተሰብ ቤት ሶስት መኝታ ቤት አለው፣ በቂ የሚባል ሳሎን አለው፣ ከጓሮም ከፊትም እርሻዎች አሉ፣ እንደምታዳምጠው ከብቶች ተለቀው ማሳ ላይ ሳይሆን ልክ እንደሰለጠነው ዓለም

የሚመገቡበት ቦታ ተዘጋጅቶላቸዋል፣ ከብቶች እና አርሶ አደሮች እንደ ከዚህ ቀደሙ አብረው አያድሩም።

ሁለተኛ የከብት ተረፈ ምርት የሰዉም ጽዳጅ ተከማችቶ ባዮጋዝ፣ በእያንዳንዱ ቤት ባዮጋዝ አለ ስለዚህ እናቶች እንጨት አይቆርጡም፤ እንደ ከዚህ ቀደሙ አይሰባቸውም ባዮጋዝ ተጠቅመው ማብሰል ይችላሉ። ሶስተኛ እያንዳንዱ ቤት ሶላር አለው። ሶላር ስላለው ሁሉም ቤት ቴሌቭዥን አለው፣ ሁሉም ቤት ስልክ ቻርጅ ያደርጋል፣ መብራት አለው። ይሄ ለእኛ አርሶ አደሮች በጣም በጣም ትልቅ ትርጉም ያለው ነገር ነው። ሁሉም ቤት የተሰራ ሽንት ቤት አለው፣ ሁሉም ቤት ውሃ አለው፣ ቦቲዎች ተሰቅለው ውሃም ተከማችቶ ለሻወር እና ለሽንት ቤት መገልገል የሚያስችል አቅም አለው፣ በእያንዳንዱ ጓሮ የጓሮ እርሻ አለው ጎመን አለ፣ ቃሪያ አለ፣ ልዩ ልዩ አትክልቶች እና ፍራፍሬ አሉ፣ አቮካዶ ማንጎ እንደየከባቢው ተተክለዋል፤ እዚህ ደግሞ እንሰትም አለ። ቡና ያለባቸው ከባቢዎችም አሉ፣ ከዚህ በተጨማሪ ማር አለ፣ ሌማቱን የሚያካትተው የዶሮ እርባታ አለ ስለዚህ እያንዳንዱ ቤተሰብ ወተት ያገኛል፣ እንቁላል ያገኛል፣ ከጓሮ ጎመን፤ ሰላጣ ያገኛል፣ ቃሪያ ያገኛል፣ ጎይል ያገኛል፣ ከቤተ ዘመድ ጋር ራቅ ያለ አካባቢ ካሉ ሰዎች ጋር በስልክ መገናኘት ይችላል፣ የዜና አውታር ለመከታተል በየቤቱ ቲቪ አላቸው።

ይሄንን የአኗኗር ዘዬ በኢትዮጵያ ደረጃ አምሳ/ስልሳ በመቶ አመጣን ማለት ከበለፀጉ ሀገራት የአኗኗር ዘዬ አስተካከልነው ማለት ነው። በቃ የሰለጠነው ዓለም ከዚህ የተለየ ምንም ነገር የለውም። ይሄ ቤት እኔ ካደግኩበት የእድገት ደረጃ በብዙ እጥፍ ይበልጣል። በንፅህናው፣ በአየሩ ጥራት፣ ባለው ቤት ውስጥ ባለው የግላዊ ነጻነት፣ የአኗኗር ዘዬ በብዙ መንገድ ይበልጣል። ነገር ግን ይሄንን ማሳያ እንዴት እናበራክተው ነው ጉዳዩ፤ እንዴት እናባዛው?

በከተማ ያሉ ሀብታሞች፣ በውጭ ሀገር ያሉ ዲያስፖራዎች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ኩባንያዎች የሚያፀድቅ ስራ መስራት ከፈለጉ ለነፍሳቸው እርካታ መስጠት ከፈለጉ ይሄንን ጉዳይ ነው ማገዝ ያለባቸው። እያንዳንዱ ኩባንያ በየመንደሩ አስር/ አስራ አምስት እየወሰደ፤ በጣም ውድ አይደለም ቤቱ ቤቱን የሰራነው ሰማንያ በመቶ ይሄ ጡብ የምታየው አፈር ነው የከባቢው አፈር ነው። አስር/አስራ አምስት በመቶ ሲሚንቶ ይቀላቀልበታል። አብዛኛው ሪሶርስ ሎካል ነው። ከቆርቆሮ ከሶላር ውጪ አበዛኛው የምታየው ጉዳይ ሎካል ነው። ሶ የሰው ጉልበት እንጠቀማለን ሎካል ማቴሪያል እንጠቀማለን፤ በረከሰ ግን ፕላንድ በሆነ መንገድ ነው የምንሰራው።

አሁን እዚህ አካባቢ ለቅሶ ቢያጋጥም እንደምታየው ነው መስኩ ሰፊ ነው፤ ሰርግ ቢያጋጥም ምንም አይነት ችግር የለም፤ መለስተኛ መገበያያ ተፈልጎ ለገበያም ይሆናል ሰፊ ቦታ ነው። ይሄን ይዘህ ዝም ብለህ ብትሰራ ከሆነ ጊዜ በኋላ መሐል ላይ የመኪና መንገድ ማስገባትና በየበረንዳው ፒክአፕ መኪና ማየት ነው የሚሆነውና ኩባንያዎች፣ ግለሰቦች፣ ትንሽም ትልቅም፣ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች፣ የሚያወርሱ እድሜ ጠገብ ሰዎች ከሚያወርሱት ሀብት አንድ ቤት፣ ሁለት ቤት ለአርሶ አደር ለማያውቀቁትም ሰው ቢሆን እየሰሩ የማለፍን ልምምድ እንደ ሀገር ብናሳድግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሄን ነገር በጣም ሰፊ ቦታ ማየት ይቻላል።

ዲያስፖራ አካባቢ ያሉ፣ ከተማ አካባቢ ያሉ ሰዎች ደግሞ እውነት ለመናገር በእረፍት ጊዜ ለሳምንት/ ለሁለት ሳምንት ከቤተሰብ፣ ከልጆች ጋር የገጠሩን ነገር ለማሳየት እንደዚህ ያሉ ቤቶች ከተበራከቱ ምንም ችግር የለውም ማንም ሰው መጥቶ መቀመጥ ይችላል። ሽንት ቤት አለ፣ ውሃ አለ፣ መብራት አለ፣ ቲቪ አለ፣ ስልክ አለ፣ ለመዝናናት የሚመች ነው። ከዚህ ቀደም ከምናውቀው የገጠር ኑሮ በጣም ሻል ያለ ነገር አለው፤ አየሩ ድሮም ያምራል፣ ከባቢው ድሮም ያምራል፣ የሰው ልብ እና ደስተኝነት ድሮም ያምራል። ችግሩ ቤት ነበር እሱን ከቀየርን እየመጣን የምናርፍበትም ሊሆን ይችላል። ከተለያየ ቦታ ቤተሰብ ጠያቂዎች ከተማን ምንም አያስፈልጋቸውም።

እውነት ለመናገር በዚህ ደረጃ ንፁህ ነገር ከተማ ውስጥ ብዙ አይታይም። ከተማ ጥግጊቱም የጠበበ ስለሆነ የመቆሸሸ አቅሙም ከፍተኛ ነው። እዚህ በጣም ንጹህ አየር በጣም የሚያምር ነገር፤ የምትበላው ሁሉ ድንች ነው፣ ስኳር ድንች ነው፣ የተቀቀለ ነው፣ ጤናማ ነው። ከምግብ አንፃርም ሲወሰድና ይሄንን ነገር ለማበራከት ለመንግስት የሚተው ሳይሆን እያንዳንዱ አርሶ አደር ይሄንን የኑሮ ዘዬ መመኘት መቅናት አለበት። ያኛው ገበሬ ከዚህኛው ገበሬ የአኗኗር ዘዬ ማነስ የለበትም።

ወረዳው፣ ቀበሌው፣ ዞኑ፣ ክልሉ ዋና ስራው የዜጎቹን ህይወት ማሻሻል ነው። ሻል ያለ ሀብት ያላቸው ደሞ ሰዎች ይሄንን መደገፍ ነው። ሁላችን አስር፣ አስራ አምስት፣ ሀያ ብንሰራ በሺህዎች ገጠር ውስጥ ይሰራሉ። ሰው ሀብት አለው፣ አቅም አለው፤ አቅጣጫ ማሳየት ማመላከት ነው የሚያስፈልገው፣ ማገዝ ነው የሚያስፈልገው፣ ገንዘቡን አስቀምጦ ኑሮው የቆሸሸ ነው። ለምሳሌ፤ አስር ላም ያለው ሰው አስር ላም አያስፈልገውም አስር ላም መስክ ላይ የምታሰማራ ከሆነ በስጋውም የምታገኘው ወተት ዝቅተኛ ነው። ግን በጊቢ ውስጥ የሚቀለቡ የማይንቀሳቀሱ ሁለት በሬ እና ሁለት ላም ያለው ሰው ሁለቱ በሬ ከሶስት ዓመት በኋላ በጣም ብዙ መቶ ሺህ ብር ሊያወጣለት ይችላል። እና አይናቸውን

መግለጥ፣ ብር የሚያገኙበትን መንገድ የኑሮ ዘዬ የሚሻሻልበት መንገድ መፍጠር ነው እንጂ የአቅም ጉዳይ ብቻ አይደለም።

ከዚያ በኋላስ?

በአቅራቢያው ትምህርት ቤት ትሰራለህ፣ ጤና ኬላ ትሰራለህ፣ አንድ አምቡላንስ ትመድባለህ፣ እናቶች እዚሁ ይወልዳሉ፣ ከውሃ የተነሳ ንፅህና አለ፣ ከመብራት የተነሳ የዓይን ትራኮማ ይቀንሳል፣ ተጽዕኖው በጣም ከፍተኛ ነው። እና ኢትዮጵያውያን እኔ በጣም በጣም ደስ ብሎኛል ዛሬ። የእኛ አርሶ አደር የራሱ የተለየ ሽንት ቤት ኖሮት ሽንት ቤት ውስጥ ውሃ ማየት፣ ሶላር ማየት፣ በጓሮ የሚበላ ነገር በስፋት ማየት፣ ትልቁ የእርካታ ምንጭ ነውና ተጋግዘን እጅ አጠር የሆኑ የእኛን ሰዎች በመደገፍ ኑሮዋቸውን እናሻሽል፣ ኑሯቸውን እንቀይር ያ ሲሆን የኢትዮጵያ ብልጽግና ወደምናስበው ደረጃ ይመጣል።
ግድብ ገድበናል ጥሩ ነገር ነው፣ ጋዝ አውጥተናል ጥሩ ነገር ነው፣ ትላልቅ ፕሮጀክቶች እየሰራን ነው ጥሩ ነገር ነው ግን ያ ነገር እያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ መግለጥ አለበት። ያ ደግሞ እንዲሆን ከአንድ ወገን የሚጠበቅ ሳይሆን የሁላችን ትብብር ስለሚያስፈልግ አጀማመራችን በጣም በጣም አስደሳች ነው፣ ይሄንን ብናሰፋ እንደ ሀገር የኩራት ምንጭ፣ እንደ ሀገር ያለመሰደድ በሀገር የመስራት፣ በሀገር የመኩራት ልምምድን የሚያሳድግ ስለ ሆነ ተባብረን እንድናሰፋው አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በተለየ ግን ማመስገን የምፈልገው እዚህ ባለፈው ጥቂት ወራት በፊት ስመጣ በከንባታ አምበርቾ ተራራ ወጥቼ ነበረ እና ያኔ የነበረው የአንበርቾ ተራራ ደረጃ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ደረጃዎች ነበረው። ተጨማሪ ቦታ ስላለው ደግማችሁ ከሰራችሁ እመጣለሁኝ ብዬ ፈተና ለከንቲባው ሰጥቼ ነበረ። የከንባታን የዱራሜን አካባቢ ሰዎች በማስተባበር ያን ሰባት መቶ የነበረውን ደረጃ ተጨማሪ አንድ ሺህ አምስት መቶ ጨምሮ ሁለት እጥፍ ጨምሮ በጣም አርዝመውታል፤ ለቱሪስት የሚመች አድርገውታል። በጉልበት ነው የሰሩት ማንም አላገዛቸውም፤ ጥያቄውን፣ ፍላጎቱን፣ ፈተናውን ተቀብለው በትብብር ነው ያሳኩት። ለዚህ ለከንባታ ህዝብ ከፍተኛ ምስጋና እና አክብሮት አለኝ፤ በጣም ላመሰግን እወዳለሁ። ከተሜዎች ደግሞ እየመጡ ይሄን ስራ እንዲያዩ እንዲዝናኑ እመክራለሁ።

ዛሬ ለከንባታ አስተዳዳሪዎች፣ ለዱራሜ ከተማ ከንቲባ እንዲሁም ለሀላባ አስተዳዳሪ ተጨማሪ ፈተና ሰጥቻለሁ። ይሄን የሰራነው እኛ ነን ተምሳሌቶቹን፤ የሚቀጥለው ዓመት የዞኑ የከተማው አመራር ሰዉን አስተባብሮ ይሄንን ቤት መቶ መቶ ካደረሰው ተመልሼ እንደምመጣ ቃል ገብቼላቸዋለሁ። መቶ ዝቅተኛው ነው ከዚያ የበለጠ መስራት ይቻላል፤ ግን አርሶ አደር አስተባብረን፣ በከተማ ያለ ነዋሪ አስተባብረን፣ ባለሀብት አስተባብረን

ይሄንን መንደር መቶ ብናደርገው በሚቀጥለው ደግሞ ሺህ ብናደርገው በዚያ መንገድ እየተበራከተ ብዙ ዜጎች የሚነካ ስለሚሆን ለከንባታ እና ለሀላባ ነዋሪዎች በሙሉ፤ ለአመራሮች በሙሉ እና በጎ ልብ ላላቸው ዜጎች በሙሉ እስከሚቀጥለው ዓመት የእኛ ድጋፍ እንደ አሁኑ ሳይታከልበት በዞኑ አቅም እና በህዝቡ ትብብር ተጨማሪ መቶ መቶ አርሶ አደሮች ኑሮዋቸው ካለበት ደረጃ ወደዚህኛው እንዲመጣ አዲስ ሃላፊነት ሰጥቻቸዋለሁ። እንደሚያሳኩት ተስፋ አደርጋለሁ። ከተሳካ እኔም በቃሌ መሰረት መጥቼ መልሼ የማያቸው ይሆናል።

እንበርታ፤ እንስራ ካልሰራን፣ ካልተጋን የሚመጣ ለውጥ የለም!

ስንተጋ ይሄው ለውጥ ልናመጣ እንደምንችል ታይቷል እና ከተጋን፣ ከሰራን፣ ከበረታን ከተባበርን ውጤት ስለሚመጣ በዚያው መንፈስ አበክረን ቀን ከሌሊት በመልፋት የሀገራችንን ብልፅግና እንድናፋጥን፣ የጀመርነውን መልካም ጅማሮ ከፍፃሜ እንድናደርስ፣ ድህነትን ታሪክ እንድናደርግ፣ችግርን ታሪክ እንድናደርግ፣ በሽታን ታሪክ እንድናደርግ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

አሁን ባያችሁት ትራኮማን፣ ተላላፊ በሽታዎችን፣ ከከብት የሚተላለፍ በሽታን ብዙ ነገር የሚያስቀር ስለ ሆነ የዜጎቻችንን የኑሮ ዘዬ መቀየር ብቻ ሳይሆን የቆይታ ዘመናቸውም እንደሚያድግ ጥርጣሬ የለኝም። በጣም ደስ ብሎኛል፣ አስደሳች ጊዜ ነበረ። ሁሉንም እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ተሳካልን እንኳን ተከናወነ ማለት እፈልጋለሁ። ያኔ እንጨርሳለን መጥተን እናስመርቃለን ብያለሁ በቃሌ መሰረት ጨርሰናል ዛሬ ተመርቀዋል። ሌሎቹንም እንደዚሁ እያስመረቅን እድገታችንን ማስቀጠል የሁላችን ድርሻ ይሆናል።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ!
ከምባታ ዞን፣ ዱራሜ ከተማ


ግብር፤ ለሀገር ክብር!

7ኛው የታማኝ ግብር ከፋይ እውቅና ሥነ-ስርዓት

መስከረም 28፣ 2018ዓ.ም

የተከበራችሁ ታማኝ ዜጎች፤ ታማኝ ግብር ከፋዮች በቃላችሁ ልክ መገኘት በመቻላችሁ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ በከፍተኛ ፍቅር ልገልጽላችሁ እወዳለው።
የተከበሩ አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣
የተከበሩ አፈ ጉባኤ አገኘው ተሻገር፣
ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣
የፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፣
የገቢዎች ሚኒስትር ክብርት አይናለም እንዲሁም የሁሉም ክልል ርእሳነ መስተዳድሮች፤ ሚኒስትሮች፣
እዚህ ከኛ ጋር ይህንን ታላቅ ቀን የምታከብሩ እንግዶች በሙሉ ዛሬ ታማኞችን የምናመሰግንበት ቀን ስለሆነ ታማኞችን ማመስገን እና የእነሱን ደስታ መጋራት መበልጸግ፣ ማደግ ለሚፈልግ ሃገር በእጅጉ አስፈላጊ ስለሆነ ሁላችሁንም እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

ባለፈው ዓመት በነበረን መሰል ፕሮግራም ጥቂት ቃል የገባሁላችሁ፤ ቃል የገባችሁልኝ ነገሮች ነበሩ። ከእነዚህ መካከል አንደኛው በእኛ በኩል ሲስተሞች አበልጽገን፣ አውቶሜሽን አስፋፍተን፣ ስርዓቱን እናዘምናለን የሌቦች ቁጥር እንቀንሳለን፣ በቢሮክራሲ የሚገጥማችሁን ተጽዕኖ እናሻሽላለን ብዬ ቃል ገብቼ ነበር ቅድም ስመጣ ያየናቸው ሲስተሞች ያውም በሀገር በቀል ተቋማት የበለጸጉ ሲስተሞች እነዚህን ችግሮች የሚፈቱና የገባሁላችሁን ቃል የሚተገብሩ ስለሆነ እናንተም ስትወጡ ምናልባት ነገ እንድታዩዋቸው፣ እንድትገለገሉባቸው በዚህ አጋጣሚ ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

ሁለተኛ ቃል የገባሁላችሁ ጉዳይ በታማኝነት በእናንተ ገንዘብ ኢትዮጵያን እንሰራለን የሚል ነበር፤ አሁን አምና ቃል የገባሁላችሁን መናገር እንብዛም አያስፈልግም ከዚህ ወጥታቹ ወደ ቤታችሁ ስትሄዱ በማስተዋል ግራ እና ቀኝ 20 ኪሎ ሜትር፣ 30 ኪሎ ሜትር ብትጓዙ የእናንተ ገንዘብ አንድ ብር፣ አንድ ዶላር እርዳታ/ ብድር ሳይታከልበት ያ የቆሸሸ ከተማችንን ለልጆቻችን በሚመጥን መልክ መስራት መጀመራችን ማሳያ ስለሆነ በእናንተ ገንዘብ ሀገር እየተሰራች መሆኑን ዳግም በኩራት ልገልጽላችሁ እወዳለው። ብዙዎቻችሁ የዘንድሮውን ውጤት በሚቀጥለው አሻሽለን እንገኛለን ብላችኋል፤ ብዙዎቻችሁን ደግሜ ማግኘት ችያለሁ በርከት ያሉ አዳዲስ ሰዎችም ታክለውበታል፤ ዘንድሮ አንድ ሺህ አንሞላም በሚቀጥለው አንዲ ሺህ ሞልቶ ዳግም እንደምንገናኝ ያለኝን

ተስፋ ልገልጽላችሁ እወዳለው። የኢትዮጵያ መንግሥት ኢትዮጵያ መቀየር አለባት፣ መበልፀግ አለባት ብሎ በቁርጠኝነት አምኖ እየተጋ ይገኛል!

ይህ ትጋቱ ሊሳካ የሚችለው፤ እውን ሊሆን የሚችለው እንደ እናንተ ባሉ ታማኝ የስራ ፈጣሪዎችና ግብር ከፋዮች፣ ሰሪዎችና አሰሪዎች መሆኑንም በጽኑ እናምናለን። በዚሁ አግባብ በመንግሥትና በታማኝ የግብር ከፋዮች መካከል በጥቂት ነጥቦች ላይ በጽሁፍ ያልሆነ ስምምነት እንድንፈጽም እፈልጋለሁ።

በእናንተ በኩል የግሉ ዘርፍ ከትርፍ በላይ ማህበራዊ አላማን ያነገበ ስራ የእያንዳንዱ ኩባንያ የስራ ሃላፊዎች እና ባለቤቶች አንዱ ዋነኛ ተልዕኮ መሆን አለበት። ሰርቶ ከግማሽ ቢሊየን ብር በላይ ግብር የሚከፍል ሰው ከትርፍ በላይ ለማህበራዊ አላማ እራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል። ሁለተኛው በታማኝነት ልናገለገላችሁ ስለወሰንን በስኬትም በተግዳሮትም ከመንግሥትና ከህዝብ ጋር የምትጋሩ ታማኞች መሆን አለባችሁ።
በደህናው ዘመን የምትሰበስቡ እና ሃብት የምታካብቱ በችግር ጊዜ ደግሞ ወደ ዱባይ የምትሸሹ መሆን የለባችሁም!

በመከራውም ጊዜ፣ በስኬቱም ጊዜ በጋራ ጸንተን የምንቆም መሆን አለብን። ሶስተኛ የሀገርን ጥቅም እና ትውልድን የምታስቀድሙ መሆን አለባችሁ፤ የምንሰራው ለኛ ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ጭምር ነው የሚለውን አምናችሁ ከልብ ተቀብላችሁ የምትተገብሩ መሆን ይጠበቅባችኋል። ያ ሲሆን ከሰፈሮቻችን ወጥተን ላቅ ያለ ስራ ለመስራት በእጅጉ ያግዘናል።

በእኛ በኩል በመደመር መንግሥት በግልጽ እንዳስቀመጥነው መንግሥታችን በችግር የማይታጠር፣ በመፍትሔ የሚሻገር መንግሥት ነው። ችግሮች ቆላልፈው አይዙንም፤ መፍትሔ እያፈለቅን እንሻገራለን። ሁለተኛ ለትጋት የጨከነ በአርያነት የሚመራ መንግሥት ነው፤ እንተጋለን፣ አርዓያ ሆነን ልንሰራት የምናስባትን ሀገር መሰረት እንጥላለን። ሶስተኛ ጀምረን የምንፈጽም፣ አልመን የምንተኩስ፣ ተናግረን የምንተገብር፣ በቃላችን ልክ የምንገኝ መንግሥት ለመሆን እየተጋን እንገኛለን። የመጨረሻው እኛን የሚመለከተው ነጥብ ጩኸት አያርደንም፤ በማንኛውም ጩኸት አንርድም፤ በክብርም አንታለልም፤ ጩኸትም አያቆመንም፤ ክብርም አያዘናጋንም። እነዚህን ነጥቦች የእኛ የስራ መመሪያ አድርገን እናንተ ደግሞ በታማኝነት፣ በቀጣይነት በመስራት የኢትዮጵያን ብልጽግና እንድናረጋግጥ አደራ እያልኳችሁ፤ ዛሬ ወርቅና ከዚያ በላይ ተሸላሚ የሆኑ ዜጎች ምርጥ ዜጎች ስለሆኑ በቪአይፒ ኤርፖርት እንዲስተናገዱ እና በኤርፖርት ያለው

መስተጓጉል እንዲቀንስ መንግሥት ወስኗል። ሁለተኛ 30 ልዩ ተሸላሚዎች ላለፉት አራት ዓመታት በታማኝነት ፕላቲንየም ሽልማት ያገኙ 30 ልዩ ተሸላሚዎች የኢትዮጵያ ዜጎች ከሆኑ ባለቤቶች ወይም የስራ አስኪያጆች ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጣቸዋል።

ይሄ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለስራ ሲንቀሳቀሱ ቪዛን ጨምሮ ላለው ማንኛውም ነገር መስተጓጉል እንዳይገጥማቸው ልዩ የፕላቲኒየም ተሸላሚዎች ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጆች እንደ ኩባንያው ምርጫ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ሰጥተን እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ዲፕሎማት የሚወሰዱ ይሆናል። ሶስተኛ የፕላቲኒየም ተሸላሚዎች በተለይ የፕላቲኒየም ልዩ ተሸላሚዎች ከሰላሳዎቹ መካከል የኢትዮጵያ ኩባንያ ለሆኑት ከንግድ ገቢዎች ኤአይኤች ጋር በመነጋገር አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ከኢትዮጵያ ውጭ በተመረጡ የአፍሪካ ሃገራት ኢንቨስት እንድታደርጉ መንግሥት የኢንቨስትመንት አርማ አድርጎ ከናንተ ጋር ይሰራል። ኢትዮጵያ ማንሰራራት የጀመረችበት ዘመን ስለሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ኢንቨስት ማድረግ ለኛ በቂ ስላልሆነ በተመረጡ የአፍሪካ ሃገራት ልዩ ተሸላሚዎችን ልዩ ድጋፍ በማድረግ አስፈላጊ ከሆነ ከኤአይኤች ጋር በሽርክና ማኅበር ወይም እናንተ በጋራ ወይም በተናጠል በምታቀርቡት ፕሮፖዛል በሁሉም መስክ የኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ ያደርግላችኋል፤ በምትሄዱበት ሀገር ኢምባሲዎቻችን ልክ እንደ መንግሥት ተቋማት እናንተን ያገለግላሉ።

የተከበራችሁ ታማኝ የግብር ከፋዮች የሚቀጥሉት አምስት፣ አስር ዓመታት ለእድሜ እየጸለይኩላችሁ በፍጹም የዛሬዋን ኢትዮጵያ ደግማችሁ እንደማታዩ በእርግጠኝነት ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። ሃገራችን ትሰራለች፤ ለልጆቻችን የበለጸገች ሃገር እናስረክባለን። የገባናቸውን ቃሎች እንፈጽማለን!

በኢትዮጵያ አጥር አንወሰንም፤ ወደ አፍሪካ እንዘረጋለን፣ ወደ መካከለኛው ምስራቅ እንዘረጋለን። ብዙ ህዝብ፣ ብዙ የሚችሉ ዜጎች ያላት ሀገር ስለሆነች መንግሥት በዕውቀት የግሉን ዘርፍ እየደገፈ ከሀገር ውጪ እያመረታችሁ ሃገራችሁን ስም የምታስጠሩ፣ ተጨማሪ ሃብት የምታመጡ እንድትሆኑ አበክረን የምንሰራ ይሆናል። በኛ በኩል ከሞላ ጎደል ስርዓት በማዘመን፣ ሌብነት ለመቀነስ ጥረት ያደረግን ቢሆንም አሁንም የተሟላ ሌብነት የጠፋ እንዲሆን የግሉ ዘርፍ ተባባሪ እንዲሆን፣ እናንተን ለማገልገል ስልጣን ይዘው ከናንተ ገንዘብ የሚቀበሉ ባለስልጣናትን የምታስተናግዱ እንዳትሆኑ፤ ጨዋነትን፣ ሲቪሊቲን፣ ማገልገልን ሰርታችሁ እንዳሳያችሁት የእኛንም ሰዎች በማስተማር እንድታግዙን በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለው።

የሚሰርቅ ሀገር፣ የማይተጋ ሀገር ፣ ያለችውን ውስን አንጡረ ሀብት የሚያሸሽ ሀገር አይበለጽግም!

እኛ መበልጸግ ስለምንፈልግ ሌብነትን የምንጠየፍ፣ ሀብት ማሸሽን የምንጠየፍ፣ ስንፍናን የምንጠየፍ እና ተግተን የምንሰራ በመሆን ለልጆቻችን የበለጸገች ሃገር ለማስረከብ በጋራ እንድንቆም አደራ እያልኩ ኢትዮጵያ ለመበልጸግ በምታረገው ጥረት የሚገጥማት ማንኛውም ፈተና ካለ መንግሥት እንደ መልካም እድል የሚወስደው ይሆናል። ከእያንዳንዱ ፈተና፣ ከእያንዳንዱ ተግዳሮት እድልን ፈልቅቀን እያወጣን የኢትዮጵያን ብልጽግና የምናፋጥን እንጂ በሚገጥሙን ተግዳሮቶች የምንቆም መሆን የለብንም። በትብብር፣ በሀብረት፣ በመተጋገዝ ሀገራችንን ካለችበት ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ለማሸጋገር በትጋት እንድንሰራ አደራ እያልኩ የውጭ ኩባንያዎች፣ የውጭ ዜጎች ሀገራችን አምናችሁ በኢትዮጵያ ኢንቨስት የምታደርጉ፣ ይበልጥ ትርፋማ እንድትሆኑ፣ ከኢትዮጵያ ኩባንያዎች ጋር እንድትዋሃዱ ልዩ በሆነ መንገድ የኢትዮጵያ መንግሥት በኢንቨስትመንት ኮሚሽንና በኢንቨስትመንት ቦርድ በኩል ድጋፍ የሚያደርግላችሁ መሆኑን ቃል እየገባው እንዘርጋ፣ እንበርታ፣ እንጣር።

የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማየት ሁላችንንም ያብቃን፤ እኔ እንደማይ አምናለሁ፣ ያመነ ከእኔ ጋር ይጓዝ!

አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ



ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለማው ስማርት የፍርድ ሥርዓት

—መስከረም 30፣ 2018ዓ.ም

የኢትዮጵያ ዲጂታል 2025 ሲጠናቀቅ፤ ዲጂታል 2030 ስትራቴጂ ሲቀረፅ ትኩረት የተሰጠባቸው መስኮች አሉ። አንደኛው በፋይናንስ ዘርፍ ሰው ገንዘብ በማስገባት፣ በማስወጣት፣ በማዘዋወር ነገሮችን ማቅለል አለብን፤ ባንክ እየሄደ ብቻ ሳይሆን ከራሱ ስልክ ከቤቱ ሆኖ ገንዘብ የማዘዋወር አቅሙ ማደግ አለበት የሚል እቅድ ነበር። በዚያ መሰረት በሞባይሉ በቴሌብር ብቻ ሳይሆን ባንኮች ባላቸው ሶፍትዌር ጭምር በቢሊየን የሚገመት የገንዘብ እንቅስቃሴ ማካሄድ ተችሏል።

ብዙ ሰዎች ገንዘባቸውን በቀላሉ በአንላይን ይቀያየራሉ ያ ጊዜን ቆጥቧል፣ ፍጥነት ጨምሯል። በሌላ መንገድ ደግሞ መንግስት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ዘርፎች አሉ ለምሳሌ ንግድ፤ ንግድ ፍቃድ ለማውጣት ወይም ገቢዎች ገቢ ለማስገባት እነዚህን አውቶሜት ተደርገው ገንዘብ የሚሰበሰብበትም፣ ፈቃድ የሚሰጥበትም ጊዜ እንዲያጥር ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል። በህግ አስከባሪ ተቋማት ፖሊስ አካባቢ፣ መከላከያ አካባቢ የተሰሩ ስራዎች አሉ። በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ በመቶዎች የሚቆጠሩ የአውቶሜሽን ስራዎች ተሰርተዋል። ለምሳሌ መሶብን ብንወስድ አገልግሎት ለመስጠት፣ መታወቂያ ለማውጣት፣ ፓስፖርት ለማውጣት የመሳሰሉ ጉዳዮች ለማድረግ የመሶብ አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ነው ያለው።

እነዚህ ሁሉ ከአስፈፃሚ በኩል ያው ስራዎች ከህግ አውጪው እና ህግ ፈፃሚው ጋር ካልተያያዙ አጠቃላይ የመንግስት ቁመና አያመጡም። በአስፈፃሚው በኩል ቅድም እንዳነሳኋቸው በጣም በርካታ አውቶሜሽኖች ተሰርተዋል። የፍትህ ስርአቱ ደግሞ ትልቁ ጥያቄ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህ በገንዘብ ይገዛል፣ በዘር ይገዛል፣ በሀይማኖት ይገዛል፣ በዶታ ይገዛል፣ በዚህ ምክንያት ፍትህ አላገኘንም፤ ፍትህ እና ርትዕ አይረጋገጥልንም የሚል ስጋት አለ። ያን ለመቀነስ አንዱ መፍትሄ አውቶሜሽን ነው።

አውቶሜሽን አራት አለባውያን ወይም አራት ምሰሶዎሽ ይፈልጋል። አንደኛው ፖሊስ፤ ፖሊስ አውቶሜት ሆኖ ወንጀለኛን በቀላሉ መያዝ ችሎ፣ የመመርመር አቅም አድጎ ትክክለኛውን መረጃ ለአቃቢ ህግ ማቅረብ ይጠበቅበታል። አቃቢ ህግም ዘምኖ፤ አውቶሜት ሆኖ ፍትህን ሳያዳለ ለፍትህ የሚቆም መሆኑን የሚያግዙ የቴክኖሎጂ አቅም ያስፈልጉታል፤ እነዚህ ሁለቱን ላለፉት ዓመታት ስንሰራ ቆይተናል ውጤቱም ጥሩ ነው።

ሶስተኛው ምሰሶ ፍርድ ቤት ነው፤ ፍርድ ቤት ቅድም እንዳያችሁት እዚህ ሆኖ በቨርቹዋል ሰበር ችሎትን ጋምቤላ ተቀምጦ ፣ ጅጅጋ ተቀምጦ፣ መቀሌ ተቀምጦ ማግኘት ማለት በጣም በጣም ትልቅ ጠቀሜታ ነው። ግለሰቦች ፍትህን ፍለጋ ግማሹን በእግር፣ ግማሹን በመኪና መጥተው፣ ቤተሰብ ፈልገው ዘመድ ጋር ተቀምጠው ወር ሁለት ወር ቆይተውም ነው ፍትህን የሚያገኙት።

አሁን ሳይመጡ ካሉበት ቦታ ሆነው ጉዳያቸውን ማስደመጥ እና ፍትህ መፈለግ መቻላቸው ከገንዘብ ከጊዜ አንፃር በጣም የማይለካ ጠቀሜታ ነው የሚያስገኘው። ሶስቱ ምሰሶዎች ብቻቸውን ግን የተሟላ ፍትህ አያመጡም። ጠበቃውም ደግሞ እንደዚሁ የዘመኑ በቨርቹዋል እነዚህን ጉዳዮች ማግኘት የሚችል፣ ማየት የሚችል፣ በዚህ ስርአት ውስጥ እራሱን አካትቶ የሚያይ መሆን አለበት። ጠበቃው ግን የአስፈፃሚውም የህግ አውጪውም ተርጓሚውም አካል አይደለም፤ ጠበቃውን ደግሞ የሚቆጣጠረው ህዝብ ነው። አገልግሎቱን የሚገዛው ህዝብ ነው፤ የሚቆጣጠረውም ህዝብ ነው። ጠበቃው ሲቀየር፣ ፖሊስ ሲቀየር፣ አቃቢ ህግ ሲቀየር፣ የዳኝነት ስርአቱም ሲቀየር ሰዎች በቀላሉ ፍትህን የሚያገኙበት እድሉ እየሰፋ ይሄዳል። በተዘዋዋሪ ዜጎች ምንዳቸው፣ ትርፋቸው የሚለካው በተሳለጠ የፍትህ ማግኘት ብቃት ነው።

ፍትህ በአንድ ቀን መገኘት ሲገባው በአንድ ወር ወይም በአንድ ዓመት የሚገኝ ከሆነ የዘገየ ፍትህ እንደ ፍትህ አይቆጠርም መፍጠን አለበት!

ሁለተኛ ያ የፈጠነው ፍትህ ደግሞ ሳይገዛ መሆን አለበት። በህግ ብቻ፤ በሆነ በጥቅም፣ በሆነ ዝምድና ሳይሆን በህግ ብቻ መሆን አለበት። እና ከዚህ አንፃር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስራ ዛሬ ያየነው በጣም አስደማሚ በአንድ ጊዜ በርካታ ችሎቶች በቨርቹዋል መቆጣጠር ይችላል። ይሄንን ልምምድ እና ስርአት ባላቸው ቀንጫፎች በሙሉ አዳርሰዋል። ከእነርሱም አልፎ ብዙ ክልሎች ይሄንን መንገድ እንዲከተሉ እያደረጉ ነው። ከዚህ አንፃር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የተከበሩ አቶ ቴዎድሮስ ምህረቱ ሊመሰገኑ ይገባል። ስራ ሲጀምሩ ከተነጋገርንባቸው ጉዳዮች አንዱ ይሄ ነው። ይሄንን በሚያስደንቅ መንገድ ለውጥ ማምጣት ችለዋል።

በእርግጥ ቴክኖሎጂ የሚሰራው በሰው ነው፤ የሰው አዕምሮ ካልተቀየረ ቴክኖሎጂ ብቻውን የምንፈልገውን ነገር አያመጣም። ሰው መቀየር ፣ ቴክኖሎጂ መቀየር፣ ስራ ከባቢ መቀየር ያ ሲደመር ደግሞ ፍትህን ማፍጠን እና ማረጋገጥ ይጠይቃል። ለፍርድ ቤት በጣም ትልቅ ህንፃ ሰጥተናቸው ስራ ጀምረዋል፤ ያ ቦታ ሲጠናቀቅ ቴክኖሎጂው

ሲጨመር ወጣቶች በዘመነ መንገድ ፍትህን ለማምጣት የሚቆርጡ፣ የሚሰሩ ሲሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የምናስበውን የፍትህ ስርአት ማረጋገጥ ይቻላል። ለረጅም ጊዜ መንግስት ሲጠየቅ የነበረው አንዱ ጉዳይ የፈጠነ እና ንፁህ ፍትህ ማግኘትን እንፈልጋለን ነው። እና ቴክኖሎጂውን እርሻውን ለማዘመን፣ ኢንደስትሪውን ለማዘመን፣ ቱሪዝሙን ለማሳለጥ፣ ከተማ ውስጥ ያሉ ስራዎች ለማዘመን፤ ከዚህ አልፈን ደግሞ ገቢ የምንሰበስብበት፣ ንግድ የምናሳልጥበት፣ ፍትህ የምናመጣበት አድርገን መጠቀም ጀምረናል።

ከዚህ አንፃር ሰው ሰራሽ አስተውሎት ኢንስቲትዮት ለዚህ በጣም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፣ ኢንሳ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፣ ኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል። እነዚህ የመንግስት የዲጂታል ማሳለጫ ክንድ ሆነው ቴክኖሎጂን እየፈጠሩ እየሰሩ ይገኛሉ። ያየናቸው ሲስተሞች በሙሉ በእኛው ሰዎች የተሰሩ ናቸው ይሄ ትልቅ እመርታ ነው። መሶብ የተሰራው በእኛ ነው፤ ዛሬ ያየነው ሲስተም የተሰራው በእኛ ነው። ይሄ ነገር እያደገ እና እየሰፋ ሲሄድ ዜጎች መጠቀም እየቻሉ ሲሄዱ በጣም በርካታ ነገር የሚያቃልል ይሆናል። ብልፅግናን ማረጋገጥ ስናስብ በገንዘብ ክምችት ብቻ አይደለም ሁለንተናዊ ነው። ፍትህንም ይመለከታል፤ የአኗኗር ዘዬን ይመለከታል። ያን ከማረጋገጥ አንፃር ዛሬ ያየነው ስራ በጣም ተስፋ ሰጪ እና አስደሳች ነው።

ዋናው መልእክቴ በዚህ እንዳንረካ! ይሄ ጥሩ ጅማሮ ነው አንደኛ ሁሉም ክልል መዳረስ አለበት፣ ሁሉም አካባቢ መዳረስ አለበት፣ ሁሉም ሰው ይሄንን መጠቀም መቻል አለበት፤ ከጥቅም በኋላ ደግሞ ፍትህን ማጣጣም አለበት። ያ አስኪሆን ድረስ በጅምሩ ሳንረካ መልካም ጅማሮ ነው በርትተን ሰርተን ወደሚቀጥለው ደረጃ የምናሸጋግረው ከሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ የምናስበውን ፍትህ ለማምጣት በእጅጉ የሚያግዝ አስደሳች ስራ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በርቱ ይቀጥል በሁሉም መስክ የጀመርናቸው ለውጦች ተሰናስለው የኢትዮጵያን ብልጽግና እስኪያረጋግጡ እንዳናሸለብ፣ እንዳናንቀላፋ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ

በምስራቅ ሸዋ ዞን የስንዴ ምርት ሥራዎች ጉብኝት

ጥቅምት 19፣ 2018ዓ.ም

በኦሮሚያ ክልል፣ በምስራቅ ሸዋ አካባቢ ያለውን የክረምት ስንዴ እርሻ ማሳጨድና የበጋ ስንዴ ማስጀመር ፕሮግራም ነበር ዛሬ የነበረን። ዘንድሮ በሀገር ደረጃ ክረምት ወደ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ የስንዴ እርሻ ታርሷል። በበጋም እንደዚሁ ይታሰባል፤ ከስምንት ነጥብ አምስት እስከ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ ስንዴ በዚህ ዓመት ይመረታል።

ዓምና ከነበረን ምርት አንጻር በእጅጉ የበለጠ እንደሚሆን ይጠበቃል። ከስንዴ በተጨማሪ ሙዝ አይተናል፣ ፓፓያ አይተናል፣ ዓሳ ምርት አይተናል፤ እነዚህ ሁሉ በካርቦሃይድሬት እና በፕሮቲን እንዲሁም በፍራፍሬ ያሉ ምግቦች ለጤናችን፣ ገንዘብና ሀብት ለመጨመር፣ በምግብ ራስ ለመቻል፣ ሸጠንም ለማትረፍ የሚያግዙ ጉዳዮች ናቸው።

እንግዲህ ይህ ጉዳይ እንዲሳካ በሀሳብና ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን የገጠር ሽግግርን ለማረጋገጥ አንዱ መንገድ ማሽን ማብዛት ነው። በሀገር ደረጃ ከመቶ ሃምሳ ሺህ በላይ ፓምፖች ባለፉት ጥቂት ዓመታት ገብተዋል፣ በአስር ሺህ የሚገመቱ ትራክተሮች ስራ ላይ ውለዋል፣ ወደ አንድ ሺህ የሚጠጋ ኮምባይነር ስራ ላይ ውሏል። አሁንም በበሬ የሚያርሱ አርሶ አደሮች ያሉ ቢሆንም ግን ማሽን የማብዛቱ ጉዳይ እየጨመረ መጥቷል።

ከውጭ ማስገባት ብቻ ደግሞ ሳይሆን ፓምፕና ትራክተር በተወሰነ ደረጃ መገጣጠምም ተጀምሯል። እና ማሽን ስንጠቀም ሰፋፊ ቦታ፤ አሁን በጋ በበሬ ማረስ ይከብዳል ደረቅ ስለሚሆን በትራክተር ሲሆን ይበልጥ ይቀላል። ከታረሰም በኋላ በእጅ መሰብሰብ እና በኮምባይነር አንድ አይደለም፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርት ለመሰብሰብና የሚጠፉ ብክነት ለመቀነስ ያግዛል።

ከፓፓያና ከሙዝ አንጻር ያየነው አዲስ ነገር ከዚህ ቀደም የነበረው ፓፓያ ግንዱ ረጅም፣ ፍሬው ያነሱ ነበሩ ይሄ አዲሱ ዝርያ አጠር ያለ ግን በጣም ምርታማነቱ ከፍተኛ የሆነ ነው። ሙዙም ጣፋጭ ዝርያ ከእስራኤል የመጣ ዝርያ ነው። እነዚህን በምርምር እያሻሻሉ ከአንድ ሄክታር የሚገኘው ምርት እያሳደጉ፣ ተጨማሪ መሬቶች እያስፋፉ፣ በክላስተር የነበረውንም ምርት እያስፋፉ መሄድ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ በእጅጉ ያግዛል። አሁን በገጠር የሚታየው እንቅስቃሴ ሰው በጓሮውም በማሳውም፣ ክረምትም በጋም እንቅስቃሴዎች አሉ እነዚህ በጣም ጥሩ ናቸው። ይህን እንቅስቃሴ ከማሳ ወደ ቤት

መውሰድ ያስፈልጋል። አርሶ አደሮቻችን ብር እያገኙ ነው፣ ብርንም በባንክ ማስቀመጥ ልምምድ እየዳበረ መጥቷል። ነገር ግን ቤታቸው አልተቀየረም፤ ቤታቸው መቀየር አለበት።

ለገጠር የሚገባ የቤት አይነት ዲዛይን ተሰርቷል፤ በገጠር ኮሪደር ውስጥ እንዳያችሁት አንድ ሰው ቤት ባዮጋዝ ያለው፣ ሽንት ቤት ያለው፣ የከብትና የሰው ቤት የተለያየ፣ የሶላር ስርዓት ያለው አዲስ ጅምር አለና ይሄ መስፋፋት አለበት። ይሄን ፓፓያ የሸጠ ሰው ከተማ ብር ማስቀመጥ፣ ከተማ ፎቅ መግዛት ብቻ ሳይሆን እዚህ ያለውን ጎጆ መቀየር፣ የጎረቤት ቤት መቀየር ያስፈልጋል። በአርሶ አደር ህይወት ውስጥ መታየት አለበት፣ በልጆቹ ውስጥ መታየት አለበት።

ቤት መብራት ካለ፣ ቴሌቪዥን ካለ፣ ባዮጋዝ ካለ፣ የእናቶች ድካም የሚቀንስ ከሆነ፣ ማሳ ከታረሰ ብዙ ከተማ መሄድ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። እዚህ ያለው አየሩም ያምራል፣ ማሳውም ያምራል። ችግሩ ምንድነው? ማሳ ላይ የምናየውን ነገር ቤት መውሰድ መቻል ላይ ነውና በተለይ ትላልቅ ምርት የሚያመርቱ አካባቢዎች በፍጥነት አርሶ አደሩ ወደዛ አይነት የኑሮ ዘይቤ እንዲሸጋገር ማገዝ ያስፈልጋል።

አሁን በጣም ጥሩ ዘመን ነው ግልጽ የሆነ ፖሊሲ አለን። በቅርበት አመራር ለመስጠት ሁሉም ይተጋል፣ ይለፋል። የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከአርሶ አደር ጋር ይውላሉ። የወረዳ ዞን አመራሮች አንዱ የሚታዩት በዚህ ውጤት ነው፣ የሚገመገሙት እንደ ዋና ስራቸው ይወሰዳል፤ ይሄን እድል መጠቀም ያስፈልጋል። ከዚህ ቀደም ግብርናን በዚህ መንገድ ብንመራው ኖሮ አሁን የምናየውን ውጤት ማየት እንችል ነበር።

አሁን አምና የነበረው ምርት እና ዘንድሮ የምንጠብቀው አይገናኝም። ከስምንት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ስንዴ በአማካይ በአርባ እንኳን ቢባዛ ምን ያህል ሊገኝ እንደሚችል መገመት ይቻላል፤ በሰላሳ አምስትም ቢባዛ ምን ያህል ሊገኝ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ከዚያ በላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፤ እና ምርታማነት እየዳበረ ሲሄድ ገበያ ይረጋጋል፣ ገቢ ይጨምራል፣ ከውጭ የምናስገባቸው ምግቦች ይቀንሳል፣ ወደ ውጭ የመላክ አቅማችንን ያሳድጋል። ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ነው ያለው።

ኢትዮጵያ ትቀየራለች፣ ትበለጽጋለች፣ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት አፍሪካ ላይ ያላት ቦታ ይስተካከላል ሲባል ዝም ብሎ ፍላጎት አይደለም፤ መሬት ላይ ያሉትን ስራዎች በማየት ጭምር ነው!

በእርሻ ያለውን ስራ እንደምታዩት ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው፤ ብዙ ስራ ይጠበቅብናል ግን ጅምሩ አስደማሚ ነው። እንግዲህ ስለ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር ስንዴ የምናወራው ከሶስት/ አራት/ አምስት ዓመት በፊት የት እንደነበርን ይታወቃል።

በማዕድን ዘርፍ ቢወሰድ በጣም ብዙ ተስፋ ሰጪ ነገሮች አሉ፤ ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ደረጃ ምላሽ እየሰጠ ነው። እነዚህን አስተሳስረን፣ ምርታማነት አሳድገን ሀብት ካገኘን በኋላ አርሶ አደሩ የሚጠቀምበትንም መንገድ ካመቻቸን የኢትዮጵያን ብልጽግና የማየት፣ የኢትዮጵያን ተለውጣ በአዲስ ቁመና የመታየቷ ጉዳይ ተስፋ ሰጪ ይሆናል።
ዋናው ለኢትዮጵያውያን ማስተላለፍ የምንፈልገው መልእክት ሁሉን አቀፍ አካሄድ መከተላችን ነው። ግብርናውን ሳንጥል፣ ኢንዱስትሪውን ሳንጥል፣ ማዕድን ሳንጥል፣ ከተማውን ሳንጥል፣ ቴክኖሎጂውን ሳንጥል ሁሉንም በሚዛን ማስኬዳችን በተጨባጭ የፖሊሲ ትሩፋት እያመጣ ነው ያለው።

ባንድ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ አንደኛውን መተው ያ የተሰጠ ጉዳይ ሊያድግ ይችላል ሌላው ደግሞ ይቀራል፤ የእኛ አካሄድ እሱ አይደለም። ዋና ዋና ዘርፎች ይዘን፤ ሌላ ዘርፍ ደግሞ እየተሰናሰለ እንዲወጣ እያደረግን ስለሆነ በገጠር የሚታየው ለውጥ በከተማ ይታያል፣ በኢንዱስትሪ የሚታየው ለውጥ በግብርና ይታያል፣ በማዕድን የሚታየው ለውጥ በቱሪዝም ይታያል። ሚዲያው የሚያስጮህ ብዙዎች የሚነጋገሩበት ጉዳይ ፓፓያ ሊሆን ይችላል ግን ሙዝም እየተሰራ ነው፤ ሚዲያው የሚያስጮህ ጉዳይ ቱሪዝም ሊሆን ይችላል ግን ኢንዱስትሪም እየተሰራ ነው። እና ተስፋ በብዙ አለ፤ እንበርታ፣ እንስራ፤ ለማይረቡ ወሬዎች ተላልፈን አንሰጥ!

ከአልባሌ ጉዳይ ወጥተን በስራ፣ በትጋት ብቻ ውጤት ለማምጣት እንጣር። ያልሰራ አይብላ ነው የሚባለው እና ካልደከምን የሚመጣ ነገር የለም። በስራ ብቻ የምንቀይረው ሀገራችንን ማንም የሚቀይርልን የለም፤ የምንቀይረው እኛ ነን፣ የምንቀይረው ደግሞ በልፋትና በስራ ነው። ያንን ነገር የጀመርን ይመስለኛል፤ እንግዲህ ይሄን ማስቀጠል ከቻልን ውጤታማ እንደምንሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ባየሁት ነገር ደስ ብሎኛል፤ እንበርታ እንስራ ማለት እወዳለሁ።

አመሰግናለሁ!
ምስራቅ ሸዋ ዞን



የታደሰውን የፋሲል ጊቢ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ጥቅምት 28፣ 2018ዓ.ም

ክቡር አፈጉባኤ አገኘው ተሻገር፣
ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣
ክቡር የክልላችን ፕሬዚዳንት አረጋ ከበደ፣
የከተማችን ከንቲባ ቻሌ፣
እጅግ የተወደዳችሁ የጎንደር ከተማ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ የከተማችን ነዋሪዎች እንዲሁም በዚህ ታላቅ ስራ የተሳተፋችሁ ባለሙያዎች በሙሉ ለዳግም ልደት፣ ለዳግም መታየት፣ ለዳግም ማሸብረቅ የፋሲል ቅጥር ግቢ እንኳን በጋራ አደረሰን ልላችሁ እወዳለሁ።

ንግግሬን ከመጀመሬ በፊት ለመላው የጎንደር ከተማ ህዝብ፣ ለክልሉ ህዝብና ለክልሉ አመራሮች የዚህ ታላቅ ታሪክ አካል ለመሆን ድጋሚ እድል ስለሰጣችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። የመጀመሪያው እድል ክብርት ናት፣ ሁለተኛው እድል ደግሞ ይህ ነው። ፋሲል በእጃችን ስለሆነ የረከሰ ወርቅ ነው። ብንዞር ብንዞር በቀላሉ የማናገኘው፤ እኛ በእጃችን ያለው የማርከስ ክፉ አባዜ ስላለብን የረከሰ ታላቅ ወርቅ ነው።

ይህን የመሰለ ስጦታ የሰጡን አባቶቻችን የእነሱ ስልት ተከተለን ሀገር ብናለማ፣ ሀገር ብንሰራ ዛሬ ኢትዮጵያ ተረጅና ለማኝ አትሆንም። ትልቁ ችግራችን እናንስና ትልቁን ጎትተን በማሳነስ መተካካል እንፈልጋለን። ከእነዚህ ታላላቅ መሪዎች በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያጋጠመ ችግር ያነሱ ትላልቁን ደግሞ ጎትተው የሚያሳንሱ ተበራክተው ነው። ታላላቆችን ማክበር፣ የታላላቆችን ስራ ማድነቅ፣ የታላላቆችን ስራ መመርመር ሲጀመር በዚያ ስራ ላይ አንድ ጡብ አስቀምጥ መባሉ አይቀርም። ታላላቆችን ማሳነስ ሲጀመር ግን የማናድግ፣ ያደገውን የምናሳንስ፣ ተያይዘን የምናጥር ያደርገናል። ትላንታችን ማስታወሻችን፣ መታወሻችን ነው። ሰው ማስታወሻው፣ መታወሻውን አይዘነጋም አያጠፋም። ሁላችን እድሜያችን ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር መለስ ብለን እድገታችንን፣ አስተዳደጋችንን፣ ጎረቤቶቻችንን በማስታወሻ በፎቶ እናስታውሳለን።

ኋላውን ማስታወስ የሁሉ ሰው ተፈጥሯዊ ልማድ ነው። ኋላውን ማስታወስ የቻለ ሰው (ማኅበረሰብ) ዛሬን ለመነሻነት ለመስሪያነት ይገለገላል። ዛሬን መነሻ ያላደረገ የተንደረደረ ነገር ማየት አይቻልም!

እኔ ዛሬ በጎንደር ከተማ የተጀመሩ ስራዎች እንዲሁም በፋሲል ቤተመንግሥት ግቢ ውስጥ ያየሁት ለውጥ ልጆቻችን ከእኛ የተሻለ ተስፋ እንዳላቸው ማሰብ ብቻ ሳይሆን በሚጨበጥ ነገር አይቼዋለሁ። የጎንደር ታዳጊዎች፣ የጎንደር ልጆች ከፊታችሁ ያለው ዘመን ብሩህ ዘመን ስለሆነ አባቶቻችሁ ገንብተዋል፣ እኛ ለማቆየት ሞክረናል፣ አልቃችሁ ጎንደርን ብትሰሩ፣ የበለጠ ያማረ፣ የተዋበ፣ የለማ ሀገር ለመፍጠር ስለሚችል ልቦናችሁን ሰብስብ አድርጋችሁ ጎንደርን በድጋሚ ለመውለድ በጋራ እንድንሰራ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ፋሲል አልታደሰም፣ ፋሲል አልተጠገነም፣ ፋሲል ዳግም ነው የተወለደው። ዛሬ ዳግም ውልደት ነው። ከሰላሳ ዓመት በፊት ጀምሮ አውቀዋለሁ ይሄን ቦታ፣ ተጠገነ የሚለው ስም ያንስበታል፣ ዳግም ተወለደ ቢባል ተገቢ ይሆናል። ነገር ግን ታሪካዊ ጭብጡ እንደሚያመለክተው የጎንደር ከተማ ምስረታ መነሻው ሀሳብ ይሄ ቤተ-መንግሥት ነበር። ይሄ ቤተ-መንግሥት አካባቢውን ፈጠረ፤ ዛሬ ቤተመንግስቱ ዳግም ተወልዷል!

አራዳ ዳግም ካልተወለደ፣ ጃንተከል ዳግም ካልተወለደ፣ ቆባስጥል ዳግም ካልተወለደ ታሪክ አልተደገመም ማለት ነው። ታሪክ ይደገም እንደሆነ አውራው የጅምሩ ስራ ራሱን በወለደው ልክ በቅርብ ርቀት ያሉ አካባቢዎች አራዳም እንደ ቀደመው እንደ መርካቶ ራሱን ዳግም ወልዶ፣ ጃንተከልም ራሱን ወልዶ፣ ቆባስጥልም ራሱን ወልዶ ጎንደር እንደ ፋሲል ራሷን ዳግም ወልዳ ማየት የሁላችን መሻት ምኞትና ስራ መሆን አለበት።
ከአዘዞ ጀምሮ እስከ ጢያሳ የተጀመረው የኮሪደር ስራ ጎንደር ዳግም ለመወለድ እያማጠች እንደሆነ ያሳያል። ግን ይህ ምጥ ሙያተኛ ይፈልጋል። ይህ ምጥ ሐኪም ይፈልጋል። አሁን ባለበት ከቀረ ይጨነግፋል አይወለድም። ደግፈን አግዘን እንዲወለድ ካደረግን ግን ልክ በፋሲል ቅጥር ግቢ እንደሚታየው ያለ ውበት በመላ ጎንደር ከተማ ውስጥ ሊታይ ይችላል።

ለዚህም እናንተ ጎንደሬዎች በዘመናት መካከል ምርጥ ከንቲባ አግኝተናል። ይሄንን ከንቲባ ደግፈን፣ ይሄንን ከንቲባ አግዘን ለጎንደር ዳግም መወለድ ግራና ቀኝ ሳንመለከት ይሄንን እድል እንጠቀምበት። እድል ያልፋል። እድል መጠቀም የብልሆች፣ የአዋቂዎች፣ የአስተዋዮች፣ የጥበበኞች ልምምድ ነው።

አሁን እንልማ እንቀየር ሲባል በየዋህነት፣ ባለማስተዋል፣ ተበታትነን ሀገር እንዳይሰራ ከምናደርግ ጎንደርን ዳግም በመስራት ጉዳይ ሁላችንም የጋራ አቋም ይዘን በሌላው በሌላው ጉዳይ ችግር የለም እንለያያለን። በስራው ጎንደርን ዳግም አስውቦ ለመውለድ ግን የሁላችን የጋራ አቋም መሆን እንዳለበት በጽኑ አምናለሁ።

ጎንደር በቅርቡ ከውጭ የመጡ ሰዎች ጎብኝተዋት ነበር። ተደንቀዋል ተደምመዋል። ከዚያም ወደ ጎርጎራ ሄደው ጎርጎራንም አይተው በውሀ ላይ ወደ ባህርዳር ሄደው ባህርዳርንም አይተው ድንቅ ሀገር አላችሁ፣ ብትበረቱ ብትሰሩ የትም ቦታ ተሄዶ የማይታይ ነገር አለ ብለው። ከዚያ መካከል በአድናቆት የነገሩኝ ከጎንደርና ባህርዳር ከጎርጎራ ባሻገር ከዚህ እስከ ጎርጎራ ያለው መንገድ በራሱ ቢጠገን አሉ።

ተራራውና ውበቱ አይጠገብም አሉ። ራሱ መንገድ ላይ ያለው ያለማው ተራራ ትልቅ ውበት ትልቅ ጸጋ አለው አሉ። ነገር ግን ከጎንደር ጎርጎራ ለመሄድ ጎንደሬዎች በወታደር ተጠብቀው እንዴት ልማት ሊሰራ ይችላል? ባእድ ሳይሆን ባላገሮች ባለቤቶች ከአንድ ሰፈር አንድ ሰፈር ተንቀሳቅሰው የሀገራቸውን ልማት ማየት፣ ማገዝ እንዲችሉ ሰላም ያስፈልጋል። እዚያ አካባቢ የወጡ ወንድሞቻችን ጊዜ ባያባክኑ። ጊዜ አዋቂነት ያስፈልጋል ተመልሶ በትብብር በአንድነት ሀገር ማልማት መስራት ያስፈልጋል።

ዛሬ ጎንደርን፣ ባህርዳርን ወይንም አማራ ክልልን ከአማሮች በስተቀር ማንም አይሰራውም። እኛ እንደው ሲፈቀድልን እንደ እድል ወስደን ከማገዝ ባሻገር በእለት ተእለት ጉዳይና ስራዎች ውስጥ እጃችንን አናስገባም። ይህ እድል ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። አሁን ከምናበላሽበት በትብብር መንፈስ ብንሰራ ነገአችን የልጆቻችን ነገ ያማረ ስለሚሆን በትብብር መንፈስ ዳግም ጎንደር ባህርዳር አማራ ኢትዮጵያ እንዲወለዱ በጋራ እንድንቆም አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም ክብርት ባለቤቴ እንኳን ደስ አለሽ። የብዙ ጊዜ ምኞትሽ፣ መሻትሽ የነበረው ነገር ዛሬ ሆኖ እኔም አንቺም ስላየን የጎንደር ህዝብም ይህን ታላቅ እድል የዚህ ደስታ ተካፋይ እንድንሆን ስለፈቀደልን ከፍ ያለ ምስጋና እያቀረብኩ ጎንደሬዎች ሽማግሌ አላችሁ፣ የሃይማኖት አባት አላችሁ፣ ብርቱ ብርቱ ሰዎች አላችሁ ሰብሰብ ብላችሁ ጎንደርን ዳግም ውለዱት። ጎንደር አሁን ካልተሰራ ይረፍዳል።

ከረፈደ የዘገየ ደግሞ ቀደሙት ለመተካከል ጊዜም ጉልበትም ይጠይቃል። እንዳይረፍድብን ተባብረን እንስራ። በእኛ በኩል ዛሬ ያየነውን ስራ እንደ ታላቅ ጅምር እንደ ድንቅ ስራ አይተናል፣ በዚህ ስራም እንድትበረታቱ እንፈልጋለን። ቻሌ እንዳትተኛ የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች እንዳትተኙ ዳግም ጎንደር ተወልዳ አሸብርቃ ጥንታዊነቷን ታሪኳን ሳትለቅ ለዓለም አሸብራቂ ከተማ እስከምትሆን ድረስ በትጋት እንድንሰራ በድጋሚ አደራ እላችኋለሁ።

ጉልበት ይሸሻል፣ ጊዜ ይሸሻል፣ ስልጣን ይሸሻል ሁሉ አላፊ ነው። የማያልፈው እንደዚህ ያለው ታላቅ ስራ ነውና ታላቅ ስራ በጋራ እንድንሰራ አደራ እላችኋለሁ።

እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን፤ እጅግ ኡድርጌ አመሰግናለሁ!
የፋሲል ጊቢ፣ አማራ ክልል



የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ኢንስቲትዩት ጉብኝት

—ህዳር 8፣ 2018ዓ.ም

እጅግ አስደማሚ ስራ ነው! የተቋም ግንባታ ራዕይ እና ዲሲፕሊን ሲገናኙ ምን አይነት ነገር መፍጠር እንደሚቻል ጥሩ ማሳያ ይመስለኛል የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት። በመጀመሪያ ከቦታው ብንነሳ ይህ ቦታ ለብዙ ዓመታት የኢቲቪ ዋና መስሪያ ቤት የነበረ ቦታ ነው። መቼም የኢቲቪ ሰራተኞች እና ተቋሙን የመምራት እድል የነበራቸው ሰዎች ዛሬ መጥተው ይህንን ቦታ ቢያዩት 'እኛ የነበርንበት ህንጻ ነው' ብለው ሊያስቡ የሚችሉ አይመስለኝም።

እኔም ኢቲቪን በደንብ አውቀዋለሁ ቦርድ አባል ሆኜ ገብቼአለሁ ይህን አይነት ቁመና መልክ አልነበረውም። ምን ማለት ነው? በደንብ ግልጥ አድርገው የማየት፣ የመስራት፣ አካባቢን የመቀየር፣ ተቋምን የመገንባት ልምዳችን አናሳ ነበረ ማለት ነው። ዛሬ ሰው ሰራሽ አስተውሎት በስራ ቦታ በኢርጎኖሚክሱ ብቻ ቢወሰድ ለኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ ዐይን ገላጭ፣ አዲስ ምዕራፍ፣ አዲስ ዕይታ የሚገልጥ፣ የሚያሳይ በጣም ለስራ ምቹ የሆነ ወጣቶች ለረጅም ሰዓት ተቀምጠው ሊሰሩበት የሚችሉበት ተቋም እና ስፍራ ሆኖ ተሰርቷል። ይህ በጣም ሳቢ ነው በራሱ። ከዚያም ባሻገር ግን ሰው ሰራሽ አስተውሎት አምስት ዓመት ገደማ ነው በተቋም መልክ ከጀመርነው፤ የዛሬ አምስት ዓመት ሰው ሰራሽ አስተውሎት የሚለውን ሀሳብ ስናነሳ ተቋም ይፈጠር ሲባል በእኛ ውስጥ በቀላሉ ተቀባይነት ያለው ሀሳብና ብዙዎች በተለያየ የገዙት ጉዳይ አልነበረም።

ግን ሰው ሰራሽ አስተውሎት የሰው ልጅ የሚያስብበትን መንገድ፣ የመሆን እድልን የሚያይበትን መንገድ እየቀረጸ መጥቷል። ብንፈልግም ባንፈልግም በዚህ የውድድር መንገድ ውስጥ እራሳችንን ማስገባት ካልቻልን ደረጃው የትም ቦታ ይሁን እንደ ሀገር እንደ ከዚህ ቀደሙ ትላልቅ አብዮት ወደ ኋላ እንቀራለን።

የግብርና አብዮት አንድ/ ሁለት/ ሶስት እያለ መጥቷል እኛ እዚያ ውስጥ አልነበርንም፤ የቴክኖሎጂ አብዮት ነበረ፣ የኢንዱስትሪ አብዮት ነበረ። በእነዚያ ሁሉ ውስጥ ኢትዮጵያ በሬና ሰውን ማላቀቅ ስላትችል የኖረችበት ዋና ምክንያት አዲስ ዕውቀት፣ አዲስ ልምምድ፣ አዲስ ፈጠራ ሲፈጠር ያንን ነገር ለማወቅ እና ለመከተል የነበረው ጉጉት፣ ዝግጁነት እና አስተሳሰብ አናሳ ስለነበረ ጥሩ ተከታይ ለመሆንም አልቻልንም። ለመተካካል ሳይሆን ጥሩ ተከታይ ለመሆንም በእጅጉ ይቀረን ነበር፤ አሁን ተቀይሯል ሁኔታው።

ለምሳሌ በከተማችን ውስጥ የኢሌትሪክ መኪናዎች ይስፋፉ እና የኤሌትሪክ መኪና ቻርጀር በየቦታው ይሁን ሲባል ብዙ ሰዎች በዋዛ ፈዛዛ አቅልለው ሊያዩት ይችላሉ፣ ግን ብዙ የአውሮፓ ሀገር ሰዎች በየቦታው የኤሌትሪክ መኪና ቻርጀር ሲያዩ አፍሪካ ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር ይቻላል እንዴ? ብለው ይጠይቃሉ። ሰው ሠራስ አስተውሎትም እንደዚሁ ነው። በአፍሪካ ደረጃ ሊወዳደር የሚያስችል አሰራርን የሚከተል ተቋም ነው። በጣም በርካታ ምርቶች አውጥተዋል፤ በጤና ዘርፍ የጡት ካንሰር ልየታ ላይ በጣም ትልቅ ውጤት አምጥተዋል። ይህ በእነሱ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ጆርናል ላይ ይፋ ያደረጉት፣ በብዙ የሰው ሰራሽ አስተውሎት አዋቂዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ፣ የአእምሮ ንብረት ፈቃድ ያገኙበት ስራ ነው። በህክምና በጣም በርካታ ስራዎችን አውጥተዋል።

በግብርና ውስጥ የቡና በሽታ፣ የሌሎች አዝርእቶች በሽታ የመለየት መንገድ እንደዚሁ ሰርተዋል፤ ለዚህም የአእምሮ ንብረት ፈቃድ አላቸው። ከህክምና ውጭ ግብርና ላይ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ የልየታ መሳሪያዎች በምርት ደረጃ ገንብተዋል። በአገልግሎት ከወሰድክ የህዝባችንን በከፍተኛ ደረጃ ከሚያማርረው፣ ቅሬታ ከሚያቀርብበት ጉዳይ አገልግሎት ነው።

አገልግሎት ውስጥ ደግሞ የጊዜ ብቻ ሳይሆን የገንዘብ አሻጥሮችም ስላሉበት “መሶብ” የሚባለውን ከመቶ በላይ ቨርቹዋል አገልግሎቶች የሚሰጠውን ስርዓት የሰራው ሰው ሰራሽ አስተውሎት ነው። ብዙ ሚሊዮን ዶላር አትርፎልናል፣ ሲስተሙ በእኛ ልጆች የተገነባ ነው። ከአገልግሎት ውጭ ወደ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ቢገባ የገንዘብ ሚኒስቴር ከዚህ በፊት በብዙ ሚሊዮን ዶላር የገዛውን አይ ኤፍ ኤም አይ ኤስ እየተካ ነው። በጉምሩክ ባለስልጣንም ከወደብ ጀምሮ ያሉ ሎጂስቲክሶችን መከታተል የሚያስችል ሲስተሞች ሰርተዋል፤ በብዙ ስራዎች ላይ እየተሳተፉ ነው።

ከዚያ በላይ ግን የእኛ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ተቋም መሪ ቃል “ሰው ሰራሽ አስተውሎት ለሁሉም” ነው። ሰው ሰራሽ አስተውሎትን ለሁሉም ሰዎች ማገልገል፣ ማገዝ፣ መጠቀም እንችላለን ብሎ መስራት ነው። አንዱ ከዚህ አንጻር የሚታየው ክላውድ ኮምፒዩቲንግ ነው። ክላውድ ኮምፒዩቲንግ እና ቢግ ዳታ ላይ እየሰሩ ያሉት ስራ በጣም ከፍተኛ የሆነ አቅም ያላቸው የዳታ ማዕከላት ገንብተዋል፣ ብዙ መረጃ እያጠራቀሙ ነው።

መረጃን ማይን ማድረግ፣ ማቀናበር፣ መተንተን አቅም እዚሁ ወጣቶቹ ናቸው እየሰሩ ያሉት። በዚያም መረጃን እንደ ሉዓላዊ ሀብት የመውሰድ ብቻ ሳይሆን የመጠቀም አቅማችን ላይም ከፍተኛ ውጤት እያመጣ ያለ ነው። ለምሳሌ ከመረጃ አጠቃቀም ጋር

ተያይዞ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሶማሊኛ፣ ትግርኛ፣ አፋርኛ ቋንቋዎች እርስ በእርስ አፋርኛ ተናጋሪ ከሶማሊኛ ተናጋሪ ጋር ሰው ሰራሽ አስተውሎትን ተጠቅሞ ሶስተኛ ሰው ሳያስገባ መግባባት የሚችልበትን መንገድ፣ በጽሁፍ የገባን መልእክት ወደ ድምጽ የመቀየር፣ በድምጽ የተሰማውን ወደ መልእክት የመቀየር የመሳሰሉትን አይነት አገልግሎት ለመስጠት በሺህ ሰአቶች የሚቆጠሩ የድምጽ መረጃ አጠራቅመው እየሰሩ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት በአምስት ዓመት ውስጥ እዚህ ደረሰ ብሎ ማሰብ በጣም በጣም ይከብዳል፤ በአፍሪካ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ ተቋም ነው። በሮቦቲክስ ላይ የ3D ማሽን፣ ሲኤንሲን በመጠቀም የሮቦት ክፍሎች ይሰራሉ፣ የሶፍትዌር ብቻ ሳይሆን የሀርድዌር ክፍሎች መስራት ጀምረዋል፣ ፒሲቢ ያላቸው ድሮኖች ማምረት ብቻ ሳይሆን የማነጋገር አቅም እየፈጠሩ ነው ያሉት። እና በጥቅሉ ዛሬ ያየሁት ነገር ሰው የጠራ ራዕይ ካለው፣ በከፍተኛ ዲሲፕሊን ሊሰራ ከሆነ አንድን ነገር ባየው ልክ ማሳካት እንደሚችል ይህ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ብቃት ያላት ሀገር መሆኗ ይታያል።

ያሉን ህንጻዎች፣ ያሉን ስፍራዎች ይሆነኛል ብለን አስበን ብንሰራቸው በራሳቸው ምንም የማያሳፍሩ እጅግ ያማሩ ስፍራዎች መሆን እንደሚችሉ ይታያል። አዲስ አበባ ትላንት የቆሻሻ የሽታ ምልክት ነበረች፣ ብዙዎች ከአዲስ አበባ እንውጣ ብለው ከተማ እንገንባ ሲሉ አይሆንም ከተማችንን መቀየር ይቻላል ተብሎ የተጀመረው ስራ ሙሉ በሙሉ ያለቀ ባይሆንም አሁን በሚታየው ደረጃ የአዲስ አበባን ውበት በከፍተኛ ደረጃ እየገለጸ ይገኛል። በተቋም ግንባታም እንደዚህ ተቋሞቻችን የግድ አዲስ ህንጻ ሳይሆን ያሉን ህንጻዎች እንዲያገለግሉ አድርገን፣ ከፍ አድርገን፣ ቴክኖሎጂ ተጠቅመን ብንሰራቸው እንደዚህ ያለ መስሪያ ቦታ መፍጠር እንደሚችል፣ ይህንን ደግሞ ኢትዮጵያውያን መስራት እንደሚችሉ ታይቷል።

ሁለት በጣም ደስ ያለኝ እና በርካታ ወጣቶች ኢትዮጵያውያን ቢያዩት ብዬ በተለየ መንገድ ያየሁት ሁለት ጉዳይ አለ። አንደኛው የኢመርሲቭ ተሞክሮ ነው። ይህ ኢመርሲቭ ቴክኖሎጂ በብዙ ሀገር መስፋፋቱ የሚታይ ባይሆንም በዳበሩ ሀገራት ግን አለ። በሌሎች ሀገራት ስናይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ የኢመርሲቭ ተሞክሮ ይኖራታል የሚል ግምት አልነበረኝም። ይህ ለወጣቶች በጣም በጣም ወሳኝ ነው። ዝም ብሎ ፊልም ማየት፣ አንድን የተቀረጸ ፊልም ማየት አለ እዚያ ውስጥ ገብቶ መመልከትስ ይንቀሳቀሳል እንዳየኸው ባሕር ሲገባ ባህር ያስገባህል፣ ውሀ ይረጭህል፣ ወደ ሰማይ ሲወጣ እውነት የሆነ ስሜት ነው ያለው።

ይህንን ነገር እያዩ የሚያድጉ ልጆች ብዙ ነገር ለመፍጠር እድል ይሰጣቸዋል፣ በሁሉም አቅጣጫ የማየት፣ በሁሉም የስሜት ህዋሳት ስሜቱን ማየት ማለት ነው። በብዙ አቅጣጫ ሰው የሚያየው ነገር አካል ሆኖ በውስጥ ገብቶ እንዲሰማው፣ እንዲያይ፣ እንዲያስተውል የሚያደርግ የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ ታዳጊዎች በሀገራቸው እንደዚህ ያለውን ነገር ለማየት እድል ማግኘታቸው በጣም በጣም ደስ ይለኛል። እኔ በሌላው ዓለም ባየሁበት ጊዜ በአጭር ጊዜ እናገኘዋለን ብዬ አላሰብኩም ነበር።

ይህ ደግሞ ብናባዛው፤ አሁን መጥቷል ብናስፋፋው በጣም በጣም ጠቃሚ ይሆናል። ልጆች ይገባቸዋል እኔም እያልኩ እንዳለሁ፣ በቪዲዮ ያዩትን ነገር በአካል መሞከር ሲችሉ ማለት ነው። ሁለተኛው በጣም አስደማሚ የሆነ ነገር ግን የጀማሪ ስራ ፈጠራ የሚያሰሩበት ቦታ ነው። እዚህ ጋር የደነቀኝ ነገር በቅርቡ ወደ ፈረንሳይ ሀገር ጉብኝት ሄደን ነበር። በዚያ ጉብኝት ወቅት አንዱ የምናየው ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ስለሆነ የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ወርቁ ከእኛ ጋር ነበሩ። እና አንዱ ያየነው በግል ተቋም የሚሰራ የጀማሪ ስራ ፈጠራ ማዕከል ነው። ሰዎች ሀሳባቸውን ብቻ ይዘው ወደዚያ ማዕከል መጥተው ሀሳባቸውን ካወዳደሩ በኋላ እዚያ ቦታ ላይ ልክ እንደ ሰራተኛ ቢሮ አላቸው፣ የስብሰባ አዳራሽ አላቸው፣ ኢንተርኔት አላቸው፣ ኮምፒውተር አላቸው፣ ሁለት ወር ሶስት ወር የተሻለ ልምድና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች እየታገዙ ያንን ያልጠራ ሃሳብ ወይንም በደንብ ያልተቀረጸ ሀሳብ ወደ ተሟላ ፕሮጀክት ከቀየሩ በኋላ ያ ፕሮጀክት ደግሞ በደንብ እንዲወለድ ከግል ዘርፉ ጋር እዚያው እያሉ ያገናኛቸዋል።

አንድ ሰው ሀሳብ ብቻ ይዞ መጥቶ ተሰንዶ፣ ቅድመ-ናሙና ሰርቶ፣ ተሞክሮ ከውጭ ኢንዱስትሪ ጋር ተገናኝቶ ይወጣል፤ እንዲገናኝ ይደረጋል። ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት ይሁነኝ ብሎ ትኩረት አድርጎ ኮምፒውተር ቦታ አሟልቶ ሀሳብ ያላቸው ወጣቶች የቢሮክራሲ የቸገራቸው፣ ኢንተርኔት የማታገኙ፣ አጋዥ ደጋፊ ያጣችሁ ወጣቶች ለሶስት ወር ለአራት ወር ኑና እኔ ቢሮ አበጅላችኋለሁ፣ ኢንተርኔት በነጻ ታገኛላችሁ፣ ደግፌ ሀሳብ አውጥቼ ከግል ዘርፉ ጋር አገናኝቼ እንዲወለድ አደርጋለሁ የሚል በጣም ቅን የሆነ፣ በጣም ደግ የሆነ እሳቤ ኢትዮጵያ ውስጥ ማየት ቀላል ነገር አይደለም።

ወጣቶች እንዲህ ያለውን ሀሳባቸውን ይዘው መጥተው፣ ታግዘው፣ ከኢንዱስትሪ ጋር አገናኝተን ሀሳቦቻቸው ሳይሞቱ፣ ሳይጨነግፉ ተወልደው ወደ ቢዝነስ እንዲያድጉ የሚያስችል ከባቢ በሰው ሰራሽ አስተውሎት መፈጠሩ በጣም በጣም አስገራሚ ነው። ከሁለት መቶ ሰው በላይ አይታችኋል ወጣቶች ተሰብስበዋል፣ እነዚህ ልጆች ከእነዚህ

ከሁለት መቶው ውስጥ አምሳው ሰው ተሳክቶለት ፕሮጀክቱ ቢወጣ፣ ከአምሳው ሰው አስር ሰው የራሱን ኩባንያ እየፈጠረ ከሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ወደ ዩኒኮርን ቢያድግ ቢሊየነሮችን እንፈጥራለን ማለት ነው።

መንግሥት ይሁነኝ ብሎ አስቦ ትውልድ ላይ መስራት እንዳለበት የሚያመለክት በሚጨበጥ ነገር ነው። በመንግሥት እና በግለሰቦች፣ በመንግሥት እና ሀሳብ ባላቸው ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት በትምህርት ቤት ውስጥ መታጠር ብቻ መሆን የለበትም። ትምህርት ቤት የራሱ የሚሰጠው መሰረታዊ ዕውቀት አለ። ከዚያ ባሻገር ግን የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች እየታገዙ ሀሳቦቻቸው እንዲወለዱ ማድረግ ከተቻለ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በርካታ ሀሳቦች፣ በጣም በርካታ ስራዎች፣ ኩባንያዎች ይፈጠራሉ ማለት ነው።

እንግዲህ አንድ መታረም ያለበት እሳቤ አለ፣ አፍሪካ ውስጥ ወይንም ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ነገር ጀምሮ መጨረስ አይቻልም፣ ከፍ ያለውን ጉዳይ እኛ መግባት አይገባንም፣ ትላልቁን ነገር ሌሎች ይስሩት እኛ እንተወው የሚባል አመለካከት አለ። ያ አመለካከት አትችሉም፣ አትሞክሩት፣ ለእናንተ አይገባችሁም የሚል የበታችነት ከሚመነጭ ሀሳብ የመነጨው ሀሳብ ትክክለኛ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ አብዛኛው ወጣት ነው። እንደሚችል ከነገርነው፣ አመቺ ሁኔታ ከፈጠርን፣ አመቺ ፖሊሲ ከነደፍን፣ የሚሞክርበትን አውድ ከፈጠርንለት አንድ ሺህ ሞክረን አስር ቢሳካ ሊሆን ይችላል፤ አስር ቢሳካ ደግሞ በጣም ብዙ ነው። ያ ሺህ በሺህ የሚቆጠር መፍጠር ስለሚቻል እንደዚህ ያለውን በጣም ከልብ ቅንነት ከሀገራዊ ህልም እና ርእይ ጋር ተገናኝተው የሚታዩ ጉዳዮችን በዚህ ተቋም ማየታችን ለትውልድ በጣም በጣም ተስፋ ሰጪ ነው።

መጥተው፣ ተምረው፣ ሞክረው፣ አይተው የወጡ ልጆች ተራ ሰዎች አይደሉም። በእርግጠኝነት በእርግጠኝነት በቻይናም፣ በመካከለኛው ምስራቅም፣ በአውሮፓም በርካታ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ተቋማትን የማየት እድል አግኝቻለሁ። የእኛ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ያለበት ደረጃ የሚናቅ አይደለም። በጥራትም አይናቅም፣ በይዘቱም አይናቅ፤ ያከማቿቸው ቁሶች፣ ሀብቶች፣ እውቀቶች፣ ሶፍትዌሮች እና የዳታ ማከማቻ ቋቶች በሙሉ የሚናቁ አይደሉም።

ይህንን በደንብ ጠብቀን ሳይበላሽ እንዲያድግ ማድረግ ከተቻለ ለኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ ፋይዳ ያለው፣ ትውልድ ነገ የሚኮራበት ስራ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ያው እንደምታውቁት በካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሀብት የጀመርናቸው ቴክኖሎጂ

ቀመስ፣ ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም የሚያስተካክሉ ተቋማት አሉ። የሰው ሰራሽ አስተውሎት ፍጥነት እና እድገት ግን ከእነዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ በጣም የሚያረካ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ ለሁላችንም ተስፋ ሰጪ ነው።

ይህ ስራ እንዲሳካ የዚህ ተቋም አመራሮች፣ ሰራተኞች፣ ደጋፊ አካላት መቼም ጠንካራ ስራ እንደሰሩ ራሱ ፍሬው ይናገራል። ይህንን ቦታ ከተሰጣቸው ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደዚህ ያለውን ድንቅ ስራ የሰሩ ሁሉ እጆች ይባረኩ። የደገፉ ግለሰቦች፣ ኩባንያዎች፣ ሀገራትም ካሉ ለእነሱ ሁሉ ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው። እና እንበርታ፣ እንስራ። በስራ፣ በድካም ብቻ ነው የተሟላ ውጤት ልናመጣ የምንችለው።

ራዕያችን ይሳካ ዘንድ የጠራ ሀሳብ፣ ርዕይ፣ ርዕዩን የምናሳካበት ዲሲፕሊን ያስፈልጋል። ያንን ካደረግን እንደዚህ ያለውን ተቋም ማበራከት እና ለኢትዮጵያውያን ለአይናችን እርካታ ሰጪ ስፍራዎች፣ ለአዕምሮአቸውም ብዙ ነገር የሚማሩበት ነገር መፍጠር ይቻላል። ዛሬ በነበረን ቆይታ ብዙ ነገር ተምረናል እንግዲህ ተጨማሪ እውቀቶች ለማግኘት እድል እንደምናገኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፣ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ!
የሰው ሰራሽ አስተውሎት ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ

በመደመር መንግሥት እይታ፣ የዘርፎች እመርታ - ለብልጽግና ፓርቲ መሪዎች የተሰጠ ስልጠና

ሀዳር 20፣ 2018 **ዓ.ም**

እንዴት ከረማችሁ፤ ያለፉት 10 ቀናት ቆይታችሁ እጅግ ስኬታማ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለው። እንደዚህ ያሉ ቆይታዎች እንደ እያንዳንዱ ግለሰብ ምዘና ውጤታቸው የሚለያይ ቢሆንም በጥቅል ሲወሰድ የተሳካ ነበር ብሎ ማሰብ የሚያስችሉ፣ የሚሉ ግብረ መልሶች አሉ። ይህንን መንግሥት የሚመሩ አመራሮች የተቀራረበ እሳቤ ለመያዝ የሚያስችል ቆይታ ነበር ብሎ በጥቅሉ መውሰድ ይቻላል። የዛሬው የማጠቃለያ ገለጻችን የሚያጠነጥነው የመደመር መንግሥት እንዴት ያለ እሳቤ እንዳለው፣ እንዴት ስራ እንደሚከውን፣ ምን ሊያሳካ ፣ ምን እንደሚሸከም በግርድፉ ለማሳየት እሞክራለው።

የመደመር መንግሥት ሲባል መያዝ ያለባቸው ፍሬ ሃሳቦች አንደኛው መፍጠር ነው፤ ፈጠራ ነው፣ ሁለተኛው መፍጠን ነው፣ ሶስተኛው ማብዛት ነው፣ አራተኛው ማጥራት ነው። ምን ማለት ነው ይህ ጉዳይ ያላችሁ እንደሆነ ፥ ብዙ ያልፈጠረ ጥራት ማረጋገጥ አይችልም፣ ከብዙ ፈጠራ ውስጥ ነው ጥራት ያላቸው ጉዳዮች የሚወጡት። ብዙ ለመፍጠር ደግሞ ፍጥነት ያስፈልጋል፣ ያልፈጠነ ሰው ባለው ውቅት ባለው ጊዜ በርከት ያሉ ጉዳዮች መፍጠር አይችልም፣ ብዙ ስንፈጥር ብዙ ስንሮጥ ከነዚያ መካከል ጥቂቶቹ ረዘም ላለ ጊዜ ለመጓዝ ጥራትን ከዚያ ውስጥ መዞ ለማውጣት ያግዛል ማለት ነው።

ብዛት ዕድል ነው፣ ጥራት ግን ውጤት ነው!

በብዛት ውስጥ በብዙ ብዙ ፈጠራ ውስጥ አዳዲስ ነገር ለመፍጠር የምንማርበት ብቻ ሳይሆን የሚዘልቅ ውጤት ለማቆየት እንጠቀምበታለን። ለምሳሌ ኮሪደር ስንጀምር እና ዛሬ አንድ አይደለም የጥራታችን መለኪያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ መጥቷል ማለት ነው እና ብዙ በመፍጠር በመፍጠን ነው ጥራትን የምናረጋግጠው። የመደመር መንግሥት በእነዚህ እሳቤዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ይሆናል።

የዛሬው ገለጻችን ግን ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች አሉት የመጀመሪያው ቁልፍ እሳቤ ስልጡንነት፣ ዘመናዊነት እና ኋላቀርነት እንዴት እንደተፈጠሩ፣ ታሪካዊ ዳራዎቻቸውን አይተን ከእነዚያ ውስጥ የምንማራቸውን ትምህርቶች ነቅሰን እናወጣለን። ሰው ዘመናዊነት እና ስልጣኔ ከዘመን መነጠል እና ኋላ መቅረት ያሉትን ጉዳቶች በእኛ በሀገራችን ያስከተለውን

ጣጣ በትንሹ በስሱ ከዓለም ሁኔታ ጋር አያይዘን እናያለን። ስልጣኔን ዘመናዊነትን ታሪክን በትክክል ካልተገነዘብን ዛሬን ለመስራት እና ነገ የምናስበውን ለመከወን ያስቸግራል። ሁለተኛው ቁልፍ ጉዳይ የምናየው መደመር መር ስልጡን ሀገር እንዴት መፍጠር ይቻላል? ስልጡን ሀገር ለመፍጠር መነሻ አድርገን የምንወስደው እሳቤ አለ፣ መሻገሪያ የምናደርገው ድልድይ አለ፣ ተሻጋሪ ብለን የበየነው ኃይል አለ፣ አሻጋሪ ያልነው ነው እና የለየነው ኃይል አለ።

እንዴት ነው መነሻ፣ መሻገርያ፣ ተሻጋሪ እና አሻጋሪውን ለይተን በሚና ከፍለን ስራ ሰጥተን ውጤት የምናመጣው። ይህ ደግሞ እንዳይከወን ሃሳብ አልቦነት ምን ያህል ጣጣ እንዳለው በስሱ ለማየት እንሞክራለን። ስለዚህ በሁለት ከፍለን ውሏችንን ካሰብን በቂ ይሆናል አንደኛው ስልጡንነት ዘመናዊነትና ኋላ ቀርነት፣ ሁለተኛው መደመር መር ስልጡን ሀገር እንዴት እዚህ ያለን ሰዎች ልንፈጥር፣ ልንመራ፣ ልናወርስ እንደምንችል የምንመክርበት ይሆናል።

የመጀመሪያው ቁልፍ ጉዳይ ሰው ዘመናዊነትና ስልጣኔ ነው፣ እዚ በስዕሉ እንደ ምታዩት ወደ ኋላ አጮልቀን ነው የምናየው። ወደ ኋላ አጮልቀን በምናይበት ሰዓት የሰው ልጅ ለመሰልጠን ያደረጋቸውን ተጋድሎዎች ስልጣኔ ብሎ የበየነውን የኑሮ ዘዬ ማቆየት የተቻለበትን ጊዜ ሲወድቅ ለምን ደግሞ እንደፈረሰ የምናይበት ይሆናል። የስልጣኔ ጉዞ ማጥናትና መረዳት ለምን ያስፈልጋል? አንድ የመለወጥ፣ የማደግ፣ የመሻሻል ትልም ያለው ሃገር የስልጣኔ ጉዞን ወደኋላ መለስ ብሎ ማየት የሚያስፈልገው ዋናው ምክንያት ሳሙኤል ሃንቲግተን እንደሚለው የሰው ልጅ ታሪክ የስልጣኔ ታሪክ ነው።

ታሪክ የሚባለው ጉዳይ ራሱ የሱልጡኖችና ስልጣኔያቸውን በበላይነት መናገር፣ ማስጨበጥ የቻሉ ግለሰቦች ስብስቦች እውነት ነው እንጂ የብዙ ተሸናፊዎች የብዙ አሸንፈው መናገር ያልቻሉ ኃይሎች የተረሱ በርከት ያሉ ጉዳዮች ይኖራሉ። የሰው ልጅ ታሪክ የስልጣኔ ታሪክ ከሆነ መፈተሽ የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት ማጎበረሰብ፣ ግለሰብ፣ ሀገር፣ አህጉር ዕውር ነቁጥ አላቸው።

ወደፊት መሸምጠጥ የሚፈልግ ማንኛውም ኃይል፣ በትልቅ መስታወት ወደፊት ማየት ብቻውን በቂ አይደለም፣ ዕውር ነቁጥን የሚያረጋግጥበትን የፊት መስታወት፣ መስታወቱን የማይሸፍንበትንም መለስ ቀለስ እያለ ማየት በወሳኝ ጊዜ ያስፈልጋል። ያን ማድረግ ካልቻለ ወደፊት መጓዝ መፍጠንም አይቻልም፤ ብንፈጥንም ከምናስበው ቦታ መድረስ አስቸጋሪ ይሆናል።

ወደፊት ለመሸምጠጥ ወደ ኋላ አልፎ አልፎ ማየት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ዛሬን በትክክል ለመረዳት ምንድነው አሁን ያለንበት ሁኔታ? የቆምንበት ባህል፣ እምነት፣ እሴት፣ ተቋማት እንዴት ተፈጠሩ? በምንስ መንገድ አድገው ዛሬ ላይ ደረሱ? የሚለውን ጉዳይ በቅጡ መመርመርና ማወቅ ይጠይቃል። ነገን ለመተንበይ የዛሬ ውሳኔዎች፣ ድርጊቶች፣ ትልሞቻችን የሚፈቱበት መንገድ ምን አይነት ነገ ሊፈጠር እንደሚችል ሙሉ በሙሉ እንኳ ባይሆን ከሞላ ጎደል ግንዛቤ እንድንይዝ ያስችላል።

አብርሃም ሊንከን ስለወደፊት ጊዜ ሲጠይቅ “ስለነገ የተሟላ ነገር ለመናገር የምትችለው በምትሰራው ስራ ነው” ይላል፣ ዛሬ በምትሰራው ስራ ነው በመፍጠር ብቻ ነው! የበቃ መሠረተ-ልማት ዛሬ የሰራ ሰው ከዛ የተሻለ ዘመን እንደሚመጣ ማሰብ ይችላል። ዛሬ የተኛ ሰው ነገ የከፋ ግዜ ለልጆቹ እንደሚያወርስ ካለብዙ አስረጅ ሊገነዘብ ይችላል። ዛሬን ማወቅ ነገን ለመስራት ብቻ ሳይሆን ነገን በቅጡ ለመተንበይ የሚያግዝ ጉዳይ ነው ማለት ነው።

ስልጣኔ ምንድነው? ስልጣኔ የባህላዊ ልማታዊ ደረጃ ከፍታ ሲረጋገጥ አንጻራዊ ቢሆንም አንድ ሃገር ለማ በባህሉ አደገ ሲባል የሚታየው ሁኔታ ማለት ነው። ለዚህ ሀገር ዜጎች የሚስማማ አኗኗር፣ የሚስማማ የኑሮ ዘዬና ስርዓት መፍጠር ሲቻል ማለት ነው። የባቢሎን ስልጣኔ በብዙ ታሪካዊ ድርሳናት እንደተቀመጠው በወቅቱ ከፍተኛ ስልጣኔ ከታየባቸው አገዛዞች መካከል አንዱ ነው። በዚያ ጊዜ ስልጣኔን የገለጹበት መንገድ እስከ ዛሬ ድረስ ላለው የስልጣኔ ትርጓሜ እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል።

ግሪኮች ስልጣኔ የሚለውን ቃል ከሶስት ቃላት ነው መዘው ያወጡት፣ እነዚያን ሶስት ቃላት ስንገነዘብ ስልጣኔን ወዲያውኑ ከምን ጋር እንደሚያያዝ ለመገንዘብ ያግዛል። የመጀመሪያው ቃል ሲቪስ ይባላል፤ ሲቪስ በግሪክ ዜጋ ሲቲዝን ማለት ነው በእንግሊዘኛ ወይም ዜጋ፣ የማኅበረሰብ አባል ማለት ነው። ሲቪስ ወይንም ዜጋ አንደኛው ቃል ሲሆን፣ ሁለተኛው ሲቪታስ ወይም ሲቲ ከተማና ከተሜነት፣ ሶስተኛው ሲቪሊስ ወይም ሲቪል ወይም ሲቪሊቲ፤ ስልጡን ባህሪና የኑሮ ዘይቤ።

ሶስት ነገር የመጀመሪያው የማኅበረሰብ አባል ሰው ማለት ነው፣ ሁለተኛው ከተማ፣ ሶስተኛው ከተማና ሰው ብቻ ሳይሆን ያንን ከተማ በሰለጠነ መንገድ መገልገል የሚችል ስልጡን ባህል የኑሮ ዘዬ፣ አንዳንዴ ከተማው እያለ በቅጡ መገልገል የማይችሉ ሰዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ስልጣኔ ስንል ሰው፣ ከተማና የአኗኗር ዘዬ መሆኑን የዛን ጊዜው አተረጓጎም እስካሁን ባለው ሁኔታም የሚሰራ ይሆናል።

ይሄን ለመገንዘብ ቀደምት ስልጣኔዎች በስሱ ስናይ ትርጉሙ እና ስልጡን የተባሉ ሃገራት በወቅቱ ያሳኳቸው ጉዳዮች አንድ እና ያው ሆነው እናገኛቸዋለን። በስልጣኔ ተርታ ውስጥ የመጀመሪያውን ወይም ቀደምት የሚባለው የሱሜሪያ ስልጣኔ ከሁሉ የቀደመው እንደሆነ የታሪክ ተመራማሪዎች ከሞላ ጎደል ይስማማሉ። ይህ ስልጣኔ የተገኘበት ቦታ ሜሶፖታሚያ ይባላል በወቅቱ በአሁኑ አጠራር ኢራቅ ያለችበት አካባቢ ማለት ነው።

የዚህ ስልጣኔ ጊዜ 4000 ዓመተ ዓለም ገደማ ሲሆን የአሁኑ ሲጨመርበት ስድስት ሺህ ዓመት ገደማ ይሆናል። የዛሬ 6ሺህ ዓመት ገደማ ሜሶፖታሚያ አካባቢ የነበረው ስልጣኔ የመጀመሪያው ፈርቀዳጅ ስልጣኔ ተብሎ ይወሰዳል። የዚያ ስልጣኔ መሰረት ግን በጤግሮስ እና ኤፍራጠስ ወንዞች መካከል የተፈጠረ ነው። እነዚህ ወንዞች እና ያ ቦታ ተደምረው የሱሜሪያን ስልጣኔን የሚገልጡ ሲሆን፣ በወቅቱ የነበረው ዋና ዋና ግኝት አንደኛ የጽሁፍ ቋንቋ ነው፣ ሁለተኛ ከሞላ ጎደል የተቀየሱ መስኖ መሰል ግብርናዎች ናቸው።

ውሃን ከመንገዱ በተወሰነ ደረጃ የቅየሳ የማድረግ ልምምድ፣ ሶስተኛ ከተማና ኪነ ህንጻ ናቸው፣ የእነዚህ ቅሪቶች አሁንም ይታያሉ እንደምታዩት ያንን ስልጣኔ የሚያሳየው ቅሪት በጽሁፍ የሚነበብ ብቻ ሳይሆን፣ በዐይን የሚታይ የሚዳሰስም ነገርም አለው፣ ያ የሚዳሰሰው ነገር ከድንጋይ ክምር የሚዘል ባይሆንም።

ሁለተኛው ከሱሜሪያን ቀጥሎ የሚገለጸው ስልጣኔ የኢንዱስ ሸለቆ ስልጣኔ ይባላል፣ የኢንዱስ ስልጣኔ ተብሎ ይጠራል። የኢንዱስ ስልጣኔ ጊዜው ወደ 3,300 ዓመተ ዓለም ገደማ ይገመታል፣ አሁን ካለው ጋር ወደ 5,300 ገደማ ዓመት ይሆነዋል። ቦታው በደቡባዊ እስያ ዛሬ ሰሜን ህንድና ፓኪስታን አካባቢ እንደሆነ ይታመናል፣ መሰረቱ የኢንደስ ወንዝ ነው፤ ወንዝ፣ ሰው፣ ከተማ አይለያይም የተመሰረተው ኢንደስ ወንዝ አካባቢ ነው። በዚያ በኢንዱስ ሸለቆ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች አንደኛው የታቀዱ ከተሞች ናቸው፣ ከነበረው የተሻለ በእቅድ የሚመሩ ከተሞች እና የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት አንዱ የሚጠቀስለት የስልጣኔው ማሳያ ነው።

ሶስተኛው በቅደም ተከተል ሲቀመጥ የጥንቷ ግብፅ ሥልጣኔ ነው። የግብጽ ስልጣኔ ጊዜው ወደ 3100 ዓመተ ዓለም ይሆናል፣ አሁን ካለው ጋር ሲደመር ወደ 5100 ዓመት ይሆናል፣ ቦታው ምስር አካባቢ ነው። አሁን ያለችውን ግብጽ እንዳለ አያሳይም ደቡባዊ ግብጽ የኑቢያ አካል ስለሆነ መሰረቱ የአባይ ሸለቆ ነው፤ ግኝቱ በዋናነት ግብርና እና ኪነ ህንጻ ነው።

አራተኛው የቻይና ሥልጣኔ ነው። አብዛኛው የታሪክ ተመራማሪ የሚስማሙበት ሶስት ሺህ ዓመተ ዓለም ገደማ የነበረ አሁን ካለው ጋር 5000 ዓመት የሆነው ስልጣኔ ነው፣ ቦታው አሁን ቻይና የሚባለው ግዛት አካባቢ ነው። መሰረቱ የቢጫ ወንዝ ሸለቆ ነው፤ የተመሰረተው የቢጫ ወንዝ ሸለቆን ተከትሎ ነው፣ ይሄም ግብርና እና መንግሥት ወይም በርከት ያሉ ሰዎች የማስተዳደር ስርዓትን ተፈጥሮበታል ተብሎ ይታመናል።

የሁሉም ስልጣኔ የጋራ ነገር የወሰዳችሁ እንደሆነ አንደኛው ድንጋይ ነው፤ ድንጋይ ማረሻ ነው፣ ድንጋይ የጦር መሳሪያ ነው፣ ድንጋይ መከላከያ ነው፣ ድንጋይ በድንጋይ ቤት መስሪያ ነው፣ እራሱ መጥረቢያውም ድንጋይ ነው። የሁሉም ስልጣኔ መሰረት ድንጋይ፣ ውሃ ወንዝ ፣ በርከት ያሉ ሰዎች ሰብሰብ ማለት፣ ከነሱ መሰብሰብ የተነሳ ደግሞ መንደሮች ከተማዎች የመገንባት ልምምድ ይታያል። እነዚህ ዋና ዋና ከሚባሉ ስልጣኔ በተጨማሪ በላቲን አሜሪካ የማያና ኢንካ የሚባሉ ስልጣኔዎች አሉ።

በሰሜን አፍሪካ የጥንቷ ካርቴጅ ሥልጣኔ የሚባል አለ። በምስራቅ አፍሪካ ኑቢያ፣ ኩሽ፣ ፑንተ፣ አክሱም የሚባል አለ ሌሎችም አሉ በርከት ያሉ ስልጣኔዎች በየቦታው የሚገለጹ አሉ። ለመነሻ ያክል ያየናቸው ጥንታውያን ስልጣኔዎች ግን ከተሜነት ሰብሰብ ብሎ መኖር፣ ድንጋይ መቆርቆር፣ መትጋት፣ በተላጠ እጅ ከሺህ ዓመት በኋላ የሚታይ ቅርጽ ለኛ መተው አለበት። እጁ ሳይላጥ፣ ለበርካታ ሰዓት ሳይፈጋ ለትውልድ የሚታይ ነገር ማቆየት አይቻልም። ይኔን በሁሉም ስልጣኔዎች ማየት ይቻላል።

የስልጣኔ አለባዊያን ምንድናቸው ሲባል አንዱ ከተሜነት ነው። ከተማነት እና ከተሜነት የዳበረ የኑሮ ዘይቤን ማህበራዊ መስተጋብርን የሚፈጥር ነው። ዊሊያም ሼክስፒር “ያለሰው ከተማ ምንድነው?” ይላል፤ ከተማ መሠረተ-ልማት ብቻ ሳይሆን ላዕላይ መዋቅር ጭምር ነው። ያማረ መንገድ፣ ያማረ ህንጻ ኖሮ ላዕላዩ ካልተሰራ የተሟላ የከተማን ውበት ማየት አንችልም። ከተማን የምንመራ ሰዎች መሠረተ-ልማት እና ላዕላይ መዋቅር በእኩል ስንመራ፣ የሚያምር ከተማ ለኑሮ የሚመች ከተማ፣ የኑሮ ዘዬው ስርዓት ያለበት ከተማ መፍጠር እንችላለን።

ሁለተኛው የዳበረ መንግሥታዊ ስርዓት ነው። የዳበረ ማለት ሰፊ ቁጥር ያላቸው ህዝቦችን በስርዓት አደርጅቶ የጋራ ፍላጎታቸውን ገልጸው ፍላጎታቸውን ለመጠበቅ በጋራ የሚተሙ ሲሆን፣ ግልጥ ያለ የዕርከን ቅደም-ተከተል ሲኖር፣ አንዱ ወደዚህ አንዱ ወደዚያ የማይነዳ ከሆነ ማለት ነው።

ሶስተኛው የዳበረ ባህል ነው። የዳበረ ባህል የአንድን ማኅበረሰብ እሳቤ፣ እሴት፣ ማንነት፣ እምነት፣ ስሜት፣ ቋንቋ፣ ኪነጥበብ በርከት ያሉ ጉዳዮች በውስጡ ይይዛል፣ ከዚያም አለፍ ሲል ስነ ጽሁፍን ይይዛል። አንድ ባህል፤ የአዲስ አበባ ባህል ምን ይመስላል ቢባል እዚ ያለውን ሰው በሙሉ ብንጠይቅ ለየብቻ፣ አንድ አይነት ምላሽ አናገኝም። ከዚህ እስከ ቦሌ ያለው አውራ ጎዳና በየት በየት በኩል ያልፋል፣ ስንት ኪሎ ሜትር ብንል ግን በጣም በርካታ ሰዎች የሚቀራረብ ምላሽ ይሰጣሉ። ለምን? ባህል እንደ መሠረተ-ልማት በቀላሉ የሚጨበጥ አይደለም፤ ባህልን ማኅበራዊ አንጎል ይሉታል። ማኅበራዊ አንጎል የተባለበት ዋናው ምክንያት የሰው ልጅ በአማካይ አጠቃላይ ካለው ቁመና ውስጥ የእያንዳንዱ ሰው አንጎል 2 በመቶ የሚያክል ክብደት አለው በአማካይ የሁሉም ሰው ክብደት ተወስዶ ሲለካ በአማካይ 2 በመቶ ይሆናል። ያ 2 በመቶ የሆነው አንጎል 25 በመቶ ፍጆታችንን ይበላል። ክብደቱ 2 በመቶ ነው ግን አጠቃላይ ከምንመገበው ነገር 25 በመቶውን ወሳጅ አንጎል ነው፤ 75 በመቶው የሚሄደው ለ98 በመቶ የሰውነታችን ነው። ምን ማለት ነው? ያ የማናየው ወደ 30 ቢሊየን የሚጠጋ ሴሎች በውስጡ ያጨቀው አንጎል ክብደቱ 2 በመቶ ሆኖ 25 በመቶ ኦክስጅን ይበላል ሲባል ምን አርገን ነው ያላችሁ እንደሆነ ብትሰሩም ብታወሩም ይበላል።

በኢንቨስትመንት ዐይን ብታዩ አንድ ሰው መቶ ብር ኢንቨስት አድርጎ 25 ብሩ የሚውልበትን በቅጡ ማየት ካልቻለ ከመቶ አስር፣ ከመቶ አስራ አምስት ማትረፍ አይችልም እንሰራለን በሰራነው እንበላለን የበላነው 25 በመቶ ይወሰዳል፣ ለምን እንደዋለ የማያስብ ሰው ሙሉ ልፋቱ ከንቱ ነው ማለት ነው።

አራተኛው እና የመጨረሻው የዳበረ ቴክኖሎጂያዊ አቅም ነው። ይህ አቅም በየዕለት የሚገጥመንን ችግር ለመፍታት የምንፈጥረው ጉዳይ ማለት ነው። የቸገረን ቤት ከሆነ እንዴት ቤት እንሰራለን፣ የቸገረን የውሃውን ይዘት መጠበቅ ከሆነ፣ የውሃውን ንጽህና መጠበቅ ከሆነ፣ ውሃን ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት ከሆነ ለቸገረን ነገር የምንፈልገው መፍትሔ በየጊዜው ቴክኖሎጂ ይባላል የግድ ኮምፕዩተር መሆን የለበትም። ስልጣኔዎች በምን መሰረት ይገለጣሉ ያላችሁ እንደሆነ ስልጣኔ የተወለደው የሰው ልጅ ገበታውን ሌማቱን ለማትረፍረፍ ባደረገው ተጋድሎ ነው። የመጀመሪያው የስልጣኔ ውልደት ምክንያት ገበታ ላይ በቂ ምግብ ማቆየት፣ በመብላት እራስን ማቆየት አስፈላጊ ስለነበረ ነው።

በዚህ ሂደት የስራ ክፍፍል ተፈጠረ፣ ትርፍ ምግብን ለማግኘት የሰው ልጅ ልምምድ የነበረው አደን መውጣት ነው፣ ከማን ጋር? ሚስቱ ጋር፣ ከህጻን ልጁ ጋር ምናልባት አንድ ፍየል፣ አንድ በግ ካለው ጎትቶ እና ቤተሰብ እየመሰረት ሚስቱን ልጁን ይዞ አደን ሲወጣ፤

ልጅ እያለቀሰ እናት ቆማ ልጅ እያጠባች በሚኖረው መስተጓጎልና ዝግታ በዕለቱ ወጥተው አድነው መመለስ ሲገባቸው ስለ ዘገዩ ብቻ ማደን እየተቸገሩ መጡ። ወጥተው በቀላሉ አድነው መምጣት የነበረው ፍጥነት ጋር አብሮ ስለማይሄድ በኋላ ምን ተፈጠረ? የስራ ክፍፍል። የለም ከምንጓተት አንቺ እዚህ ቆዪ ልጆች ይዘሽ እኔ ወጥቼ አድኜ ልምጣ፣ ካገኘው ይዜ እመጣለው፣ ካጣውም ትላንትና የተራረፈውን ሞቅ ሞቅ አርገሽ ታበይኛለሽ በሚል ስራ ክፍፍል ተፈጠረ እሷ ሰፈር ስትቆይ እሱ ውጪ አድኖ ሲመጣ፣ ውጤታማ እየሆነ መጣ። ፈጥኖ አድኖ ይመጣል እሷም ቤት ትሰራለች ከዚያ ግድ የለም ብቻዬን ከምሄድ ያንተና የኔ ሚስት እዚ ይቆዩ እኔ እና አንተ አድነን እንምጣ አምስት፣ አስር፣ ሃያ እያደገ ሄደ ማለት ነው።

በጋራ የሚያድኑ ሰዎች፣ በጋራ ሰፈር የሚቆዩ ሰዎች፣ ነገር ግን ይሄ የሥራ ክፍፍል በርከት ያሉ ሰዎችን ሰፈር የሚያቆይ በርከት ያሉ ሰዎች ወደ አደን የሚወስድ ሲሆን እየቆየ ሲሄድ ልጇን መታሸቢኝ፣ ወንበሬን ገፋሽቢኝ፣ እቃዬን ሰበርሽቢኝ ጭቅጭቆች ሰፈር ይፈጠራሉ ባሎች ሲመለሱ ሰፈር ጦርነት ነው ያለው ለዚያ ሲባል ማኅበራዊ መዋቅር እና የመንግሥትነት ባህሪ መፍጠር ተጀመረ።

በል ከኛ መካከል አንተ ቆይና የፖሊስ ስራ ስራ፣ ጠብቅ እየተባለ ልክ መንግሥት የመምሰል፣ ፖሊስ የመሰየም፣ የማስተዳደር እና መንግሥትን መፍጠር ቀጥሎ መጣ ማለት ነው። ከዚያ በኋላስ? ሰው ሲሰባሰብ ልማት ብቻ አይደለም፣ ጥፋትም አለ፣ ግጭትም አለ፣ ሽሚያም አለ፣ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥም አለ ያን ለመፍታት በጣም ብዙ በርካታ ፋይሎች ሲፈጠሩ መጻፍ፣ በጽሁፍ ማቆየት፣ ማስታወሻን ቴክኖሎጂ ተፈጠረ ማለት ነው። ሰው በሌማት እራሱን ለማትረፍረፍ ገበታውን ለመሙላት ካደረገው ጥረት ከተማና መንግሥት እስከፈጠረበት ጊዜ ሂደት ውስጥ በየጊዜው ምን አለ? ፈጠራ አለ፤ በየቀኑ ፈጠራ አለ በዛ ሂደት ነው ስልጣኔ መጣ የሚባለው። እነዚህ የስልጣኔ ሞዴሎች የተለያዩ የታሪክ አጥኚዎች ፈላስፋዎች ተመራማሪዎች በተለያየ መንገድ አስቀምጠውታል። አንድ ስልጣኔ የት ጀምሮ የት ጋር እንደሚያበቃ፣ ታሪካዊ ሞዴል የሚባል አለ፣ ዑደታዊ ሞዴል የሚባል አለ፣ በኃይል ላይ የተመሠረተ ሞዴል የሚባል አለ ሌሎች ሞዴሎችም አሉ።

አንድ በአንድ ለማየት ታሪካዊ ሞዴል የሚባለው የስልጣኔ መለኪያ መስፈርት አርኖልድ ቶይንቢ ሞዴል ይባላል። አርኖልድ ቶይንቢ የሚባለው ሰው የታሪክ ጥናት የሚባል ጥናታዊ ጽሁፍ በመጽሐፍ መልክ የዛሬ 90 ዓመት ገደማ ነው የጻፈው። በዚያ ጽሁፉ ስልጣኔን በአራት መንገድ ገለጸ፤ በተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ይሉታል የሰው ልጅ ተወልዶ፣ አድጎ፣ አርጅቶ እንደሚሞተው ሁሉ ስልጣኔ ይፈጠራል፣ ጅማሮ አካባቢ ላይ

እየዳበረ አድማስ እያሰፋ ሲሄድ ያድጋል፣ እያረጀ መሰንጠቅ ሲጀምር ደሞ የእድገቱ ጫፍ ላይ ደርሶ ማሽቆልቆል ይጀምራል። ሲፈረካከስ፣ ሲንኮታኮት፣ ሲሞት ደግሞ ልክ በብዙ ስልጣኔዎች እንደምናውቀው ቅሪት ቢኖረውም ያ ስልጣኔ የነበረውን ኃይል ይዞ አይቆይም ማለት ነው።

በዚህ መንገድ አርኖር ቶም ካስቀመጠ በኋላ ምናልባት ወደ 25/ 26 ዓመት ቆይቶ ዑደታዊ ሞዴል የሚባል ተፈጠረ። ይሄ ካርሎ ኪንግ የሚባል ሰው ቀደም ሲል የነበረውን የተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ሞዴል ካጠና በኋላ የሥልጣኔ ዝግመተ-ለውጥ ብሎ ጥናታዊ ሰነድ አዘጋጀ። በዚህ ሰነድ ላይ ያስቀመጠው ምንድነው፣ እያንዳንዱ ስልጣኔ በድንገት አይወለድም ከትናንትና ማንነቱ የሚጸነሰው የሚደረገው ከትናንትና ከነበረ ፣ ለምሳሌ ደርግ ጽንሰቱ የንጉሣዊ ሥርዓት ዘመን ነው።

ከንጉሣዊ ሥርዓት ጥፋትና ልማት የተማረውን ተምሮ ማንነቱን ፈጠረ ሚቀጥለው በዚያ መንገድ እንደማለት ነው። አንድ ስርዓት ዝም ብሎ አይወለድም። ካለስርዓት ድካም ስንፍና፣ ካለ ስርዓት የማድረግ አቅም ውስንነት እራሱን አደርጅቶ እና አሻሽሎ ብቅ ሲል የተጸነሰው በቀደመው ውስጥ ነው፤ በኋላ ግን ይዳብራል፣ ይስፋፋል። መስፋት ሲመጣ ደግሞ ተፈጥሯዊ ስለሆነ ግጭት ያቆጠቁጣል። ግጭት እና ጠብ እየሰፋ ደግሞ ሲሄድ መፈረካከስ፣ መበስበስ ይመጣል። ውስጣዊ ድክመቶች ለነዚህ ሁሉ መውጣት እና መውረድ መንስኤ ይሆናሉ በሰባት ከፈላቸው። የቅድሙ በአራት ከፈላቸው ከውልደት እስከ ሞት፣ ይሄኛው ደግሞ ጽንሰትን ጨምሮ ግጭትን ጨምሮ ትንሽ መጠንን እና የፈጠራ ጥበብን ማዕከል አድርጎ ሰራው።

ሦስተኛው ሞዴል በተወሰነ መልኩ ቴክኖሎጂያዊ እና ታላቅ ግብ ያነገበ የመምሰል ነገር አለው ካርደሺፕ ልኬት ይባላል ሩሲያዊ ሰው ነው። ካርደሺፕ የሚባለው ሰውዬ ስልጣኔ መለካት ያለበት በኃይል አጠቃቀም ነው ይላል። አንድ ሃገር በሚጠቀመው ኃይል ልክ ስልጣኔውን መናገር ይቻላል ብሎ ዜሮ አይነት ስልጣኔ የሚባለው በምድር ላይ ያለን ኃይል አሚጦ የማይጠቀም ማንኛውም ሀገር በዜሮ ስልጣኔ ደረጃ ላይ ነው ያለው ይላል። ምን ማለት ነው? የምድር ኃይል ምንጭ ሲባል እሳተ ጎመራን ይጨምራል አውሎ ንፋስን ይጨምራል፣ የመሬት መንቀጥቀጥን ይጨምራል በነዚህ ምክንያት የትኛውም ሀገር በዜሮ አይነት ስልጣኔ ደረጃ ነው ያለው ማለት ነው።

የትኛውም ሃገር ሁሉንም የኃይል ምንጭ መጠቀም አልቻለም። እሱ አይነት አንድ የሚለው የምድር እና ሶላር ኃይልን በተሟላ ደረጃ መጠቀም የሚቻልበት ደረጃ ሲደረስ

አይነት አንድ ይባላል ይላል። አይነት ሁለት የሚለው ደግሞ ሶላር ስርዓት ብቻ ሳይሆን ሙሉ ኮኮቦችን ሁሉም ኃይል ስላለው፣ እነዛን ኃይሎች መጠቀም የሚችል ሀገር ሲፈጠር ይላል ይሄን በዳይሶን ንፍቀ ክበብ መጠቀም ይቻላል ነው እሱ የሚያስቀምጠው፤ ግን የሶላር ሲስተሙ እና ኮኮቦች በሙሉ ኃይላቸውን ሲሰጡ ታአይነት ሁለት ስልጣኔ ደረስን ተብሎ ይወሰዳል ይላል።

አይነት 3 የሚላቸው ጋላክሲ ላይ ሚልኪ ዌይ ጋላክሲ ላይ ያለውን ኃይል በሙሉ መጠቀም ሲቻል ነው እያለ በኋላ ትንሽ ከበድ ያሉ ሃሳቦች እያነሳ ይሄዳል። ምንድነው የዚህ የካርድሺፕ ልኬት ለብዙዎች እንደ ማነቃቂያ የሚወሰደው ኃይልን በብዛት መፍጠር፤ ኢንዱስትሪ፣ ከተሜነት፣ ግብርና፣ ቴክኖሎጂ ላልነው ጉዳይ እንደ ግብአት ያገለግላል። ኃይል መፍጠር ያልቻሉ ሃገራት ሰለጠንን ቢሉም በስልጣኔ ደረጃ መወሰድ የለበትም ይላል። ሰዎች እንዲፈጥሩ የሚያግዝ ነው።

አሁን በውኃ ብቻ ተወስዶ ሲታይ አፍሪካ ውስጥ ከሰሃራ በታች አፍሪካ በጠቅላላ አፍሪካ 15 ትላልቅ ግድቦች ስማቸው ይጠራል 11ኛው ተከዜ ነው፣ ሰባተኛው ግቤ ነው፣ ሁለተኛው ኮይሻ ነው አንደኛው ህዳሴ ግድብ ነው። ከአስራ አምስቱ፣ አራቱ በአፍሪካ ያሉ ግድቦች ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ አንደኛ፣ ሁለተኛም፣ ሰባተኛ እና አስራ አንደኛ ነገር ግን በውኃ ኢትዮጵያ ማምረት የሚገባት የኃይል አቅምና ዛሬ እያመረተች ያለች ደግሞ ገና ብዙ ይቀረናል። አሁን ውድድሩ ከአፍሪካ ሲሆን በርከት ያለ ቁጥር አለ፣ በሀገር ካለ አቅም አንጻር ደግሞ ሲሆን ገና ብዙ ይቀራል።

ሌሎች ሞዴሎች አሉ የማቲው ሜልኮም ሞዴል የሚባል አለ። ይሄ ደግሞ በመንግሥት ስርዓት ነው የሰራው፣ ያልዳበረ ባህል እና የማኅበረሰብ ድርጀታ ያለበት ስርዓት ሲሆን፣ ፊውዳላዊ ሲሆን፣ የተበታተነ ያልተማከለ ስርዓት ሲሆን፣ ሀገረ መንግሥታዊ ሲሆን ሪፐብሊክ ሊሆን ይችላል። ግዛት ሊሆን ይችላል በማዕከላዊ መንግሥት ስር ሰፋ ያለ ህዝብ ሲተዳደር ኢምፔሪያላዊ ሲሆን የማዕከላዊ መንግሥት ተጽዕኖ በአካልም በተለያየ መንገድ ከቅጥሩ ከድንበሩ ሲዘል በሚል ያስቀምጠዋል።

ስልጣኔን ልዩ ልዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል። ሁሉም ደምራችሁ ግን ስታዩ ዐሻራ አለው፤ ዐሻራው ድንጋይ፣ ዐሻራው ወንዝ ነው መሰረት ያደረጉበት የዓለም ስልጣኔን ካየን በኋላ ወደእኛ ሁኔታ ስናመጣው የኢትዮጵያ ስልጣኔ አንዳንዴ ለየብቻ፣ አንዳንዴ በጋራ ሰብሰብ ያሉ ግዛቶችን ይመለከታል። ኢትዮጵያ ሲባል አሁን ያለው ካርታ ማለት አይደለም። ኢራቅ ሲባል አሁን ያለው ካርታ ማለት አይደለም፤ ቻይናም ሲባል

እንደዚሁ።በጊዜ ብዛት ወደዛ ወደዚህ የሚሉ ነገሮች ይኖራሉ። ያም ሆኖ የኢትዮጵያ ስልጣኔ የሚያድግባቸው ዘመናት የኢትዮጵያ ስልጣኔ የሚወድቁባቸው ጊዜዎች በጥቅል ሲታዩ የድምጽና የጩኸት ፍትጊያ ነው። ድምጾች ጎልተው ሲወጡ፣ ድምጾች ጩኸትን መደበቅ ሲችሉ፣ ድምጾች በብዙዎች በሚገባ ተደምጠው ተከታይ ሲያገኙ እድገት ስልጣኔ አለ። ጩኸቶች ሲበረቱ ድምጽ ሲደበቅ ደግሞ ስልጣኔን ማውደም አለ። ጩኸት እና ድምጽ ሲተካከሉ መሳ ለመሳ ሲጓዙ ያዝ ለቀቅ ይሆናል። መሄድ መመለስ፤ ሁለት መራመድ አንድ መመለስ ይሆናል። እዛው ባለበት ሂድ አይነት ነገር ይፈጠራል።

እንዴት ነው ድምጽ ጎልቶ ጩኸት የሚደበቀው ያላችሁ እንደሆነ ወደ አምናው ትሄዱና ትርክት ሃሳብ፣ ሃሳብ ትርክት ጎልተው ተገዝተው መሪነትና እና ተከታይነት ሲስማሙ ስልጣኔ እና እድገት ይመጣል ያ ሲደበዝዝ ደግሞ ጥፋት ይመጣል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ስልጣኔዎች ቅድመ አክሱም እና ከአክሱም በኋላ ብለን በሁለት ብንከፍል አክሱም ብዙ የተነገረለት ስለሆነ ቅድመ አክሱም የዛሬ ሁለት ሺህ አምስት ዓመተ ዓለም ገደማ አሁን 3ሺህ/ 4ሺ ገደማ ሆኗል ማለት ነው። የፑንት ስልጣኔ ነበረ፣ የፑንት ስልጣኔ ግማሽ የሚያህል ኢትዮጵያን ይዞ ዋና ትኩረቱ ቀይ ባህርን የሚቆጣጠር ነው፣ ፑንት ወጥቶ ሲወርድ የኩሽ ስልጣኔ መጣ። የኩሽ ስልጣኔ እንደገና ቀይ ባህርን በስፋት ይዞ እዚህ ጋር እንደምታዩት ወደ ኋላ እስከ ሱዳን ድረስ ይሰፋል። የኩሽ ስልጣኔ ወድቆ የዳማት ስልጣኔ ደግሞ ሲመጣ የተወሰነ የሚከፋፈሉ አሉ ግን አሁንም ቀይ ባህርን፣ አባይን መቆጣጠር ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ስልጣኔዎች ሁሉ መሰረት ነበረ። በኋላ የአክሱም ሲመጣ አክሱም ወደ ኋላ ያለውን ቀንሶ ወደ የመን በተወሰነ ደረጃ፣ ወደ ደቡባዊ ሳውዲ ህንድ ድረስ የሚዘረጋ ሰፋ ያለ ተጽዕኖ ያለው በወቅቱ ከነበሩ አራት ሃያላን መንግሥታት እንደ አንድ የሚወሰድ መንግሥት ነበር።

በዓለም ላይ ስልጣኔ ነበር ከተባለ በዓለም ላይ ከድንጋይ ጋር የሚያያዝ ሙከራዎች ነበሩ ከተባለ አንዱ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው!

ለምሳሌ አክሱም ብትሄዱ፣ ይሃ ብትሄዱ፣ ላሊበላ ብትሄዱ፣ ሶፉ-ዑመር ብትሄዱ ታዩታላችሁ ድንጋይ እና ሰው የነበረውን ትስስር። ግብጽ ያለው ፒራሚድ የብዙ ፊልሞች፣ የስልጣኔ ምንጭ፣ ብዙዎች ሊያዩት የሚጓጉለት ሲሆን ኢትዮጵያ ያለው እንደዚህ ያለው ስልጣኔ በእኛ ስንፍና ምክንያት ብዙ ያልተነገረለት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ላሊበላን

ስትወስዱ ያኔ አይደለም ዛሬም እንደዛ ያለ ምህንድስና የለም። ሁሌ የምናውቀው ወደታች ይቆፈራል፣ መሰረት ይሰራል ቤት ወደ ላይ የሚገነባው ላሊበላ የተገነባው ከላይ ወደ ታች ነው የተለየ ጥበብ ነበር ማለት ነው።

እነዚህ ቀደምት እውቀቶች የመጡበት ዋናው መንገድ ያኔ የነበረው ስልጣኔ፣ ድንጋይ እና ሰው ለረዥም ጊዜ ያላቸውን ትጋት የሚያሳይ ነው። ከዚያ በኋላ ያሉትን ብንወስድ ከአክሱም በኋላ ዛጉዌ ነበር። ከዛጉዌ በኋላ ጊዜው በትክክል ባይታወቅም ዛግዌ አካባቢ ወይም በፊት ባሌ አካባቢ ስልጣኔ ይነሳል። የጎንደር የዛሬ 400 ዓመት አካባቢ የነበረው ስልጣኔ ይነሳል አሁንም የሚታይ ነገር ስላለ፣ የሀረር ስልጣኔ ይነሳል፣ የጅማ፣ የሸዋ፣ የከፋ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ ይቀጥላል በየቦታው ማለት ነው። ለምሳሌ የዳውሮ ስልጣኔ የዛሬ አራት መቶ ዓመት ገደማ አላላ ኬላን ሲሰሩ 47/48 ዓመት ነው የፈጀው። ስራው አሰራሩ እንዴት ነው፣ አንድ ትውልድ ግዴታው ሰባት ዓመት ነው። ሰባት ዓመት ግዴታ ያለበት አንድ ቤተሰብ አንድ ዓመት ልጅ ጥሎ ቢሄድ ሰባት ዓመት ድንጋይ ቆርቁሮ ሲመለስ ልጁ ስምንት ዓመት ይሞላታል። ስምንት ሲሞላው ይተካል በሌላ ሰው ማለት እንደዛ እያሉ አራት/ አምስት ትውልድ በቅብሎሽ 47/48 ዓመት ነው።

አላላ ኬላን የገነቡት ያሁሉ ድንጋይ ምን ይፈልጋል? መቆርቆር ይፈልጋል፣ መደርደር ይፈልጋል። በየቦታው የምናያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ስልጣኔዎች ሌላ ቦታ ከተማርናቸው ስልጣኔዎች ጋር የሚቀራረብ ባህሪ አላቸው፤ ታድያ እንዴት ማሽቆልቆል መጣ? ስልጣኔ ከነበረ እንዴት ማሽቆልቆል መጣ? ያልን እንደሆነ ውጫዊ ምክንያት አለ ውስጣዊ ምክንያት አለ። የመንግሥታት መዳከም አለ፣ የህዝብ ብዛት እና የአቅርቦት መሳሳት፣ ህዝብና አቅርቦት አብረው የማያድጉ ከሆነ ግጭት፣ ግጭት ደግሞ መዳከምን መፍጠሩ አይቀርም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣኔ የመጣባቸውን ኋላም ውድቀት የታየባቸውን ዘመናት በአንድ ምሳሌ ብቻ ለመገንዘብ ፥ አንድ አራት ጎማ ያለው መኪና ከዚህ ተነስቶ የሚፈልግበት ቦታ ለመድረስ ቢያንስ ቢያንስ አራት ሁነኛ ነገሮች ይጠበቁበታል። አንደኛው የመኪናው አራቱም ጎማ ተመጣጣኝ መጠን መኖር አለበት፤ ሶስቱ መካከለኛ ሆነው የሚኒባስ ጎማ ሆነው አንደኛው የትራክተር ጎማ ቢሆን መፍጠን ቀርቶ መጓዝ አይችልም ምክንያቱም ትልቁ ትንሾቹን ይገለብጣቸዋል። ጎማው መመጣጠን አለበት፣ የጎማው መጠን በከፍተኛ ደረጃ የሚለያይ ከሆነ የአንደኛው ማደግ ወይም ማነስ ሌሎቹ የመውደቅ ጦስ ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛው መመዘኛ አንድ ላይ መሸከርከር አለባቸው ሶስቱ ጎማ እየተሸከረከረ አንደኛው ቢነክስ፣ ባይሸከረከር መኪናው ወደፊት ሳይሆን የሚሄደው የነከሰው ጎማ ስለሚጎትተው አደጋ ሊያስከትል ይችላል። እኩል መሆን አለባቸው አራቱም መሸከርከር አለባቸው። ሶስተኛው በአንድ አቅጣጫ መሄድ አለባቸው ሁለቱ ወደፊት፣ ሁለቱ ወደ ኋላ ከሆነም አይቻልም አይደርሱም። አራተኛ እኩል ፍጥነት ያስፈልጋቸዋል እያንዳንዱ ጎማ በእኩል ፍጥነት መጓዝ የማይችል ከሆነ የአንደኛው መፍጠን የአንደኛው መዘግየት አደጋ ያስከትላል።

ተመጣጣኝ መጠን፣ አንድ ላይ መሸከርከር፣ በአንድ አቅጣጫ መጓዝ፣ በእኩል ፍጥነት መጓዝ ያስፈልጋል። ወደ ብልጽግና አምጡት የኢትዮጵያን ብልጽግና ህልውና ለማረጋገጥ የምንፈልግ የኢትዮጵያን ብልጽግና መስራት፣ መሰረት መጣል የምንፈልግ ከሆነ በእኩል መሮጥ ይኖርብናል። አንድ ሀገር ከሌሎች ኋላ ቀረ የሚባለው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ መስፈርያዎች ስላሉ በነዚያ ከፍ ካለው ያለው ሀገር ዝቅ ብሎ ሲገኝ፤ በኢኮኖሚ፣ በቴክኖሎጂ ከፍ ካሉ ሀገራት ተርታ ዝቅ ብሎ ሲገኝ ኋላ ቀር ይባላል።

የእድገት መጓተት ካለ ቀጣይነት ያለው እድገት ከሌለ፣ የፍጥነት መጓተት ካለ፣ የፖለቲካ አዙሪት ካለ፣ የኢኮኖሚ ስብራት ካለ እነዚህ የኋላ ቀርነት መገለጫ ተደርገው ይወሰዳሉ። መንስኤዎቹስ? መበስበስ ነው፤ አንደኛው የተቋማት መበስበስ ነው። ለምሳሌ ፖሊስ ብለን አደራጅተን የህዝብን ሰላም መጠበቅ ካልቻለ፣ ከበሰበሰ፣ በማኅበረሰብ እና በፖሊስ መካከል እምነት እየጎደለ ከሄደ፣ ቅቡልነቱን ካጣ ወይም ፍርድ ቤት ብለን ሰው ተበድሎ ፍትህን ፍለጋ ፍርድ ቤት ሄዶ ፍትህ የማያገኝ ከሆነ፣ የፍትህ ተቋማት የማይታመኑ ከሆነ የተቋማት መበስበስ ያጋጥማል መንግሥታት ስራቸውን በወጉ መስራት ሲሳናቸው ማለት ነው።

ሁለተኛው የባህል መበስበስ ነው፤ መልካም የሆነ እሴት ሲሸረሸር መከባበር፣ መተማመን፣ አደራ መጠበቅ፣ በቃል መገኘት፣ አለመስረቅ፣ አለመቅጠፍ፣ አለመዋሸት የመሳሰሉ ጉዳዮች እየላሉ ሲሄዱ። ሶስተኛው የኢኮኖሚ መበስበስ ነው፤ የኢኮኖሚ ተዋንያን እየቀጨጩ ሲሄዱ፣ የቢዝነስ አድማስ ሲጠብ፣ ምርታማነት ሲቀንስ፣ የጥቅል ኢኮኖሚ መኮስመን ሲያጋጥም፣ እዳ ሲበራከት፣ የምናመርተው እና የምንፈልገው ሲለያይ ያኔ የኋላ ቀርነት መንስኤ ተደርጎ ይወሰዳል።

ኢትዮጵያ ቅድም እንዳነሳሁት በዘመን መካከል ቀደምት ነበረች። ተቸክላ ቆይታለች፤ በሆነ አዙሪት ውስጥ ገብታለች፣ በጣም በጣም ዘግይታለች፣ ተንሸራታለች፣ ኋላ ቀርታለች።

በጊዜና በዘመን መቀደም የሚያስከትለው ጣጣ፣ መዘጋት፣ መዘግየት፣ መንሸራተት ነው እየዘገየን በዘመን ስንቀደም ብዙ ጉዳዮች በኛ እየተዘጉ ዘመን ሲለወጥ እኛ እዛው ቆመን እንቀራለን። በኢትዮጵያ የባለፉት ሺህ ዓመታት ሂደት ውስጥ የነበረ ችግር ነው። ነገር ግን አንድ ተስፋ አለ የኢትዮጵያን መዘግየት፣ ማሸቆልቆል፣ መድከም፣ መደህየት፣ ብንናገርም ሶስት ሺህ ዓመት በላይ እያነሰች፣ እየሰፋች፣ እየቆመች፣ እየተነሳች እንደ ሀገር መቆየቷ ደግሞ የባሰ ስላለ እሱ ቢያንስ እንደ መልካም ነገር ይወሰዳል ማለት ነው።

ከነችግሩም ቢሆን ሀገር አለን፤ እኛ ከነችግሩም ቢሆን ቢያንስ እንደዚህ ሁሉም ብሄር ያለበት፣ ስለ አንድ ሀገራዊ ፍላጎት መነጋገር እንችላለን። ስለዚህ ምንም እንኳ የከፉ ጉዳዮች ቢኖሩም አሁንም ሃገር ነን፣ አሁንም መነጋገር መቻላችን ተመልሰን ለመነሳት፣ ተመልሰን ለማደግ ተስፋ ነው። የባሰ ስላለ ከፈረሱት ስለምንሻል በመቆዘም ብቻ ሳይሆን በተስፈኝነትም ማየት ይገባናል ማለት ነው።

የሀገር እድገት ከልካይ አጥሮች አካላዊ አጥር፣ ተቋማዊ ወይም ስርዓታዊ አጥር እና ባህላዊ አጥሮች አሉ። እነዚያ አጥሮች መስበር ካልቻሉ እንደ ሀገር፣ እንደ ክልል፣ እንደ ከተማ እድገት አይመጣም። ለምሳሌ አዲስ አበባን ብንወስድ አዲስ አበባ እራሱን ከአጥር ገላግሏል፤ ብር ያለው ሰው ኢንቨስት የሚያደርግ ሰው ከመጣ አዲስ አበባ ይጠቀማል። ያ ሰው ኦሮሚያ ቢሄድስ? አማራ ቢሄድስ? ሌላ ክልል ቢሄድስ? የመጀመሪያው ጥያቄ ዕውቀትና ገንዘብ አለህ ወይ ሳይሆን ከየት ነው የመጣኸው ነው! ያ አጥር ምን እያረጋቹ ነው? እንዳታድጉ እያረጋቹ ነው! ካፒታል ድንበር የለውም፤ ዕውቀት ድንበር የለውም።

ገንዘብ ያለው ሰው፣ ዕውቀት ያለው ሰው፣ የሚሰራ ሰው ከየትም ቢመጣ መቀበል አለብኝ ብለን ካላመንን በቀር እዚህ ያየነውን እድገት አንደግመውም!

በነገራችን ላይ አጥሩ ማለቂያ የለውም። በኦሮሚያ ውስጥ ከሆነ ጅማ፣ ከኢሉባቦር፣ ከሀረር ከወለጋ መለየት ይቸግራል። አማራም ከሄዳችሁ እንደዚሁ ነው። በነገራችን ላይ በኢንቨስትመንት ብቻ አይደለም የምንቸገረው፤ በዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትም ቢሆን ጎንደር ውስጥ አንድ ጎበዝ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ቢኖር እሱን አጥምጄ ደሞዝ ጨምሬ ጅማ መውሰድ አልችልም። የግድ የጅማ ልጅ መሆን አለበት ባይችልም። ዕውቀትም አጥረን፣ ገንዘብም አጥረን፣ ማደግ ፈልገን አብሮ አይሄድም።

እድገት የሚመጣው ዕውቀትና ገንዘብ ያለበትን ቦታ አነፍንፈን ስንሰበስብ ነው፤ ስንገፋ አይደለም!

የትኞቹም ያደጉ ሀገራት ብትወስዱ የትኞቹም ዕውቀትና ገንዘብ ያለበትን በከፍተኛ ደረጃ ያጠምዳሉ። ይሄ አጥር ተቋማዊ አጥር እና ባህላዊ አጥር ከእኛ እምነት፣ ከእኛ ቋንቋ፣ ከእኛ እሳቤ ውጪ ያለው ወደ ውጭ የሚለው እሳቤ ሌላ አጥር ነው። ብዙ ለማወቅ፣ ብዙ ለመማር ፍላጎት የለም። በነገራችን ላይ አሁን ባሉ ጥናቶች የሰው ልጅ እድሜው 70/80/90 ሲጠጋ አልዛይመር እንዳይዘው የመዘንጋት የመርሳት በሽታ እንዳይዘው ሁለት/ሶስት ቋንቋ ማወቅ ጠቃሚ ነው ይባላል ሳይንሳዊ ግኝት ነው። ሁለት/ሶስት ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎች እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ አንድ ቋንቋ እንደሚያቅ ሰው አይደለም የመጠቃት አቅማቸው የሚጎቀሳቀስ፣ ሰውም እንደዚሁ ያ ችግር እንዳይመጣ መንቀሳቀስ ብዙ ቋንቋ፣ ብዙ ባህል ለማወቅ መሞከር ጠቃሚ እንጂ ጎጂ ነገር አይደለም።

በሳይንስም ተረጋግጧል፣ በልምድም ይታወቃል። አጥሮቻችንን እንስበር ለምሳሌ ድሬዳዋ፣ ሃረር አካባቢ ስትሄዱ አራት አምስት ቋንቋ ማንም ሰው ማንም መንገደኛ ይችላል። ጣልያንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ ምናምን አረቢኛ ይሞክራሉ ነው። እነዛ ሰዎች አራት/ አምስት ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ዛሬ በስተርጅና እንኳን ብታገኟቸው ልክ እንደ ሊቅ እንደ አዋቂ እንደ ጠበብት ናቸው ዛሬ እንኳን። ከብዙ አንግል ስለሚማሩ ለመማር የሚያቅ የሚችል ለመቀበል አለመሞከራችን ትንሾቹ ያሉትም እየሸሹ አለቁ ማለት ነው፣ እነዚህ አጥሮች መሰበር አለባቸው። ልማት የሚያመጣ እስከሆነ ድረስ፣ ዕውቀት የሚያመጣ እስከሆነ ድረስ። ሰላም የሚረብሽ ከሆነ አታስጠጉ ጥሩ አይደለም አጥር ያስፈልጋል! ልማት የሚያመጣ ከሆነ ግን በድንበር ዕውቀት ማቆየት ጉዳት አጥር ለዘጋው ሰውዬ እንደሆነ ማሰብ አስፈላጊ ነው።

ለስርዓት ስብራት ዋናው ምክንያት ለለዉጥ ዝግ መሆን፣ ለውጥ የሚባል ነገር ለማድመጥ፣ ለመጠየቅ፣ ለመመርመር፣ ለማንበብ ዝግጁ ያልሆኑ ዝግ ሰዎች አሉ። ምንም ነገር ከነሱ እሳቤና ፍላጎት ውጪ ሲሆን አላስፈላጊ አድርገው የሚያስቡ። ሁለተኛው የተዛባ የለውጥ ጥያቄ የቸገረውን ትተው ያልቸገረውን ለመፍታት የሚጥር ማጎበረሰብ እና ግለሰብ እንዲሁ ለስብራቱ ዋነኛ ምክንያት ይሆናል። ሶስተኛ አፍራሽ የለውጥ ሂደት፤ ማፍረስን እንደ ግብ መያዝ።

በመጀመሪያው ክፍል ምን አየን? ስልጣኔ ታሪክ፣ ሰው ያላቸውን መስተጋብር በዓለም ስልጣኔ የሚበየንበት፣ የሚመረምርበት፣ በደረጃ የሚታይበት። እነማን እንዴት ሰለጠኑ የሚባልበት ነገር ካየን በኋላ ወደእኛ ሁኔታ ስናመጣው ኢትዮጵያ ውስጥም ያ የስልጣኔ ቅሪት እንደነበረ በማስረጃ ማየት ቻልን። ለምን ተንኮታኮትን? ያልን እንደሆነ በጋራ አንድ ሃሳብ ይዘን እኩል ስለማንጓዝ አንዱ ሲሄድ አንዱ ስለሚቆም ነው፤ ያን ማረቅ ማስተካከል

ማረም ያስፈልጋል። ለምን የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ሰው በተሰጠው እና ባለው ጊዜ ሳይሆን ከዚያ በላይ የሚተጋ መሆን አለበት። ያን ማድረግ ከቻልን ነው ስልጣኔ ማረጋገጥ የምንችለው።

ዛሬ ያለችውን ኢትዮጵያ ካለችበት አረንቋ አውጥቶ ስልጡን ሀገር ለማድረግ ፍቱን መድሃኒቱ መደመር መር መንግሥት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ታሪክ አለ፣ የታሪክ ቅሪት አለ፣ ጥንታዊነት አለ ነገር ግን የሚታይ የሚጨበጥ ስልጣኔ የለም፤ ለምን? ታሪክ እንደወንዝ ነው ፈሳሽ ነው፣ ወራጅ ነው። ስልጣኔ ምን ይፈልጋል? መገደብ ይፈልጋል፣ መቀየስ ይፈልጋል፣ ማረስ ይፈልጋል፣ ኃይል ማምረት ይፈልጋል። ይሄ ደግሞ ድካምና ስራ አለው። ታሪክ ይፈሳል ይሰለጥን ዘንድ ስራ ይጠይቃል፤ ካልሰራን ስልጣኔ አይመጣም።

አባይ ታሪክ ነው፣ ንጋት ግን ስልጣኔ ነው። ንጋት ታሪክ በማውራት ብቻ ሳይሆን ታሪክ በመስራት ጭምር ያገኘነው ድል ነው!

ደጋግመን እንደዚህ ያለውን ስራ ብንሰራ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ስልጣኔን መጎናጸፍ፣ ማቆየት፣ ማሸጋገር እንችላለን ማለት ነው። ታሪክ ሞልቷል፤ የእኔ እና የእናንተ ስራ ስልጣኔን ማረጋገጥ ነው በስራ! የመደመር ሚና በስልጣኔ ጎዳና አንደኛው ስብራትን መጠገን፣ ለሚቀጥለው ጉዞ መሰረት መጣል፣ ስልጣኔን የማስቀጠል ስራና አቅጣጫ መቀየስ ነው።

እንዴት ይቻላል ይሄ? አንደኛ ሀሳብ፣ መነሻው ሃሳብ ነው። የመደመር እሳቤ እንደ ሃሳብ ዘር ነው ይህንን ዘር በጊዜው በሚገባው ልክ በቦታው ከዘራነው ይበራከታል፤ ብናዘገየውስ? ዘር አይሞትም፣ ዘር አይጠፋም ግን ማምረት የሚገባውን ምርት እንዳናመርት ያደርገናል። እመኑኝ የመደመር ሃሳብ ኢትዮጵያ እስካለች አይሞትም! እንዲህ እንዲህ ይደረጋል እንጂ አይሞትም። አይሞትም ነገር ግን ዛሬ ባንጠቀምበት ዘር ነውና መራባት ሲገባው ዝም ብሎ ይቆያል። አሁን ብንጠቀምበት እየተባዛ፣ እየተባዛ ከእኛ አልፎ ሌሎች የሚያግዝ ሊሆን ይችላል።

ለምንድነው የመደመር ዘር አይጠፋም አይሞትም የሚባልበት ምክንያት? የመደመር እሳቤ ካለፈው ተምረንና አርመን፣ መማር ብቻ አይደለም የሚስተካከለውን አርመን፣ በዛሬው ተጠቅመንና ተመስርተን የነገውን የምንሰራበት እና የምንረዳበት መነጽር ነው። ትላንትናን እማራለሁ አርቃለው ይላል። ዛሬን እጠቀማለሁ፣ እሰራለሁ፣ መሰረት እተዋለው ይላል።

ነገን ለልጆቼ አልቄ አሻሽዬ የተሻለ የስልጣኔ መሰረት እሰጣቸዋለሁ ይላል። ይሄን የማይቀበል የትኛውም መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አይችልም። ከዚህ ቀደም

ይቻል ነበረ፤ አሁን ግን አይቻልም! ዘመን መዋጀት ማለት አሁን ያለውን ነገር መገንዘብ ማለት ነው። አሁን ያለውን ነገር የማይገነዘብ ሰው ሲጀመር መንግሥት አይሆንም ምክንያቱም የተቀየረ ዓለም ውስጥ ያልተቀየረ እሳቤ መምጣት አይችልም። የተቀየረ ዓለም ውስጥ እራሱን ቀይሮ የመጣ ደግሞ ካለ ትላንትና እና ነገን ማያያዝ ግዴታው ይሆናል። ይሄንን የማይቀበል ከሆነ በተሟላ መንገድ መሻቱን ሊከውን፣ ሊያሳካ አይችልም።

በተደጋጋሚ መደመር ማለት የሃሳብ የአቋምና የአቅም ድማሮ ነው፤ መደመር ማለት አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ማለት አይደለም ከዛ ይዘላል፣ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት ነው ብለን እናነሳ ነበር፤ የመደመር አእማዶች በሰባት ‘ኤስ’ የገለጽናቸው የመጀመሪያው የአቅም ተደማሪነት ‘ሲነርጂ’ ያልነው ነው። ሲነርጂ የአቅም ተደማሪነት ነው፤ የግዜ ተደማሪነት ‘ሲንክሮኒ’ ነው። የስርአት ተደማሪነት ‘ሲስተም’ ያልነው ነው። የስልት ተደማሪነት ‘ሲሜትሪ’ ያልነው ነው።

ስልት ደምሯል፣ ስርዓት ደምሯል፣ ጊዜ ደምሯል፣ አቅም ደምሯል። ከዚያ ቀጥሎ ግን ሶስት ‘ኤስ’ ያልናቸው የሚደምራቸው አንደኛ መዋቅር ነው መገንባት ‘ሲንትሮፒ’፤ መደመር በመገንባት ‘ሲንትሮፒ’ እንጂ በማፍረስ ‘ኢንትሮፒ’(ቀውስ) አያምንም። በመገንባት እንጂ በማፍረስ አያምንም። በመገንባት ማመኑ በራሱ በታሪክ ጉድለትና ትስስር ውስጥ ያለውን ስፍራ በግልጽ ያመላክታል። ማንኛውም ታሪካዊ ሂደት ተገንብቶ መሸጋገር አለበት የሚለው እሳቤ ከእድገት እምነት የመጣ ነው። ሌላውሳ? የህይወት ተደማሪነት ‘ሲምባዮሲስ‘፤ የመጨረሻው የራዕይ ተደማሪነት ወይም ‘ሲኖፕሲስ’ ይባላል። ዋናውን ነገር በቀለለ መንገድ፣ በአጠረ መንገድ የሚገልጠው ማለት ነው።

እነዚህ ሶስት ‘ኤስ’ ያልናቸው የስርአት ተደማሪነት፣ መዋቅርና ስትራቴጂ ወይም የስርአት ተደማሪነት፣ ስልት ተደማሪነት እና መገንባት የአቋም ድማሮ ሲሆኑ ሲነርጂ የአቅም ድማሮ ነው። አቅምና አቋም ሲደመሩ፣ ጊዜና ህይወት ሲደመር የበለጸገ ሀገር ይፈጥራል ያ ነገር ነው የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ሊያደርግ የሚችለው።

የኢትዮጵያን ለወጥ እውን ሊያደርግ የሚችለው፣ የኢትዮጵያን መሻሻል እውን ሊያደርግ የሚችለው ለምን በሁሉም ውስጥ ይብዛም ይነስም የሚጠቅም ዕውቀት፣ የሚጠቅም ሃሳብ ስላለ። ቀመሩስ ምንድን ነው? አንደኛው ማሰባሰብ፣ ዛሬ ላይ የሚገኙ ሃሳቦች፣ ሀብቶች፣ አቅሞች፣ ሙከራዎች ካሉ ሳይንጠባጠቡ ማሰባሰብ ካልተሰበሰበ ይበተናል። እንኳን ሀሳብ፣ እንኳን ሀብት እህል እንኳን በጊዜው በወቅቱ ሰብስበን ካላስቀመጥን ይባክናል፤ መሰብሰብ አለበት። ሁለተኛው ማከማቸት ነው፤ በትናንት ሃሳብ፣ በትናንት

አቅም፣ በትናንት ሀብት ላይ ዛሬን መጨመር፣ ማከማቸት እሱ ነው። ሶስተኛው ማካበት ለለውጥ ለብልጽግና የሚያበቃ ወረት ማጠራቀም እዳን መቀነስ፣ የተሻለ ሀሳብ፣ የተሻለ አሰራር፣ የተሻለ ጅማሮ ማቆየት ነው። ይሄን ማድረግስ እንዲሁ ቀላል ነገር ነው? አይደለም። ሁልጊዜም ወጣ ያሉ ሃሳቦች ትላንት በነበረው ስልጣኔ አሁን ባለንበት ዓለም ነገም በሚፈጠረው ዓለም ውስጥ የሃሳብ ጅማሮን በፍጥነት ተቀብለው የሚሄዱ ሰዎች ውስን ናቸው። መጀመሪያ ያላግጣሉ፣ መጀመሪያ ይስቃሉ፣ መጀመሪያ አቃቂር ያወጣሉ እየደረመሰ ሲሄድ ግን ይከተላሉ። ለምሳሌ ሁላችሁም እንደምታውቁት በኢህአዴግ የመጨረሻው ጉባኤ ሀዋሳ ላይ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን ሲባል ኢሕአዴጎች ነበሩ እና እንኳን እናንተ እኛም አልቻልናትም ነው ያሉት።

ኮሪደር ሲባል፣ የኮሪደር ልማት ሲባል እዚህ ጢያሳ አካባቢ ሲጀመር ብዙ ሃሜት ነበረ። ዛሬ ጢያሳ ያየ ሰው ግን በእርግጠኝነት ያንን ቋንቋ አይደግመውም ምክንያቱም አዲስ ነገርን ለመፍጠር ማፍረስ፤ አዲስ ለማውጣት አሮጌም መቀነስ የግድ የሚባልባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ስለሚያምን። እኛ ጨክነን የያዝነውን መልካም ሃሳብ እና ስራ ስንቀጥል የማናውቃቸው በርካታ ሰዎች ተከታይ ብቻ ሳይሆን የተከታይ መሪ ይሆናሉ ምክንያቱም መደመር መሪነትን እና ተከታይነትን ያላቸውን ትስስር በተለየ መንገድ ነው የሚያየው። ማንኛውም ሃሳብ በመሪነት ቢፈጠር መልካም ተከታይነት ከሌለ አይከናወንም።

በጋራ ሰልጥነን፣ በጋራ አይተን፣ በጋራ ሰምተን አንዱ ጋር የሚሰራው አንዱ ጋር የማይሰራበት ምክንያት የተከታይነት ችግር ነው!

ስንሰማ ከልብ እንስማ፣ ስንሰማ አሚልተን እንስማ፣ ስንሰማ ለመጀመር ለመሞከር ለመስራት እንስማ። የነበረብን ችግር መነሻ ላይ ሃሳቡን በቅጡ መረዳት፣ ሃሳቡን መቀበል፣ ሃሳቡን መገንዘብ፤ ሃሳቡን ከተገነዘብን በኋላ በተግባር በስራ መግለጥ ነበር ችግሩ፤ አሁንሳ? ያው ሰምታችሁ ይሆናል፣ መደመር በፓኪታን ቋንቋ፣ በኪስዋሂሊ፣ በጀርመን በብዙ ቋንቋዎች እየተተረጎመ ነው። ብትፈልጉም ባትፈልጉም ሄደ ማለት ነው።

ሃሳብ ሲጀመር እንዲህ ያለ መከራ አለው ሲጀመር፣ እየቀጠለ ሲሄድስ? ተከታዩ ብዙ ነው። አደጋው የት ጋር ነው አሁን? አደጋው የሰው ልጅ የራሱን ድል ማሸሞንሞን፣ የራሱን ድል መሞሸር ሲጀምር ራሱን መግደል ጀመረ ማለት ነው። ዘርን ተዘርቶ ካልበቀለ በቀር፣ በቅሎ በብዙሃን ካልታየ በቀር አሸናፊ መሆን አይችልም። ለምሳሌ ሀረሪን አይታችሁ ከሆነ ሃረር ከተማ ሃረሪ የሰሩት ስራ እውነት ለመናገር በጣም በጣም አስገራሚ ነው ከአዲስ

አበባም በላይ። ለምን? አዲስ አበባ ይብዛም ይነስም እንደተባለው ብዙ አመራር አለ፣ ብዙ ዐይን አለ፣ ብዙ አጋዥ ሊኖረው ይችላል። እነሱ በራሳቸው አቅም በሌለ ሃብት ያንን ህዝብ አንቀሳቅሰው ያስገኙት ውጤት ለብዙዎቻችሁ ትምህርት ይሆናል። ሃረሪ ተለውጦ አሶሳ ወይም ቦንጋ ወይም ጋምቤላ ባይለወጥ እውነተኛ ልብ ያለው ሰው መገምገም ነው። የሃረሪ ሃብት እና የአሶሳ ሃብት፣ የሀረሪን ሰው እና የጋምቤላን ሰው መፈተሽ ነው። በየትኛውም መመዘኛ ሃረሪ ከሌሎች ክልሎች ያነሰ ስፋት እና ሃብት ነው እንጂ ያለው የበለጠ የለውም። ባነሰ ገንዘብ እና ሰው እንደዚያ ያለውን ታሪካዊ ስራ መስራት ከቻሉ ሁላችንም ጋር ይቻል ነበር ማለት ነው። ሃሳቡን በትክክል ገዝተን ብንተጋ እና ሃሳብ መነሻ ነው፣ ዘር ነው።

ሁለተኛውስ? መሻገርያ ነው፤ የመደመር መንገድ መሻገሪያ ነው። የመደመር ሃሳብ መነሻ ዘር ነው፣ መሻገሪያ ግን ድልድይ ውድ ነው። መንገድ መስራትና ድልድይ መስራት እኩል አይደለም፤ ድልድይ ውድ ነው። ውዱን ለመሻገር፣ ከባዱን ለመሻገር ውሃን ሸለቆን መሻገር ይጠይቃል። ዝም ብሎ መፍሰስ መንገድ ላይ ይቻላል፤ መሻገር ሲታሰብ ግን መሃል ላይ ጎርጅ አለ ማለት ነው። ያ ጎርጅ ድልድይ ይጠይቃል ድልድይ ደግሞ ውድ ነው የላቀ ዕውቀት ይፈልጋል፣ ትጋት ይፈልጋል። ስራውም እንደ መንገድ ቀላል አይደለም ሸለቆን ለመሻገር የምናነሳቸው ጥያቄዎች፣ ጥያቄዎቹን የምንረዳበት መንገድ የምንፈታበት መንገድ በጣም ወሳኝ ነው።

ታላቁ የሃገራችን ጥያቄ፣ ዋናው ጥያቄ ምንድነው ፥ በወጉ፣ በስርዓት፣ በቅጡ ጥያቄውን መገንዘብ የመጀመሪያው እርምጃ ስለሆነ ተሞክረው ያልተሳኩ ሞዴሎች እነማን ናቸው? ያለፈውን ማፍረስ ያለፈውን ማንቋሸሽ፣ ያለፈውን መጣል እንደግብ የያዘ ኃይል ነገን ሊሰራ ይችላል ወይ? እየደመሰሱ አዲስ መቅዳት ያዋጣል ወይ? ብልጽግናን ልማትን ለውጥን እኩልነትን አብሮ ማደግን ግብ ያላደረገ ማንኛውም ኃይል አሁን ካለንበት ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ሊወስደን ይችላል ወይ? እነዚህ ለመመለስ ስልቶቻችንን ማየት ያስፈልጋል።

ስልቶቻችን አንደኛው የፈጠራ መንገድ ነው። ሁለተኛው የፍጥነት መንገድ ነው። ሶስተኛው የዝላይ መንገድ ነው። ከኋላ ቀርነት ለመውጣት፣ አዙሪትን ለመሻገር፣ የወረት ውስንነትን ቀንሰን ወረት ለማበራከት፣ የጊዜ ውስነትን ለመሻገር ትናንትን ከነገ ለማስተሳሰር የዛሬን ድልድይ መስራት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ዛሬ ያልተገነባ ድልድይ ወደ ነገ ስለማያሻግር። የሚፈጠረው አዙሪት አንዳንዶች ትላንት ትላንት ትላንት ሲሉ ዛሬ ነገ ይረሳል የነገ የነገ የነገ ሲባል ደግሞ የዛሬ ይዘገያል ውስጣዊ ውስጣዊ ሲባል ዓለም አቀፋዊ ጉዳይ ያልፈናል

ትናንትም ብቻ ካልን ተከታይ ነን ነገም ብቻ ካልን መሻገር አንችልም ውስጥም ብቻ ካልን ተከታይ ነው የምንሆነው።

ለዚህ ሁሌ ተከታይ፣ ሁሌ በችግር ውስጥ የምንሸከረከር እንዳንሆን። ዓለም የምንገነዘብ፣ ውስጣችን ምንገነዘብ፣ ዛሬም በቅጡ የምንሰራ ዕውር ነቁጦቻችንን ደግሞ ዞር እያልን የምናይ መሆን መቻል አለብን። ያን ስናደርግ መፍጠር፣ መፍጠንና ሲያስፈልግም ዘልሎ መሻገር ይቻላል ማለት ነው። ፈጠራ፣ ፈጠራ ማለት ውስንነትን መሻገር ነው። ከአዙሪት መውጣት ነው። የተለየ አካሄድ መከተል ነው። የዝመናን መሰረት መጣል ነው።

ሃረሪ ቅድም ያልኳችሁ ወይም ጋምቤላ የምላችሁ የግድ አዲስ አበባን መምሰል የለበትም ችግሩን ካየ በኋላ አካባቢውን ቃኝቶ በራሱ መንገድ ባለው ሃብት ካለበት ሁኔታ ትንሽ ሻል ያለ መፍጠር ይችላል። ሁሉ ተመሳሳይ እና አንድ መሆን የለበትም ምክንያቱም የፈጠራ ምንነት እና ባህሪያት እንዲሁም መንገዱን መገንዘብ ያስፈልጋል። የፈጠራ ምንነት እይታና አመለካከት ነው። ከዚያስ? አሰራር እና ሂደት ነው። መጨረሻ ላይስ? ውጤትና ልዩነት ነው።

ፈጠራ ምንድነው? ያልሆነ አተያይ፣ አመለካከት፣ አሰራር ሂደት፣ ውጤቱ እና የፈጠረው ለውጥ ነው። ባህሪያቱስ? ባህሪያቱ ያልተገደበ ነው ፈጠራ፤ ፈጠራ እንደ ወርቅ አይደለም፣ እንደ ጋዝ አይደለም። ሶማሌ ክልል ጋዝ አለ፣ ጋምቤላ ወርቅ አለ፣ አሶሳ ወርቅ አለ እንደሚባለው አይደለም ያልተገደበ ነው፤ ዓለምአቀፋዊ ነው። ማንም ሰው ያለበትን ሁኔታ ማስተዋል ከቻለ ከዚያ የሚያወጣውን ነገር መፍጠር ይችላል። መጨረሻ ግን አነቃቂ ነው።

ከፈጠረ፣ ካሳካ በኋላ በከፍተኛ ደረጃ የሚያነቃቃ፣ ለሌላ ፈጠራ የሚያዘጋጅ ነው መንገዱ፣ ፈጠራን እንደ ግብዓት። ከምርት ግብዓቶች መካከል እንደ አንዱ ለምሳሌ የሰው ኃይል፣ መሬት፣ ካፒታል እንደሚባለው ሁሉ የመፍጠር አቅም ፈጠራን እንደ ግብ፣ ፈጠራን እንደ ምርት ማየት ያስፈልጋል። ፈጠራ ያልታከለበት ሌሎች ካፒታሎች ብቻቸውን የምንፈልገውን ነገር ሊያመጡ አይችሉም። መለስ ብለን እንመልከት የሰው ልጅ በምርታማነት የታጀበ ጉዞውን ስናይ ሙሉ በሙሉ ፈጠራ ነበር ፈጠራው ያዘገመ ወይም ፈጣን ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ ሶስቱ የግብርና አብዮቶች የመጀመሪያው የግብርና፣ ሁለተኛው የግብርና አብዮት፣ ሶስተኛው የአረንጓዴ አብዮትን ብንመለከት አንድ ባህሪ አላቸው የማምረቻ

ሂደቱ ከፍተኛ የጉልበት ሥራን የሚጠይቅ ነበረ ከፍተኛ የሰው ኃይል ይጠይቅ ነበር ብዙ ምርት ማምረት። ሁለተኛ ፈጠራን ከአንድ ጫፍ ሌላ ጫፍ ለመሄድ በጣም በጣም ቀርፋፋ ነበር። እዚህ ያለው ዕውቀት ባለበት ለመቶ ዓመታት ይቆይ ነበር። በዚያ ምክንያት የመጀመሪያው የግብርና አብዮት የጀመረው ወደ 10 ሺህ ዓመተ ዓለም ገደማ ነው ይባላል።

እስከ ሁለት ሺህ ዓመተ ዓለም ገደማ ለስምንት ሺህ ዓመታት የሰው ልጅ ከአደን ለቀማ ወደ ግብርና የተደረገ ሽግግር ውስጥ ለሺህ ዓመታት ኖሯል፣ በጣም ቀርፋፋ የሆነ እንቅስቃሴ ነበር። ሁለተኛው የግብርና አብዮት 17ተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የመጣው እስከ 19ተኛው ክፍለ ዘመን ሁለት መቶ ዓመት ቆይቷል ምን አመጣ ይሄ? ሰብል ማፈራረቅ፣ ሁሌ በቆሎ ብቻ ሳይሆን በቆሎ፣ ስንዴ፣ ሩዝ ማድረግ። አነስተኛ ሜካናይዜሽን የተጀመረበት ነው ያኛው ለሺህ ዓመታት ሲቆይ ይሄ ደሞ ሁለት መቶ ዓመታት ቆየ።

ሶስተኛው አረንጓዴ አብዮትስ? 1930 ገደማ ጀምሮ 1960 ገደማ ድረስ ነው የሄደው፣ አንደኛ ምርታማነት ጨመረ በስፋት ምን አዲስ ነገር አመጣ ያላችሁ እንደሆነ ማዳበሪያ መጠቀም፣ ተባይ መከላከያ መጠቀም መስኖ መጠቀም ሜካናይዜሽን መጠቀም ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ በአጫጭር ጊዜ የሚበቅሉ ሰብሎች መመራመርና ማየት ማግኘት፣ ውስን ውሃ፣ በውስን ቦታ ሰፊ ምርት በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያው ለሺህ ዓመታት ቆየ ሁለተኛው ለመቶ ዓመት ቆየ ይሄኛው ደግሞ ለአስር ዓመታት ቆየ።

የእኛስ? ሶስተኛው አረንጓዴ አብዮት ባለቀበት ዘመን የኢትዮጵያ ዘፈን በሬና ገበሬው ይላል ቢያንስ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሜካናይዜሽን ሲፈጠር ያ የበራለት አንቂው ሰው በሬና ገበሬ ትስስር የለውም። በሬ ከትራክተሩ ቢል ኖሮ ሰው ምን እያለ ነው ምን አስቦ ነው ይጠይቅ ነበር ግን ከአረንጓዴ አብዮት በኋላም ዘፈኖቻችን በሬና ገበሬው፣ ስዕላችን በሬና ገበሬው፣ ማረሻ እና ቀንበሩ ስለሆነ እዛው ቀረን ማለት ነው።

የግብርና አብዮት ከጀመሩ ሀገራት ተርታ የምንመደብ ቢሆንም እስከ ዛሬ በሬና ገበሬን ማላቀቅ አልቻልንም። ለምን? በፈጠራ የታጀበው መንገድ በጣም ቀርፋፋ ስለሆነ እኛ በዚያ ውስጥ ተጽናንተን መኖር መቆየት አለመስፈንጠር ልምምዳችን ስለሆነ፣ ሁለተኛው አምስቱ የቴክኖሎጂ አብዮት ነው። የመጀመሪያ የኢንዱስትሪ አብዮት 80 ዓመት ገደማ ነው የቆየው፣ ሁለተኛው የእንፋሎት እና የባቡር ሀዲድ ዘመን የሚባለው ወደ 46/47 ወይም 50 ዓመት ነው የቆየው። ሶስተኛው የብረት፣ የኤሌክትሪክ እና የከባድ ምህንድስና

ዘመን የሚባለው ደግሞ ከ 1875 እስከ 1908 - 33 ዓመት የቆየው፣ የነዳጅ፣ የሞተር መኪና እና የጅምላ ምርት ዘመን በኋላ የመጣው ደግሞ 60 ዓመት ገደማ ቆይቷል ግን ራሱን በጣም እያዘመነ እየለወጠ፣ የመጀመሪያው አውቶቢል ሳይሆን በጣም ፈጣን፣ በጣም ትላልቆች እየተፈጠሩ ማለት ነው። አምስተኛው የመረጃ እና የቴሌኮሙዩኒኬሽን አብዮት ነው።

እስካሁንም ያለው በጣም በከፍተኛ ደረጃ እየተስፈነጠረ፣ አሁንም ያለው እስከ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ዘመን ያለው ማለት ነው። ምንድነው ከቅድሙ ሚለዩ ያላችሁ እንደሆነ በፍጥነት፣ ምርት እና ኢኮኖሚ አድጓል መሠረተ-ልማት ሰፍቷል የስራ አይነት ተቀይሯል የአኗኗር ዘዬ ተቀይሯል ከተሞች ተስፋፍተዋል ኢንዱስትሪ ሰፍተዋል ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ በከፍተኛ ደረጃ ፈጥኗል ይፈጠራል ይስፋፋል ድሮ ቢፈጠርም አይስፋፋም፣ የመግባቢያ መንገድ አልነበረም የኢንዱስትሪ አብዮት ለዓለም ያስገኘው ነገር በከፍተኛ ደረጃ የምርት መትረፍረፍ እንዲመጣ ማስቻል ነው።

ከዚያ መቋደስ ያልቻሉ ሃገራት ወይም አልሰሙም ታጥረዋል ከሰሙም አልፈጠሩም ማለት ነው። የዛሬ ሶስት ዓመት አራት ዓመት አብራሪ አልባ በራሪ አካላትን ምናምን ስንል እንደምታስታውሱት ለብዙዎቻችን ተረት ነው። ሰው-ሰራሽ አስተውሎት ሲባል ለብዙዎቻችን ቀልድ ነው። ዛሬ ግን ሰለጠንኩ አደኩ የሚል ሀገር ምረቱን ሲያመጣ እኔም እኮ እንደዚህ ሞክሬያለሁ፣ እኔም እኮ እንደዚህ አለኝ ማለት ቻልን። አርፍዶ የመምጣት ጠቀሜታን፣ እንስፈንጠር አንቀመጥ ያልነው ስራ ማለት ነው።

በግብርናው እና በኢንዱስትሪ አብዮት እንደዚህ ቀድመን ሙከራዎች ብናደርግ ከዋናዎቹ እንኳን ባንሆን ቢያንስ በበቂ ከሚጠቀሙት መሆን እንችል ነበር። ያ ድጋሚ እንዳይደገም ነው አሁን ሙከራዎች የሚደረጉት። የፈጠራ ሙላት የሚፈጠረው ከችግር ተንታኝነት ወደ መፍትሔ አመንጭነት። ችግርማ ኖርንበት እሱ መተንተን ሳይሆን እንዴት ነው ከዛ ልንወጣ የምንችለው የሚል መፍትሔ ማፍለቅ መቻል፣ በፈጠራ ማምረት እራሱ ፈጠራን ማምረት ሲቻል በችግር አለመታጠር፣ በመፍትሔ መሻገር ሲቻል ገደብ የለሽ እና ሁሉን አቀፍ የሰፋ እና የፈጠነ ጅማሮች ማስናሰል ሲቻል ነው።

ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር በሚመለከት ድርቅ እናውቀዋለን አብረን የኖርነው ያደግንበት ጉዳይ ነው። የተበጣጠሰ እርሻ እናውቀዋለን ችግር ነው። የዝናብ ጥገኝነት እናቀዋለን፤ የአየር ንብረት ለውጥ እናቀዋለን። ችግሮቻችን ናቸው። ምን እድል አለ? ሰፊ መሬት አለ የውሃ ሃብት አለ የሰው ኃይል አለ፤ ይሄንን እናውቃለን። አሁን ከኛ የሚጠበቀው

የተበጣጠሰ መሬት ሳይሆን ኩታ ገጠም ማስፋት፣ ያልታረሱ ጦም ያደሩ መሬቶችን ወደ እርሻ ማስገባት፣ የበጋ ስንዴን ማስፋት፣ ሜካናይዜሽንን ማስፋት፣ አረንጓዴ ዐሻራን ወደ ፍራፍሬ ወደ ሀገር-በቀል ዛፎች ማሳደግ፤ በጥራት ማስፋት።

ምንድነው ይሄ? መፍትሔ አመጣን ማለት ነው። አረንጓዴ ዐሻራ ሲሰፋ የአየር ንብረት ለውጥ አደጋ አያስከትልብንም፣ ክረምት ከበጋ ማረስ እንችላለን፣ ምርት ይሰፋል፣ ረሃብ ይጠፋል ማለት ነው። ችግሩን እናውቀዋለን መፍትሔው ላይ ነው ርብርብ እና ስራ የሚያስፈልገው። መደመራዊ የፍጥነት መንገድ ይደርሳል አይደርስም፣ ይቻላል አይቻልም በሚል መላምት እና ግራ መጋባት ውስጥ መቆየት ሳይሆን ከዚያ የወጣ በውጤት የሚገለጥ ፍጥነትን ማረጋገጥ ነው። የሂደት እና የውጤት ፍጥነት ማሳየት ነው። በትልቅ ማሰብ በትንሽ መጀመር፤ ማበራከት ማሰናሰልና ማላቅ ነው። ከጊዜ ኋላ እንድንገኝ ያደረገው የሂደት እና የውጤት ፍጥነት መጓደል ነው። ቀርፋፋ የሆነ አካሄድ ከጊዜም ከውጤትም እንድንዘገይ አድርጎናል። ጊዜ ተሻግሮ አለማሰብ፣ ለነገ አለመዘጋጀት፣ ለትውልድ አለማቆየት ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ። አስፓልት ከሆነ ሽሮ ፈሰስ፣ ጊዜን ማሳደር ችግርን ማሳደር፣ ፕሮጀክቶች በጊዜ አለማጠናቀቅ ሄዶ ሄዶ ለትውልድ የሚቆይን ወረት ማሳነስ ነው።

በትልቁ ማሰብ ከትንሽ መጀመር!

ለምሳሌ ጽዱ ኢትዮጵያን የመፍጠር ግብ ከቢሮ ተጀመረ ከተማ ተባለ ወደ ሃገር እየሰፋ ሄደ። ኮሪደር፣ የበጋ ስንዴ፣ ሌማት፣ አረንጓዴ ዐሻራ ሁሉም ተነሳሽነት ጅማሮ አነስተኛ ነበር። በሂደት እየፈጠነ፣ እየሰፋ፣ እያደገ፣ ጥራት እያረጋገጠ በሃገር ደረጃ ተጽዕኖ የሚያመጣ ሆነ። አሁን ከጀመርናቸው ውስጥ ኮሪደር አሸልሟል፣ አረንጓዴ ዐሻራ አሸልሟል፣ ስንዴ አሸልሟል፣ አብዛኛው የእኛ ሥራዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው እና ሽልማት ያሰጡ ናቸው።

ለምን? በቀጣይነት እና በውጤት ማረጋገጥ ስለቻልን። ፍጥነት ሲባል ሶስት አይነት ፍጥነቶች አሉ አንደኛው ፍጥነት ነው በአማርኛ 'ቶሎታ' ይባላል በቶሎ መድረስ ፍጥነት ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሊሆን ይችላል። ፍጥነት ወደፊት ወደ ኋላም ሊሆን ይችላል፣ ፍጥነት ወደ ላይ ወደ ታችም ሊሆን ይችላል። ብቻ መፍጠር ብቻ ቶሎታ ሁለተኛው ፍጥነት ይባላል ፍጥነት ከትክክለኛ አቅጣጫ ጋር መፍጠን ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ መንገድ መሆን አለበት። ያ ፍጥነት፣ ሶስተኛው አክስለሬሽን ይባላል ወይም ሽምጠጣ፣ ጥድፊት ይባላል በአማርኛ ይሄ ደግሞ ፍጥነት አለው፣ አቅጣጫ አለው።

አቅጣጫው ላይ እያደገ የሚሄድ ፍጥነት አለው። ለምሳሌ የመጀመር ፍጥነት እንደምታዩት በአንድ ጊዜ ሁሉም ሯጭ ስብስብ ብሎ ይከመራል ይሄ የመጀመር ፍጥነት ነው። በሂደት ምን ያጋጥማል? ይሄው እንደምታዩት በሂደት እየሳሳ እየሳሳ እየፈጠነ የሚሄደው እየቀደመ የሚዘገየው ደግሞ ከፊት ፊት እያለ ይቀጥላል። በኋላ ላይ በሂደት ያለው ትጋት ወደ ውጤት ጥራት ሲመጣ እንደምታዩት የመጀመሪያው ሯጭ በከፍተኛ ፍጥነት ሲሄድ ተበተነ ሰው ከኋላ የሚከተለው ሁለት ሰዎች አሉ፣ ሁለት ኢትዮጵያውያን ሶስተኛውን ተመልከቱት። ሶስተኛው ሁለተኛውን ቀደመ ለምን? ለውጤት ጥራት ቀድሞ ከፊት ያለው ግን ሰፊ ልዩነት አላቸው።

ሞፋራ በጣም ርቋል፣ እሱን ለመከተል የማስቀጠል ትሩፋት በእያንዳንዷ ሰከንድ መፍጠን ብቻ ሳይሆን እየሸመጠጠና እየተጣደፈ ፍጥነት እየጨመረ በመሄድ በመጨረሻ የፍጥነትን፣ የትጋትን በቀጣይ የመልፋትን ውጤት ታዩበታላችሁ። ልዩነቱ እየጠበበ፣ እየጠበበ፣ እየጠበበ መጨረሻ ተመልከቱ። ምን ማለት ነው? ሲጀመር ሁሉም ይሰበሰባል፣ በቀጣይነት ሳናቋርጥ የያዝነውን ቅን ሃሳብና መልካም ሃሳብ ይዘን የምንቀጥል ከሆነ ቀድሞ ከኛ ጋር አጃቢ የነበረው ታዛቢ ይሆናል። እኛ ስንጨርስ ታዛቢ ይሆናል። ያኔ አልመሰለኝም ነበር፤ በደንብ አልነገራችኝም ነበር፤ ችግሩ እኮ አነጋገራችሁ ነው በደንብ ቢገለጽልን ኖሮ እኮ እኛ እንከተላችሁ ነበር ወደሚል ይሸጋገራል። ከእኔና ከእናንተ የሚጠበቀው የጀመርነው መልካም ዘር፣ የጀመርነው ፍጥነት፣ የጀመርነው ትጋት የተሟላ ፍሬ እስኪያፈራ ድረስ ባለማቋረጥ በቀናው ሃሳብ ቀን ከሌት ተግቶ ሰርቶ በስራ ማሳየት ነው። ያን ማድረግ ስንችል አብዛኛው የተራገፈ፤ ብልጽግና የምንጨብጠው፣ የምናሸተው፣ የምናየው ፍሬ ለዜጎቻችን እየሆነ ይሄዳል ማለት ነው!

አዲስ አበባ

በመደመር መንግሥት እይታ፣ የዘርፎች እመርታ - ክፍል 2

ሀዳር 21 **ቀን** 2018 **ዓ.ም**

የመደመር ፍጥነት አለባዊያንን ካየን በኋላ የመደመር ዝላይ፣ ዘሎ ማለፍ የምንለው ጽንሰ ሃሳብ በመፅሃፉ ላይ በዝርዝር የተቀመጠ ቢሆንም ዋና ዋና ሁለት አላማዎች አሉት፡ ፡ አንደኛው ከቀዳሚው ጋር ያለን ልዩነት ማጥበብ ነው፤ ሁለተኛ እመርታዊ እድገት ማምጣት ነው፡፡ ሌሎች የረገጡትን ሁሉ መርገጥ ተገቢ አይደለም! ውጤት አይተን ከዚያ መማር እንችላለን፣ ጊዜ ወሳጅነትን ማሸነፊያ፣ የአርፋጅነት ፈተናን ማሸነፊያ መሆን አለበት። ከሌሎች ስኬት እና ውድቀት መማር፣ ከሃገርም ከሀገር ውጪም መማር ያስፈልጋል ግን እያንዳንዱን ዱካ መከተል ውጤታማ አያደርግም ብሎ ይነሳል።

ይህ መደመራዊ የዝላይ የሽግግር ሂደት አንደኛ ወደ ውጤት መቀየር፣ ወደ ሌላ መሻገር ፣ ወደፊት መስፈንጠር በውስጡ ይይዛል። ነባር አቅሞችን ወደ ውጤት መቀየር፣ አሉ አቅሞች እዚህም እዚያም። አዳዲስ ዘርፎች መፍጠር ወደዚያ መሻገር፣ በዘርፎች ውስጥም የሚፈጠር ሽግሽግን መከወን፣ አዳዲስ የመልማት አቅሞች ማውጣት፣ አዳዲስ የገበያ እድሎችን መፍጠር፣ ያለንን አቅም ማዘመን ወደ ዓለም መስፈንጠር፣ መዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጥ፣ ዕውቀት እንደ ምርት መጠቀም ችግር፣ ፈተና ከውስጡ ሊፈለቀቅ የሚችል ዕድል ካለ ችግርን ወደ ዕድል ወይም ወደ መልካም አጋጣሚ መቀየር ነው። ለምሳሌ ኮሮና መጣ፤ አፍሪካ መሬት ላይ ይረፈረፋል፣ ያልቃል፣ ትጠፋላችሁ ተባለ። አናልቅም ሚርት ነው ይልቁንስ መሬት ጦም ማደር የለበትም እየተጠነቀቅን እንሰራለን አልን፡፡ በኮሮና የስንዴ አብዮት ፈጠርን፣ በኮሮና በዓለም ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው ትርፋማ ሆኖ እራሱን አመቻችቶ ነው ያለፈው። ችግሮች አሉ ግን ከዚያ ውስጥ ዕድልን ፈልቅቆ ማውጣት፤ ከዚያ ውስጥ መልካም ዕድል ፈልቅቆ አውጥቶ መጠቀም መቻል ይኖርብናል።

ችግር ጠልፎ የሚጥለን ሳይሆን፣ ገፍቶ የሚያስፈነጥረን መሆን አለበት!

በችግር ትብታብ ታስረን እንዳንቀር ተስፈንጥረን ወደ ምንፈልገው ነገር እንድንደርስ በአንዳንድ ጉዳይ ዝላይ ያስፈልጋል፡፡ የዝላይ ትኩረት ግን ሰው ተኮር፣ ትውልድ መር መሆን አለበት። ሰው ላይ ያነጣጠረ መሆን አለበት፣ ብዝሃ ዘርፍ፣ ሀገር አቀፍ መሆን አለበት፣ በምክክር ተግባቦት ፖለቲካዊ እልባት በሚያመጣ መንገድ መሆን አለበት፣ ዕውቀት ሸማች ብልጽግናን አምራች መሆን አለበት፡፡ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ዱካ መከተል ቀላል ቢሆንም፣ ዳሩ ግን ከሚፈለገው ግብ አንፃር ባጠረ ጊዜ ለመድረስ አያስችልም። አንድ

ሰው ከዚህ እስከ አዳማ በእግሩ ሲሄድ ያን ዱካ ተከትለን ብንሄድ እሱ የወሰደበትን ጊዜ ያክል ይወስድብናል። መኪና፣ ሳይክል፣ አቋራጭ ብንጠቀም ግን ባጠረ ጊዜ እናሳካዋለን፡ ፡ የእድገት መሰላሉን ደረጃ በደረጃ ለመውጣት መሞከር ሀብትና ጉልበት ያባክናል። ያስፈልጋል መሰላል፣ ግን እያንዳንዱን የደረጃ እርከን መርገጥ የለብንም። መደመራዊ ዝላይ የሚያስፈልገው ክፍተቱን ለመሙላት ድልድይ ለመሆን ነው። እመርታ ከትልቅ እርምጃ ውጪ፣ ከዝላይ ውጪ ሊመጣ አይችልም የሚል እሳቤ በውስጡ አለው። ምን አየን? መነሻ አየን ዘር፣ ሃሳብ፤ መሻገሪያ አየን ድልድይ። አሁንስ መዳረሻው ምንድነው? ድልድይ ገንብተን የት ነው የምንደርሰው? ለሚል ጥያቄ ሁለንተናዊ ብልጽግና ነው።

ሁለንተናዊ ብልጽግና ምንድነው ይሄን ስእል ያየ ሰው ይበቃዋል። ፈረሶች መጋለብ ያውልማዳቸው፣ ተፈጥሯቸው ነው ግን መስኩን ተመልከቱት የሚጋልቡበትን ለም ለመስክ፣ ፀሀይዋን ተመልከቱ ፣ ከዋክብት ተመልከቱ ዝላይ ብቻ ሳይሆን ፈንጠዝያ ተመልከቱ። መጋለብ ልማዳቸው ቢሆንም፣ በተፈጥሮ ውበት የታቀፈውና ከወትሮው ግልቢያ ባሻገር ልዩ ደስታን የሚሰጥ አውድ ነው።

ሁለንታዊ ብልፅግና ማለት ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሁሉን ነገር በውስጡ ያሟላ ማለት ነው። የበለጸገ ግን ያልሰለጠነ፣ የሰለጠነ ግን ያልበለጸገ ሰው እንዳይኖር ማለት ነው!
የሰለጠነ ግን ያልበለጸገ፣ የበለጸገ ግን ያልሰለጠነ ክፍተተ ማጥበብ ማለት ነው። ሁሉን ነገር ያሟላ እንዲሆን ማድረግ። በአንድ ወቅት አንድ የውጭ ሀገር ቀጣሪ በሥራ ልምዳቸው የሸመገሉ ሰውን ይቀጥራል። እኚህ ሰው ለሥራቸው እጅግ ታማኝና ትጉህ በመሆናቸው ጠዋት በማለዳ ይገባሉ፤ ቀኑን ሙሉ ሥራቸውን በትጋት ያከናውናሉ። ጠባያቸው፣ ታዛዥነታቸውና ትህትናቸው እጅግ መልካም በመሆኑ ቀጣሪው በጣም ወዷቸዋል። ነገር ግን ቀጣሪው ወደ ሀገሩ በሚመለስበት ጊዜ አንድ ችግር አጋጠመው፤ እኚህ አባት ኢሜይል መጻፍ አይችሉም፣ ኮምፒውተርም አያውቁም። ሥራውን በሚገባ ቢሠሩም፣ ኢሜይል ስለማያውቁ ለሪፖርት አልተመቹም። በዚህ ምክንያት ቀጣሪው ወጣቶችን አወዳድሮ ሌላ ሠራተኛ ቀጠረ። ለአዲሱ ወጣትም፡- “እሳቸው ዋናውን ሥራ ይሠራሉ፣ አንተ ደግሞ የኢሜይልና የኮምፒውተር ሥራዎችን እያገዝካቸው አብራችሁ ሥሩ” ብሎ የሥራ ኃላፊነት ሰጠው። ይህ ወጣት ልጅ ኢሜይል ለመጻፍ አሥር ደቂቃ ብቻ ይፈጅበታል፤ የእንግሊዘኛም ሆነ የኮምፒውተር ችግር የለበትም። ነገር ግን አሥር ደቂቃ ጻፍ ጻፍ ካደረገ በኋላ ቀሪውን ጊዜ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ያሳልፋል።

አይነሳም። ደሞዝ እየተከፈለው ቢሆንም፣ ታላቅ ሲመጣ የማይነሳ፣ ሥራ የማያከብር፣

እኚህ አባት ከውጭ ወደ ሥራ ሲገቡ እንኳ ልጁ ከአክብሮት የተነሳ ከመቀመጫው አይነሳም። ደሞዝ እየተከፈለው ቢሆንም፣ ታላቅ ሲመጣ የማይነሳ፣ ሥራ የማያከብር፣ በሥራ ሰዓት የግል መዝናኛውን የሚጫወት በመሆኑ ከሰውየው ጋር ሊግባቡ አልቻሉም። ቀጣሪው ሲጠይቃቸው፡- “ልጁ ትህትና የለውም፣ ግብረገብነት የለውም፣ የሥራ ሥነ-ምግባር አያከብርም፣ ለታላቅ አይነሳም፤ አሥር ደቂቃ ሰርቶ አሥር ሰዓት ይቀልዳል፣ ቲክቶክ ያያል፤ ደሞዝ እየተከፈለው በሥራው አይተገብርም” አሉት። ልጁ በበኩሉ፡- “እኚህ ሰውዬ በጣም ኋላ ቀር ናቸው፤ ቲክቶክ ላይ የሚያስቅ የቀልድ ቪዲዮ ልኬላቸው እንኳ አይስቁም፤ ዝም ብለው የድሮ ዘመን ሰው ናቸው፤ ሥራ እየሠሩ ዘመናዊ መሆን መዝናናት አይችሉም” ይላል። ይህም በሁለቱ መካከል ያለው የባህልና የዕሴት ልዩነት ያመጣው ችግር ነው። እሳቸው የሚያስቡበት የራሳቸው ዕሴት አላቸው፣ እሱም የሚያስብበት የራሱ ዕሴት አለው።

ሁለንተናዊ ማለት ምንድን ነው፤ ትጋት እና ዘመን የዋጀ ብቃት ደምሮ መያዝ ማለት ነው። ትጋትና ዘመን የዋጀ ብቃት ግን ባህል ደግሞ ያበላሸ መሆን የለበትም ማለት ነው። ግብረገብነት ያጠፋ መሆን የለበትም ማለት ነው። ሁለንተናዊ ብልጽግና ስንል ያንን በሙሉነት ማረጋገጥ ነው። አዕማዱስ? ኢኮኖሚ ለሁሉም፣ ከሁሉም፣ በሁሉም ሲፈጸም ነው። ፖለቲካ አካታችና አሳታፊ ሲሆን፣ ማህበራዊ ትውልዳዊ ልማትን የተንተራሰና ያሰበ ሲሆን። አንድ በአንድ እንያቸው፡- ኢኮኖሚው መዋቅራዊ እና ሰው ወለድ ጭቆና ይወገድ ነው ያለው በኛ ስርዓት ውስጥ ስርአት ወለድ ጭቆና አይኖርም የሲቪክ ባህል መጎልበት አለበት። ክልሎች ይነቃቁ የነገዋን ሀገር ዛሬ እንስራ፣ ዕውቀት ቴክኖሎጂን እንቀበል እሳቤው ይሄ ነው። አሁን ተቃርኖዎች አሉ ለመልማት ማን ከለከለህ ኦሮሚያ እኮ በእርሻ በጣም ተሻሽሏል ማን ከለከለህ እንዳታርስ መሬት የለህም? ውሃ የለህም? አዲስ አበባ ኮሪደር የወንዝ ዳርቻ ልማት ተአምር እኮ ነው ማን ከለከለ? ወንዝ የለህም አንተ ጋር? ራስህን መጠየቅ አለብህ፣ ማን ከለከለህ? ተነቃቅተሃል? ክልል ላይ እንደፈለክ እንደተሰራ የተነቃቃህ ነህ፤ በቀና መንገድ ተወዳድረን ያለንን ለማውጣት ነው የምንሰራው ግን ፖሊሲው፣ አሰራሩ፣ ስልጠናው አንድ ነው ልምዱ አንድ ነው። ለምሳሌ ከተማ ላይ ሰምታችሁ ሊሆን ይችላል፣ የከተማ እሳቤ ሲነሳ በኢትዮጵያ ያሉ ከተሞች ከንቲቦች እኔ ቢሮ መጥተው ከተማ እንዴት እንደሚሰራ እንዴት እንደሚመራ ገለጻ አቅርቤላቸው ሀሳቤን ሰጥቻቸው ሄደው፣ ከሆነ ጊዜ በኋላ አዲስ አበባ ደግሞ ስራ ሲጀምር ኮሪደር መጥተው ስንጀምር ጎብኝተው፣ ከዛ ደግሞ የመጀመሪያው ኮሪደር ሲያልቅ ተጠርተው መጥተው እንዴት እንደተሰራ አይተው ነው የሄዱት። ማን ተማረ? አላቅውም።

የምንጠብቀው ነገር ሁለንተናዊ ብልጽግና የምናስብ ከሆነ ለሁሉም ያስፈልጋል ግን ከሁሉም ያስፈልጋል። መፍጠር ለሁላችንም የተፈቀደ ስለሆነ አትልማ የሚል ነገር ካለ

ያኔ ጥያቄ ይነሳል። አቁም እኛ ሳንሰራ እንዳትሰራ የሚል ነገር ካለ ችግር ነው። እኩል ዕድል ባለበት ቦታ ላይ ግን ፈጥረህ ከባቢህ መቀየር የሁላችን ስራ መሆን አለበት እንጂ አንዱ አንዱን ጠብቆ አይሆንም። መነሻ ሃሳብ፣ መሻገሪያ ድልድይ፣ መዳረሻ ብልጽግና ካልን በኋላ፤ ተሻጋሪው ማነው? ማነው የሚሻገር? የሚሻገረው ትውልድ ነው፤ አንተ አይደለህም ብልጽግናን የሚያጣጥመው ትውልድ ነው። ባለቤት እንዳለው ያንተ ሚናና ስራ ምን እንደሆነ ካወክ እናሳካለን ከተቀላቀለ ግን አናሳካውም።

ትውልድ ስንል አንደኛ ኢትዮጵያ ምን ትምሰል፤ ምክንያቱም የኢትዮጵያ መልክና ምሳሌ አከራካሪ አጨቃጫቂ ስለሆነ ብዙ ሃሳቦች የኢትዮጵያን ምስል በራሳቸው መንገድ ስለሚቀርጹ እና ግራ ስለሚያጋቡ ትውልዱ ኢትዮጵያ ምን አይነት መልክና ቅርጽ ይኑራት የሚለውን ጥያቄ ያነሳል። ሁለተኛ መንግሥትስ ምን ይምሰል? የመንግሥት አስተዳደር ስርዓት ምን ቢሆን ነው ህዝቦች በሰላም፣ በጋራ፣ በትብብር መኖር መበልጸግ የሚችሉት? ሦስተኛ ትውልዱ ራሱ ምን ይምሰል? ልንገነባ የምንፈልገው ትውልድ ምን አይነት ነው? እየፈጠርን ያለነው ትውልድ ግለሰባዊ፣ ማህበረሰባዊ፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ ሉዐላዊነቱ ምን ይመስላል? እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ግድ ይላል።

የመጀመሪያው እዚህ ባለን ሰዎች የተሟላ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ነገር ኢትዮጵያ ህብረ ብሄራዊ አንድነት ያለባት ሀገር ካልሆነች በቀር ሰላማዊና ልማታዊ ጉዞ ማድረግ አይቻልም። ህብረ-ብሄራዊ አንድነት ያለበት ሲባል አንደኛ አስተዳደሩ እውነተኛ ፌደራሊዝም የሚተገብር መሆን አለበት። እያንዳንዱ ክልል በህግ በተሰጠው ስልጣን ለሰላም፣ ለልማት፣ ለብልጽግና ካለ ጣልቃ ገብነት የሚተጋ መሆን አለበት። ምን እስኪሆን? የኢትዮጵያን የህልውና ጥያቄ እስከሚያደርግ ድረስ። ሁለተኛ ቋንቋ ብዝሃ-ልሳን የሚያስተናግድ መሆን አለበት። ቋንቋ ተናጋሪዎች ባሉበት ሀገር ውስጥ እነዛን መቀበል ካልቻልን በጋራ መቀጠል ያስቸግራል። ሁለት ሶስት ቋንቋ መልመድ ጠቀሜታውን ቅድም አንስቼላችኋለሁ። ሶስተኛ ማንነቶች ብዝሃ ማንነት የሚያቅፍ መሆን አለበት። ስለዚህ ህብረ-ብሄርነት ስንል አስተዳደሩ፣ ቋንቋው ፣ማንነቱ አካታች መሆን አለበት ነው። የወንድማማችነት እሴት ሲባልስ? ሌላውን እንደራሱ የሚመለከት ብሄርና ሀገራዊ ብሄርተኝነትን ማስታረቅ የሚችል፤ እኔ ኦሮሞ ነኝ ምንም ችግር የለውም ኦሮሞነቴ ኢትዮጵያዊ መሆኔን የሚያሰቃየኝ መሆን የለበትም። እኔ ሰው ነኝ ፣ እኔ ዐቢይ ነኝ ፣ እኔ ወንድ ነኝ እነዚህ ማንነቶችን አስታርቄ መጓዝ የሚችል መሆን መቻል ይኖርብኛል። አንደኛውን ገፎ ሌላውን በማኮስመን አብሮ መኖርን የሚያጠፋ እንዳይሆን መጠበቅ ያስፈልጋል። ሶስተኛው የሲቪክ ባህል ይጎልብት ሲባል በስምምነት፣ በመግባባት የጋራ አስታራቂ ተቋማት እና ህጎች መፍጠር ያስፈልጋል። ለዚህ ነው ሕገ መንግሥቱን እኛ

ስልጣን ስላለን አንቀደውም፤ ተወያይተን ህዝብ አወያይተን የህዝብ ግብዓት ወስደን ዘላቂ የሆነ ነገር ለመስራት ጊዜ ቢወስድም እንድከም ያልነው፤ አሳታፊ መሆን ስላለበት። ቀጣናዊ ትስስር ላይ ከሁሉም ጎረቤቶች በሰላም አብሮ ማደግን ታሳቢ ያደረገ በጋራ ለማደግ ጥረት የሚያደርግ በንግድ፣ በኢኮኖሚ የሚተሳሰር መሆን አለበት። ይሄ ማለት ብሄራዊ ጥቅምን ወደኋላ የሚያደርጉ መሆን የለበትም።

ሶስት የግንባታ መርሆዎች አሉት ትውልዱ፤ መደመር አፍርሶ የመጀመር የፖለቲካ ባህል ለኢትዮጵያ አይጠቅምም መቆም አለበት ብሎ ያምናል። ስለዚህም ማስተካከል፡- ያለፉ ስህተቶች የሚያርም የሚያርቅ። ማስፋት፡- የቀደሙ ድሎች ጠብቆ የሚያሰፋ። ማበርከት፡- ለዛሬና መጪው ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት የሚሰራ ሃሳብ እና ተቋም ሃብት ወረት ማንበር ማቆየት ያስፈልጋል። በምን ስትራቴጂ ነው የምንገነባው ያላችሁ እንደሆነ አንደኛው በጎ ፈቃድ ማገልገል መስጠት መሰጠትን ልምምዱ ባህሉ ያደረገ መሆን አለበት። በጃፓን ሀገር ጽዳት አስቸገራቸው ይባላል፤ እና መንግሥት ልጆች ከትምህርት ሰዓት ውጪ አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ ያስገድዳል። ልጆች ካጸዱ በኋላ እየተለመደ ሲሄድ ወላጆች ሶፍት ሲጥሉ ልጆች አንሺው አንሳው ይላሉ ምክያቱም እነሱ ስለሚያፀዱት ጠባቂ ሆኑ በዛ መንገድ ባህል ተፈጥሮ አሁን ጃፓን ቆሻሻም ማየት ብርቅ ነው፣ ጩኸትም ብርቅ ነው። እዛ እንደዚህ ሁከት የለም ሰው በሰላም ካመመው መተኛ ይችላል ከደከመው ማረፍ ይችላል እዚህ አይቻልም። ያን የሚቀይር ትውልድ ያስፈልጋል።

ሁለተኛ ዲጂታል አርበኝነት፤ ዲጂታልን ካልተቀበልን መጪው ዘመን መዋጀት አስቸጋሪ፣ አታካችም አደገኛ ስለሚሆን ቴክኖሎጂን የሚቀበል መሆን አለበት። 5 ሚሊየን ኮደሮች ያልነው ለዛ ነው፤ 5 ሚሊየን ኮድ የሚጽፉ ልጆች ካሉ ቴክኖሎጂው መሸከም ይችላሉ ምክንያቱም ከ5 በመቶ ያላነሰ ሰው ኮድ የሚጽፉ አለን ማለት ነው። አሁንም ኢንቨስት የምናደርገው 5 ሚሊዮን ኮደሮች ለነገው አስተማማኝ መሰረትን ይሆናል። ሶስተኛው የትምህርት ተሃድሶ አልን ብልህነትን የሚያነቃ የሚያነቃቃ መሆን አለበት። እኛ እየመራን ያለን ሰዎች ከሁሉ በላይ የስሜት ብልህነታችን ያደገ መሆን አለበት ሌላውን የማናቃቸውን ጉዳዮች ባለሙያዎች መጠቀም እንችላለን። የስሜት ብስለቱ ደካማ የሆነ ሰው ግን ችግር ነው። በጣም ችግር ነው፤ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ከልካቸው በላይ፣ ከስራቸው በላይ ያስጮሀሉ በተግባር ስራቸው አይጮሁም እነሱ ያስጮሁታል። የላቁ የተሻሉ ለመሆን ያሰቃዩናል በተገባር ግን ምን እያደረጉ ነው ስንል ቢሯቸው አይጮሁም፤ አይናገርም ስራቸው። ይሄ የስሜት ብልህነት ችግር ነው።

ሰው ሊያውቅ ይችላል ያለሁበትን ነገር ብሎ አለመገንዘብ ማለት ነው። ከሚሰሩባቸው

ሰዎች ጋር ሰላም የላቸውም ሌላ ስራ ግን ይመኛሉ፣ ባሉበት ሰላም የለም፣ ኢንዱስትሪው ሰላም የለውም ግን መንግሥት አዳዲስ ስራዎች እንዲያመጣ ይጠብቃሉ። ወጥ የሆነ ልህቀት፣ ወጥ የሆነ እድገት በሌላው ነገር ዝቅ ያረጋል ማለት ነው። በሆነ ጉዳይ በጣም ጎበዝ ሆነን በሆነ ጉዳይ ዜሮ ከሆነ ይጓተታሉ። የስሜት ብልህነት ላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ የአስተሳሰብ ብልህነት ላይ ካላደገ በቀር በሒሳብ፣ በፊዚክስ፣ በኢንጂነሪንግ ብቻ መጎበዝ ሰውየውን ሙሉ አያረገውም፤ ያ ደግሞ ማጎበረሰብ አይገነባም፣ ተቋም አይገነባም ማለት ነው። የእኛ ትምህርት ስርዓት ሁሉን የብልህነት ብቃት የሚያነቃ፤ የሚያነቃቃ መሆን አለበት።

የባህል ኢንዱስትሪ፤ የባህል አብዮት የስራ ልምምድ ትርፍ ሰዓት መስራት፣ በመንቀሳቀስ ውስጥ ያለ ልምምድ መፍጠር ያስፈልጋል ማለት ነው። ይሄኛው ትውልዱ ላይ ይሄንን ስንሰራ ነው የሚሻገር፣ የሚያነብር፣ የሚያቆይ፣ የሚያጸና ትውልድ የሚፈጠረው። መነሻ ያያል፣ መሻገሪያ ያያል፣ መድረሻ ያያል፣ ተሻጋሪ ያያል፤ ማነው አሻጋሪው? አሻጋሪው የሃላፊነት መቀላቀል ካለበት፣ የመሸከም ተግባር ተሰቶት እንድንሸከመው ከፈለገ ይዛባል ማለት ነው። ያንተ ስራ መሸከም ነው፣ ሰርቶ በላ ነህ። እዚህ ያለው ተሸክመህ፣ ድልድይ ሰርተህ፣ ትውልድ ሰርተህ፣ ማሻገር ነው ያንተ ፋንታ። የሚያርፈው ያ የተሻገረው ትውልድ ነው። እኔው ሰርቼ፣ እኔው ገንብቼ፣ እኔው አርፌ ካልክ ይቀላቀልና አይመጣም፤ ውጤቱ አይሳካም። አሻጋሪ ያልነው መንግሥት ካለንበት አረንቋ ወደ ምንፈልግበት ብልጽግና የማሸጋገሪያ መንገዱን የዘመነ ማጎበረሰብ፣ የበለጸገ ማጎበረሰብ ለመፍጠር ሁለት/ ሶስት ነገሮች ማየት ተገቢ ይሆናል።

የሽግግር ተዋንያን ሚና በመደመር በግልፅ ነው የተቀመጠው። መንግሥት፣ ገበያ፣ ማጎበረሰብ ሁልጊዜ ርዕዮተ አለሞች በነዚህ ጉዳይ ይሽከረከራሉ። ድርሻቸውን ወደ መንግሥት፣ ድርሻቸውን ወደ ገበያ፣ ድርሻቸውን ወደ ማጎበረሰብ በማጉላት እና ሌላውን በማኮሰስ የተሞከሩ ሙከራዎች በዓለም ላይ ያስገኙት ውጤትና ስብራት ታይቷል። ከዚህ ተምሮ ነው የሚወጣው የእኛ የስርአት አማራጭ። የገበያ ጉድለት፣ የመንግሥት ጉድለት፣ የስርዓት ጉድለት አለ አንደኛ በሊበራል ስርዓት ውስጥ ካፒታሊዝም የሚባለው መነሻ የሚያደርገው የመንግሥት ጉድለት አለ፤ የግል ተቋማት ወይም የግለሰቦች ቢዝነስን መቆጣጠር እና መምራት አለባቸው። የምርት ሂደት፣ የማከፋፈል ሁኔታ እና የአገልግሎት እና ምርቶች ግብይት በግል ተቋማት ቁጥጥር ስር መዋል አለበት። ይሄ በሚሆንበት ሰዓት የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር በፍላጎት እና አቅርቦት ይወሰናል ዋጋ፣ ሲመረት ባለ ፍላጎት ልክ ይወሰናል። ትርፍ ደግሞ ካለ ግል ዘርፉ ኢንቨስት ያደርገዋል። ተመልሶ ይፈሳል ወደ ማጎበረሰብ እና ምርት ክፍፍል እና ግብይት የግል ዘርፍ መቆጣጠር አለበት፤ የግሉ

ድርሻ መሆን አለበት፤ በውድድር እና ትርፋማነት መርህ ብቻ ነው እድገት የሚረጋገጠው አልያ ፈጠራ እና ፍጥነት አይመጣም ይላል። የመንግሥት ሚናስ ስትሉት የግሉን ንብረት ባለቤትነት የአእምሮ ንብረት ጥበቃ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ደህንነት ማረጋገጥ በቂው ነው ይላል።

እንደኛ ያሉ ሃገራት ትልቅ ጥያቄ ያነሳሉ መሠረተ-ልማት ማን ይገንባ ብለው። ለምሳሌ ከጓንዙ እስከ ጅቡቲ ያለ አንድ ካርጎ ከቻይና እስከ ጅቡቲ ፖርት የሚደርስበት ዋጋ እና ከጅቡቲ ፖርት አሶሳ ከጅቡቲ ጋምቤላ የሚደርስበት ዋጋ እኩል አይደለም። ከጅቡቲ ጋምቤላ በጣም ውድ ነው። ስንት ዓለም አቋርጦ የመጣው ካርጎ እኛ ጋር ከደረሰ በኋላ ከአንድ ጫፍ አንድ ጫፍ ለመሄድ ዋጋ በጣም ውድ ነው። ለምን? መሠረተ-ልማት ውስንነት አለ። ባቡር የለም የፍጥነት መንገድ የለም። ይሄንን ክፍተት ማን ይገንባው? ማን ኢንቨስት ያድርግ? ግል ዘርፉ እንደሆን መንገድ ላይ ኢንቨስት አያደርግም እንደምታውቁት። ለዚያም አልደረሰም። በዚህ ሂደት ውስጥ መቼ ነው እኛ ሰው ምንሆነው፤ መሠረተ-ልማት ገንቢ ኃይል ካልተፈጠረ ችግር አለበት በተለይ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት እንዲህ ያለውን ኢኮኖሚክ ስርዓት ሳቢ ቢያደርጉ ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም። የጠቀማቸው አሉ ከነእንከኑ ያም ቢሆን ጥቂቶችን በጣም ሃብታም አድርጎ ብዙዎችን አዳክሟል ወደኛ ሲመጣ ግን ክፍተቱ ይበዛል ይሉና ሁለተኛው ደግሞ የለም መንግሥት መር መሆን አለበት።

የገበያ ጉድለት አለ የግሉ ዘርፍ ትርፍ ብቻ ያግበሰብሳል ስግብግብ ነው። ስግብግብ ስለሆነ ትርፍ ብቻ ስለሚያስብ ፍትሃዊነት አይረጋገጥም ይላሉ። ስለዚህ መንግሥት የልማት አቅሞችን መቆጣጠር አለበት። መዋቅራዊ ሽግግርን በቀጥታ መንግሥት መምራት ይገባዋል ያኔ ነው ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ሊረጋገጥ የሚችለው ይላሉ። እሺ ይሁን መንግሥት ሲቆጣጠር ልማት ያምጣ ፍትህ ያረጋግጥ ግን ብልጽግና ቅድም እንዳልነው ፈጠራ እና ፍጥነት ይፈልጋል። መንግሥት ደግሞ አይፈጥንም ወይም ውስን ነው ፈጠራው። ፈጠራ እና ፍጥነት ከሌለ ደግሞ ያ የምናስበው ፍትህ ያ የምናስበው መወቅራዊ ሽግግር ሊረጋገጥ አይችልም። መቀየር አለበት ብሎ የመደመር መንግሥት ጉዳዩ የገበያ እና የግል ዘርፉ እና የመንግሥት ሳይሆን የስርአት ስብራት ነው ይላል። የስርዓት ውድቀት ነው ይላል። ለምሳሌ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ተራማጅ የፖለቲካል ልሂቃን እና የኢኮኖሚ ሊሂቃንን በእኩል አያይም። ተራማጅ የፖለቲካል ሊቃን ለህዝብ አሳቢ፣ ተቆርቋሪ፣ እራሳቸውን እንደ ሻማ አቅልጠው ለህዝብ የሚተጉ ናቸው ይልና ኪራይ ፈላጊነት ሲባል ግል ዘርፍ ነው ይላል ግን አይታችኋል እነዛ ተራማጅ አብዮታውያን ልሂቃን ዘራፊ ሆነው እነሱ ሀብታም ሆነው እንዴት የግል ዘርፍ እንዳቆረቆዙ አይተናል በተግባር። ያ የተዛባ ምልከታ

እነዛን ተራማጅ የፖለቲካል ልሂቃን ንጹህ ብዕዕ አድርጎ የማሰብ እና የኢኮኖሚ ሊቃን ደግሞ የኪራይ ፈላጊነት ምንጭ ናቸው ብሎ ማሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ተሞክሮ አከሰረ። ስለዚህ ምን አልን እኛ መንግሥት የነጠረ የታወቀ ሚና የሚጫወትበት፣ መንግሥት ከግል፣ መንግሥት ከህዝብ፣ መንግሥት ከአጋር ድርጅቶች ተቀናጅቶ የሚሰራበት የመደመራዊ ፈጠራ እና ፍጥነት ያስፈልጋል። ያ ነው ሁለንተናዊ ብልጽግና የሚያመጣው ለምሳሌ የመንግሥት ግል አጋርነት ኢትዮጵያ ውስጥ የገበታ ፕሮጀክቶች ጎርጎራ፣ ወንጪ ሰርቷል ምንም አጋንኜ አይደለም እስካሁን በዞርኩበት ዓለም ጎርጎራን የሚያክል ጥራትም ግዝፈትም ያለው ሪዞርት አይቼ አላቅም። ለምሳሌ ይሄን የማያምን ሰው ጎርጎራ ብቻ ነው መሄድ ያለበት ከዛ ይገባዋል። ግን የሰራው የመንግሥት ግል አጋርነት ነው፤ ግልም አይደለም ፕብሊክም አይደለም። ትብብሩ ያዋጣል ማለት ነው።

ወንጪ ባለፉት ሶስት ወራት ሶስት ወር ብቻ አስር ሺ የሳውዲ ሰዎች ወንጭ ጎብኝተዋል ነዐሺ፤ ሳውዲ ብቻ፤ ቦታ የለም አልጋዋ ትንሽ ናት ድንኳን እያሰሩ ማለት ነው። ቢበዛ አስቡት ምን እንደሚያመጣ ወንጪ አስር ሺህ ሳውዲ የሳበው የተሰራው የመንግሥትና የግል አጋርነት ነው፤ ያዋጣል ማለት ነው ይሄ ትብብር። ሁለተኛ በመንግሥትና በህዝብ ያለ ትብብር ለምሳሌ አረንጓዴ ዐሻራ ብዙ ጊዜ ብየዋለው 48 ቢሊየን ዶላር ህዝብ እና መንግሥት ባይተባበሩ ይቻል ነበር? ግል ዘርፉ ያደርገዋል ይሄን? መንግሥት ብቻውን ያደርገዋል? አንችልም መንግሥትና ህዝብ ለጋራ አላማ አብረው ሲቆሙ አሳኩት። ኮሪደር ማልማት አዲስ አበባ ማልማት ከጀመሩ በኋላ በሸርከና ማሕበር በአዲስ አበባ እና በግል ዘርፉ ልማት ጀምሯል። ምን አደረገ? መሬቱን ያለውን ሃብት ይዞ ባለሃብት አምጥቶ 70/30 ፣ 40/60 እያለ ዛሬ ግን አዲስ አበባ ውስጥ የሚሰሩ ህንጻዎች፣ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች ማንኛውም ነገር ቢያንስ 30 በመቶ ድርሻ አዲስ አበባ አለው።

በአንድ በኩል ስራ እየፈጠረ ነው በሌላ በኩል ከነዚህ የሚገኘውን ገቢ አስቡት ከነዚህ በሚገኝ ገቢ ነገ መልሶ በርካታ ልማት ሊያመጣ ይችላል። በምን ሰራ ይሄ? በመንግሥት እና በግል፣ በመንግሥትና በህዝብ ትብብር ነው። አሁን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማምጣት መንግሥት ጣልቃ መግብዓት አለበት ያልነው መሠረተ-ልማት ላይ ብቻ አይደለም፣ መንገድ ላይ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ ኢንሳና ሰው ሰራሽ አስተውሎት የክረምት ትምህርት ብለው ወደ 1000 የሚጠጋ ተማሪ ሁለቱ ክረምት ወስደው አስተምረው ብቁ አድርገው ያወጣሉ በነፃ፤ አሁን ደግሞ ሁለቱም ስታርት አፕ ህንጻ አላቸው። ሰው ሰራሽ አስተውሎት ውስጥ የመንግሥት ቢሮ አለ ከነኑ ደግሞ የስታርት አፕ ቢሮ አለ G+4 /G+5 የሚሆን ትንሽዬ ህንጻ ገንብተው ኮምፒውተር፣ ወንበር፣ ሁሉን ነገር ዋይፋይ አዘጋጅተው ተማሪ አወዳድረው ከነሃሳቡ መጥቶ ሶስት ወር፤ አራት ወር ተቀምጦ እነሱ ጋር አንድ ብር

ሳይከፈል ለቢሮ፣ ለኢንተርኔት ሳይከፍል ፕሮጀክቱን እየሰራ ከግል ዘርፉ ጋር አያይዘውት እያሳደጉ፣ እያባዙ ያወጡታል። መንግሥት በራሱ ገንዘብ፣ በራሱ ቦታ፣ በራሱ ጊዜ አዳጊ ትውልድን መልምሎ፣ አስተምሮ፣ አብቅቶ፣ ከኢንዱስትሪ ጋር አስተሳስሮ ማውጣት መቻል ልክ መንገድ እንደመስራት ያለው ጣልቃ ገብነት ነው። እንዲህ ያለውን ሁለንተናዊ ብልጽግና ሊያረጋግጥ የሚችል መደመራዊ ፈጠራ እና ፍጥነት ስናረጋግጥ ነው።

የስታርት አፕ ሀሳብ በጣም ከፍ ያለ ሃሳብ ነው። ቢሮ ሰርተህ፣ ኮምፒውተር አዘጋጅተህ፣ ጎበዝ ወጣት ታዳጊ አምጥተህ፣ አሰልጥነህ፣ ፕሮጀክት አሰርተህ፣ መንገድ መርተህ፣ ፕሮጀክቱን ደግሞ ገበያ እንዲወስድ አገናኝተህ፣ ከባለሀብት ጋር ስራ እንዲፈጥር አድርገህ መውለድ ብዙ በአፍሪካ ምድር የተለመደ ልምምድ አይደለም። እንዲህ ያለውን ነገር በመስራት ነው የስርዓት ጉድለት የምንሞላው እንጂ ሀብታሙን ኪራይ ፈላጊ ነህ እያልን፤ ሰጪ ነው እንጂ ተቀባዩን ብጹዕ እያደረግን፤ ተቀባዩን ሳንነካ፣ ሰጭውን ደግሞ ኪራይ ፈላጊ ብለን የምናመጣው ልማት የተሟላ ብልጽግናን አያረጋግጥም። በነገራችን ላይ እነዛ ተራማጅ የፖለቲካ ልሂቃን የተባሉ ሰዎች በጣም በጣም ሃብታሙ ግለሰቦች፣ ሀብታሞች ቢታዩ እነሱ ናቸው። በዱባይ፣ በአዲስ አበባ በምናምን በጣም ሃብታሞች እነሱ ናቸው። የተዛባ ምልከታ ነበር፤ ውጤቱም የፈረሰ ነው፣ የከሰረ ነው። ከዚያ ወጥተን በእኛም በነሱም ያለውን ስርዓት ውድቀት ለይተን በስርዓት በቴክኖሎጂ አግዘን ክፍተት እዚህም እዛም እንዳለ አምነን ብንሰራ ግን ልክ አዲስ አበባ እንዳደረገው በቅርብ ዓመት 1.5 ትሪሊየን ሽርክ ማሕበር ኢንቨስትመንት መሳብ እንችላለን ማለት ነው። እንዲህ ባለው መንገድ ነው የሽግግር ስርዓቱ የሚረጋገጠው።

የመደመር ባህርያትስ፤ አንዱ የመደመር መንግሥት ባህሪ ምናባዊ ጥልቀትና ከፍታ ነው። ስራን ጀምር ሲባል ይሄ ጉዳይማ አይሳካም። ሲሳካ እና ስናይ ደግሞ፣ ማን አግዞ ነው? የሚለው ጥያቄ በብዙዎቻችን ጭንቅላት የሚመላለስበት ዋናው ምክንያት ሀብትን እንጂ ምንጭን ስለማናውቅ ነው። የሀብትና የምንጭ ዝምድናን በትክክል ያልተረዳ ሰው የሚያገኘውን አንጡራ ሀብት፣ አንጡራ ዕውቀት፣ አንጡራ ጉልበት ደምሮ ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። ሀብት ማወቅ ያስፈልጋል፣ ምንጩ ተፈጥሮ ነው፣ ሀብት ከዛ የሚቀዳ ነው። የሰው ሀብት ሲባል፣ የሰው ባለቤቱ ምንጩ ተፈጥሮ ነው። ማዕድን ሲባል ምንጩ ተፈጥሮ ነው። ማዕድን ከምንጭ የተቀዳ ሀብት ነው። ብዙዎቻችን ሀብትን ሳናይ ምንጭ፣ ከሀብትም የካፒታል ሀብት ብቻ ስለምናይ ሌሎችን አናንቀንና አሳንሰን፣ አሰናስለን የምናመጣውን ልማት ማሰብ አንችልም። ምናባዊ ጥልቀትና ከፍታ ያለበት ምክንያት መደመር፤ ሀሳብ ማለት ምን ማለት ነው። ስርወ ቃሉ የቃሉ መሰረት ሀሳብ ማለት መመልከት ማለት ነው። ሀሳብ ማለት ማየት ማለት ነው። በኋላ አድጎ አድጎ የተሰናሰለ ሃሳብ የሚለው ጥቂቷን

ዘር ከማየት ተነስቶ የሚሰናሰን ሃሳብ ሆኖ፣ ንድፍ ሆኖ የሚተላለፈው። ምናብ ማለት ምን ማለት ነው? ምስእል ማለት እኮ ነው፤ በምእናብ መመልከት መቻል ከመመልከት ይመጣል። ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ እንዳነሳውላችሁ የግራ አእምሮአችን እና የቀኝ አእምሮአችን ስራ ለየቅል ነው የግራው ማሰብ፣ መተንተን፣ ቋንቋ ነው። ማድመጥ፣ መረዳት፣ መናገር የግራ አእምሮአችን አካል ነው። በምስል ማየት ግን የቀኙ ነው። ምእናብ በቀኝ ጭንቅላት የሚሰራ ነው። ቀኙን አደንዝዞ ግራውን ብቻ መጠቀም ወይም ግራውን አደንዝዞ በቀኙ ብቻ ማየት ሙሉ ብልጽግና አይመጣም መሰናሰል አለበት። ምናባዊ እይታ በጊዜና በቦታ ያልተገደበ ተሻጋሪ ምልከታ ሊኖረን ይገባል ጊዜ ሳይገድበን፣ ቦታ ሳይገድበን አልቀን፣ አርቀን አጥልቀን ማየት መቻል አለብን።

ሶስት አጥሮች ተሻግረን ማየት ስንችል ነው ምእናባዊነት ውጤታማ የሚሆነው። አንደኛ የዕውቀት አጥር በዕውቀት ውስንነት ሳንገደብ፣ የቦታ አጥር የጊዜ አጥር ተሻግረን ማየት ስንችል፣ ነገን አስበን ዛሬ ለመገንባት ያግዘናል። በግዜ ክፍልፋይ ውስጥ ተጨባጩ ዛሬ ነው፤ የሚጨበጠው ዛሬ ነው። ስለ ትላንትና ማወቅ ይቻላል፣ ማጥናት ይቻላል መለወጥ ግን አይቻልም፤ ትላንትናንም በሙሉ ማወቅ አይቻልም፤ በሙሉ ማወቅ አይቻልም። የተጻፈው ብቻ ነው ያለው ብዙ የቀሩ ጉዳዮች ስላሉ። እሱንም መቀበል እንጂ መለወጥ አይቻልም። ነገ ደግሞ ምንተልመው፣ ምንሰራው፣ የምናስበው ነው እንጂ በተሟላ መንገድ የሚገለጽ አይደለም ነገ የማይታወቅ ስለሆነ። በጊዜ ሽርፍራፊ ውስጥ የሚጨበጥ የሚዳሰስ የኔና የናንተ የሆነው አሁን ዛሬ ነው እሱን መጠቀም ስንችል ነው። የተሻለ ነገ ልጆቻችን ሊኖራቸው የሚችለው። የጥልቀት ከፍታ፣ የማሰናሰል ከፍታ፣ ከችግር ባሻገር የመሆን ከፍታ ያስፈልጋል ማለት ነው። ሁለተኛው የማድረግ ፍላጎትና አቅም ነው። እውነታውን የተረዳ ለእውነት የሚጎዳ አመራር ያስፈልጋል። በትጋት የሚሰራ በአርአያነት የሚመራ ትጋት ከቦታ ቦታ ይለያያል ምንም ጥርጥር የለውም።

አንዳንዶች እንደ አንበሳ የሚተጉ አሉ፤ ስለሰሩም ውጤት አይተናል። በዛው ልክ ደሞ የማይተጉ አሉ፤ ጀምሮ የሚፈጽም፣ አልሞ የሚጨብጥ መሆን አለበት ባህሪያቱ። እንደ መንግሥት የመደመር መንግሥት ካሉት ባህሪያት አንዱ በአራቱ አይ (I) የሚነሳው ነው፤ የመጀመሪያው ፍላጎት ነው። ለብልጽግና፣ ለማደግ፣ ለመለወጥ ፍላጎት አለ ወይ? ሁለተኛ ፍላጎት የወለደው ሀሳብ አለ ወይ? ሀሳቡን ከግለሰብ ወደ ማኅበረሰብ፣ ከአንድ ሰው ወደ ተቋም የመለወጥ ተቋማዊ የማድረግ ጅማሮና ስራዎች አሉ ወይ? ተቋም ተግባራዊ ያደርጋል ወይ? ፍላጎት፣ ሀሳብ፣ ተቋም፣ ትግበራ አራቱን አይ ሲሟላ ፍላጎትና አቅም ወደሚጨበጥ ነገር ይቀየራሉ ማለት ነው። ተስፋ ማጣት ፍላጎትን ይገለዋል፤ አቅም የቱንም ያህል ቢገዝፍ ፍላጎት ከሌለበት ትርጉም የለውም። ተስፋ በማድረግ ፍላጎት

መጨመር፤ ፍላጎት በመጨመር የማድረግ አቅም ማሳደግ ያስፈልጋል፤ የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው። ፍላጎት ለመኖር፣ ለመዝለቅ፣ ለመቀጠል ሁላ የሚያስፈልገን ነገር ነው። በ1950ዎቹ ሳይንቲስቶች አንድ ምርምር አካሂደው ነበር አይጦች ላይ በርከት ያሉ አይጦች ወስደው ምርምር ሰሩ። አይጦችን በውሃ የተሞላ ገንዳ ውስጥ ጨምሯቸው። እነዛ አይጦች ለ 15 ደቂቃ ብቅ ትልቅ ብቅ ትልቅ እያሉ እራሳቸውን ለማዳን ሙከራ አደረጉ። ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ መውጣት አንችልም፤ የመዳን ተስፋው የመነመነ ነው ብለው ያን ሙከራ አቋርጠው ወደ ውሃው መስጠም መግብዓት ጀመሩ ብቅ ጥልቁ እየቀረ መስመጥ ጀመሩ ያኔ ሳይንቲስቶች ተስፋ እንደቆረጡ አውቀው አይጦቹን አወጧቸው። ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላ ሁለተኛ ጊዜ በመሰል ገንዳ ውስጥ አስገቧቸው እነዛ 15 ደቂቃ ሞክረው ተስፋ ቆርጠው የተዉት አይጦች በሁለተኛ ሙከራ ስልሳ ሰዓታት እየወጡ እየገቡ ራሳቸውን ለማዳን ሙከራ አደረጉ ስንት እጥፍ 240 እጥፍ ቀድሞ ከነበረው ሙከራ ሞከሩ፤ ለምን? ባለፈው ሞክረው ስለዳኑ መዳን ይቻል ይሆናል ብለው ስላመኑ ከ15 ደቂቃ ወደ 60 ሰዓት አሳደጉት። ለምን? ተስፋ ስለያዙ ይሄ ሳይንሳዊ ሙከራ ነው ምርምር ነው። ተስፋ ያለው ሰው፣ የሚሞክር ሰው፣ የሚተጋ ሰው ነገን አርቆ የሚያይ ሰው ነገን የላቀ ውጤት ሊያመጣ ይቻለዋል። ያ ደግሞ እንዲሆን ተላማጅነትና እና ተለማጭነት ያስፈልጋል ተላማጅነት እና ተለዋዋጭ ዝግጁነት ያስፈልጋል።

ተመልከቱ እቺን እስስት የምትባለው ማለት ነው እዚጋ የዚህኛውን ከለር ይዛለች፤ እዚያጋ የዚህኛውን ከለር ይዛለች እራሷን አላምዳ ህልውና ለማረጋገጥ ከጥቃት ለመታደግ ሞክራለች። ይሄ ሚሰራባቸው ጊዜዎች አሉ ፕራግማቲስት መሆን ያስፈልጋል በሂደት መሻሻልም ያስፈልጋል ቅድሚያ መስጠትም ያስፈልጋል። እዚህ ጋር ፕራግማቲክ ሆና መላመዷ ጥሩ ቢሆንም አስፈላጊ በሚሆንበት ሁኔታ ተሻሽላ መዝለል ይጠበቅባታል። ይሄኛውን ደሞ እንመልከት፤ የአሳው ጃር ይሄ ነው ብዙ አሳ በትንሽ ጃር ውስጥ በትንሽ ውሃ ውስጥ አሉ። ይሄኛው አሳ ግን ወሰነ፤ ከፊት ለፊቴ ይሄን የሚያክል ጃርና ውሃ እያለ ዝም ብዬ አልቀመጥም ብሎ ከዚህ ዘሎ ለመግብዓት ሞከረ። ይሄ ሙከራ አደጋ አለው፤ ሞት፣ አለመከናወን፣ አለመሳካት ሊያስከትል ይችላል። እብድ ያስብላል፣ ጊዜያዊ ህመም ሊያስከትል ይችላል ዘላቂውን ግብ አተኩሮ የማይነሳ ማንኛውም ሰው ሹክሹክታውን፣ ወሬውን፣ ሃሜቱን ከሰማ የሰላ ትጋት የማያደርግ ከሆነ በጩኸት የሚሸበር ከሆነ ይሄን አይሞክርም ይሄ ሪስክ አለው። አልፎ አልፎ መላመድ ብቻ ሳይሆን መሻሻል ያስፈልጋል መስፈንጠር ያስፈልጋል። ይሄ አይነት ሙከራ ግን ፈተና አልባ፣ ውድቀት አልባ፣ ጩኸት አልባ መሆን አይችልም። ከተለመደው ልምምድ ባሻገር ስለሆነ ጩኸቶች ይኖራሉ ያን ለመሻገር የፈቀደ መሆን አለበት።

የሽግግር ትስስር በመደመር መንግሥት ውስጥ ሶስት ጉዳዮች ላይ ያጠነጥናል። አንደኛው መንደርደሪያ፣ ሁለተኛው መሻገሪያ ሶስተኛው መስፈንጠሪያ ነው። መንደርደሪያው አቅምን ከችግር ማላቀቅ ነው። ችግርን ከአቅም ከዕድል ማላቀቅ መንደርደሪያ ነው። መሸጋገሪያው መደላድል መሰረት መጣል ነው። መስፈንጠሪያው ማሳለጥና ማስተሳሰር ነው። ሰሞኑን ያያችኋቸውን ርዕሰ ጉዳዮች አንድ በአንድ ስናይ ከተማና ግብርና መንደርደሪያ ናቸው። አቅምን ከችግር ማላቀቂያ ናቸው። ቱሪዝም እና ማዕድን መሸጋገሪያ ናቸው። መደላድል የሚፈጥሩ መሰረት የሚጥሉ ናቸው። ኢንዱስትሪ መስፈንጠሪያ ነው ዲጂታል የሚያስተሳስር ነው። በጉብኝታችሁ ግብርና አይታችኋል፣ ከተማ አይታችኋል፣ በተወሰነ ቱሪዝም አይታችኋል፣ ኢንዱስትሪ አይታችኋል፣ ዲጂታል አይታችኋል ለምን መንደርደሪያ፣ መሻገሪያ፣ መስፈንጠሪያ፣ ማስተሳሰሪያ ዘርፎቻችንን በድምር መገንዘብ እንድትችሉ ነው።

አንድ በአንድ እንይ ግብርና አንደኛ በአዲስ እይታ መምራት ፣የአመራሩን ሙሉ እገዛ መስጠት፣ የግሉን ዘርፍ ማሳተፍ፣ ማህበረሰቡን ባለቤት አድርጎ የስራው አካል ማድረግ ያስፈልጋል። ለምን? ግብርና አዳጊ ሚች ነው ምርታማነት እየጨመረ ነገር ግን በኛ ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለው ድርሻ እየቀነሰ ነው የሚሄደው እኛ ግብርናን እንደ አንድ መነሻ ዘርፍ የወሰድነው አቅሙን ገና አሟጠን አልተጠቀምንበትም ስለዚህ ከተረጂነት ወደ አምራችነት መቀየር አለብን ያን ለማድረግ መሬቱ፣ ውሃው፣ ጉልበቱ አለ፣ ምርምሩ አለ። ሙከራዎች አሉ።

በርትተን ብንሰራ ተረጂነት ታሪክ አምራችነት የእኛ የነገ መገለጫ መሆን ይችላል!

ለዚህ ደግሞ የገጠር ሽግግር እናረጋግጥ። የገጠር ሽግግር ማለት በነፍስ ወከፍ አምርቶ ከመብላት ምንበላውን ለነገ የምናቆየውን ተሻግረን ለገበያ ምናወጣው ምርት ይኑረን። ከነፍስ ወከፍ ወደ ገበያ ይሸጋገር በእያንዳንዱ አርሶ አደር ማሳያ ያለው ከመብላት ያለፈ ይሁን፤ ለክፉ ቀን ከማቆየት ያለፈ ይሁን ለገበያ ምናውለውን ያክል እናምርት ያን እንድናደርግ ምርጥ ዘር እንጠቀም፣ ማዳበሪያ እንጠቀም፣ ኤክስቴንሽን ሙያተኛ እንጠቀም፣ ኩታ ገጠም እናድርግ፣ ማሽን እንጠቀም የመሆን እድሉ አለ ግብርናን ከአንድ ብቸኛ ከሆነ እሳቤና አሰራር ወደ ብዝሃ ገጠር እንቀይረው ግብርና ማለት እንስሳትም፣ አሳም፣ የባዮጋዝ ኃይልም ብዝሃ አቅጣጫ ትግበራ ያሉበት መሆን ይችላል፤ ግብርና ሲባል በሬና ገበሬ ብቻ አይደለም ከዛ ያለፈ ሚና እንዲጫወት ማድረግ ይቻላል። የአኗኗር ዘያችንስ? ከመበተን ወደ መሰብሰብ፤ ከጭቃ ወደ ጡብ መሸጋገር አለበት። እንጨት ማገዶ ከመጠቀም ባዮጋዝ ወደ መጠቀም ማደግ አለበት። የአርሶ አደሩ አርሶ የማምረት ሂደት

አይበገሬ መሆን አለበት። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚቆም መሆን የለበትም። እና ምን እናርግ? የጀመርነውን እናባዛ! አዳዲስ በየአከባቢያችን እንፍጠር! እንጀምር! በአርሶ አደሩ አርብቶ አደሩ ኑሮ ይገለጥ ለውጡ!

አርሶ አደር ቡና ሸጦ ሀብታም ከሆነ፤ አርብቶ አደር ወተት ሸጦ የተሻለ ኑሮ ካለው፤ ህይወቱን በመቀየር እናረጋግጠው፤ ግብርናችን የአርሶ አደሮቻችን ህይወት የቀየረ ከመብላት ያለፈ ለክፉ ቀን ከማቆየት ያለፈ ገበያ የሚያረጋጋ፣ ከገበያ አልፎ ደሞ ወደ ውጭ ወጥቶ ተጨማሪ ሃብት የሚያመጣ እናድርገው ነው። ሁለተኛ ከተማ መስፈንጠሪያ ነው፤ ከተማ ላይ የጀመርነው ስራ ወሳኝ ነው። በመደመር መንግሥት የቅይጥ ባህል መፍጠሪያ ማዕከል የሆነውን ሳናለማ መደመርን ማሰብ አንችልም ምክንያቱም ከተማ አዳጊ ነው። እንደ ግብርና አዳጊ ሚች አይደለም። አሁን እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ከ4 በመቶ በላይ እያደገ ነው። በቀጣይም እያደገ ነው የሚሄደው። ይሄን የሚያድግ ነገር ከአሁኑ አውቀን በእቅድ፣ በዕውቀት እንምራው መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን በስርዐት መኖር የምንችል፤ ህዝባዊነትን የተላበሰን መሆን አለብን። መሠረተ-ልማት ብቻ ሳይሆን ላዕላይ ላይም የሰራን መሆን አለብን።

የመደምር መንግሥት ከተሜነትን የሰው ልጅ የብልጽግና መዳረሻ ነው ብሎ ያምናል!

ከተሜነት በእቅድ እና በዕውቀት ካልተመራ አይደረስበትም። ማህበራዊ እይታ ከተሞች የቅይጠ ባህል መፍጠሪያ ናቸው። ከተሜነት ደግሞ ስርዓት ያለው ህብራዊ አንድነት ነው። ኢኮኖሚያዊ እይታውስ ከተሞች ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለስራ ፈጠራ ማዕከል ናቸው። ፖለቲካዊ እይታ ውስጥ የዳበረ የፖለቲካ ስርዓት ማፍለቅ የሚቻለው ከተሞች ውስጥ ነው። የሲቪክ ባህል መሰረት የውይይት የንግግር ባህል የሚገነባው ከተማ ውስጥ ነው። በነዚህ ምክንያት ከተማና ከተሜነት በዕውቀት መመራት አለበት እንጂ በከተማ መሃል ሸንት ቤት እንዲያልፍ ማድረግ ከተማን ማቆሸሽ ከዚያ በሽታ መውለድ ተገቢ አይደለም። ውሃችን ንጹህ ሆኖ ለጓሮ እርሻ መሆን ሲገባው አጠገቡ መቆም መኖር የማያስችል ሽታ እንዲፈጥር መፍቀድ ከተማና ከተሜነት በወግ እና በእቅድ ካለመምራት ሚፈጠር ችግር ነው። ለዚህም በአዲስ ራዕይ እና አስተሳሰብ እንምራ፤ ከግብዓት እስከ ገበያ በፈጠራ ማገዝ አለብን። የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሳደግ አለብን። ማጎበረሰብ ማስተባበር፣ ማሰራት፣ ማንቃት፣ ማስጠበቅ አለብን። ትውልዱን መታደግ አለብን፤ ከጫት ቤት መናጠቅ አለብን፤ ከሸሻ መናጠቅ አለብን። ፓርክ ስንሰራ ስታድየም ስንሰራ የእግረኛ መንገድ ስንሰራ ለዜጎቻችን ዛሬ ሳይሆን በስተእርጅና የተሻለ ጤና እንዲኖራቸው ያስችላል። ከተሜነት መሠረታዊ ነገር ነው በዕውቀት እንምራው፣

በቅርበት እንምራው፣ እየኖርንበት እንምራው ያን ስናደርግ ብልጽግናን እናረጋግጣለን። ሲንጋፖር እንደ ፒያሳ ነበረች። ወሰኑ፣ ጨከኑ፣ ቆፈሩ፣ ጎተቱ፣ ሰሩ፣ ተከሉ አሁን በዓለም ምርጥ የሚባል ከተማ፣ ንጹህ ከተማ ፈጠሩ። እኛም እንችላለን እንስራ ነው!

ቱሪዝም ቱሪዝምን ከቅርስነት ወደ ቁርስነት እንቀይረው ነው፤ ቅርሱ አለ ግን ቁርስ መሆን አልቻለም። ትላልቅ ቅርስ ይዘን ወደ ቁርስ መቀየር ባለመቻላችን የገንዘብ ምንጭ መሆን የሚችሉ ቅርሶች መጠገን እንኳን ወደማንችልበት ደረጃ ወርደዋል ነው። የእኛ ቅርሶች ወደ ቁርስ ይቀየሩ ወደ ቁርስ ለመቀየር ደግሞ ዘመኑን እንገንዘበው አሁን ያለው ዘመን አሁን ያለው ትውልድ አሁን ያለ ጎብኝ እሴት ገንዘብ እና ተሞክሮ ደምሮ የሚያይ ነው። ቅርስ ብቻ ስላለህ መጥተው አያይህም ለሚያወጣው ወጪ የሚመጣጠን አገልግሎት፤ የሚመጣጠን ከባቢ፤ የሚመጣጠን ሰላም መኖሩን ማረጋገጥ ይፈልጋል። ምክንያቱም አሁን ያለው እንደ ድሮ በጀልባ ሀገር አቋርጦ የሚጓዝ ሰው አይደለም። መስእብ አሉን ግን መዳረሻ የለንም። መስእብ እና መዳረሻ አዋህደን እንስራ። ማረፊያ በሌለበት መስእብ ስላለ ብቻ በበቂ ደረጃ ሰው አይመጣም። እንዳልኳችሁ ባለፉት ሶስት ወራት አስር ሺ የሳውዲ ዜጎች ወንጪን የጎበኙት መስእቡ ብቻውን ባለበት ሰዓት አልመጡም መዳረሻም ስለሰራን ጭምር ነው። ሁለቱ ተደምሮ መሆን አለበት ገበያ ላይ እናልም ሁሉንም ማሰብ አንችልም ለኛ ወጪ፣ ለኛ ባህል፣ ለኛ አየር የሚመጥነውን ሰው ለይተን እናምጣ ለወንጪ የሚመች ጎብኚ አለ፣ ለአርባ ምንጭ የሚመች ጎብኚ አለ፣ ለጅጅጋ ሚመች ጎብኚ አለ፣ ለሀረር የሚመች ጎብኚ አለ ያን ለይተን ለዚያ ጎብኚ እንስራ።

ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በርካታ አቅሞች አሉ ከአቅሙ አንዱ ጋስትሮኖሚ ነው። ጋስትሮኖሚ በብዙ ሀገራት የጎብኚ መስእብ እየሆነ ነው ያለው። ጋስትሮኖሚ ማለት የሃገር ውስጥ ምግቦች ለዚያ ጎብኚ እንዲመች አድርጎ ማዘጋጀት ከዚያም ባሻገር ደግሞ እሱም እንዲሳተፍ ማድረግ። ለምሳሌ እንጀራ ቅመስ ሳይሆን እንጀራ እንዲጋግር ማድረግ፣ ቀይወጥ ብላ ሳይሆን በሼፍ እየታገዘ ትንሽ እንዲሳተፍ ማድረግ ጥሩ ተሞክሮ መፍጠር፤ ሰው አርባ ምንጭ ሄዶ በጣም በርካታ የሃገር ውስጥ ምግቦች አሉ። ሰርተን ስንሰራ እያሳየን በክፍት ማዕድ ቤት እንዲሳተፍ እያደረግን ጎብኚው እንዲበላ ብናደርገው አርባ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ምግቡንም አይረሳውም። ጋስትሮኖሚ ማለት እሱ ነው። ጨንቻ አካባቢ ያለን ሽማ ከምናለብሰው ሽማ ሲሸመን ስራ ሞክር ብለን እንዲሰራ እያደረግነው ልብስ እንዴት እንደሚሰራ ብናሳየው፤ ያ በራሱ ትልቅ የጎብኚ መስእብ መሆን ይችላል። ፋሽን ታይቶ ማይጠገብ ፋሽን ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው። አለም አቀፍ ህይወት፣ የዱር ህይወት በጣም ብዙ ቦታ አሉ። አጥር አጥረን ብንጠብቃቸው በጣም ብዙ መጠበቅ የሚችሉ ጎብኚ መሳብ የሚችሉ አሉ አልጠበቅናቸውም።

አድሼንቸርስ አሉ፣ ሩጫ አለን፣ የሃይማኖት በዓላት አሉ። አሁን ለምሳሌ መስቀልን ብትወስዱ መስቀል አደባባይ የሚደረገው የመስቀል ፕሮግራም ብዙ ሀገር እኮ እንደዛ የለም፣ በጣም የሚያጓጓ ነው። እስላም ክርስቲያን አማኝ የማያምነው ሁሉም ሰው ቢያየው አጠቃላይ ስርዓቱ በጣም በጣም የሚስብ ነው። ሌላውም ሌላውም የእኛ በዓሎች በዛ መንገድ ለጎብኚ መስህብ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን ለጎብኚ ሳቢ ለማድረግ ለሁሉ ነገር ታሪክ ያስፈልጋል። የእኛ ነገር ደረቅ ነው መሳጭ ታሪክ የለውም።

በሰባተኛው አጋማሽ ክፍለ ዘመን አንድ ንጉስ ነበር በህንድ ሀገር ውስጥ ሸሃጀሃን ይባላል ይሄ ሸሃጀሃን የሚባል ንጉስ። ሚስቱ በወሊድ ምክንያት ሙንታዝ መሃል የምትባል ሚስቱ ትሞታለች፤ ስትወልድ ለሙንታል መሃዝ ህልፈት መታሰቢያ እንዲሆን መቃብሯን ሃያ ሁለት ዓመት የፈጀ ስራ ይሰራል፤ ይሄ ንጉስ የሷ መቃብር 22 ዓመት የፈጀው መታሰቢያዋ ማለት ነው። ያው እንደ ሃውልት አስቡት አሁን በህንድ ሃገር ውስጥ ታጅ መሀል የሚባል ቦታ ሰዎች በሰልፍ የሚጎበኙት የአንድ ንጉስ ባልተቤት በወሊድ ምክንያት አርፋ ለሷ የተሰራ መታሰቢያ መቃብር ቦታ ሰው ተሰልፎ ያያል አንተ ግን ላሊበላን የሚያክል፣ ሶፍመርን የሚያክል ምናምን ተሸክመህ ታሪክ መፍጠር ስለማትችል ለመስህብ መዳረሻ ስለማትሰራ የማየት የማሳየት ልምምድ ስለሌለህ፤ ስንት የሚንጋጋበት ቦታ መግቢያ መውጫ የሌለው፣ በለሊት ወፍ የታጀበ፣ ሽታው ማያስገባ፣ የተጣለ ሆኖ እኔና እናንተ የህንዱን በማድነቅ መከራችን እናያለን።

ታሪክ በጣም መሰረታዊ ነው። መጀመሪያ አቅሞቻችንን፣ ያሉንን አቅም እንለይ፤ ብዙ ነገር ነው ያለው፤ እንወቅ አንድ አይነት መሆን የለበትም። በየአካባቢ ያለውን ጸጋ ለይተን እንወቅ። ከዛስ እንጠብቅ፣ ያወቅነውን እንጠብቅ ወደሚታይ ወደሚጨበጥ ወደሚነበኝ ነገር እንቀይረው፤ ጉብኝቱ ደሞ እንዲያድግ እንነግደው። ይሄ የቱሪዝም ሚኒስቴር አይሰራውም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር አይሰራውም፤ የክልል ፕሬዚዳንት አይሰራውም፤ እንደ ማኅበረሰብ በጋራ ታሪካችን፣ ቅርሶቻን፣ ቦታችን የማድነቅ፣ የማወደስ፣ የማክበር እና የማሳወቅ ስራ እንስራ የሁላችን ስራ መሆን አለበት። የጋራ የሃገር ሀብት መሆኑን አምነን በሃሽታግ ብናስተዋውቅው፣ ከፍተኛ ሀብት ሊያመጣልን ይችላል። ለምሳሌ በዚህ ዘመን ሃሽታግ ብናደርግ #አክሱም #ሰሜንተራራ #ባሌ ብንል ስንት ዓለም መድረስ ይችላል?

ሌላውም ማዕድን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ እርግማን ይቆጠር ነበረ። እንደ እርግማን የሚያስበውን እሳቤ ሰብረነዋል፤ የለም አሁን እርግማን አይደለም። ነገር ግን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ አምጥቶ ለመሰረንጠር ሊያግዘን ይችላል፤ ምን ከሆነ የማዕድን መገኛ “መገኛ የማህበረሰብ ሀብት ነው” ይባላል። ሀብቱ ማህበረሰቡ ነው።

ማዕድን የህብረተሰቡ ሃብት ነው። ነገር ግን ሀብት ማስተዳደር የመንግሥት ኃላፊነት ነው። ማዕድን የዜጎች ሀብት ነው የሚያስተዳድረው ግን መንግሥት ነው። ለምን? ማዕድን ዓለም አቀፍ አይደለም። ውስን አላቂ አንድም ማኅበረሰብ የሚያስፈነጥር ስለሆነ የህዝብ ሃብት ነው የሚያስተዳድረው መንግሥት ነው፣ የሚያነቃቃው ግን ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ እድገትን ማረጋገጥ ነው። ለምሳሌ ጋዝ ለኢንዱስትሪ ሃይል ነው። ማንኛውም ኢንዱስትሪ እንደ ነዳጅ ይጠቅመዋል። ጋዝን ለአፈር ምግብ ነው፤ ማዳበሪያ ነው፤ አፈርን በጋዝ አማካኝነት ካልመገብከው አፈር አንተን አይመግብህም። በጋዝ አፈርን ትመግባለክ፣ አፈር ደሞ ምርታማነትን እያሳደጉ አንተን ይመግቡሃል የተያያዘ ሂደት ነው። ሶስተኛ ለቤት ኃይል ነው፤ የፍጆታ ወጪ ይቀንሳል፤ ሎጀስቲክስ ይቀንሳል፤ የትራንስፖርት አማራጭ ያሳድጋል ጠቀሜታው ብዙ ነው። ሌላው ማዕድን ይሄ ባህርይ አለው ታዲያ ምን እናርግ፤ ማዕድንን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ማቀድ አለብን። ስናቅድ ግኝት እና ማውጣት መለየት አለብን። የተገኘ የማዕድን ሀብት ከማውጣታችን በፊት ጥንቅቅ ያለ እቅድ ያስፈልገናል፤ አላቂ ጠፊ ነው ሊበላ ይችላል። አለ በቂ አይደለም፤ ያለውን ወደ ልማት ስንቀይር የተሟላ እቅድ ያስፈልገናል። አንዳንዱ ማዕድ በጊዜ ውስጥ ውድ እና ተፈላጊ ይሆናል። ለምሳሌ ውድ ማዕድናት የሚባሉት ሊቴየምን ብቻ ብንወስድ የዛሬ 15 ዓመት ሊቴም ምንም አልነበረም። ምንም አፈር በሉት ዛሬ ሊትየም የሁሉ ኮምፒዩተር፣ የሁሉ ኃይል አንቀሳቃሽ አካል ስለሆነ በ15 ዓመት በከፍተኛ ፍጥነት ተፈላጊነትና ዋጋው እያደገ መጥቷል። አሁን የማናውቀው የሆነ ማዕድ በሆነ ጊዜ እንደዛ ሊሆን ይችላል። ዛሬ አታውቀውም ማለት ነገ አይፈለግም ማለት አይደለም።

ስለዚህ ማቀድ በጣም መሠረታዊ ነው ማለት ነው። ነገር ግን ይሄ ዘርፍ ብርታት ይፈልጋል። ትጋት ይፈልጋል። ሀብቱን ከመጠቀማችን በፊት ከፍተኛ ድፍረት እና ብርታት ከሌለ አስቸጋሪ ነው እንደ ሌሎቹ ዘርፎች ቀላል አይደለም። ካፒታል ፈላጊ ነው፤ ከፍተኛ ፈተና አለው ኢንቨስት አርገህ ላታገኝ ትችላለህ፤ ሃብትህን ዛሬ ኢንቨስት አርገህ ነገ አታገኝም ይሄን ተገንዝቦ የሚያቅ ዘርፉ የገባው ሀብት ያለው ዕውቀት ያለው ውስን ነው፤ ያን ውስን ማደን ይፈልጋል። ዛሬ እኛ የመጨረሻ ተጠቃሚ ነን አናመርትም ላይገባን ይችላል፤ ልጆቻችን ሲያመርቱ ግን ያ ሀብት በጣም መሠረታዊ ነው የሚሆነው። ለዚያ ነገ ፈጠራን እንደሚያበረታታ ትልቅ ግብዓት እንደሆነ አስበን ነው በእቅድና በዕውቀት መጠቀም ያለብን። ለምሳሌ ወርቅ እንውሰድ ወርቅ በ2012 ኢትዮጵያ ኤክስፖርት ያደረገችው 28 ሚሊዮን ዶላር ነው። 28 ባለፈው ዓመት ኤክስፖርት ያደረገችው ሶስት ቢሊየን ዶላር ነው። በጥቂት ዓመታት ውስጥ ምን ያክል የማምረት አቅሙ እንዳደገ አስቡት።

ጋዙም፣ ፈርቲላይዘሩም፣ ብረቱም ምናምን እየወጣ ሲሄድ ይሄ ብዛት አለው። ኢትዮጵያ እርግማን ብቻ ሳይሆን የጋዝ የሰማችሁት ነው፤ የማዳበሪያ የሰማችሁት ነው፤ የመስታወት በቀደም አይታችኋል፣ መስታወት ካስጀመረች ማዳበሪያ ካመረተች፤ ለትራንስፖርት ጋዝ ካወጣች፤ ኃይል ካመረተች ጌታ ነች ማለት ነው፤ ጌቶች ምትባል ሃገር። ይሄ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎታችንን ይገለብጠዋል፤ ስለዚህ ማዕድን በእቅድና በዕውቀት መመራት አለበት። ክልሎች እና የማዕድን ሚኒስቴር ጥንቃቄ ማድረግ ያለባችሁ ፈቃድ ስትሰጡ ነው። አቅም ያላቸውን ለይተን አጥንተን፤ እንደዚያ ካልሆነ ጥፋት ስለሚያስከትል ሚኒስትሪውም ክልሎችም ጥንቃቄ አድርጉ ትልቅ ሃብት ነው፤ እንጠቀምበት ብልጽግናችን ለማስፈጠር የሚያገለግል ቱል ይሆናል።

ኢንዱስትሪ ሶስት ዓላማዎች አሉት፤ ኢምፖርትን መተካት፣ ምክንያቱም የውጭ ምንዛሬ ራስ ምታት ስለሆነ። ሁለተኛ በኤክስፖርት መቃኘት፣ የምናመርተው ምርት በዓለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆን አድርጎ መቃኘት። ሶስተኛ ሌሎች ዘርፎች ማገዝ፣ ግብዓት ማምረት፣ ከመዛባት ወደ ማንሰራራት ማደግ አለበት ተዛብቷል ኢንዱስትሪው። ፈቃድ ሰጥተናል መሬት የለም? መሬት አለ፤ ኃይል የለም? ኃይል አለ፤ ፋይናንስ የለም? ይሄን የተዛባውን ኢንዱስትሪ በቅርበት መርተን እንዲያንሰራራ እናድርገው አንድ መንግሥት ስንባል የተካነው ከልካይነት ነው።

ከልካይነትን ቀንሰን አስቻይነትን እናብዛ ግል ዘርፉ እንዲሰራ የሚያስችል አውድ እንፍጠርለት እንደገፈው!

ካልደገፍክ ኢንዱስትሪ አያንሰራራም፤ ካላንሰራራ ብልጽግና አይመጣም። እና ከከልካይ ወደ አስቻይ እንሸጋገር ከመንግሥት መር የኢንዱስትሪ ጉዞ ሚዛናዊ ትብብር እናረጋግጥ መንግሥትም ሚናውን ግሉ ዘርፍ ሚናውን ይጫወትና በጋራ ፈጠራን አሳልጠን እድገት እናምጣ። ከተነጣጠለ ወደ ተሰናሰለ እንውሰደው። እያንዳንዱ የጨርቃጨርቅ ምርት ግብዓት የሚሆነውን አንድ ግብዓት ከለየን በኋላ ለዚያም ሰው ፈልገን እናምርት። መሬት አለ፣ ጥጥ አለ፣ ጋርመንት ግብዓት ያገኛል፤ ጋርመንት ከተሰራ ጨርቃጨርቅ በቀላሉ ግብዓት ያገኛል ይሄን ማሰናሰል የእኛ ስራ ይሁን በተናጠል ያሉ ምርቶችን እያገናኘን ከA እስከ Z በተግባቦት በውስጥ እንዲመረት ማስቻል አለብን። ከብድር ወደ ኢንቨስትመንት እንቀይር፤ በብድር በንግድ ብድር የመጡ ኢንቨስትመንቶች ኢትዮጵያ ውስጥ አዋጭ አልነበሩም። ኢንዱስትሪ ፓርኮች አዳማ፣ ኮምቦልቻ፣ ሀዋሳ፣ ባህርዳር፣ ደብረብርሃን፣ ጅማ ሌላም ቦታ ሰመራ ተበድረን የገነባነው በብድር በዶላር ግለሰቦች መስራት እየቻሉ በውጭ ምንዛሬ በብድር ካመጣን በኋላ ሰዎቹ ታክስ አይከፍሉም፤ መንግሥት እዳ

እየቀፈቀፈ ለትውልድ ወረት ማኖር ሲገባን እዳ የምናቆይ ከምንሆን ግል ዘርፉን ብናግዝ እና ሃብቱ እንዲያወጣ ብናደርግ ለሀገር እዳ ሳናመጣ ከብድር ወደ ኢንቨስትመንት ሊያድግ ይችላል። በቅጡ መሬት ብናዘጋጅ፤ ኃይል ብናቀርብ፤ መሠረተ-ልማት ብናገናኝ፤ በህግና ፖሊሲ ብንደግፍ፤ በፋይናንስ ብንደግፍ፤ ኢንቨስትመንቱን መሳብ ይቻላል። እራሱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት አሰራራችንን መቀየር አለበት። በመደዳው ኢንቨስትመንት ሳይሆን መርጠን የሚያግዘንን ሰው እናምጣ። መጠበቂያ እናቁም እና ጂቪ እናስፋፋ ያን ብናደርግ ኢንዱስትሪው ይቀየራል ኢንዱስትሪው ዘርፎች ይቀይራል ኢንዱስትሪው የኢትዮጵያን እድገት ያሳልጣል የምንመኘውን ብልጽግና ያመጣል።

ዲጂታል መታወቂያ፤ ሞባይል ባንኪንግ፤ ዘመናዊ ክፍያ ዘዴዎች ተጀማምሯል ታቃላችሁ። ግን እንድትገነዘቡ ምፈልገው ነገር ሰው ሰራሽ አስተውሎት ሚባል ነገር፤ ኳንተም ሳይንስ የሚባል ነገር፤ የሰው ልጆች እንዴት እንደሚኖሩ እንዴት እንደሚሰሩ እንዴት ምእናብ እንደሚያስቡ ድረስ እየቀየረ ይገኛል ብትፈልጉም ባትፈልጉም። ቴክኖሎጂን መቀበል አለብን ለምን የኃይልን፣ የምርትን፣ የተሳትፎን ህግጋት እንደገና እየጻፈ ነው ያለው። ሰው ሰራሽ አስተውሎት በአዲስ መልክ ኃይል እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ፤ ምርት እንዴት እንደሚፋጠን፤ ተሳትፎ እንዴት እንደሚያድግ በአዲስ መልክ እየቀየረ ነው። ፋይዳ፣ ፓስፖርት፣ መሶብ፣ ሞባይል ባንኪንግ፣ ዘመናዊ ክፍያ ዘዴ፣ የከስተም አቶሜሽን፣ ገቢዎች፣ በመላ በሃገር ውስጥ አቅም እየጎለበተ እያደገ መሄድ አለበት። አንዱ ግብ በኋላ አስቀምጣለው አንዱ ግብ ቱሪዝም ስንት በመቶ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ተጠቅሟል፣ ፋይናንስ ስንት በመቶ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ተጠቅሟል፣ ግብርና ምን ያክል ተጠቅሟል ያንን መለካት ካልጀመርን ምንም እንኳን ዘመን ለማዋጀት ብንፈልግም አንደርስም። ቴክኖሎጂ መቀበል አለባችሁ ለሁሉ ስራችሁ፤ ማዕድንና ኢንዱስትሪ ቱሪዝም ሁሉን አስተሳስሮ የተሟላ ብልፅግና የሚያመጣው ቴክኖሎጂ ነው። እሱ ላይ በቅጡ ካልሰራን እና ካላስተሳሰርን በስተቀረ የምናስበውን ብልጽግና ማምጣት ያስቸግራል። መነሻ፣ መሻገሪያ፣ ተሻጋሪ፣ አሻጋሪ፣ አሻጋሪ የሚሻገርበት ስርዓት እና ስርዓት ዘርፎችን አየን ይሄ ጉዳይ እንዳይከወን እንቅፋት የሚሆነው ምንድነው? ይሄ ጉዳይ በእንጭጭ እንዲቀር እንዳይሳካ የሚያደርገው ሃሳብ አልቦነት ነው።

ወደ ሃሳብ ሉዓላዊነት መሻገር አለበት ዘር ከሌለ ምርት የለም የብልጽግና ዘር ሃሳብ ነው ሃሳብን መቅዳት ብዙ ጣጣ አመጣብን ምክንያቱም የተቀዳ ዘርና አረም የተቀላቀለ ስለሆነ እኛን የመሰለ፣ የእኛን የሚቀይር፣ ለኛ የሚሰራ ዘር መቅረጽ ችለናል። ያን መንግሥታዊና የጋራ አድርገን ብንሰራበት ለውጥ እናመጣለን። ሃሳብ አልቦ ማለት ምን ማለት ነው? በህዝበኝነት መታወርና መስከር በነባር ባህል መታጠር ይሄ ከናንተ ያልፍና ማጎበረሰብ

ጋር ይገባል። ለምሳሌ ተረጂነት ስንዴ ረዳኝ ትላለህ እንጂ ሁል ጊዜ ለማኝ እንድትሆን ነው የሚሰራው። ሁለተኛ መፍትሔ አልቦ ጩኸት ሃሳብ የለውም መፍትሔ የለውም ይጮሃል። በጊዜያዊ ችግር ይጮሃል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ይሄ ነው ሃሳብ አይደለም በየተራ መጮህ፣ በየተራ ተበዳይ መሆን፣ በየተራ ከሳሽ መሆን፣ በጋራ የሚል እሳቤ አለመያዝ። ሃሳብ አልቦን ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህች በኩል ብቻ ማየት ትችላላችሁ። ኢትዮጵያ መርከብ ናት። ሰዎች የሚሰቃዩት ግን መርከቡን አፍርሰው ጀልባ በመስራት ነው።

ጀልባ ውቅያኖስ አያሻግርም፣ መርከብ ግን ውቅያኖስን ያቋርጣል ትልቁን ሩቅ ሚወስድህን አፍርሰህ ትንሹን ብትሰራ ሰፈር ትቀራለህ እንጂ አትሻገርም ማለት ነው!

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፖለቲካ እንደዚህ ነው፤ መርከቧን ማፍረስ ጀልባ መስራት! ሌላ የቆረጥክ እየመሰለህ እግርህን መቁረጥ! ተመልከቱ እዚጋ ያለውን ዛፍ ዛፍ ቆራጩ ሁላ አንዱ አንደኛውን እግር ይቆርጣል ቀይ ባህር ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትም ባይ ማለት ነው። ሶስተኛው ደግሞ ይሄ ሰው የሚሰቃየው ይሄን ለማዳን ነው ታንቋል እንደምታዩት ቆርጦ ሊያድነው ነው፤ ይሄ ግን የሚሰቃየው አዳኙን ለመግደል ነው። ልክ ሲቆርጠው እሱ ድኖ እሱን ለመግደል ይሄን ደግሞ ተመልከቱት ባላንሱ ያለው በሰዎች መካከል ነው። ይሄኛውን ረግጦ በመጣል የሚኖር ይመስለዋል። ይሄ ካለ ብቻ ነው እሱ የሚኖረው፤ ግን ሊጥለው ይሞክራል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፖለቲካ እንደዚህ ነው።

ሃሳብ አልቦ የወለደው ፖለቲካ ሶስት ኤ አሉት መደመር እንደሚለው። አንደኛ አቀራረብ አንታጎኒስቲክ ነው። ጭፍን ተቃርኖ ያለበት ነው አጥቀራረቡ። ለሁሉ ነገር አንታጎነስቲክ ነው። ግንኙነቱ አስሜትሪክ ነው። ሚዛን የሳተ ነው፣ ሚዛን አይጠብቅም ውጤቱ ጭንገፋ ነው። ሃሳብ ከሌለ አመዛዛኝ እና ምክንያታዊነት የለም ይሄ ነው የመደመር መንግሥት የተሸከመውን ቀንበር የተሸከመውን ሃላፊነት በብቃት ሰርቶ ትውልድ እንዳያሻግር የሚያደርገው በሽታ ይሄ ነው።

ሃሳብ የምርጥ ነገር ዘር እና ስር፤ ስር እና ዘር ሳትቀበል ግንድና ፍሬ ለመልቀም መሞከር ውጤታማ አያደርግም። የሃሳብ ሉዓላዊነት በመደመር አሸናፊነት ለማምጣት ሚዛናዊ የሆነ ፍትጊያ ያስፈልጋል፤ ይሄም 3 ሲ እንለዋለን ትብብር እና ፉክክር በሚዛን፤ ቀጣይነት እና ቆራጥነት ፥ ያዝ ለቀቅ ሳይሆን ሂደቱ መርህ ላይ ተመስርቶ የማይቆራረጥ፣ የሚቀጥል መሆን አለበት። ሶስተኛ ለውጥ እና ተከታታይነት ነው አዎንታዊ ለውጥን በመፍጠር በማስተሳሰር በማስቀጠል መድረስ ያለበት ቦታ ማድረስ ነው።

የመደመር መንግሥት ታሪክን ከማውራት ይልቅ ታሪክን በመስራት እራሱን መግለጥ የሚሻ ነው። የሚያሻግር ሃሳብ የሚሻገር ህዝብ ይዞ ለለውጥ የሚተጋ እራሱን እንደ ሻማ አቅልጦ ትውልድ የሚያሻግር ስርአት ነው!

መደመር እንደ ዕድል ነው ብልጽግና ግን እንደ ድል ነው። መደመር ዕድል እንጂ ድል አይደለም ድል የሚያረገው ትጋት ነው ስራ ነው። የመደመር ሃሳብ ውጤታማ የሚሆነው የሚቆጠር ነገር ሲያመጣ ነው ለዚያ ደግሞ ትጋት ይፈልጋል። ሃሳብ መግዛት ለሀሳብ መገዛት በሀሳብ መግዛት ልምምዳችን ስናደርግ መደመር ፍሬያማ ይሆናል። ቀመሩ ምንድነው የዚህ ሃሳብ አልቦን ገርቶ ለብልጽግና ተሰናስሎ የሚሰራው መንግሥት ቀመር ፍሪሊዮን ነው፤ በነፃ መከፈል ነው። በነፃ መስጠት ነው። ከትናንትና መቆንጠር ሳይሆን ለነገ ማበደር ነው። ከትናንትና በመቆንጠር የሚሰራ ነገ የለም ለነገ በማበደርና ወረት በማቆየት የሚሰራ የበለጸገ የሚሸጋገር ሀገርና ትውልድ ይፈጠራል። ሰውን የማትረፍና ገንዘብ የማድረግ ብለሃት በውስጣችን ያሉ ከውጭ የምንሸከማቸውም ሰዎች፣ ሰውን ማትረፍ ብልጽግና ብልሃቱ ስለሆነ ነው።

ትላንት በሌላ ጎራ የምናያቸው ሰዎች ዛሬ ወደኛ ተርታ መጥቶ የምናያቸው ዋናው ምክንያት ሰው ማትረፍ እና ገንዘብ ማድረግ የመደመር መርህ ስለሆነ ነው። ሰላም እና ብልጽግና የመደመር ቀመር ፍሬዎች ናቸው። ሃሳብና ሰው እና ተቋም ማገናኘት ነው የመደመር ቀመር ሃሳብን ከሰው ሰውን ከተቋም አሰናስለን ውጤት ስናመጣ ማለት ነው። ይሄን በማድረግ በዚህ ቀመር ሀሳብ አልቦነትን ገርተን የመደመር መንግሥት ጫንቃ ላይ የተጫነውን ኢትዮጵያን ከአረንቋ አውጥቶ ወደፊት የማሻገር ተጋድሎ በብቃት እንድንጋደል ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለኛ ከልካይ ሳይሆን አስቻይ እሳቤ የያዘ አመራር ይፈልጋል። ይሄን ማድረግ ከቻልን የሚቀጥሉት አምስት፣ስድስት ዓመታት ካለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያን ሌላ ምዕራፍ የምናይበት ይሆናል።

ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች ጥርጥር የለውም እሱ ይሄ ዘመን የኢትዮጵያ ብልጽግና ዘመን ስለሆነ የሚቆም ነገር አይኖርም። እና ምን እናርግ እኛ ካላችሁ፤ አቅጣጫ አንደኛው ሉዓላዊነት ነው። ሉዓላዊነት የፖሊሲ ሉዓላዊነት፤ የምግብ ሉዓላዊነት፤ የሃሳብ ሉዓላዊነት፤ የተረጋገጠበትን ኢትዮጵያ መፍጠር፣ መስራት፣ መግራት ይጠበቅብናል። ሁለተኛ መስፋፋት ነው። የተጀመረ የገጠር ኮሪደር፣ የተጀመረ የከተማ ኮሪደር የተጀመረ የበጋ እርሻ፣ ኩታ ገጠም፣ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ፍራፍሬ፣ የጓሮ እርሻ እነዚህን ማሳደግ ማበራከት ያስፈልጋል። ሶስተኛ አገልግሎት፣ ዜጎች ከኛ በቅንነትና በሳቅ የተሞላ አገልግሎት ይፈልጋሉ። የዐይን ከለር እያየን መርጠን ሳይሆን ለዜጎች በሙሉ የሚሰጥ በፈቃድ ላይ

የተመሰረተ አገልግሎት አቅራቢ እንድንሆን ይፈልጋሉ አገልጋይነት ያልተላበሰ አመራር ብልጽግናን ማረጋገጥ እና ሃገር ማሻገር ይቸገራል። አራተኛ ዘላቂነትን ማረጋገጥ፤ የተገኙ ድሎች፣ የተገኙ ውጤቶች፣ የተገኘ ሰላም ተመልሶ እንዳይደፈርስ ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ። አምስተኛ አመቺ ሁኔታ መፍጠር፣ ለሚቀጥለው ምርጫ አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ምቹ ሁኔታ መፍጠር እነዚህ ሲሳኩ ስድስተኛው ሲ ይመጣል ማለት ነው።

እነዚህን ትንሽ በተን ላድርጋቸው አንደኛ የመቀነስ ግቦች፤ ኑሮ ውድነት እንቀንስ፣ ባለአንድ አታዝ እናስገባ፣ ያመረትነውን ከኮንትሮባንድ ታድገን የገበያ ትስስር ፈጥረን የከተማው ደሃ በደላሎች እንዳይመሰቃቀል በማድረግ የተረጋጋች ሀገር ለመፍጠር ስለሚያግዝ በርብርብ ኑሮ ውድነትን ሲባለአንድ አታዝ እናስገባ መቀነስ፤ ሁለተኛ ሌብነት መቀነስ መሬት ቸብቻቢው፣ ፍትህ ቸብቻቢው፣ ወርቅ ቸብቻቢው እንዲቀንስ እና ወደ ሃገር ሀብት እንዲገባ ማድረግ፤ እንደ ሀገር ዘረፋ ስላቆምን እንዳያችሁት አይነት ስራዎች ሰርተዋል፤ ግለሰብ ሌቦች ብንቀንስ ደሞ ያ ሀብት መልሶ ለሀገር ልማት ይውላል። ሌብነት መቀነስ ያስፈልጋል። ሶስተኛው መንደርተኝነት መቀነስ፤

በመንደር ተከበን ያለን ሰዎች እንደግ፣ እንብቃ፣ እንውጣ በመንደር ታጥረን ከቀረን ብልጽግናን አናረጋግጥም፤ እንቆራቆዛለን!

ከመንደር እሳቤ ከወረደ እሳቤ ያለውን አመለካከት እንቀንስ። አራተኛ ጠባቂነት እንቀንስ እነዚህ የመቀነስ ግቦች ናቸው። የዜሮ ግቦች ደሞ አሉ የቅድሙ መቀነስ ነው የዜሮ ግቦች 5 ናቸው። ዜሮ ተረጂነት፤ ዜሮ መሬት ጾም ማሳደር፤ ዜሮ ተፈናቃይ፤ ዜሮ ኮንትሮባንድ፤ ዜሮ ሽፍታ ይሄን የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ የዜሮ ግብ አርነ እያንዳንዱ ወረዳ በሱ ወረዳ በሱ ዞን ተረጂነት ዜሮ የማይታረስ መሬት፣ ዜሮ የሚፈናቀል ዜጋ፣ ዜሮ ኮንትሮባንድ፣ ዜሮ ሽፍታ፣ ሌባ አጭበርባሪ ዜሮ ካደረገ እንድናድግ ያግዛል። ማን? እያንዳንዱ ወረዳ የራሱን። ከዜሮ ግቦች ደግሞ የአንድ ግቦች እንይ፤ አንድ ገጠር ኮሪደር በወረዳ እያንዳንዱ ወረዳ ሞዴል የሚሆን ገጠር ኮሪደር በራሱ ወረዳ ይስራ፤ ከመንገድ የሸሸ ባዮጋዝ የሚጠቀም አንድ መንደር ይስራ።

እያንዳንዱ ወረዳ ህዝቡን ካስተባበረ ይችላል። በወረዳ አንድ የገጠር ኮሪደር እያንዳንዱ ወረዳ አንድ የምርት ማከማቻ በወረዳ ይስራ። ይሄ ምርት ማከማቻ የግድ ህንጻ መሆን የለበትም የግድ ትልቅ መሆን የለበትም፤ ቢያንስ ግን እያንዳንዱ ወረዳ ከሚመረት ምርት እንዳይባክን ማከማቻ በየወረዳው ይስራ። በቆሎ የሚያመርት ለበቆሎ የሰሊጥ፣ ለሰሊጥ የኑግ፣ ለኑግ የስንዴ፣ ለስንዴ የሩዝ፣ ለሩዝ ማከማቻ ለወረዳው የችግር ጊዜ የሚሆን ድሮ

ወላጆቻችን የክፉ ቀን የሚሉት ማለት ነው። እሱን እንገንባ ከተረፈስ ለገበያ እናወጣዋለን፤ ወደ ሌላ ወረዳ ወደ ሌላ ከተማ። እያንዳንዱ ወረዳ አንድ ኮሪደር አንድ የምርት ማከማቻ ቢሰራ። እያንዳንዱ ዞን አንድ ዞን አንድ የጎብኚ መዳረሻ ቢሰራ ያ የጎብኚ መዳረሻ ጎርጎራን ማከል የለበትም ወንጭን ማከል የለበትም የውሃ ፏፏቴ ካለህ ግድ የለም ቡና መጠጫ በድንጋይ በኮብልስቶን ወጥቶ ይስራበት ጠብቀው ሞር ስታገኝ ሞር የሚያይ ሲመጣ ይሰፋል ግን ቢያንስ ባንተ ዞን አንድ ሰዎች ሄደው የሚያርፉበት፤ የሚያርፈው ሰው የግድ ከሌላ ዞን አይደለም ከአንተው ከአንተ ወረዳ በዞናቸው ብዙ ወጪ ሳይወጡ የሚያዩበት ቦታ መስራት። ለምሳሌ ልክ እንደ ሃምበሪቾ፣ ሃምበሪቾ የሰሩት እዛ ያለው ከንቲባ የሰራው አስደናቂ ስራ ነው። እዛ አካባቢ ያለ ሰው ይዝናናበታል እናንተም ብትሄዱ መጥፎ ነገር አይደለም። የተሰራው ግን በከንቲባው በዞን አመራር ጥረት እና በህዝብ ብቻ ነው።

አንድ በዞን የትምህርት መዳረሻ፣ አንድ የእንሰሳት ጤና ማዕከል በአርብቶ አደር ዞን፤ አንድ የእንስሳት ጤና ማዕከል መገንባት አንዳንድ በወረዳ አንዳንድ በዞን ማለት ነው። አንድ የመሶብ አገልግሎት በከተማ ከተሞች ደግሞ አንድ፤ አንድ የሽያጭ ማዕከል በከተማ፤ ከተማ ሽያጭ ማዕከልና መሶብ ከሰራ ዞን አርብቶ አደር ከሆነ የእንስሳት ጤና ማዕከል፤ አርሶ አደር ከሆነ የትምህርት መዳረሻ፤ ወረዳ ገጠር ኮሪደር የምርት ማከማቻ፤ ክልል ጋር ሲደርስ ግን አንድ ስትራቴጂክ ኢንቨስትመንት በክልል፤ የሆነ ሰው ሃንት አድርገን ስትራቴጂክ የሆነ ኢንቨስትመንት የክልሉ ነገር የሚቀይር ኢንቨስትመንት ማምጣት 20 አያስፈልግም አንድ፤ አንድ አግሮ ፕሮሰሲንግ ማዕከል በክልል መገንባት አግሮ ፕሮሰሲንጉ የግድ ትልቅ መሆን የለበትም መጠነኛ ሆኖ የግብርና ምርታችን ፕሮሰስ የሚያደርግ አርብቶ አደር ከሆነ የወተት የስጋ ምርታችን ፕሮሰስ የሚያደርግ አንድ የአግሮ ፕሮሰሲንግ በክልል፤ መቀነስ አየን ዜሮ አየን አንድ አየን።

ሁለት ዲጂት እና ከዛ በላይ እድገት ማረጋገጥ የሚገቡን ግቦች፤ አንደኛ የሌማት ትሩፋት በተለይ አርብቶ አደር አካባቢ ግመል ያለበት ዶሮ መጨመር አሳ መጨመር የሌማት ትሩፋት የእንቁላል ምርታችንን በሁለት ዲጂት ማሳደግ መቻል አለብን። ፕሮቲን በበቂ ካላመረትን ስነ-ምግብ በበቂ ካላመረትን ያልቀነጨረ ትውልድ አንፈጥርም። የቀነጨረ ትውልድ ደሞ ብልጽግናን ዘላቂ ማድረግ አይችልም። ባለሁለት አኃዝ ኩታ ገጠም፤ ኩታ ገጠም አሁንም ይቀረናል በየሄድንበት የምናየው አሁንም የኩታ ገጠም ስራ በቂ አይደለም የግብርና ቢሮዎች የክልል ፕሬዚዳንቶች የኩታ ገጠም ስራ በበቂ አልተሰራም። ቢያንስ ባለሁለት አኃዝ እድገት ያስፈልገዋል ለምን እሱን ስናሳካ ምርታማነት ስለሚያድግ። ሶስተኛ የበጋ እርሻ ቢያንስ 10 በመቶ ቢያንስ ነው፤ የበጋ እርሻ ጾም ያደሩ መሬቶች ማስፋት በፓምፕ በመጠነኛ መስኖን ማብዛት ካልቻልን ሰው እየጨመረ ስለሆነ የአሁኑ ምርት በቂ አይደለም።

አራተኛ ኢንዱስትሪ የቆመ በማስነሳት በውስን አቅም የሚሰራው አቅም በማሳደግ አዳዲስ በመጨመር ቢያንስ 10 በመቶ እና ከዚያ በላይ እድገት ማረጋገጥ አለብን። ኢንዱስትሪ ጋር ተጠግተን ችግሩን ፈተን አግዘን እድገት ባለሁለት አኃዝ በላይ ማረጋገጥ አለብን። አምስተኛ ማዕድን፣ ከፍተኛ አቅም በየቦታው አለ ይሄ አቅም በጌጣጌጥ መልክ በኮንትሮባንድ እንዳይወጣ ቢያንስ 10 በመቶ ማደግ አለበት፤ ወርቅም ይሁን ፖታሽም ይሁን ታንታለም ይሁን ሊትየም ይሁን ማንኛውም የማዕድን ውጤት 10 በመቶ አድጎ የኢትዮጵያን ብልጽግና እንዲያረጋግጥ ማስቻል አለብን። ይሄ ተደምሮ የ10 በመቶ እና ከዚያ በላይ የአሃዝ እድገት መረጋገጥ አለበት እንደ ሃገር ማለት ነው። እያንዳንዱ ዞን 10 በመቶ እድገት፤ እያንዳንዱ ክልል 10 በመቶ ካለ እንደ ሃገር አሰናስለን ላቅ ያለ እድገት እናመጣለን።

ቀጥሎ የመቶ በመቶ ግቦች ናቸው። የመቶ በመቶ እድገት አንደኛ ፋይዳ መታወቂያ መቶ በመቶ መዳረስ አለበት ወረዳ ዞን ቀበሌ ክልል አግዛችሁ ዜጎቻችንን ለይተን ማወቅ አለብን፤ እያንዳንዱ ወረዳ እና ዞን እርግጠና መሆን በበቂ ደረጃ ፋይዳ መሰራጨቱን በእናንተ ወረዳ መቶ በመቶ፤ 5 ሚሊየን ኮደሮች በጣም መሠረታዊ ስራ ነው መቶ በመቶ መሳካት አለበት፤ ሶስተኛ የተጀመረ ኮሪደር በገጠርም በከተማም በተሟላ ማለቅ አለበት መቶ በመቶ፤ ጀምረን የምንተው ጀምረን ነካክተን የምንተው ሳንሆን የምንጨርስ መሆን አለብን። አዲስ ለመጀመር የጀመርናቸውን በገጠርና ከተማ ኮሪደሮች መቶ በመቶ ማሳካት። አራተኛ የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች መቶ በመቶ ተጠናቀው አገልግሎት ማቅረብ አለባቸው። ከገረአልታ እስከ አርባ ምንጭ፤ ከጅማ እስከ ሸበሌ፤ ከፓልም እስከ ደምቢ ያሉ የገበታ ለሀገር ስራዎች መቶ በመቶ ተጠናቀው አገልግሎት ማቅረብ አለባቸው። ሌላ መቶ በመቶ የምርጫ ምቹነት ማረጋገጥ አለብን። ሰላም የለም ምርጫ አያስፈልግም የሚባል ነገር ስርዓተ መንግሥት ለማዳከም ለማፍረስ እንደ መግቢያ የሚሰራ ስለሆነ እያንዳንዱ ወረዳ ዞን ክልል እራስህን መፈተሽ ያለብህ ህጋዊ ለመሆን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ለሁሉም ሃይሎች አስቻይ እንዲሆን መስራት ነው። ውድድሩን ብቁ ካደረግን በሃሳብ ልቀን ለመመረጥ ሰፊ ዕድል አለን። ያ ዕድል የሚበላሸው አስቻይ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ካቃተን ነው።

የመጨረሻው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ በየደረጃ መቶ በመቶ ተከውኖ በኦሮሚያ ያያችሁት የቀበሌ አገልግሎት የመስጠት ስርዓት በኦሮሚያም ሰፍቶና አድጎ በሌሎቻችሁም ተጀምሮ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓታችን መቶ በመቶ መሟላት አለበት። ቀነስን ዜሮ አልን፣ አንድ አልን፣ 10 አልን፣ 100 አልን፤ አሁንስ ለውጥ የሚያስፈልግባቸው አካባቢዎች ፦ አንደኛ የአመራር ለውጥ፣ የአመራር እሳቤ ለዓላማ የተገዛ፣ በዓላማ የሚሰራ ጭረት

የማይሰበሰብ፣ የሚሰራ የሚያበረታታ፣ ከቢሮ ወጥቶ የሚሰራ፣ የማይኮፈስ፣ የአመራር አመለካከት፣ አስተሳሰብ አሰራር ለውጥ ያስፈልጋል። ሁለተኛ የተቋም ለውጥ፤ አመራር ብቻ ሳይሆን ተቋሞቻችን የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለመከወን የሚያስችል ለውጥ ያስፈልጋቸዋል። የተሰሩ ሪፎርሞች፣ ስልጠናዎች ስራዎች በተጨባጭ በተቋም ፍሬ መታየት አለባቸው። ሶስተኛ የባህል ለውጥ፤ ምቀኝነት ሸረኝነት፣ መንደርተኝነት፣ ቅናት፣ አለመስራት፣ አለመትጋት አደገኛ ባህል ናቸው፤ ይቀነሱ ይለወጡ ይሻሻሉ። የትውልድ ግንባታ ልጆች ኳስ ሜዳ እንዲውሉ፣ በእግራቸው እንዲሄዱ፣ ትምህርት እንዲያጠኑ፣ መምህራን ኤክስትራ ሰዓት እንዲያስጠኑ፣ የትምህርት ጥራት እንዲያድግ፣ መልካም ሃገር እንዳላቸው በተቀናጀ መንገድ እንዲጎበኙ እንዲያዩ፣ ሀገራቸውን እንዲወዱ እንዲጠብቁ ማስቻል የሃገር እሴት ማሳየት ከተቻለ ከክልል ክልል ጉብኝት ማዘጋጀት ኢትዮጵያ ታይታ የማትጠገብ፣ የምትወደድ፣ የምታድግ ሀገር መሆኑን እያመነ እያወቀ እንዲያድግ ማድረግ። ሌላ ሰው ሰራሽ አስተውሎት አጠቃቀም እያንዳንዱ ተቋም ጤና፣ ትምህርት፣ ኢንዱስትሪ፣ ግብርና ሁሉም ዘርፍ ስንት በመቶ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ተጠቀምኩ የሚል እንደ ግብ ማስቀመጥ አለበት። ይህ አጠቃቀማችን ካላደገ የምናስበውን ሽግግርን ትስስር አናመጣም። ሁሉም በዘርፉ ግብ ይዞ ማሳካትን ተልዕኮ ማድረግ አለበት።

ሲጠቀለል መደመር ትውልድን ወደ ብልጽግና የሚያደርስ መንገድ ነው። የመደመር መንግሥት ለሀገር ብልጽግና ባላደራ ሆኖ ብዙ ተሸክሞ፣ ብዙ ደክሞ፣ ብዙ ተግቶ የማሸጋገር ሀላፊነት ያለበት መንግሥት ነው። አሻጋሪ መሆን ከፍተኛ ሀላፊነት ነው። ወደን ፈቅደን ፈልገን የምንሸከመው ሃላፊነት ነው። አሻጋሪዎች መድከም፣ መቁሰል፣ መሰደብ፣ መጎሳቆል ሊኖር ይችላል ግባችሁ ማሻገር ብቻ መሆን አለበት። ፈተናው ከባድ ነው። ካሳካችሁት ግን ፍሬው ጣፋጭ ነው። በፈጠራ እና ፍጥነት ጥራትንና ብዛትን እውን ለማድረግ መትጋት ነው የመደመር መንግሥት ቁልፍ ስራ። በብዝሃ ዘርፍ ትስስር እያንዳንዱ ዘርፍ አንደኛው ላንደኛው ግብዓት እየሆነ አንደኛው አንደኛውን እየደገፈ ወደ ስልጣኔ የምናደርገውን ጉዞ የሚያፋጥን መሆን አለበት። የሚቆም ጎማ ወደ ኋላ የሚሽከረከር ጎማ፣ መጠኑ አብጦ ሌላ የሚያቀጭጭ ጎማ ሳይሆን ተመጣጥኖ ተለካክቶ ወደ አንድ አቅጣጫ በእኩል ተሞ ብልጽግናን በየቀኑ እውን ለማድረግ የሚተጋ መሆን አለበት።

የሃሳብ ሉዓላዊነት ሃሳብን እንደ ዘር እንደ መነሾ መውሰድ የብልጽግና መሰረት ነው። በነበራችሁ ቆይታ የተገኙ ሃሳቦች፣ እርስ በእርስ ስትወያዩ በገለጻ ባያችሁት ያ ሃሳብ የእያንዳንዱ አመራር ስንቅ ሆኖ፣ ግብዓት ሆኖ፣ አቅም ሆኖ ያን አቅም ይዛችሁ ሄዳችሁ የተቋማችሁ ምልክት፣ አሰራር ስርዓት አድርጋችሁ፣ ተቋም ከተቋም አሰናስነን፣ ቅንጅትን ፈጥረን፣ ሀሳብ ግለሰብ ተቋም መቀናጀት እንዲችሉ ካስቻልን በልበ ሙሉነት

በአካባቢያችሁ ስራችሁን ከሰራችሁ፣ በ2036 ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚውን ኢኮኖሚ ትይዛለች!

ብረት ካወጣን፣ ወርቆች ካወጣን፣ ጋዝ ካወጣን፣ እርሻ ከተስፋፋ፣ ኢንዱስትሪው አሁን እንደጀመርነው ካደገ፣ ሁላችን የምንተጋ ከሆነ፣ ከተሞቻችን ካሸበረቁ ካማሩ፣ ጎብኚ መሳብ ከቻልን ኢትዮጵያ የድህነት ታሪኳን የምንቋጭ ትውልድ መሆን እንችላለን። ይህን በማድረግ ይሄ አመራር የተጣለበትን ከፍተኛ ሀላፊነት በብቃት በመወጣት የኢትዮጵያን ብልጽግና አንድ ደረጃ ወደፊት የሚወስድ መሆን ከቻለ፤ ከታሪክ ተወቃሽነት መዳን ብቻ ሳይሆን በታሪክ ውስጥ ለዘላለም የሚነገር የሚጨበጥ ሃውልት ሰርተን ማለፍ ስለሚያስችል እንበርታ፣ እንስራ፣ ሃሳብ አለን፣ ፓርቲ አለን፣ ጅማሮ አለን ውጤት አለን፣ የሚደግፍ ህዝብ አለን በትብብር እና በአንድ መንፈስ ኢትዮጵያን ለማሸጋገር ብንጥር እቺ ሀገር ድንቅ አጓጊ መበልጸግ የምትችል ለሌሎች አርዓያ የምትሆን፤ ዕድዋን ድጋሚ በብልጽግና ማረጋገጥ እና የአፍሪካ ወንድሞቻችንን ስበን ማውጣት ስለሚያስችል፤ በዐድዋ አዳራሽ የተደረገው ይህ ስልጠና ለዚያ ለዳግም ዐድዋ ምስረታ ፈርቀዳጅ እና ጡብጣይ እንዲሆን በጋራ መንፈስ በትብብር እና በትጋት እንድትሰሩ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ


20
የኢትዮጵያ

20ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል

ሀዳር 29፣ 2018 **ዓ.ም**.

አመሰግናለሁ!
ክቡር አገኘሁ ተሻገር የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፤
ክቡር አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፤
ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፤
ክቡር አቶ አደም ፋራህ፤
ክብራን የሁሉም ክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች፤
የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ የውቢቷ ሆሳዕና ከተማ ነዋሪዎች፤

ከሁሉ በላይ በጀግንነቱ፣ በሀገር ወዳድነቱ፣ በትጋቱ፣ በአቃፊነቱ የሚታወቀው የሀድያ ህዝብ ዛሬ መላ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች በማዕከላዊ ኢትዮጵያ መዲና በሆሳዕና ከተማ ሰብሰብ ብለን በጋራ ለማክበር ስላስቻላችሁን ከፍተኛ ምስጋና ላቀርብላችሁ እወዳለሁ። ሀድያ በወታደራዊ መስክ ጀግናውን ኮሎኔል በዛብህን ለኢትዮጵያ ያበረከተ ህዝብ ነው። ጀግናው ኮሎኔል በዛብህ የጀመረውን ጀግናው የሀድያ ወጣት ያሳካዋል።

የተከበራችሁ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይም የሆሳዕና ከተማ ነዋሪዎች፤ በመጠሪያው እጅግ ልዩ በሆነው የኢትዮጵያ ማዕከላዊነትንም በሚያሳየው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ስንሰበሰብ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ማዕከላዊ የሆነው ዋና ሀሳብ ብሔራዊ መሻትና ፍላጎታችን ነው። ኢትዮጵያ በህብረ ቀለም የሚሳል፣ በህብረ ባህል የሚኖር፣ በህብረ ቋንቋ የሚነገር፣ በህብረ ደም የተሰራ፣ በህብረ ላብ የሚገነባ፣ በህብረ ጥበብት የሚሻገር፣ ኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያ የነበሩ፣ የሚኖሩ፣ የሚጸኑና የማይናወጡ መሆናቸውን ዛሬ ዳግም በኩራት ለጀግናው የሀድያ ህዝብና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መግለጽ እወዳለሁ!

ክቡራትና ክብራን፤ የአፋር ዳጉ ለዳውሮ ኩራቱ፣ የሲዳማው ጨምበላላ ለአማራው ሃሴቱ፣ የኦሮሞው ገዳ ለሐረሪ ምኞቱ፣ የአክሱም ሀውልት ለሀድያው ታሪኩ፣ የጀንል ግንብ ለቤንሻንጉል ቅርሱ፣ ፋሲል ቤተመንግሥት ለሀድያው ሀብቱ፣ የሶማሌው ዳንቶ ለጋሞ ባህሉ፣ የጉራጌ ክትፎ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጣዕሙ፤ የአንዳችን ለሌላችን ውበት፣ የአንዳችን ለሌላችን ክብር የሆነባትን ሀገር ኢትዮጵያ አንዱ ከፍ ሌላው ዝቅ ብሎ ሳይሆን ሁላችን እኩል ሆነን በወንድማማች ዐይን ተያይተን በመደመር እሳቤ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን እንድናሻግር አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።በአባቶቻችን ደም የወረስነውን ነፃነት በብልጽግና ማጽናት ከዚህ ትውልድ የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል!

ዛሬ ከተሞቻችን እያሸበረቁ፣ ገጠር መንደሮቻችን ለመሻገር ደፋ ቀና እያሉ፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችን አቧራቸውን አራግፈው የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም ኩራት መሆናቸውን በግሃድ በሚያሳዩበት በዚህ ጊዜ፤ መሬት ክረምት ከበጋ በማረስ የምግብ ጥገኝነትን ለመላቀቅ መላ ኢትዮጵያ በተለይም አርሶ አደሮቻችን እየተጉ ባሉበት በዚህ ጊዜ፤ የማዕድን ሀብታችን እየተገለጠ፣ የቱሪዝም ሀብቶቻችን እያበቡ፣ ቴክኖሎጂን የመጠቀም አቅማችን እየሰፋና ልምምዱ እያደገ፣ ኢትዮጵያ በሁሉም መመዘኛ ከጨለማ ወደ ንጋት እየተሻገረች ባለችበት በዚህ ታሪካዊ ጊዜ በሆሳዕና ከተማ ተገናኝተን ዳግም ቃልኪዳናችንን ለመጠበቅና ለማጽናት መላው የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ ጀግና ህዝብ ፊትና በሆሳዕና ከተማ ዳግም ተገናኝተን የጀመርነውን ለመጨረስ፣ ያልጀመርነውን ለመጀመር፣ ኢትዮጵያን ለማጽናት በጋራ እንድንቆም በድጋሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የተከበራችሁ የሀድያ ወጣቶች፣ ሴቶች፤ ብልጽግናን ማሳካት ፈታኝ ሂደት ነው። የወረስነውን ነፃነት ብቻ ሳይሆን የተሸከምነውን የትውልድ አደራ ማሰብ ይኖርብናል። ባለፈው ሆሳና ስመጣ ከነበረው የልማት ጅማሮ ላቅ ያሉ ስራዎች በዚህኛው ዙር ማየት ችያለሁ፤ ነገር ግን ፕሪቶሪያን፣ ጆሃንስበርግን፣ ኬፕ ታውንን ያቀናው የሀድያ፣ የከምባታ ወጣት... አዲስ አበባን፣ ጅማን፣ ድሬዳዋን ያለመለመው ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ከምባታ፣ ማረቆ በዚህ ክልል የሚገኙ ሁሉም ብሔሮችና ብሔረሰቦች ብልጽግናን ማጽናት ይቻለን ዘንድ ተግተን መስራት ይኖርብናል።

የኢትዮጵያን ችግሯን ብቻ ሳይሆን አቅሟን ማየት አለብን!

አይካድም በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። እንደዚሁም ገና እጅግ ልንጠቀምበት የሚገባ በርካታ አቅሞች ያሏት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። ይህ ትውልድ ችግሯን ብቻ ሳይሆን አቅሟን ፈልፍሎ የማየትና የማውጣት ብቃት እንዳለው ከጅማሮ ስራዎቻችን የሚታይ ስለሆነ፤ ችግሯን ብቻ ሳይሆን አቅሟን፣ ከኢትዮጵያ መቀበል ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ መስጠት፤ ብዙ እጆች በትብብር ካልሰሩ እህል ዳቦ መሆን ስለማይችል በትብብር መንፈስ፣ በብዙ ትጋትና ልፋት አዲስ የታሪክ ገጽ ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካም ብርሃን የሚሆን የብልጽግና ጅማሮ በእኛም በሌሎችም የሚታመንበትና ለትምህርት የሚውል ዳግም ዐድዋ በኢትዮጵያ ይከበር ዘንድ ዛሬ አፍሪካ የምትፈልገው ብልጽግናን ነውና በልጽገን ለማበልጸግ በጋራ እንድንሰራ በድጋሚ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

የኢትዮጵያ ብልጽግና፣ የኢትዮጵያ ሙሉነት የሚጓደለው ኢትዮጵያውያን በህብረት፣ በትጋት መስራት ካልቻሉ ብቻ ነው!

ይህንን ተገንዝበን እኛ ኢትዮጵያውያን ህብረ-ብሔራዊነትን እያጠናከርን፣ በገዥ ትርክት አቃፊ በሆነው እሳቤ እየተሸመን፣ በተቋማዊ ለውጥ የሀገር ግንባታና የሀገረ-መንግሥት ማጽናት ጅማሯችንን እያጎለበትን፣ ብሔራዊ ጥቅማችንን በስልት፣ በብቃት፣ በውጤትና በጥበብ እያሳካን ሁለንተናዊ ብልጽግናን እያረጋገጥን የተወበች፣ የላቀች፣ የጸናች ሀገር ለልጆቻችን ማስረከብ እንድንችል ዛሬ የተሰጠን ታላቅ የእድል ቀን ነውና እንድንጠቀምበት አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

ለመላው ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ አንድ ክር ደካማ ነው ብዙ ክር ግን የማይበጠስ ገመድ ነው። ስንበዛና ስንሰባሰብ በቀላሉ የማንበጠስ ጠንካራ ገመድ ስለሆን መተባበርን፣ መከባበርን፣ በጋራ መቆምን፣ ብሔራዊ ጥቅም ማስቀደም የሁላችን ሀብትና ስንቅ እንዲሆን አደራ እያልኩ፤ የሀገርን መሻትና የባዳን ክፋት መለየት ይጠበቅብናል። ባዳ በክፋት የእኛን መሻት ለማጨለም ሲነሳ ኢትዮጵያውያን ለባዳ ፍላጎት መሳሪያ እንዳንሆን ምክንያቱም በባዳ የተጠለፈ ገመድ አይፈታም አያስርም።

እርስ በእርስ መተሳሰር ሲገባን ክፉ እሳቤ ያለውን የባዳን መሻት በውስጣችን እንዳናስገባና በታሪክ ተወቃሽ እንዳንሆን ኢትዮጵያውያን ቀልብ ገዝተን ሰላማችንን እናጽና፣ በንግግር እንመን፣ በተሰማራንበት የስራ መስክ ሁሉ በትጋት እንሰራ፣ ሌብነትን እንጠየፍ፣ የሀገር ጥቅም እና የህዝቦቻችን ክብር እናስቀድም፣ ለዘመናዊነት፣ ለለውጥ ክፍት እንሁን፣ ሉዓላዊነታችንን በሁሉም መስክ እናሳካ፣ ልመናን ታሪክ እንድናደርግ የጀመርነውን መልካም ጅማሮ ሁሉ ለፍሬ እንድናበቃ ሰላምን፣ ንግግርን፣ ውይይትን፣ አንድነትን፣ ብሔራዊ ጥቅምን እንድናስቀድም በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ በብዙ ተስፋ የተሞላች ሀገር ናት!

ኢትዮጵያ አስደናቂ ጅማሮዎችና ውጤት እያሳየች፣ እየተመነደገች፣ እያንሰራራች ያለች ሀገር ናት። ይህ መልካም ጅማሮ በፈጣሪያችን የሚደገፍ ቢሆንም በሰይጣን ትጋት ቀን ከሌት ለማደናቀፍ ሙከራዎች ይደረጋሉ። ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዳግም ከሆሳዕና ምድር ላረጋግጥ የምፈልገው ማንኛውም ፈተና፣ ማንኛውም ትንኮሳ፣ ማንኛውም የክፉ ሀሳብ ኢትዮጵያን ከብልጽግና ማቆም አይችልም።እያንዳንዱን ፈተና ወደ እድል በመቀየር የኢትዮጵያን ብልጽግና እናፋጥናለን፤ የኢትዮጵያን አንድነት እናጠናክራለን። ኢትዮጵያ ትጸናለች፣ ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የብልጽግና ምልክትና ምሳሌ ትሆናለች።

በሰላም እንደጀመርን በሰላም እንጨርሳለን። እኛ የኮሎኔል በዛብህ ልጆች አንሸማቀቅም፣ በጀግንነት የጀመርነውን በጀግንነት እንጨርሳለን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር፣
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ፤
እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ሆሳዕና፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ

የምሁራን ሚና ለሀገር ብልጽግና ጥናታዊ ፅሑፍ

—ታኅሣሥ 24፣ 2018ዓ.ም

ጡረታ ከወጣሁ በኋላ ደጋግሜ የምመጣበት መድረክ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ዛሬ አስቀድመው እንድንለማመደው ለጋበዙኝ ሰዎች ምስጋና እያቀረብኩ በመጀመሪያ የዚህ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስተማሪዎች አጠቃላይ ማኅበረሰቡ ይህ አንጋፋ ተቋም ለ75ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉ እንኳን አደረሳችሁ፤ እንኳን አደረሰን። 50ኛውን አክብራችሁ 75ኛውን የተቀላቀላችሁ ለ100ኛው ያድርሳችሁ ማለት እወዳለሁ።

ዛሬ የማቀርብላችሁ መነሻ ጽሁፍ፤ ምሁር፣ የምሁር አመራር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ምሁራን፣ ብልጽግናው ላይ ያላቸው ሚና የሚዳሰስ ይሆናል። የመጀመሪያው ርዕሴ ቀደም ሲል ፕሮፌሰር እንዳነሱት የምሁራን ሚና በፈጣን ዘመን የሚል ቢሆንም ወደ እኛ ለማውረድ የምሁራን ሚና ለሀገር ብልጽግና ወደሚል ትንሽ አሻሽዬዋለሁ፤ ይሄን ያሻሻልኩበት ዋናው ምክንያት ወደ እናንተ ለመምጣት ስሰናዳ አንድ ፈላስፋ ተናገረ የተባለውን ነገር አስታወስኩኝ ሰዎች በሶስት መደብ ይከፍላቸዋል ሶስት አይነት ሰዎች አሉ ይላል ይህ ፈላስፋ ገሚሱ ሰው አፍቅሮተ ነዋይ ያለው ነው ይላል፤ ገሚሱ ሰው አፍቅሮተ ክብር ያለው ሰው ነው ይላል። ገሚሱ ደግሞ አፍቅሮተ ጥበብ ያለው ነው ይላል። እና ዛሬ እኔ የመጣሁት የጥበብ አፍቃሪዎች ወደሚባለው ስብስብ ነው በሚል ተስፋ ሀሳብን የማይፈሩ፣ ሀሳብን የሚያስተናግዱ ሰዎች ከሆኑ፤ የተንሳፈፈ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ትንሽ ወረድ ብሎ ወደ እኛ ሁኔታ ቢመጣ አይከፋቸውም በሚል እምነት በተወሰነ ደረጃ ርዕሱን አሻሽዬዋለሁ።

የምሁራን ሚና ለሀገር ብልጽግና እጅግ ከፍተኛ ሚና ያለው፣ ምሁር በዘርፉ የሚሰጠውን አመራር በተሰጠው ገንዘብ፣ዋጋ የሚሰጠውን አመራር አውቆ፣ ለይቶ የሚገለገል ሲሆን ነው። ምሁራን የጋራ ትርክት በመፍጠር፣ ምሁራን የበለጸገች፣ ከድህነት የተላቀቀች ኢትዮጵያን ለማየት የሚጠበቅባቸው ሚና ይወጡ ዘንድ ምሁራዊ አመራር መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ምሁራዊ አመራርን ከማየታችን በፊት በተወሰነ መልኩ መሪ ማነው ማለት ይኖርብናል። መሪ በመጀመሪያ እራሱን ያሸነፈ እራሱን የሚያነጋግር በውስጡ ያለውን ጩኸትና ድምጽ መለየት የሚችል፣ ጩኸትን እያፈነ ለድምጽ ቦታ የሚሰጥ፣ ከራሱ ጋር መወያየትና ራሱን ማድመጥ በዚያም ሂደት ራሱን ማሸነፍ ያስቀደመ ሲሆን ነው። እራሱ ጋር መነጋገር ከተለማመ'ደ በኋላ፣ በራስ እና ከራስ መነጋገር በቂ ስላልሆነ ጊዜን ለመዋጀት፣ ጊዜን ለማትረፍ፣ ጊዜ ፈጣን ጋላቢ ፈረስ መሆኑን አውቆ እያንዳንዱን ወቅት ለተገባ አላማ ማዋል የሚችል ሲሆን፤ ራሱን ያሸነፈና ጊዜን መጠቀም የሚችል

ከሆነ በኋላ ሶስተኛው ምዕራፍ ስለ ሃሳብ ያለው አፍቅሮት፣ ስለ ሃሳብ ያለው መከፈት፣ ሃሳብን ለማስተናገድ ያለው ዝግጁነት ነው። ሰው ራሱን ካደመጠ ከራሱ ጋር ከተወያየ የግዜን ዋጋ ከተገነዘበ ለሃሳብ ቦታ ከሰጠ የመጨረሻው ከአንድ ምሁር ተፅዕኖ ፈጣሪ እንቅስቃሴ በፊት የሚቀርመው ነገር ግብ ነው።

ዝም ብሎ እንደዚሁ ሃሳብ የሚገበይ፣ የሚሸጥ ሳይሆን የሆነ ነገር ለማሳካት ግብ የሚያስቀምጥ መሆን አለበት። በዚህ ጊዜ በዚህ ሁኔታ እነዚህን ጉዳዮች አሳካለው የሚል መሆን አለበት። ያንን ማድረግ ሲችል ከራሱ አልፎ ሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድ ከራሱ አልፎ ሌሎችን መጥቀም የሚችል ይሆናል። ለዚህም ነው መሪነት በያዝነው ቦታ ስላለው ሥልጣን አይደለም የሚባለው ። ስለ ዓላማና አቅም ነው፤ ስለያዝነው ቦታ ሳይሆን ባለንበት ቦታ ሁሉ በነዚህ ልምምዶች የለውጥ ወኪል ሆነን አመራር መስጠት ሰዎች ይችላሉ፣ በተለይ ምሁራን! አንደኛው አዎንታዊ ተጽእኖ በመፍጠር፣ መሪነት በዋናነት ተጽእኖ ስለ መፍጠር ነው የሚባለው ማለት ነው፤ ከራስ አልፎ የሚከተልን ኃይል ላይ ተጽእኖ መፍጠር ስለሆነ የለውጥ ትልም ገንብተው፣ የለውጥ ትልም ነድፈዉ፣ ሰዎችን ማስተባበር፣ ሰዎችን ማብቃት፣ ሰዎችን ማሰማራት፣ ሰዎችን በበላይነት መምራት ሲችሉ፣ የዚያ ሁሉ ድምር ደግሞ ውጤት ሲያመጣ አንድ ሰው የመሪነት ብቃት ተጎናጽፏል ይባላል።

ውስን ወሳኝ የመሪነት አንኳሮችን ለማንሳት፣ መሪነት ለስልጣኔ ስምረት ያለውን ዋጋ በተወሰነ አንስቼ ማለት እፈልጋለሁ። መሪነት በጊዜና በዘመን ላይ መሰልጠን ማለት ነው። የዛሬ ሰባ አምስት ዓመት የነበሩ የዚህ ተቋም ምሁራን የዚህ ተቋም መሪዎች የሰለጠኑበት ሁኔታ እና ዛሬ ምንሰለጥንበት ሁኔታ አንድና ያው አይደለም። ምሁርነት በግዜና በዘመን ላይ መሰልጠን ነው። ምሁርነት ከጊዜ ጋር ያለን እሽቅድድም ሳይታለፉ ሳይቀደሙ መኖር ማለት ነው፤ ከተቀደሙ ይበላሻል። ለዚህም ሶስት ዋና ዋና የምሁርነት አንጓዎች በመሪነት አስታክኬ ልይ፡-

የመጀመሪያው መሪዎች የሃሳብ መሪዎች ወይም ምሁራን ናቸው። የሃሳብ መሪዎች ወይም ምሁራን ያለፈውን ያለንበትን የሚረዱ መጪውን ማየት የሚችሉ ዛሬን አበክረው የሚሰሩ ናቸው። ትናንትናን በቅጡ መለስ ብለው መዳሰስ የማይችሉ ከሆነ፣ ስውር ጎን እንዳላቸው የማይገነዘቡ ከሆነ ወደ ኋላ መለስ እያሉ ማየት ወደፊት ለመስፈንጠር ያለውን ፋይዳ የማይገነዘቡ ከሆነ፣ ነገን አርቀው ለማየት ይቸገራሉ። ትናንትናም መዳሰስ እና ነገን ማየት በቂ አይሆንም። ዛሬን ጠንክሮ መስራት ይጠይቃል፤ የሃሳብ ምሁር ለመሰኘት። ለምን ሃሳብ የለውጥ ኃይል ነው። ምሁራን የለውጥ ወኪል ናቸው። ምሁራን ልክ አንድ

ሰው የህዝብ ወኪል ሆኖ ተመርጦ፣ ተወክሎ ፓርላማ እንደሚገባው ሁሉ ሃሳብን ወክለው በፖለቲካል አውድ በኢኮኖሚ አውድ በሰዎች መስተጋብር ውስጥ የሃሳብ ወኪል ሆነው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ናቸው። ሃሳብ የለውጥ ኃይል ነው ምሁራን የዚያ ወኪል ናቸው። ውክልናቸውን በወጉ የማይወጡ ከሆነ ውክልናውን በወጉ እንደማይወጣ የህዝብ ተመራጭ ማለት ናቸው።

ሁለተኛው ወሳኙ የአመራር አይነት የተቋም መሪዎች ወይም መንግሥት በሚባለው ሊካተት ይችላል። ይሄ የተቋም ለውጥ ቅድም ያነሳዋቸውን የሃሳብ መሪዎች ጥንስስ ተቋማዊ የሚያደርግ፣ ተቋማዊ ቅርጽ የሚያስይዝ ኃይል ማለት ነው። ለምሳሌ ሰዎች ከአደን ወጥተው በምግብ ራሳቸውን ለመቻል ወደ ግብርና እንቅስቃሴ ወደ ግብርና ቴክኖሎጂ ወደ ግብርና እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡት በሃሳብ ነው፣ በተቋሙ አይደለም። የግብርና አብዮት ከተስፋፋ በኋላ ያ ያመጣው አጠቃላይ ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴ የነበረው ተቋም ሊያስተዳደረው ብቃት ስላልነበረው ፊውዳሊዝምን ፈጠረ። ፊዉዳሊዝምን የወለደው የግብርና አብዮት ነው። ግብርና አብዮት የፈጠረው ደግሞ ሃሳብ ነው። እነዚያ የሃሳብ ወኪሎች በማኅበረሰብ ውስጥ በሚፈጥሩት ተጽእኖ ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴ ከፈጠሩ በኋላ ሄዶ ሄዶ ተቋማዊ ለውጥ አምጥቶ ሙሉ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ የተሟላ ውጤት ሊያመጣ አይችልም ተቋም ይፈልጋል። የካፒታሊዝም ስርአት በግብርና አብዮት ጊዜ በሃሳብ ደረጃ በጽሑፍ ደረጃ ነበረ ግን ተቋማዊ የመሆን አቅም አልነበረውም።

ኢንዱስትሪያል አብዮት ሲፈጠር ኢንዱስትሪያል አብዮቱ የፈጠረው ሃሳብና ማኅበረሰብ በፊውዳል ስርዓት መገዛት መተዳደር በቂ ስላልሆነ ፊውዳል ስርአትን ማፍረስና ካፒታሊዝምን መፍጠር ግዴታ ነበር። ሃሳብ ንቅናቄ ይፈጥራል፣ ንቅናቄ ስርአት ይፈጥራል። ካፒታሊዝም ኢንዱስትሪ አብዮት ከፈጠረው በኋላ አሁን ሁላችሁም እንደምትታዘቡት ያለው አዝማሚያ በቅርቡ 4.0 ኢንዱስትሪያል አብዮት የሚባለው ሃሳብ በስፋት በዓለም ላይ መነጋገርያ ሆኗል። 4.0 ማጠንጠኛ መካከለኛ ሀሳብ የራስ-ሰር አሠራርን ቅልጥፍና ማሳደግ ሰው ሰራሽ አስተውሎትን በጣም መጠቀም ላይ ያተኮረ ነው። ሰው ሰራሽ አስተውሎት እንጠቀም መተግበሪያዎችን እንስራ፣ ራስ-ሰር አሠራርን እንስራ፣ በዚህም ቅልጥፍናን እናሳድግ ነው። የለም በ4.0 መታጠር የለብንም 5.0 መጠቀም አለብን የሚለው እሳቤ ደግሞ በአንድ ዘመን የመጣን ቴክኖሎጂ ብቻውን መጠቀም በቂ ስላልሆነ ቴክኖሎጂዎች ሰውን ማዕከል ያደረጉ ሆነው መገልገል ያስፈልጋል፣ ሰውን ማዕከል ያደረጉ ካልሆኑ 4.0 የሰውን ልጅ ህልውና፤ የሰውን ልጅ ስራ፤ የሰውን ልጅ ህይወት የሚገዳደር ሊሆን ይችላል። እና በ5.0 ቴክኖሎጂዎች አቀናጅተን ሰውን ማዕከል አድርገን ለመጠቀም ካፒታሊዝም ይችላል ወይ ነው ጥያቄው።

አይችልም፤ ፊውዳሊዝም ኢንዱስትሪያል አብዮት ሊመራ እንዳልቻለው ሁሉ አሁን በምናስበው በሰው ሰራሽ አስተውህሎት ዘመን ሰውን ማዕከል ያደረጉ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ፍላጎት ባለበት ዘመን ካፒታሊዝም ስርዓት ሆኖ አሁን ያለውን አውድ ሊመራ አይችልም፤ ይሄን በብዙ ነገር አሳይቷል። አንደኛ ክላይሜት ላይ በሰጠው አመራር ካፒታሊዝም አሁን ያለውን ዘመን መዋጀት እንደማይችል አሳይቷል። እንደ ካምፕ 60፣ 70 ዓመት ጠንክሮ አይሎ ያሻውን ሲያደርግ የነበረው ካምፕ እንዳያችሁት ተነቃንቋል፤ እርስ በእርሱም ሊግባባ አልቻለም። እርስ በእርሱ ብቻ ሳይሆን በውስጡም ቢሆን በሚታይ ሁኔታ የመውደቂያው ምዕራፍ ላይ ነው ያለው። በዚህ ጊዜ እዚህ ያለን የሃሳብ ወኪሎች ቁጭ ብለን መጠበቅ ነው ያለብን ወይስ በኛ ሁኔታ የሚስማማ ስርአት መፍጠር ነው ያለብን? የመጀመሪያው ጥያቄ እሱ ነው።

ለዚህም በመደመር መንግሥት በግልጽ የተቀመጠው፣ መንግሥታት መሆን ያለባቸው፣ እኛ የምንፈጥረው መንግሥት መሆን ያለበት አንደኛ ቀላል ቢሮክራሲ መሆን አለበት ፤ ቢሮክራሲ ላይ ጊዜ የሚያጠፋ መንግሥት መሆን የለበትም። በስትራቴጂው ረገድ ታላቅ መሆን አለበት፤ ትላልቅ ስትራቴጂዎች ያሉት መሆን አለበት፤ መጨረሻ ወሳኙ ክፍል ግን ጠንካራ የበላይ አመራር መኖር አለበት መንግሥት የመቆጣጠር አቅም እንጂ የቀበሌ መታወቂያ በሚሰጥበት ደቂቃና ሰአታት ላይ የሚያጠፋ ከሆነ፣ ቅልጥፍናና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን የመላመድ ብቃት ስለማይኖረው ዘመን ያን እሳቤ መሸከም የሚችል ተቋም መሆን አይችልም። ለዚህም ተቋማት ራሳቸውን ማሻሻያ አለባቸው፤ ማዘጋጀት አለባቸው።

ሶስተኛው መሪ የማኅበረሰብ መሪዎች ናቸው። እነዚህ ቅድም ያነሳዋቸው የማኅበረሰብ መሪ አይደሉም ማለት አይደለም ከዚህ ከነዚህ ውጪ በተለያየ ተቋማት በማኅበረሰባ መዋቅር ደረጃ በማንቃት ማኅበረሰብ የሚመሩ ግለሰቦች እና ቡድኖች አሉ። የእነዚህ ደግሞ ዋናው ጉዳይ ለለውጥ ክፍት ያልሆነን ማኅበረሰብ፣ ለውጥን በቀላሉ ለማይቀበለው የፖለቲካ ምህዳር አዳዲስ ነገር እንዲቀበል አዳዲስ እሴቶችን መሸከም እንዲችል ማስተማር ነው። የዲሞክራ ባህል መፍጠር ነው፤ ኢንዱስትሪ ባህል መፍጠር ነው። ግቢን ለምሳሌ የአካባቢ ውበትን ማስተካከል፣ ግቢን ማስዋብ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ይሁነኝ ብለው የሚያስቡት እና የሚሰሩት ጉዳይ ላይሆን ይችላል።

ትላንትና ዛሬ ግን እንዳያችሁት በየቦታው ወሳኝ እየሆነ መጣል እንግዲህ ከዚህ ግቢ ስንወጣ ያለው አከባቢ እና እዚህ ግቢ ውስጥ ስንገባ ያለው አከባቢ ይወዳደር እና የጥያቄ ምልክት መነሳቱ አይቀርም ማለት ነው። ትላንትና ትኩረት ላይሰጠው ይችላል፤ ዛሬ ግን የግድ ነው ምክንያቱም አሁን ያለው ዘመን ሰውን ማእከል ያደረገ ነው ሲባል፣ ሰዎች በእግራቸው

ከሚንቀሳቀሱበት፣ ከሚስቡት አየር፣ ከሚጠጡት ውሃ፣ በከባቢያቸው ካለው ሽታ፣ አይናቸውን ፣ጆሯቸውን፣ ውስጣቸውን የሚመግቡት ነገር ሙሉ በሙሉ በተቻለ መጠን የተሰናሰለ፣ የተስተካከለ መሆን አለበት የሚል እሳቤ ነው። ለዚህ የማኅበረሰብ አንቂዎች ለለውጥ ክፍት የሆነ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ሃላፊነትና የአመራር ሚና ይጠበቅባቸዋል። የሃሳብ መሪዎች፣ የተቋም መሪዎች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የሚደማመጡ፣ የሚሰናሰሉ፣ የሚማማሩ ከሆኑ አሁን ባለንበት ዘመን ውስጥ ተሰብረን፣ ተቀጭተን የምንቀር ሳንሆን ቀና ብለን የምንራመድ እንድንሆን ያስችላሉ።

ይሄ እንዲሆን ከነዚህ ሶስቱም በተጨማሪ የአመራርን ተጽዕኖ የሚገለጥበትን መንገድ በቀለለ መንገድ ነካ አድርጌ ማለፍ እሞክራለሁ። ቅድም እንዳነሳሁት የሃሳብ መሪዎች የሚባሉት የእውቀት መሪዎች ይባላሉ። የእውቀት መሪዎች ገንዘባቸው ሃሳብ ነው፣ የሚገበያዩበት ገንዘብ ሃሳብ ነው፤ ያንን ገንዘብ በደንብ የማያቅ የእውቀት መሪ፣ መሪ ነኝ ቢልም ያሻውን ማሳካት አይችልም። ምንድነው ሚሰራው በፈጠራና በተቀየረ የልቦናው ዉቅር ሰውን ለዘመን ማዘጋጀት ነው ስራው። የልቦናው መቀየር ፈጠራን ማስፋፋት፤ ዋጋውን በወጉ ባላወቀ ሰው ሊሰራ አይችልም። እግረ መንገድ ለማንሳት ብዙ ጊዜ ሰምታችሁ ሊሆን ይችላል ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የታዘብኩት ነገር በሀሳብ እና በግል አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት በወጉ አለመገንዘብ ነው። እኔ ስላደረግኩት ከረባት እዚህ ካላችሁት ሀያ ሰዎች ሀያዎቹን ብጠይቅ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የግል አስተያየት አለው፤ እሱ ሃሳብ አይደለም። የግል አስተያየት ለሃሳብ ምንም ፋይዳ የለውም ማለት አይደለም። ፋይዳ አለው፤ ግን ሃሳብ አይደለም። ብዙ ጊዜ ሰዎች በአንዳንድ ጉዳይ ላይ የግል አስተያየት ይሰጡና ሃሳብ ሰጥተን ነበር አልተደመጥንም ይላሉ። ሃሳብ እንደዛ አይደለም ሃሳብ ቅደም-ተከተላዊ ሥርዓት አለው፤ ሃሳብ መነሻና መድረሻ አለው፤ ሃሳብን የሚያሳካው ግብና ቀጥሎ ለሚመጣው መዘዝ የሚያስቀምጠው ሳይንሳዊ አቅጣጫዎችና መንገዶች አሉ።

የግል አስተያየት የሰጠ ሰው ሁሉ አልተደመጥኩም ሳይሆን የግል አስተያየት ተሰናስሎ፣ ተደምሮ ከዛ ውስጥ ሀሳብ ሊወለድ እንደሚችል ማሰብ ያስፈልጋል፤ ይሄ ብዙ ጊዜ የምታዘበው ነገር ነው። ሁለተኛው መሪ የመንግሥት መሪ ናቸው። የእነዚህ የመንግሥት መሪዎች ገንዘባቸው ደግሞ ቅቡልነት ያለው ስልጣን ነው፤ በህዝብ ውክልና የተሰጠ ቅቡልነት ያለው ስልጣን። ቅቡልነት ያለው ስልጣን ያለው ሰው በፖሊሲ፣ በሐሳብ፣ በአፈጻጸም ሊመራ ይችላል ያ የሚሆነው ግን ቅቡልነት ያለው ሲሆን ነው። ሶስተኛው የንግዱ ዘርፍ መሪዎች ናቸው። የእነዚህ መገበያያ ደግሞ ገንዘብ ነው። በገንዘባቸው ኢንቨስት በማድረግ፣ የኢኮኖሚ ተፅዕኖ በማምጣት በመቅጠር ግብር በመክፈል ችግር

ሲያጋጥም በማገዝ ባላቸው ሪሶርስ አመራር ይሰጣሉ። አራተኛው የሃይማኖት መሪ ናቸው። ዋጋቸው ሞራል ነው። ይሄንን ዋጋ ስተው የሃይማኖት መሪዎች የሃሳብ መሪ እንሆናለን ወይም የገንዘብ መሪ እንሆናለን ሲሉ ይበላሻል ነገሩ። የነሱ መገበያያ ዋጋ ሞራል ነው። በዚህም የወል እሴት ይገነባሉ። ንቃተ-ሕሊና ላይ ይሰራሉ። ያን ማድረግ ሲችሉ አመራሮች በየዘርፋቸው ባላቸው መገበያያ የሚጠበቅባቸውን እያደረጉ ስለሚሆን ሲሰናሰል በሃገር ላይ ለውጥ ያመጣል።

የሚዲያ መሪዎች ገንዘባቸው መረጃ ነው። የተዛባ መረጃ፤ አይደለም መረጃ ነው። የተዛባ መረጃ ሲሆን፣ ለአንድ ቀን፣ ለሁለት ቀን፣ ለሶስት ቀን ይደመጡና ከዚያ በኋላ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይገባሉ። በዚያ ምን ያደርጋሉ? ትርክት ይገነባሉ፤ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፤ የወል ትርክትን ይሰራሉ፤ ህዝብን ያነቃሉ ያሰናዳሉ ያዘጋጃሉ ምን ሲሆን፣ መረጃ! የመረጃ መሰረቱ መረጃ ነው፤ ተገቢ መረጃ የሚሰበስብ ሳይኖር ሰው ቁጭ ብሎ የሆነ ነገር በመንደፍ ብቻ በመናገር ትርክት መገንባት አይችልም። ወጥነት ያለው ስለማይሆን የነቃና ፍላጎቱን ለመጠበቅ የሚችል ማኅበረሰብ ሊፈጥር አይችልም ለጊዜው ማራኪ አጭር መልእክት ሊሆን ይችላል። የሚዲያ መሪዎች ገንዘባቸው መረጃ መሆኑን ካወቁ የመረጃ መሰረት ደግሞ መረጃ ነው። እያንዳንዷን መረጃ አሰናስለው፣ መርምረው በሚሰጡት እና በማይቋረጥ እውነት ውስጥ ነው ተጽእኖ መፍጠር የሚችሉት።

የኢንዱስትሪ መሪ ደግሞ ዋጋቸው ቴክኖሎጂ ነው፤ ይፈጥራሉ የኑሮ ዘዬን ያቀላሉ፤ ይፈጥራሉ የመንግሥታት የአሰራር ዘዬን ያቀላሉ። ያን ሲያደርጉ አመራርነታቸው ይረጋገጣል። ታዲያ ያለው ችግር ምንድነው? መገበያያ ዋጋን ያለአግባብ መጠቀም ያለው። በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የመገበያያ ዋጋን ያለአግባብ መጠቀም አለ፤ አንዳንዶቻችሁ የሱዳን ፓውንድ ይዛችሁ መርካቶ ትሄዱና ጎመን ትላላችሁ፤ አንዳንዶቻችሁ የኬንያ ሽልንግ ትይዙና መገበያያ ገንዘባችሁ የኬንያ ሽልንግ ነው፤ ፒያሳ ትሄዱና ሸሚዝ ትላላችሁ። እነዚህ ገንዘቦች ምናልባት ባንክ ቤት ሄደው በዕለቱ ምንዛሬ ዋጋ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፤ ከባንክ ቤት ውጭ ከሄዱ ግን ወረቀት ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት አሁን እየገጠመን ያለው የአመራር እጦት ሳይሆን የራስን ዋጋ በውል አለማወቅ ነው። የገንዘብ መሪው፤ የፖሊሲ መሪ ካልሆንኩ ይላል። የሃይማኖት መሪው፤ ሄጄ ዛሬ እስረኛ ካልፈታው፣ ካላሰርኩ ይላል።

የሃሳብ መሪው በሃሳብ ተጽእኖ ማሳደር ሲገባው ከሱ ዘርፍ፣ ከሱ ገንዘብ በወጡ ጉዳዮች መጫወት ያምረውና እንዲሁ ስንዋከብ የአንዱ ገንዘብ አንዱ ጋር ወረቀት፣ ሆኖ ምንም ነገር ሳንገዛ እንውላለን። ሰው የያዘውን ገንዘብ አውቆ የት ጋር እንደሚገበያይ ማወቅ

አለበት፤ ወይም ገንዘቡን ዓለም-አቀፋዊ ማድረግ አለበት። አሉ ጥቂት ሰዎች ገንዘባቸውን ከፍ አድርገው የሚጠቀሙ፤ አብዛኛው ሰው ግን ገንዘቡንና እና ሚናውን ሳያቅ መሪ መሆን ነው የሚያስበው። ማህበረሰቡን እንዲ አርጉ፣ ተነሱ፣ ተቀመጡ፣ ሂዱ፣ ይላል የያዘው ገንዘብ እና የሚገበይበት ገበያ አልገጥም ሲል ነገሮች አይከናወንም። ገንዘባችንን ማወቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

እነዚህን ጉዳዮች ካነሳው ምንወያይበት አንድ ጉዳይ ስለ ምሁር ስለሆነ፣ ምሁር ማነው? የሚያስብ ሁሉ ምሁር ሊባል ይችላል ወይ? ምክንያቱም ሰው ሁሉ ያስባል፤ ሰው ሁሉ ግን ምሁር አይደለም። ታዲያ ምሁራን ከሌላው ሰው የሚለያቸው ምንድነው ብለን እንጠይቃለን። ዩኒቨርስቲ መቆየት ምሁር ያስብላል ወይ? ሃርቫርድ መማር ምሁር ያስብላል ወይ? ዩኒቨርሲቲስ ማስተማር ምሁር ያስብላል ወይ? ምክንያቱም መልህቅ ዘላለሙን ውሃ ውስጥ ቢኖርም መዋኘት ግን አይችልም። ዘላለሙን በእንደዚህ ያለ ግቢ ውስጥ መኖር ምሁር አያሰኝም። ታድያ ምሁርነት መገለጫው፣ እሳቤው ተግባሩ ምንድነው? ዩኒቨርሲቲ መሄድ ለምሁርነት አንድ እርምጃ ወደፊት የሚወስድ ቢሆንም ምሁር የሚያሰኝ ካልሆነ ምሁርነት አስተሳሰብ ነው። ምሁርነት ነገሮችን ለማወቅ ያለ ጉጉት፣ ለጥያቄ ዝግጁ መሆንና የመጠየቅ ብቃት ነው። ለምንድነው የመጠየቅ ብቃት የሚሆነው? ሁሌም ትክክል ጥያቄ ብቻ ነው። መልስ ትክክል ሆኖ አያውቅም። “ጥያቄ ሁሌም ፍጹም ነው፤ መልስ ግን መቋጫ የለውም” ይባላል። ምን ማለት ነው? የዛሬ 2000 ዓመት እግዚአብሔር ማነው፤ ጠይቋል ትውልድ። ግማሹ x ነው፣ ግማሹ y ነው ብሏል። የዛሬ 500 ዓመትም ምናምንም ዛሬም ይጠይቃል። ጥያቄው ይቀጥላል መልሱ ግን እንደየዘመኑ, እንደየሰው ዕውቀት፣ እንደየሰው አረዳድ ይለያያል። አንድ አይደለም፤ የእኛ የቀደሙ አባቶቻችን በእድሜ ማጠር ምክንያት ፈተና ውስጥ ስለነበሩ እድሜ ማርዘምን እንደ ዋና ጥያቄ አርገው አንስተዋል። አንዳንዱ ጤና አዳም በውሃ መጠጣት እድሜ ብሎ መልሷዋል። ግን ይሄ መልስ መቋጫ የሌለው ነው። የለም ተጨምቆ በሶ ቢላ ጋር ሆኖ መድኃኒት የሚል ሃሳብ በየዘመኑ እንደየ እድገት ደረጃችን መጥቷል። አሁን ደግሞ፣ የለም ስፖርት እንስራ፤ ውሃ እና ምግብ እንቅንስ፤ በቀን አንዴ እንብላ፤ ይሄ ሁሉ ነገር መልስ ማለቂያ የለውም ጥያቄ ግን ፍጹም ነው። ሶቅራጥስን ለየት የሚያደርገው የመጠየቅ ብቃቱ ስለሆነ፤ ምሁር በመጠየቅ ብቃቱ ለመጠየቅ ባለው ድፍረትና ቁርጠኝነት የሚለካበት ዋናው ምክንያት ጥያቄ የሚያስከትለው ነገር አለ፤ በጥያቄ ውስጥ ከጥያቄ በኋላ ከውስብስብ ሐሳቦች ጋር ለመታገል ያለው ዝግጁነት ይከተላል፤ የሚጠይቅ ሰው ውስብስብ ሃሳብን ለማስተናገድ የተዘጋጀ ነው ማለት ነው። ኮምፕሌክስ አይዲያን ደሞ ራስን ከማቅናትና ከባለሙያነት ውጪ ሊመጣ አይችልም።

ምሁርነት መጫር መጫር፣ መጫር፤ የጫሩት ነገር እራሱን መጠየቅና መቅደድ፣ መቅደድ፣ መቅደድ፣ እንደገና መጫር፣ መጫር፣ መጫር ይሄ ጽሁፌ አያምርም፣ የቃላት አሰካኬ በቂ አይደለም፤ ዐረፍተ ነገሮቹ ትርጉም የላቸውም ብሎ ያንን ወረቀት መጣል፤ ደግሞ ዝም ብሎ ማንበብ በእንደዚያ ባለ ራስን ከማቅናትና ከባለሙያነት ፍላጎት ውስጥ የሚፈጠር ነገር ነው። እኛ ጋር ሲመጣ የሚቀላቀል ነገር አለ ምሁርነት ጋር፤ ማነው ሊቃውንት? ለቃውንት የምንለው በአንድ የትምህርት መስክ፣ በባዮሎጂ የተማረ፣ ያነበበ፣ ያስተማረ፣ የተመራመረ ሰው ከሆነ፣ ስለ ባይሎጂ እሱን እንጠይቀው ይባላል፤ ሊቅ ነው። አንድ ሰው በኮምፒውተር የተማረ፣ የተመራመረ፣ ያስተማረ፣ ኮድ የጻፈ፣ ከሆነ ኮምፒተር ነክ ነገር ሲገጥመን እሱን እንጠይቀው እንላለን፤ እሱ ነው ሊቅ። ይሄ ሊቅ ምሁር የሚሆነው መቼ ነው፤ ከራሱ የዕውቀት ዘርፍ ባሻገር ከባይሎጂ ባሻገር፣ በፖለቲካዊ ውይይት ውስጥ ከፍ ባሉ ጥያቄዎች፣ ሰብሰብ ባሉ ማኅበረሰብ በተለያየ የዕውቀት ዘርፍ ውስጥ ባለፉ ሰዎች ውስጥ ሀሳብ ማስተናገድ ሲችል፣ የተሰላሰለ ሃሳብ መስጠት ከዚያ የሚመጡ ፈተናዎችን መቀበል፣ እነሱን ማስተናገድ ሲችል ከራሱ የዕውቀት ዘርፍ ሲወጣ፣ ከአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ሲወጣ፤ በማህበረሰብ ሁለንተናዊ ውይይት ውስጥ ጠብ የምትል ነገር የሚያኖር ሲሆን ያኔ ምሁር ይባላል። እኛ ሃገር እንደዛ ነው ወይ የሚለውን እናንተ ጠይቁ እዛው መልሱ።

ሶስተኛው ልሂቃን ናቸው። ሲመስለኝ ኢትዮጵያ ውስጥ በቅርቡ በጣም የቀለለው የቃል አጠቃቀም ልሂቅ ነው። ልሂቅ ማለት በማንኛውም መስክ ተመጣጣኝ ያልሆነ ከፍተኛ ሀብት፣ ሥልጣን፣ ክብርና ልዩ ዕድል ያገኙ ሰዎች ማለት ነው። በጣም ጥቂቶች ናቸው፤ እዚህ ውስጥ ልሂቅ በጣም ጥቂት ነው። ምሁራን ቀጥሎ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ሊቃውንት ብዙ ሊኖሩ ይችላሉ። ልሂቃን በጣም ጥቂቶች ናቸው። ጥቂት የሚያረጋቸው ምንድነው? ከተወሰነ መስክ ሚዛኑን ያልጠበቀ እጅግ ከፍተኛ ድርሻ የወሰዱ ማለት ነው። ለምሳሌ ሀይሌ ገብረ ስላሴ የሩጫ ልሂቅ ነው፤ ደራርቱ የሩጫ ልሂቅ ናት፤ ጥሩነሽ የሩጫ ልሂቅ ናት፤ ቀነኒሳ የሩጫ ነው። የግድ ግን ምሁር ፣ የግድ ግን ሊቅ አይደሉም።

ታዲያ ልሂቅ ማለት በአንድ የተለየ ዘርፍ ትልቅ ድርሻ የወሰዱ የግድ ምሁራን፣ ሊቃውንት ያልሆኑ ብቻ ናቸው? ካላችሁ አይደለም፤ አልፎ፣ አልፎ በጣም አልፎ፣ አልፎ ሰብሰበው የሚወስዱ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን እንውሰድ፤ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሺህ፣ አምስት ሺ የሚጠጉ ታሪክ አጥኚዎች አሉ። ያነበቡ፣ የተማሩ፣ ያስተማሩ፣ የታሪክ አጥኚዎች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። እኚህ ምሁር “የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ” ብለው ለ 140 ዓመት ገደማ ከ1855 እስከ 1991 ገደማ ያለውን የኢትዮጵያ ጉዞ ወደ ኋላ በወፍ በረር፣ ስውር ጎኖችን እንድናይ በከፍተኛ ጥረት አንድ ድልብ ሰነድ አውጥተዋል። ያን ሰነድ ያየ ሰው ከሞላ ጎደል ኢትዮጵያ ምን አይነት ስርዓት እንደነበራት

ምን አይነት መንግሥት መንግሥታት እንደነበሯት፣ እነማን ምን እንዳደረጉ የተወሰነ ግንዛቤ ያገኛል። እኚው ሰው፣ የኢትዮጵያ የለውጥ ፈር ቀዳጆች ብለው ይህ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በነበረበት ወይም ከመመስረቱ በፊት ወደ ተለያየ ሀገር በተለያየ መንገድ ሄደው ተምረው ያዩት የተማሪዎችን ጉዳይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማምጣት ኢትዮጵያ ውስጥ ማሻሻያ ለማካሄድ ስለሞከሩ ሰዎች፣ ስለገጠማቸው ፣ የባህልና የአስተሳሰብ ግጭት የመሳሰሉ ጉዳዮች የሚዳሰስ ሰነድ ሰንደዋል። በዛም ሳይወሰኑ "የሶሻሊስት ኢትዮጵያ ፍለጋ" ብለው የተማሪዎች ንቅናቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን አይነት እንቅስቃሴ እንደነበር አሳይተዋል። ሌላም በርካታ በርካታ ጉዳዮች። በታሪክ በመማራቸው በማስተማራቸው ሊቅ ናቸው። ከታሪክ ውጭ ጂአ ፖለቲካን ለመዳሰስ በመሞከራቸው የአስተዳደር ሥርዓትን በማንሳታቸው፣ የፖለቲካ ውይይት ውስጥ ሀሳብ መስጠት ባለመፍራታቸው፣ ምሁር ያስብላቸዋል፤ ግን ኢትዮጵያ ካለቻቸው አንድ ሺህ ወይም አምስት ሺህ የታሪክ አጥኚዎች ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፤ ልሂቅ ቢባሉ የሚያጣላ ጉዳይ አይመስለኝም። ልሂቅ ያሰኛቸው ብዙ የታሪክ አጥኚዎች ያልሰጡንን ጉዳይ ስለሰጡን ነው። ከታሪክ ውጭ በቋንቋ በስነ ጽሁፍ የሳቸውን ጽሁፎች ምታውቁ ሰዎች እንደምታውቁት፣ በስነ ጽሁፍ ሊመጻደቁ የሚያስችል ብቃት አሳይተዋል። በጂአ ፖለቲካ ተናግረዋል፤ ጽፈዋል። በዚህ ምክንያት የአደባባይ ምሁር የሚሰኝ ማዕረግ ከወሰዱ በኋላ በዘርፋቸው ጎልተው ስለወጡ ደግሞ ልሂቅ ሊባሉ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት ሰዎች አልፎ አልፎ ያጋጥማሉ።

አሁን እኛ ግን ልሂቅ የምንለው እንደዛ ነው ወይ ነው? ዩቲዩብ ላይ የተጣደ በሙሉ እኮ ነው ልሂቅ የሚባለው። ምንድነው በተግባር በዛ ቦታ ላይ ምን አይነት ሀሳብ ነው ያመነጨው፤ በዛ ሃሳብ ምንድነው ተጽእኖ ያደረገው? ከሌሎች በምን ይበልጣል? በምን ያንሳል? የሚባል ግልጥ ያለ መስፈርት በሌለበት ስያሜውን እንጠቀማለን። የመጨረሻው መካንቶች ናቸው፤ መካንንት ማኅበረሰባዊ የደረጃ መደብ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከጥቂት አስር ዓመታት በፊት የነበረ ጉዳይ ነው፤ አሁን እየተዳከመ ይመስለኛል። መሳፍንት ፍጹም በደም የሚገኝ ነው። ራስ እምሩ፣ ራስ መኮንን ሲባል በደም የሚገኝ ነው። መካንንት ግን የግድ ደም ላይሆን ይችላል። በእውቀት መካንንት የሚሆኑ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ እንዳልካቸው መኮንን መውሰድ ይቻላል፤ መካንንት ነበሩ ግን በደም አልነበረም። አክሊሉ ሃብተወልድን መውሰድ ይቻላል፤ መካንንት ነበሩ ግን በደም አልነበረም። ወይም ሀብቴ አባ መላ መውሰድ ይቻላል፤ መካንንት ነበሩ ግን በደም አልነበረም። በእውቀት ያንን ማእረግ የሚያገኙ ሰዎች፣ በዚያም ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሰዎች ነበሩ።

አሁን በመካከለኛው ምስራቅ በስፋት ማኅበረሰቡን በመምራት ረገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩት ኃይሎች መካንንት ናቸው። የወደቀ ነገር አይደለም፤ እኛ የት ውስጥ

እንደምንኖር በትክክል አውቀን ገንዘባችንን ለይተን መጠቀም ስንችል እምብዛም ጭቅጭቅ ላይፈጠር ይችላል። አልያ ግን ሁሉም እየተቀላቀለ ስሞችን በሚወስድበት ሰዓት ውዥንብር ብቻ ሳይሆን መግባባት እና አብሮ መስራት ያስቸግራል። በተለይ ብናየው ምፈልገው ጉዳይ የምሁርነትና ብልህነት ጉዳይ ላይ ያለው መረዳት ነው። ምሁርነት ቅድም እንዳነሳሁት ውስብስብ ጉዳዮች ለመዳሰስ መሞከር፣ ያን ሃሳብ ለመናገር ለማድመጥ፣ ለመጠየቅ መዘጋጀት፣ በማሰብ አቅም ላይ የሚሰራ ስራ ነው። በማሰብ አቅም ግንባታ ላይ የሚሰራ ስራ ነው ብልህነት ከማሰብ አቅም ይሻገራል፤ የስሜት ብልህነትን ያቅፋል፤ ማኅበረሰባዊ ወይም የቦታ አረዳድ ብልህነትን ያቅፋል፤ በማሰብ አቅም ላይ ይሰራሉ። ይሄም ተቀላቅሎ የምንቸገርባቸው ጊዜ በርካታ ናቸው። ብልህነት ችሎታ ነው። በሌላ በኩል ምሁርነት ያንን ችሎታ እንዴት ወደ ተግባር እንደምንቀይር የሚገራን ነው።

ይሄን በምሳሌ ለማሳየት ለምሳሌ አይዛክ ኒውተን እንውሰድ አይዛክ ኒውተን በጥንታዊ መካኒክስ ላይ፣ ፊዚክስ እና በሒሳብ 16ኛው አጋማሽ ጀምሮ ላለፉት 400 እና ከዚያ በላይ ዓመታት በተከታታይ መሠረታዊ የሆኑ ሃሳቦች፣ ያልተቆራረጠ በየጊዜው እያደገ ወይም ቴክኖሎጂ እያደገ ሀሳቦች በእንቅስቃሴ ሕግጋት፣ በዓለም-አቀፍ ስበት ሕግ ፣ በብርሃን ሳይንስ ደግሞ የብርሃንን ጣሪያ ፣ ካልኩለስ የመሳሰሉትን ሰቶናል። ካልኩለስ የሰጠን 1665 ነው። አይዛክ ኒውተን ካልኩለስ ከሰጠን በኋላ የነበረው እድሜ 26 ዓመት ነው፤ ይሄን ሁሉ ነገር ሲፈጥር ይሄ ሰው ከ ሰላሳ አመት በታች ነበረ፤ ለ60 ዓመት ያነበብን ሰዎች ለ70 ዓመታት ያነበብን ሰዎች ያልፈጠርነውን ነገር ከፈጠረ ይሄ ሰው በዛ እድሜው፤ ብዙ አንብቦ ምሁር ስለሆነ ነው ብለን ማሰብ አንችልም። በእርግጥም ምሁር ነው። ግን ብልህነቱን በተለየ መንገድ መጠቀም የቻለ ሰው ነው። ምክንያቱም በሃያ ምናምን ዓመት የሚነበበውን 70፣ 80 ዓመት አንብበው ሰዎች መስራት ካልቻሉ አንደኛው ብልህነቱን ብቻውን እንደዚህ ላለው ወጣ ላለ ፅውቀት አስቻይ አይሆንም ማለት ነው። ሁለተኛ አልበርት አንስታይን እንውሰድ አልበርት አንስታይን የአንጻራዊነት መርህን ትርጉም ሲሰጥ 26 አመቱ ነው። በ26 ዓመቱ፣ ከሰላሳ በታች እያለ የፈጠራቸውን ጉዳዮች በኋላ ከፈጠራቸው ጋር አታወዳድሩትም፤ ብዙ ካነበበ በኋላ እና በ26 አመቱ ምሁር ስለነበረ በጣም አንብቦ ነው እዛ የደረሰው ቢባል አይደለም። በእርግጥም ምሁር ነው፤ ነው ግን ከምሁርነት በተጨማሪ፣ ብልህነቱን በብቃት መጠቀም የቻለ ሰው ነው። አሌክሳንድር ዘግሬት ያን የሚያክል ግዛት የፈጠረው 30 ዓመት ሳይሞላው ነው። ግዛት ለመፍጠር ከሰሜን አፍሪካ ፣ አውሮፓን በከፊል የሚያክል ሃገር ለመፍጠር የ30 ዓመት ንባብ በቂ ነው ወይ? ምንም አስተማሪው አሪስቶትል ቢሆንም ብልህነትን መጠቀም ካልተቻለ አይሳካም። ማሪ ኩሪ የጨረራ አመንጪነትን ትርጉም ስትሰጥ ሰላሳ ዓመቷ ነው፤ የኖቤል ተሸላሚ ስትሆን ሰላሳ ስድስት አመቷ ነው፤ በ30 ዓመቷ የጨረራ አመንጪነትን ትርጉም

ስትሰጥ ሰላሳ ዓመቷ ነው፤ የኖቤል ተሸላሚ ስትሆን ሰላሳ ስድስት አመቷ ነው፤ በ30 ዓመቷ የጨረራ አመንጪነትን ትርጉም የሰጠች አንዲት ብልህ ሴት፣ 60 70 80 90 ዓመት ሰዎች በዚያ ዙሪያ አንብበው በዛ ዙሪያ ተነጋግረው አስተምረው ጨረራ አመንጪነትን ወደ ቴክኖሎጂ ለመቀየር አሁንም አለ።

የሷ ቴክኖሎጂ ባይኖር ኖሮ ኒየኒውክሌር ግብረ-መልስ የሙቀትና የኤሌክትሪክ ኃይል እንዴት እንደሚፈጥሩ፣ የጨረራ መበስበስን ወይም ራዲዮአክቲቭ ዲኬይ ማወቅ አይቻልም ነበር፤ በ30 ዓመቷ እንደዚህ ያለውን ብልህነትን የሚረዳና የሚያበረታታ የምሁር ማኅበረሰብ ካልተፈጠረ በስተቀረ ባነበብናቸው መጽሐፍት፤ ባጠራቀናቸው ወረቀት ልክ ብቻ የሚለካ ከሆነ ዘመን ቀያሪ ትውልድ አሻጋሪ ማርሽ ቀያሪ የሆኑ እሳቤዎች መፍጠር አይቻልም። ይሄንን ሁላችሁ የምትገነዘቡት ቢሆንም በየቀኑ የምንኖረው መሆን አለበት ችግር ስለሆነ። ኢትዮጵያ ውስጥ እዚህ አብሮት ላይብረሪ ህጻን ልጅ ሮቦት ለመስራት ሞክሮ ድሮን ለመስራት ሞክሮ ያሳየኝ ልጅ አለ። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያላጠናቀቀ ይህንን ልጅ በሮቦት ጥናት፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ በቁስ ሳይንስ “ተመርቄያለሁ” የሚለው ሰውዬ ያልሰራውን ስራ የሰራውን ሰው እንዴት እንደሰራው አውቄ ማበረታታት ካልቻልኩ፣ ግድ የለም አንተ ለመፍጠር መጀመሪያ መመረቅ አለብህ ካልኩት እንዳለን እንቀራለን ማለት ነው።

የምሁርነት መገለጫው ምንድነው? ምሁርነት ሃሳብ አከባሪ፣ ሃሳብ አፍቃሪ መሆን አለበት። ጥልቅ አሰላሳይ ብዙ ጠያቂ መሆን አለበት። አንባቢ፣ ነቃሽ፣ ተንታኝ መሆን አለበት። ችግር ፈቺ እና ያነበበውን፣ ያደረጀውን ዕውቀት ወደ ተግባር ቀይሮ የማኅበረሰብን የኑሮ ዘዬ የሚያቀል መሆን አለበት። አመዛዛኝ ሰዎች ነገሮችን ከተለመደው መንገድ በተለየ መልኩ የሚያዩ መሆን አለባቸው። ውስብስብ ጉዳዮች ብዙ ጋሪጣ ብዙ ችግር፣ የሚያጋጥማቸውን ፈተና ለመፍታት፣ ለመተንተን ብቃት ያላቸው፤ ዕውቀትን ወደሚጨበጥ ተግባር መቀየር የሚችሉ መሆን አለባቸው።

እንደ ሐሳብ ወይም የጥበብ አፍቃሪ እንደምሳሌ ብዙ ጊዜ የሚነሳው ፕሌቶ ነው። ፕሌቶ እንደምታውቁት በነበረበት ዘመን ቤተሰቦቹ ከሞላ ጎደል ሻል ያለ የደረጀ ኑሮ ያላቸው የሚባሉ ናቸው። በዚያ በቤተሰብ በሀብት በተለመደው መንገድ ከመሄድ ይልቅ ጠያቂውን ሶቅራጥስ መከተል ፈለገ። የሶቅራጥስ ህይወት በጥያቄ የተሞላ፤ በኑሮ ደረጃ ከቤተሰቡ ያነሰ ነው። ይህ ሰው ግን ጥበብ አፍቃሪ ስለሆነ በዚያ ጊዜ በነበረው እሳቤ ምኞት ከሚመስለው የህይወት ሁኔታ ወቶ ጠያቂውን መከተል መረጠ። ሶቅራጥስ የመጠየቅ ዘዴን በማስተማር፣ በመራመር ፕሌቶን ሰራው። ሶቅራጥስ ብዙ አልፃፈም

ብዙ ጠየቀ እንጂ። ፕሌቶ ግን የሱ ተማሪ ሆኖ እስከ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ምነጋገርበትን የዛሬ ሁለት ሺ አራት መቶ ምናምን ዓመት ነው ይሄ ሰውዬ የነበረው፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት አራት መቶ ምናምን ዓመት ያኔ ነው ፍትህ፣ ስለ እውነታ ተፈጥሮ ፣ ስለ መንግሥት ምሥረታ ሐሳብ ፤ ከዚያም ባለፈ ደግሞ የአውሮፓን የከፍተኛ ዕውቀት መቅሰሚያ ተቋም የፈጠረው።

ፕሌቶ በነበረበት ዘመን ያሉ ወላጆቹ የነበሩበት ማኅበረሰባዊ ደረጃ የተሻለ ቢሆንም ዛሬ ግን እነሱን እንኳን የምናስታውሰው በሱ ምክንያት ነው አናስታውሳቸውም። ለምን? የሚወደውን አውቆ የሚወደውን መርጦ ለሚወደው ተከትሎ ጠይቆ የጠየቀውን ደግሞ በተሰናሰለና በቅደም-ተከተላዊ መንገድ ዕውቀትን ማደራጀት፣ ማሸነፍ መሸጋገር ስለቻለ ነው። ያ ብቻ ግን አይደለም ከሱ የላቀውን ማስተማር ስለቻለ የፕሌቶ ተማሪ የሆነው አሪስቶትል ከሱ ከመማሩ ባሻገር ተፈጥሮን በትኩረት በመመልከት፣ የተፈጥሮን አጠቃላይ ስርዓት ለማስተዋል በጥልቀት ለማሰብ ከአስተማሪዎች የተሻለ ጉዞ ተጉዟል። በደንብ ለማየት ችሏል። በዚያም ምክንያት ሥነ-አመክንዮን ፣ ሥነ-ምግባርን፣ የፖለቲካ ሳይንስንና የሕይወት ጥናትን በጣም በርካታ ጉዳዮች አርስቶትል አበርክቶልናል። ይሄ ብቻ ግን አይደለም፤ የአሪስቶትል ደሞ ለየት የሚያደርገው ከነሱ እዚህም ያለውን ውዥንብር ለማጥራት ታላቁን እስክንድርን ያስተማረው አሪስቶትል ነው። አሪስቶትል ያነበበ የጻፈ ቢሆንም፣ ግዛት ለመገንባት እኔ ነኝ አላለም። ግዛት ለመገንባት የሚችልን ሰው ነው የሰራው። እናንተ ያነበባችሁ እና የጻፋችሁ የግድ ግዛት ገንቢ መሆን አይጠበቅባችሁም፤ ግዛት ገንቢ መስራት ግን ትችላላችሁ። ግዛት ገንቢ ስትሰሩ፣ በዚያ ሰው ስራ ውስጥ የእናንተ ትምህርት ጎልቶ ሊታይ ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እንደዚህ አይደለም። እኔ ኬንያ ዩኒቨርሲቲ የተመረቅኩ ሰውዬ እያለሁ እንዴት ጅማ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀው ሰውዬ ሚኒስቴር ይሆናል ይላል። በሱ ሳይሆን ገብቶ በወጣበት ግቢ ራሱ ሲለካ ማለት ነው። ምሁራን ግዛት ገንቢን ከሰራን ስራችንን ሰራን ማለት ነው።

ምሁራን ዘርፈ ብዙ ሚናዎች አሉን፤ መጫወትም እንችላለን። አንደኛውየእርስ በርስ ተፅዕኖ ነው። በምሁራን መካከል ጥብቅና ጥልቅ ሙግት በማካሄድ የተመረጡና የተራቀቁ የዘመኑን ጽንሰ-ሐሳቦች ማፍለቅ ይችላሉ። እዛም፣ እዛም እዛም ያለን የንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ) አንብበው የነሱን ነባራዊ ሁኔታ አጥንተው ወደ የሃገር አውድ ይመልሳሉ። እንዳለ ቀድተው አያመጡም። እንዳለ ቀድቶ ማምጣት ጣጣውን አይታችሁታል። ያነባሉ፣ ይማራሉ፤ በራሳቸው አውድ ውስጥ ያ ነገር እንዲመጣ ያደርጋሉ። ወደ እኛ መገለጫና ባሕርይ መቀየር የሚያስፈልገው ዓለም ላይ በምናብ በርቀት የምናዳምጠው ነገር ስንገባበት በሙሉ እንደዛ ላይሆን ስለሚችል ነው። ሁለተኛው ትውልድ ላይ

ተጽእኖ ማሳደር ነው። ጠያቂ፣ አሰላሳይ፣ ስራ ወዳድ፣ ሀገር ወዳድ ትውልድ መፍጠር በረባ ባረባው የሚሸሽ፣ በረባ ባረባው ልውጣ የሚል ሳይሆን በፈተና ውስጥ አልፎ ሃገር የሚሰራ ትውልድ መስራት።

ሶስተኛው ማኅበረሰብን የሞራል አቅጣጫ እንዳይስት የሥነ-ምግባር መሪ ሆነው በተለይም ውስብስብ ከሆኑ ዕሴቶች ጋር እንዲታገል ማኅበረሰብን ማንቃት ማስተማር ሌላው ስራቸው ነው፤ አስኳል ሆነው የሚያገለግሉበት ስራቸው ነው። ዕሳቤን በሚመለከት ሼልፍ ላይ ያሉ ንድፎች ተግባር እንዲቀየሩ ሃሳቦች አሉ፤ ጽሁፎችሑ ያ ግን ወርዶ ወደ ተግባር እንዲቀየር የማድረግ ስራ ነው። በዓለም-አቀፋዊው ሒደትም ቅድም እንዳልኩት፣ አዳዲስ እየመጡ ያሉ አዝማሚያዎችን በማየት፣ በማንበብ በማወቅ ወደኛ፣ ወደ ሃገርኛ ቋንቋ፣ ወደ ሃገርኛ አሰራር በመመለስ የዓለም አቅፉን አዝማሚያዎች የሚከተሉ መሆን አለባቸው። ለዚህ ሁሉ ውስጥ ዘርፈ ብዙ ሚና ነው ያላቸው ማለት ነው። ይሄ ሚናቸውን ወደ ተግባራዊ ሚና ብንከፍለው በሶስት ከፍለን ማየት እንችላለን።

አንደኛው የዕውቀት ዘር መዝራት ነው። የዕውቀት ዘር መዝራት ማለት ከቀደምቶች፣ ከአባቶች ከታሪክ የገበዩትን ዕውቀት ለዛሬ እንዲመች ቅርጽ ማስያዝ፤ ተጨማሪ ማንበብ፣ ተጨማሪ መከራከር፣ ተጨማሪ መወያየት እና ያ እውቀት ከነሱ ሰፈር ከነሱ ክፍለ-ትምህርት ወቶ ዓለም አቀፋዊ እንዲሆን ማድረግ ነው። የዕውቀት ዘር ጠብ ካለ በኋላ ጊዜውን ጠብቆ ዓለም አቀፋዊ ይሆናል ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ደግሞ የመቶኛው ዝንጀሮ ውጤት የሚባለው ነው።የመቶኛው ዝንጀሮ ውጤት 1950 በጃፓን ኮችሞ በምትባል ደሴት የሚኖሩ ዝንጀሮዎች ነበሩ። ከነዚህ ዝንጀሮዎች መካከል አንደኛው ዝንጀሮ አንድ ቀን ጠዋት ተነስቶ ስኳር ድንች አጥቦ ይበላል። ከዚያ በፊት አጥቦ አይበሉም አንስተው ይበላሉ።

ማን እንዳስተማረው፣ ማን እንደነገረው አይታወቅም አንስቶ አጥቦ ይበላል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁለተኛው ሶስተኛው አራተኛው እያለ እዛ ደሴት ላይ ያሉ ዝንጀሮች በሙሉ በነሱ አገላለጥ መቶኛው ዝንጀሮ ጭምር እያጠቡ መብላት ባህላቸው ይሆናል በደሴት ውስጥ። መቶኛው ዝንጀሮ ማጠብ ከጀመረ በኋላ ከደሴት ውጪ ሌላ ቦታ ሄደው፣ ያን ዝንጀሮ ሲያዩ እነሱም እያጠቡ መብላት ጀምረዋል፤ ይሄ 1950 የሚወራ ታሪክ ነው፤ ታውቂት ይሆናል ሃሳቡን ከኮሽሚ ደሴት ውጪ ያሉ ዝንጀሮች እንዴት በሉ የሚለውን በአእምሮ ግንኙነት ሊሆን ይችላል። ወይም አንድ ዕውቀት ተዘርቶ መጥቶ የሆነ ቦታ ከደረሰ በኋላ የመዳረስ አቅም አለው፤ የሚል ድምዳሜም የሰጡ ሰዎች አሉ። እነዚህ የዕውቀት ዘር የመዝራት ጉዳይ ዓለም አቀፋዊ እስከሚሆን ስንሄድበት የለውጥ አቅጣጫን የመቀየስ፤ ያሰብነውን

የመተግበር፤ ለለዉጥ ለዝመና የሚሆን ሃሳቦች ዘዴዎች እሴቶች ከፈጠርን በኋላ ያ ዓለም አቀፋዊ እስከሚሆን የሚወስድ ጊዜ ቢኖርም፣ ዘሩ ግን ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከዘሩ በኋላ ያ የለውጥ አቅጣጫ፣ ያ ዘር የለውጥ አቅጣጫ ትክክለኛውን መስመር ከያዘ በኋላ፣ ማጎበረሰብ ውስጥ የፈጠረውን የዕውቀት ጥግታ ለማወቅ፣ ማስተማር፣ የሞራል ደረጃን ከፍ ማድረግ፣ ምክንያታዊ እሳቤን ማጉላት፣ ማህበረሰቡ የዛን ዘር የዛን የለውጥ አቅጣጫ ተሸካሚ እንዲሆን ማድረግ ይጠይቃል። ይህ እንዲሆን የለውጥ አቅጣጫ የምንቀይስ ዘር የምንዘራ ሰዎች የፈጠራ ባህል፣ የስራ ባህል የዴሞክራሲ ባህል፣ የሲቪክ ባህል፣ የጽዱ ከተማ ባህል፣ እኛ ስላሰብን እና ስላወራን በአንድ ምሽት የሚሆን ከመሰለን አይሳካም። ያቺ የመጀመሪያዋ ዝንጀሮ መቶ ጋር እስኪደርስ ረዥም ጊዜ ወስዶባታል። መቶ ጋር ከደረሰ በኋላ ግን የማታውቀው፣ የማትደርስበት ቦታ ሁሉ ደርሷል። ለምሳሌ እዚህ ሀገር የጀመርነው የኮሪደር ልማት ብንወስድ ገና ነው፤ የመቶኛው ዝንጀሮ ውጤት ላይ አልደረሰም፤ ገና ነው። ሲደርስ ግን እንዴት ብሎ ሌሎች አፍሪካ ሃገሮችን ተፅዕኖ እንደሚያደርግ ከኛ ቁጥጥር እና ልፋት ውጪ ሊሆን ይችላል። በማናውቀው መንገድ ያ እሳቤ፣ ያ አሰራር፣ ያ ፍልስፍና ቦታ ይዞ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ያ እስኪመጣ ግን በትጋት ሳናቋርጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ በመትጋት ማረጋገጥ ይኖርብናል። ምሁራን ልዩ ልዩ ዘርፍ ከመንካታቸው በተጨማሪ አስተሳሰብ ላይ ለይቶ ለማን ምን አይነት አስተሳሰብ ያስፈልጋል የሚለውን እንደዘር መዝራት ይፈልጋል።

ሁሉም ቲንኪንግ አንድ እና ያው አይደለም፤ ለሁሉም አስተሳሰብ ላይ ግን ምሁራን አስኳል ናቸው፤ ኒውክለስ ናቸው። ያን የማሳደጉ ጉዳይ የተማረው ሰው ጉዳይ ቢሆንም፣ ለምሳሌ ስትራቴጂካዊ አስተሳሰብ የምንለው የተቋማት መሪዎች የውትድርና መሪዎች አካባቢ የሚሰራ ጉዳይ ነው። ትልቅ ምስል ማየት፣ ዘላቂ ጥቅምን አስቦ መወሰን፣ ቀድሞ የመተንበያ አቅምን ማሳደግ ይሄ የወታደራዊ፣ የተቋማት መሪ ባህሪ ነው። ለምሳሌ አንድ ለምሳሌ አንድ ስትራቴጂካዊ አመራር የሚባል ወታደር በውጊያ እና በጦርነት መካከል ያለውን ልዩነት በደንብ አድርጎ የሚገነዘብ መሆን አለበት። እኔ ያለኝ የወታደር ቁጥር መቶ ቢሆን ዶክተር ሳሚ ያለው የወታደር ቁጥር አንድ ሺህ ቢሆን፣ መቶ ወታደር፣ አንድ ሺህ ገጥሞ ማሸነፍ አጠቃላይ ውጊያንና ጦርነቱን ማሸነፍ እንደማይችል ስለምገነዘብ፣ ሁልጊዜ ጥንቃቄ ማረግ ያለብኝ ከኔ ያነሰ ኃይል ከሌለ በስተቀር ግጭት አለመፍጠር ነው። ለምሳሌ አንድ ሺዎቹ እየመጡ በቅርብ ርቀት አስር ሰው የጠላት ባገኝ እኔ አስሩን ልመታ እችላለው የኃይል ብልጫ ስላለኝ፤ እሱን ካሸነፍኩ በኋላ ግን ከ900 በላይ የሆነው ይውጠኛል። ይቺን አስር ሰው ማሸነፍ ማለት አጠቃላይ ውጊያ ማሸነፍ ማለት አይደለም፤ አጠቃላይ ጦርነት ከብዙ ውጊያ ድምር የሚመጣ ቢሆንም በአንዳንድ ውጊያ ማፈግፈግ፣ መሸሸ፣ መደበቅ፣ የሚያስፈልገው በድምር ጦርነት ለማሸነፍ ነው። ይሄን የሚያስብ

መሆን አለበት እንጂ ፻፴ ሰው ስላለው ሶስት ሰው ሲያይ የሚገል ከሆነ በስትራቴጂካዊ መንገድ አያስብም ማለት ነው።

ይሄ ስትራቴጂካዊ አስተሳሰብ ነው። ሥርዓተ-መዋቅራዊ አስተሳሰብ ከሆነስ? ሥርዓተ-መዋቅራዊ አስተሳሰብ ፖሊሲ አውጪዎች፣ መሃንዲሶች ሃኪሞች፣ የሚገለገሉበት፤ ለምሳሌ ሀኪም አንድ ሰው ኩላሊቴን አሞኛል ብሎ ሲሄድ ዘሎ ኩላሊት ጋር አይሄድም፤ የሙቀት መጠን ይለካል፤ ደም ስር አንዳንድ ነገሮችን ያያል፤ ሁሉንም ሥርዓት ነው የሚያየው እንጂ ያ ችግር አለበት የተባለን የሰውነት ክፍል ብቻ ሮጦ አያክምም። ዙሪያ መለሱን ካየ በኋላ ወደዛ ይሄዳሉ። ወይንም አንድ መሃንዲስ ይሄንን ቤት ሲሰራ መጀመሪያ ይሄኛውን ምሰሶ ቀጥዬን ግድግዳ አይልም፤በዲዛይኑ በእያንዳንዱ ደረጃ ምን እንደሚያስቀምጥ ኮንክሪቱም ምን እንደሚመስል መጀመሪያ ነው የሚያስበው። ለምን የዚህ ጣራ የሚቀጥለውን ለመሸከም ያለው አቅም የሚወስነው አስቀድሞ ስለሆነ፣ መሐንዲስ ሥርዓተ-መዋቅራዊ ነው እንጂ የሚያስበው በእያንዳንዱ ክፍል አያስብም።

ሶስተኛው የፈጠራ አስተሳሰብ ነው። ቴክኖሎጂዎች፣ የንግድ ፈጠራዎች፣ ከያኔዎች ዋና ጉዳያቸው ከልምድ እስር እራሳቸው ማላቀቅ ነው። ኋላ ቀር የልማድ አጥሮች የሚሸብቡት ማንኛውም የፈጠራ አሳቢ ነኝ ባይ አዲስ ፈጠራ መፍጠር አይችልም፤ ያን አጥር መስበር ካልቻለ በቀር። አደጋ መጋፈጥ ብቻ ሳይሆን ተሻግሮ ማየት ይጠይቃል። አመዛዛኝ ሰዎች አሉ፤ ፈላስፋዎች፣ ጸሃፍቶች፣ የህግ ሙያተኞች፣ ነገርን መሠረታዊነት የሚያዩ፣ ምክንያት መተንተን፣ ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚችሉ፤ የተደራጀ ሃሳብ ሰንሰለት መፍጠር የሚችሉ፤ አንድ ጊዜ የሚያስቡት ሃሳብ ሳይሆን ሲሰናል ውጤቱን ማየት የሚችሉ፤ ግን እነዚህ ብቻ አይደለም ከተለመደው ውጭ አዲስ አቅጣጫ የሚቀይሱ አሳቢዎች አሉ፤ ከተለመደው አስተሳሰብ ውጭ የሚያስቡ ማለት ነው። እነሱን የሚያስተናግድ፣ የሚያረግ ለነሱም አስኳል የሆነ መሆን አለበት ምሁር።

የንድፍ አስተሳሰብ አለ፤ የተጠቃሚን አገልግሎት ማዕከል አድርጎ የሚሰራ፤ ማዕከላዊ መፍትሔ ላይ የሚያተኩር አስተሳሰብ ፣ አንዲት ምርጥ ነጠላ መፍትሔ ላይ የሚያተኩር፤ ሊኖሩ ከሚችሉ በመቶዎች ከሚቆጠሩ መፍትሔዎች መካከል ያቺን አንዲን ነጠላ መፍትሔ መምረጥ ማዕከላዊ አስተሳሰብ ይባላል። ወይም ዘርፈ-ብዙ አማራጭ የሚያመነጭ አስተሳሰብ ሊኖር ይችላል፤ እሱ ደግሞ በርካታ ሐሳቦችን ማፍለቅ ነው። እነዚህን የአስተሳሰብ መንገዶች በየፈርጁ፣ በየደጁ እያወቅን አስኳል ካልሆንን፣ ብዙ ዓይነት እሳቤዎችና ፍላጎቶች ስላሉ የቋንቋ አለመግባባትና የዕሴት መደባለቅ ይፈጠርብናል።

በምሁርነት ውስጥ ያሉ እንቅፋቶች ታዲያ ምንድናቸው? ምሁራን ያሰቡትን የጻፉትን ያስተማሩትን መኖር እንዳይችሉ የሚያደርጋቸው እንቅፋት ምንድነው? አንደኛው ስሜታዊነት ነው። ምሁር ማለት የስሜት ህዋሶቹን ተጠቅሞ መረጃ የሚሰበስብ, አካባቢውን የሚረዳ እንጂ በስሜት የሚነዳ ማለት አይደለም። በነዛ መረጃ ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ግን በስሜት የሚነዳ መሆን የለበትም። ሁለተኛው አድሏዊ እሳቤዎች የሚያስከትሉ፣ ኢ ምክንያታዊ እንዲሆን የተዛባ ድመዳሜ ላይ እንዲደርስ የሚያደርጉትን ባህሪዎች ምሁር ከራሱ ያርቃል። አድሎ ካለ ወገንተኝነት ይከተላል፤ ድምዳሜው ይበላሻል። ሶስተኛው ጀመኝነት ነው፤ ቡድንተኝነት ነው፤ ሰው በግሉ ነው ማሰብ ያለበት። ሰው በቡድን ማሰብ ከጀመረ ፈቀቅ ማለት አይችልም። በግል የማሰብን አቅም የሚገዳደር ነገር እንዳይፈጠር ምሁራን ሚናቸው ከፍተኛ ነው። ከእውነት ይልቅ ከሌሎች መመሳሰል ተጨማሪ ብቻ ይሆናል ማለት ነው። ለምን የሚል ጥያቄ ከቀረ የምሁር አንዱ አንጓ ሞተ። አራተኛው ርዕዮት እና ቀኖና፣ አዲስ ነገር ለመመልከት ዝግጁ አለመሆን፤ ይሄ ለምሳሌ የተማሪዎች እንቅስቃሴን ብትመለከቱ ከብዙ አስርት አመታት ዛሬ በዚህኛው ጎራ የነበረ ሰው በምክንያታዊነት ያኛውን ጎራ መገመገም አይችልም። ዛሬ እየሞተ ትክክል ነበርኩ ይላል እንጂ እዚህ ጋር ጥሩ ነበርኩ፤ እዚጋ ጥሩ አልነበርኩም አይልም ዛሬም። ይሄ የሚያሳየው ቀኖናዊነት ነው፤ ለርዮት የበዛ ጥብቅና ሲኖር ማለት ነው።

አምስተኛው የመረጃ ጎርፍ ነው፤ በጣም ብዙ መረጃ ነው ያለው። የመረጃ ብዛት ከልክ ያለፈ እንደሆነ የማመዛዘን እድልን ያጠፋል። ልክ የተለያዩ ነገሮች በብዛት ስንመገብ የመፈጨት ችግር እንደሚያጋጥመን መመርመር የማንችለው የኢንፎርሜሽን ፍሰት ወደ አእምሯችን ከመጣ የአእምሮ አለመስማማት ያስከትላል። በጣም ብዙ መረጃ ሳይሆን፣ የተተነተነ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ስድስተኛው ትዕቢት እና ማን አለብኝነት ማን አህሎኝነት፤ ለነገሮች ልብን ከፍቶ ለመማር ዝግጁ አለመሆን፤ አእምሮ “አስቀድሜ አውቀዋለሁ” ሲል፣ የማወቅ ጉጉት ይሞታል ይላሉ። መጠየቅ ማለት፣ ለመማር በር መክፈት ማለት ነው። ያልጠየቀ ሰው ለማወቅ በር አልከፈተም፤ በር ካልተከፈተ መግቢያ መንገድ የለም። እነዚህ ባህሪያት እንቅፋቶች ናቸው፤ እነዚህን ባህሪያት እያንዳንዱ ምሁር እራሱን እየፈተሸ እራሱን እያዳመጠ ሊገራቸው ሊያስተካክላቸው ይገባል።

አንድ ጥሩ ምሳሌ አለ ይሄንን የሚገልጽ፤ አንድ አሳቢ አንባቢ ምሁር በአንድ ወቅት በአንድ ጀልባ አንድን ባህር ይሻገራል። ልክ እንደ ተሳፋሪ ትራንስፖርት ከፍሎ ነው የሚሻገረው። ውሃ እንደምታውቁት ጠጋ እያላችሁ ስትሄዱ ድምጸቱ፣ ቅዝቃዜውና አጠቃላይ የባህር

ሁኔታ ለሀሳቢያን የመመሰጥ እድል ይፈጥራል። እና ሰውየው ባህር ላይ በሚያያቸው እንቅስቃሴዎች፣ ወጀቦች፣ የውሃ ፍሰቶችና ንፋሶች ተመስጦ ሰማይ እያየ ይቆይና መለስ ብሎ ጀልባ ቀዛፊውን "አንተ ሰው ሰማይ ላይ ስላሉ እውቀቶች፣ ስለ ከዋክብት ፣ ስለ ጨረቃ፣ ስለ ጠፈር ምን ያክል አንብበሃል? ምን ያክል ታውቃለህ?" ይለዋል። ጀልበኛውም "ኧረ ጌታዬ ምንም አላነበብኩ፣ ምንም አላውቅም" ብሎ ይመልሳል። "እሩብ ያህሉን እድሜህን እንዲሁ በከንቱ በልተኸዋል" ይለዋል። ጀልባ ቀዛፊው ዝም ይላል። ትንሽ እየተጓዙ ሲሄዱ በርቀት ተራራ ያያል። ያስብና መለስ ብሎ "ለመሆኑ ስለመሬት፣ በከርስ ምድር ስላሉ ሀብቶች፣ ስለ እጽዋት ምን ያክል አንብበሃል?" ይለዋል። መልሶ ጀልባ ቀዛፊው "ኧረ ጌታዬ አላነበብኩም" ይለዋል። "በቃ ሩብ ያህሉን እድሜህን በከንቱ በልተኸዋል" ይለዋል አሁንም። ትንሽ ከቆዩ በኋላ ውሃውን እያየ ተመስጦ ቀና ይልና "እሺ ስለ ውኃስ፣ ስለ ውቅያኖስ ጥናት ምን ያክል ታውቃለህ? በውቅያኖሱ ስላሉ ሀብቶች ምን ያክል አንብበሃል?" ይለዋል። "ኧረ ጌታዬ እኔ ከመቅዘፍ ውጪ አላነበብኩም" ሲለው "ሩብ ያህሉን እድሜህን በከንቱ አሳልፈኸዋል፣ በልተኸዋል" ይለዋል። ሰባ አምስት በመቶውን የሰውየውን እድሜ፣ ፈራጅ የሆነው ምሁር ወሰደበት እና በሁለቱ መካከል ዝምታ፣ በሁለቱ መካከል ቁዘማ መጣ። ምሁሩም አብዛኛው ህይወቱን በከንቱ ካጠፋ ሰው ጋር ነው እየተጓዘ ያለው። አሳፋሪውም "የማደርሰው ጋር ደርሼ ከፍሎኝ እንደሄደ ህይወቴን በየፈርጁ እየቀናነሰ፣ ህይወቴን የማልኖር ሰው አደረገኝ" ብሎ ቁዘማ ውስጥ ገብቶ እያሰበ እያለ ከተወሰነ አፍታ በኋላ ባህሩ ላይ ወጀብ ይነሳል።

ቀዛፊው አንዳንዴ ወጀብ ሲነሳ እንዴት አቅጣጫን ማስተካከል ማድረግ እንዳለበት ያውቃል፣ ባህሪያቸውንም ያውቃል፣ ከየት አቅጣጫ ንፋስ ሲመጣ አደገኛ እንደሆነም ያውቃል፤ ሁኔታውን አይቶ እንደማያዋጣ ሲገባው "ለመሆኑ ጌታዬ ዋና መዋኘት ይችላሉ?" ይለዋል። "ስለ ዋና ብዙ አንብቤያለሁ፣ መዋኘት ግን አልችልም" ሲለው "መቶ በመቶ እድሜዎን በከንቱ አጥፍተዋል ማለት ነው" ብሎ ተለያዩ ይባላል። እብሪተኝነት፣ ማናለብኝነት፣ ከኔ ወዲያ ላሳር ማለት አደገኛ መርዝ ነው ለምሁር። ብዙዎችን የሚያስቸግራቸው ይሄ ነው። ሲጀመር ሰው አያውቅም አይባልም፤ ሰው ወሰን የለሽ አቅም አለው። እዚህ ቢመጣም ባይመጣም እንደው "ሰው አያውቅም፣ እኔ ነኝ የማውቀው" የሚል ማናህሎኝነት አደገኛ መርዝ ነውና እሱን መትፋት ይኖርበታል።

እስካሁን ያወራሁት አጠቃላይ ምሁርን፣ አጠቃላይ ባሕርይን ከእኛ ጋር እያየን ወደ እኛ ስናመጣው በአምስት ከፍለን ልናይ እንችላለን። የኢትዮጵያን ምሁራን፣ የኢትዮጵያ ቅድመ-ዘመናዊ፤ የኢትዮጵያን ምሁራን ወይም ጥንታውያን አሳቢያን የምንላቸውን በአንድ ምድብ ብናስቀምጥ ዘመን በጣም ሰፊ ነው። እነዚህ የዕውቀት ገበያቸው የአብነት

ትምህርት ቤት፣ መድረሳዎች በጥልቅ ማሰብ፣ ማሰላሰል ሊሆን ይችላል። የዕውቀት ዘርፎቻቸው ብዙ ጊዜ ሕግ ወይም ፍትሐ-ነገሥት፣ ሥነ-መለኮት ፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ የባህል ሕክምና ፣ ቅኔ፣ ፍልስፍና ሊሆን ይችላል፤ ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያን የቀን አቆጣጠር እንዴት ሰራነው፣ የኢትዮጵያን ፊደላት ማን ሰራው ካልን ደግሞ ብዙ አጠያያቂ ጉዳይ ያነሳል። እነዚያ ቅድመ-ዘመናዊ ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹን አናውቃቸውም ፤ ስማቸው አልተነገረም፣ ወይም ስማቸው በዘዴ ጠፍቷል። ቢያንስ ቢያንስ ግን ዘርዓ ያዕቆብን እናውቃለን። ዘርዓ ያዕቆብ ሁላችሁም እንደምታውቁት እዚህ አልመጣም፣ ሐርቫርድ አልሄደም፤ አሁን ባለው መመዘኛ ቢሆን ኖሮ መሃይም ነበረ። ግን ዘርዓ ያዕቆብ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በእሳቤዎቹ፣ በፍልስፍናው እኛ የምንጠራው ልክ እንደ ዘርዓ ያዕቆብ በጣም በርካታ የሚጠሩ ሰዎች ደግሞ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ያልተጻፈላቸው፤ ያልተነገረላቸው። እነዚህ አንድ ምድብ ናቸው።

ሁለተኛው የዘመናዊት ኢትዮጵያ ምሁራን በመደመር ትውልድ ላይ “የወግ አጥባቂው ትውልድ” ነው እኔ ያልኩት፤ ወይም “የኢትዮጵያ የለውጥ ፈር ቀዳጆች” ፕሮፌሰር ባህሩ ያሏቸው ሌሎቹ ናቸው ፤ ሁለተኛው ምድብ ናቸው። እነዚህ ባሕር ማዶ ትምህርት የቀመሱ፣ በአውሮፓ ሚሲዮኖች የተማሩ፣ አንዳንድ ስመ-ጥር ምሁራን ስማቸው የሚጠሩ ሰዎች ያሉበት፤ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ከነዚህ መካከል ሊጠቀስ ይችላል፣ ሐኪም ወርቅነህ ሊጠቀስ ይችላል፣ ፊት አውራሪ ተክለሐዋርያት ሊጠቀስ ይችላል፣ መላኩ በያን ሊጠቀስ ይችላል፤ አሉ እንደዚህ ዓይነት ምሁራን።

በሦስተኛ ምድብ አብዮታውያን ምሁራን የምንላቸው፣ ከዚህ ትምህርት ቤት ታሪክ ጋር ታሪካቸው የተሳሰሉትን ነው፤ በመደመር ትውልድ እኔ “ህልመኛው ትውልድ” አልኳቸው፤ በቅርብ መጽሐፋቸው ፕሮፌሰር ባህሩ ደግሞ “የሶሻሊስት ኢትዮጵያ ፍለጋ” በሚል የዳሰሷቸው ምድቦች ወይም ትውልዶች ናቸው። እነዚህ ፎቶአቸውን ከዚህ በኋላ የምናያቸው ሰዎችን ይመለከታል። ግርማሜ ነዋይ በእነዚህ ምድብ ሊታይ ይችላል፤ ሃይሌ ፊዳታ እዚህ ሊካተት ይችላል፤ ብርሃነመስቀል ረዳ እዚህ ሊታይ ይችላል፤ ተስፋዬ ደበሳይ እዚህ ሊካተት ይችላል፤ ሌሎችም ብዙ ብዙ አሉ።

አራተኛው ስደተኞች ምሁራን ናቸው። በዚህ ቤት ያለፉ፣ በሌሎች ኮሌጆች ያለፉ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ዲግሪያቸውን በውጭ ሀገር የተማሩና እዚያው የቀሩ ማለት ነው። ፕሮፌሰር ገቢሳ እጀታ ሊወሰድ ይችላል፤ ፕሮፌሰር ኃይሌ ገሪማ ሊወሰድ ይችላል, ፕሮፌሰር ጌታቸው ሊወሰዱ ይችላሉ፤ ዶክተር ተስፋዬ ቢፍቱ ሊወሰድ ይችላል። ዶክተር ተስፋዬ ቢፍቱ ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ምሁራን ውይይት ውስጥ ስሙ አይነሳም፤ ግን በአሜሪካ ካሉ

በጣም ጥቂት፣ በጣም ጥቂት ተግባራዊ ዕውቀት ለዓለም ካበረከቱ ሰዎች፣ በእኛ መመዘኛ አይደለም በአሜሪካም ከሙቶ በላይ የፈጠራ ባለቤትነት መብት አለው። በመድኃኒት ጥናት ላይ ነው ጥናት ያካሄደው፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ኤች አይ ቪ የሚያስከትለውን የቫይረስ ስርጭት የሚከላከልለውን መድኃኒት በመፍጠር ግንባር ቀደም ነው። በጣም በርካታ መድኃኒቶች ፈጥሯል። በኒው ዮርክ የሚኖር ስመ-ጥር ምሁር ነው። እንደነዚህ ያሉ ምሁራን በዚህ ያለፉ ቢሆኑም እዚያው ተሰደው የቀሩበትን “ለምን?” የሚለውን ጉዳይ እኔ እጠይቃለሁ፤ እነሱና ዘመን ይመልሱታል እንጂ እኔ አልመልሰውም።

አምስተኞቹ ተስፈኞቹ ናቸው። ልክ እንደ አራተኛዎቹ ምሁራን ውጭ ሀገር ሄዶ የመማር፣ የውጩን ዓለም የማየት ዕድል ገጥሟቸዋል። ወደ ሀገር ሲመለሱ በጥያቄ የተሞሉ ሁሉ ስለሆኑ እስር፣ እንግልት ገጥሟቸዋል፤ ያም ቢሆን ግን በውስጥ ያለውን ፈተና ተቋቁመው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ፈተናም ዕድልም የተቋደሱ ሰዎች ናቸው። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም እዚህ ውስጥ ሊጠቀሱ ይችላሉ፤ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ሊጠቀሱ ይችላሉ፤ ዶክተር ዳኛቸው እዚህ ውስጥ ጎልቶ ሊጠቀስ ይችላል፤ ተስፈኞች ናቸው። ባሉበት ዓለም ማስተማር ሲችሉ፣ ባሉበት ዓለም መኖር ሲችሉ፣ ባሉበት ዓለም በዩቲዩብ መሳደብ ሲችሉ ፤ “የለም! እስርም ቢኖር ችግርም ቢኖር እጋፈጣለሁ” ያሉ ማለት ነው። አሁን መጠየቅ እንጂ መምረጥ አትችሉም፤ አራተኛው ይሻላል ወይስ አምስተኛው ይሻላል? ምርጫ መጠየቅ ብቻ ነው፤ “ለምን?” የሚለውን ግን ጥያቄ እናነሳለን።

ምሁራኖቻችን በዚህ ምድብ ቢከፈሉ፣ ሦስቱ ላይ፣ ሦስተኛው ፣ አራተኛው፣ አምስተኛው ላይ ባለፉት 75 ዓመታት ይህ ትምህርት ቤት የራሱን ዐሻራ አኖሮባቸዋል። ይህ ትምህርት ቤት እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በመፍጠር፣ በሸሹትም፣ ተስፋ ባደረጉትም በመፍጠር፣ በቀናውም በጎደለውም የሚጠየቅ ይሆናል ማለት ነው። ብዙ ጊዜ የተማሪዎች ንቅናቄ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ “ያን ፈጠረ፣ ይህን ፈጠረ” ሲባል የምናነሳው ብቻ ሳይሆን፣ “ለምን አልተሳካም?” ብለን የምንጠይቀውም ተቋም ይሆናል።

እንደምታዩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነገር ብዬዋለሁ፤ “ነገር” ብለው ስለሚሻል። እዚህ ቤት የዘመናት ጥያቄዎች ተነስተዋል፤ በርካታ ጥያቄ የተሞከረ፣ ያልተመለሰ፤ የተሞከሩ አሉ፣ ያልተመለሱ አሉ። ይሄ ቤት በኢትዮጵያ የአስተሳሰብ መነቃቃት ውስጥ በጣም ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ነው። በመጻፉም ፣ በማንበቡም፣ በመናገሩም፣ በመጠየቁም፣ በመሞከሩም ይሄ ይባላል፤ ባለመሳካቱም ግን ተጠያቂ ነው። ያንን ኃላፊነት መውሰድ ሲጀምር፣ የሚቀጥለው 25 ዓመት ፍሬያማ ይሆናል። የለውጥ ጥያቄ አስኳል መሆኑ አይካድም፤ የለውጥ ጥያቄ ለመነጋገር አውድ የፈጠረ መሆኑ አይካድም፤ ለመጻፍ የሞከሩ

ሰዎች የተፈጠሩበት መሆኑ አይካድም። ነገር ግን ያ ዘመን እንደምታውቁት ስሜታዊነት፣ ቀኖናዊነት፣ ማንአህሎኝነት የተጠናወተው፤ ዘረ-ሐሳብ የጨነገፈበትን ምክንያትም ፈልቅቆ ማየት ያስፈልጋል። ሐሳብ ነበረ፤ ያንን ሐሳብ ምን ተጭኖት ጨነገፈ የሚለውን በደርዙ ማየት ያስፈልጋል።

እዚህ ትምህርት ቤት ኬኔዲ የሚባል ቤተ-መጻሕፍት አለ፤ ይሄ አብርሆት የሚባል ነገር ከመምጣቱ በፊት ግርማ ሞገሱን ምታውቁት ነው። ኬኔዲ ቤተ-መጻሕፍት ውስጥ እዚህ ትምህርት ቤት ገብቶ ያላለፈ ሰው ያለ አይመስለኝም፤ ግን “ለምን ኬኔዲ ተሰኘ? ኬኔዲ ስለ ሀገር ምን አሉ?” የሚለውን ደግሞ ሁሉ ሰው መጠየቁን እርግጠኛ አይደለሁም። ኬኔዲ “ለሀገሬ ምን አደረግኩላት እንጂ፣ ሀገሬ ምን አደረገችልኝ ብለህ አትጠይቅ” ያሉትን ሁሉን ምሁር መጠየቁን እርግጠኛ አይደለሁም። በኬኔዲ ቤተ-መጻሕፍት ላይ ማለፍ እና መገልገል ብቻውን በቂ አይደለም፤ የዚያ ስያሜ ባለቤት የሆነ ሰው ያለውን እሳቤ መጋራት ያስፈልጋል። ብዙዎቻችን “ምን ተደረገልን?” ባዮች ስለሆንን፣ ማድረግ የሚገባንን ሳናደርግ ዘመን ያልፋል።

ይህ ዩኒቨርሲቲ በአንድ ወቅት እኔ እንደማስበው 1966/67/68 አካባቢ “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዩኒቨርሲቲ” ይባል ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዩኒቨርሲቲ መባል ስያሜ ብቻ አይደለም፤ ግብር ጭምር ነው። ኢትዮጵያውያንን የሚሰበስብ ትርክት፣ ለሁሉ ኢትዮጵያውያን እኩል የሚዳረስ የፖለቲካ እሳቤ የሚፈጠርበት ቤት ነው ማለት ነው፤ አድርጓል አላደረገም የሚጠየቅ ጉዳይ ሆኖ። ሁሉም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሦስት መሠረታዊ ሥራዎች ይጠበቁባቸዋል፤ መማር ማስተማር በዚህ ይህ ዩኒቨርሲቲው እምብዛም አይታማም በመማር ማስተማር፤ መመርመር መመራመር በዚህም ቢሆን ብዙ ሙከራዎች አድርጓል። ሦስተኛው ግን መፍጠር እና መተግበር ላይ ነው ዕዳው። መፍጠር እና መተግበር ላይ እንደ መማር እና ማስተማር፣ እንደ መመርመር እና መመራመር አልቀለለም፤ እሱን ጠይቆ ማለፍ በጣም ጠቃሚ ይሆናል ለሚቀጥለው ሥራችን ።

ዩኒቨርሲቲው ይሄ ከሆነ፣ እንደ ሀገርስ ያለን ተግዳሮት ምንድን ነው? እንደ ምሁር ያለን ተግዳሮት አየነው፤ እንደ ሀገር ያለን ተግዳሮት ምንድን ነው? አንደኛ የሐሳብ ስብራት ነው፤ ሁለተኛ የተቋም ስብራት ነው፤ ሦስተኛ የባህል ስብራት ነው። የሰው፣ ተቋምና ባህል ሲሰበሩ፣ የእነዚያ ድምር ስብራት ደግሞ በሀገር ደረጃ ያለውን ውድቀት ያስከትላል። የሐሳብ መሪ ጉድለት፣ ወይም የሰው ጉድለት፣ የጋራ የሚሠራ ራዕይ መፍጠር አለመቻል ነው። የጋራ የሆነ የሚሠራ ራዕይ፤ በርዕዮተ ዓለም ተጽዕኖ ሥር መጠቅለል ሌላው ችግር ነው፤ አክራሪነት፣ የስሜት ብልህነት ማነስ፣ ማን ማንአህሎኝነት እና ሌሎችም ሰው

ያመነጨውን ሐሳብ ተክሎና ተንከባክቦ ዛፉ ፍሬ እንዲያፈራ እንዳያደርግ እንቅፋት ይሆናል።ሁለተኛው የተቋማት ጉድለት ነው፤ ተቋማዊ ተቀባይነት፣ ሕጋዊነት ፤ የዚህ አንዱ ጎልቶ የሚታየው ችግር የግል ጥቅምና ትስስር አሠራር ነው፤ ነፃና ገለልተኛ ተቋም መገንባት አልተቻለም። የትም ቦታ ሲኬድ የመሳሳብ ችግሩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ጊዜን የሚሻገሩ ተቋማት፣ ተልዕኮን የሚፈጽሙት ተቋማት፣ ከተልዕኮ የተግባቡ ተቋማት መፍጠር ስንክሳርና እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል።

ሦስተኛው የባህል ጉድለት ነው፤ ለለውጥ ዝግ መሆን፤ ማንኛውንም አዲስ ነገር ከመማር ይልቅ አቃቂር ማውጣት። እኛ አቃቂር በማውጣት የምንፈጥራቸውን የቋንቋ ዓይነቶች በመማር ብንፈጥራቸው ኖሮ፣ የሚተካከለን ባልነበረ ነበር። የመጣውን ሁሉ ላለመቀበል የማንፈጥረው ጉዳይ የለም፤ ከጊዜ በኋላም ዛሬም ተቸክለን እዚያው እንገኛለን። መቸከላችን፣ ለውጥን አለመቀበላችን ፣ ለመማር የማንተጋ መሆናችን ካለፈ በኋላ ደግሞ በጣም በከፍተኛ ጸጸት የምንጎዳ መሆናችን ነው።

አሁን ባለንበት ዘመን ዕድል አለ፤ አጣብቂኝ ፈተና አለ። ዕድል አለ፤ አጣብቂኝ ተግዳሮት አለ። እኛ እንደ ሀገር የጋራ እውነት፣ የሚያግባባ እውነት ሳንፈጥር ዓለም ወደ ድኅረ-እውነት ሄደ። የሐሰት ወሬን ስም በወጉ ሳንረዳ፣ ሰው-ሠራሽ የቪዲዮና የድምፅ ማጭበርበሪያ ተፈጠረ። ሰው-ሠራሽ ማጭበርበሪያ ማለት ሐሰት መሆኑን ለመገንዘብ እራሱ የሚያስቸግር ማለት ነው። ዓለም የጋራ እውነት ባልፈጠሩ ሀገራት እየሄደ ያለበት ርቀት በጣም አሳሳቢ ነው። ድኅረ-እውነቱ እያመጣ ያለው ነገር እና እኛ ያለንበት ጉዳይ አይጣጣምም። እንዴት የጋራ እውነት ፈጥረን፣ ለለውጥ ክፍት ሆነን ዓለም እየተጓዘ ያለበትን ፍጥነት ማየት ካልቻልን፣ እንዲሁ የገባን መስሎን ሳይገባን ዘመን ያልፋል።

ሁለተኛው፣ ሰው-ሠራሽ አስተውሎትና አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት (4.0) የሰውን ልጅ ሥራ ይቀማል፤ የሰውን ልጅ ሥራ ይጋራል፤ ሰውን ሥራ ያሳጣል በሚባልበት ዘመን፣ እኛ ሞፈርና ቀንበር አልጣልንም፤ በትራክተር እንኳን ማረስ በቅጡ አልተለማመድንም። ይሄ አደገኛና የሚያስፈራ ነገር ነው፤ ዕድል አለ፣ የሚያስፈራ ጉዳይ ደግሞ አለ። ልዩነትን ከግጭት ውጭ ባሉ አፈታቶች ማየት፣ በሰላም በንግግር ማየት ሙሉ በሙሉ ከእኛ ባህል ውጭ ሆኗል።

ዓለም ግራጫማ የጦርነት ስልት ያካሄዳል። ግራጫማ የጦርነት ስልት ማለት፣ ጦርነቱ እያለ በጋራ እውነት እየሠሩ መቀጠል ማለት ነው። እኛ በንግግር እየተቃረንን ለጋራ እውነት መቆም አልቻልንም፤ ይሄ ሥጋት ያስከትላል። የሥነ-ምሕዳር አጥር፣ የጂኦ ፖለቲካ ውድድር፤ ለምንድን ነው ሀገራት እዚህ እኛ ጫፍ መጥተው እኛ ሰፈር ውስጥ

የሆነ ነገር የሚፈልጉት? እኛ የማያገባን ለምንድን ነው? እንደ ትልቅ ሀገር ራሱ ሌሎች የተመኙትን እኛ የማንመኝበት ምክንያት ምንድን ነው የሚለውን ጉዳይ ለመወያየት ያለን ፈቃደኝነት፤ “እኔ የቀይ ባሕር ጉዳይ አያገባኝም፣ ይህ ጥያቄ የእኛ ጥያቄ አይደለም” የሚል ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ማለት ነው። ይሄ የምናስበውን ነገር ለማሳካት ያለብንን ውስንነት ያመጣል፣ ያመለክታል።

እንዴት እንሻገር? ለመሻገር አንደኛ የተሻገረ ብሔራዊ ራዕይ ያስፈልገናል። ገቢርነበብ የተባበረ የለውጥ አቅምና ኃይል ያስፈልገናል። እኛን ዘግይቶ የመጣ የሚለው አይገልጸንም፤ በጣም ወደ ኋላ የቀረን ነን። በጣም ዘግይቶ የመጣ ማኅበረሰብን ዘግይቶ የመጣ በሚባል ምድብ ካስገባነው እንሸወዳለን ። በጣም በብዙ ጉዳይ የቀረን ስለሆነ፣ የ ወረት እና የጊዜ ውስንነት፣ ያለፈው ዕዳና የነገው ሥጋት አጣብቂኝ ስላለ፣ በከፍተኛ ደረጃ ብሔራዊ ራዕይ ኖሮን ለዚያ መትጋት ይጠበቅብናል። መጪውን ዘመን ያገናዘበ ራዕይ፣ ነባራዊ ሁኔታን በቅጡ የተረዳ ራዕይ፣ አዲስና የሚሰራ እሳቤዎችን ለማስተናገድ አውድ ያስፈልገናል። ይህ ጉዳይ መሠረታዊ ስለሆነ በአንዳንዱ ልየው፡-

ራዕይ፣ የተሻገረ ብሔራዊ ራዕይ ሲባል ከትናንትና መማር፣ ስህተቶችን የሚያርም፣ ጠንካራ ጎኖቻችንን የሚያሰፋ፣ ጥያቄዎችን በተሟላ መንገድ ለመመለስ የሚጥር፤ ይህ ከትናንት ጋር ያሉት ሥር ነው፤ ዛሬስ? ለመሥዋዕትነት ዝግጁ መሆን። እኔና እናንተ የበለጸገች ኢትዮጵያን በተሟላ መንገድ የምንቋደስ ሰዎች አይደለንም፤ ለዚህ የዚያን መሠረት ጥለን ልጆቻችን በበለጸገች ሀገር ውስጥ እንዲኖሩ፣ ከችግር እንዲላቀቁ ለማድረግ መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለብን። መሥዋዕትነት በጣም በብዙ መንገድ ይገለጻል። ለምሳሌ የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክታችን፣ የዛሬ አምስት አሥር ዓመት ምን አትጠራጠሩ በጣም ለብዙ ሀገራት ምሳሌ የሚሆን ሥራ ነው፤ ጥያቄ የለውም። ለልጆቻችን ምንዳ እንዲሆን አስበን ከሠራነው ብቻ ነው ራዕያችን ተሻጋሪ መሆን የሚችለው። ለትውልድ መሥራትን ይሁን ብሎ ያመነ አመራር፣ ያመነ ምሁር፣ ያመነ ማኅበረሰብ ከሆንን መቀየር ይቻላል።

ከዚህ አንጻር እንደ መንግሥት በ2023 የዛሬ አምስት ዓመት ኢትዮጵያ አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት መሆን አለባት የሚል ራዕይ ሰንቀናል፤ መቶ በመቶ እናሳካዋለን፣ መቶ በመቶ ጥያቄ የለውም። በአፍሪካ አንደኛ አላልኩም፤ በአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት እናደርጋታለን፣ ጥያቄ የለውም። ይሄ በ2040 የዛሬ 22 ዓመት በዓለም አርአያ የሆነች ሀገር ትሆናለች፤ ለዚህ ራዕይ ሦስት ትልሞች አሉን፣ ሦስት ትልሞች አሉን።

አንደኛው፣ ሰብዓዊ ልዕልና የማይናቅ ፓስፖርት ያላቸው ልጆች፣ “የስንዴ እርዳታ ሄደላት” የሚባል ዜና የማይሰማባቸው ልጆች፣ አንዳንድ ሀገር ረዱ የሚባሉ ልጆች፤ ሰብዓዊ ልዕልና ያላቸው፣ የተከበሩ፣ ራሳቸውን ያከበሩ ልጆች ይኖሩናል።

ሁለተኛ፣ ኢኮኖሚያዊ ሉዓላዊነት ይረጋገጣል፤ ለምሳሌ በስንዴ ራሳችን መቻል ብቻ ሳይሆን “እርዳታ አያስፈልገንም” ብለን ማወጅ ብቻ ሳይሆን፣ ያለን የደረጃ ምዘና በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ በ2023 ካልኩት በፊት አብዛኛውን የደረጃ ምዘናችንን እናስተካክላለን። ለዚህ አስቻይ ሁኔታዎች በሚጨበጥ ሁኔታ በሀገራችን ውስጥ እየተከወኑ ይገኛሉ።

አፍሪካዊት ኃይል መሆን እንፈልጋለን። በምግብ ራስ መቻል ብቻ አይደለም፤ በአፍሪካ ሀያል ምክር የምትጠየቅ፣ በአፍሪካ ጉዳይ “እነ ኢትዮጵያን ካላማከርን” የሚባል ሀገር መሆን አለባት ኢትዮጵያ፤ ትልሟ እንደሱ ነው። ራሷን መቻል ብቻ አይደለም፤ በቀጣናው ባላት ሚና ውስጥ በስንዴ ምክንያት፣ በድህነት ምክንያት ያላት ጥበብ እና ብቃት ዝቅ ተደርጎ እንዳይታይ ማድረግ ነው። ለዚህ ደግሞ አምስት ምሶሶዎች አሉን፤

አንደኛው ምሰሶ ጥራት ያለው ዕድገት ነው፤ ላለፉት 7 ዓመታት አንድ ዶላር የንግድ ብድር አልወሰድንም ፣ ፣ ፣

የምንሠራቸው ሥራዎች ሦስተኛውም ምሰሶ ነው። በተለይ ዲጂታል 2030 ይህንን ለማሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፤ እኛ ከመጣን ጀምሮ 30፣ 40 ሺ መዋለ-ሕፃናት ገንብተናል፣ በጣም በርካታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና መጀመሪያ ደረጃ ገብተናል፤ ዩኒቨርሲቲ አልገነባንም በምታውቁት ምክንያት ያለው ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን፣ ከስም ወጥቶ ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን በሚል። አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው-ሠራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ ልንገነባ ነው፤ ምናልባት የሚቀጥለው ስድስት ወራት ሥራዎቻችንን እንጨርሳለን።

የሰው-ሠራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ ስንፈጥር ቢበዛ 1,000 ተመራቂ ካለን ይበቃናል፤ ቢያንስ 100 ግን የነፃ ትምህርት ዕድል ነው፤ ለእያንዳንዱ አፍሪካ ሀገር ሁለት ሁለት የነፃ ትምህርት ዕድል እንሰጣለን። ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ተማሪ ቢበዛ 2 በመቶ ነው ተወዳዳሪ ከሆኑት የምንቀበለው ፤ ቢበዛ በጣም ትንሽ ግን ተግባራዊ የሆነ ሰው እንፈጥራለን። ለዚህ ከእናንተም ከዲያስፖራውም የምናሳተፋቸው ሰዎች ይኖራሉ። ቴክኖሎጂ ላይ መሸቀዳደም አለብን፤ የሰው-ሠራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ በዓለም ደረጃ አንድ ሀገር ብቻ ነው ያለው፤ የሰው-ሠራሽ አስተውሎት ክፍለ-ትምህርት የፈጠሩ አሉ፤ የሰው-ሠራሽ አስተውሎት ትምህርት የሚሰጡ አሉ እናንተን ጨምሮ፣ እነሱ አሉ። ሰው-ሠራሽ አስተውሎትን ብቻ የሚሠራ የማሽን ትምህርት ላይ፣ በሮቦት ጥናት ላይ, መረጃ ፍለጋና ትንተና ላይ፣ ስሌት ማከናወን ላይ የሚሠራ ብቻ ተቋም ግን በዓለም ላይ እስካሁን አንድ ነው ያለው፤ እኛ ሁለተኛው እንሆናለን ከፈጠንን። ለምን ያላችሁ እንደሆነ፣ ትውልድ ላይ ለመሥራት መሸቀዳደም ስለምፈልግ።

አራተኛው አረንጓዴ ኢኮኖሚ ነው፤ አምስተኛው ተቋማዊ ማሻሻያ ነው። በእነዚህም ምሰሶዎች በ2023 ምንም ጥርጥር የለውም፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ኤክስ ዋይ ዜድ ኢትዮጵያ፣ ኤክስ ዋይ ዜድ ኢትዮጵያ ይባላል ማለት ነው፤ አንደኛ አንሆንም፤ “ስለ አረንጓዴ ዐሻራማ ኢትዮጵያ፣ ስለ ወንዝ ዳርቻ ልማትማ ኢትዮጵያ፣ ኮሪደርማ ኢትዮጵያ፣ በስንዴ ራስ መቻልማ ኢትዮጵያ፤ ሥርዓትን ራስ-ሰር አድርጎ አገልግሎትን በምናብ መስጠትማ ኢትዮጵያ” እየተባለ የሚጠቀስበት ጊዜ ይመጣል፤ ያ እንዲመጣ የእናንተ የመረጃ ማመንጨት በጣም ወሳኝ ነው፤ የተሠሩ ሥራዎች ብዙ የምርምር ጽሑፍ የማንጽፍ ካልሆነ ሥርዓቱ አያየውም፤ ለዚያ የእናንተ ሚና ይኖራል።
ሁለተኛው፣ ገቢር ነበብ የለውጥ ሒደት ነው። ተግባራዊ የሆነ የለውጥ ሒደት እዚህ ጋር እንደምታዩት እንደ ራዕዩ አይደለም፤ ሁካታና መለዋወጥ የበዛበት ነው። “የአዲስ አበባን ወንዞች እናጽዳ” አያጣላም፤ “እናፍርስ ቤት” ግን ያጣላል። ተግባር ነው የሚያጣላው እንጂ በሐሳብ አያጣላም። መተግበር ውስጥ ስንገባ ተቃርኖ ይፈጠራል፤ ለዚህ ስልታዊ

ወንዞች እናጽዳ" አያጣላም፤ "እናፍርስ ቤት" ግን ያጣላል። ተግባር ነው የሚያጣላው እንጂ በሐሳብ አያጣላም። መተግበር ውስጥ ስንገባ ተቃርኖ ይፈጠራል፤ ለዚህ ስልታዊ መንገዶች፣ ሥርዓታዊ ለውጦችና ብዝኃ-ዘርፍ አሠራር መከተል ያስፈልጋል። የመደመር መንግሥት አማራጭ፤ በውስብስብና ከመደበኛ በተለየ ምኅዳር ውስጥ ዘርፈ-ብዙ እና ተለዋዋጭ ፤ ብዙ ተዋናዮችንና ብዙ ዘርፎችን ያቀፈ ውህደት ካላመጣን በስተቀረ፣ በተናጥል ጉዞ አናሳካውም ብሎ ያምናል። ሦስቱን ገረፍ ገረፍ አድርጌ ልሂድ፤ ስልታዊ መንገድ፣ ሥርዓታዊ ለውጥ እና ብዝኃ-ዘርፍን ። ስልታዊ መንገድ መደመራዊ ፈጠራ፣ መደመራዊ ፍጥነት፣ መደመራዊ ዝላይ፤ ምን ማለት ነው? እናንተ መደርደሪያ ላይ ብዙ ሐሳብ አለ፤ ከኢንዱስትሪ ጋር ካልተደመራችሁ ፈጠራ አይሆንም፣ ቴክኖሎጂ አይሆንም። እናንተ መደርደሪያ ላይ ብዙ ሐሳብ አለ፤ ከአርሶ አደር ማሳ ካልተዋደዳችሁ ቴክኖሎጂ አይሆንም፣ ምርታማነትን አያፋጥንም፣ አያባዛም።

መደመር ሲባል ፖለቲካዊ ብቻ አይደለም፤ በእያንዳንዱ ዘርፍ ያለ ዕውቀት ሐሳብን ማሰናሰል ማለት ነው። አሁን ባለው ልማዳዊና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ቅድም ያስቀመጥነውን ራዕይ ማሳካት አንችልም፤ ምክንያቱም ዕድገት ወጥና ተገማች አይደለም፤ በጣም ብዙ እርግጠኛ ያልሆነ ሁኔታዎች በውስጡ አሉ። ያንን የመላመድ አቅም ካልፈጠርን በስተቀረ፣ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን ካላሳደግን በስተቀረ፣ የሁሉን ተዋናይ ሚና መጠቀም ካልቻልን በስተቀረ ሊሳካ አይችልም። ሐሳብና ጊዜ ትልቁ የለውጥ አቅም በሆኑበት በዚህ ዘመን፣ ሐሳብና ጊዜ ትልቅ ድርሻ በሚወስዱበት በዚህ ዘመን ያ የተሰናሰለ ሒደት በጣም ወሳኝ ነው። ሥርዓታዊ ለውጥ፤ ሚዛናዊ ትብብር በአራት ተዋንያን ነው፤ በመንግሥት፣ በገበያ፣ በትምህርትና በማኅበረሰብ ያስፈልጋል። ንቁ መንግሥት—የግል ዘርፉን ጉድለት የሚሞላ፣ ሐሳብ የሚገዛ፣ ጠንካራ የበላይ ክትትልና አመራር የማድረግ አቅም ያለው መንግሥት ያስፈልጋል።

ስኬትንና ተግዳሮትን የሚካፈል የግል ዘርፉ ያስፈልጋል፤ ድል ብቻ አይደለም፣ ተግዳሮትን የሚካፈል፤ የሚያስተሳስር፣ ተሰጥኦን እንደ መሠረተ-ልማት ወስዶ የሚገነባ መንገድ ስፈልጋል። ተሰጥኦ መንገድ ነው፣ ተሰጥኦ መሠረተ-ልማት ነው፤ ተሰጥኦ የሌለው ማንኛውም ማኅበረሰብ ያለውን መጠቀም አይችልም፣ እንኳን አዲስ ሊፈጥር፤ ያንን የሚሠራ ሥርዓትና ትምህርት ያስፈልጋል። ማኅበረሰቡ ደግሞ ባለቤት የሆነ ሕብረተሰብ፤ በሒደትም በውጤትም ያሉ ፈተናዎችና ድሎች የሚቋደስ መሆን አለበት። ብዝኃ-ተዋናይ ስንል፤ ሥራ ፈጣሪ የግል ዘርፍ ያስፈልጋል ዕሴት የሚፈጥር፣ ሥራ ፈጣሪ መንግሥት ያስፈልጋል አስቻይ ሥርዓት የሚፈጥር፣ ሥራ ፈጣሪ ምሁር ያስፈልጋል ሐሳብ የሚፈጥር፣ ሥራ ፈጣሪ ባህል ያስፈልጋል የሚነሳሳ፣ መላመድ የሚችል፣ ለመማር

ዝግጁ የሆነ። ለምን ቢሉ አሁን እኛ ያለን መዋቅራዊ የአቅርቦት ችግር፤ የበላይ መዋቅሩም መሠረተ-ልማቱም፣ የበታች መዋቅሩም መሠረተ-ልማቱም የሚፈታው እነዚህ ተዋንያን ተሰናስለው ሥራቸውን ከሠሩ ብቻ ነው። በአንድ ወገን ጥረትና ሥራ የተሟላ ውጤት ልናመጣ አንችልም። የተሻገረና የተሳሰረ ምሁራዊ ሚና እንዴት እንወጣ? አንደኛ፣ ንቁ ተሳትፎ፤ በእያንዳንዱ የሐሳብ ገበያ ውስጥ የራስን ድርሻ ለማበርከት በንቃት መሳተፍ፣ ከራስ የተሻገረ ዓላማ መያዝ፣ ሐሳብ ትልቁ ምርት እንደሆነ ማመን፣ የሰው ዋነኛው የዕድገት አቅም ዘር የሚነሳው ከሐሳብ እንደሆነ ማሰብ፣ ምሁራን ድልድይ መሆን። በመነሻ ሐሳብ እና በተቃራኒ ሐሳብ እምብዛም ችግር የለም፤ ሐሳብ ሲመጣ በተቃረነ ሌላ ጽንፍ መቆም ችግር የለም፤ የሐሳቦች ውህደት ላይ መሥራት፣ ከሁለቱም ወገኖች ጠቃሚ ነገር ካለ ወስዶ መካከለኛ የሆነ አሻጋሪ ሐሳብን መንደፍ የምሁራን ሚና ይሆናል።

ብሔራዊ እይታ፤ ከሐሳብ ፣ ከሐሳባዊ ፋይዳ ባሻገር፤ ዕውቀት ከዕውቀታዊ ፋይዳ ባሻገር ብሔራዊ ፋይዳውን ማየት። “አውቄያለሁ፣ ተመርቄያለሁ” ሳይሆን ለሀገር ፣ ለማኅበረሰብ ያለውን ተፅዕኖ ማየት፤ ምሁርነት ከሙያዊ ስኬት፣ ከሙያዊ የሥራ ዕድገት ባሻገር ለሀገር ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ማየት፤ ከክፍል ከጊዜ ሰሌዳ ባሻገር፣ ከጠባብ ክፍል ባሻገር ሀገርና ትውልድን እያሰቡ መሥራት ፤ ጊዜ የማይገድበው፣ ሙያዊ ልዩነት የማያጥረው፣ ፖለቲካዊ ልዩነት የማያስቀሩት ምሁር መሆን ይኖርበታል። ሥራ ፈጣሪ እይታ ሲባል መፍጠር፣ መተግበር፣ መለወጥ ነው። አዲስ ነገር የምንፈጥረው ፣ መጠቀም ብቻ ሳይሆን ሐሳብን ማመንጨት ያስፈልጋል። ማመንጨት ስንችል አጠቃቀማችን ይሳለጣል፣ ክፍተት ካለውም ይሞላል። ሁለተኛው፣ ተግባራዊ ማድረግ ነው፤ ዕውቀት ከመደርደሪያ የሚሻገር፣ ሀብትን የሚጠብቅ ሳይሆን ሀብት የሚፈጥር መሆን አለበት።

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ከዩኒቨርሲቲ ወጥቶ የአርሶ አደር ማሳ ውስጥ ቡና ላይ ካልሠራ ፣ የአዳማ ዩኒቨርሲቲ ከማሳ ወጥቶ ስንዴ ላይ ካልሠራ፣ ቁጭ ብሎ ከጠበቀ የምናስበውን ነገር ተግባራዊ ማድረግ አንችልም። ሦስተኛው ተፅዕኖ ነው፤ ውጤትና መፍትሔ ተኮር መሆን። ችግር መተንተን፣ ጉድለት ለማሳየት መሞከር እሱ ችግር የለውም፣ ሁሉም ሰው ይችለዋል፤ ያንን ችግር ተሻግሮ መፍትሔ ማምጣት ላይ ግን ቀዳሚ ሚና መጫወት ይኖርበታል። ቀዳሚ እና ማዕከላዊ እይታ፤ ቀዳሚ እና እውነት ገላጭ። በዚህ ድኅረ-እውነት ዘመን እውነት የሚገልጥ፤ አራቂ ዕሴት ገንቢ፣ ዕውቀት መር ውይይቶችን የሚመርጥ፣ የሚወድ፣ የሚያደርግ፣ ምሁራዊ ምክረ-ሐሳቦች የሚሰጥ፤ የሴራ ትንታኔ መበራከት እውነት አንሶ እንዲታይ ስለሚያደርግ የዳታ፣ የመረጃ እና የዕውቀት ቅደም-ተከተል ሳይበላሽ እውነት እንዲነላ ማድረግ አለበት። እውነትን መርምረው መግለጥ፣ ነገርን ከሥረ-መሠረቱ ማየት የሚችሉ ምሁራን ሲበራከቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር ተፈቶ የምናስበውን ነገር እናሳካለን።

ማጠቃለያ፤ ከነባሩ የሐሳብ አጥር እንውጣ፣ አዳዲስ ሐሳብ ለመፍጠር እንሂድ፤ ከልማድ እስር እንውጣ፣ ሽብቦ የያዘን የልማድ እስረኝነት ወደፊት እንዳንሻገር ስለሚያደርገን፤ ከጎራ፣ ከሰፈር እንውጣ፤ ሐሳብ ድንበር የለውም። ከጎራ፣ ከሰፈር ወጥተን የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር በጋራ እንሥራ ። ለምን ያላችሁ እንደሆነ፣ ኢትዮጵያ ረጅም ዘመን ያላት ሀገር ናት። የዛሬ አራት አምስት ዓመት “ኢትዮጵያ አትፈርስም” ብዬ በምናገርበት ሰዓት ብዙ እምነት አልነበረም። አሁን ብዙ ጥርጣሬ ያለ አይመስለኝም።

ኢትዮጵያ አትፈርስም፣ ኢትዮጵያን ማፍረስ የሚችል ኃይልም የለም፤ የሚፈልግ ሞልቷል፣ ማድረግ የሚችል ግን የለም። ከዚያ አልፋለች፤ ለምን ቢሉ ሥረ-መሠረቷ ሰፊ ሀገር ስለሆነች፣ ሀገር በቀል እሳቤዎች ቅድም እንዳነሳሁት በአፍሪካ ውስጥ ብቸኛው በጽሑፍ ቋንቋ ለመግባባት የሚያስችል ፊደልና የቀን አቆጣጠር ያላት ሀገር፤ በራሷ አውድ ለመመላለስ የሚያስችል በጣም ብዙ ፈጠራዎች ያላት ሀገር ናት፣ የዳበረ ባህል ያላት ናት። ተናበን፣ ተሰናስለን፣ ተማምረን፣ በጋራ ቆመን መናናቅን፣ እብሪትን፣ ማን ማንአህሎኝነትን አስቀርተን ብንሠራ ልናመጣ የምንችለው ውጤት ትልቅ ነው። ለዚህ ዋናው ነገር መልካምነትና በጎ ሕሊና ነው። መልካምነትና በጎ ሕሊና ከሌለ እኩይ ፍላጎትና አሳቢዎች ይኖራሉ፤ ግን አይከናወኑም፣ አይከናወኑም።

በአንድ ወቅት አንድ ሼክ ግመል ሊገዙ ገበያ ይወጣሉ። ገበያ ሲወጡ እኚህ ሼክ ረዳት ነበራቸው። ገበያ ወጥተው ካሉ ግመሎች አንደኛውን መርጠው፣ ዋጋ ተደራድረው፣ ከፍለው ይገዛሉ። ገዝተው ወደ ቤት የመልስ ጉዞ እንደጀመሩ፤ ግመሉም እንዲያርፍ እነሱም እንዲያርፉ አንድ ቦታ አረፍ ብለው ሲቀመጡ፣ አጋጣሚ ግመሉ ኮርቻ ነበረው። ግመል ትልቅ ነው፤ ላዩ ላይ ያለው ኮርቻ እምብዛም አይታይም።

ኮርቻውን ረዳቱ ሲያነሳው ከሥሩ ትንሽ የተቋጠረ ነገር ያገኛል። ያ የተቋጠረ ነገር በውስጡ ብዙ ዕንቁዎች ይዟል። ሰውየው ዕንቁ መሆናቸውን ሲያይ ረዳቱ በእጅጉ ይደሰታል፣ ይፈነጥዛል፤ ለሼኩም “አለፈልን! ግመሉን ከገዛንበት በብዙ እጥፍ የላቀ ሀብት አግኝተናል” ይላቸዋል። ሼኩ “የለም! ይህንን ስላልገዛነው እንመልሳለን” ይላሉ። “ሰዎቹ እኮ እዚህ እንደነበረም አያውቁም፣ እንደሸጡልንም አያውቁም፤ መመለስ አያስፈልግም” ይላል ረዳቱ። “አይ! እነሱ ባያውቁም እኛ እናውቃለን፤ ስለምናውቅ ማስቀረት አንችልም” ብለው ወደ መጡበት፣ ወደ ገበዩበት ገበያ ይመለሳሉ።

ተመልሰው ሰውየውን አፈላልገው፤ “ይቅርታ፣ በስህተት እነዚህን ዕንቁዎች ከግመሉ ጋር ሰጥተኸናል። ይህ ዕንቁ የአንተ ነውና ውሰደው” ይላሉ። ሰውየው ይደነቃል፤ ከፍቶ ይቆጥራል። ያስቀመጠው 24 ዕንቁ ነበር፤ ሃያ አራቱም ዕንቁዎች አሉ። “በጣም ደስ

ብሎኛል ታማኝ ስለሆኑ፤ እና ሁለት ዕንቁ ልስጥዎት” ይላቸዋል። ሼኩ “የለም፣ ሁለት ዕንቁማ ወስጃለሁ” አሉት። ደግሞ ቆጠረና “አልወሰዱም፤ 24 ነበረኝ አሁንም 24 ነው ያለው” አላቸው ። “እናቴ ‘መልካምነትና በጎ ሕሊና የሚባሉ ሁለት ዕንቁዎች አስተምራኛለች፤ እነሱ ይበቁኛል” አሉ ይባላል።

በመልካምነትና በበጎ ሕሊና ተባብረን ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና እናሸጋግራት!

አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ


Ethiopian
የኢትዮጵያ
THE NEW SPIRIT OF AFRICA
STAR ALLIANCE
BISHOFTU INTERNATIONAL AIRPORT
GROUNDBREAKING CEREMONY
January
26
Ethiopian
የኢትዮጵያ

የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፍያ ግንባታ ማስጀመርያ

—ጥር 2፣ 2018ዓ.ም

የተከበራችሁ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣
የተከበራችሁ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ አመራሮች፣
ሠራተኞች ፣ እጅግ የተከበራችሁና የተወደዳችሁ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣
የተከበራችሁ የአፍሪካ ዜጎች በሙሉ፣ የተከበራችሁ የጥቁር ዘር በሙሉ፣ የተከበራችሁ የአፍሪካ እና የኢትዮጵያ ወዳጅ ደጋፊ ሀገራት እና ግለሰቦች በሙሉ፤
ለዚህ ታላቅ ብስራት፣ ለዚህ ታላቅ ዜና በጋራ እዚህ መገናኘት በመቻላችን እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እወዳለሁ።

ዛሬ ታላቅ ቀን ነው። የኢትዮጵያ የዝመና ጉዞ፣ የኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ፣ የኢትዮጵያ የመለወጥ እና ራሷን ችላ በሁለት እግሯ የመቆም መሻት፤ ላለፉት 100 ዓመታት በርካታ ጥያቄዎች ሲነሱ ገሚሱ ሲከሽፍ ገሚሱ የሰመረበትን ምዕተ-ዓመት አሳልፈናል። በኢትዮጵያ ከተነሱ አንኳር አንኳር ጥያቄዎችና በኩራት ሰመሩ ከሚባሉ ሥራዎቻችን አንደኛው እና ቀዳሚው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ነው። ባለፉት 80 ዓመታት ይህ አየር መንገድ በሚያስደንቅ ሁኔታ የጥንታዊት ሀገር ምልክት፣ የጥንታዊት ሀገር ኩራት፣ የጥንታዊት ሀገር መሻት ማሳያ ሆኖ ቆይቷል።

አየር መንገዱ ላለፉት 80 ዓመታት አልጋ ባልጋ የነበረ ጉዞ አላሳለፈም። የመንግሥታት መውደቅና መነሳትን ተሸክሞ ዕድገቱን ሳያቋርጥ ማለፍ ችሏል። የኮሮና ወረርሽኝ እና ሌሎች ተፈጥሮ ያመጣቸውን እንደ ድርቅ ያሉ ከፍተኛ ፈተናዎች ተሻግሮ ማለፍ ችሏል። በኢትዮጵያ ላለፉት 100 ዓመታት በውስጥና በውጭ የተደረጉ ከፍተኛ ጦርነቶች ዕድገቱን ሳያግቱት ቆይተዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የኢትዮጵያ ኩራት የሚባለው ምንም ዓይነት ተግዳሮትና ፈተና ሳይገጥመው ሳይሆን፣ በተፈጥሮ እና ሰው-ሠራሽ የገጠሙትን ፈተናዎች በከፍተኛ ብቃት አልፎ የአፍሪካ ኩራት፣ የአፍሪካ መመኪያ፣ የእኛም የብልጽግና መሻት ማሳያ መሆን መሆን ችሏል።

ይህ አየር መንገድ በብዙ ነገር ፈር ቀዳጅ ነው። በአፈጣጠሩም በእድገቱም ፈር ቀዳጅ የሚሰኘውን ክብር ለመጎናጸፍ የሚያበቁ ሂደቶችን አልፏል። የዛሬ 80 ዓመት አሁን የአፍሪካ ጎብረት አባላት የሆኑ ሀገራት ብዙዎቹ ነፃ አልወጡም። የአፍሪካ ሀገራት ነፃ ሳይወጡ፣ ራሱን በአፍሪካ ግንባር ቀደም ኩባንያ አድርጎ ማቆም የቻለ ተቋም ነው። አሁን ባለው ዕድገትም ስንመለከት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአፍሪካ ቀዳሚው አየር መንገድ

ብቻ አይደለም፤ በአፍሪካ ሁለተኛ ሆኖ የሚከተለው አየር መንገድ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በግማሽ ያነሰ ነው። በአንደኛው እና በሁለተኛው የአፍሪካ አየር መንገድ መካከል የእጥፍ ያህል ልዩነቶች አሉ። ይህ በአውሮፕላን ቁጥር፣ በዓመት በሚያጓጉዟቸው ሰዎች፣ በሚያስገባው ገቢና በመሳሰሉት የሚገለጽ ቢሆንም፤ ዛሬ ባስጀመርነው ታላቁ ኤርፖርት ግን በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ጥቂት ሀገራት ያሳኩትን፣ እጅግ ዘመናዊ ፲0 ሚሊዮን ሕዝብ በዓመት ሊያጓጉዝ የሚችል ታላቅ የአየር ኤርፖርት ለመሥራት በቅቷል።

ይሄ የአየር መንገድ የስኬቱ ምስጢር ምንድን ነው? ኢትዮጵያውያንና ሌሎች ኩባንያዎች ከዚህ አየር መንገድ ስኬት ምን ልንማር እንችላለን የሚለውን ጉዳይ በወፍ በረር ማንሳቱ፤ መሰል ተቋማት መገንባት ለሚፈልጉና እንደ ሀገር ልናሳካው ለምናስበው ብልጽግና በእጅጉ ወሳኝ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የስኬቱ ምስጢር የተቋማዊ አሠራርና እሴት ባህል መገንባት መቻሉ ነው። የተቋማዊ አሠራርና እሴት ባህል መገንባት ማለት በተቋሙ እና በሕዝብ፣ በተቋሙ እና በመንግሥት፣ በተቋሙ እና በሚገለገሉት ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት የሚገመት፣ የሁሉም ጥቅም ያረጋገጠ፣ ለሁሉም በኩል የሚያገለግል፣ አስተዳደሩ ከማንኛውም ጣልቃ-ገብነት በንግድ ሕግ ብቻ ራሱን ሲያስተዳድር እና ሲመራ የቆየ መሆኑ አንኳር ጉዳይ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አራት ዋና ዋና ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል። አንደኛው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለደህንነት ቅድሚያ የሚሰጥ አየር መንገድ መሆኑ ነው። በዓለም ላይ ላለፉት 80 ዓመታት የዘለቁ ግዙፍ የአየር መንገዶችን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ብናወዳድር፣ ከብዙዎቹ እጅግ ያነሰ፣ በጣም ውስን ጥቃቅን አደጋዎች ከማጋጠም ውጭ ሰላማዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሚባል የአየር መንገድ ነው ሊባል የሚያስችሉ ውጤቶች ባለፉት አሥርት ዓመታት ማሳየት ችሏል።

ሁለተኛው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አመራሮች በፈጠራ እና በትጋት የሚሠሩ ፣ በስምንት ሰዓት የቀን ሥራ የማያምኑ፣ ራሳቸውን እያደጉ ከዓለም የአመራር ብቃት ጋር ራሳቸውን የሚያስተካክሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ባለፉት ዓመታት፣ ባለፉት አሥርት ዓመታት ይህንን ተቋም መምራት በመቻላቸው ጭምር ነው።

ሦስተኛው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የኢትዮጵያን ባንዲራ ተሸክሞ ኢትዮጵያን የሚያሳይ መሆኑን የሚያምኑ፣ የተደመሩ፣ የሚተጉ፣ ራሳቸውን እንደ ወታደር የሚያስቡ እጅግ የሚያኮሩ ሠራተኞች ያሉት ተቋም በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ከሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ወታደሮች ተለይተው አይታዩም። በየቀኑ የተሸከሙትን ሰንደቅ ዓላማ፣ የተሸከሙትን ባንዲራ አክብረው፣ ኢትዮጵያን አክብረው ለሁላችን ኩራት

ሰንደቅ ዓላማ፣ የተሸከሙትን ባንዲራ አክብረው፣ ኢትዮጵያን አክብረው ለሁላችን ኩራት ለመሆን በከፍተኛ ትጋት፣ እኛ አውሮፕላን ላይ ስንተኛ ሳይተኙ ማለት ነው፤ በከፍተኛ ትጋት ያገለገሉ የሀገር ኩራት ሠራተኞች ያሉት በመሆኑ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቋሚና ጊዜያዊ የቀጠራቸው ሠራተኞች 26,000 ገደማ ይጠጋሉ። 26,000 ልዩ ኮማንዶ ያለው ኩባንያ ነው ማለት ነው።

አራተኛው ይህ ኩባንያ ሁሌ ተማሪ መሆኑ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት አዲስ አውሮፕላን፣ አዲስ ቴክኖሎጂ፣ አዲስ ዕውቀት ዓለም ላይ ተፈጠረ ሲባል ያንን ዕውቀት ለመገብየት፣ ያንን ዕውቀት እና ያንን አውሮፕላን ከአፍሪካ ለማስተዋወቅ ከማንም ቀድሞ የሚገኝ ነው። ከዚያ በተጨማሪ በጥገና፣ በትምህርት ዘርፍ ያስገኘው እመርታ አስደናቂ ቢሆንም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መለዋወጫ ዕቃዎችን የማምረት ሥራዎች ጀምሯል። በእነዚህ ባሕርያቱ ይህ የተቋማዊ አሠራርና እሴት ባህል የገነባው የአየር መንገድ የተሳካ 80 ዓመት ተጉዟል።

የሚቀጥለው 80 ዓመት ከባለፈው 80 ዓመት በብዙ መልኩ ይለያል። በሰው-ሠራሽ አስተውሎት የማንዘጋጅ ከሆነ፣ አብዛኛውን የአውሮፕላን ተግባራት የሚፈጽመው ማሽን በሚሆንበት ሰዓት ይህንን ክብራችንን ይዘን መቀጠል አንችልም። ለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት በሁለት አንጓ የተከፈለ፣ ነገን መዋጀት የሚያስችሉ ሥራዎች ጀምሯል።

አንደኛው፣ የሕፃናት መሠረታዊ የቅድመ-ትምህርት ሥርዓት የሚባለው ሕፃናት ላይ አበክሮ መሥራት ነው። ባለፉት አምስት ስድስት ዓመታት ከ35 ሺ በላይ መዋዕለ-ሕፃናት በሀገር ደረጃ ገንብተናል። ባለፉት አምስት ስድስት ዓመታት ታዳጊዎችና ሕፃናት በአካል የበረቱ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር የሚውሉ እንዲሆኑ በርካታ አረንጓዴ ቦታዎች ገንብተናል። በመናገሻችን አዲስ አበባ ብቻ ከ1,600 በላይ ትናንሽ ስታዲየሞች ልጆች የሚውሉበት ገንብተናል። ይህ ከጅምሩ ችግኙ ለመብቀል፣ ለማደግ የሚያስችል ዝግጅት እንዲኖረው የሚያስችል ሥራ ሲሆን፤ በቅርቡ እንደገለጽኩት፣ ቢበዛ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዓለም ሁለተኛ የሆነውን የሰው-ሠራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ በአዲስ አበባ እናስጀመራለን። ታች ላይ የምንሠራው እና በሰው-ሠራሽ አስተውሎት የምንሠራው ሥራ ሲደመር፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚቀጥለውን 80 ዓመት የሚገጥሙትን አዳዲስ ዕውቀትና ፈተናዎች ተጋፍጦ ለማለፍ፣ ለመሻገር የሚያስችለውን ብቃት እንዲጎናጸፍ ያደርገዋል። ይህንን ሙሉ ዝግጅት ማድረግ ካልቻልን ግን ቀጣዩ 80 ዓመት እንደ ትናንቱ ቀለል ያለ ላይሆን ይችላል።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣ ክቡራትና ክቡራን፤ ዛሬ በሰማይ ላይ ለሚበሩ መርከቦች መቶ ሠላሳ ሚሊዮን ሕዝብ የሚመጥን ወደብ በዚህ ስፍራ ሥራ አስጀምረናል። በዚህ ስፍራ በሰማይ ለሚበሩ መርከቦች ያስጀመርነው ወደብ፣ ከዚህ ቀደም ከነበረን በአጠቃላይ ብቃቱ ይለያል። የአዲስ አበባ ኤርፖርት 700 ሄክታር አካባቢ የመሬት ስፋት አለው፤ እዚህ ቦታ 3,900 ሄክታር ገደማ የአየር መንገዱ ብቻ፣ ለተነሱ ሰዎች የጠቀምናቸውን ቦታ ሲጨምር 5,000 ሄክታር አጠቃላይ የአየር መንገዱን ከባቢ የሚሸፍን ስፋት ያለው ቦታ ነው። ለምን ሰፋ ያለ እንደሆነ፣ በስፋቱ ልክ በአየር ላይ የሚመላለሱ መርከቦችን በብቃት ማስተናገድ ችሎ፣ የኢትዮጵያ የዕድገት ሰብራት የሆነውን ሎጀስቲክስ ለመፍታት በእጅጉ ስለሚያግዝ ነው።

በዚህ ቦታ እና በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት 38 ኪሎ ሜትር ርቀት አለ። በዚህ ርቀት ውስጥ የምንገነባው የፍጥነት መንገድ፣ ከአዲስ አበባ አዳማ ከገነባነው የፍጥነት መንገድ ጋር በብዙ ነገር የሚለይ ይሆናል። አንደኛ፣ ከአዲስ አበባ አዳማ የሚሄደው የፍጥነት መንገድ በእያንዳንዱ መስመር ሦስት መኪና የሚያስተናግድ፣ በድምሩ ስድስት መኪና መሄጃ እና መምጫ ያለው ሲሆን፤ ከዚህ ወደ ቦሌ የሚሄደው በእያንዳንዱ አቅጣጫ ስድስት መኪና፣ በድምሩ 12 መኪና የሚያስተናግድ እጅግ ዘመናዊ እና ባደጉት ሀገራት የምናየውን ዓይነት የፍጥነት መንገድ የምንገነባ ይሆናል። ይህ የፍጥነት መንገድ እንደ አዳማ፣ እንደ አዲስ አበባ የፍጥነት መንገድ ከመንገዱ ቀጥሎ ግንባታዎች የምናይበት ሳይሆን፤ ከመንገዱ ቀጥሎ በእቅድ፣ በዕውቀት የሚሠሩ ጥልቅ የአረንጓዴ ዐሻራ ዐሻራዎች ያሉት፣ ከዚህ ኤርፖርት እዚያ ኤርፖርት እስከሚገባ ድረስ ሙሉ በሙሉ አረንጓዴ አካባቢ እያየን የምንሄድበት ይሆናል።

ሁለተኛው፣ 38 ኪሎ ሜትር የሚጠጋ፣ በሰዓት ዝቅተኛ 120 በከፍተኛ እስከ 200 ኪሎ ሜትር በሰዓት ፍጥነት ያለው የባቡር መንገድ እንገነባለን፤ ፈጣን የባቡር መንገድ እንገነባለን። የዚህ የባቡር መንገድ ግንባታ ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ከገነባነው የሚለየው፣ ሙሉ በሙሉ ይህንን የባቡር መንገድ የሚገነባው ሀገራዊ ኩባንያ ይሆናል። ይህ ማለት ኤርፖርቱን ስንገነባ ቅድም እንደተገለጸው፣ በርካታ የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ተሳትፈዋል። የባቡር መንገድ እኛ እንገነባለን፤ በፍጥነት መንገድ ግንባታ ውስጥ የማይናቅ ድርሻ እንወስዳለን። ግንባታ ብቻ ሳይሆን የሚገነቡ ተቋማት እንገነባለን፤ እነዚህ ተቋማት ከአምስት ዓመታት በኋላ ከኢትዮጵያ ገበያ እየወጡ በሌሎች ገበያዎች ላይ የሚወዳደሩ እንዲሆኑ አበክረን እንሠራለን ።

የዚህን አየር መንገድ አሁን ማስጀመር፣ በፍጥነት መጀመር ወሳኝ የሆነበት ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓመት ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ አዳዲስ ደንበኞች ማስተናገድ

ጀምሯል። የዛሬ ሰባት ዓመት ገደማ የለውጡ ሰሞን በቦሌ ዓለም አቀፍ ሰባት ሚሊዮን ሰዎች በዓመት ያስተናግድ ነበር። ባለፉት አምስት ስድስት ዓመታት በተሠሩ ሰፋፊ ማስፋፊያዎች በዚህ ዓመት 21 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ የቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ያስተናግዳል። አሁን ባለው ዕድገት በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን የሚጨምር ከሆነ፣ ከሁለት እና ሦስት ዓመታት በኋላ የቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ተጨማሪ ሰው ማስተናገድ አይችልም። ያንን ችግር ከወዲሁ ተገንዝበን ዛሬ ሥራ ካልጀመርን፣ በቀጣይነት “የአፍሪካ ኩራት ታላቁ የአየር መንገድ” የሚለውን ስም ተጎናጽፈን ማቆየት ስለምንቸግር፤ ለነገ ዛሬ አስቀድመን መሥራት በማስፈለጉ ነው ይህ ውሳኔ የተወሰነው።

ከቡራትና ከቡራን፤ የኢትዮጵያ የትግል ስልት፣ የእኛ የትግል ስልት ተለውጧል። የእኛ የትግል ስልት ዛሬ ሠርቶ ነገን መዋጀት ነው። ዛሬ በቅጡ ተግተን ነገን ለልጆቻችን የሰመረ፣ የተሻለ ማድረግ ነው። የገጠሙን ጠላቶቻችን ግን ትናንትና ላይ ቆመው ዛሬን የሚሻሙ ናቸው። እኛ ዛሬ ሠርተን ነገን ለማዋጀት እንተጋለን፤ እነሱ ትናንትና ላይ ቆመው ዛሬን ለመሻማት ይሽቀዳደማሉ። ከጅምሩ እና ከስልቱ እንደምትመለከቱት በተለያየ የፍጥነት መንገድ የምንጓዝ መንገደኞች ስለሆንን፣ ከመተላለፍ አልፈን አንዱ ለሌላው በተሟላ መንገድ እንቅፋት መሆን አይችልም፤ ስልታችን የተራራቀና የተለየ ነው።

ፈተና አልቦ ጉዞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አላደረገም፤ ፈተና አልቦ ጉዞ ኢትዮጵያም አታደርግም። ፈተናዎችን ተጋፍጣ፣ ፈተናዎችን ተሻግራ የጸናችና የበለጸገች መሆን እንድትችል፣ እኛ የምናስብበትና ጠላቶቻችን የሚተጉበትን አውድ በቅጡ መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል። በተለየ የፍጥነት መንገድ ስለምንጓዝ ፈተና አልቦ ነው ማለት ግን አይደለም፤ እያንዳንዱ ፈተና ለሕልማችን፣ ለጅማሬያችን ፣ ለሥራችን የሚያጸናን፣ የሚያስተምረን፣ የሚያነቃን፣ የሚያተጋን ይሆናል። ፈተና አልቦ ጉዞ ለፈጠራ፣ ለትጋት እንቅፋት ነው። እያንዳንዱን ፈተና በቅጡ ተገንዝቦ ወደ ዕድል መቀየር የሚያስችል አውድ ከፈጠርን ግን የምንጎዳበት ሳይሆን የምንሻገርበት ይሆናል። እያንዳንዱ የሚወረወሩብን ድንጋዮችና ተግዳሮቶች ለግንባታ እንደሚውል ድንጋይ እንጠቀምባቸዋለን። እያንዳንዱን ጦር፣ እያንዳንዱን ፍላጻ እንደ አርማታ እንጠቀምበታለን። እያንዳንዱን ስድብ፣ እያንዳንዱን የቅናት ጩኸት እንደ ማንቂያ ደወል እንጠቀምበታለን። በድምሩ ግን የኢትዮጵያን ብልጽግናና የኢትዮጵያን መጽናት ማረጋገጥ የሆነውን ታላቁን ሕልማችንን በእነዚህ አስቻይ ሁኔታዎችና ፈተናዎች ታግዘን እናሳካለን።

በሀገራችን አንድ አባባል አለ፤ “ከሚያድግ ልጅ ጋር አትቀያየም” የሚል ታላቅ አባባል አለ። በቅርብ እና በርቀት ላሉ ሀገራት ያለኝ ምክር፤ ከሚያድግ ሀገር ጋር አትቀያየሙ። ይህ

የሚያድግ ሀገር ነገ የሚታደጋችሁ ስለሚሆን፣ ከወዲሁ እያደገ ያለው፣ ለማደግ ሕልም ያለው፣ የጠራ ሐሳብ ያለው፣ ሐሳቡም በልዩ ልዩ ሥራዎች ተፈትነው በተግባር የታዩ መሆኑን ተገንዝባችሁ፣ ከሚያድግ ሀገር ጋር ላለመቀያየም ራሳችሁን ምከሩ፣ ራሳችሁን ገሥጹ ማለት እፈልጋለሁ።

አንዳንድ አውሮፕላኖች በተለያየ ምክንያት መሬት ላይ ኤርፖርት ውስጥ የአየር በረራ አቋርጠው ቆመው እንመለከታቸዋለን ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላኖች ቦሌ ብትሄዱ ለተወሰኑ ሰዓታት መሬት ላይ ቆመው እናያቸዋለን፤ ያ ግን የአውሮፕላን ተፈጥሮ አይደለም። የአውሮፕላን ተፈጥሮ በሰማይ ላይ መብረር ነው። በመሬት ላይ የቆመን አውሮፕላን ስትመለከቱ የገዘፈ፣ ለመነሳት እንኳን የሚቸገር ይመስላል። መሬት ላይ የቆመ አውሮፕላን ተነስቶ ለመብረር መጀመሪያ የሚገፋው መኪና ሁሉ ይፈልጋል። ተገፍቶ መስመሩን ከያዘ በኋላ መሬት ላይ ለመነሳት የሚያደርገው ትግል፣ ድምጸቱ፣ ፍጥነቱ በምናይበት ሰዓት አውሮፕላን ተነስቶ ከምድር በሰማይ ላይ የሚበር አይመስልም። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ግን ያ የቆመበት ስፍራ ሳይሆን መላው ኤርፖርቱ፣ መላው ኤርፖርቱ ብቻ ሳይሆን መላው ከተማ ትንሽ ይሆንና አውሮፕላኑ ይገዝፋል። መሬት ላይ ሳለ የሚንቀሳቀስ ያልመሰለን ትክክለኛ ቦታውን፣ ተፈጥሮአዊ ቦታውን በሚይዝበት ሰዓት ኤርፖርቱም፣ ከተማውም፣ በምድር ላይ የምናየው ሁሉ ያንሳል።

ይህ በትክክል የኢትዮጵያ ታሪክ ነው። በጊዜያዊነት የአየር በረራ አቁመን ሊሆን ይችላል፤ ለጊዜው ቆመን ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ተፈጥሮ ግን መቆም አይደለም፣ መበልጸግ ነው። መለመን አይደለም፣ መርዳት ነው። የኢትዮጵያ ተፈጥሮ ለሌሎች ሥጋት መሆን አይደለም፤ በመላው አፍሪካ እንዳሳየው ነው፣ ለነፃነታቸው እርሾ እንደተውነው። ለአፍሪካ ኩራት፣ ለአፍሪካ ነፃነት ፣ ለአፍሪካ ብርታት፣ ለአፍሪካ ሰላም የሚተጋ ሀገር ነው። አሁን የአየር በረራ ማቋረጡን አይታችሁ የምትስቱ ሰዎች፣ የኢትዮጵያ ተፈጥሮ አለመሆኑን አውቃችሁ ከሚያድግ ሀገር ጋር ላለመቀያየም ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ተፈጥሯችን መጽናት፣ ተፈጥሯችን መበልጸግ፣ ተፈጥሯችን ሰላም ማጽናት፣ ተፈጥሯችን መርዳት ስለሆነ፤ የዛሬ 10 ዓመት በ2036 የአውሮፕላን ማረፊያው ሁለቱም ምዕራፎች ሲጠናቀቁ፣ በርካታ የጀመርናቸው ታላላቅ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚውን ኢኮኖሚ ትገነባለች። ይህ ፍላጎት አይደለም፤ ልክ ዛሬ እንጀምራለን ብለን እንደጀመርነው፣ ጨርሰን እንደምናሳየው በገሀድ የሚታይ፣ የሚጨበጥ እውነት ነው። ኢትዮጵያ መበልጸግ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀዳሚውን ኢኮኖሚ ትገነባለች። ታላቅ ጥንታዊት ሀገር መሆኗን፣ ለአፍሪካ ነፃነት መሥራቷን ዳግም ታረጋግጣለች። በዚህ ጊዜ

ልጆቻችን “ትናንት እንዲህ ስታደርጉን ነበር” እንዳይላችሁ አሰላለፋችሁን ማስተካከል አስፈላጊ ይሆናል።በመጨረሻም በዚህ ከባቢ ያሉ አርሶ አደሮች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባ ገዳዎች ለኢትዮጵያ ልማት ለከፈሉት ዋጋ፣ ለኢትዮጵያ ልማት ላሳዩት የባለቤትነት ስሜት፣ ለኢትዮጵያ ትጋት ቀያቸውን ፣ እርሻቸውን ጥለው ለመነሳት ላሳዩት ቁርጠኝነት ከፍተኛ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ።

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት 5,000 ሄክታር ለሚጠጋ ለዚህ መሬት አንድም ብር ሳያስከፍል፣ የሊዝ ክፍያ ሳያስከፍል ይህንን ልማት በመጋበዙ፣ በመደገፉ፣ አብሮን በመምራቱ ከፍተኛ ምስጋና እንዳቀርብ እና ሌሎች ክልሎችም ታላላቅ ፕሮጀክቶች በመጡበት ሰዓት የእናንተን ኃላፊነት ተወጥታችሁ ለጊዜያዊ ጥቅም ፣ ለሊዝ ሳይሆን ለዘላቂ ጥቅም መሥራት ፤ በአርአያነት፣ በትምህርት ይህንን ፕሮጀክት እንድትወስዱ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ባለፉት አንድ ዓመት ከምናምን ገደማ በእኛ ቢሮ የተደራጀው አስተባባሪ ኮሚቴ ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የቦርድ አባላት፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ አመራሮች በሙሉ፤ ከዚህ የሚነሳው አርሶ አደር እንደ ከዚህ ቀደሙ ተፈናቅሎ የሚለምንና የሚወድቅ እንዳይሆን፣ ይህ ፕሮጀክት ለእያንዳንዱ የአካባቢ ነዋሪ በረከት እንዲሆን፣ አርሶ አደሩ የሚማረርና የሚያለቅስብን ሳይሆን ዕንባውን እየረጨ የሚያመሰግን፣ ፕሮጀክቱን የሚጠብቅና የሚደግፍ እንዲሆን ለማስቻል፤ የእያንዳንዱ አርሶ አደር መኖሪያ ቤት፣ መንደርና የወደፊት የሥራ ሁኔታ የተገነባበት መንገድ እጅግ አስደማሚ፣ አስደናቂና ትምህርት ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

እዚህ ያላችሁም ሰዎች፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት፤ ሥራ ዛሬ አልጀመርንም። በሺሕ ለሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ከተማ ገንብተን፣ በሺሕ ለሚቆጠሩ አርሶ አደሮች የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ መንደር ገንብተን፣ እነዚያን አርሶ አደሮች አሰልጥነን፣ በአዲስ ሕይወታቸው ፣ በአዲስ ሰፈራቸው መኖር አለማምደን፣ የአንድም ሰው ሕይወትሳናስተጓጉል ነው ዛሬ ሥራ እየጀመርን ያለነው እንጂ ገና ሀ ብለን እየጀመርን አይደለም። ለምን? ሰው ተኮር ካልሆነ ፕሮጀክት፣ ሰውን ማዕከል ካላደረገ ፕሮጀክት አይጠበቅም፣ አይጸናም፣ አይዘልቅም። ይህ ጉዳይ እንዲሳካ የአስተባባሪ ኮሚቴው፣ የቦርድ አባላት፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፣ ዲዛይነሮች፣ አመራሮች፣ ሙያተኞች፣ የሥራ ተቋራጮች ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላሳያችሁት የላቀ ጥረት ከፍ ያለ ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ዛሬ 2018 በገና እና በጥምቀት መካከል ያለ እና የማይረሳ ጊዜ ነው። በፈረንጆች 2030 ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ባላችሁበት በጋራ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ፣ የ60 ሚሊዮን መንገደኛ ማስተናገጃ እዚህ ቦታ እናስመርቃለን። አበዳሪዎች፣ በዚህ ጉዳይ የሚተባበሩ ኩባንያዎችና ሀገራት፤ ጊዜ እንዳያልፍባችሁ እኛ በገበያ ሕግ ከብዙዎች ጋር ተባብረን መሥራት እንፈልጋለን። እግራችሁን የምትጎትቱ ካላችሁ፣ ኢትዮጵያ ሕዳሴን የገነባች ሀገር ስለሆነች ይሄኛውንም ብቻዋን ትደግመዋለች!

አመሰግናለሁ!
ቢሾፍቱ፣ ኦሮሚያ

በደቡብ ምዕራብ ክልል በጉራፈርዳ ወረዳ የገጠር ኮሪደር ጉብኝት

ጥር 2፣ 2018ዓ.ም

አሁን የምንገኘው በደቡብ ምዕራብ ክልል በጉራፈርዳ ወረዳ ነው። ጉራፈርዳ ወረዳ በለምነቱ፣ በሚያመርተው ቡና፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ የእርሻ ምርቶች የሚታወቅ አካባቢ ነው። የማኅበረሰቡ ሁኔታ ቅይጥ ነው፤ ከተለያየ አካባቢ የመጡ ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት፣ እጅግ ለም በሆነ በእርሻና በቡና የሚተዳደር ሕዝብ ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ ባለው ባህል የተነሳ፣ ምንም ቡና አምራችና ሻጭ ቢሆንም አርሶ አደሩ የኑሮ ዘዬው በሚጠበቀው ደረጃ አይደለም።

ከዚህ ቀደም “የተሻገረ ገጠርን እንፍጠር” ያልነው፤ ቡናም ለቅመን፣ ስንዴም አምርተን፣ በቆሎም አምርተን መጨረሻ ላይ ለዜጎቻችን የኑሮ ዘዬ መለወጥ ያለውን አንድምታ ማየት አግባብነት ስላለው፤ “በከተማ የጀመርነውን የኮሪደር ሥራ ወደ ገጠር እናምጣ” ብለን በሁሉም ክልሎች፣ በሁሉም ዞኖች እነዚህ አዳዲስ የተሻገሩ የገጠር መንደሮች እየተሠሩ ይገኛሉ፤ ባለፉት ጥቂት ወራት እኔም ብዙዎቹ ጋር የመድረስ ዕድል አግኝቻለሁ።

ዛሬ በደቡብ ምዕራብ ያየነው የተሻገረ የገጠር መንደር ወይም የገጠር ኮሪደር ልማት የሚያስደስተው ነገር፤ ሰዎች በሳሎን እና በመኝታ ቤት፣ በመጸዳጃ ቤት እና በመኝታ ቤት፣ በከብቶች ማደሪያና በሰዎች ማደሪያ፣ በኩሽና እና በሰዎች ማደሪያ መካከል መለያ አበጅተው፤ የጓሮ አትክልት፣ የጓሮ ሌማት፣ ዶሮን ጨምሮ ላም፣ የላም ወተትና ማር በእያንዳንዱ ቀዬና ጓሮ የማየት ዕድል አግኝተናል። ይህንን ጉዳይ በሀገር ደረጃ እንደየከባቢው ተፈጥሯዊ ጸጋ መጠቀም ችለን የዜጎቻችንን ሕይወት መቀየር ከቻልን፣ የተሟላ ብልጽግና እናመጣለን ማለት ነው። አንድ ሰው መብራት አለው ማለት ዜናና ቴሌቪዥን ይሰማል ማለት ነው፤ መረጃ ያገኛል ማለት ነው። መረጃ ያገኛል ካልን ስልክ አለው ማለት ነው፤ ስልክ ካገኘ ከወዳጅ ዘመድ ይገናኛል ብቻ ሳይሆን ይነግድበታል፣ ይበደርበታል፣ ያለውን ምርት ለማውጣት የዋጋ ሁኔታን ያጠናበትበታል ማለት ነው።

መረጃ ያለው ማኅበረሰብ ወይም አርሶ አደር ያመረተውን ምርት በደላሎች እንዳይነጠቅ፣ በተገቢ ዋጋ ለመሸጥ እና አትራፊ ለመሆን ያግዘዋል። ቅድም እንዳየነው በእያንዳንዱ ጓሮ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ማር ካለ፤ ሰው ቢያንስ በምግብ ምክንያት ሕይወቱ አደጋ ላይ አይወድቅም። በጓሮ ያሉ ምግቦች በከባቢው ካሉ የእርሻ ውጤቶች ጋር ተደምረው በቂ ምግብ የሚያገኙበትን ዕድል ይፈጥራል። እዚህ ጉራፈርዳ የተሠራው የገጠር ኮሪደር

ልማት ከሌላ አካባቢ ለየት የሚያደርገው፣ የራሱ መዋዕለ-ሕፃናት ደግሞ አሉት፤ ልጆች እዚሁ ሰፈር ውስጥ መዋዕለ-ሕፃናት ተምረው ከዚህ ከፍ ሲሉ፣ ወደሚቀጥለው ከተማ ሄደው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የማግኘት ዕድል አላቸው። እነዚህ ልጆች ደግሞ ዛሬ ሠርተንባቸው ነገ ሀገር የሚረከቡ ይሆናሉ። በድምሩ ብልጽግናን እናረጋግጥ ሲባል፣ በቁጥር የሚታይ ዕድገት ብቻ ሳይሆን በከተማም በገጠርም የእያንዳንዱን ዜጋ ሕይወት መንካት አለበት ማለት ነው። የዜጎች ሕይወት ሲነካ ለውጡ የሚጨበጥና የሚታይ ሲሆን፤ ሰዎች እየተነቃቁ፣ እየተጋገዙ፣ ይበልጥ እያሰፉና ይበልጥ እያሳደጉ፣ የማይቆም ቀጣይነት ያለው እና ጥራት ያለው ዕድገት ማረጋገጥ ይቻላል፤ እና ጅማሮው በጣም በጣም ጥሩ ነው።

ደቡብ ምዕራብ ብዙ አቅም ያለው ክልል ነው፤ ሀብታም ክልል ነው። ይህ ክልል ሀብቱን መንዝሮ ዜጎችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ፣ ቅድም ሱርማ ላይ እንዳየነው፣ በዚህ ሁሉ ሀብት ውስጥ ገና ያልተቀየረ የኑሮ ዘዬ ደግሞ እንዳለ ያሳያል። በዚህ ሁሉ አቅም ውስጥ ዜጎቻችንን አሁንም ማስተማር፣ የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል፣ ቤታቸውን መቀየር ያስፈልጋል። እኛ ሁሉን ሠርተን አንችልም፤ እዚህ ጋር የተሠራው ማሳያ ነው። እያንዳንዱ አርሶ አደር በአካባቢው ባሉ ቁሳቁሶች የራሱን ቤት ወደዚህ ደረጃ ማዘመን አለበት የሚል ሰርቶ ማሳያ ተደርጎ መወሰድ አለበት።

አሁን ይህ የተሠራው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትና ተጠሪ ተቋማት ትብብር ነው፤ እዚህም፣ ጉራጌም፣ ባሕር ዳር ላይም፣ ኦሮሚያም አንዳንድ አካባቢ፣ ጊንጫ አካባቢ በየቦታው ማሳያ እንዲሆን የእኛ ጽሕፈት ቤት የጀመራቸው ሥራዎች አሉ፣ የክልል መንግሥታት የጀመሯቸው ሥራዎች አሉ፣ የዞን አመራሮች የጀመሯቸው ሥራዎች አሉ፤ እነዚህ ሲደመሩ እና እየተበራከቱ ሲሄዱ የምናስበውን የተሻገረ ገጠር ለማረጋገጥ ያግዛሉ። በዚህ አጋጣሚ ይህንን ሥራ ያስተባበሩ፣ እንደዚህ ያለ ሥራ እንዲሠራ ጥረት ያደረጉ የእኛን ጽሕፈት ቤት አመራሮችና ሠራተኞች ማድነቅና ማመስገን እፈልጋለሁ። በክልሉ በተለይ ይሄንን ቦታ ላይ ፕሮጀክቱን ወስዶ፣ ባጠረ ጊዜ ውስጥ እንደዚህ ያለ መንደር መሥራት የቻለውን ወጣት እና የተባበሩትን የአካባቢ ሰዎች በሙሉ ማመስገን እፈልጋለሁ።

አደራ ማለት የምፈልገው ግን ይህ በቂ አይደለም፤ ይህ ማሳያ ነው። እያንዳንዱ አርሶ አደር ቡናውን ሸጦ በዚህ ዲዛይን መልክ ቤቱን ለመሥራት የሚያስችል አቅም አለው፤ ብዙ ውድ አይደለም እንዳያችሁት፤ ሐሳብ ነው የጠፋው እንጂ ቁሳቁስና ግብዓቱ እዚሁ ያለ ነው፣ የሚሠሩ ሰዎችም እዚሁ ያሉ ናቸው፤ ከሞላ ጎደል አብዛኛው ነገር እዚህ አለ።

ግን መብራት ያለው፣ ቴሌቪዥን ያለው፣ ስልክ ያለው፣ ራቅ ባለ ቦታ መጸዳጃ ቤት ያለው ሰው ከተበራከተ በሽታ ይቀንሳል ወይም ይጠፋል ማለት ነው። የሚማር ትውልድ ካለ ፈጠራ ያድጋል ማለት ነው፤ እንደ ሀገር የምናስበውን ነገር ለማሳካት ስለሚያግዝ፣ የዚህ ከባቢ አመራሮች በዚህ ሳትዘናጉና በዚህም ሳትኩራሩ ፤ ይህ ማሳያ እንጂ ካለን አቅም አንጻር ምንም ስላልሆነ፣ በስፋት አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በመላው ኢትዮጵያ እንደዚህ ያሉ ጅማሮዎች ተጀምረዋል። እንግዲህ ገጠሩን በእርሻ መጀመሪያ ካነቃቃን በኋላ፣ በአረንጓዴ ዐሻራ ያ የጀመርነውን ሥራ ካጠናከርን በኋላ፣ ቀጥለን በጓሮ ሌማት በየመንደሩ ዶሮና ላሞች እንዲበራከቱ የሠራናቸው ሥራዎች የሚጨበጥ ውጤት ማምጣት እየጀመሩ ሲሄዱ፤ ይህ ጉዳይ ቤተሰብ ላይ ማረፍ አለበት፣ ዜጎች ላይ ማረፍ አለበት።

በስንዴ ያገኘነው ውጤት፣ በቡና ያገኘነው ውጤት፣ በጓሮ ሌማት ያገኘነው ውጤት የእነሱን ሕይወት ቀይሮ ማየት አለብን በሚል የጀመርነው የገጠር ኮሪደር ልማት ፍሬ እያፈራ ነው። እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ግን እንድንበረታ፣ እንድንጠነክር፣ እንድንሠራ ፣ ይህን ነገር በፍጥነት እንድናባዛ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፤ እጅግ ጥሩ ጅማሮ ነው፤ ይስመርላችሁ፣ ይቀጥልላችሁ፣ የዜጎቻችሁን የደስታ ዕንባ ለማየት ያብቃችሁ። ቅድም ያየነው የደስታ አምባ የእያንዳንዱ አመራር መሻት ነው። ዜጎች ደስ ብሏቸው ሲያነቡ ማየት የእኛ ፍላጎት ነው፤ በዚህ አግባብ ተባብረን በመስራት የዜጎቻችንን ሕይወት እንድንቀይር አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ!

እኔ በጣም ደስ ብሎኛል እናንተም እንኳን ደስ አላችሁ!
ጉራፈርዳ ወረዳ

የደንቢ ሎጅ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ጥር 2፣ 2018ዓ.ም

በመጀመሪያ፣ ይህንን ስፍራ ዛሬ ስመለከት የሚታሰበኝ ነገር በኢትዮጵያ አባባል “አባይን ያላየ ምንጭ.....” እንደሚባለው ነው፤ እኔ እና የኔ ቢጤዎች የሆንነው፤ ይህንን መልክዓ ምድር ፣ ይህንን ውበት፣ ይህንን የቦታ አቀማመጥ የተፈጥሮ ጸጋ ሳላይ፤ የማየት ዕድል ሳይኖረኝ ሌሎች አገራት ከዚህ በጣም ያነሰ ነገር በማይበት ሰዓት “ኢትዮጵያ ተስፋ የለላት፣ የማትደርስ፣ ሌሎች የሚያምሩ እኛ ግን ውበት የሌለን፣ ሌሎች የሚችሉ እኛ ግን የማንችል” አድርጌ ያሰብኩባቸው ጊዜያት ቀላል አልነበሩም ። ብዙ ሰው አገሩን ጠንቅቆ ሳያውቅ፣ በአገሩ ያለውን ውበትና በአገሩ ያለውን ጸጋ በአንክሮ ማስተዋል ሳይችል፤ ወጣ ሲል የሰው አብዝቶ ያደንቃል ። ነገር ግን ካለንም ማጋነን፤ ማንም ኢትዮጵያዊ ይሄንን ስፍራና ይሄንን ከባቢ መጥቶ ማየት ቢችል፤ እንደው በዓለም ብቸኛው የሚል የተጋነነ ስያሜ እንኳን ባይሰጠው፣ ከዓለም ልዩ እና ምርጥ ቦታዎች አንዱ ለመባል ግን በቂ መሆኑን ሁላችሁም እንደምታምኑ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ኢትዮጵያውያን በተቻለ መጠን አማን ሚዛን እየመጡ የደንቢ ሎጅን ማየት እንዲችሉ እና የኢትዮጵያን የውበት ልክ፣ የፀጋ ልክ ማስተዋል እንዲችሉ እጋብዛለሁኝ ። ወደዚህ ስፍራ መምጣት እንደዚህ ቀደሙ አስቸጋሪ አይደለም ። ኤርፖርት አለን፤ ከኤርፖርት እስከ ሎጁ ያለው ርቀት አምስት፣ አሥር ደቂቃ ቢወስድ ነው ። ማንም ሰው ከየትም ቦታ በአውሮፕላን ተሳፍሮ መጥቶ፣ በሎጁ በሚሰጠው አገልግሎት በአምስት እና በ10 ደቂቃ እዚህ ቦታ መጥቶ አንድ ቀን፣ ሁለት ቀን ከቤተሰቡ ጋር ቢያሳልፍ፤ ዘመኑን ሙሉ የተመኘውን ገነት በጨረፍታ የሚያይበት ቦታ ይሆናል ማለት ነው።

“መደመር” ስንል ለአማን ሚዛን፣ ለቤንች፣ ለሸካ ምን ማለታችን ነው ያላችሁ እንደሆነ፤ ይህ ስፍራ እኛ አልሠራነውም ፣ ፈጣሪ አድሎ ሰጠን፤ ተራራው፣ ሸንተረሩ፣ ዛፎቹ፤ አብዛኛው ነገር የፈጣሪ የእጅ ሥራ ነው ። ፈጣሪ የሰጠንን ብቻ ወስደን ዝም ካልን አሁን የምናየውን ውበት ማየት አንችልም ። እሱ ላይ የደርግ መንግሥት ዜጎችን በማስተባበር በሺህ የሚቆጠር ሄክታር ቡና ተከለ፤ ጫካውን ወደ ገንዘብ ቀየርነው ማለት ነው። የደርግ መንግሥት ይሄንን ግድብ በመገደብ፣ አነስተኛ የኃይል ማመንጫ ያለው የኃይል ማምረቻ እዚህ ቦታ ሠራ ። ይሄ ሥራ በዚያ ሁኔታ እያለ አምናም አቻምናም መጥተን ነበር፤ እናንተም ነበራችሁ፤ በፍጹም ግን ዛሬ ያለው ውበት አልነበረውም ። ምክንያቱም የጎደለ ነገር ነበረ ። ይሄ ውበት ኤርፖርት ይፈልጋል፤ ይሄ ውበት እንደዚህ ያለ ሎጅ ይፈልጋል።

ኤርፖርቱን መንግሥት ሠራው፤ ይህንን ደግሞ ጀማል ሠራው ። መደመር ማለት ግል ፣ መንግሥት፣ ተፈጥሮና የትናንትና ሥራ ድምር ውጤት ማለት ነው።

ይሄ ግን ብቻውን በቂ አይደለም ። የዚህ አካባቢ ከባቢ ሕዝብ ውጫ ውጪውን ስንመለከት በኑሮ የደኸየ ሊመስል ይችላል፤ ግን ልቡ ሀብታም ነው ። ሕዝቡም ልቡ ሀብታም ፣ አርቆ አስተዋይ፣ የተፈጥሮ ጸጋ የገባው፣ ተፈጥሮን መጠበቅ የራሱ ኃላፊነት እንደሆነ ያመነ በመሆኑ፤ የእነዚህ ሁሉ ተግባር ሲሰናሰል እና ሲደመር ዛሬ እንዲህ ያለውን ድንቅ ነገር በሀገራችን ለማየት በቃን ። እውነት ለመናገር፣ ብዙ ሰዎች የዚህን ቦታ ተንቀሳቃሽ ምስል ሲመለከቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ብለው ያምናሉ ብዬ አልገምትም ። እንደዚህ ያለ ሁለንተናዊ የተሟላ፣ በሰው እጅ ሊሠራ የማይችል፣ በሥዕል ብቻ የሚገለጥ ውበት ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ብሎ ለማመን ያስቸግራል፤ ነገር ግን አለ ።

ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ሀገር፣ የተባረከች ሀገር፣ የተወደደች ሀገር ፣ የተመረጠች ሀገር የሚባለው ውሸት አይደለም፤ እውነት ነው ። እኛ ነን ማስተዋል፣ ማየት ያቃተን እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ የሌለ ውበት፣ የሌለ ጸጋ፣ የሌለ ሀብት የለም። ዓይን ካልተገለጠ፣ የከባቢን ሀብት ማየት ካልተቻለ፣ ቢቀመጥም ልክ በአፈር ውስጥ እንደተቀበረ ወርቅ ማለት ነው ። አለ፣ አናየውም፣ አንጠቀምበትም ። ዛሬ ግን ዘመን ደርሶ በመንግሥት እና በግል ትብብር፣ በመንግሥት እና በሕዝብ ትብብር እንደዚህ ያለው ድንቃ ድንቅ ሥራ በሀገራችን መሠራት ሲጀምር፤ ይሄ ውበት ይሄንን ውኃ፣ ይሄንን ጫካ፣ ይሄንን ቡና ይተካል ማለት አይደለም፤ አይተኩም እነሱ፤ ግን የነሱን ውበት ይገልጣሉ ። እነሱን ለማድነቅ እንደዚህ ያለ ምቹ ከባቢ ይፈጥራል ።

እነሱን ለመመራመር፣ ለማድነቅ የፈለገ ሰው «የት ሄጄ አርፋለሁ?» ብሎ እንዳያስብ፣ እንዳይጨነቅ ያደርጋል ። ያ ምቾት ከሌለ ሰው በመሳብ አቅም ብቻ፣ በሚያምር ነገር ብቻ ጥቂቶች ደፋሮች ይሞክሩ ይሆናል እንጂ ብዙ ሰው ይቸገራል ። እና የዚህ መገንባት ሀገራቸውን ለማየት፣ ውበት ለማድነቅ፣ ሰላም የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ በእጅጉ ጠቃሚ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያውያን በቻላችሁት መጠን በቅርብ ርቀት ያላችሁ በመኪና፣ በርቀት ያላችሁ በአውሮፕላን የመጣችሁ አማን ሚዛንን ማየት የሰርክ ሥራችሁ እንዲሆን አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ለአማን ሚዛን ሰዎች እምብዛም ምክር አያስፈልጋቸውም፤ ደጋጎች፣ እንግዳ ተቀባዮች መሆናቸውን እኔም በራሴ አውቀዋለሁ፣ ዓለምም ያውቀዋል ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ነገር አለ ። ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ነገር፤ ከሌላ አካባቢ ሰዎች

እኛን ለማየት ሲመጡ ሁለት ዓላማ አላቸው ። አንደኛው ዓላማ ሀገር ማየት፣ ተፈጥሮን ማየት፣ ሀገር ማድነቅ የሚፈልጉ ናቸው ። ሁለተኛው ዓላማ ተራሮቻችን ምን እንዳላቸው፣ ጫካዎቻችን ምን እንዳላቸው ለመፈተሽ፣ ለመመርመር፣ ለማወቅ፣ ቀድመውን ለመጠቀም ይመጣሉ ። የመጣ ሁሉ ለመልካም ነገር ይመጣል ማለት አይደለም፤ የመጣ ሁሉም ለጥፋት ይመጣል ማለት አይደለም ።

በጥፋትም ይምጣ በመልካም ሐሳብ ፣ የዚህ ሕዝብ ተግባር መሆን ያለበት የመጣውን ከገባበት እስከሚወጣበት በቅርብ ርቀት ጥርሳችን ሳይከደን፣ እየሳቅን፣ እያስተናገድን፣ የከፋ ነገር ደግሞ እንዳይወስዱ እየተከታተልን በሰላም ወደ አገራቸው እንዲሄዱ ማስቻል ይኖርብናል ። ያ የምትመከሩ ሆናችሁ ሳይሆን ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ። ሰው እናንተን ተማምኖ ወደዚህ ሲመጣ ምናልባት ጎማ ቢተነፍስበት፣ ወጣቶች ይሁነኝ ብለው አስበው፣ ጎማ ጠግነው ደግፈው ወደዚህ ያለ ስፍራ ማምጣት፣ ውኃ ቢቸግር ውኃ መስጠት፣ ለእለት ባለ ግብይትና ግኝት፣ የገንዘብ ግኝት ብቻ ሳይሆን በዘላቂነት ለኛ መልካም ስም ባለው ዋጋ ልክ ሰዎችን በቅጡ መቀበልን የወል ሥራችን እንድናደርግ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ ።

ይህ ሎጅ ስናየው ያምራል፤ በማንኛውም ሰው ጭንቅላት ይህ ሎጅ አብዛኛው በዚህ ከባቢ፣ ጥቂት ከሌላ አካባቢ፣ ከኢትዮጵያ ውስጥ በመጡ ጥሬ ዕቃዎች ተገነባ ብሎ ሰው አያስብም ። አማን ሚዛን የዛሬ 30፣ 40 ዓመት ሸክላ አምርቶ የሸክላ ቤት መሥራት የሚችል ማኅበረሰብ ያለበት ቤት፤ ሸክላ ለማምረት የሚያስችል በቂ ያልተቀነባበረ ጥሬ ዕቃ ያለው ከባቢ ነው ። የሃይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌዎች፣ እናቶች፤ ልጆቻችሁን አረቄ ሰፈር፣ ጠላ ሰፈር እንዳይውሉ፣ ሸክላ እንዲያመርቱ፣ አጥር እንዲያስተካክሉ፣ ቤት እንዲያስተካክሉ ማድረግ ብትችሉ፤ ሙያተኛ፣ መሥራት የሚችል ሰው፣ ብርቱ ሰው ስለምንፈጥር እንጨት ያለው እዚህ ነው፤ ግንባታ ማገጃ ያለው እዚህ ነው፤ ለብዙ ነገር የምናውለው መቼም እዚህ መትከል አያስፈልግም እኮ፤ መርጨት ብቻ ነው፣ ከረጨነው ራሱ ይበቅላል ።

እንደዚህ ባለው ምድር የቆሸሸ ከባቢ ማየት ተገቢ አይደለም ። ይሄንን አባቶች አበክራችሁ ልጆቻችሁን እንድታስተምሩ፣ እጃቸውን እንዲጠቀሙበት፣ ጊዜያቸውን እንዲጠቀሙበት፣ ለመልካም ነገር ተገልግለው ከባቢያቸውን ይበልጥ ማስዋብ እንዲችሉ ማድረግ አለብን ። ከውጭ ሲገባ እንቸገራለን ። የሀብት ውስንነት አለ፤ ሸክላው እዚህ ካለ ግን በትናንሽ የሸክላ ማምረቻ በየመንደሩ፣ በየቀበሌው በርከት ያለ ሸክላ ማምረት ይቻላል ። ይሄንን ሥራ እኛ ከውጭ ያመጣነው ሰው የለም፤ የተጠቀምነው እዚሁ አካባቢ ያለን

ሰው ነው ። ይሄንን መሥራት የሚችል እጅ ካለ ሲቀጠር የሚሠራ ፣ ለራሱ፣ ለወላጆቹ፣ ለአዛውንቶች፣ ለአረጋውያን መሥራት የማይችል ሰው ከሆነ ግን ችግር ነው ማለት ነው ። ይሄ ለሌላ የመቀጠር፣ ለሌላ የመሥራት ዝንባሌያችን ለመማር ብቻ መሆን አለበት እንጂ የሁል ጊዜ ልምምድ መሆን የለበትም ።

በጣም የሚያሳዝነውና የሚያስደንቀው ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ፕሮጀክቶች አሁን ይሰራሉ ። በየቦታው ብትሄዱ አራት፣ ሶስት፣ ሁለት የውጭ ዜጋ አለ ። መቶ፣ አንድ ሺህ የሚጠጋ ኢትዮጵያዊ አለ፤ አብዛኛው ስራ የሚሰራው በኛው ልጆች ነው ። እነዚህ ልጆች ስራ ችለዋልና ጠቅለው ስራውን ደግሞ ይውሰዱ ሲባል፣ ሲቀጠሩ በሚሰሩት ልክ ስራውን ሲወስዱ አይሰሩትም ። ለኛ መቀጠር የተገባ ይመስል፣ ለሰው ስንሰራ የምንታዘዝ፣ የምንሸቆጠቆጥ፣ የምንፈራ፤ ስራውን እኛ ስንወስድ ሃላፊነት ሲሰጠን ግን በታመንንበት ልክ የማንቆም ከሆነ የምናስበውን ብልጽግና ማረጋገጥ እንቸገራለን ።

የማናውቃቸው በጣም በርካታ ነገሮች አሉ፤ ከሚያውቁ ተጠግተን መማር ተገቢ ነው፣ ከእነሱ ጋር ሰርተን መማር ተገቢ ነው ። ካወቅን በኋላ ግን ይበልጥ በርትተን፣ ተጋግዘን ያንን ዕውቀት ማስቀረት ነው ያለብን እንጂ ሁለት ሶስት ሰው ሲገራው በሺ የሚነዳ፣ ያ ሁለት ሰው ሲጠፋ ግን ስራ የማይሰራ ከሆነ አስቸጋሪ ይሆናል ። ወጣቶች ተሰፍሮ፣ ተለክቶ የተሰጣችሁ ዘመን አለ፤ ያንን ዘመን በአግባቡ መንዝራችሁ የማትጠቀሙበት ከሆነ ያልፋል። ያንን ጊዜ ብንጠቀምበት ተመልከቱ፤ እንደዚህ ያለውን ውበት ነው ላለፉት 100 ዓመታት ደብቀን የኖርነው። በአንድ በኩል በመጠበቃችን የምንደነቅ፣ እስካሁን ይሄን ማድረግ ባለመቻላችን ግን የምንወቀስ መሆን አለበን ። ይሄንን ሳያዩት ያለፉ ደግሞ ብዙ ሰዎች ስላሉ፣ እንደዚህ ያለውን ብናበራክት ምን ሊፈጠር እንደሚችል በሀገራችን አስቡት።

በተለይ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ እንደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ያለ ሀብታም ክልል ማግኘት ትቸገራላችሁ ። በእያንዳንዱ ዞን ብትሄዱ፤ ከፋ ብትሄዱ፣ ዳውሮ ብትሄዱ፣ ኮንታ ብትሄዱ፣ ቤንች ብትሄዱ፣ ሸካ ብትሄዱ የሄዳችሁበት ቦታ በሙሉ ታይቶ የማይጠገብ ውበት ያለበት ክልል ነው ። ቡና ሲባል በኢትዮጵያ ከኦሮሚያ ቀጥሎ ሁለተኛው ቡና አምራች ከባቢ ነው ። ይሄ ሁሉ ሃብት፣ ይሄ ሁሉ ቅን ሰው ያለበት ክልል ለምንድነው አንዳንድ ዐይን ገላጭ ስራዎች ሲጀመሩ እነሱን ወስዶ በራሱ የማይሮጠው? ማንን ነው ቁጭ ብሎ የሚጠብቀው? የሚለው ጉዳይ አመራሮችም, የሀገር ሽማግሌዎችም፣ ወጣቶችም እንድታስቡበት እፈልጋለሁ ። ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን የምታለሙት እናንተ ናችሁ። ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ራሱን ማልማት ብቻ አይደለም፣ ለሌላም መትረፍ ይችላል ። ሩጫው እና ሽኩቻው ከሚዛን፣ ከቦንጋ፣ ከተርጫ እየሮጡ አዲስ

መትረፍ ይችላል ። ሩጫው እና ሽኩቻው ከሚዛን፣ ከቦንጋ፣ ከተርጫ እየሮጡ አዲስ አበባ መግባት መሆን የለበትም ወጣቶች፤ ከአዲስ አበባ እየተመለስን ይሄንን ቦታ ዐይን እየገለጥን ማስዋብ ነው መሆን ያለበት ። ትንሽ ዕውቀት፣ ትንሽ ስልጣን ሲገኝ ሁሉም እየሮጠ ወደዛ የሚሄድ ከሆነ ይሄኛው ለማን እንደሚተው አላውቅም ። እንደዚህ ያለውን ውበት ለማምጣት እኮ ነው አረንጓዴ ዐሻራ እያልን መከራ የምንበላው ። ውበት ባለበት ቦታ ደግሞ ወደ ገንዘብ መቀየር አለበት ። ያ እንዲሆን የዚህ አካባቢ ሰዎች ብዙ የተፈጥሮ ጸጋ አላችሁ፣ የሚያስደንቅ ባህል አላችሁ፤ ክረምቱን ጨምረን ብንሰራ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን፣ ሌሎች ከሌሎች ስፍራ እየመጡ ለማየት የሚጓጉት፣ አይተውት ደግሞ አመስግነውና አድንቀው የሚሄዱበት ስፍራ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም ። ከዚህ እስከ ቦንጋ መቶ ምናምን ኪሎ ሜትር በዚህ ያለ ውበት እየነዱ መሄድ ሁሉ ቦታ እኮ አይገኝም፤ የለም እኮ ይሄ! ይሄንን ውበት ማየት፣ ማድነቅ፣ መጠበቅ፣ ወደ ሀብትነት መቀየርና ለሌሎች አስተማሪ እንዲሆን አድርጎ መገልገል የእኛ ተግባር መሆን አለበት።

ክቡር ፕሬዚዳንት፣ ትልቅ ዕድል እና ትልቅ ፈተና ከፊትህ ተደቅኗል ። ይሄንን ምርጥ ክልል፣ ይሄንን ምርጥ ህዝብ ለመምራት መታደል ትልቅ ጸጋ ነው ። መምራት ማለት ግን ያለንን ነገር፣ ያልታየን ነገር እየደከሙ፣ እየጎረጎሩ ማውጣት መሆኑ ግን ሊሰመርበት ይገባል ። ጨበራ የተሰራበት፣ ሃላላ ኬላ የተሰራበት፣ የኮይሻ ግድብ እየተሰራ ያለበት፣ አሁን የደንቢ ማረፊያ ቤት ደንቢ ሎጅና ኤርፖርት እየተሰራ ያለበት ክልል ተነቃቅቶ ተጨማሪ ስራዎች የማይሰራ ከሆነ፣ በዚህ ደረጃ የሚሰራበት ክልል እናንተ እዚህ ሆናችሁ እንደምታስቡት ሳይሆን የለም ።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ልክ የፌደራል መንግሥት መዋዕለ-ነዋይ ያፈሰሰበት ክልል የለም ። ለምሳሌ ኮይሻ ማለት ሶስት አራት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለት ነው፤ ቀላል መዋዕለ-ነዋይ አይደለም ። በሺህ የሚቆጠር ሰው የያዘ ነው፤ የዛን ከባቢ ልክ እንደዚሁ የሚቀይር ማለት ነው ። ከሀዳሴ ቀጥሎ ትልቁ ፕሮጀክት የነበረው ኮይሻ ነው ። አሁን በጋዝ፣ በኤርፖርት ከጀመርናቸው ውጪ ማለት ነው ። እነዚህ ጉዳዮች የእኛን ልጆች ስራ አስተምረው፣ መጠነኛ ለስራ መነሻ የሚሆን ገንዘብ አስገኝተው፣ ተባብረን አካባቢውን ለመቀየር ካልተገለገልንበት ዋጋ የለውም ። ለምሳሌ ትናንትና ያየነው የገጠር መንደር 100 በመቶ የተሰራው እዚሁ ነው፤ ፕሮጀክቱን የመራው የእናንተው ልጅ ነው ። ያስተባበሩት፣ የሰሩት የክልሉ አመራሮች ናቸው ። ታዲያ ያንን አስር ቤት 100፣ 200 ብናደርገው ምንድነው ችግሩ? እቃው ያለው እዚህ፣ የሚሰራው ሰው ያለው እዚህ ። ይሄኛው በሶስት ወር ተሰርቶ ከሆነ ስድስት ወር ይፍጅብን፣ ችግር የለውም፤ ዓመትም ይፍጅ ግን እንስራው።

የብዙ አርሶ አደሮች ቤት እንደዚያ አምሮ ማየት እንዴት ያለ መታደል እንደሆነ ለናንተ መንገር አያስፈልግም ። የእኛ አርሶ አደሮች ከዘመን ዘመን ተሰቃይተው፣ መከራ በልተው ከሰሩ በኋላ መከራ እንደበሉ ተመልሰው ይሄዳሉ ። እፎይ የሚሉበትን ከባቢ መፍጠር ከእኔና ከእናንተ የሚጠበቅ ተግባር ስለሆነ፣ እኔ አደራ ልላችሁ የምፈልገው ነገር፦ ወርቁም፣ ቡናውም፣ መልካም ስራ ወዳድ ሰውም፣ ተፈጥሮም ያለው እናንተ ጋር ነው ። ይሄ በኮንትሮባንድና በስርቆት እንዳይጠፋ ጠብቃችሁ፣ ከባቢውን ለማልማትና ለሌሎች ለመትረፍ እንድትተጉ አደራ እያልኩኝ፤ ጀማል ጥሩ ስራ ስለሰራህ በዚህ ስፍራ እና ውበቱን ስላወጣህ እያመሰገንኩ፣ በነካ እጅህ ይሄንን ከባቢ ለመቀየር አንዱ የሚያስፈልገው በአፍሪካ ትልቁ የቡና እርሻ ያለበት ከባቢ ነው፤ የቡና እርሻ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሻይ ምርትም ያለበት ክልል ነው፤ እነዚህን ቡናዎች እዚሁ ተዘጋጅተውና ተቀነባብረው፣ ታሽገው ለወጣቶች ስራ ፈጥረው፣ አሁን የትራንስፖርት ማጓጓዣ መንገዱም እየተቀያየረ ስለሆነ ለዓለም ገበያ ሲሄድ ጀንፈል ወይም ቀሽር ቡና ሳይሆን የተቆላ፣ የታሸገ እንዲሆን በከፍተኛ ኃላፊነት ስሜት እንድትሰራ አደራ ማለት እፈልጋለሁ ። ምክንያቱም ያ ሲሰራ ለብዙዎች እንጀራ ይፈጥራል፣ ለብዙዎች ተስፋ ይፈጥራል ።

እሱ ብቻ ሳይሆን፣ በጀመርከው መንገድ እዚህ ቦታ ያለው የቡና ምርት በቂ አይደለም፤ በሄክታር 10 15 ኩንታል በቂ አይደለም ። እዚህ ያለው ቡና ከተቻለ በአመቱ ሁለቴ እያመረተ ምርታማነቱ 20፣ 30፣ 40 ቢሆን፣ አሁን ከምናገኘው ሃብት በተጨማሪ በርከት ያለ ሀብት እናገኛለን ማለት ነው ። ይሄን ለማድረግ ልምዱም፣ ሞያውም, አቅሙም ስላለህ፤ ይሄን አካባቢ በመቀየር ረገድ ያለህን የጎላ ሚና ለዚህ ማኅበረሰብ የማይረሳ ታሪክ ጥለህ እንድታልፍ አደራ ልልህ እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም በለመድነው መንገድ ሄደን አንቀየረውም፤ ይሄን ሃገር በለመድነው የስራ ባህል፣ በለመድነው የትርፍ ግኝት አይሆንም፣ አዳዲስ መንገዶች መከተል ያስፈልጋል ።

ጀማል ብቻህን ሳትሆን ደግሞ መሰል ሰዎች እንዳንተ ሊሰሩ፣ ሊቀይሩ የሚፈልጉ ሰዎች በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ካሉ እዚህ አርፈው አካባቢውን አይተው፣ ልክ ያንተ መሰል የካፒታል ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና እንዲሰራ የበኩልህን እንድትወጣ አደራ እያልኩኝ; ክቡሩ ፕሬዚዳንት በቴፒ አካባቢ በርከት ያሉ የግል ባለሃብቶች ሰፋፊ ቦታዎች ወስደዋል፣ ሀብት አላቸው፣ በሺህ ሄክታር ነው የወሰዱት ። እንደዚህ አይነት ነገር አምስት ስድስት በክልላችን እዚህ አካባቢ ቢኖር በጣም ጠቃሚ ነው ። በዚህ አግባብ ሁሉም ባለሃብት የጀማልን ፈለግ ተከትሎ ተጨማሪ እሴት እንዲያደርጉ፣ የሚታይና የሚጨበጥ ነገር እንዲያስቀምጡ ማድረግ ያስፈልጋል ።

በተረፈ፣ በጀማል ስር ሆናችሁ ባለፈው ስመጣ “ይሄንን ስራ በጊዜው ጨርሰን እናጠናቅቃለን” ያላችሁ ወጣቶች፣ ባላችሁት ቃል መሰረት፣ በገባችሁት ቃል መሰረት እንዲህ ያለውን ውብ ስፍራ በአካባቢ ውበት፣ በቤት ጥራት፣ በእውነት አስተማሪ የሆነ ስራ ስለሰራችሁ እናንተንም ማመስገን እፈልጋለሁ ። ይሄ ቦታ ተሰርቶ ከተውነው ያው ይበላሻል ። የሰራውን ሰውዬ ተጨማሪ ስራ፤ ስራ ልንለው የምንችለው፣ ይሄንን ተገልግለን አዋጭ መሆኑን ካመነበት ብቻ ነው ። አሁን ካለው ቁጥር 10 ጨምር፣ 20 ጨምር የምንለው እስከ አሁን መዋዕለ-ነዋይ ያፈሰሰው ውጤታማ ከሆነ ነው ።

የክልሉ አመራሮች፣የዞኑ አመራሮች፣ ልዩ ልዩ እንግዶች ሲመጡ ስብሰባዎች እያደረግን ቦታውን ማስተዋወቅ፣ ገበያው እንዲጠናከር ማድረግ፣ ጎብኚዎች መጥተው እንዲሄዱና እንዲገለገሉ ማድረግ የዚህ ሆቴል ባለቤት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁላችን ኃላፊነት መሆኑን ከግምት እናስገባ ። ይሄ በመንግሥትና በግል አጋርነት የተሰራ በጣም ድንቅ ስራ ነው ። ተጨማሪ እንደዚህ ያሉ ድንቅ ስራዎች በክልሉ በራስ-ተነሳሽነት ተሰርተው እንደምናይ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ዛሬ ጥምቀት ነው፤ ዛሬ ደንቢ ሎጅ ብስራት የተበሰረበት ቀን ነው ። ሁለቱን ድርብ በዓላት ለአማን ሚዛን፣ ለዚህ አካባቢ ሰዎች እንኳን ደስ ያላችሁ ። መጪውም ጥምቀት ብስራት እና የሰመረ ዘመን እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ቤንች ሸኮ ዞን፣ ኢትዮጵያ

የአይሻ-2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ጥር 23፣ 2018ዓ.ም

ክቡር ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦመር ጌሌ የጂቡቲ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት፣
ክቡር ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ የሶማሌ ፌዴራል ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት፣
የተከበሩ አቶ አደም ፋራህ፣
የተከበሩ አቶ ሙስጠፌ ኡመር፣
የተከበረ ወንድማችን ኑረዲን ሐጂ ኬንያን ወክሎ በመካከላችን የሚገኝ፣
የተከበሩ ውጋዛችን፣ ወጣቱ ውጋዛችን እንዲሁም በዚህ አካባቢ ያላችሁ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ የቻይና ሪፐብሊክ አምባሳደር እና የኩባንያው የሥራ ኃላፊዎች፤
ክቡራትና ክቡራን እንኳን በደህና መጣችሁ፣ እንኳን ደስ ያላችሁ።

ክቡራት እና ክቡራን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ልናረጋግጥ የምንወደው የብልጽግና ጉዞ የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ የ21ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አጠቃላይ የዓለም ኢኮኖሚ ጉዞን ከግምት ያስገባ ነው። በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ የነበረው የዓለም የእድገት ጉዞ ለምዕራቡ ያደላ ሲሆን፣ ከምዕራቡ ዓለም ውጪ የነበረው የዓለም ሕዝብ ከሞላ ጎደል በጨለማ ውስጥ የነበረ ነው ማለት ይቻላል። ያ የሆነበት ምክንያት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አጠቃላይ የዓለም መዋቅር ፣ የዓለም ተቋማት የተገነቡት በዚያ ጦርነት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸውን ሀገራት መልሶ ለመገንባት ታሳቢ ያደረገ ስለነበረ፣ የተቀረው ዓለም የበታች ነው ማለት ይቻላል። በዚያ ምክንያት እምብዛም እድገት የታየበት አልነበረም።

21ኛው ክፍለ ዘመን ግን አዲስ ምልከታ፣ አዲስ እይታ እና አዲስ የዓለም እድገትን ይዞልን መጥቷል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው የሩብ ምዕተ-ዓመት ወይም የመጀመሪያው 25 ዓመታት የምዕራቡ ዓለም እድገት የመጨረሻ ጣሪያ የደረሰበት መሆኑን በገሃድ አሳይቷል። ሁለተኛው የሩብ ምዕተ-ዓመት የኤዢያ ሀገራት ወደ ከፍተኛ የእድገት ማማ የሚደርሱበት ጊዜ እንደሆነ ያመላክታል። ሶስተኛው እና አራተኛው የሩብ ምዕተ-ዓመት የአፍሪካ ዘመን የመሆን እድሉ በጣም ከፍተኛ ነው።

ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ከ25 ዓመት በኋላ በዓለም ላይ ካሉ አራት ሰዎች አንዱ አፍሪካዊ ከመሆኑም ባሻገር፣ በአፍሪካ ውስጥ ያለው ወጣት ትውልድ አሁን ያለውን

የዲጂታል ዓለም በትክክል አንብቦ መጠቀም ከቻለ፣ ለመስራት፣ ለመፍጠር፣ ለመስፋት እድል ያለው ወጣት ኃይል የሚኖረው በአፍሪካ ነው። በዚህ ምክንያት በሁለተኛው የሩብ ምዕተ-ዓመት የሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ጥሩ ዝግጅት ያደረጉ፣ መሰረት የጣሉ የአፍሪካ ሀገራት በሶስተኛው እና በአራተኛው የሩብ ምዕተ-ዓመት በዓለም ከፍተኛ እድገት ካላቸው ሀገራት ተርታ የመቀላቀል እድላቸው በእጅጉ የሰፋ ነው።

ይህ እድል በልጆቻችን መታየት እንዲችል የእድገት መሰረቶች ለይተን እነዛ ላይ ማተኮር ይገባናል። አንደኛው በህጻናት ላይ ያተኮረ ትምህርት ነው። በህጻናት ላይ ያተኮረ ትምህርት እነሱን ለነገ ስለሚያዘጋጅ፣ ሁለተኛው መሠረተ-ልማት ነው። መሠረተ-ልማት ሲባል መንገድ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ መብራት ያካትታል። በተለይ በተለይ የመብራት እድገት በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ እድገት ያረጋገጡ ሀገራት ምንም እንኳን ኢኮኖሚያዊ እድገት ያረጋገጡ ቢሆንም፣ በነበረው የኃይል አመራረት ችግር ምክንያት በተፈጥሮ እና በዓለም ላይ ጥቁር ጠባሳ የጣለ እድገት ነበር። በአንድ በኩል የዓለምን ከባቢ የጎዳ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እድገት ያረጋገጠ ጉዞ ነበር።

እኛ በ21ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እና ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ፣ አፍሪካ ውስጥ እድገት እንዲመጣ የምናስበው ተፈጥሮን በሚጎዳ መልክ ሳይሆን፣ ከተፈጥሮ ጋር በስምምነት፣ ተፈጥሮን ሳንነካ የሚረጋገጥ እድገት ለማምጣት ነው። ለዚያ ሁነኛው መድኃኒት ደግሞ ንጹሕ ኃይል ላይ ማተኮር ነው። ኢትዮጵያ በድፍን አፍሪካ እንደሚታወቀው ካላት የኃይል ምንጮች ከሞላ ጎደል ከንጹሕ ኃይል የሚመነጩ ናቸው።

ለዚህም አንዱ ማሳያው የአፍሪካ ግርማ ሞገስ፣ የአፍሪካ የመቻል ማሳያ፣ የአፍሪካ ሕዝቦች ከፈለጉና ከወደዱ እንዲሁም ከተደመሩ አንጋፋ ሥራ ጀምረው ሊጨርሱ እንደሚችሉ ያሳየው፣ በኢትዮጵያውያን ታስቦ በኢትዮጵያን ሀብት ብቻ የተገነባው የሕዳሴ ግድብ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ኩራት፣ ለመላው አፍሪካ ደግሞ የምሳሌነት ምልክት ነው። በሕዳሴ ግድብ በውኃ ኃይል ከውኃ የምናመርተው ኃይል፣ ንጹሕ ኃይል ነው። ቅድም እንደተገለጸው በርካታ ቦታ፣ ከንፋስ፣ በውስን ቦታ በጂኦተርማል ሌላም ግድቦች እየገነባን ስለሆነ፣ ኢትዮጵያ የሚቀጥለውን የአፍሪካን ዘመን ዕድገት ለማረጋገጥ የሚጣለው መሠረት ከሞላ ጎደል በንጹሕ ኃይል ላይ ያተኮረ መሆን አለበት ብላ ታምናለች።

በዚሁም ምክንያት የተነሳ አይሻ ላይ እንደምታዩት በዚህ ክልል ኃይል የማምረት ጅማሮ 2017 የተጀመረ ቢሆንም፣ በኮቪድ እና በፋይናንስ እጥረት ዘግይቶ ባለፉት አንድ ዓመት ተኩል ወይ ሁለት ዓመት ቢበዛ ይህ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ምዕራፍ መጠናቀቅ

ችሏል። ለዚህም የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለሥልጣን የቦርድ አባላት፣ የሠራውን ኩባንያ፣ በጥቅሉ የክልሉን ማኅበረሰብ ማመስገን እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ ዕድገት ፣ የኢትዮጵያ ኃይል ከአካባቢ ሀገራት ትስስር ውጪ ለብቻ በማደግ የሚረጋገጥ አይሆንም። የ21ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ለመላው አፍሪካ የመጣ የብስራት ስለሆነ፣ እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ የጀመርነው ዕድገት ጎረቤት ወንድም ሀገራትን የሚነካና አስተሳስሮ እንድናድግ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል።

የኤሌክትሪክ ትስስር በእኛና በጂቡቲ መካከል፣ የንጹሕ ውኃ ትስስር በእኛና በጂቡቲ መካከል፣ በከፍያ የሚደረግ የከፍያ መንገድ በእኛና በጂቡቲ መካከል፣ በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ይገኛል። ሁላችሁም እንደምታውቁት ጂቡቲ በእጅጉ ለልባችን ለኪሳችን የቀረበ ሀገር በመሆኑ አብዛኛው መዋዕለ-ነዋይ ከጂቡቲ ጋር የተሳሰረ ነው። በባቡር መስመር ፣ በዋና የፍጥነት መንገድ , በኤሌክትሪክ፣ በውኃ ፣ በአየር፣ በዲፕሎማሲ ከዚያም በተጨማሪ እንደ አንድ ቤተሰብ የመታየት ከፍተኛ ጠንካራ የሆነ ዝምድና ያለው ሀገር ነው ጂቡቲ። ፕሬዚዳንቱ ይህንን ለማረጋገጥ በመካከላችን ተገኝተዋል፣ እሳቸውንም እጅግ አድርገን እናመሰግናለን። ከሱዳን፣ ከኬንያ፣ ከታንዛኒያ ጋር እነዚህን ነገሮች የምንጋራ ሲሆን፣ በቅርቡ ከሶማሊያ እና ደቡብ ሱዳን ጋር በመንገድና በመብራት ለመተሳሰር ጥረት ተጀምሯል። ይህ ጥረት እንዲሳካ በኢትዮጵያ በኩልም፣ በሶማሊያ በኩልም እንዲሁም በደቡብ ሱዳን በኩል በከፍተኛ ቅንጅት የሚሠራ ይሆናል።

ምክንያቱም ኢትዮጵያ ያላት የተፈጥሮ ጸጋ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ተካፍላ የምትበላ ከሆነ፣ ጎረቤቶቿም እንደዚሁ ያላቸውን ጸጋ ከእኛ ጋር የሚካፈሉ ከሆነ፣ ምስራቅ አፍሪካ፣ አፍሪካ የሚለምን ሳይሆን የሚረዳ፣ የሚበደር ሳይሆን የሚያበድር፣ ከሌሎች የሚጠብቅ ሳይሆን የሚጠበቅበት ከባቢ የመሆን ዕድሉ በጣም በጣም ሰፊ ነው። እጅግ ሀብታም፣ ትልቅ የሕዝብ ቁጥር ፣ ትልቅ ገበያ፣ በወጣት የተሞላ ትውልድ ያለበት ከባቢ ስለሆነ፤ በትብብር አብሮ የመሥራትን ፣ ከልማት የመቋደስን፣ በጋራ የማደግን፣ አንዱ ከሌላው የመማርን ልምምድ እያሳደግን ከሄድን ምንም ጥርጥር የለውም የሀያ አንደኛው ኢጋማሽ የአፍሪካ ዘመን ይሆናል። ያ የአፍሪካ ዘመን ማሳያ ፈር ቀዳጅ ምሳሌዋ ደግሞ ኢትዮጵያ ትሆናለች። ይህንን ለማረጋገጥ ዘርፈ-ብዙ የልማት ሥራዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እየተከናወኑ ይገኛሉ። በከተማ ልማት ቅድም በጅጅጋ እንዳየነው፣ በድሬዳዋ፣ በሐረር፣ በባሕር ዳር ፣ በጎንደር, በደሴ፣ በጅማ፣ በሐዋሳ ፣ በአርባ ምንጭ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ፣ በነቀምት፣ በሮቤ በብዙ ከተሞች ከተማን እያለማን ነው። የዚያው ዋነኛው ምክንያት የእድገት ማሳያው አንዱ ከተሜነት እና ማኅበረሰብን ከገጠር ወደ ከተማ ማስገባት ስለሆነ፤ ዜጎቻችንን ከተሜ ለማድረግ ባለን መሻት ከተሞቻችንን ማዘመን፣ ደረጃን ማስተካከል ቅድሚያ የተሰጠው

ሥራ ነው። ከከተሞች በተጨማሪ በግብርናው ዘርፍ በዚህ ዓመት 1.3 ቢሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት አቅደን፣ ባለፉት ስድስት ወራት 999 ሚሊዮን ኩንታል ወይም 78 በመቶ ከዓመቱ እቅድ በስድስት ወር ብቻ ማሳካት ተችሏል።

በግብርናው፣ በከተማው፣ በማዕድን, በኢንዱስትሪ, በቱሪዝም ከምናመጣቸው ውጤቶች በተጨማሪ በዋና ዋና ዘርፍ በምናደርገው መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ መሠረተ-ልማት እንገነባለን። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የንጹሕ ኃይል ነው። ዛሬ በአይሻ ያስመረቅነውን በቅርቡ በሌሎች አካባቢዎች እንዲሁ እያስመረቅን እንቀጥላለን፤ እንዲሁም የኮይሻ ፕሮጀክት ከአንድ ዓመት፣ አንድ ዓመት ተኩል በኋላ የሚጠናቀቅ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ የንጹሕ ኃይል ኢንቨስትመንት በዓለም ደረጃ ለኢትዮጵያ ዕውቅና ያሰጠ መሆኑ፣ ኮፕ ኮፕ32 ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በኢትዮጵያ ምድር እንዲዘጋጅ የተወሰነበት ዋነኛው ምክንያት፤ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ፣ ወንዞቿን በማጽዳት፣ በንጹሕ ኃይል ፣ አጠቃላይ በምትከተለው ፖሊሲና ባስገኘችው ውጤት ዓለም ሥራዋን ዕውቅና ለመስጠት፣ ዓለም ሥራዋን ለማበረታታት ኮፕ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ወስኗል። ይህን ውሳኔ አድንቀን አክብረን የተቀበልን ሲሆን፣ ከአፍሪካ ወንድሞቻችን ጋር በመሆን በዓለም ላይ ለረዥም ጊዜ ከሚጠቀሱ የኮፕ ጉባኤዎች አንዱ የሆነውን ጉባኤ በ2027 በኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያውያንንም በሚያኮራ፣ አፍሪካውያንንም በሚያኮራ፣ በተለይ በተለይ ጂቡቲን፣ ሶማሊያን፣ ኬንያን፣ ደቡብ ሱዳንን በሚያኮራ መንገድ የምናዘጋጅ መሆኑን፣ ያከበሩንን በማያሳፍር መንገድ የምንፈጽም መሆኑን እያረጋገጥኩ፤ እንደዚህ እንደዚህ ያለው ድል እንዲበረታ፣ እንደዚህ ያለው ውጤት እንዲጠናከር በድል እርካታ ሳይፈጠር በትጋት በትብብር አብረን እንድንሠራ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ጥሩ ጅማሮ ነው ያለው፤ በርትተን ውጤት እንድናስገኝ፣ በርትተን ሀገራችንን የብልጽግና ማማ ላይ እንድናስቀምጥ፣ በርትተን አፍሪካን በአድዋ ነፃነት ለብዙዎች አርአያ እንደሆንን፣ ለብልጽግና ዳግም አርአያ ለመሆን የበኩላችንን ሚና እንድንወጣ በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ። በዚህ ሥራ የተሳተፋችሁ በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ፤ ክቡር ኢስማኤል አመር ጌሌ የጂቡቲ ፕሬዚዳንት የሁላችን አባት፣ ወንድማችን ሐሰን ሼክ ተገኝታችሁ የዚህ ደስታ ተካፋይ በመሆናችሁ ያለኝን ምስጋና እየገለጽኩ፤ ይህ ፕሮጀክት የጋራ ፕሮጀክት ነው፤ ማስመረቅ ብቻ ሳይሆን ከኃይሉም በጋራ የምንጠቀም መሆኑን ልገልጽ እፈልጋለሁ!

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ሶማሌ ክልል



የሸበሌ ሪዞርት ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ጥር 23፣ 2018ዓ.ም

ሙዳኔ ኢስማኤል ኡመር ጊሌ፣
ሙዳኔ ሃሰን ሼህ ሞሃመድ፣
ሙዳኔ ሞሃመድ ሃጅ አወር ወንድማችን ከኬንያ ፣
ሙዳኔ አደም ፋራህ፣
ሙዳኔ ሙስጠፌ ሞሃመድ፣
ሙዳኔ ሳላህ፣
ኤክሰለንሲስ ሱ ዶዋዳ፤
ሸበሌ ስለሰበሰበን ሃምበልዮ ሃምበልዮ፤
በቅድሚያ ክቡር ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦመር ጊሌ በሶማሌ ክልል በገበታ ለትውልድ የተሠራ አዲስ ፕሮጀክት አለ ሲባል “ከእናንተ ጋር ሆኜ የሶማሌን ሕዝብ፣ ሕዝቤን ማየት ሰላም ማለት እፈልጋለሁ” ብለው ከ50 ዓመት በኋላ ወደ ጅጅጋ ስለመጡ፣ በራሴና በክልላችን ሕዝብ ስም እንኳን ደህና መጡ፣ እንኳን ወደ ቤትዎ በሰላም ተመለሱ ማለት እፈልጋለሁ። ሃሰን ሼክ ከ10፣ 11 ዓመት በኋላ ጅግጅጋ ተመልሶ መጥቷል፤ የመምጣቱ፣ የመመለሱ ዋናው ምክንያት ሱማሌዎች በኬንያም፣ በጂቡቲም፣ በኢትዮጵያም በተለያየ ሀገር ያለን ሰብሰብ ብለን ስለ አንድነት፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ ሰላም የምንመክርበት በቤታችሁ ስለመጣችሁ፤ ወንድማችን ኑረዲን በኬንያ ያሉ ወንድሞቻችንን በመወከልና ዊሊያም ሩቶን በመወከል እኛ ጋር ተገኝተዋል። ስለመጡ እንግዶች ሁሉ ምክንያት የሆነው በሶማሌ ክልል የተሠራው ይህ ፕሮጀክት ነውና፤ ፕሮጀክት፣ ልማት፣ ሰላም የሚያሰባስብ ስለሆነ፣ ሰላማችን ከቀጠለ ከዚህ ቀጣና በላይ ብዙዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዕድል ስለሚፈጥር፣ ስለተፈጠረው ሰላምና ልማት የክልሉን አመራር እያደነቅኩ ስለመጡ እንግዶቻችን ደግሞ እንኳን በደህና ወደ ሀገራችሁ መጣችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ከዚህ ቀደም የሶማሌ ክልል የሚታወቀው በግጭት፣ በጦርነት ሲሆን፤ አመራሮች ወደዚህ አካባቢ የሚመጡት ለማስታረቅና ሰላም ለማስከበር ነበር። ዛሬ ግን ሁላችሁም እንዳያችሁት ሰላም ወዳዱ የሶማሌ ሕዝብ በክልሉ የተጀመሩ ሰፋፊ የመሠረተ-ልማት ሥራዎች፤ በሺህ ኪሎ ሜትር የሚቆጠሩ መንገዶች፣ የቤት ግንባታዎች፣ በቅርብ ያስጀመርነው የጋዝና የነዳጅ ማጣሪያ፣ የማዳበሪያ ፕሮጀክት፣ የኤርፖርት ማስፋፊያ ፕሮጀክት፣ አሁን ደግሞ የሸበሌ ሪዞርት በስፋት የሚሠራበት ፣ የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ያለበት ክልል ሆኖ፤ ወጣቶች በታላቅ ተስፋ መሪዎቻቸውን በደስታ ሲቀበሉ፣ ሰላም እንደ ዝናብ በሶማሌ ምድር ሲዘንብ ያየንበት ዕለት ስለሆነ ይህንን አቅልለን

አንወስደውም፤ ታላቅ ድል፣ ታላቅ ሥራ ነው። የዚህ ክልል አመራሮች ለዚህ ሁሉ ስኬት ስላበቃችሁ፣ ሶማሌን ከግጭት፣ ሶማሌን ከጦርነት ወደ ልማት ስለመለሳችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ሸበሌ እንዳያችሁት ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ክልል ልማት ማምጣት እንደሚቻል፣ እንደዚህ ያለውን ሰፊ ሥራ ስንሠራ የቤቱ ግንባታ የከባቢውን ባህል፣ የከባቢውን የቤት አሠራር የተከተለ፤ ዝም ብሎ ሌጣ ፕሮጀክት ደግሞ ሳይሆን፣ በጣም በስፋት እንደዚህ ያሉ አረንጓዴ ቦታዎች የተፈጠሩበት፣ በሺህ የሚቆጠሩ ዛፎችና የፍራፍሬ ተክሎች የተተከሉበት፤ አብርሃም በላይ በወንጪ ያሳየውን ብቃት በሸበሌ የደገመበት፤ አብርሃም በላይ ከትግራይ ተወልዶ ኦሮሚያንና ሱማሌን እየዞረ ለማልማት ዕድል ያገኘበት፤ በኦሮሚያም በሶማሌም ማንም ሰው ልማት፣ ሰላም፣ ፍቅር ይዞ እስከመጣ ድረስ እንደ ልጅ የመቀበል ባህል መኖሩን በድጋሚ ያረጋገጥንበት፤ ሶማሌዎች የጂቡቲ ወንድሞቻቸውን፣ የኬንያ ወንድሞቻቸውን፣ የሱማሊያ ወንድሞቻቸውን ብቻ ሳይሆን፣ የሰላም ባንዲራ፣ የፍቅር ባንዲራ፣ የልማት ባንዲራ ከያዘ ከየትኛውም ጫፍ ዘር ሳይለዩ፣ እምነት ሳይለዩ መቀበል እንደሚችሉ አብርሃም በላይ ማሳያ ነው።

በሶማሌ ክልል በጅጅጋ ከተማ በኮሪደር ልማት ፕሮጀክት፣ ጅጅጋ በምስራቁ የኢትዮጵያ ቀጣና፣ በምስራቁ የአፍሪካ ቀጣና አንድ ፈርጥ ሆና እየወጣች እንዳለች የሚያሳይ ነው። በተለይ በጅጅጋ አካባቢ ሁሌም የሚያስደንቀኝ፣ ዛሬም በጣም የተደመምኩበት ጉዳይ፤ እያንዳንዱ ዜጋ ለራሱ መኖሪያ የሚገነባው ቤት ለአንድ ሳምንት፣ ለአንድ ወር፣ ለስድስት ወር መቆያ ሳይሆን ለልጆቹ ለማውረስ እያሰበ አጽድቶ፣ አትልቆ፣ አሳምሮ የመሥራት የሶማሌ ክልል ባህል መላው ኢትዮጵያን እንዲወርስ፣ መላው ኢትዮጵያን ልምድ ከዚህ እንዲወስድ፣ እንደዚህ ያለው የጸዳ ለልጆች የሚሸጋገር የቤት ግንባታ ልምምድ እና ባህል መስፋት እንዳለበት በድጋሚ እኔና የጎረቤት ሀገራት መሪዎች ዛሬ ስንመጣ አይተን የተደሰትንበት፣ የተደነቅንበት ትልቅ ሥራ ስለሆነ፤ የሶማሌ ክልል ነዋሪዎች በሙሉ ይህንን መልካም ልምዳችሁን ወደ ሁሉም ክልሎች እና ጎረቤት አገሮች እንድታስፋፉ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ዛሬ የደስታ ቀን ነው፤ ዛሬ የፍቅር ቀን ነው፤ ዛሬ የድል ቀን ነው፤ ለሐጅ ሙስጠፋ ያለኝ መልእክት የተሠራው ሥራ አስደናቂ ነው። በከተማም በገጠርም ይህ አመራር የሠራው ሥራ የሶማሌ ሕዝብ ቀና ብሎ እንዲሄድ፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ ብቻ ሳይሆን የኬንያ ሶማሌም፣ የሞቃድሾ ሶማሌም፣ የጂቡቲ ሶማሌም ኮራ ብሎ እንዲሄድ፤ ሶማሌዎች ከለመድነው የኑሮ ዘዬ በተጨማሪ ከተማ መሥራት ልማት መሥራት እንደምንችል ያሳየ

ሥራ ስለሆነ፤ ለዚህ ታላቅ አርአያ መሆን፣ መብቃት፣ መታደል ስለሆነ ያለኝ መልእክት ሁለት ነው፤ ሐጂ ሙስጠፌ ባለፉት ዓመታት የሶማሌ ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእርስዎ የሚጠብቀውን፣ ከእርስዎ ካቢኔ የሚጠብቀውን 2 በመቶ በተግባር ስላከናወኑ በጣም እያመሰገንኩ፤ በሚቀጥለው ዘመን የቀረውን 90 በመቶ በመልፋት፣ በመትጋት ጅጅጋን አሁን ካለበት አሥር እጥፍ፣ አሁን ያለው ልማት በ10 በ20 እጥፍ አድጎ ለምስራቅ አፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ኩራት የሆነ፣ ብዙዎች መጥተው የሚያዩት ሥራ እንዲሆን፤ በትንሽ ሥራ እንዳንረካ፣ በትንሽ ሥራ እንዳንቆም፣ ሩጫችን የሕዝባችንን ኑሮ እስኪቀይር ድረስ እንዳይቆም አደራ እያልኩ፤ ባየነው ሥራ ሁሉ ግን በጣም ከፍተኛ አድናቆት የተሰማን ስለሆነ እርስዎን እና አመራሩን እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

እንዲሁም አብርሃም በላይ፣ መንግሥታችን ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ያሉ ጭንቅላት ያላቸው፣ ልብ ያላቸው፣ እጅ እና እግራቸውን ተጠቅመው አገራቸውን የሚያለሙ ሰዎች በሚጠቀምበት መርህ፣ በየሄድክበት ጀምረህ ስለምትጨርስ፣ በየሄድክበት ከሕዝብ ጋር ተስማምተህ የሕዝብን ችግር ተረድተህ ለመፍታት በምታደርገው ጥረት በራሴ እና በመንግሥታችን ስም ከፍ ያለ ምስጋና ላቀርብልህ እፈልጋለሁ።

እንኳን ደስ ያላችሁ በሁሉም በከባቢ ሃገራት የምትገኙ የሶማሌ ልጆች በሶማሊያ፣ በጅቡቲ፣ በኬንያ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በታንዛኒያ ያላችሁ የሶማሌ ተወላጆች ጅጅጋ እናንተን ለመቀበል እናንተን ለማስተናገድ ከምን ጊዜውም በላይ ዝግጁ ስለሆነች በመመላለስ እንድትጎበኙን፤ በመመላለስ እንድታለሙን፤ በመመላለስ እንድታስተምሩን፤ ደግሞም እንድትማሩብን ተጋብዛችኋል እና ከዛሬ ጀምሮ ሸበሌ የእናንተ ነው እየመጣችሁ እንድትዝናኑ እጋብዛችኋለው።

ጅጅጋ፣ ሶማሌ

የብላቴ ወንዝ ሰፋፊ የፍራፍሬ ልማቶች ጉብኝት

የካቲት 15፣ 2018 **ዓ.ም**

ትናንት ማታ በሐዋሳ ከተማ የሚሠራውን የኮሪደር ልማት ለማየት ዕድል አግኝተን ነበር። ሐዋሳ አፈጣጠሯ በጣም ውብ ነው። ሰዎቹ ውበትን መሥራት ፣ ውበትን መልሶ መጠበቅ የሚችሉ ናቸው። ሐዋሳ ላይ ያየነው አስደማሚ ውበት ተጠናክሮ ከቀጠለና ከሰፋ፣ ምን ያህል የቱሪስት መስህብ መሆን እንደሚችል የሚያመላክት ነው። በሐዋሳ ከተማ አዲሱ ከንቲባ ከከተማው ነዋሪዎች ጋር በመተባበር፣ የክልሉ መንግሥት አጠቃላይ በሚያደርገው ድጋፍ ከተማዋን መልሶ አስውቦ የመሥራት ተግባር በጣም ተስፋ ሰጪ ጅማሮ አይተናል።

በሐዋሳ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየተመረቱ ያሉ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ምርቶች፣ በሚቀጥለው ዓመት ከግማሽ ቢሊዮን ዶላር በላይ ከሐዋሳ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ብቻ ወደ ውጭ እንልካለን ። ኢንዱስትሪውና ከተማው እያደጉ መጥተው የአገልግሎት ዘርፉን በሚስቡበት ሰዓት፣ በተለይ ከአዲስ አበባ እስከ ሐዋሳ ያለው የፍጥነት መንገድ በዚህ ዓመት የተጠናቀቀ ስለሆነ፤ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ከሐዋሳ ወደ አዲስ አበባ ቢበዛ ሁለት ሰዓት ነው የሚወስደው፤ ያንን ተጉዞ ሥራ ለመሥራትና ለመዝናናት በእጅጉ የሚያግዝ ነው።

ከከተማውና ከኢንዱስትሪው ሲወጣ ደግሞ፣ ይህ ብላቴ አካባቢ ነው፤ እንደምታውቁት የዛሬ ሁለት ዓመት፣ ሦስት ዓመት ገደማ መጥተን ነበር። ብላቴው በረኃ ነው። ምንም ዓይነት ምርት የሚሰጥ አካባቢ አልነበረም። አሁን ግን እንደምታዩት ብርቱካኑ፣ ሎሚው፣ ሙዙ፣ ሽንኮራ አገዳው፣ ፓፓያው፣ አቮካዶው በጣም ብዙ ፍራፍሬ ይመረቱበታል።

ለ100 ሄክታሮች በመስኖ እየታረሰ ነው ያለው። ለገበያ የሚውሉ በጣም ከፍተኛ የሆነ ምርት እየወጣ ነው ያለው። መጥቼ ነበር ከጥቂት ጊዜ በፊት፤ እንደዚህ ዓይነት ቦታ አልነበረም፣ አሁን ሙሉ በሙሉ ጫካ መስሏል። የሙዙ ጣዕም፣ የአቮካዶው ጣዕምና መጠን ፣ የሐብሐቡ መጠን ሲታይ፤ ይህ በረኃ የሰው ልጅ በርትቶ ከሠራ ምን ሊያመጣ እንደሚችል ያመላክታል።

ከሲዳማ ክልል ፕሬዚዳንት ጋር ስንነጋገር፣ በዚህ ዓመት ወደ 15 ሚሊዮን ዶሮ ሲዳማ ብቻ እያመረተ ነው ያለው። የዛሬ ሦስት ዓመት ስንመጣ ሦስት ሚሊዮን ገደማ፣ አራት ሚሊዮን ገደማ የነበረው በብዙ እጥፍ አድጓል። በዚህ የጓሮ ሌማት እየተስፋፋ ነው

ያለው፤ ፍራፍሬ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነው ያለው፤ ከተማ እየተለወጠ ነው ያለው፤ ኢንዱስትሪ ብቻ ሳይሆን ወደ ውጭ የመላክ አቅም እያደገ ነው ያለው። ይህ ሁሉ ሲደመር፣ ኢትዮጵያን ከነበረችበት የልመናና የድህነት ታሪክ አስቀርተን ብልጽግናን ለማረጋገጥ፣ ያንን የሚጠብቁ ተቋማት ለመገንባት፤ ቅድም እንዳየነው የልዩ የጦር ኃይል አባላት በጣም አስደማሚ ብቃት አሳይቷል። ተቋም እንገነባለን፤ እርሻችንን በብርታት፣ በብዙ ጥረት እናዘምናለን፣ እንሠራለን ፤ ከተሞቻችንን እናሳድጋለን፤ ኢንዱስትሪዎቻችን ለአላማቸው የሚበቁ እና ወደ ውጭ ልከው ገቢ የሚያመጡ እናደርጋቸዋለን፤

በዚህ ሁሉ ትስስር ውስጥ በአጭር ጊዜ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚያግዝ ይሆናል። እንግዲህ አሁን በሁሉም መስክ አስተማማኝ ጅማሮዎች አሉ፤ ይህ እርሻ እንደምታዩት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ነው የጀመርነው፣ በጣም ተስፋ ሰጪ ነው ግን መስፋት አለበት። ድፍን ደቡብን ማጥለቅለቅ አለብን በዚህ መንገድ፤ ያ ደግሞ ሥራ ይፈልጋል።

ሀዋሳ ከተማ ያየነው ብርሃን በጣም ደስ ይላል ግን ሙሉ ሀዋሳን ወደዛ መቀየር አለብን፤ ኢንዱስትሪው ወደ ውጭ በመላክ በተለይ በፀሐይ ብርሃን ኃይል ሰሌዳ ወደ ውጭ በመላክ ወደ ሶስት ኩባንያዎች ናቸው ሀዋሳ ላይ እየሰሩ ያሉት፤ ጅማሮ ነው ማስፋት እና ወደ ውጭ የመላክ አቅማችን ማደግ አለበት።

በመሠረተ-ልማት ሀዋሳን ከአዲስ አበባ የሚያገናኘው መንገድ የፍጥነት መንገድ አልቆ ፍራፍሬ የሚመላለስበት፣ ቱሪስት የሚመላለስበት፣ የኢንዱስትሪ ምርት የሚመላለሱበት፣ ብዙ ሃብት የሚንቀሳቀስበት መሆን አለበት፤ ከሀዋሳ እስከ ሞጆ ያለው ግራና ቀኝ እንደምታውቁት ለፍራፍሬ ምቹ ነው፣ ለምርት ምቹ አካባቢ ነው፣ ወደ ምርት መቀየር አለበት።

ግብርናችንም በዕውቀት በትጋት ከሰራን፣ ኢንዱስትሪ በዕውቀት ገበያ ተኮር አድርገን ከሰራን፣ ከተሞቻችንን ካዘመን፣ መሠረተ-ልማት ከገነባን፣ እነሱን የሚጠብቅ ደግሞ ጠንካራ ተቋም ሰራዊት ከገነባን የኢትዮጵያ ህልውና ነጻ፣ ሰላማዊ የመሆን አቅሟ እያደገ የሚሄድ ይሆናል፤ እና በሁሉም መስክ ነው መለፋት ያለበት። ዘርፈ-ብዙ ያልንበት ዋናው ምክንያት በአንድ መስክ ያለ ስኬት፣ በአንድ መስክ ያለ ውጤት ሁሉን ችግር አይፈታም፡ ፡ በግብርናውም፣ በኢንዱስትሪውም፣ በከተማውም፣ በሌማቱም፣ በገጠር ኮሪደሩም የጀመርናቸው ስራዎች ሲሰናሰሉና ሲተሳሰሩ የምናስባትን ኢትዮጵያ ለመስጠት በእጅጉ የሚያግዝ ነው።

ዛሬ ያየሁት ስራ በጣም ደስ ይላል፤ ይሄን የሰሩ የግሉ ዘርፍ ሰዎች ሊመሰገኑ ይገባል። ማህበረሰቡ ይሄንን ጠብቆ፣ አስፍቶ ኢትዮጵያን የምግብ ቅርጫት የማድረጉን ትልም ለማሳካት አሁንም ይበልጥ መረባረብ፣ መስራት፣ መለፋት አለብን እላለሁ፤ በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍኩት።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ብላቴ



የመከላከያ ሠራዊት የልዩ ዘመቻዎች ዕዝ 65ኛ ዓመት የምስረታ በዓል

የካቲት 15፣ 2018 **ዓ.ም**

አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣
የክልላችን ርዕሰ መስተዳድር ደስታ፣
ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣
ጀነራል አበባው ታደሰ፣ የውቢቷ ከተማ ሀዋሳ ከንቲባ ጥራቱ በየነ፣ ጀነራል መኮንኖች፣ የልዩ ኃይል የአየር ወለድ ምሩቃን እና አባላት፣ የሀዋሳ ከተማ ነዋሪዎች፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ታሪክ ከማይዘነጋው የመለዮ ለባሽ የአዲስ ምሩቃን፣ በተለይም በርከት ያሉ ሴት አየር ወለዶች የተመረቁበትን በዓል በጋራ በሀዋሳ ከተማ ለማክበር በመገናኘታችን የተሰማኝን ታላቅ ደስታ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ሀዋሳ የኢትዮጵያ ሁነኛ ራዕዮች የሚበሰሩበት፣ ቁጤላ በውስጥ የሸሸግነውን፣ በቤት የመከርነውን፣ በዝማሬ የምንገልጥበት፤ ይህ ቦታ በተደጋጋሚ ያለምነውን የተናገርንበት፣ ስናሳካም በጋራ ድል ያበሰርንበት ቦታ ስለሆነ ለመላው የሲዳማ ህዝብ፣ በተለይም ይህንን ቁጤላን በውብ መንገድ ላቆዩልን አባቶች የተከበረ ምስጋናዬን ላቀርብ እፈልጋለሁ። የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ በዚህ ቦታ “አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን” ባልነው መሰረት፣ ባለፉት አምስት ዓመታት አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በርካታ ከተሞች አበባ ሆነው፣ ሀዋሳ ደግሞ ብርሃን ሆና ስላየናት የተሰማንን ከፍተኛ ደስታ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሀዋሳ ተሞሽራለች፤ “ቅዳሜ እና እሁድ ምን ታደርጋላችሁ? ኑ እናስተናግዳችሁ” እያለች ስለሆነ፣ በአዲስ አበባ ያላችሁ ሰዎች የሀዋሳን ብርሃን፣ የህዝቡን ፍቅር እንዲሁም ታሪካዊ ማንነቱን በቅዳሜ እና እሁድ እየመጣችሁ እንድትጋሩ፣ የእኛን ደስታ እንድትካፈሉ ከሀዋሳ ግብዣ አቀርብላችኋለሁ ።

የሰው ልጅ ከእናት እና ከአባቱ ደም ዘር ተጋርቶ ይወለዳል። የሰው ልጅ ከሀገሩ ባህል፣ ቋንቋ፣ ማንነት ተጋርቶ ይወለዳል። የዛሬ አየር ወለዶች ደግሞ ከእናት ከአባታቸው፣ ከድንቂቷ ኢትዮጵያ ሀገራቸው እንዲሁም ከአየር የተወለዱ የኢትዮጵያ ልዩ ስጦታዎች ናቸው። ቀይ በርኔጣ የለበሱ፣ ከአየር ተምዘግዝገው የሚወርዱ ባለ ሁለት ክንፍ፣ ልዩ ተምዘግዛጊ አየር ወለዶች በአንደኛው ክንፍ አላማ፣ በሌላኛው ክንፍ ስነ-ስርዓት አንግበው

ከአየር የሚወርዱ፤ ውኂያ የሚያስቀሩ፣ ውኂያ የሚጨርሱ፣ የአፍሪካ የነጻነት ቀን ድል የሆነውን አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ ሰንደቃችንን በድል የሚያውለበልቡ ጀግኖች ስለሆኑ የሚገባቸውን ክብር እንደ ሀገር በጋራ እንድንሰጣቸው በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።
የእኛ ተልዕኮ ራዕይ ያለው፣ ለትውልድ የሚሸጋገር ሁነኛ ተቋም መፍጠር ነው። የእኛ ተልዕኮ ውኂያ የሚያስቀር፣ ውኂያ የሚጨርስ የልዩ ጦር ኃይል መገንባት ነው። የእናንተ ተልዕኮ ኢትዮጵያን መገንባት፣ ኢትዮጵያን መጠበቅ፣ ኢትዮጵያን ማጽናት እና ኢትዮጵያን ማሸጋገር ነው። ኢትዮጵያ በልጆቿ ላብ ትሰራለች። ኢትዮጵያ በልጆቿ አጥንት እና ደም ትጸናለች። ኢትዮጵያ አልተደፈረችም፣ አትደፈርም፤ በክብርና በነጻነት ለልጆቻችን የምናሸጋገራት፣ ብቸኛዋ የአፍሪካ ፈርጥ ሆና ትቀጥላለች።

የእኛ ዝግጅት በድፍን አፍሪካ ሰላም ለማረጋገጥ፣ በድፍን አፍሪካ ብልጽግናን ለማረጋገጥ፣ በቀጣናችን ላሉ ሀገራትአለኝታ፣ መከታ፣ ጋሻ ለመሆን ነው። ለዚህም ሲባል በምድር፣ በተራራ፣ በጅረት የነበረውን ስልጠና ዛሬ ወደ ባህር ያሸጋገርነው፤ ከውሃ የመራቅ፣ ከውሃ የመሸሽ፣ ውሃን እንደ ባዕድ ነገር የማየት ክፉ ልማዳችን አሁን ባለው የልማት እሳቤ በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በሰው-ሰራሽ አስተውሎት፣ ግድቦች በመገንባት “ውሃ ህይወት፣ ውሃ ልማት” መሆኑን ማረጋገጥ መጀመራችን ይታወቃል። በዚህ ብቻ ሳይጠናቀቅ ከሱማሌ ጫፍ እስከ ምጽዋ ጫፍ በባህር የሚያጋጥሙ ሽብሮችን ወንድም ህዝቦችን ደግፈን ሽብርን ለማስቀረትና ልማት፣ ብልጽግናን በቀጣናችን ለማረጋገጥ፤ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናው በቂ የሆነ፣ የልዩ ጦር ኃይል ቴክኖሎጂ የታጠቀ፣ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም፣ በራሪ አልባ ንቁ የስለላ ቴክኖሎጂ የሚያደርግ፣ ተወርዋሪ ፈንጂዎችምሽግ የሚያፈርስ፣ በምሽግ ብቻ ሳይሆን በስትራቴጂካዊ ቦታ፣ በሰላም ወረዳዎች ውኂያን የሚያጧጥፍና የሚያሳጥር ተቋም ኢትዮጵያ ስለገነባች ድፍን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ፣ ድፍን የአፍሪካ ሀገራት እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እፈልጋለሁ።

ተቋም የምንገነባው፣ የልዩ ጦር ኃይል የምንገነባው በቀጣናችን፣ በከባቢያችን ውኂያ፣ በቀጣናችን፣ በከባቢያችን ሽብር እንዳይፈጠር ነው፤ ሲፈጠርም በአጠረ ጊዜ ለመቋጨት ነው። የገነባነው ኃይል ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ዓለም አቀፍ ስምሪቶች ስመጥር ተግባራት ሲፈጽም እንደኖረው ሁሉ፣ በዚህም ዘመን ያንን ታሪክ የሚደግም፣ የቀይ በርኔጣ ክብር የገባው፣ ለባንዲራ ክብር፣ ለሀገር ክብር፣ ለሀገር ነጻነት እራሱን የሚሰዋ፣ በአእምሮም በአካልም የበለጸገ፣ ቴክኖሎጂን የሚያጫውት፣ የሚጠቀም፣ ውኂያን የሚሰራ፣ የሚጨርስ ኃይል ስለገነባን፤ የመከላከያ ኃይላችን የኢትዮጵያን ነጻነት፣ የአፍሪካን ሰላም ዛሬም እንደ ትናንቱ የሚያስከብር አስተማማኝ ኃይል መሆኑን ዛሬ በድጋሚ ከሀዋሳ ለመላው ህዝባችን ለማብሰር እፈልጋለሁ ።

ከአየር የሚወርዱ፤ ውኂያ የሚያስቀሩ፣ ውኂያ የሚጨርሱ፣ የአፍሪካ የነጻነት ቀን ድል የሆነውን አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ ሰንደቃችንን በድል የሚያውለበልቡ ጀግኖች ስለሆኑ የሚገባቸውን ክብር እንደ ሀገር በጋራ እንድንሰጣቸው በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።
የእኛ ተልዕኮ ራዕይ ያለው፣ ለትውልድ የሚሸጋገር ሁነኛ ተቋም መፍጠር ነው። የእኛ ተልዕኮ ውኂያ የሚያስቀር፣ ውኂያ የሚጨርስ የልዩ ጦር ኃይል መገንባት ነው። የእናንተ ተልዕኮ ኢትዮጵያን መገንባት፣ ኢትዮጵያን መጠበቅ፣ ኢትዮጵያን ማጽናት እና ኢትዮጵያን ማሸጋገር ነው። ኢትዮጵያ በልጆቿ ላብ ትሰራለች። ኢትዮጵያ በልጆቿ አጥንት እና ደም ትጸናለች። ኢትዮጵያ አልተደፈረችም፣ አትደፈርም፤ በክብርና በነጻነት ለልጆቻችን የምናሸጋገራት፣ ብቸኛዋ የአፍሪካ ፈርጥ ሆና ትቀጥላለች።

የእኛ ዝግጅት በድፍን አፍሪካ ሰላም ለማረጋገጥ፣ በድፍን አፍሪካ ብልጽግናን ለማረጋገጥ፣ በቀጣናችን ላሉ ሀገራትአለኝታ፣ መከታ፣ ጋሻ ለመሆን ነው። ለዚህም ሲባል በምድር፣ በተራራ፣ በጅረት የነበረውን ስልጠና ዛሬ ወደ ባህር ያሸጋገርነው፤ ከውሃ የመራቅ፣ ከውሃ የመሸሽ፣ ውሃን እንደ ባዕድ ነገር የማየት ክፉ ልማዳችን አሁን ባለው የልማት እሳቤ በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በሰው-ሰራሽ አስተውሎት፣ ግድቦች በመገንባት “ውሃ ህይወት፣ ውሃ ልማት” መሆኑን ማረጋገጥ መጀመራችን ይታወቃል። በዚህ ብቻ ሳይጠናቀቅ ከሱማሌ ጫፍ እስከ ምጽዋ ጫፍ በባህር የሚያጋጥሙ ሽብሮችን ወንድም ህዝቦችን ደግፈን ሽብርን ለማስቀረትና ልማት፣ ብልጽግናን በቀጣናችን ለማረጋገጥ፤ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናው በቂ የሆነ፣ የልዩ ጦር ኃይል ቴክኖሎጂ የታጠቀ፣ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም፣ በራሪ አልባ ንቁ የስለላ ቴክኖሎጂ የሚያደርግ፣ ተወርዋሪ ፈንጂዎችምሽግ የሚያፈርስ፣ በምሽግ ብቻ ሳይሆን በስትራቴጂካዊ ቦታ፣ በሰላም ወረዳዎች ውኂያን የሚያጧጥፍና የሚያሳጥር ተቋም ኢትዮጵያ ስለገነባች ድፍን የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ፣ ድፍን የአፍሪካ ሀገራት እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እፈልጋለሁ።

ተቋም የምንገነባው፣ የልዩ ጦር ኃይል የምንገነባው በቀጣናችን፣ በከባቢያችን ውኂያ፣ በቀጣናችን፣ በከባቢያችን ሽብር እንዳይፈጠር ነው፤ ሲፈጠርም በአጠረ ጊዜ ለመቋጨት ነው። የገነባነው ኃይል ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ዓለም አቀፍ ስምሪቶች ስመጥር ተግባራት ሲፈጽም እንደኖረው ሁሉ፣ በዚህም ዘመን ያንን ታሪክ የሚደግም፣ የቀይ በርኔጣ ክብር የገባው፣ ለባንዲራ ክብር፣ ለሀገር ክብር፣ ለሀገር ነጻነት እራሱን የሚሰዋ፣ በአእምሮም በአካልም የበለጸገ፣ ቴክኖሎጂን የሚያጫውት፣ የሚጠቀም፣ ውኂያን የሚሰራ፣ የሚጨርስ ኃይል ስለገነባን፤ የመከላከያ ኃይላችን የኢትዮጵያን ነጻነት፣ የአፍሪካን ሰላም ዛሬም እንደ ትናንቱ የሚያስከብር አስተማማኝ ኃይል መሆኑን ዛሬ በድጋሚ ከሀዋሳ ለመላው ህዝባችን ለማብሰር እፈልጋለሁ ።

ሃዋሳ የፍቅር፣ የሰላም፣ የደስታ ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ራዕይ የሚፈልቅባትና የሚነገርባት ከተማ መሆኗ ይታወቃል። በዚህች ከተማ ዛሬ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ማረጋገጥ የምፈልገው፤ የኢትዮጵያ ብልጽግና ይረጋገጣል፣ የኢትዮጵያ የአፍሪካ መሪነትና ምሳሌነት ይረጋገጣል፤ ልጆቻችን ድህነትን ታሪክ አድርገው ለመላው አፍሪካ ኩራት የሆነች ኢትዮጵያን እናስረክባቸዋለን። ይህ ግን በዋዛ ፈዛዛ ሳይሆን፣ ላባችንን አንጠፍጥፈን፣ ደማችንን አፍስሰን፣ አጥንታችንን ከስክሰን ኢትዮጵያን እንገነባለን፤ ሲዳማን እንገነባለን፤ ሃዋሳን እንገነባለን፤ አፍሪካን እንገነባለን።

የሃዋሳ ከተማ ነዋሪዎች ምርጥ ከንቲባ አግኝተናል። እንደዚህ ያለው ዕድል ሁልጊዜ ስለማይሳካ፣ ከንቲባችንን በመደገፍ ውቢቷን ሃዋሳን ዳግም በመስራት፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊመጣባት የሚጓጓት ዓለም አቀፍ ከተማ እንድትሆን፤ ባላችሁ አቅም ሁሉ ከከንቲባችንና ከርዕሰ መስተዳድሩ ጎን በመቆም ሃዋሳን ዳግም እንድንገነባ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ለከንቲባችንና ለርዕሰ መስተዳድሩ፤ ሃዋሳ ከሚገባት ትናንት ያየነው አንድ በመቶ ብቻ ነው። በዚህ ሳንረካና በዚህ ሳንቆም፣ ቀን ከሌት በመስራት ሃዋሳን ብዙ አፍሪካውያን መጥተው የሚጎበኟት፣ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች የሚካሄዱባት፣ እንዲህ ያለው ትልቅ በዓል የሚከናወንባት መዲና እንድትሆን፤ መንግሥትና ህዝብ በጋራ በመሆን እቺን የፍቅር ከተማ እንድንገነባ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ።

በነበረን ቆይታ ላሳያችሁን ፍቅር፣ ላሳያችሁን ክብር፣ ለሲዳማ ህዝብ ማንነት መገለጫ ለሆነው እንግዳ ተቀባይነትና ለዚህ የቄጤላ ስነ ስርዓት እንዲሁም መልዕክቶቹ በሙሉ፤ ታላቅ አክብሮትና ፍቅር ያለኝ መሆኑን እየገለጽኩ፣ ዳግም ወደ ሃዋሳ ስንመጣ በአዲስ ታሪክ፣ በአዲስ ድል, በአዲስ መከናወንና በአዲስ ምስጋና እንደምንገናኝ ያለኝን ሙሉ እምነት እገልጻለሁ ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና ተከብራ፣ በደምና በላባቸው ተገንብታ የነጻነት ቀንዲል ሆና ለዘላለም ትኑር! ፈጣሪ ላደረገልንና ለሚያደርግልን ሁሉ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን፤

አመሰግናለሁ!
ሃዋሳ

በድሬዳዋ የተደረገ ጉብኝት

የካቲት 30፣ 2018ዓ.ም

ድሬዳዋ የመጣነው ባለፈው ዓመት ነበር። ባለፈው ዓመት ስንመጣ ያስቀመጥናቸው ግቦች አሉ፤ እንዲሳኩ የምንሻቸው፣ ተሠርተው እንዲቆዩን ያስቀመጥናቸው ግቦች ነበሩ። እነዚያ ግቦች በምን ያህል ደረጃ እንደተሳኩ ለማየት ነበር የመጣነው። አሁን ካለሁበት ስፍራ ለመጀመር ይህ በመደመር ትውልድ የተገነባ “እመርታ” የተሰኘ ቤተ-መጻሕፍት ነው። ይህ ቤተ-መጻሕፍት አዲስ አበባ ላይ “አብርሆት” እንዳልነው ዓይነት ማለት ነው። ለብዙ አገልግሎት የሚውል ቤተ-መጻሕፍት ነው። የመደመር ትውልድ መጽሐፍ የተጻፈው ትውልዱን ለማነጽ ስለሆነ፣ ለትውልድ መሥሪያ የሚሆን ቦታ አንዱ ደግሞ የዕውቀት መገበያያ፣ አእምሮን ማጎልበቻ ቤተ-መጻሕፍት ነው።

በድሬዳዋ ላይ ቤተ-መጻሕፍት ተገንብቶበታል። ከዚያ ባሻገር ለታዳጊዎች፣ ለወጣቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታ፤ ትናንት እንዳየነው ልጆችን በሚመለከት መራመድ ፣ ማንበብ፣ መናፈሻ መሄድ፣ ቤተ-መጻሕፍትን መጠቀም፣ ብስክሌት መንዳት የመሳሰሉ ጉዳዮች በመልካም ጅማሮ እንዳሉ ማየት ተችሏል።

ከዚያም ባሻገር በከተማው በተለይ ኮኔል አካባቢ ማታ የእግር ጉዞ አድርገን ነበር፤ ደቻቱ የእግር ጉዞ አድርገን ነበር። ቀፊራ፣ ረባሌና አካባቢው የእግር ጉዞ አድርገን ነበር። በኮሪደር ልማት አምና ኮኔልን ስናይ አሁን ማታ እንዳየነው አልነበረም። ደቻቱ እንደዚያ አልነበረም። ቀፊራ፣ ለገሃሬ አካባቢ፣ ከዚራ አካባቢ የነበረው እንቅስቃሴ ከአምናው ይለያል። ይህ ሰፈር ልክ አዲስ አበባ ላይ መርካቶ እንደምንለው አሮጌው የገበያ ማዕከል የሚመስል ነገር ነው። እዚያ ውብ ተደርጎ መብራት ገብቶለት፣ እያንዳንዱ ሱቆች ትይዩ ሆነው ሰው አንዴ ከገባ በኋላ የፈለገበት ስፍራ ሄዶ እንዲገባ የሚያስችሉ ናቸው።

አምና ያስቀመጥነው ግብ አሁን ባለበት ደረጃ ነው። አሁን ደግሞ ያስቀመጥነው ግብ የውስጥ ለውስጥ መሆን አለበት። ከላይ በሐረግም ይሁን በግልጽ መስታወት ነገርም ይሁን ቢሸፈን፣ የውስጥ መገበያያ ማዕከል የመሆን ታሪካዊም ነው። ልክ እንደ ሐረር እንዳለው ጀጎል ወይም ኢየሩሳሌም እንዳለው ጥንታዊ ገበያ ዓይነት ነገር የመሆን ዕድል አለው። ማፍረስ ሳይሆን አስውቦ አሳድጎ ከላይ ጣራ ቢገባለት፤ አንደኛ ጥላ ይሆናል፣ ሁለተኛ የውስጥ ይሆንና ልክ ዘመናዊ የገበያ አዳራሽ የምንላቸውን ይመስላል። በዚህም ሱቅ ነው፣ በዚህም ሱቅ ነው። ቢዘንብ፣ ፀሐይ ቢሆን አንቸገርም። ብዙ ሰዎች የሚገበያዩበት ብቻ ሳይሆን የሚጎበኙት ሰፈር ይሆናል።

ከዚያ ውጭ ያየናቸው አብዛኛው የከተማው የኮሪደር ስራዎች እጅግ አስደማሚ ናቸው። ድሬዳዋ ከተማ ውስጥ አሁን ባገኘሁት ሪፖርት ወደ 187 ኪሎ ሜትር መንገድ ተገንብቷል። የነበረውም የተጨመረውም ታክሎ ማለት ነው። 187 ኪሎ ሜትር መንገድ ተገንብቶ አሁንም ያህል መንገድ ይፈልጋል። ብዙ ውስጥ ለውስጥ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች አሉ። እና ከከተማ ሥራ አንጻር እመርታ እንዳለ፣ ለውጥ እንዳለ ማየት ተችሏል። ግን ያ እመርታ በአገልግሎት ካልታከለ፣ በሕዝባዊ አገልግሎት መሶብ ላይ የጀመርነው ሥራ ካልታከለ፣ የሠራናቸውን ሥራዎች የመጠገን እና ዘላቂ የማድረግ አቅም የማናበጅ ከሆነ፣ አዳዲስ ፍላጎቶች አሉ። የሠራናቸውን መጠበቅ የማንችል ከሆነ አይዘልቅም።

እና በከተማ መብራት ላይ፣ በአረንጓዴ ልማት ላይ፣ በትንሽ ስታዲየም ላይ፣ አጠቃላይ ከተማውን ማስዋብ ላይ የተሠራው ሥራ በጣም ተሰፋ ሰጪ ቢሆንም፤ አሁን ተጨማሪ ሆቴሎች፣ የምግብ አዳራሾች ፣ ሥራ ፈጣሪ፣ ሥራ የሚያስይዙ፣ እንቅስቃሴን የሚይዙ ጉዳዮች ደግሞ ተጨማሪ የሥራ ድርሻ ተሰጥቷቸዋል ማለት ነው። ወደ ሬስቶራንት እንዲቀየሩ፣ ወደ ሆቴል እንዲቀየሩ፣ ወደ ቡና መሸጫ ቤቶች እንዲቀየሩ፣ ሰው ሥራ እንዲሠራ ፣ እንዲቀጠር የሚያስችል አውድ እንዲፈጥሩ የምናያቸው እነዚህ የሚያምሩ ፎቆች ዝም ብሎ ቢሮ ብቻ ከሆኑ ዋጋ የለውም፤ ወደ ገንዘብ መቀየር አለበት። እና ከተማው ሕይወት ያለው፣ ሥራ የሚፈጥር፣ ገንዘብ የሚያመጣ፣ ዕድገቱ የማይቋረጥ እንዲሆን የከተማ ሥራችን በተሟላ መንገድ ተጨማሪ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን አይቻለሁ።

እርሻን በሚመለከት ድሬዳዋ ሞቃታማ አካባቢ ነው። በተለይ ፍራፍሬ ላይ ብርቱካን ላይ፣ ፓፓያ ላይ፣ ቴምር ላይ ጥሩ ጅማሮዎች ጀምረዋል። በርከት ያሉ ቦታዎች ላይ ሥራ ጀምረዋል። ይህ መስፋት አለበት፤ ምክንያቱም ሞቃታማ ቦታ ነው፤ ፍራፍሬ ብንሠራ የበለጠ እርሻው ለከተማውም፣ ለአጎራባች ከተሞችም ለመዋል የሚያስችል ስለሆነ።

ከዚያ በተጨማሪ ኢንዱስትሪውን ብንወስድ ድሬዳዋ ላይ ከአራት መቶ በላይ ፋብሪካዎች አሉ። የኢንዱስትሪ ሀገር ነው። ይህንን ኢንዱስትሪ ነፃ የንግድ ቀጣና ጨምረን፣ ትናንት ያየነውን የነዳጅ መፈተሻ ተስማሚነት ማለትም መፈተሻ ጣቢያዎችን፣ የኮንስትራክሽን መፈተሻ ጣቢያዎችን እያሰፋን ስንሄድ፣ ወደ ውጭ ለምናስገባቸውም ወደ ውጭ ለምንልካቸውም ምርቶች በእጅጉ የሚያግዝ ይሆናል። ከኢንዱስትሪ አንጻር ጨርቃ-ጨርቅ ብቻ ሳይሆን ለግንባታ የሚውሉ የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች ተጀምረዋል። ይህንን ነገር አስፋፍተን እና መሬት አስይዘን፣ የድሬዳዋን ገቢ በማሳደግ ከተማዋን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አካባቢውን መቀየር እንዲችል ማድረግ ያስፈልጋል።

ለድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ፣ አመራሮች እና ለመላው የድሬዳዋ ነዋሪዎች ያለኝ መልዕክት፤ እንዳያችሁት ድሬዳዋ በተራሮች የተከበበች ከተማ ናት። እነዚህ ተራሮች ለድሬዳዋ በረከቷም ናቸው፣ ጥፋቶቿም ሊሆኑ ይችላሉ። ጥፋቶቿ የሚሆኑት በትክክል እርከን ካልተሠራ ፤ ዛፍ ካልተተከለ፤ የምንገነባቸዉ ቤቶች በንድፍ ካልተገነቡ፣ ዝም ብሎ እንደ ወፍ ዘራሽ የተረጨ ቤት ከሆነ፤ የትም ቦታ ታች ሆነን ተራሮቹን ስለምናይ በታቀደ መንገድ ያልሆነ ከሆነ በአደጋ ጊዜም ይሁን በደስታ ጊዜ መውጫ መግቢያው የሚታወቅ መንደር አይሆንም። ትንሽ ከከተማ ወጣ ወጣ ያሉ ስለሆነ፣ አሁን እየተወረረ ያለበት መንገድ የታቀደ አይደለም። ይሄ ከተስፋፋ ኃይለኛ ዝናብ ቢመጣ ላይ ያሉትም ይጎዳሉ፣ ታችም ጉዳት አለው። ተራሮቹ ጉዳት ናቸው ስል፣ ከከባቢው የሚዘንበው ዝናብ ተራሮቹን ታኮ የመጣው ድሬዳዋ ላይ ነው ታች ስላለች። ይሄ የሚቀረፈው እርከን ተሠርቶ ፣ ዛፍ ተተክሎ፣ ቤቶች በሥርዓት ከተቀመጡ፣ ውኃ የሚፈስበት ሥርዓት ካለ ላይም አይጎዳም፣ ታችም አይጎዳም።

በረከት ደግሞ የመሆን ዕድሉ ምንድን ነው? ተራሮች በጣም ነው የሚያምሩት። በትክክል የቤት ግንባታ ሥርዓት ብንከተል ድሬዳዋ አሁን ካለችበት ሦስት፣ አራት፣ አምስት እጥፍ የሰፋች፣ ያማረች፣ ለጎብኚ የምትመች ትሆናለች። ታች ሲታይ አረንጓዴ ናት፣ ንጹሕ ናት ዋናው ታች ያለው ቦታ፤ ከፍ ያለ ቦታ ግን በጣም ብትንትን ያሉ ቤቶች ናቸው ያሉት። እነዚህን ለሚቀጥለው ትውልድ ዕዳ አድርገን ማሸጋገር የለብንም። አሁኑኑ አቅደን፣ መስመር አበጅተን፣ ቤቶች የሚገነቡበትን፣ ዛፍ የሚተከልበትን፣ እርከን የሚሠራበትን ብናደርግ ለዓይን ውብ ነው፣ በቀጣይነት ላለው ዕድገትም ምቹ ነው። አልያ እዚያ አፍርሰን፣ ሠርተን ደግሞ ቆይተን እዚያ ማፍረስ ነው የምንገባው። እያፈረስን እንዳንኖር አንዳንዱን ምርጫ የሌለን እንጠግናለን፣ እናፈርሳለን፣ እናሻሽላለን፤ የምንጀምራቸው ቦታዎች ግን በዕውቀት፣ በንድፍ መሆን አለበት።

እሱን ማድረግ ከቻልን እንዳያችሁት ድሬዳዋ ትልቅ ከተማ ነው። ብዙ ነገር ማስተናገድ ይችላል። እዚህ የነበረውን ቤተ-መንግሥት ልክ እንደ ሌሎቹ ቦታዎች እንደሠራናቸው የገበታ ፕሮጀክቶች፣ ለምሳሌ እንደ ወንጪ ወይም እንደ ጎርጎራ እዚህ ያለውን ቤተ-መንግሥት ሙሉ በሙሉ ታድሶ ለግል ዘርፉ ተሰጥቶ ቱሎ ሰዎች የሚስተናገዱበት ቦታ ሆኗል። ለመንግሥት ተቆልፎ የሚቀመጥ ሳይሆን፣ መንግሥትም ይሁን ግለሰብም ይሁን አቅሙ የሚፈቅድለት ሰው ሰርግ ማድረግ እንዲችል፤ ልደት ማድረግ እንዲችል፤ ምርቃት ማድረግ እንዲችል፤ ገብቶ ምሳ፣ ስብሰባ ማድረግ እንዲችል ተመቻችቷል ቦታው። ለምንድን ነው አንዳንድ ቦታ ያለንን አድሰን እንሠራለን ፣ አንዳንድ ቦታ አዲስ እንሠራለን ። ግን የድሬዳዋ ቤተ-መንግሥት የታደሰበት ደረጃ እና ለሕዝብ ክፍት የተደረገበት ደረጃ፣

ከሠራናቸው ሌላ አዲስ ከሠራናቸው የሚያንስ ነገር አይደለም። ቅርሻት ሳይሆን ቅርስ ነው መጠበቅ አለበት። አስውበን አልቀን ነው የሠራነው ። ይህንን በየከተማው አንዱ ጋር አዲስ፣ አንዱ ጋር ያለውን አስውበን ስንሠራ ለጎብኚዎች መዳረሻ ይሆናል። ማንም ሰው ቢመጣ አያሳፍርም። አሁን ያ ቦታ ማንም ሰው፣ ማንም እንግዳ ቢመጣ ድሬዳዋ ተቀብላ ማስተናገድ ትችላለች። ንጹሕ ከተማ አላት፤ ኤርፖርት አላት፣ ያ ቦታ አለ፤ ግን እንደዚህ ዓይነት 10፣ 15 ደግሞ ቢኖር የጉባኤዎች ማዕከል የመሆን ዕድል አላት።

በተለይ ሐምሌና ነሐሴ አዲስ አበባ እንደሚታወቀው ይበርዳል፣ ይከብዳል። እና ብዙ ሰዎች ትምህርት የላቸውም፤ ሐምሌና ነሐሴ ትምህርት የለም ከረምቱ ከበድ ይላል አዲስ አበባ፤ ወደዚህ መጥተው 15 ቀን፣ 20 ቀን ማሳለፍ ይችላሉ። የተሻለ አየር ስላለ ያ መሆን የሚችለው ግን በቂ ማረፊያ ቦታ ሲኖር ነው። ያ መሆን የሚችለው ግን ከተማው ላይ የምናየው ጽዳት እየሰፋ ሲሄድ ነው፣ የተሟላ አገልግሎት ሲሆን ነው። እና ያንን በማድረግ ድሬዎች ሰው ለመቀበል፣ ለማስተናገድ፣ በተለይ እዚህ ሙቀት በሚሆንበት ሰዓት የከረምት ወራትን ሌሎች ሰዎች ከብርድ ቦታ መጥተው እንዲስተናገዱ ጥሩ አማራጭ ሆኖ መቀጠል አለባቸው።

ድሬዎች ያላቸው ጥራት ብዙ ነው። እኔ ሁለት ሦስቱን ለመጥቀስ፤ አንደኛ፣ ምግብ ዝግጅት ላይ በጣም ጣፋጭ ጣፋጭ የሆኑ እንደ ባቅላባ ያሉ ብዙ ዓይነት ምግቦች ያዘጋጃሉ። ከቴምር፣ ከሰሊጥ ፣ ከለውዝ በጣም የሚጣፍጡ ነገሮች ያዘጋጃሉ። ብዙ ቦታ አይገኝም ይሄ። ሁለተኛ፣ በፍቅር ማስተናገድ ይችላሉ፤ ሰው መቀበል ይችላሉ። የብዙ ቋንቋዎች፣ ብሔሮች፣ ልምዶች፣ ባህሎች ስብጥር ያለበትና ፍቅር ጎልቶ የሚታይበት ከተማ ነው። “አብሮ ለመኖር ገንዘብ፣ አብሮ ለመኖር ቋንቋ፣ አብሮ ለመኖር እምነት ሳይሆን፤ አብሮ ለመኖር ሰውነት ይበቃል” ብለው የሚያምኑ ሰዎች ናቸው። ለብዙዎቻችን ትምህርት መስጠት ይችላሉ። እና ፍቅራቸውን፣ የምግብ ጣዕማቸውን፣ ሰው በፍቅር የመቀበል ልምምዳቸውን ተጠቅመን እኛ እንመጣለን እነሱ ያስተናግዳሉ፤ እኛም እናተርፋለን እነሱም ያተርፋሉ። እና ቆይታችን ድሬ፣ ሲደመር ከትውልድ ግንባታ አንጻር፣ ከእርሻ አንጻር፣ ከኢንዱስትሪ አንጻር, ከከተማ አንጻር፣ ከሕዝብ ለሕዝብ ውህደት አንጻር፣ የነገውን የምናስበውን የምናልመውን ብልጽግና የምናረጋግጥበትን መንገድ ከመቀየስ አንጻር ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎችና ሥራዎች እንዳሉ አይቼ በጣም በጣም ደስ ብሎኛል። እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ስለነበራችሁ አቀባበል፣ ፍቅር እና መስተንግዶ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን። ደጋግመን ለመምጣት እንድንችል፣ የመንግሥት ሕንጻዎች ወደ ንግድ ያልተቀየሩ፣ ሕንጻዎች

ያልተሠሩ ሆቴሎች እንዲስፋፉ እንዲሠሩ እና በርከት ያሉ ሰዎች መቀበል እንድትችሉ አሁንም በርትታችሁ ሥሩ። ጅማሮው መልካም ነው ግን ጉዞ ገና ብዙ ብዙ ይቀረዋል ማለት እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ድሬዳዋ

በቁንድዶ ተራራ የተደረገ ጉብኝት

የካቲት 30፣ 2018ዓ.ም

አሁን የምንገኘው በምስራቅ ሀረርጌ “ቁንድዶ” በሚባለው ተራራ ላይ ነው። ይሄ ተራራ ከፍተኛ ታሪክ ጠገብ ቦታ ነው። በዚህ ቦታ ላይ አዋቂዎችና የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚናገሩት፣ የአህመድ ግራኝ እና ልብነ ድንግል በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ግጭት እዚህ አካባቢ ላይ ሸሽቶ የመጣው ጦር ሙሉ በሙሉ ከመደምሰስ እና ታሪኩ ከመጥፋቱ በፊት ውስን ፈረሶች እዚህ ተራራ ላይ እንዲወጡ አድርገው ነበር ይባላል፤ የዚያ ምክንያት “እኛ በውጊያው ብንወድቅ/ብንቀር ታሪካችን ጠፍቶ አይቅር” ከሚል መነሻ እንደሆነ የዚህ አካባቢ ሀገር ሽማግሌዎች እና አዋቂዎች ገልጸውልናል። በዚያ ጊዜ የተዋቸው ፈረሶች ሲሞቱ፣ ሲጎሉ፣ ሲጨምሩ ቆይተው ዛሬ ወደ 48 ገደማ ቤተሰብ የለመዱ የቤት ፈረሶች ሳይሆኑ የዱር ፈረሶች እዚህ ቦታ ላይ ይገኛሉ።

ተራራው ትንሽ ከፍታ ያለው ቦታ፣ መጠነኛ ቅዝቃዜ ያለው ቦታ ነው። የፈረሶቹን ቅርጽ ያየን እንደሆነ በተለምዶ ከምናውቃቸው ፈረሶች በተለየ ሁኔታ አንገታቸው ረዘም ያለ ነው፤ እና እነዚህን የዱር ፈረሶች እና በዚህ ተራራ ያለውን የእግር ጉዞ ማድረጊያ ሰዎች እየመጡ እንደሚያዩ ሰምተናል። ከዚያም በተጨማሪ ልክ እንደ ባሌ ሦስት፣ አራት ቦታ በጣም ረጃጅም ዋሻዎች እዚህም አካባቢ አሉ፤ እንደገለጹልኝ ከሆነ በርዝመታቸው ባሌ ካለው የሚበልጥ ነው የሚል ሰምቻለሁ በዐይኔ አላየሁም። እነዚያን ዋሻዎች፣ የእግር ጉዞ ማድረጊያ ቦታዎች፣ እነዚህን የዱር ፈረሶች እንደምታዩት፤ ይሄ ተራራ ቁንድዶ ብቻ ሳይሆን አንዳንዶች ‘ደብሊው ተራራ ይሉታል በቅርጹ የተነሳ። ተራራው በራሱ በጣም በጣም ከፍተኛ ውበት ያለው ለእይታ የሚማርክ ቦታ ነው የምናየው።

ፈረሶቹንም ያየን እንደሆነ ትናንሾችም ስላሉ ትውልድ የሚቀጥል ይመስላል፤ እዚያ ማዶ የምናያቸው የተወሰኑ ፈረሶች አሉ እዚጋም እንደዚሁ አሉ፤ እነዚህ ፈረሶች በቤት ከምናውቃቸው ፈረሶች ለየት የሚያደርጋቸው ዝርያቸው ሳይሆን፣ ከጊዜ በኋላ እዚህ በመቆየት በቅርጻቸው በቁመናቸው የተለየ ቅርጽ እንዳላቸው ማየት ችለናል። እነዚህን መጠበቅ ያስፈልጋል፤ ተፈጥሮን መጠበቅ፣ ታሪክ መጠበቅ፣ ይበልጥ አስውቦ በማስቀጠል ለትውልድ ጠቃሚ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ የቱሪስት መስዕብም ሊሆን ይችላል።

እንግዲህ አስቡት፣ የዛሬ አምስት መቶ ዓመት ከባቢ የነበረ ግጭት ውስጥ እንደ ቅሪት የቀሩ ፈረሶች ዛሬ እነሱን ተንተርሶ ታሪክ እንዲወሳ፣ ያኔ በውጊያ የተሳተፉ ሰዎች እንዳይዘነጉ

ማድረግ መቻላቸው በቀላል የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ታሪክ ባስቀመጥነው ልክ፣ ባስቀመጥነው ቦታ እንዳለ ሳይሸረሸር የማይቀመጥ ቢሆንም፤ ብርቱ ትውልድ፣ አዋቂ ትውልድ፣ አስተዋይ ትውልድ ሲኖር ግን በዚህ መንገድ ከልጅ ልጅ እየተሸጋገረ ሊቀጥል ይችላል። እና ከዚህ ቀደም በተለያየ መንገድ ሰምተን ሊሆን ይችላል፤ አሁን ግን በመገናኛ ብዙኃን ሲቀርብ፣ እኛ መጥተን ስናይ የብዙኃን የማየት ፍላጎታቸው ሲነሳሳ ከታሪክነት ባለፈ የሚጎበኝ ቦታ፣ ሀብት የሚመጣበት ቦታ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው።

በቅርቡ ዋሻዎቹን እናያቸዋለን፤ እነዛን ዋሻዎች እና ይህንን አካባቢ የእግር ጉዞ ማድረጊያን ጨምሮ ከፍተኛ የቱሪስት መስህብ እንደሚሆን ይጠበቃል። የምስራቅ ሀረርጌ ሰው በጣም ብርቱ ሰራተኛ፣ ስራ የሚወድ፣ ታሪክ የሚወድ፣ እምነቱን የሚያከብር፣ አካባቢውን የሚጠብቅ ህዝብ ነው። እዚህ ብቻ ሳይሆን ከዚህም ወጥተው ወደ ሌላ አካባቢ የሰፈሩ ሀረርጌዎች በስራ ይታወቃሉ፤ በርትተው ሰርተው ኑሯቸውን ያሻሽላሉ። እዚያ ላይ የቱሪዝም መስዕብነቱ ታክሎበት በእርሻ፣ በንግድ፣ በቱሪዝም ከዚያም እያለ ወደ ኢንዱስትሪ የሚያድግ ከሆነ የሰውን ህይወት ያሻሽላል፣ የከባቢውን መልክዓ ምድር አሁን ካለበት በላይ ሰዎች እየተበረከቱ ሲሄዱ ዛፍ እየተከልን ለማስዋብ ይመቻል፤ እና እዚህ የተመለከትነው ጉዳይ ኢትዮጵያ ተዝቆ የማያልቅ ታሪክ፣ ተነግሮ የማያልቅ ታሪክ፣ ታይቶ የማይጠገቡ ስፍራዎች ያላት ሀገር መሆኗን ያመላክታል።

በሌላው ዓለም እንደዚህ ያለ ቦታ ብዙ ሰው የሚጎበኘው የሚያየው ነው። በእኛ ሀገር እንደ መንግሥት ከተሰጠው ዝቅተኛ ትኩረት የተነሳ እንደዚህ አይነት ቦታ ብዙ ባይታይም፤ ለወደፊቱ ግን እነዚህን አቅም በፈቀደ መጠን እያለሙ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛና ታሪክ ማስቀጠያ ቦታ መሆን እንዳለባቸው ይሰማኛል። ባየነው ነገር በጣም በጣም ደስ ብሎናል። እዚህ ቦታ መጥቶ የሚያይ ሰውም በሚያየው ነገር እንደሚደሰት ተስፋ አደርጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ምስራቅ ሐረርጌ

በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ናሲኦል ዋሻ የተደረገ ጉብኝት

—መጋቢት 1፣ 2018ዓ.ም

ዛሬ የምንገኘው በምስራቅ ሀረርጌ ዞን ውስጥ ነው። ትናንት የዱር ፈረሶች የማየት ዕድል አግኝተን ነበር፤ ያንን ስናይ በምስራቅ ሀረርጌ በርከት ያሉ ቦታዎች እንደዚህ ያሉ ዋሻዎች ከሺህ ዓመታት በፊት የነበሩ እንዳሉ መረጃ ስለደረሰን ይሄኛውን ዋሻ ለማየት መጥተናል፤ አሁን ወደ ውስጥ ወደ 500 ሜትር የሚጠጋ ተጉዘናል፤ ከጀርባ እንደምታዩት 30 ሜትር ርዝመት ያለው ውብ የሆነ ስፍራ ይታያል። እንግዲህ ይህ ቦታ ሰፋ ያለ ጥናት ይጠይቃል። እንዴት ተፈጠረ? ሰዎች ምን ሚና ነበራቸው? እንዴትስ መልሶ አሁን ወደ እዚህ ሁኔታ ተቀየረ የሚለው ጥናት ይፈልጋል። ግን ኢትዮጵያ ገና ታውቆ ተዝቆ የማያልቅ ታሪክና ሀብት እንዳላት አንዱ ማስረጃችን ይህ ዋሻ ነው።

በዚህ ዋሻ ውስጥ በዐይን ብቻ በጣም ነጭ፣ ከእብነ-በረድ የነጣ የድንጋይ ዓይነቶች አይተናል፤ የኖራ ድንጋይ መሳይ ነገሮች አይተናል፣ ባልጩት ድንጋዮች አይተናል፣ ከዚያም ያለፈ ቅይጥ ያላቸውን ድንጋዮች አይተናል። ይሄን በዕውቀት፣ በጥናት፣ ምንድናቸው? ከምን መጡ? እንዴት ተሰሩ? የሚለውን ማየት ይፈልጋል። አንዳንዱ ቦታ ያሉ ዋሻዎች የውኃ መስመር እንደሆኑ የሚነገሩ አሉ፤ ግን ይሄኛው እንደምታዩት የውኃ መስመርም አይደለም፤ እንዴት ተፈጠረ? እንዴት ተሰራ? ሰዎች ምን ሚና ነበራቸው? የሚለውን ሙያተኞች በግርድፍ ሳይሆን በዕውቀት እና በጠራ መረጃ ማጥናት ይኖርባቸዋል። ግን ምስራቅ ሀረርጌ የገባኝ ነገር መሠረተ-ልማት ከፍተኛ ችግር ቢሆንም፤ ብዙ ዋሻዎች፣ የዱር ፈረሶች፣ ዝሆኖች፣ የተተከሉ ድንጋዮች በብዛት የሚታዩበት፣ ፍል ውኃዎች ያሉበት፤ ይሄ ሶማሌ ሀረሪን ጨምሮ ያለው መሠረተ-ልማት ቢሰራለት ብዙ ሊመረመሩ ሊታዩ የሚችሉ ሀብቶች እንዳሉ መገንዘብ ችያለሁ።

በተለይ እብነ-በረድና ባልጩት ድንጋይ የመሳሰሉ ውድ ውድ ድንጋዮችን በሚመለከት፣ ይህ አካባቢ በብዙ ሀብታም እንደሆነ ማየት ችያለሁ ። እንግዲህ የዛሬው እይታ ከመስማት የዘለለ ዕውቀት ለመፍጠር ነው፤ ከዚህ በኋላ ሙያተኞች ተጨምረው በሚኖረው ጥረት መሠረት እንዴት አድርገን ወደ ልማት ወደ ሀብት ቀይረን የዜጎቻችንን ሕይወት እናሻሽላለን፣ የሀገራችንን ሀብት እናሻሽላለን የሚለው ጉዳይ የቤት ሥራ የሚሆን ይሆናል። ትናንት በሀረሪ ክልል የነበረን ቆይታ እጅግ አመርቂ ነበር ማለት ይቻላል። ጀነልን አይተናል፤ ጀነል አምና ካየነው በእጅጉ ተሻሽሏል። በእጅጉ አምሯል፤ ለማየት ለሚሹ ሰዎች የተሻለ ስፍራ ሆኖ ተሰርቷል። ቀሪ ሥራዎች አሉ በሚቀጥለው ጊዜ የሚሰሩ፣ ግን

ሀረር ወደ ነበረ ስሟ፣ ወደ ነበረ ክብሯ፣ ወደ ነበረ ገናናነቷ የመመለስ ጉዞ እንደጀመረች ያመላክታል። የሀረር ሕዝብ ፣ የሀረር ከተማ ሕዝብ ከተማውን ለመቀየር ለማስተካከል የተለየ ሀብት ኖሮት ሳይሆን፣ የተለየ ዕውቀት ኖሮት ሳይሆን፤ “ሀገሬ መቀየር አለባት፣ ስሟ ክብሯ መመለስ አለበት” በሚል እምነትና ሐሳብ በመነሳሳት ከክልሉ መንግሥት ጋር በመሆን ሀረሪን በእጅጉ እያስዋቡ ይገኛሉ። የሀረሪ ክልል ውበት ከምስራቅ ሀረርጌ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። በጋራ የሚኖሩ ሕዝቦች፣ የተዋለዱ ሕዝቦች ናቸው። እዚህ ያለው ሀብት እዚያ ካለው ሀብት ጋር ሲተሳሰር፣ እዚህ ያለው የሰው ሀብት እዚያ ካለው ጋር ሲተሳሰር ተሰናስለው የሚወጣ ነው የሚሆነው፤ እስከ ሶማሌ ክልል ይቀጥላል።

ጅግጅጋ ከዚህ በቅርብ ርቀት ያለ ቦታ ነው፤ ሸበሌ የሚባለውን ፍል ውኃ አካባቢ ማልማት ስንችል፣ ጅጅጋን ፣ ሀረርን፣ ምስራቅ ሀረርጌን እዚያ ያሉ ሀብቶችን ደምሮ ለማንሳት በእጅጉ የሚያግዝ ይሆናል። እንግዲህ አቅም በፈቀደ መጠን እየታየ፣ እየተጠና የሚሰራ ይሆናል። ዛሬ ባየሁት ነገር አሁንም ኢትዮጵያን አውቀን እንዳልጨረስን፣ አሁንም ሀብታችን ተዝቆ እንደማያልቅ፣ ብዙ መማር፣ ብዙ መድከም፣ ብዙ መጓዝ፣ በድረ-ገጽ መፈለግ ፣ ማሰስ እንዳለብን የሚያመላክት ጉዳይ ነው።

ብዙዎቻችን ሀገራችን ሳናውቅ ፣ የሀገራችን በቂ መረጃ ሳይኖረን በሰው መረጃ ተንተርሰን የምናወጣቸው ፖሊሲዎች፣ የምናወጣቸው ስትራቴጂዎች የተሟላ ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም። አንድ ሀገር በራሱ ሉዓላዊ በሆነ መረጃ ላይ ተንተርሶ የሚሰራው ፖሊሲ ትክክለኛ ነው፤ የሀገሩን መልክና ቅርጽ ያሳያል። ነገር ግን በሌሎች መረጃ ላይ ተንተርሰን የምንሰራቸው ማንኛውም ፖሊሲዎች የእኛን አሁናዊ ሁኔታ ስለማያሳዩ፣ የተሟላ ለውጥ እና ልማት ሊያመጡ አይችሉም፤ እና የመረጃ ሉዓላዊነት፣ መረጃን በራስ ማወቅ፣ ሀብትን በራስ ማወቅ፣ በራስ ልክ መለካት በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

አንድ ሀገር የራሱን ሀብት፣ የራሱን የተፈጥሮ ጸጋ በራሱ ማየትና መለየት ሲችል ልክ መስታወት እንደማየት ነው። አንድ ሰው መስታወት ሲያይ በተቃራኒ ቦታ የሚመለከተው ነገር ሙሉ ቅርጹንና ምልክቱን ነው። ነገር ግን ከሌሎች መረጃ ስንወስድ መስታወት ሳይሆን እንደተቀባ ቀለም ነው። አንድ ሰው የፈለገበት ጥቁር ከቀባ ጥቁር ቀለም ይታያል፣ ነጭ ቢቀባ ነጭ ቀለም ይታያል፣ አረንጓዴ ቢቀባ አረንጓዴ ቀለም ይታያል፤ ያ የተቀባው ነገር ከጀርባው ያለ ማንነቱ እሱ ላይሆን ይችላል። ከውጭ የሚነገረን የተቀባ ቀለም ነው፤ እውነተኛ የእኛ መረጃ፣ እውነተኛ የእኛ ሀብት፣ እውነተኛ የእኛ ታሪክ አይደለም። እውነተኛው የእኛ ታሪክ እኛ በተገለጠ ዐይን፣ በበራ አእምሮ ስናይ እንደ መስታወት ነጸብራቅ የሚያደርገው ብቻ ነው። ያ እንዲሆን ደግሞ አዋቂዎች, ምሁራን፣ ሀገር ወዳድ

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር ይሄንን ዋሻ በሚመለከት መረጃ ብፈልግ ኤክስ ወይም ዋይ ሀገር እንዳለው ነው የሚባለው። ኤክስ ወይም ዋይ ሀገር ባሻው መንገድ የሠራው ትርክት፣ የቀባው ቀለም የኢትዮጵያን ገጽ አያሳዩም። ኢትዮጵያውያን በራሳችን ሀብታችንን፣ ልካችንን አውቀን በእኛ መንገድ መግለጥ የማንችል ከሆነ፤ ሰዎች የእኛን ልክ በሚፈልጉት መንገድ እንጂ፣ እኛ በሆንነው መንገድ ይገልጣሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። እና ይሄ በጣም ሥልጣኔ ያለበት ጥንታዊ የሰው ልጅ መገኛ፣ በጥንት ዘመን ብዙ ታሪክ የተሠራበት ሀገር መሆኗን ያመላክታል።ይህ አሁን ያለንበት ቦታ ከባሌ ሁለት ወረዳ ገደማ ቢርቅ ነው፤ የተቀራረበ ነው። ምንድን ነው በአጠቃላይ በቦታው ላይ የነበረው ሥልጣኔ ፣ ዕውቀት፣ በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች እንዴት ያስቡና ይሠሩ ነበር፤ ከተፈጥሮ ጋር ተዋሕደው ይኖሩ ነበር የሚለውን ትንሽ መለስ ብሎ፣ ቆም ብሎ ማጥናትና ማስተዋል የሚፈልግ ይመስለኛል። ለማንኛውም እኔ የተማርኩት ነገር ኢትዮጵያ ሰሜንም፣ ደቡብም፣ ምዕራብም፣ ምስራቅም ቢኬድ ጥንታዊት ናት፤ ተፈጥሮን መቀየርና መሥራት የሚሹ ጀግኖች ሕዝቦች የነበሩባት ሀገር ናት፤ ኢትዮጵያ ኃያል የነበረች ሀገር ናት፣ ትልቅ ሀገር ናት፤ ያ ቢሸፈን፣ ቢቀባ፣ ቢቀበር በተሟላ መንገድ ሊጠፋ አልተቻለም። ቅሪቶች አሁንም ይታያሉ፤ እነዚህን ቅሪቶች አይቶ አቧራ አራግፎ የነበረውን ቅርጻችንን፣ አቋማችንን፣ ቁመናችንን ለመያዝ በትብብር፣ በመደመር፣ በማስተዋል፣ ወደ ውስጥ በማየት መቆም ያለብን ጊዜ አሁን ይመስለኛል።

እኔ ብዙ ተምሬበታለሁ፤ እንግዲህ መማር የሚፈልጉ ሰዎች መጥተው ቢያዩ ብዙ ዕውቀት ይገበያሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ወደ ኋላ መለስ ብሎ “ማን ነበርን? ከየት መጣን?” የሚለውን ለማወቅ ዕድል የሚሰጥ ይመስለኛል። በበኩሌ ዛሬ ባየሁት በጣም ደስተኛ ነኝ። የምስራቅ ሀረርጌ ሕዝብ ላደረገልን አቀባበል እና ግብጣ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። የዞኑን አስተዳዳሪ ወይዘሮ ምስኪን አሚኖን አመሰግናታለሁ፤ ገፋፍታ ነው ያመጣችኝ። ባየሁት ደስ ብሎኛል፤ ተመላልሼ እንደምመጣ ተስፋ አደርጋለሁ።

እንግዲህ ኢትዮጵያ አሁንም ታውቃ፣ አሁንም ተቆፍራ፣ አሁንም አቧራው ረግፎ ያላለቀ ብዙ ምስጢር ያላት ሀገር መሆኗን መገንዘብ በመቻል፣ እጅግ አድርጌ ላመሰግን እወዳለሁ። ጥሩ ቆይታ ነበረን፤ ቀሪውን ታሪክ እና ትውልድ ፈልፍሎ የሚያወጣው ይሆናል።

አመሰግናለሁ!
ናሲኦል ዋሻ

የኒዚን ሌ ፓልም ሎጅ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

መጋቢት 17፣ 2018ዓ.ም

ክቡር አቶ አወል አርባ የክልላችን ርዕሰ መስተዳድር፣
ክቡር ኢንጂነር መሐመድ የዚህ ውብ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን አስተዳደር ዋና ስራ አስፈጻሚ፣
ክቡራን ሚኒስትሮች፣ የክልል አመራሮች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ከአፋር በተለይም ከአዋሽ ኤርታሌ ወረዳ የተወከላችሁ የማኅበረሰብ አባላት፤ ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ አለን ማለት እወዳለሁ።

አፋር በታሪክ፣ በተፈጥሮ በእጅጉ የታደለ ክልል ነው። ይህ የምታዩት የዘንባባ እርሻ፣ ብዙ ቦታ ልዩ ልዩ ጫካዎች፣ ዛፎች፣ ደኖች አይታችሁ ሊሆን ይችላል፤ በዚህ ጥግግት ፣ በዚህ ጥርቅም በአንድ አካባቢ ላይ በተፈጥሮ የበቀለ የዘንባባ ጫካ ማየት እምብዛም የተለመደ አይደለም። እዚህ የምናየው የጫካ ዘንባባ መልኩ፣ ቅርጹ፣ ቁመቱ መለየቱ ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ምግብ የሚጠጣው ፍል ውሃ ነው። እዚህ አካባቢ ላይ ያለው በሙሉ ፍል ውሃ ነው። ከዚህ ሜዳማ አካባቢ እምብዛም ሳንርቅ በርካታ የሚያማምሩ ተራራዎች ያሉበት አካባቢ ነው። ውሃው፣ ተራራው፣ ዛፉ፣ ልዩ የሆነ የሳር ዝርያ አይነቱ በሙሉ ለሺህ ዓመታት እዚህ ቦታ ነበር።

ይህንን ቦታ በርካቶች እንዲያዩት፣ ዐይን ለመግለጥ የተሰራው የገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት፤ አፋር ካላቸው በጣም ብዙ ሀብቶች መካከል አንደኛው ላይ የዋለ ቢሆንም፤ ከዚህ ፕሮጀክት ብዙ ርቀት ሳንጓዝ የአሰቦት ፓርክ፣ የአዋሽ ፓርክ ይገኛል። በእኔ እምነት ከአዲስ አበባ ቢበዛ ቢበዛ ሁለት ሰዓት መንገድ ተነድቶ ሊታይ የሚችል፣ ሁለት ታላላቅ ፓርክ፣ የዱር እንስሳት ጉብኝት ሊደረግበት የሚችል አካባቢ ብዙ ያለ አይመስለኝም። ትልቁ ችግር የነበረው መሠረተ-ልማት ነው፣ ፈጣን መንገድ ነው።

አሁን ከአዳማ አዋሽ የሚገነባው ምናልባት ቢበዛ አንድ ዓመት ቢፈጅ ነው፤ ከአዋሽ መውጫ አድርገን እዚህ ለመምጣት የሚወስደው ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ብቻ ነው። ይሄንና አሰቦትን ስናገናኝ ማንኛውም ሰው ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ተነስቶ በሁለት ሰዓት የመኪና መንገድ እዚህም በይኑና አዋሽም መድረስ ይችላል፤ በተለይ መንገዱ ሲያልቅ ባቡርም አለው። ይሄ ከአዲስ አበባ ነው። አዲሱ የአየር ማረፊያ ኤርፖርት ቢሾፍቱ ሲሰራ ይቀንሳል። ከቢሾፍቱ ኤርፖርት ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በእንደዚህ ባለ

ስፍራ መጥቶ ፓርኮች ለማየት እና ብዙ የተፈጥሮ አስደናቂ ሁኔታዎችን ለማየት መታደል የብዙዎች ፍላጎት ነው፤ እኛም አቅማችን እየጨመረ ሲሄድ የምንሾው ጉዳይ ነው። ነገር ግን አሰቦትም አዋሽም እዚሁ አካባቢ እያሉ እንዲህ ያለው ጽዱ ማረፊያ ካልተሰራ፣ ሰዎች ቀልባቸው መጥተው ሊገለገሉ ሊያዩ አይችሉም፤ ቢመጡም ውለው አያድሩም ተመልሰው ይሄዳሉ ። ይሄ ለአፋር የመጀመሪያው በር ነው።

ከዚህ ስንቀጥል ከአሰቦት በኋላ አፍዴራን ያየን እንደሆነ፤ በብዙ የዓለም ቦታ ላይ ሊታይ የማይችል ነገር፣ በአንድ በኩል ሀብት በሌላ በኩል ደግሞ ውበት የሚታፈስበት ቦታ ነው። ከአፍዴራ እልፍ ስንል ዳናኪልን እናገኛለን፤ እጅግ አስገራሚ ውበት አለ፣ ኤርታሌ አለ፤ ብዙ ቦታ ፍል ውሃዎች ሲፈልቁ የሚታይበት ክልል ነው። ይህንን ውብ ክልል መጠነኛ መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ እየሰራን፣ መጠነኛ ድካም እየደከምን, መጠነኛ ላብ እያፈሰስን ወርቁን ለማፈስ የሚያስችል እድል ለልጆቻችን መስጠት እንችላለን ከሚል እምነት የሚነሳ ነው።

አፋር ምድሩ ብቻ ሳይሆን ሰው በእጅጉ የተባረከ ነው፤ ሀገሩን የሚወድ ብርቱ ትጉ ህዝብ ነው። ለዚህ ህዝብ እንዲህ ያለውን ስራ መስራት፣ ዐይን መግለጥ፣ የተፈጥሮን ጸጋና ውበት ማሳየት መቻል ለኛ እንደ ትልቅ እድል የሚወሰድ ነው። አፋሮች ስለ ትጋት፣ ስለ ብርታት፣ ስለ መስራት፣ ስለ አለመዘናጋት ብዙ ይናገራሉ። ከዚህ ንግግራቸው መካከል አንዱ በአፋር የሚታወቅ አባባል ‘እድል ያንቀላፉ ሰዎችን አትቀሰቅስም’ ይላል አፋር። እድል አለች፣ ከአንቀላፋችሁ ግን አትቀሰቅስም። እዚህ ቦታ ላይ ለረጅም ጊዜ እድል ስትዞር፣ ስትዞር, ስትዞር በእኛ ማንቀላፋት ምክንያት አላረፈችባቸውም፣ አልቀሰቀሰቻቸውም፣ ትታቸው ሄዳ እንጂ፤ ይህ ጉዳይ መሰራት የነበረበት የዛሬ 50 60 ዓመት ነበር።

አሁን ስለዘገየን አንቆጭም፣ ነገር ግን ይህንን ስለሰራን ደግሞ አንረካም። ሩጫችን ገና ብዙ እንደሆነ፣ አፋር ገና እንዳልተነካ አስበን ይህን መነሻ፣ ይህን ጅምር ይበልጥ አልቀን ለማስቀጠል እንተጋለን። ሁልጊዜም ለውጥ ተዘጋጅተው ለሚጠብቁ ሰዎች የሚበረከት ጸጋ ነው። ያልተዘጋጀ ሰው እዚህ ቢመላለስም የባለፈውን የዘንባባ እርሻም የዛሬውንም ብናሳየው፤ ለለውጥ ዝግጁ ያልሆነ ሰው ማየት አይችልም። ሰው ለለውጥ፣ ለእድገት ራሱን ያዘጋጀ እንደሆነ ከትናንሽ ነገሮች ውስጥ በርከት ያለ ጸጋ ለማውጣት፣ ለማየት፣ ማለም ለማድረግ ይታደላል። ያ የለውጥ መሻት በውስጡ ከሌለ ግን ምንም ያህል ያማረ ውብ ስጦታ ቢኖረንም ያን ወደ ሀብት ለመቀየር የሚተጋ አይሆንም።

ይህ ማለት አሁን እንደምታዩት የዘንድሮ በልግ አስደማሚ ዝናብ እየዘነበ ነው። አርሶ አደሮች እና በአመራር ሥራ ላይ ያላችሁ ሰዎች ይህንን የበልግ ዝናብ እንደ ዋዛ አያዩትም፤ የበልግ ዝናብ በዚህ መጠን እየዘነበ ነው ማለት የሚቀጥለው ዓመት ጥጋብ ነው ማለት ነው። ቋንቋው፣ ተፈጥሮው እንደዛ ነው። አሁን ከዘነበ የሚቀጥለው ዓመት ጥጋብ ነው ማለት ነው። ግን ጥጋብ የሚሆነው ለማን ነው? መሬቱን አርሶ፣ አለስልሶ፣ ፈጣሪውን ታምኖ ለሚጠብቅ ሰው ነው። መሬት አለስልሶ አርሶ ያልተዘጋጀ ሰው ዝናቡ ያልፈዋል። የዘንድሮ ዝናብ ከአምናው፣ ከአቻምናው ከዚህ ቀደም ከምናውቀው ዝናብ በተለየ መንገድ እኛ ኢትዮጵያውያን ልንወስድ ይገባናል።

ምክንያቱም ዘንድሮ በመካከለኛው ምስራቅ በተፈጠረው ችግር ሁለት አንኳር አስፈላጊ ጉዳዮች፣ አስፈላጊ ግብዓቶች አደጋ ደርሶባቸዋል። አንደኛው ነዳጅ ኃይል ነው፣ ሁለተኛው ማዳበሪያ ነው። ሁለቱ ቁልፍ ግብዓቶች በደረሰባቸው አደጋ መጀመሪያ ጥቃት የሚያጋጥመው ምግብ ነው። በማዳበሪያውም በኃይል እጥረት ምክንያት የሚጎዳው የምግብ እጥረት የሚያስከትለው አደጋ ነው። ምግብን ለማምረት ነዳጅ ቢያዝብን፣ ማዳበሪያ ቢያዝብን፣ በልግ በዚህ ልክ ከተሰጠን ፈጣሪ በብዙ ሊጎበኘን ፍላጎት አሳድሯል ማለት ነው። ምን ከሆነ? አርሰን፣ አለስልሰን፣ ተዘጋጅተን ከጠበቅን።

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በዓለም ላይ የመጣው ፈተና ከባድ ቢሆንም ፈጣሪ በሰጠን ዝናብ በርትተን ከሠራን ቢያንስ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት፣ ቢያንስ ነው፣ በበልግ ማረስ ከቻልን ከዚያ የምናገኘው ለምሳሌ የስንዴን ብቻ ብንወስድ በርካታ አትክልት ሊዘራ ይችላል፤ ስንዴ 40 ኩንታል በሄክታር ብናገኝ ሁለት ሚሊዮን ባይሆንም ባነሰ በአንድ ሚሊዮን እንኳን ቢታሰብ 40 ሚሊዮን ኩንታል እናገኛለን ማለት ነው። የበልግን ዕድል ያበላሸ ክረምትም ያመልጠዋል።

እዚህ ቦታ ላይ የነበረው ችግር እንደዚሁ ሆኖ ነው ተፈጥሮ የሰጠችውን ጸጋ ማንበብ፣ ማወቅ, ጊዜን መገንዘብ ተስኖን ለረጅም ዘመናት እንዲህ ያለው ገነት እንዲህ ያለው ውበት ሳናየው ቆየን እንጂ፤ ሌሎች ዓለማት እቺን ቤት ከገነቡ በኋላ መከራቸውን የሚያዩት እንደዚህ ያለውን ዘንባባ በዚያ አካባቢ ላይ ለመትከል ነው። በነገራችን ላይ አሁንም ቢሆን አዲስ አበባ አካባቢ ጥሩ የዘንባባ ዝርያ በሺዎች ብር ይሸጣል ችግኙ፣ የደረሰ ችግኝ በሺዎች ብር ይሸጣል። እዚህ እንደምትመለከቱት በመቶ ሺዎች ምናልባት በሚሊዮን የሚቆጠር የዘንባባ ጫካ አለ፤ እኛ ለዚያ አልከፈልንም ለዚህ ፍል ውኃ አልከፈልንም እኛ የሠራነው ጎጆ ነው፤ ግን ያ ጎጆ ከተፈጥሮ ጋር እንዲስማማና ይህን ውበት እንዲያወጣ አደረግን። ልክ እንደዚሁ የዘንድሮውን በልግ የተዘጋጀ፣ ያለሰለሰ፣ ያረሰ አርሶ አደር የሚቀጥለው ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ መከራ፣ ችግር፣ ረኃብ ሳይሆን ጥጋብ እንዲመጣ

ስለሚያደርግ ወቅትን ጊዜን ማወቅና መጠቀም የሁላችን ትጥቅ ልብስ መሆን አለበት። ምክንያቱም አፋሮች 'ላብ ወርቅ ያስገኛል ስንፍና ግን አቧራ ያስታቅፋል' ይላሉ። በላብ ወርቅ ይታፈሳል በስንፍና አቧራ ይለበሳል። ዘንድሮ በልግን በበቂ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ማረስ፣ ማስተራረስ በመካከለኛው ምስራቅ በተፈጠረው ችግር ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሚቸገሩ ሰዎች እንደ መፍትሔ ጭምር ትልቅ ዕድል ስለሚሰጥ፤ ሳንዘናጋ ልክ በዚህ ቦታ ላይ ያልታየን አይተን መልካም ነገር እንዳስቀመጥን የበልግን ዝናብ በዚያው ልክ መጠቀም ያስፈልጋል። ይህን ካደረግን የምናስበውን ብልጽግና ለማረጋገጥ በእጅጉ የሚያግዝ ይሆናል።

ታዲያ አፋር፣ ኢትዮጵያ እንደዚህ ያለው ጸጋና ስጦታ ካላቸው እስካሁን ለምንድነው ያንን መልካም ነገር ተጠቅመው መበልጸግ መልማት ያልቻሉት የሚል ጥያቄ ቢነሳ አግባብ ነው። ይሄ ሁሉ ነገር እያለን ምን ነካን ቢባል መጥፎ ፖም ተፅዕኖ የሚባል ነገር አለ። በአንድ ኩንታል ውስጥ ያሉ ጤነኛ ፖምች መካከል አንድ የተበላሸ በሽተኛ ፖም ቀላቅለን ብናስቀምጥ፣ እነዚያን ጤነኞች ፖምች የማበላሸት አቅም አለው። ምንም እንኳን መልካም ነገሮች የበዙ ቢሆንም አንድ የተበላሸ ነገር ካለ ያ የተበላሸው ነገር አብዛኛውን ጤነኛውን ነገር ያበላሸዋል። ይህ ችግር የአፋር፣ የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የደቡብ፣ የቤንሻንጉል፣ የጋምቤላ፣ የትግራይ፣ የሁሉ ኢትዮጵያ ችግር ነው።

ብዙ መልካም ሰዎች ብዙ መልካም አሳቢዎች ቢኖሩም፣ የተበላሸ ጨለምተኛ እሳቤ ያላቸው ሰዎች በውስጡ ሲቀላቀሉ አብዛኛው መልካም ነገር የተበላሸና በችግር ችግርን በማውራት፣ በችግር ውስጥ በመኖር፣ ችግርን በመተንተን ዘመን የሚታለፍ መስሎት ያስባል። በችግርም በመተንተን የሚታለፍ ዘመን የለም፤ ችግርን ረግጦ፣ መከራን ረግጦ አሻግሮ በማየትና በመትጋት ብቻ ነው ለውጥ የሚመጣው። እንደዚህ ያለው ጨለምተኛ ስብስብ ባለበት አካባቢ ሁሉ ያማረ ውጤት አይመጣም፤ ከመጣም የዘገየ ይሆናል።

በ2006 የዛሬ 20 ዓመት ገደማ በተደረገ አንድ ጥናት አምስት ሰዎች መካከል አንዱ ጨለምተኛ የሆነ እንደሆነ፣ አሉታዊ አሳቢ የሆነ እንደሆነ፣ መልካም ነገር ማየት የሚሳነው የሆነ እንደሆነ፣ ከጨለማ ውስጥ አርቆ የብርሃን ጭላንጭል ማየት የሚሳነው ከሆነ የእነዚያ አምስት ሰዎች የሥራ ውጤት ቢያንስ በ40 በመቶ ይቀንሳል ይላል፤ ጥናት ነው ይሄ። ከአምስቱ አንዱ ጨለምተኛ ከሆነ የዚያ አጠቃላይ የቡድኑ የሥራ ውጤት በ40 በመቶ የቀነሰ ይሆናል። ከ130 ሚሊዮን ምን ያህል ጨለምተኛ እንዳለ አስቡና ያ በጋራ በሚሆንበት ሰዓት አብዛኛው መልካም አሳቢ ቢሆንም ጥቂት ጨለምተኞች ካሉ ውጤቱ የዘገየ ይሆናል። ጨለምተኝነት ትውልድ ይገድላል፣ ጨለምተኝነት ሀገር ያዘጋጃል፣

ጨለምተኝነት መለወጥ፣ ማደግ፣ መሻገር ስንችል የምንለምን፣ የምንዘገይ ያደርገናል፤ ከጨለምተኛ አመለካከት፣ ‘አይቻልም’ አመለካከት፣ ‘አይሳካልኝም’ አመለካከት ወጥተን ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል።

ቅድም እንዳያችሁት የዛሬ ሁለት ሦስት ዓመት እዚህ ቦታ ስንመጣ መንገድ አልነበረም፤ አስቸጋሪ አካባቢ ነው፣ ከመንገድ ራቅ ይላል እንዳያችሁት እና ሙቀቱ ከፍተኛ ነው። በማንኛውም መስፈርት በዚያ ጊዜ ይህ ቦታ አሁን ያለውን መልክ፣ አሁን ያለውን ቅርጽ ይይዛል ብሎ መናገር በቀላሉ ሊታመን አይችልም። ሐጅ አወል ብቻ ሳይሆን በርካታ ሰዎች ይህንን ለማመን ይቸገራሉ። ነገር ግን ያየነውን ለመኖር፣ ያየነውን ለማሳየት፣ ያየነውን ለማበራከት ባደረግነው ተከታታይ ጥረት ዛሬ በምንም መስፈርት ማንም ሰው ቸል፣ ናቅ ሊያደርገው የማይችል መልካም ዘር በዚህ ስፍራ ተዘርቷል።

ይህ ስፍራ ግን የተዘራው ዘር ማሳ መሆን እንዲችል ቅድም እንደተባለው አራት፣ አምስት፣ ስድስት ቦታዎች አፋር ውስጥ መሰል ሥራ ያስፈልጋል። እነዚህ እየተሠሩ ሲሄዱ የግል ዘርፉ ዓይኑ ተገልጦ፣ የክልሉ አመራር ዓይኑ ተገልጦ እያንዳንዱን ቦታ ሲሠራ አንድ ሰው አፋር ገብቶ ዛሬ ዛሬ አይወጣም፣ ሳምንት ይቆያል፤ ብዙ የሚያቆይ ነገር ስላለ ውብ ተፈጥሮ አለ፣ በጣም ደጋግ ሰዎች አሉ። ሁሉ ቢጠፋ የግመል ወተት አለ፣ በከል አለ፤ ያንን እየበሉ ሳምንት በደስታ መቆየት የሚቻልበት ክልል መፍጠር ይቻላል።

ይህ እንዲሆን ጨለምተኝነት፣ ‘አይቻልም’፣ ‘አይሳካም’ ከሚል መንፈስ መውጣት፣ አሁን ባለው ሁኔታ አለመታሰር፣ አሁን ባለው ችግር አለመታሰር፤ ከዚያ አልፎና አሻግሮ ማየት መቻል፣ ያንን ስናደርግ የምናስበውን የበለጸገች ኢትዮጵያ ለማየት፣ ለልጆቻችን ለማስረከብ ዕድል እናገኛለን። ይህ ቦታ ኒይን ሌ ፓልሞ ሎጅ ለኩሪፍቱ ሪዞርት ተሰጥቷል። አቶ ታዲዮስ ሁላችሁም እንደምታውቁት ጎብኚ በመሳብ ለኢትዮጵያ ፊር ቀዳጅ የሚባል ሰው ነው። እንዲህ ያለውን ተፈጥሮ በሚያገኝበት ሰዓት የውኃ ፓርክ በመጨመር፣ መኝታ ክፍሎች በመጨመር፣ ብዙ ጎብኚዎች እንዲመጡ በማድረግ፣ ከአዋሽ ጋር በማያያዝ፣ ከበይኑና ጋር በማያያዝ, ከአሰቦት ጋር በማያያዝ ትልቅ የጎብኚዎች መንደር እንዲሆን በራሱ፣ በጓደኞቹም፣ ሌሎችም አካላት የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት ምንም ጥርጥር የለውም።

ይህንን ቦታ ሐጅ አወል እና አቶ ታዲዮስ ማሰብ ያለባችሁ እንደ አዲስ ማሳ ነው። አዲስ ማሳ ሁለት ቁልፍ ነገሮች ያጋጥሙታል። በመታረሱ፣ በመቆፈሩ ምክንያት የተዘራ ዘር አለ፤ ያ የተዘራ ዘር ከተንከባከብነው ፍሬያማ ሆኖ በብዙ ተባዝቶ ሊመጣ ይችላል፤ በሌላ

መንገድ ደግሞ ያ ማሳ ከዘሩ በፊት የለመደው አረም አለ። አረም ከአዲስ ማሳ ይነቀላል እንጂ አይጠፋም። በአዲስ ማሳ ዘር ይዘራል እንጂ እንክብካቤ ካላገኘ አይበቅልም። አረሙም አለ ዘሩም አለ። ዘሩ አብቦና ተባዝቶ መልካም ፍሬ እንዲሰጥ፣ ያ የተነቀለው አረም ተመልሶ መብቀል እንዳይችል መጠበቅ አለበት፤ ማሳው መኮትኮት አለበት፣ ውኃ ማግኘት አለበት። ያንን እንክብካቤ መስጠት ካልቻልን ቀድሞ የለመደው አረም ብቻውን ሳይሆን ተባዝቶ ይወርሰዋል። አረሙ ይበዛና ዘሩ ያንሳል። ያ እንዳይሆን መልካም ጅምር፣ መልካም ሥራ ያየን ቢሆንም፤ አረሙን በቀጣይነት ማጥፋትና ዘሩን ማባዛት ግን ገና ተጨማሪ ድካም የሚጠይቅ ስለሆነ ለሀጅ አወል ለአቶ ታዲዮስ አደራ የሚሰጥ ጉዳይ ይሆናል።

እኛ ሰርተናል አለቀ ብለን አንተውም፣ መጥተን እናያለን፣ እንደተባለውም እንገለገላለን። ክልላችን መምጣት ሀጅ አወል ስለጋበዘን እኛ እንመጣለን፣ ሀጅ አወልም በከል ያርዳል፣ ግመል እንኳን ይበዛብናል፤ በዚህ መንገድ ይሄ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁላችንም የበኩላችንን እንድንወጣ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያውያን በተለይ መንዳት የምትችሉ በቡድን፣ መንዳት ባትችሉም ባቡር መጠቀም የምትችሉ፤ ለቱሪዝም ዓላማ አይደለም ሀገራችሁን ለማወቅ፣ በዚህ ስፍራ ስላሉ ድንቃ ድንቅ ውበቶች ለማየት፣ ለማድነቅ፣ ለመውደድ፣ ለመስራት እንድትችሉ ይህንን ቦታ ከማየት እንዳትቦዝኑ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።በተለይም የተለየ ብቃት እና ዕውቀት ያላችሁ ምሁራን፤ በእኔ እምነት በዚህ ስፍራ ያልዳሰስነው፣ ያልደረስንበት፣ የተደበቀ ብዙ ሀብት ሊኖር ይችላል። የድንጋዩ ቅርጽ የተለየ ነው፣ የውሃው ጣዕም ፣ ክብደት የተለየ ነው፣ የምናያቸው እፅዋት የተለዩ ናቸው፤ ተጨማሪ ምርምር፣ ተጨማሪ ጥናት ቢደረግ አዳዲስ ሀብት ሊወጣ ስለሚችል የምትመረምሩ ሰዎች መጥታችሁ እንድትመራመሩ ፣ የምትማሩ ሰዎች መጥታችሁ እንድትማሩ፣ ማረስ የምትሹ ሰዎች መጥታችሁ እንድታርሱ፣ ሀገራችሁን እንድታዩ አደራ እያልኩ፤ አፋር የኢትዮጵያ በረከት ነው፣ አፋር የኢትዮጵያ ጠባቂ ነው፣ አፋር የኢትዮጵያ ባለአደራ ነው። ብዙ ሰጥታችኋል፣ ብዙ አድርጋችኋል፤ ላደረጋችሁት ሁሉ ኢትዮጵያም እኔም እናመሰግናለን። የቀረውን ያስቀራችሁትን ደግሞ በጋራ እናመጣለን፤

አመሰግናለሁ!

ኒሚን ሌ ፓልም ሎጅ፣ አፋር

የአዲስ ስፖርት ፓርክ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

መጋቢት 26፣ 2018ዓ.ም

የሀገር ግንባታ ሥራ ሁለት መሠረታዊ ምሰሶዎችን የያዘ መሆን አለበት። ትናንትን በወጉና በቅጡ የሚያስታውስ፣ በወጉ በቅጡ የሚያወሳው፤ ነገን ደግሞ የሚሠራ መሆን አለበት። ለምሳሌ ዓድዋ ሙዚየም ስትሄድ አባቶቻችንን እናስታውስበታለን፣ ጀግንነታችንን፣ ነፃነታችንን እናስታውስበታለን፤ ሙዚየሞቻችንን ስታይ ያ መልክ አላቸው፤ ያም ምሰሶ አላቸው። ነገር ግን ብቻቸው በቂ አይደለም፤ ነገን ደግሞ የምንሠራው በልጆቻችን ነው።

ልጆቻችንን አስተውለህ ከሆነ፣ ባለፉት ስምንት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ 35 ሺ ገደማ መዋዕለ-ሕፃናት ገንብተናል፤ 35 ሺሕ ግን ዩኒቨርሲቲ አልገነባንም፤ ብዙ ሰዎች አይገባቸውም፤ ዩኒቨርሲቲ ከ20 - 30 ዓመታት በኋላ ሚች ነው። ነገ ያለው የሕፃናት መሠረታዊ የቅድመ-ትምህርት ሥርዓት ላይ ነው፤ ታች ነው ሥራውን ሊሠራ የሚገባው። መዋዕለ-ሕፃናት ስንገነባ፣ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስንገነባ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስንገነባ፣ እነዚያ ልጆች ሲደርሱና ሲበቁ ኢትዮጵያ ቀና እንድትል የሚያስችል አቅም ይዘው ይነሳሉ ማለት ነው።

አምስት ሚሊዮን ወጣቶች ኮደር ስንፈጥር ያልነው፣ ነገን ለመሥራት የሚያስችል ትውልድ ለመሥራት ነው። ያ ብቻ ግን በቂ አይደለም፤ ብዙዎቻችን በተለያየ ሀገር ስንንቀሳቀስ ፣ በውጭ ያሉ ወንድሞቻችን እንደሚያውቁት ቅዳሜና እሁድን ሲመጣ “ልጆቼን ዋና ላስዋኛቸው፣ ስፖርት ላሰራቸው፣ ቅርጫት ኳስ ላጫውታቸው” እያሉ በቅርብ ርቀት ልጆቻቸውን ይወስዳሉ፤ እኔም እንደዚህ ዓይነት ዕድል አጋጥሞኝ ያውቃል፤ እና ያስቀናል። በውጪው ዓለም እንደዚህ ባለ ቦታ ልጆች ሄደው ሲዝናኑ፣ ሲሰለጥኑ፣ ሲዋሃዱ ስታይ “መቼም ያንን ነገር በሀገሬ ማየው?” የሚል ቁጭት ይፈጥራል፤ ምክንያቱም የሀገር ግንባታ እና የሰው ስሪት፣ ሰውን ለመሥራት የመማሪያ ክፍል ገብቶ የሚነገረውን አድምጦ፣ ያንን ሸምድዶ ፈተና አልፎ ብቻ ሰው አይሠራም ።

ሰው የሚሠራው ከነኑ የተቀመጠው ሰው ሲያለቅስ “ምን ሆንክ?” ብሎ መጠየቅ ሲችል፣ ሲበድል ይቅርታ ማለት ሲችል፣ ሲያጠፋ ይቅርታ መጠየቅ ሲችል። ደግሞ ሲመሰገን ምስጋናን መቀበል የሚችል፣ ሲነካካም የራሱን ፍላጎት፣ የራሱን መብት መከላከል የሚችል ሆኖ በማኅበራዊ መስተጋብር ሲሠራ ነው። ያንን ማኅበራዊ መስተጋብር የማይችል ከሆነ፣ ቀለም ብቻውን የተሟላ ትውልድ አይፈጥርም።

ዛሬ እዚህ ቦታ እንዳየኸው ሁለት ነገር አቅፎ ይዟል። አንደኛ፣ እነ አበበ ቢቂላ፣ እነ ምሩፅ ይፍጠር፣ እነ ቀነኒሳ፣ እነ ደራርቱ ሐውልት የተሠራላቸው ቦታ ነው። እነ ጥሩነሽ ፣ እነ መሰረት ደፋር ተራ ዜጋ አይደሉም። ብዙዎቻችንን በእንባ ያራጨ፣ ለትውልድ ምሳሌ የሆኑ፣ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ላይ ከፍ ብላ እንድትነሳ ያደረጉ ጀግኖች ናቸው። እና ሰዎች ከሞቱ በኋላ በሰልፍ ብንቀብራቸው በቂ አይደለም፤ በሕይወት እያሉ መከበር አለባቸው። የእነሱን ክብር ያየንበት ቀን ነው። ያ ግን ብቻውን በቂ አይደለም።

እንዳየኸው በሁሉም መስክ ሕፃናትና ታዳጊዎች መሰልጠን የሚችሉበት ሥራ ሠርተናል ። ማንን እያዩ? ደራርቱን እያዩ፣ ሀይሌን እያዩ፣ ቀነኒሳን እያዩ፣ ጥሩዬን እያዩ፤ እነዚህ ይህንን እያዩ ካደጉ እሷን ለመሆን፣ እሱን ለመሆን ስለሚሠሩ ኢትዮጵያ በቀጣይነት በዓለም መድረክ ስሟን የሚያስጠሩ ጀግኖች ትፈጥራለች ማለት ነው። ሳንዘራ ማጨድ አይቻልም። መዋዕለ-ነዋይ ሳናፈስ የአማረ ጉዳይ መጠበቅ ከንቱ ምኞት ነው። በዓለም አቀፍ መድረክ ስመ-ጥር ኢትዮጵያውያንን ለማየት ይህ ሥራ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ ዋና፤ ከዚህ ቀደም እንደምታውቀው ብዙም ስማችን አይጠራም። አሁን ግን ከሰባት ዓመት በታች፣ ከአስር ዓመት በታች፣ ከዚያ በላይ በኦሎምፒክ መመዘኛ በቤት ውስጥና በውጭ የዋና ቦታ አለ፤ እዚህ ያሰለጠንበትና በዚህ ያደገ ሰው ሊወዳደር ይችላል ማለት ነው። ስፖርት እንዳየኸው ቮሊቦል ፣ መረብ ኳስ፣ የውጭ ስፖርት መሥሪያ ቦታ፣ የውስጥ የአካል ብቃት ማሰልጠኛ ኳስ መጫወቻ ደረጃውን የጠበቀ፤ መረብ ኳስ መጫወቻ በተለይ ደግሞ አፈር የሆነ ብትንጋለልበት የማይጎዳ፣ ልክ በውጪው በብራዚል እንደምናየው ማለት ነው። ይህ ሁሉ ነገር በውስጡ የያዘ ፓርክ ነው።

ለልጆቻችን በጣም በጣም ትልቅ ዕድል ነው። እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ስናድግ እንደዚህ ያለውን ነገር ለማየት እምብዛም አልታደልንም። አሁን እያደጉ ያሉ ልጆች ይህንን እያዩ ካደጉ፣ በቅርብ ርቀት ፓርክ ማየት ከቻሉ፣ በቅርብ ርቀት ንጹሕ የመራመጃ መንገድ ማየት ከቻሉ፣ የሰው ሀገር መመኘትና መቅናት ይቀርና በሀገር መኩራት፣ በሀገር መኖር፣ በሀገር መጽናት፣ ለሀገር መሥራት እያደገ ይሄዳል፤ በዚህ ሒደት ውስጥ ኢትዮጵያ ትገነባለች። የሀገር ግንባታ የምናስብ ሰዎች መገናኛ ብዙኃን ብቻ የሚገነባው፣ ትምህርት ብቻ የሚገነባው አድርገህ መውሰድ የለብንም፤ ብዙ መስክ ሊሠራ ይገባዋል፤ በተለይ ደግሞ ትናንትናንና ዛሬን ማስተሳሰር፤ ዓድዋንና ታዳጊውን ማስተሳሰር፤ ደራርቱን እና የነገዋን ደራርቱ ማስተሳሰር፤ እንዲህ እያደረግን በሄድን ቁጥር ኢትዮጵያ የሚገባትን ቦታ፣ የሚገባትን ክብር ትይዛለች።

ሁላችን ልንገነዘብ የሚገባው፣ በዓለም አሥረኛውን የሕዝብ ቁጥር የያዘች ሀገር ናት ኢትዮጵያ፤ ከ30 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ሀገር ናት፤ ከዚህ ውስጥ በጣም አብዛኛው፣ 70 በመቶ በላይ ከ20 ዓመት በታች ዕድሜ የያዘ ነው። የኢትዮጵያ በአማካይ ዛሬ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ገደማ ወጣቶች ነን። ብንሮጥ፣ ብንሠራ ፣ ብንሰለጥን፣ በዕውቀት ብናድግ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን ለመሥራት ሚያስችል ዕድል አለ ማለት ነው፤ ግን ከፍተኛ መዋዕለ-ነዋይ የሚጠይቀው ክህሎት ነው። ዛሬ ዓለም የክህሎት ዓለም ናት። አንድ ሰው የሚያገኘውን ደሞዝ አንድ ሺህ ሰው ሊያገኘው ይችላል በክህሎቱ ፣ በብቃቱ ምክንያት፤ ብቃት የሌለው ሰው ተወዳድሮ ማሸነፍ፣ ተወዳድሮ መላቅ አይችልም። ተወዳድሮ የሚልቁ ሰዎችን ለማብዛት ከታች የሚሠሩበት ፣ የሚለማመዱበት፣ የሚሰለጥኑበት እና ክህሎት የሚያሳድጉበትን ቦታ መሥራት አስፈላጊ ነው።

እንደ መንግሥት እነዚህን ጉዳዮች አስበን የምንሠራው ዛሬ ያለውን ነገር አይተን አይደለም፤ ነገ ለምናስባት፣ ለምናልማት ኢትዮጵያ ለልጆቻችን በውጭ በፊልም አይተው የሚቀኑ ሳይሆን “እኛም ሀገር አለ፣ ግን ላስፋው፣ ግን ላስውበው፣ ግን ላሳምረው” የሚል ትውልድ መፍጠር እንፈልጋለን፤ በዚህ አግባብ የተሠራ ሥራ ነው። እንግዲህ ካሳንቺስ በብዙ መልኩ አብባለች ፣ አምራለች፤ ይህንንም ስፍራ ይዛለች። ካሳንቺስ ላይ ማንም ይህንን አይጠብቅም፤ ከዚህ ቀደም በስፋት የተለመደው የጫትና የሺሻ ቦታ ማበራከት ነው። እሱ ትውልድ ገድሏል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሠራ ፣ ኢትዮጵያ ሊለውጥ የሚችል ትውልድ ሞቷል።

ያንን ስህተት መርገም የለብንም። ይሁን ብለን አስበን መዋዕለ-ነዋይ አፍስሰን ታዳጊዎች የሚሰሩበት፣ የሚያድጉበት፣ የሚወዳደሩበት፣ የሚልቁበት፣ የሚበልጡበት አውድ ያስፈልጋል፤ ከዚያ ውስጥ ደግሞ አንዱ ይሄ ነው።

እዚህ ስፖርት ይለማመዳሉ፤ ዐድዋ ሄደው ታሪካቸውን ይማራሉ፤ ደራርቱን እያዩ፣ ሃይሌን እያዩ፣ ቀነኒሳን እያዩ ይጓጓሉ፤ በቁጭት ይሞላሉ፣ ይነሳሳሉ፣ ይሰለጥናሉ፣ እነሱ ይተካሉ፤ ልቀውም አልፈው ይሄዳሉ፤ እና በዚህ አግባብ ትውልድ ለመስራት፣ ኢትዮጵያን ለመስራት የሚያስችል ቦታ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ተስፋ ሰጪ ስራዎች አሉ፤ ኢትዮጵያ እየተሰራች ነው በሁሉም መስክ፤ ልብ ያለው፣ ዐይን ያለው፣ ማስተዋል ከቻለ ኢትዮጵያ በስራ ላይ ነች፣ ትሰራለች።

ፈተናዎችና ችግሮች ሁሉ ወደ እድል በመቀየር፣ ኢትዮጵያን የማጽናት፣ ኢትዮጵያ የመስራት፣ ኢትዮጵያን የማቆም ጉዳይ ታስቦበት እየተከወነ ነው ያለው። ፈጣሪም በብዙ

እየረዳን ነው። መከናወን ሆኖልናል፣ መከናወን ተሰቶናል። የነካነውና የጀመርነው ሁሉ ያልቃል፤ የነካነውና የጀመርነው ሁሉ አምሮበት፣ አብቦ ያልቃል።

እንግዲህ ትውልድ ይህንን ዘመን የሥራ ዘመን፣ የመነሳት ዘመን፣ የመንቃት ዘመን አድርጎ ደግሞ የሚያወሳበት ጊዜ ይመጣል፤ እኛ በጣም ደስተኞች ነን። የጀመርነውን፣ ያሰብነውን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ማየት የምንፈልገውን፣ ልጆቻችን እንዲያዩና እንዲኖሩበት የምንፈልገውን ኢትዮጵያ እየሰራን ነው ያለነው።

በሁሉም መስክ ኢትዮጵያ እየተሰራች ነው ያለችው። ይህ ጉዳይ ይቀጥላል፤ ትብብር፣ መደማመጥ፣ ማስተዋል፣ በሙሉ ልቦና ማየት፣ አርቆ ማየት፣ ማለም ያስፈልጋል። በዚያ በእውነት ላይ ስንመሰረት መከናወን ከላይ የተሰጠ ይሆናል ማለት ነው።

እና ስለዚህ ስራ ፈጣሪን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፤ ካለእርሱ እርዳታ እንዲህ አይከናወንም። የሰሩ፣ በጣም የተጉ ብዙዎች አሉ፤ የሥራ ተቋራጮች ፣ መሐንዲሶች ፣ ሞያተኞች፣ የከተማ መስተዳድር፤ ብዙ ሰው ተሳትፎበት የተሰራ ስራ ነው። ሁሉም ምስጋና ይገባቸዋል። እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

የአዲስ አበባ ታዳጊዎች፣ ወጣቶች በእንደዚህ ባለው ስፍራ እየመጣችሁ ጊዜ እንድታጠፉ፣ ራሳችሁን እንድትሰሩ፣ አካላችሁን እንድታበለጽጉ ፣ ከሰው ጋር መዋሃድን እንድትለማመዱ በዚሁ አጋጣሚ ልጋብዛችሁ እፈልጋለሁ። እጅግ አስደሳች እለት ነበር፤ ይህ ደስታ የሁሉም ደስታ እንዲሆን ምኞቴ ነው።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ

አርማወር ሐንሰን የምርምር ተቋም

—መጋቢት 26፣ 2018ዓ.ም

በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ ወይም በአንድ ሀገር ጉዞ ውስጥ መከራ፣ ችግር፣ ተግዳሮት አይፈጠር አይባልም፤ ነገር ግን አንድ ችግር፣ አንድ መከራ፣ አንድ አታካች ነገር ሲፈጠር ያንን ነገር ወደ ዕድል ለመቀየር እና ከዚያ መከራ ውስጥ፣ ከዛ ችግር ውስጥ ዕድል ለማውጣት መስራት ለሰው ልጅ እንዲሁም ለሀገር በእጅጉ ያስፈልጋል። እንደሚታወሰው የኮሮና ወረርሽኝ በመጣበት ወቅት፣ የሰለጠነው ዓለም ያልሰለጠነውን ዓለም—አፍሪካን—በስፋት “ሰው የሚያልቅበት፣ ከዚያ በሽታ ማምለጥ የማይችል አህጉር፣ በየመንገዱ ሰው እየሞተ የሚታይበት ሊሆን ይችላል” ብለው ብዙዎች ተንብየዋል ፣ ገምተዋል። በፈጣሪ ቸርነት ያ ትንበያ ያልሰራ ቢሆንም፣ በሒደቱ የተማርነው ነገር ዝግጅት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ነው። እነሱ ክትባት ስላላቸው፣ መድኃኒት ስላላቸው መትረፍ እንደሚችሉ፤ እኛ ግን ክትባት በበቂ ማምረት ስለማንችል፣ መድኃኒት ማምረት ስለማንችል ልንቋቋመው የማንችለው መከራ እንደመጣብን በስፋት ተናግረው ነበር።

እና ያንን ጊዜ በምግብም በመድኃኒትም ራስን ለመቻል እንደ ዕድል መጠቀም አለብን የሚል አቋም እንደ መንግሥት ወስደን ነበር፤ ለዚያ ነው “በቦጋ እንረስ፣ መሬት ፆም አይደር” ብለን ስንዴ ላይ የዘመትነው፣ ውጤትም ያመጣው። የስንዴው ቶሎ ታየ እንጂ በመድኃኒትም መሰል እርምጃ ተወስዷል። ያኔ ኮሮና ሲመጣ ኢትዮጵያ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማምረት የምትችለው መድኃኒት 8 በመቶ ብቻ ነበር፤ እና በቂ መድኃኒት ማምረት አንችልም፣ ወይ ለምነን ወይ ገዝተን ነው የምናመጣው። ሻጮች ደግሞ በነበረው ችግር መድኃኒት ያዝ አድርገዋል። የግል ዘርፉን ደግሞ “መጥታችሁ እኛ ጋር አምርቱ” ስንል በወቅቱ እምብዛም ፍላጎት አልነበረም። ያ ጉዳይ የፈጠረው ቁጭት፤ መድኃኒት ላይ በበቂ አምርቶ የራሱን ፍጆታ የማይሸፍን ሀገር፣ ልብስ በበቂ አምርቶ የራሱን ፍጆታ የማይሸፍን ሀገር፣ ምግብ በራሱ አምርቶ የራሱን ፍጆታ የማይሸፍን ሀገር እንደ ሀገር ሉዓላዊ ሀገር ነኝ ብሎ መቀጠል አይችልም። ምግብ፣ ልብስና መድኃኒት በጣም መሰረታዊ ነው፤ መኪና ሊቀር ይችላል፣ አውሮፕላን ሊቀር ይችላል፣ ምግብ ግን ሊቀር አይችልም። እነዚህ ሶስቱ ላይ ጠንክረን እንሰራ የሚል እቅድ ነበረን፤ ልብስ በጣም ሰፊ ርቀት ተኪዷል፣ በምግብም የሚታወቅ ነው።

የመድኃኒትን ብቻ ብንወስድ ግን ያኔ የነበረው 8 በመቶ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ለሀገር ውስጥ የሚያስፈልጋትን መድኃኒት 44 በመቶ አምርታለች። በዚህ ዓመት ብቻ፣ በሚቀጥለው

ሳምንት ሁለት የሚመርቁ ፋብሪካዎች ስላሉ በዚህ ዓመት ከ50 እስከ 55 በመቶ እንደርሳለን። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የእኛ ፍላጎት በመድኃኒት፣ በክትባትም ጭምር ኢትዮጵያ ቢያንስ ለራሷ የሚያስፈልጋትን ፍጆታ ማምረት መቻል አለባት የሚል እምነት በመያዝ የተሰራ ስራ ነው።

አህሪ እንግዲህ ለረዥም ዓመት ነበር ይታወቃል፤ ግን ይሄ ያየነው ላብራቶሪ አልነበረም፤ ባለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት ሰፊ መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ ተደርጎ የተሰራ የሙከራ ክፍል ነው። የሙከራ ክፍሉ መነሻና እሳቤ መድኃኒት ለማምረት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ እውቀቶች አሉ፤ ይህ የምርምር ዕውቀት ከሌለ የሚመረተው መድኃኒት በቂ ፈውስ ላይሰጥ ይችላል። አንደኛው የሚያስፈልገው ነገር የጂን ነው። የአንድን ሰው የዘር መረጃ ቅደም-ተከተል ማወቅ የበሽታውን አይነት ለመለየት እና ለዛ በሽታ የሚገባውን መድኃኒት ለመወሰን ያግዛል። ይህ የሙከራ ክፍል ኢትዮጵያ ውስጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ እናያለን ብለን የማናስባቸው በጣም በርካታ አቅሞች ይዟል። ሮና ሲፈጠር አብዛኛው ሙከራ የሚሄድ የነበረው ወደ ደቡብ አፍሪካ ነበር። አሁን ሙሉ በሙሉ ለዘር መረጃ ቅደም-ተከተል የሚያስፈልጉ እውቀቶች በመሳሪያም በሰው ኃይልም እዚህ ቦታ ስለሚገኝ፣ ማንም መድኃኒት አምራች ሀገር ለኢትዮጵያውያን የሚያመርተውን መድኃኒት ከማምረቱ በፊት የእኛ የዘር መረጃ ቅደም-ተከተል ምን መልክ እንዳለው ለማወቅ በቂ መረጃ ማግኘት ይችላል።

ከዚያም በተጨማሪ ቅድም እንዳያችሁት ከሁለት ሚሊዮን ያላነሰ ናሙና መያዝ የሚችል የሙከራ ክፍል ገንብተዋል። ናሙና በጣም በጣም ወሳኝ ነገር ነው። ብዙ ናሙና ካለ በዛ የድግግሞሽ ጥናት ነው የአንድ ሰው በሽታ የሚለየውም፣ ለዛ ፈዋሽ መድኃኒት የሚፈጠረውም፤ ያንን ለማድረግ የሙከራ ክፍሉም የምርምር አቅሙም፣ የዘር መረጃ ቅደም-ተከተሉም በከፍተኛ ደረጃ የኢትዮጵያን መድኃኒት የማምረት፣ ክትባት የማምረት አቅም የሚያሳደግ ነው።

እንዳያችሁት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን የእንስሳት ለምሳሌ አይጥ በመጠቀም የቲቢ በሽታን የመለየት ሥራ ይሰራሉ። የምርምር ሂደቱ ሳይንስንም የሃገር ውስጥ አቅምንም ታሳቢ ያደረገ ነው። ይሄ ደግሞ ከነሱ የሙያ መስክ ወጥቶ ሌሎችም የሙያ መስኮችን ለማገዝ በእጅጉ የሚያግዝ ነገር ነው። ቅድም እንደሰማችሁት አይጦች ለበሽታ ልየታ ብቻ ሳይሆን በደንብ ከሰለጠኑ ለማዕድን ዘርፍም በጣም በጣም ጠቃሚ ናቸው። እነዚያን ነገር እያሳደግን ለመሄድ እንደዚህ ያለ በዕውቀት የደረጀ፣ በቴክኖሎጂ የደረጀ ለብዙዎቹ ምርቶች ግብዓት የሚሆን ተቋም በእጅጉ ያስፈልጋል።

ዛሬ አህሪ ላይ ያየነው ጅማሮ የሙከራ ክፍል ብቃት የሰው ኃይል የተነሳሱበት ደረጃ እና የተገኘው ውጤት በቀጣይ ዓመታት ልናሳካ ያሰብነውን፤ በመድኃኒት እራሳችን የቻልን ፍላጎታችን በተሟላ ለመከወን የሚያግዝ ነው። እንግዲህ ያኔ ብዙዎች ክትባት እናምርት አብረንም ከፈለጋችሁ በግልም ስንላቸው ኢትዮጵያ ለማምረት አትችልም ይሉ ነበር እንደዚህ ያለው ዕውቀት ስላልነበረ ማለት ነው፡፡ አሁን ግን ያ ነገር ታሪክም ይመስለኛል በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ክትባት ማምረትም የሚያስችል መሰረት ተሰርቷል፡፡ ክትባትም ኪኒንም እናመርታለን። በመድኃኒት እራሳችንን ከቻልን፤ በምግብ ራሳችንን ከቻልን፤ በልብስ ራሳችንን ከቻልን የተቀረው የሚከተል ስለሆነ የተሟላ ሉዓላዊነት ያረጋገጠች ሀገር ለማድረግ የሚያግዝ ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያ በጣም ዘግይታለች ይሄንን ነገር ለመስራት ይሁን እንጂ አሁን ያለንበት ደረጃም አጭር ጊዜ ስለሆነ ሙከራ የተደረገው ተስፋ ሰጪ ነው ፡፡ እንግዲህ ኮሮና ጣጣ ብቻ ሳይሆን እንደዚህ ያለውን ቁጭት፤ እንደዚህ ያለውን ዕውቀት፤ እንደዚህ ያለውን ሥራ በሃገራችን ለማስጀመርም እድል ሰጥቷል ማለት ነው፡፡ እና በድምሩ የተሰራው ሥራ በጤና ሚኒስቴር በአህሪ የሥራ አመራርና ተመራማሪዎች እዚ ቦታ ያየነው የሙከራ ክፍሉ ቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን ጽዳቱም የመሬት ገጽታውም እጅግ ማራኪ ስለሆነ ይህ ነገር እንዲቀጥል እንዲበረታ እና ለላቀ ውጤት እንድንበቃ አደራ ማለት እፈልጋለሁ ።

እንበርታ እንስራ ወደ ገበያ እናውጣው ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራ ዘልቃ አድጋ እንድትኖር ያለው መፍትሔ ጥረን ግረን መስራት ብቻ ነው። ጥረን ግረን ከሰራን አሁን ካለንበት መከራ አሁን ካለንበት ችግር መሻገር እንችላለን የሚል ሙሉ እምነት አለኝ በጣም በጣም ደስ ብሎኛል እናንተም እንኳን ደስ ያላችሁ በርቱ ተበራቱ ማለት እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ



አሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ

—ሚያዚያ 8፣ 2018ዓ.ም.

ክቡር ፕሬዚዳንት፣
ክቡራን እንግዶች፣
የሃይማኖት አባቶች፣ እናቶች፣ የኢተያ አካባቢ ነዋሪዎች
ከሁሉ አስቀድሜ እንዲህ ባለው መልክ ስራ ጨርሰን ለመገናኘት ለማስመረቅ ሪቫን ለመቁረጥ ስላበቃን እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እወዳለሁ።

አርሲ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቀው በመትጋት በመስራት እና ምግብ በማምረት ነው። የአርሲ ስንዴ የአርሲ ገብስ ለአርሲ ብቻ ሳይሆን ለኦሮሚያ ብቻ ሳይሆን ለድፍን ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ከፍተኛ አምራች በመሆን የኢትዮጵያን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት የተለየ ጥረት ከሚያደርጉ ቴክኖሎጂ ከሚወዱ በጋራ መስራት ከሚወዱ አካባቢዎች አንደኛውና ግንባር ቀደሙ አርሲ ነው። ነገር ግን አርሲ በስንዴ እና ገብስ ብቻ ሳይሆን በኃይል ዘርፍም ለከባቢ ብቻ ሳይሆን ለድፍን ኢትዮጵያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚያስችል የንፋስ ኃይል፣ በጂኦተርማልም ሁለት የጀመርናቸውን ፕሮጀክቶች እና ወደፊት የምንጀምራቸውን ጨምሮ አርሲ በኃይል ዘርፍ ልክ እንደ ስንዴ እና ገብስ ተጨማሪ የመልማት አቅም ያለው አካባቢ መሆኑን ማየት ችለናል። አርሲዎች በተፈጥሮ በመታደላችሁ በሰማይ በመወደዳችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እወዳለሁ።

ሁላችሁም እንደምታስታውሱት በለውጡ ማግስት ኢትዮጵያ የምታመርተው የኃይል መጠን 4000 ሜጋዋት ገደማ ሲሆን በገንዘብ ደረጃም 7 ቢሊየን ገደማ ገንዘብ ታስገባ ነበር። በዚያም ምክንያት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለስልጣን በከፍተኛ እዳ ውስጥ የነበረ ተቋም ነው፣ አብዛኛው የጀመራቸው ፕሮጀክቶች በጊዜው በታለመለት ገንዘብ መጠናቀቅ ባለመቻላቸው ተቋሙ ከሞላ ጎደል በእዳ የተዘፈቀ ነበር። በሰራነው ማሻሻያ ባለፉት ስድስት ሰባት ዓመታት 4000 ገደማ የነበረው ሜጋ ዋት ዛሬ ወደ 10ሺ ገደማ ሜጋ ዋት ማሳደግ ተችሏል፣ ከእጥፍ በላይ ማሳደግ ተችሏል።

7 ቢሊዮን ገደማ ያስገባ የነበረው ተቋም ከ75 ቢሊየን ብር በላይ ማስገባት ችሏል። በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለፉት ስድስት ወራት 7 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማስገባት ችሏል፣ ትርፍ የሚባል አያቅም ተቋሙ ከዚህ ቀደም። ትርፍ ማስገባት ችሏል ማለት የያዛቸውን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ተጨማሪ እድል አግኝቷል። አዳዲስ ስራ ለመጀመርም

እድል አግኝቷል ማለት ነው። በየተቋማቱ ገንዘብ እንዳይዘረፍ ፕሮጀክቶች ተጀምረው እንዲጠናቀቁ፣ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች እንዲሁ ለመጀመር ሳይሆን በአዋጭነት መስፈርት ተለክተው እንዲሆኑ በተሰራው ስራ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለስልጣን የተጀመረው ውጤት እጅግ አበረታች ነው።

ባለፉት አምስት፣ ስድስት ዓመታት አራተኛ ፕሮጀክት ስናስመረቅ ነው፣ በውሃ ኃይል ህዳሴን እና ገናሌ ዳዋን አስመርቀናል፤ በንፋስ አይሻን እና ዛሬ የአሰላ ንፋስ አስመርቀናል መጀመር ብቻ ሳይሆን መጨረስ የተለማመድንበት፣ መክሰር ብቻ ሳይሆን ማትረፍ የተለማመድንበት ስራ ነው። የአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በአዋጭነት ደረጃ ሲታይ የወጣው ወጪ 145 ሚሊዮን ዩሮ ገደማ ነው። ይሄንን ገንዘብ ምናልባት ቢበዛ በሁለት ዓመት ውስጥ መመለስ ይችላል፣ መዋዕለ-ነዋይ ስናፈስ ፣ ስንበደር በጥቂት ዓመታት ውስጥ መመለስ የሚያስችል ከሆነ ኪሳራ አይደለም፤ ስንበደር ወይም በእርዳታ መልክ ስንቀበል ገንዘቡ 100 በመቶ ስራ ላይ ውሎ ያንን ብድር መክፈል የማይችል ወይም የተራዘመ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ግን ወደ ልጆቻችን እዳ ይሸጋገራል። አሁን ይሄ ፕሮጀክት በሁለት ዓመት ቢበዛ ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ ከሁለት ዓመት በኋላ ትርፋማ ፕሮጀክት ስለሚሆን ልጆቻችን ትርፍ ሃብት የሚያገኙ እንጂ እዳ የሚረከቡ አይሆንም። በሁሉም ስራዎቻችን እንዲህ ያለውን ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ በመከተል በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

ከዚያም በተጨማሪ የዴንማርክ መንግሥት ምሳሌያዊ የሆነ ስራ ነው የሰራው። ብዙ ወዳጅ ሀገራት የዴንማርክን መንግሥት አርአያነት መከተል ይኖርባቸዋል። የዴንማርክ መንግሥት ግማሹን ማበረታቻ የተደረገበት ረዥም ጊዜ ብድር ምንም አይነት የአራጣ መልክ የሌለው ለመክፈል የማያስቸግር ብድር ሲሆን ግማሹን ግን በእርዳታ ነው የሰጠው በዚያ ምክንያት ይህ ፕሮጀክት የዴንማርክ መንግሥት ስጦታ ነው ቢባል ምንም የተጋነነ አይሆንም።

ብድሩም እርዳታውም የነበራቸው ክትትልም ምስጋና የሚገባው ስለሆነ ሌሎች ኢትዮጵያን ማገዝ ከኢትዮጵያ ጋር መስራት የኢትዮጵያ ብልጽግና አካል የኢትዮጵያ ድል አካል መሆን የምትፈልጉ ወዳጅ ሀገራት በዚሁ ማስተለፍ የምፈልገው መልእክት ለኢትዮጵያ 10 ብር ስታበድሩ ያ 10 ብር መቶ በመቶ ስራ ላይ መዋሉን በሚያረጋግጥ መንገድ ካላገዛችሁ የግለሰቦች ኪስ ያብጥ ይሆናል እንጂ የኢትዮጵያ ችግር አይቀረፍም። ባለፉት ዘመናት የነበረው የብድር ዋነኛው ችግር ወደዚህ የሚፈሰውና ወደ ውጭ የሚሸሸው እኩል መሆኑን። እኛ የተረፈን እዳው ነው፣ በተበደርነው ልክ ፕሮጀክቶች

አልቀው እዳቸውን መልሰው በዚህ ዘመን ትርፋማ መሆን ሲገባቸው እዳው እኛ ላይ ተጭኖ ገንዘቡ ግን አብዛኛው ሸሽቷል። ያ ልምምድ ሀገር ጎጂ ስለሆነ ከእንደዚህ ያለው የብድር የእርዳታ የፕሮጀክት አፈጻጸም መራቅ እንደ ሀገር በእጅጉ ያስፈልጋል።ለአሰላ ለአርሲ እና ለከባቢው ምስራቅ ሸዋን ጨምሮ ያለኝ መልእክት፤ አርሲ በእርሻ የታወቀ ነው፣ ነገር ግን በቂ መንገድ የለውም፣ ለምሳሌ ይህ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ብቻውን በግቢ ውስጥ በዚህ ከባቢ ከ27 ኪሎ ሜትር በላይ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሰርቷል።

ይሄ መንገድ ከአሁን በኋላ የሚሰራው ለኮምባይነር፣ ለትራክተር፣ ለእርሻ ማሽነሪ ጭምር ስለሆነ እዚህ የተመረተው ምርት ወደ ገበያ እንዲወጣ በቅርብ ርቀት የሚገኘው የክፍያ አውራ ጎዳና የክፍያ መንገድ ተጨምሮ ምርቶች ወደ ማዕከላዊ ገበያ ወጥተው አርሶ አደሩ በድካሙ ልክ እንዲጠቀም የሚያግዙ ይሆናሉ።

ተጨማሪ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪው በቅርብ ርቀት የሚገኝ ስለሆነ የእርሻ ውጤቶች ተመርተው እንዳሉ የሚሸጡ ሳይሆኑ ወደ ኢንዱስትሪ ገብተው ተቀነባብረው ከቅንብር በኋላ የሚመጣውን የእሴት ጭማሪ ተከትሎ የተሻለ ገቢ እንዲያስገቡ ስለሚያስችል ኢንዱስትሪውን ማስፋት፣ መንገድ ማስፋት፣ ኃይል ማስፋት፣ ግብርናን በማሽነሪ ማዘመን አርሶ አደሮች በአጠረ ጊዜ ከድህነት እንዲላቀቁ ያደርጋል።

ገቢ ደግሞ እያደገ ሲሄድ በገጠር የጀመርነው ኮሪደር የፀሐይ ብርሃን ኃይል፣ የኃይል ከተፈጥሮ ጋዝ የሚገኝ ኃይል የእናቶችን ድካም የሚያቀል፣ ብርሃን የሚሰጥ፣ በዐይን ላይ የሚያጋጥመውን በሽታ የሚከላከል፣ የኑሮ ዘዬን የሚያሻሽል ስለሆነ፤ ቅድም ከገለጽኩት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከሚመረተው ኃይል በተጨማሪ በየገጠሩ በሚሰፋፉ ከዋናው መስመር ውጭ ሶላሮች ብዙ ኃይል ስለሚመረት፣ የኃይል ፍላጎታችንን ለማሳካት የዜጎቻችንን ህይወት ለማሻሻል በጥቅሉ በርከት ያሉ ፕሮጀክቶች ጀምረናል፤ ሁሉም ስራዎቻችን ከሞላ ጎደል እያለቁ ይገኛሉ፤ በከፍተኛ ክትትል የጀመርናቸውን ስራዎች በማጠናቀቅ ለኢትዮጵያ ብልጽግና መሰረት መጣል እንቀጥላለን።

የኢትዮጵያን ብልጽግና ስራ ሳንጨርስ ያያችሁ፣ ያመናችሁ፣ የተባበራችሁ፣ አብራችሁን የቆማችሁ እንኳን ደስ አላችሁ! ሰርተን ጨርሰን ማየት ስለቻላችሁ። ስራ ስንጀምር ጨርሰን ማስተንፈሻ ሪባን ስንቆርጥ ያላመናችሁ የእኛ ጸሎት እድሜ ይስጣችሁ፤ ደጋግመን ደጋግመን እናሳያችኋለን! እኛ ደጋግመን መፈጸም አናቆምም፣ እናንተም ደጋግማችሁ ማየት እንድትችሉ ጤና እንመኝላችኋለን! የጀመርነው የብልጽግና ጉዞ በየትኛውም

አይነት ጩኸት እንዳይናወጥ በደም መሰረት ያቆምነው ስለሆነ፤ በብዙ ውጣ ውረድ፣ በብዙ ስቃይ፣ በብዙ ችግር ያለፈ ስለሆነ አሁን ትናንሽ እዚህ ከተከልናቸው ፋርሞች/እርሻዎች የአንዱን ያክል ንፋስ የማያንቀሳቅሱ አጀንዳዎች የሚያውኩን ሰዎች አይደለንም። የምናደርገውን እናውቃለን፣ የምናደርገው የህዝባችን ሕይወት እስኪለወጥ በሙሉ ልብ፣ በሙሉ አቅም ስራችንን እንሰራለን፤ ሊያደናቅፈን የሚችል ማንኛውም እንቅፋት ካለ እንደ የትኛውም ጉዶ ነቅለን በመጣል እናልፋለን። ለዚህ ደግሞ ብቃት እንዳለን በተደጋጋሚ ስላሳየን ከዚህ በኋላም የሚሞከሩ ሙከራዎች ካሉ በዚያው መንገድ የሚቀጥል ይሆናል።

የጀመርነውን ልማት እንቀጥላለን፤ ግራ ቀኝ ሳንል በትኩረት በትብብር መንፈስ የልማት ጉዞአችንን እናስቀጥል፤ ከዚህ ውጪ ያለው አማራጭ የጥፋት የጉዳት አማራጭ ብቻ ነው። ዓለም እንደምታዩት በከፍተኛ መተራመስ ውስጥ ነው ያለችው፤ ምግቡን ያላመረተ፣ ተቋሞቹን ያላጠናከረ፣ ኃይል ያላዘጋጀ፣ በብቃት ራሱን ያላሰናዳ ሀገርና ህዝብ ይጠፋል፣ ይበተናል።

ያ እንዳይሆን በብዙ መልኩ አቅማችንን እያደራጀን በቅርብ ላሉ ጠላቶች ብቻ ሳይሆን፣ ከሩቅ ለሚሰነዘር ማንኛውም ሙከራም ኢትዮጵያ መከላከል እና እንደ ሀገር መጽናት እንድትችል ከፍተኛ ስራዎች እየተሰሩ ስለሆነ፤ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ዛሬም እንደ ትናንቱ ኢትዮጵያን ለመመገብ የምታደርጉት ጥረት ይበርታ፣ ይቀጥል፣ እንዳይቋረጥ። የነቃ፣ የተማረ፣ የሚያደርገውን የሚያውቅ፣ አርቆ ማየት የሚችል፣ የሚተጋ ትውልድ ለባርነት ስለማይጋለጥ፤ እኛ አባቶቻችን ባለፉበት መከራና ችግር ልጆቻችን እንዳያልፉ መሰረት ጥለን እንድናልፍ በጋራ እንድንቆም በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር። ብልጽግናችን ይቀጥላል፣ ኢትዮጵያ ትለመልማለች፣ ጠላቶቻችን ይረግፋሉ፣ እኛም እንቀጥላለን!

አመሰግናለሁ!



የቱሪዝም ጸጋ ለሀገር ብልጽግና

ሚያዚያ 11፣ 2018ዓ.ም

መንግሥት የጠራ ፖሊሲ ሲኖረው፣ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂው ያን ለመመገብ የሚያስችል ሲሆን፣ የማስፈጸም አቅም በተቋም እየገነባ ሲሄድ ምን ዓይነት ፍሬያማ ሥራ ሊሠራ እንደሚችል ኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች ያመላክታሉ። ያው እንደሚታወቀው አምስት ዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶ ብለን የለየናቸውን ዘርፎች ሁሉንም ብንመለከት ከፖሊሲ, ከስትራቴጂ እና ከአፈጻጸም አንጻር ከፍተኛ ውጤት እያስገኙ ይገኛሉ።

ለምሳሌ በግርድፉ ኢንዱስትሪን ብናነሳ፣ ከዚህ በፊት ኢንዱስትሪ ፓርኮች መንግሥት ይገነባ ነበር፤ አሁን ግን ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገነቡ የግል ዘርፍ መፍጠር ችለናል። በርካታ በሺ የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች፣ ኢንዱስትሪያል ፓርኮች፣ ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎች መሥራት ስንጀምር በሀገር ውስጥ ከዚህ ቀደም ማምረት የማንችላቸውን፣ ከውጭ የምናስገባቸውን ምርቶች በበቂ ደረጃ በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ወደ ውጭ የምንልከውን ቁጥር ለማሳደግ በጅጉ አግዟል፤ ምላሽ አሳይቷል ኢንዱስትሪው።

ኢንዱስትሪ ብቻ ሳይሆን ግብርናንም ብንመለከት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ግብርና ይታወቃል ምን ዓይነት ችግር እንደነበረበት። በሚሊዮን የሚቆጠር አርሶ አደር በክላስተር ካደራጀን በኋላ ትራክተር፣ ኮምባይነር፣ ፓምፕ፣ የተለያዩ ማሽነሪዎችን ማቅረብ ስንችል የአነስተኛ አርሶ አደሮች በሚያርሷቸው ማሳዎች ላይ የሚገኘው ምርት እየጨመረ ሲሄድ የግል ዘርፉ በዚያው ልክ መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ ማድረግ ጀምሯል። ለምሳሌ ቡናን እንኳን ብንወስድ መቶ ሺ ሄክታር ገደማ መሬት የግል ዘርፉ ወስዷል። መቶ ሺውን በመስኖ ከሠሩ የምናመርተውን ግማሽ ያክል ሊያመርት ይችላል። የጥንቃቄና ጥራት እርሻ ፣ መስኖ በከፍተኛ ደረጃ የግል ዘርፉ ፍላጎት አድሮበት፣ ትርፋማ እንደሚያደርገው አምኖ እየሠራ ነው። በተለይ ፍራፍሬ ላይ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። ግብርናውም ምላሽ አሳይቶ በፍጆታችን ብቻ ሳይሆን በውጭ ንግድ ምርታችን የሚታይ ሆኗል።

በማዕድን ዘርፍ ስንወስድ ከዚህ ቀደም ማዕድን ኢትዮጵያ ውስጥ ሊጠራ የሚችል ሥራ አለ ለማለት ይከብዳል፣ የውጭ ንግድ ምርታችን ውስን ነው። አሁን ግን በወርቅ፣ በማዳበሪያ፣ በጋዝ፣ በሴራሚክ፣ በሲሚንቶ የግል ዘርፉ ጣልቃ ገብነት መንግሥት ዓይን ሲገልጥና ሲያመቻች ምን ሊያመጣ እንደሚችል ያሳያል። ሲሚንቶ ለምሳሌ ቦሌ ለሚን

ብንወስድ ትልቁን የሲሚንቶ ፋብሪካ የገነባነው በግል ነው። በቅርቡ ምናልባት በወር በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ትልቁን የወርቅ ፋብሪካ እናስመርቃለን። የማዳበሪያ ፋብሪካችን እየሄደ ያለበት ጉዞ ይታወቃል፤ በጣም በፍጥነት እየተሠራ ነው ያለው። ካልነውም ጊዜ ፈጥነን ልንጨርስ እንደምንችል እንጠብቃለን። በጋዝ ያለን ሥራ ይታወቃል። እና የማዕድን ዘርፍ በፖሊሲ ላይ ባስቀመጥነው ልክ ምላሽ ማሳየት መጀመሩን በውጭ ንግድ ምርት ውጤታችን ይታያል።

ቴክኖሎጂ ብንወስድ ሞባይል ማስፋት፣ መረጃ ማስፋት ብቻ አይደለም፤ በቴሌኮም ብቻ የነበረውን ሌላ የግል ዘርፍ ሳፋሪኮምን ስናመጣ፣ ውድድር ሲፈጠር, የዳታ ስርጭት ስርገት ሲያድግ፣ እነ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ሲጨመሩ፣ እነ መሶብ ሲጨመሩ፣ እነ አምስት ሚሊዮን ኮደርስ ሲጨመሩ ቴክኖሎጂው በደንብ ምላሽ እያሳየ ኢኮኖሚያችን የሚያነቃቃና የሚያስተሳስር እየሆነ ነው የመጣው።

ከነዚህ ጋር እንግዲህ አምስተኛው ቱሪዝም ነው። ቱሪዝም ሁላችሁም እንደምታስታውሱት ኢትዮጵያ ታሪክ አላት፣ ኢትዮጵያ ባህል አላት፤ ያንን ለማሳየት የሚያስችል ምቹ መሠረተ-ልማት ግን አልነበራትም። ያንን እንቀይር የሚል ሐሳብ ነበረ። በገበታ ለሀገር፣ በገበታ ለሸገር፣ በገበታ ለትውልድ የሠራናቸው ሥራዎች ባለሀብት አስተባብረን፣ በመንግሥት በጀት በመንግሥት ሀብት ሳይሆን የቱሪዝም ዘርፉን ዓይን ገልጠን አስተምረን ግል ዘርፍ እንዲገባ ማድረግ አለብን የሚል ነበረ።

ወንጪን በገበታ ሠራን፤ ደንዲን የግል ሠራው። ሱማሌ ላይ ሸበሌ ላይ በገበታ ሠራን፤ ከጎኑ የግል ገባ። በይኑናን ሠራን፤ አዋሽ የግል ገባ። አርባ ምንጭ ሠራን የግል ባለሀብቶች ገቡ። ጂማ የግል ገባ ከገበታ ጎን። ሚዛን ተፈሪ እንደምታውቁት ከዚህ ቀደም እነዚህ ሁሉ የግል ዘርፎች ምን እጅ እግራቸውን ያዛቸው የተባለ እንደሆነ በግልጽ ስትራቴጂ የሚደገፉ መሆን ስላልቻሉ ነው፤ አሁን በጣም በስፋት ሥራ ጀምረዋል። ለዚህ ለዓለም-አቀፉ የአየር ንብረት ጉባኤ (ኮፕ32) እንኳን ስንወያይ አሁን 20 ሺ ገደማ ያለው የአልጋ የማስተናገድ አቅማችን እንግዳ መቀበል ወደ 80 ሺ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እየተሠሩ ነው፤ በጣም ትልቅ ሥራ ነው። ከዚህ ላይ እንግዲህ ኤርፖርቱ፣ መንገዱ፣ ኃይሉ እየተጨማመረ ሲሄድ እየመገበው ሲሄድ መላው ፖሊሲውን በከፍተኛ ደረጃ አጉልቶ ያሳያል።

አሁን የምንገኘው ደንዲ ሎጅ ነው። ከወንጪ 10-13 ኪሎ ሜትር ገደማ ራቅ ይላል፤ በጣም በጣም የሚያምር መልክዓ ምድር ነው። የሚያምር መልክዓ ምድር መሆኑ

ብቻ ግን አይደለም። በጣም የሚደንቀው ይሄ ወንጪ, ደንዲ, ወሊሶ የሚባለው እዚህ በ30-40 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ውስጥ ያለ አካባቢ ታሪካዊ አካባቢ ነው። ኢትዮጵያን እንደ ኢትዮጵያ እየሠሩ፣ ኢትዮጵያን እንደ ኢትዮጵያ ያቆሙ፣ ለኢትዮጵያ ደማቸውን ያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱ፣ የጀግንነት ልክ የሆኑ፣ የኢትዮጵያዊነት ልክ የሆኑ፣ የኢትዮጵያዊነት መግለጫ የሆኑ ጀግኖች የፈሩበት አካባቢ ነው። ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያ ጀግኖች መነሀሪያ ቢባል ምንም አያሳፍርም።

ለምሳሌ የመጀመሪያው መከላከያ ሚኒስትር ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) ሀገራቸው እዚህ ነው። የመጀመሪያውን የዐድዋ ውጊያ ላይ ጦሩን የመራው የጦር ኢታማዦር ሹም ገበየሁ ጉርሙ ሀገራቸው እዚህ ነው። ገበየሁ ሲሞት የተካው ባልቻ ሳፎ (አባ ነፍሶ) ሀገራቸው እዚህ ነው። በኋላ የምናውቃቸው እነ ሙሉጌታ ቡሊ፣ እነ ጃጋማ ኬሎ ሀገራቸው እዚህ ነው። ሙሉጌታ ቡሊ ሆለታ ላይ መታሰቢያ ማሠልጠኛ ተቋም ያለው ማለት ነው። እነ ከበደ ቡዙነሽ ጣሊያንን በማሰቃየት የሚታወቁ፣ እነ ገረሱ ዱኪ የብዙ ጀግኖች መፍለቂያ ነው። ኢትዮጵያ ስንል ደምና አጥንታቸውን ከስክሰው እየሠሩ አባቶቻችን መነሀሪያ ይሄ ነው።

ይህንን ታሪክ፣ ይህንን እውነታ መግለጥና ማሳየት የምንችለው እንደዚህ ያሉ ቦታዎች አብረው ሲገለጡ ነው። ሰው እዚህ ሲመጣ የሀብተ ጊዮርጊስ አባ መላ ሀገር፣ የባልቻ አባ ነፍሶ ሀገር፣ የገረሱ ዱኪ ሀገር፣ የከበደ ቡዙነሽ ሀገር እያለ ታሪካቸውን እየመነዘረ ጠላትን ወራሪን እንዴት አሸመድምደው የኢትዮጵያን ነጻነት እንዳስጠበቁና ኢትዮጵያ የምትል ሀገር ስትሸጋገር ቆይታ እኛ ጋር እንደደረሰች፣ የእኛም ኃላፊነት እነሱን መስሎ እነሱን ተከተሎ ማሸጋገር እንደሆነ ለማሳየት ለመግለጥ ያግዛል።

እንግዲህ ደንዲ እንደምትመለከቱት በጣም በተፈጥሮ የበለጸገ የሚያምር ቦታ ነው። ያ ታሪክ አለው፣ ተፈጥሮ አለው፤ ይሄንን ግን የሚመግብ ነገር አልነበረውም። የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት ወንጪ ደንዲ መምጣት አስቸጋሪ ነው። መንገድ የለም፣ መብራት የለም፣ ቴሌኮሙኒኬሽን የለም፤ እኔ እንኳን ስመጣ አልነበረም። ዛሬ ግን ከአዲስ አበባ አምቦ ብቻ ከአምቦ ወንጪ፣ ከወንጪ ደንዲ ብቻ አይደለም፤ ከአስጎሪ ደንዲ መንገድ እየተጠናቀቀ ነው ያለው፣ ከወሊሶ ወንጪ ደንዲ መንገድ በሙሉ ለማለት ይቻላል አልቋል። ስለዚህ በወሊሶ በኩልም በአምቦ በኩልም መምጣት ቢፈልግ የሚያስቸል ነገር አለ። መንገዱን ሠርተናል, መብራት አስገብተናል, ቴክኖሎጂም አምጥተናል፤ እንደዚህ ያለ ያማረ ሪዞርት በመንግሥት አስተባባሪነትም በግል ዘርፍም ተሠርቷል። ይሄንን አይቶ ከአዲስ አበባ በአንድ ሰዓት አንድ ሰዓት ተኩል ቢበዛ ሁለት ሰዓት መጥቶ መስተናገድ የሚቻልበትን

እንደዚህ ያለውን ቦታ ማንም ሰው ማምለጥ ማድረግ አይፈልግም። በነገራችን ላይ ከአዲስ አበባ መነሻ አድርጎ ወደ አምስቱም በሮች መቶ መቶ ኪሎ ሜትር፤ ወደ አዳማ ይታወቃል ፈጣን መንገድ አለ። ለምሳሌ ወደ አምቦ የቀደመው መንገድ እንዳለ ሆኖ ሌላ መንትያ መንገድ እየሠራን ነው። ስንጨርስ አንዱ መሄጃ አንዱ መምጫ ይሆናል፤ መሀል ላይ ተክለን ፈጣን መንገድ እንለዋለን።

ወደ ደብረ ብርሃን አንድ መንገድ እየጨመርን ነው፤ አንዱ መሄጃ አንዱ መምጫ ነው። ወደ ፊቼ፣ ወደ ወሊሶም አለ በአምስቱም በር። ለምን? አዲስ አበባን ማዕከል አድርጎ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ስላለ፣ በእነዚህ አማራጭ መንገድ መቶ መቶ ኪሎ ሜትር ሠርተን፣ እነሱ ደግሞ ውጤት ሲያመጡ ደግሞ መቶ መቶ እየጨመርን ለማዳረስ ማለት ነው። በዚህ ምክንያት በይኑና እና አዋሽ የሠራነውም ሥራ፣ ፈጣን መንገዱ ወደዚህም የሚሠራው ቀደም ባልኩት ሐሳብ በወሊሶም ይሁን በአምቦ በሁሉም አቅጣጫ ሰው ከአዲስ አበባ ሳምንቱን እረፍት ቀናት እየወጣ በእንዲህ ባለው ነፋሻ አየር፣ በጣም በሚያምር ለዓይን ታይቶ የማይጠገብ አካባቢ ላይ ሊዝናና ይችላል።

ብዙ ሰዎች የእኛን ሥራ በቱሪዝም ለመለካት ይሞክራሉ። እንደዚህ መሳሳት ጥሩ አይደለም፤ ፖሊሲዎቻችንንና ስትራቴጂዎቻችንን በደንብ ማየት ጠቃሚ ነው። የእኛም ቢቀር ግን ዛሬ የዓለም ባንክ እና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባ ዋሽንግተን ላይ እያደረገ ነው ያለው፤ እና የዚህን ዓመት የዕድገት ግምት አውጥቷል። በአፍሪካ ውስጥ ቁጥር አንድ ከፍተኛ ዕድገት ያላት ሀገር ኢትዮጵያ ናት፤ ከፍተኛ ቁጥር አንድ። በምን መጣ ሲባል፤ በቱሪዝም በሠራነው ሥራ፣ በግብርና በሠራነው ሥራ፣ በኃይል በሠራነው ሥራ፣ በቴክኖሎጂ በሠራነው ሥራ፣ በማዕድን በሠራነው ሥራ በድምር ውጤት ነው ይሄ ነገር የመጣው። ከአፍሪካ በእነሱ ግምት ከዘጠኝ በመቶ በላይ ዕድገት የምታረጋግጥ ብቸኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ናት፤ እኛ ከዚህም በላይ እንጠብቃለን፣ ሲደርስ የምናየው ይሆናል። ይህ ግን የመጣው ግልጽ ያለ ስትራቴጂ ኖሮን፣ የት ጋር ምን እንደምናደርግ አውቀን፣ እንዴት ክትትል እንደሚደረግ ገብቶን በትጋት መሥራት ስለቻልን ነው። ኢትዮጵያ የምትሠራው በአባቶቻችን ደም ብቻ ሳይሆን በእኛም ላብ እንደሆነ ስለምናምን፤ አባቶቻችን በደም ሀገር ሠርተው አቆይተዋል፣ እኛ ደግሞ በላባችን ኢትዮጵያን መገንባት እንችላለን። ከዚህ ውጭ ያለው አማራጭና አካሄድ እምብዛም አዋጭ አይደለም።

እንግዲህ ከአባቶቻችን ሲያስፈልግ ተዋግቶ ነጻነትን መጠበቅ ተምረን እኛም በተግባር አሳይተናል። ከአባቶቻችን በብዛት ያላየነው ደግሞ በላብ፣ በደም፣ በፖሊሲ፣ በድካም ሀገር ሊገነባ ደግሞ እንደሚችል የነበረውን ውስንነት ማካካስ ተችሏል። ሲደመር

የኢትዮጵያ ብልጽግና ዓለም፣ አፍሪካ በሚያምነው ልክ እየተረጋገጠ ይገኛል። ይህንን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል። መሰልቸት አያስፈልግም፤ ለበለጠ ውጤት መትጋት እንጂ የእርካታ መንፈስ አያስፈልግም፤ ደግሞ ለማራከስ እንደሚሞክረውም እንዳልሆነ ከእቅዳችን አንጻር በጣም አርኪ ሥራ እየሠራን፣ ሕልማችንን የምንኖር፣ ሕልማችንን ገና የምንዘረጋ፣ ለልጆቻችን የምናሸጋግር፣ አስተማማኝ መሠረት ላይ ያለን ደግሞ በመሆኑ የበለጠ ኩራት፣ የበለጠ ተስፋ, የበለጠ መተማመን ይሰጠናል። እና እንደዚህ ያለው ሥራ ኢትዮጵያውያን ልባቸውንና አእምሯቸውን ሰብስበው በቀና መንገድ ወደ ፊት ለመራመድ በጋራ መቆም እንዳለባቸው በተደጋጋሚ እንደምናደርገው ዛሬም መልእክቴ ይሄው ነው።

እንደዚህ ዓይነት ሥራ ሲሠራ ቅናት ሊኖር ይችላል፣ መትጋት አለመፈለግ ሊኖር ይችላል፣ የገንዘብ ውስንነት ሊኖር ይችላል፤ ይህንን ነገር በአጠቃላይ ውጤቱን የመለካት አቅም ውስንነት ሊኖር ይችላል። እንደዚህ ያለውን ጉዳይ ራዕይ ያላቸው ሰዎች፣ ሥራውን የሚሠሩ ሰዎች ማየት ያለባቸው በእነሱ ልክ ነው። እና ማጠቃለያ እንዲሆነኝ እንደዚህ ያለውን ሥራ አጠቃለን ለማየትና ወደ ፊት ለመወንጨፍ የንስርና የቁራ ዝምድና ማየት ጠቃሚ ነው። ንስር በባሕሪው አርቆ የሚያይ፣ ብዙ ቀለማት የሚያይ፣ በከፍታ የሚበር፣ በከፍታ የሚመላለስ፣ ከከፍታውም በከፍተኛ ርቀት አይቶ፣ አልሞ፣ አድኖ መብላት የሚችል በጣም ብርቱ የብዙ ጀግንነት፣ የብዙ ብቃት መለኪያ ነው። ቁራ በአንጻሩ የቆሸሸ ቦታ የሚውል፣ በመጮህ በማልቀስ አካባቢ የሚበክል፣ ባለበት አካባቢ ላይ ከሚበላውም ከሚረጨውም የተነሣ ብዙ የሚቆሽሹ ነገሮች የሚታዩበት የአእዋፍ ዝርያ ነው።

ይሄ የአእዋፍ ዝርያ ከሌሎች የተለየ መንገድ ንስርን ሊፋለመው ይሞክራል፤ መቼ? ንስር መጥቶ መሬት በሚያርፍበት ሰዓት ቁራ ከላይ ያርፍበትና ንስሩን አንገቱ ላይ የመደብደብ፣ ለመናከስ የመሞከር፣ የመተናኮል ሥራ ይሠራል። ንስሩ ግን ቁራው ከላይ ተቀምጦ እየደበደበው ስለሆነ ምላሽ ልስጥ አይልም። “ምን እያደረግክ ነው?”ም አይለውም፤ “ሙከራህ ምንድነው?”ም አይለውም፤ ከቁራው ሰፈር በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ራሱ ሰፈር ይበራል። ከፍታን ለንስር፣ ዝቅታን ለቁራ አድርጎ ተፈጥሮ ስለሰጠችው ወደ ላይ እየወጡ በሄዱ ቁጥር ቁራው እንኳን ከላይ ሆኖ መደብደብ፣ እንኳን ከላይ መቀመጥ፣ ከፍታውን መቋቋም ስለማይችል መፈጥፈጥ ይጀምራል። ንስሩ ግን ምንም ነገር አይሠራም፤ በድግ ብሎ ወደ ከፍታው ነው የሚሄደው። እኛ እንደዚያ ነን፤ ወደ ከፍታችን እንበራለን፣ ሕልማችንን እናሳካለን፣ ጩኸቱንና ለቅሶውን ለቁራዎች እንተዋለን። በዚህ አግባብ የኢትዮጵያን ብልጽግና እናረጋግጣለን። ሰዎች የንስር እይታና ምልከታ ካላቸው በንስር ልክ ለመመላለስ ባዩትና በያዙት መንገድ ነው መጓዝ ያለባቸው። ያ ሲሆን ብልጽግና ማረጋገጥ ይቻላል።

በቱሪዝም ዘርፍ መቶ በመቶ ያቀድነውን አሳክተናል። መቶ በመቶ ከዚህም በላይ ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ዓለም አቀፍ ኩነት አምና እና ከአምና በፊት ከነበረው ይበልጣል። ቱሪዝም አድጓል፤ በአገር ውስጥም በዓለም አቀፍ ደረጃም ይቀጥላል። የዓለም-አቀፉን የአየር ንብረት ጉባኤን (ኮፕ32) ጨምሮ በጣም ሰፊ ዕድል ከፊታችን ስላለ በመበርታት፣ በመሥራት፣ በመልፋት፣ በውጤት፣ ተቋም በማጠናከር, አቅም በማጎልበት ወደ ፊት መጓዝን ብቻ ማሰብ ተገቢ ይሆናል።

እዚህ ቦታ ላይ ይህን ሥራ የሠሩ ዲዛይነሮች፣ የሥራ ተቋራጮች ፣ የተሳተፉ ሰዎች፣ መዋዕለ-ነዋይ ያፈሰሱ ሰዎች በሙሉ ምስጋና ይገባቸዋል። የአካባቢው ማኅበረሰብ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እወዳለሁ። በርትቶ፣ ተጠናክሮ ይህንን ሥራ በማስፋት የቱሪዝም ፍሰትን በማሳደግ እያንዳንዱን በነፍስ ወከፍ ገቢ ማሻሻል የሚችል ሥራ እንደምንሠራ ተስፋ አደርጋለሁ። እጅግ በጣም አስደሳች ውሎና ቆይታ ነው።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ሀሮ ደንዲ ሎጅ፣ አሮሚያ


addis.mesobcenter.et
Service

የመሶብ አንድ ማዕከል ተንቀሳቃሽ አውቶቡስ አገልግሎት ስራ ማስጀመሪያ

ሚያዝያ 14፣ 2018ዓ.ም

እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ዘመናት ካሉብን ማነቆዎች፣ ካሉብን ችግሮች፣ ካሉብን ድካሞች አንዱ በምንሰጣቸው አገልግሎቶች የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ ላይ መንግሥትም፣ የግል ኩባንያም፣ እያንዳንዱ ዜጋም የማጎበረሰባዊ አኗኗርና ባህል ለውጥ የሚያስፈልገው ዘርፍ ነው። አንድ ሰው ከፍሎ ታክሲ ለመገልገል፣ ወይም ከፍሎ ማኪያቶ ለመጠጣት፣ ወይም ከፍሎ መታወቂያ ለማውጣት በመንግሥትም ይሁን በግል የሚሰጠው አገልግሎት በቂ አይደለም። እንደ ባህል ከፍተኛ ለውጥ የሚያስፈልገው፣ ጣልቃ ገብነት የሚያስፈልገው አካባቢ አገልግሎት የምንሰጥበት ልክ ነው።

ይህንን ለማስተካከል ኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት አስርት ዓመታት መንግሥታት በተለይ የመንግሥት የሥራ ዘርፍ ማሻሻያ ማድረግ አለብን ብለው ሲናገሩ፣ ሲያሰለጥኑ፣ ሲሞካክሩ ነበር። የመንግሥት የሥራ ዘርፉን በሚፈለገው ልክ አሻሽለው ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ግን አልተቻለም። ያ የሆነበት ዋናው ምክንያት ለረጅም ጊዜ የቆየውን ተቋማዊ ባህል፣ ግለሰባዊ ባህል ቀይሮ፣ እጅ መንሻን ቀንሶ ወይም አስቀርቶ፣ ተገልጋይን አክብሮ፣ ስቆ አገልግሎት መስጠት ቀላል የሚባል ለውጥ የሚጠይቅ አይደለም።

እኛ በለውጡ የወሰናቸው አምስት የልማት ዋና ዋና ምሰሶ ያልናቸው፤ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድን አራቱ የሚታወቁ ሲሆን፣ አምስተኛው ግን ቴክኖሎጂ ነው። ቴክኖሎጂ ማዕድንን ምርታማነት ለማሳደግ፤ የግብርናን ምርታማነት ለማሳደግ፤ የኢንዱስትሪ ምርታማነት ለማሳደግ፤ እንዲሁም ቱሪዝም ላይ ያለውን ትስስርና የቅኝት ተደራሽነት ለማሳደግ ሁሉን የልማት ዘርፎች የሚያሳልጥልን አንዱ ዋናው ምሰሶ ቴክኖሎጂ ብለን ነበር፤ እያንዳንዱ ዘርፍ ውጤት አግኝተንበታል ቴሌኮም ላይ፣ የፋይናንስ ዘርፍ ላይ፤ እንደሚታወቀው ወደ አገልግሎት ሲመጣ ግን በጣም በቅርብ ጊዜ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ማዕከል ብዙ አገልግሎቶች መስጠት የጀመርነው፤ ቢበዛ ዓመት ገደማ ይመስለኛል ከጀመርን ስራውን።

በዚህ አንድ ዓመት የሥራ ጊዜ ውስጥ በአንድ ማዕከል የጀመርነውን ዛሬ 45 ገደማ ማዕከላት ደርሰናል። በዚህ ዓመት መጨረሻ እስከ መስከረም ከመቶ በላይ ማዕከላት ይጠናቀቃሉ፤ ቢሮ ተገንብቶላቸው፣ ሰው ሰልጥኖ፣ ሥርዓት ተጭኖላቸው ለማህበረሰቡ

አስተዋውቀን አገልግሎት የምናቀርብባቸውና ለሕዝብ የምናደርስባቸው ማዕከላት ማለት ነው። ባለፈው ዓመት ከአንድ ሚሊዮን ሰው በላይ አገልግሎት ተገልግሏል። 3ሺ ገደማ አገልግሎቶች አሁን መታወቂያ፣ የልደት የምስክር ወረቀት ፣ የንግድ ፈቃድ ፣ ፓስፖርት እንደሚባለው አይነት እያንዳንዱ ተቆጥሮ 3,000 ገደማ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ትስስር ከአንድ ማዕከል ይሰጣሉ።

ያ ግን እንደ ኢትዮጵያ ላለ ትልቅ ሀገር በቂ አይደለም መቶ ማዕከል፤ በተለይ እንደዚህ ያለው በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪ ያንን አገልግሎት ሙሉ በሙሉ የሚሰጥ፣ ግን የተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪ አገልግሎት ሲኖር፣ ችግር ያለበት አካባቢ ላይ ሰው ከሚመጣ ወደ ሰው ቀርበን ደግሞ አገልግሎቱን እናቀርባለን። በቴክኖሎጂ ትስስር ለምሳሌ፣ ኮልፌ በጣም መታወቂያ ማውጣት ካለ፣ ወይም ፓስፖርት ማውጣት ካለ፣ ብዙ ሰው ከኮልፌ ወደ ማዕከሉ ከሚሄድ፣ እኛ ወደ ማዕከሉ ሄደን፣ ቀድመን ችግሮቻቸውን ለይተን አውቀን ሄደን፣ በአንድ ቀን በሁለት ቀን የተወዘፈ ነገር መፍታት እንችላለን። ተንቀሳቃሽ የመሶብ አገልግሎት ይህኛውን አስጀመርን እንጂ በጣም ብዙ መኪናዎች እያዘጋጀን ነው ያለነው።

አዲስ አበባ ላይም ከአዲስ አበባ ውጪም በስፋት የምንሰራበት አሰራር ይሆናል። ነገር ግን አሰራሩን ትንሽ የተሻለ የሚያደርገው የምንጠቀመው የኤሌክትሪክ መኪና ነው። ወይም ጋዝ የሚጠቀም መኪና ነው። ኤሌክትሪክም ጋዝም በሀገር ውስጥ ስለምናመርት፣ እንደዚህ አሁን እንደምናየው አይነት የነዳጅ ችግር በሚያጋጥም መንገድ አንጠቀምም፤ በአብዛኛው ግን የኤሌክትሪክ ነው። ኤሌክትሪክ በመሆኑ ንጹሕ ኃይል ይጠቀማል።

የኢንተርኔት መረጃ ፍሰት ይጠቀማል፤ ውስጡ በቂ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሠረተ-ልማት አለው፣ ሥርዓት አለው። ሰው እየለመደ ሲሄድ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ሄደን፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር ሄደን፣ ገበያ ሰፈር ሄደን፣ ሰዎች ሰብሰብ ያሉበት አካባቢ ሄደን ሌላ ጉዳያቸውን እየፈጸሙ እግረመንገድ መታወቂያ ይወጣሉ። የገበያ አዳራሽ ሄደው እየገዙ እዚያው ፓስፖርት ያድሳሉ፤ የገበያ አዳራሽ ሄደው እየገዙ እዚያው ንግድ ፈቃዳቸውን ያድሳሉ ማለት ነው። ሕይወታቸውን ያቀልላቸዋል፤ የመሶብ አገልግሎት ኢትዮጵያ ውስጥ እያመጣ ያለው እርካታ በየጊዜው የሚነገር ስለሆነ እሱን አልደግመውም፤ ነገር ግን መስፋት አለበት፣ መለማመድ አለብን።

ከስልክ ሰው እነዚህን አገልግሎቶች ማግኘት አለበት፤ ከተንቀሳቃሽ መኪና ቀጥሎ ወደ ስልክ መግባት አለበት አገልግሎቱ ፤ በቀላሉ መገልገልም መቻል አለብን፤ ያ ደግሞ እንዲሆን ዲጂታል መታወቂያ ወሳኝ ነው፤ የምናገለግለውን ሰውዬ ካላወቅን፣ ለማን አገልግሎት እንደሚሰጥ ካላወቅን ጥፋትን ሊያስከትል ይችላል። ሰውየውን ካወቅነው ግን

የሚፈልገውንና የሚገባውን ነገር ለማቅረብ፤ ብድር ለመስጠት፤ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት፤ ንግድ እንዲሳለጥ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ፍላጎቶች ለማሟላት በከፍተኛ ደረጃ የሚያግዝ ነገር ነው፤ እና ይህ ትልቅ መሻሻልና ዕድገት ነው፤ በአፍሪካ ፈር ቀዳጅ የሚባል የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ሥራ ነው። ማንም ሰው ወደኛ የመሶብ ማዕከል፣ ወደ መሥሪያ ቤቶቹም አሁን ደግሞ ወደ መኪናውም ሄዶ እንዴት አገልግሎት ማሻሻያ እንደተደረገ፣ እንደተሻሻለ ማየትና መመስከር ይችላል።

እንደዚህ ያለው ሥር ነቀል ለውጥ የሚያመጡ ጣልቃ ገብነቶች ለምናስበው የብልጽግና ጉዞ በጣም ወሳኝ ናቸው። አገልግሎት ከታነቀ ብልጽግና ማረጋገጥ አይቻልም። አገልግሎቱ ሲፈታታ ሰው ከቤቱ ቢሮ የሚሄድበት ሰዓት አንድ ሰዓት ሲሆን እና 30 ደቂቃ ሲሆን አንድ አይደለም። እኛ የትራፊክ አስተዳደርና ቁጥጥር መንገድ አስፋፍተን ከእያንዳንዱ ዜጋ ነ0 ደቂቃ በቀን ብናተርፍለት፣ ነ0 ደቂቃ ስጦታ ሰጠነው ማለት ነው፤ ሰውየው በሕይወቱ ላይ የሚባክን ነ0 ደቂቃ ሰጠነው ማለት ነው። በገንዘብ ቢለካ ብዙ ሊሆን ይችላል፤ ያቺን አሥር ደቂቃ ተጠቅሞ መነገድ፣ ማትረፍ, ማረፍ፣ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችላል፤ ሲደመር ደግሞ ብዙ ቀናት ይሆናሉ። በዚህ አግባብ የሰውን አገልግሎት የሚያገኝበትን ጊዜ ማሳጠር፣ አገልግሎቱን አውቆ በቀለለ መንገድ እንዲያገኝ ማድረግ፣ ንግድ እንዲያሳልጥ ማድረግ እንደ ሀገር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ጉዳይ ነው። የመንግሥት የሥራ ዘርፍ ማሻሻያ ማካሄዳችን፤ ስትራቴጂውን ካወጣን፣ አመራር ካሰለጠን፣ ሥርዓት ካደራጀን በኋላ እየሄድንበት ያለው ሂደት በጣም በጣም ደስ የሚል ነው።

ቴክኖሎጂ ምላሽ እየሰጠ ነው በሁሉም ዘርፍ፣ በተለይ አገልግሎት ላይ እየመጣ ያለውን ለውጥ አፋጥነን በሚቀጥሉት ሁለት ሦስት ዓመታት በተሟላ መንገድ ሰዎቻችን ከያሉበት ስፍራ ሆነው አገልግሎት የሚያገኙበትን ነገር ለማምጣት ጥረት ይደረጋል። በአንድ ዓመት የሥራ ውስጥ ግን ሁለት ሺም ገደማ አገልግሎቶች ከ45 ያላነሱ ማዕከላት፣ አሁን ደግሞ ተንቀሳቃሽ መኪናዎችን ማስፋት በጣም በጣም ምሳሌ የሚባል ሥራ ነው። ይህንን እንግዲህ የሚያውቀው ያውቀዋል፤ በጣም አስቸጋሪ፣ አታካች፣ ለመፈጸም አደገኛ የሆነ አሠራር ነው፣ ቀላል አይደለም፤ ከነበርንበት ባህል፣ ከነበርንበት ልምምድ፣ ከነበርንበት የአሠራር ዘይቤ ወጥቶ አዲስ ነገር መለማመድ ቀላል ነገር አይደለም፣ የባህል ለውጥ ይፈልጋል፤ እና እየመጣ ያለው ለውጥ በጣም በጣም ተስፋ የሚሰጥ ነው።

ዜጎቻችን አገልግሎቱን በደንብ ማወቅ አለባቸው፣ መገልገል አለባቸው፣ ማትረፍ አለባቸው፤ ከአገልግሎቱ በሚገኝ ትሩፋት ደግሞ የሀገር ዕድገት ውስጥ ግብዓት ሆኖ ማገልገል አለበት፤ በዚህ መንገድ በተሳሰረና በተሰናሰለ አካሄድና ስልት የኢትዮጵያን

ብልጽግናን ለማረጋገጥ የጀመርነውን እጅግ አስደሳች፣ ተስፋ ሰጪ፣ አመርቂ ሥራ በሁሉም ዘርፍ ታይቶና ተሰምቶ በማይወቅ ልክ ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ አመርቂ ጉዳዮች እየመጡ ስለሆነ፤ እሱን በሚያፋጥን እና በሚያሰናስል፣ የተሟላ ብልጽግና በሚያረጋግጥ አግባብ የምንመራ፣ የምንሰራ ይሆናል።

ዛሬ ባየሁት ነገር በጣም በጣም ደስ ብሎኛል። ዜጎቻችን እንዲያዩና እንዲገለገሉ እመክራለሁ፤ እንዲሰፋና እንዲያድግ ደግሞ አመራሮች አሁንም አበክረው እንዲሰሩ አበረታታለሁ። በጣም ጥሩ ነገር ነው፣ በዚህ ይቀጥል፣ እንበርታ ማለት እፈልጋለሁ፤

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ

የቶዮ ሶላር ኢነርጂ ሁለተኛው ምዕራፍ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ሚያዝያ 17፤ 2018ዓ.ም

ክቡር አቶ ደስታ ሌዳሞ የክልላችን ርዕሰ መስተዳደር፣ ክቡራን ሚኒስትሮች፣ የኢንዱስትሪያል ፓርኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ የሀዋሳ ከተማ ነዋሪዎች፣ የዚህ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሠራተኞች በሙሉ፤ ለዚህ ታላቅ ቀን ኢትዮጵያ፣ ሀዋሳ ስለደረሰች እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እወዳለሁ!

ሁላችሁም እንደምታውቁት ከዚህ ቀደም ወደ ሀዋሳ የሚመጣበት ዋናው ምክንያት፤ ሀዋሳ ውብ ስለሆነች፣ ሕዝቧ ሰላም ወዳድ፣ ፍቅር የተሞላ፣ ፍቅር የሚሰጥ ስለሆነ፣ አሳ በቀላሉ ከሀዋሳ ሐይቅ ወጥቶ የሚበላበት፣ ቡርሰሜ የሚገኝበት፣ ቅቤ ያማረው መጥቶ ቡርሰሜን የሚቀምስበት፣ ጨኮ የሚበላበት፣ የእግር ጉዞ ሲደረግ በጣም ነፋሻማ የሚያምር የአየር ጠባይ ስላለ፣ በከባቢው ማኅበረሰብ ልማድና ባህል ሁል ጊዜም ወደ ሀዋሳ ሰው ደስታን፣ ሰላምን, ፍቅርን እና ቅድም የጠቀስኳቸውን የምግብ ዓይነቶች ለመቅመስ፣ ለመዝናናት፣ ለመደሰት ይመጣ ነበረ። ዛሬ ግን ያ ታሪክ አዲስ ታሪክ አክሏል፤ ጨምሯል። ሀዋሳ የውበት፣ የአሳ፣ የቡርሰሜ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካ ብርሃን የሚያመነጭ የሶላር ሴል በብዛት የሚመረትባት፣ ትልቁ የሶላር ሴል በአፍሪካ የሚመረትባት ከተማ ሆናለች። ለዚህም ሀዋሳዎች እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከጥቂት ዓመታት በፊት ይህ ፓርክ የጨርቃጨርቅ ምርት የሚመረትበት የነበረ ቢሆንም፣ በመሃል በገጠመን መንገራገጭ ከአሜሪካ ነፃ የንግድ ዕድል ሲነሳ ብዙዎች ኢንዱስትሪዎች ለቀው ወጥተው ይህ ፓርክ ሙሉ በሙሉ ለማለት ይቻላል አና ሆኖ ነበር፤ 90 በመቶ የማምረቻ ሼዶቻችን ሥራ አልነበራቸውም። ይህ አካሄድ አያዋጣም፤ ትምህርት ይወሰድበት፤ ዘርፈ-ብዙ ማድረግ አለብን፤ በአንድ ዘርፍ ላይ፣ በአንድ ገበያ ላይ የተንተራሰ አካሄድና ስልት ለኢትዮጵያ የሚያዋጣ መንገድ አይደለም ብለን ትምህርት ከወሰድን በኋላ፤ ምናልባት ዓመት ቢሆን ነው ወደ ቬትናም ሄደን ዋናና መሠረታዊ ባለሀብት በዚህ ዘርፍ ተለቅ ያለ ገንዘብ መዋዕለ-ነዋይ አፍስሰው በቀላሉ ገበያ ማምጣት የሚችሉ ሰዎች ለማምጣት ግብግ ያደረግነው። የዛሬ ዓመት ገደማ ቶዮን በቬትናም ጎብኝተን እንደዚህ ያለ ዘመናዊ ፋብሪካ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማየት በጣም በጣም ከፍተኛ ጉጉት አድሮብን ነበር።

ቶዮ መጥቶ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ሁለት ጊጋ ዋት ገደማ ሥራ ካስጀመረ በኋላ ራሱ

ቶዮ ወደ አራት ጊጋ ዋት ለማሳደግ ወሰነ። ሌሎች ሁለት ተጨማሪ ትላልቅ ኩባንያዎች ወደዚህ ኢንዱስትሪ ፓርክ መጥተው የፀሐይ ብርሃን ኃይል ለማምረት ወሰኑ። ዛሬ የምናስመርቃቸው ሦስቱ የፀሐይ ብርሃን ኃይል ማምረቻ ፋብሪካዎች ዘ.3 ጊጋ ዋት ኃይል ማምረት የሚያስችል የሶላር ሴል ያመርታሉ። ቅድም በነበረን ቆይታ የሀዋሳ የኮሪደር ልማት ስራ እያማረ ሀዋሳ ቦታ የጨመረ ስለሆነ፣ “ይሄ አይበቃንም፤ ተጨማሪ አራት ጊጋ ዋት በሁለት ምዕራፍ ለማምረት አዲስ ሥራ እንጀምራለን” ብለው ቃል በገቡት መሠረት ከጥቂት ወራት በኋላ ሀዋሳ ላይ የሚመረተው አጠቃላይ ቁጥር 15.3 ጊጋ ዋት ይሆናል።

ይህ ቁጥር ምን ማለት ነው? 15.3 ጊጋ ዋት ማለት ሕዳሴ በአፍሪካ ትልቁ ግድብ የሚያመርተውን አምስት ጊጋ ዋት ሦስት እጥፍ የበለጠ ማለት ነው። በእርግጥ ከሕዳሴ የምናገኘው ኃይል እና እዚህ የምናመርተው ሶላር ሴል አንድና ያው አይደሉም፤ ሶላር ሴል ኃይል ለማምረት ተጨማሪ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች አሉ። ቅድም በኦክስጅንና ናይትሮጂን ምርት እንዳየነው ለግብዓት የሚውሉ ተጨማሪ አስፈላጊ ጉዳዮች ስላሉ እነዚያን ለይተን ወደ ኋላ ከሚገናኙ መሠረታዊ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ሠርተን፣ ባትሪ በሀገር ውስጥ ማምረት ከቻልን፤ ሊትየም ስላለን የሶላር ፓኔል ማምረት ከቻልን፣ ሌሎች ግብዓት ከጨመርን፤ 100 በመቶ ኃይል ማምረት የሚችለውን አቅም በሀገራችን መፍጠር እንችላለን ማለት ነው።

እዚህ ብቻ ሳይሆን በደብረ ብርሃን ሦስት ጊጋ ዋት፣ በአዲስ አበባ ሁለት ጊጋ ዋት አስቀድሞ ሥራ የጀመሩ ስላሉ፣ በድምሩ በሚቀጥለው ዓመት ከ20.3 ጊጋ ዋት በላይ ኃይል ማምረት የሚያስችል የሶላር ሴል ኢትዮጵያ ውስጥ ይመረታል። ይሄ በድምር ሲታይ የሕዳሴን አራት እጥፍ ማለት ነው። ይህ የሆነው በአንድ ዓመት ውስጥ በሠራነው ሥራ ነው። የዛሬ ዓመት ቬትናም ስንሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሶላር ሴል አይመረትም፤ የእኛም ትኩረት የነበረው ጨርቃ ጨርቅ ማምረት ላይ ነበር።

ጨርቃ ጨርቅ ስናመርት እናገኝ ከነበረው የውጭ ምንዛሬ ገበያ አንጻር፣ በሚቀጥለው ዓመት እነዚህ አምስት፤ እዚህ ያሉት፣ አራት እና ደብረ ብርሃንና አዲስ አበባ ያሉት ሲጨመሩ፤ ስድስት ፋብሪካዎች በድምሩ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለኢትዮጵያ ያስገባሉ። ይህ ደግሞ ከጨርቃ ጨርቅ ልናገኝ ከነበረው አራት አምስት እጥፍ ይበልጣል ማለት ነው። ስድስት ፋብሪካ ከነዚያ ሁሉ ፋብሪካዎች በላይ የውጭ ንግድ ግኝት ማስገኘት የቻለበት ዋናው ምክንያት ዘርፈ-ብዙ እናድርግ ብቻ ስላልን ሳይሆን፣ ወደሚቀጥለው የአመራረት ሥርዓት እንደግ ስላልን ነው።

በጨርቃ ጨርቅ ሁላችሁም እንደምታውቁት ከኛ የሚፈለገው ንጹሕ ኃይል እና የሰው ኃይል ነበር። ያ ፍላጎት በዚህኛው ዘርፍ ያለ ቢሆንም፣ በሶላር ሴል ምርት ግን እንዳያችሁት ኤን ታይፕ የሚባለው የአመራረት ዘይቤ ሙሉ በሙሉ በሰው-ሰራሽ አስተውሎት የታገዘ ራስ-ሰር የሮቦት የአመራረት ሥርዓት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንዱስትሪ በዚህ ንጽሕና፤ በሰው-ሰራሽ አስተውሎት ታግዘው በሮቦት ሲያመርቱ ማየት የመጀመሪያችን ነው። ይህንን በሶላር ሴል ያየነውን ቴክኖሎጂ የመጠቀም፣ ምርት የማሳለጥ፣ ጥራት የመጠበቅ ልምምድ፤ ኮምፒውተሮች ፣ ስልኮች ወደ ማምረት ካሳደግን፣ ሌላ ሀገር የምንቀናባቸውን የአመራረት ሥርዓት የተከተሉ፣ ሰው-ሰራሽ አስተውሎት የሚጠቀሙ፣ በአጭር ጊዜ ብዙ ምርት የሚያመርቱ እና ትልቅ ሀብት የሚያስገኙ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ እንቀላቀላለን ማለት ነው።

ሰው-ሰራሽ አስተውሎት የነገ የልጆቻችንን ዕጣ ፈንታ ይወስናል፤ ሰው-ሰራሽ አስተውሎት ላይ አበክረን እንሥራ ያን አካሄድ ከኢንዱስትሪ፣ ከማኑፋክቸሪንግ አንፃር፤ ቅድም እዚህ ባየናቸው ሦስት ፋብሪካዎች እንዳያችሁት ከሞላ ጎደል አብዛኛው ሥራ የሚሠራው በሮቦት ነው። ፈጣን፣ ጥራትና ጥንቃቄ የተሞሉ፣ የሚሄዱበትን ቦታ የሚያውቁ፣ የድምፅና የእንቅስቃሴ መለኪያ ያላቸው፣ የተሳለጠ የማምረት ሥርዓት የሚፈጽሙ፣ በከፍተኛ ደረጃ ምርትን የሚያሳድጉ፣ ዘመናዊነት የተላበሱ የማምረቻ ፋብሪካዎችን ማየት መቻላችን ለሀዋሳም ለኢትዮጵያም ትልቅ የምስራች ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እወዳለሁ። ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ 13 ወራት ፀሐይ ከሚገኙባቸው ጥቂት ሀገራት ብቸኛዋ ወይም የመጀመሪያዋ ተብላ ትጠራለች፤ ቢያንስ 300 ቀናት ፀሐይ አለን። ፀሐይ ካለን፣ ውድ ማዕድን፣ ሊትየም ካለን፣ ሶላር ሴል ማምረት ከጀመርን፤ በሀገር ውስጥ በብዙ መቶዎች የሚቆጠር ጊጋ ዋት ማምረት የሚያስችል አቅም አለን። በድፍን አፍሪካ ያለውን አቅምም ለማሳደግ እና በንጹሕ ኃይል ኢትዮጵያ፤ አፍሪካ መቅደም አለባቸው ብለን የምናልመውን ነገር በእጅጉ የሚያሳካ ስለሆነ፣ ይህ ልምምድ በዚህ ዘርፍ ሳይታጠር በሌሎች ዘርፎች ሰፍቶ፣ በቅርቡ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ አሰላ አስመርቀናል፤ ከዚያ ቀደም ብለን በውኃ ኃይል ሕዳሴ ተመርቋል፤ አሁን በሶላር ዘርፍ ደግሞ ከውጭ አስገብተን መሥራት ብቻ ሳይሆን ሴሉን ማምረት የሚያስችል አቅም ፈጥረናል።

እነዚህን በማቀናጀት ንጹሕ ኃይል በስፋት እያመረትን ከቀጠልን የኢትዮጵያ አምራችነት፣ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ሽግግር, የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ሀብት ግኝት ማሳደግ፣ ሥራ አጥነትን መቅረፍ በእጅጉ የሚሻሻል እና ለብልጽግናችን መሠረት የሚጥል ስለሆነ፤ በኢንዱስትሪ ረገድ የመጣው አጠቃላይ ውጤት እጅግ ተስፋ ሰጪ፤ የተቋቋመውም የኢንዱስትሪ ኮሚቴ የሠራቸው ሥራዎች እና የተገኙ ውጤቶች ተስፋ ሰጪ፤ በሚቀጥሉት

ጥቂት ዓመታት ምናልባት ኢንዱስትሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ግብርናን ተክቶ ከፍተኛውን የኢኮኖሚ ድርሻ የሚይዝበት እንደሚሆን አሁን ያሉ ምልክቶች ያሳያሉ። እስካሁን በነበረው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አንደኛ ደረጃ የያዘው አገልግሎት፣ ሁለተኛ የያዘው ግብርና ሲሆን፣ በሦስተኛ ደረጃ ነው ኢንዱስትሪ የነበረው። ይህ መዋቅራዊ ሽግግር በጥቂት ዓመታት የሚፈጸም ይመስለኛል። ያ በተሟላ መንገድ እንዲከናወን የአስተባባሪ ኮሚቴው፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን በቅንጅት እና በትብብር የጀመራችሁትን ሥራ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ ከወዲሁ አደራ እያልኩ፣ ሀዋሳ የብዙ ባለሀብቶች መሰባሰቢያ ቦታ ለመሆን የሚያስችሉ በርካታ መመዘኛዎች ታሟላለች። ከመመዘኛዎች ሁሉ የላቀው ደግሞ የሀዋሳ ከተማ የሲዳማ ክልል ነዋሪዎች የመጣውን ለማቀፍ፣ ሀብት ያመጣውን አብሮ ለመሥራት፣ አብሮ ለማደግ ያላቸው ዝግጁነት ስለሆነ፤ ሕዝባችን ሰላም ወዳድ፣ ሥራ ወዳድ፣ ሀብት እና ዕውቀት ይዞ የመጣን አቅፎ የማሠራት ልምምዳችሁ በዚሁ እንዲቀጥል፣ የውጭ ባለሀብቶች ሀዋሳ ከተማ ወጥተው ስልክ እንኳን ቢጥሉ ያሉበት ድረስ አምጥተን የምንሰጥ፣ ሰላም እንጂ ሌብነት የምንጠላ, ሠርተን የምናድግ ሰዎች መሆናችንን ኢትዮጵያን ወክላችሁ እዚህ ለመጡ በሺ ለሚቆጠሩ ባለሀብቶች እና ሠራተኞች ልታሳዩ ከአደራ ጭምር እያሳሰብኩ፤ የተጀመረው የኮሪደር ስራ ከወዲሁ ባለሀብት መሳብ ጀምሮ ለ፲ ጊጋ ዋት መጥተን “ተጨማሪ አራት ጊጋ ዋት እንሠራለን፣ እንደ ሀዋሳ ያለ ውብ ከተማ በዞርንባቸው ቦታዎች አላገኘንም” እያሉ ስለሆነ ይህ ጅምር ሥራ እንዲጠናከር፣ ሀዋሳን ከጫፍ ጫፍ እንዲነካ በይበልጥ ዛፍ እንድንተክል፣ አረንጓዴ እንድንሆን፣ ንጹሕ እንድንሆን፣ እዚህ ያለው ፍቅር እንዲሰፋ እንዲስፋፋ፣ ኢትዮጵያን እንዲወርስ እንድናደርግ, እንድንበረታ፣ እንድንሠራ፣ አርቀን እንድንመለከት፣ ያ የተመለከተውን ደግሞ ለመያዝ አበክረን የምንሮጥ የምንዘረጋ እንድንሆን አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

ባየሁት እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፤ እናንተም እንኳን ደስ ያላችሁ። እንደዚህ ያለው መልካም ሥራ ይቀጥል፤ ይበርታ። የኢትዮጵያ ብልጽግና ለልጆቻችን መልካም ሀገር የመተው ጅማሮ በአስተማማኝ መሠረት እንዲጣል በጋራ እንድንቆም አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ሀዋሳ



የማህበራዊ ልማት እመርታ ለሀገር ግንባታ ፎረም

ሚያዚያ 20፣ 2018 **ዓ.ም**

ክቡራን ሚንስትሮች፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ የእናንተን ዘርፍ ስራዎች በአሃዝ አስደግፋችሁ ለማሳየት የሄዳችሁበትን ርቀት አደንቃለሁ በጣም ጥሩ ገለጻ ነው የቀረበው እንደዚህ ያለ መረጃ ለህዝብ ያስፈልጋል፣ ህዝብ የማድመጥ የመግምገም፣ ቅድም ሲነሳ እንደነበረው “ንደለ፣ አነሰ” በሚለው ጉዳይ ላይ ሀሳብ እንዲሰነዝር እንዲህ ያለው የውይይት መድረክ በጣም ጠቃሚ ነው። ለዚህ ነው በፋይናንስ ዘርፍ፤ በዲሞክራሲ ተቋማት፤ በቴክኖሎጂ መሰል ውይይቶች ልማድ እየሆኑ መጥተዋል ኢትዮጵያ ውስጥ እና ቢጠናከር ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ።

የተነሱ ጥያቄዎች አንድ በአንድ አልመልስም ጊዜም የለም ሚኒስትሮች ለመመለስ ሞክረዋል። ግን እዚህ ያላችሁ ሰዎች ከዚህም ውጪ ያላችሁ ሰዎች የተወሰነ የመንግሥትን አተያይ እና አሰራር ለመገንዘብ እድል ይሰጣችሁ እንደሆነ የተወሰነ ሃሳብ ማንሳት እፈልጋለሁ። አንደኛው የማህበራዊ ዘርፍ ግንባታ ከሌሎች ዘርፍ ግንባታ በጣም የተለየ ነው፣ ህንጻ ስንገነባ ወደ ታች እንቆፍራለን መሰረት እናስቀምጣለን ሁለተኛ፣ ሶስተኛ፣ አራተኛ እያልን ስንሄድ ሰው ያየዋል ባጠረ ጊዜ ውስጥ ይታያል። ኢንዱስትሪም ስንገነባ የሚሳተፉ ተዋንያኖችም ሻል ያለ ዕውቀት ገንዘብ የገበያ ልምምድ ያላቸው ስለሆኑ ምርት ከወጣ በኋላ ምንም ድምጽ ሳይሰማ ወደ ሚፈልጉ ሰዎች ሊደርስ ይችላል።

የማህበራዊ ዘርፍ ግን በጣም አስቸጋሪ ነው። የአንዳንዶቻችሁ ጥያቄ የተሰራውን ስራ የተገኘውን ውጤት አይታችሁ “ይሄንን ካደረጉማ ምን ይሳናቸዋል” ብላችሁ እንደሆነ እገምታለሁ። ባይሳነን እና ብንሰራው እንኳን ግን የእናንተን ፍላጎት አያሟላም። የተስተካከለ ምግብ መመገብ እና የፈጣን ምግብ መመገብ ሁለቱም እድገት ውጥረት ያመጣሉ፤ ግን የፈጣን ምግብ እድገት ሰው የሚፈልገው ለጤና የሚመቸው አይነት እድገት አይደለም። በማህበራዊ ዘርፍ በመዋለ ህጻናት ላይ የምናደረገውን ኢንቨስትመንት በኔ እና በእናንተ እድሜ ውጤቱን ላናየው እንችላለን። በአንድ ምሽት ምላሽ የሚሰጥ ዘርፍ አይደለም።

ተደጋጋሚ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የተገነቡበት መንገድ ከኮንትራት ያለ አይደለም፤ ከኮንዶሚኒየም ግንባታ ያለፈ አይደለም የሚለውን ነገር ስናነሳ ሰው ፖለቲካ ይመስለዋል፤ ፖለቲካ አይደለም። መዋለ ህጻናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት ተገንብቷል፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የገነባናቸው ግን በምንም መስፈርት ከነበረው ጋር አንድ አይደሉም። እዚህ አዲስ አበባ እንኳን የቦሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚባለው ስንቶች የሚመጻድቁበት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቅርቡ ተቀይሮ አይታችሁት ከሆነ፣ ስሙ ከዝናው ጋር የማይመጥን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመቀየር የተሄደው ሂደት ከፍተኛ ሃብት፣ ከፍተኛ ድካም፣ ከፍተኛ ክትትል የሚጠይቅ ነው።

በኛም መዋለ ህጻናት መስተካከል ያለበት ነገር አለ፤ ቻይና ላይ መዋለ ህጻናት ይሰራሉ ዋና ስራዋ ግን ኤ፣ቢ፣ሲ፣ዲ ማስቆጠር አይደለም፣ ሽምደዳ አይደለም፤ ሰዎች ያቦካሉ፣ ይበላሉ፣ ያጥባሉ፣ ሲያቦኩ ይጣላሉ፣ አጥፊው ይቅርታ ይጠይቃል፣ በዳይ ይቅር ይላል። ይሄን እየተማሩ ያድጋሉ፤ ልጆች ሲገነቡ ይጣመማል አስተማሪ ያቃናለታል። በትምህርት ስርዓት ውስጥ ተግባራዊ አፈጻጸምን፣ የአፈጻጸም ኃይልን የማያቅ ማኅበረሰብ እንዲሁ ሲመኝ ይኖራል እንጂ መፈጸም አይችልም፤ ለመፈጸም ደሞ የሚሰሩ ስራዎች ከጅምሩ ከታች ይሆናሉ፤ እና በማህበራዊ ዘርፍ መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት፣ እነዚህ ክቡራን ሚኒስትሮች የሚያደርጓቸውን ጥረቶች፣ ማህበረሰቡ የሚያደርገውን ጥረት በአንድ ሌሊት ለውጥ የምንጠብቅ ከሆነ አይሳካም፤ ትውልድ መዘ ያነሳዋል ብለን የምናስብ ከሆነ ደግሞ ጊዜ ይፈታዋል። አሁን አንድ ቀላል ነገር ለማንሳት እኔ እና አደም፣ እኔና ብርሃኑ እኩል የሚያግባባን ነገር፤ እኔ ሃሳብ ባነሳ ያው እዛው እርግጫ ነው ማለት ነው፤ አደም እና ብርሃኑ ከቆረቆራቸው ካመማቸው ግን የሆነ ነገር ያላዩትን ነገር አይቻለሁ ማለት ነው። መስማማት የጥሩ ነገር ውጤት አይደለም፤ አርቆ ስንጠባበቅ ነገን ስንመለከት ዛሬ ላይ ያሉ ሰዎች አይመቻቸውም ፤ በየቀኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የምናየው ይሄንኑ ነው።

ወገኖቼ ልነግራችሁ ምፈልገው ነገር ኢትዮጵያ ከምታስቡት እና ከማስበው በላይ እየተገነባች ነው! ከምታስቡት እና ከማስበው በላይ፤ ተስፈኞች ስንሆን መልካም ነገር ማየት ስንጀምር የተነሱ ጥያቄዎች እዛ ውስጥ ምላሽ ያገኛሉ። ለምሳሌ ዓለም ላይ የነዳጅ ችግር አጋጥሟል፣ ሉፍታንዛ በረራ ቀንሷል፣ አንዳንድ አውሮፓ አገራት “15 ቀን 20 ቀን ከቀጠለ ሙሉ በሙሉ በረራ እናቆማለን” ብለዋል፤ የእናንተ አየር መንገድ እንዴት ነው መብረር የቻለው? ይሄን የሚጠይቅ ኢትዮጵያዊ አልሰማም፤ እኔ እንቅልፍ የለኝም እናንተ ግን ስትጠይቁ አልሰማም። “ተሰለፍን” ብቻ ነው ምትሉት። ተሰለፋችሁ እንጂ መኪና ኢትዮጵያ ውስጥ አልቆመም። ዛሬ እንቅስቃሴ አለ እንዴት ሆነ ይሄ ነገር? 100 በመቶ ተጨማሪ የነዳጅ ወጪ የኢትዮጵያ መንግሥት ይደጉማል ላለፉት አንድ ወር ሁለት ወር ገደማ 20 ቢሊዮን በወር፤ ያ ቢቀር ኖሮ ቅድም የተነሳው ጥያቄ ግማሹ ሊመለስ ይችላል። 27 ሚሊዮን ተረጂ የነበረበት ሀገር ሶስት ሚሊየን ገባ ሲባል እንደው እንደተራ ዜና

ነው እንዴ ሚሰማው? እንደዛ ነው? ለነገሩ “ዜሮም ገባ” ብንል “እንዴት ዜሮ ይገባል?” እንደምንባል እናቀዋለን። እውነቴን ነው የምነግራችሁ፣ የጋራ የሆነ እይታ፣ የተገለጠ እይታ፣ የማየት ብቃት ብዙዎቻችን ጋር ወደን ፈቅደን ስንተው፣ ስንዘል፣ ስንናልፍ ስለሚታይ፣ ይሄን ነገር ብናስተካክል እቺ ሀገር ትልቅ እድል አላት፤ ብንሰራ፣ ብንሮጥ፣ ብንለፋ ውጤት እናመጣለን።

አንዳንዱ ጉዳይ ተደጋግሞ የሚነገርበት ምክንያት ከሌላው ዘርፍ የተሻለ ቅድሚያ ስለሚሰጠው አይደለም፤ ካልተነገረ ውጤት ስለማያመጣ ነው፤ ኢንዱስትሪ የቱሪዝምን ያክል አልተናገርንለትም ምክንያቱም ሳሙና ከተመረተ ገበያ አያጣም፣ ቱሪዝም ግን በጣም መሸጥ መነገር አለበት፤ በኛ ደረጃ ያ ገብቶን ነው ምንናገረው እንጂ ቱሪዝም ከኢንዱስትሪ በልጦብን አይደለም፣ ከስንዴ በልጦብን አይደለም፤ “ስንዴ ስንዴ” ስንል “ስንዴ ምን ያረጋል” አላችሁ? ከኪነ-ጥበብ ጋር የተነሳው ጥያቄ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ሊመልስ እንደሞከረው ሙከራ አርገናል፣ በግልም ሙከራ አርጌያለሁ በቂ አይደለም እንሰራበታለን፤ ግን በቅርቡ እያያችሁ ከሆነ አላውቅም የውጭ ሀገር እንግዶች ኢትዮጵያ ሲመጡ ከዚህ ቀደም ከምናደርገው ልምምድ ትንሽ ወጣ ባለ መንገድ የሰርከስ ትዕይንት የኢትዮጵያ ኪነ-ጥበብ የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግቦች ከቀረቡ በኋላ መጨረሻ እንኳን ለሰዎች ስጦታ የምንሰጠው ኪነ-ጥበብ ነው፤ የፎቶአቸውን በቆዳ የሚሰሩ አንድ ሰው ብቻ እንዳልጠራ ብዬ ነው ብዙዎች ይኖራሉ ኪነ-ጥበብ ነው የምንሰጠው ለሰዎቹ “ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራ ከፍየል ቆዳ” እያልን ማለት ነው።

ኪነ-ጥበብ እንወዳለን፣ ኪነ-ጥበብ እናደንቃለን ኢንቨስት ማድረግ ባለብን ልክ አላደረግንም ይሆናል። ቅድም ብርሃኑ እንዳለው ውስንነት ስላለ እናሻሽላለን እንሞክራለን፤ ግን እንጦጦም እንደተባለው እዛው ስድስት ኪሎም እንደተባለው ሙከራዎች አሉ፤ በጣም የሚገርመው ነገር በሚሰራው የጫካ ሳተላይት ከተማ ዋናው እዚህ ከተማ ሆናችሁ የምታዩት ትልቁ ታላቅ ክብ አዳራሽ ግማሽ አካሉ የኪነ-ጥበብ ማሳያ ነው፤ እና ቅድም ሲነሳ ይገርመኝ ነበር እንኳን ለዛሬው፣ ለነገው እንኳን አስበን፣ ማሳያ አዳራሽ እያስቀመጥን ስለሆነ የፍላጎት ጉዳይ አይደለም፤ ባለሙያዎቹ አስደናቂ ጭንቅላት ያላቸው፣ የመፍጠር ብቃት ያላቸው፣ ልዩ ተሰጦ ያላቸው ሰዎች ናቸው፤ በዛ ልክ ደሞ ቀበጦች ናቸው፣ ይሄን ማወቅ አለባችሁ እናንተ ባህሪያቸው እንደዛ ነው፤ ኖርማል ሰው የሚመላለስበት መንገድ አይመላለሱም፣ ኖርማል ሰው የሚያስብበት መንገድ አያስቡም፤ እነሱ ለመፍጠር፣ እነሱ ለማሰብ፣ እነሱ ለመስራት አንዳንዴ እኛ ከምንሄድበት መንገድ ወጣ ያለ ስነ-ምህዳር ይፈልጋሉ። ያንን ማሟላት ለኢትዮጵያ ቀላል አይደለም።

ሶስና በአካል ያየሁሽ ዛሬ ነው ደስ ብሎኛል እኔም ስላየሁሽ፣ በጣም በጣም የምትገርም ሴት ናት፤ ሶስና በሰርከስ ላይ በጣም ብዙ ስራ ትሰራለች። ስራዎቿን አያለሁ ምትገነባውን ነገር እየሄድኩ አያለሁ አጋጣሚ ሆኖ በአካል አልተገናኘንም እኔም ደስ ብሎኛል በስራሽ በጣም በጣም ከሚደሰቱ ሰዎች አንዱ ነኝ ግን ፈጥነሽ ጨርሺ አንቺም አልጨረሽም ስራውን ማለት ነው። የጫካ የደቡብ በር ፊት ለፊት 70/80 ሄክታር መሬት በጣም በድሮ ቋንቋ ቁልፍ የሚባል ኪስ መሬት ሁለቱን ያዋልነው ለቡና ሙዚየም እና ለሉሲ ሙዚየም ነው፤ የቡና ሙዚየም ብቻ 20 ሄክታር በላይ ቦታ ነው የሚወስደው፤ የሉሲ ሙዚየም ያልነው ቅድም ጠያቂው ያነሱትን ዋናው ብሄራዊ ሙዚየም በቂ ቦታ ስለሌለው ለጊዜው ያለውን አድሰን እንስራ ብለን ነው፤ ግን ዋጋው በጣም ከባድ ስለሆነ ለጊዜው የንድፍ ቦታ አዘጋጅተናል። ስናገኝ ደግሞ በደንብ ቆንጆ ነገር ሰርተን የእናንተን ደስታ እናበዛለን ግን ቀላል ነገር አይደለም። ቀላል ስራ አይደለም።

ከጤና ቱሪዝም ጋር ተያይዞ የተነሳው ጥያቄ መቶ በመቶ ከኛ ፍላጎት፣ ከኛ ፖሊሲ፣ ከኛ እሳቤ ጋር የሚሄድ ነው። የዋጋን ጉዳይ አንስቷል ወንድሜ ግን ዋጋ ብቻ አልመስለኝም፣ በቅርቡ ፓርላማ በነበረኝ ቆይታ አንስቼ ነበር፣ የኢትዮጵያ ሃኪሞች በጥርስ ጥቂት ሊሆኑ ይችላሉ። ግን በጣም ምርጥ ሃኪሞች አሉ፣ የኢትዮጵያ ሃኪሞች በተለይ ስትሮክን በሚመለከት እነ ዶክተር ወንደወሰን ስንት የውጭ ሀገር ዜጋ እንደሚያድኑ ማመን አትችሉም። ብዙ ሞያተኞች አሉ፣ በአጥንት አንዳንዱ ለማምን ይከብዳል እኮ እጁ ተቆርጦ የተሰበረን ሰው ጠግኖ እጅ የሚቀጥሉ ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ግን ሃኪሞች አንድ ማወቅ ያለባችሁ ነገር አለ። ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን ጀግኖች በህይወት ሳሉ ለማድነቅና አብረን ለመስራት አልበቃንም ገና እኛ የምናደንቀው ሌላ ቦታ ስናይ ነው።

የወዳጅነት አደባባይ ኬንያ ቢሆን ኖሮ መቀመጫ አልነበረንም፣ ይሄ የእግረኛ መንገድ፣ ይሄ ኮሪደር ልማት ሌላ ቦታ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያውያን ብርቱዎች ነበር፣ እዚህ ሲሆን ግን ብዙ አያይም፣ የነደለ አይሞላም፣ አያደንቅም፣ አያበረታታም በአንጻሩ እንዲህ ስንገናኝ በጥያቄ ያጣድፈናል፣ እና በህክምናው ዘርፍ መቶ በመቶ ያልከው ትክክል ነው ግን ዋጋ ብቻ ሞያ ብቻ በቂ አይደለም። የእኛ የህክምና ጣቢያዎች የህክምና ሆስፒታሎች ለበሽተኛ አይሆኑም። በቀላል ቋንቋ ለበሽተኛ አይሆኑም። በሽተኛ ቅድም ከያኒ እንዳልኩት ነጭናጫ ነው። እና ሽታው አካባቢው አይመችም፣ አይመችም ይሄን በግልጽ ማወቅ እና መስራት አለብን። ለዚያ ነው ለማደስ ለማሻሻል የምሞክረው፣ ለምሳሌ ጫካ ከሙዚየሙ ቀጥሎ አንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ የሚባል ሆስፒታል ሰርተን ወደ ውጭ የሚወጡ ሰዎችን እናስቀር ብለን ዲዛይን ሰርተን ጨረታ ስናወጣ ለቤቱ ግንባታ ብቻ 300 ሚሊየን ዶላር ጠየቁ ለቤቱ ግንባታ ብቻ እቃውን ደሞ አስቡት ያ ሆስፒታል ቢሰራ ልክ እንደ

ክሊቭላንድ እንደሚባለው ደረጃ ነው ሰው ውጭ ሀገር ሄዶ ከመታከም ይድናል ግን ገንዘቡ መጀመሪያ የምናፈሰው መነሻ ኢንቨስትመንቱ ግን ቀላል አይደለም ያም ሆኖ ነው፣ እሱንም እንሰራዋለን፣ እያሻሻልን ለመሄድ እንሞክራለን።

ኖሯቸው ቢሰሩ ያ ቀዳሚ ፍላጎቴ ነው በቅርቡም በነበረኝ የሚዲያ ጊዜ ሰምታችሁ ከሆነ አላውቅም ለአንድ መድኃኒት አምራች ኩባንያ ብድር አልተሰጠም ብዬ እንዴት ብስጭት እንዳልኩ ሰምታችኋል እና ጤና በጣም በጣም ወሳኝ ነገር ነው፣ ጤናና ሰላም ካልጎደለ አይታወቅም ሲጎል ግን የጎደለባቸው ያውቁታል ያን ቀድሞ መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ የመንግሥት መሻት እንደሆነ ሃሳብህ ከኛ ጋር ይሄዳል፤ ጽዳት አንደኛ ሁለተኛ አገልግሎት መድኃኒት የለም ግን “አይዞህ” ብሎ ስቆ የሚሸኝ ሃኪም ካለ ግማሽ ፈወስ ነው፣ ምናልባት የጎደለ ነገር አለ አልጋ የለም ግን በተቀመጠበት በሽተኛውን አይታ አንድ ነርስ “አይዞህ ውኃ አመጣልሃለሁ” ካለችው ከሳቀች ቀላል ነገር አይደለም እኛ ደግሞ ሲፈጥረን ስቀን ማስተናገድ አይሆንልንም ታውቃላችሁ፤ አገልግሎት፣ ጽዳት፣ ብታዩ ጥሩ ነው ሃኪሞች ዋጋ ብቻ በቂ አይደለም ዋጋ ትክክል ነው ማስላት ብዙ መዋዕለ-ነዋይ ማፈስ አለብን የግል ዘርፉ የጀመረው ነገር አስደሳች ነው ብትበረቱ የምናስበውን ነገር በዛ ዘርፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ማምጣት እንችላለን ብዬ አስባለሁ።

አካል ጉዳተኞች በሚመለከት እውነት ነው እንሞክራለን ነገር ግን ለምሳሌ መነጽር በሰው ሰራሽ አስተውሎት የተደገፈ እኔ ራሴ በጣም ብዙ ለምኜ ያመጣኋቸው አሉ። ቀዳማዊት እመቤት መሸከርከሪያ ወንበር በጣም ብዙ ለምና ታመጣለች ቅድም የተነሳው የአጥንት መገጣጠሚያ ሆስፒታል ሙሉ ሃብቱን ለምነን ነው ያመጣነው በመንግሥት በጀት አይደለም፣ ሄደን አይተን ትክክል አይደለም በሚል። መሠረተ-ልማት ላይ እኛ ምንገነባቸው ሁሉም ተቋማት የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ እንዲያደርጉ ጥረት ይደረጋል መንገድ ጨምሮ ለአይነ ስውራንም ለሌሎቹም፤ ነገር ግን ካለው ፍላጎት አንጻር በቂ ስላልሆነ እንሰራበታለን ለምሳሌ የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ዳዉን ሲንድረም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰራው በመደመር መጽሃፍ ነው የዳውን ሲንድረም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመንግሥት ስላልቻልን በግል ከግል ፋውንዴሽን ጋር ከዲቦራ ፋውንዴሽን ጋር ለገጣፎ የገነባን እኛ ነን።

ሁለተኛ የአይነስውራን ትምህርት ቤት ቅድም በተደጋጋሚ ያነሱት አዲስ አበባ ያለው የአይነስውራን ትምህርት ቤት አንዱ ካላጋነንኩት 30 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይሰራል 30 በጣም ውድ ነው አንድ የአይነስውራን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መገንባትና አንድ መደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መገንባት አንድ እና ያው አይደለም።

መመገቢያው፣ ማደሪያው፣ መማሪያ ክፍሉ እዛው ጤና ጣቢያ ያለው ትምህርት ቤቱ ትንሽ ውድ ነው፤ እቃው ውድ ነው የተሰራበት መንገድ ውድ ነው፤ ለምነን አብዛኛውን የጎደለውን ሞልተን ተሞክሯል አሁን ተጨማሪ አራት አምስት ቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት ለመገንባት በምስራቅ በምዕራብ በሰሜን ተጀምሯል በተለይ የጎንደሩ እየተፋጠነ ነው ያለው የአይነስውራን ትምህርት ቤትም ፣ እንዲሁ ተሞክሯል።

ምናልባት ከሥራ ቅጥር ጋር ተያይዞ የሞከርንባቸው ቦታዎች አሉ መልሰን እንፈትሻለን ለምሳሌ በቅርቡ በኢሚግሬሽን ቢሮ ስትወጡ ስትገቡ ፓስፖርት የሚቀበሏችሁ ሰዎች የዕድገት እክል ጸባይ ተፈጥሮ ያላቸው ቢሆኑ ይሻላል ተብሎ በተለያየ መንገድ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ለማስገባት እንደተሞከረ አውቃለሁ እኔም ሂደቱን ስለማውቀው፣ ግን የሚጎድል ነገር ካለ እናያለን፣ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች ማለት በሽተኞች ማለት አይደለም፣ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ሰዎች ከጤናማ ሰው በተለየ የመፍጠር አቅም ያላቸውም ሰዎች ማለት ነው! የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች ዓለም ላይ የተፈጠረውን አብዛኛውን ትላልቅ ነገር የፈጠሩ ሰዎች ማለት ናቸው። ግን እነሱን ተረድተን እነሱን አግዘን ከነሱ ጋር ኖረን እነሱን አስተምረን የነሱን መሻት ለመመለስ እንዳነሳችሁት በትምህርትም በጤናም በመንግሥት ቤትም ገና ብዙ ስራ ይጠበቅብናል ሙከራዎቻችንን ግን ከተገነዘባችሁ በቂ ነው ሌላውን ሃላፊነት ወስደን ለማክል ለመስራት እንሞክራለን ምንም እንዳልሰራን ብቻ እንዳታስቡ። አብዛኛው ነገር በልመና ነው የሚሰራው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስራ የላቸውም እንዴ እንዴት፤ ለምነው የቱሪዝም መዳረሻ ይሰራሉ እኔም ግራ ይገባኛል በነገራችን ላይ ለምን እንደሚሰሩ ሰውዬው? ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስራ የላቸውም እንዴ፣ እንዴት መጽሃፍ ሽጠው ትምህርት ቤት ይገነባሉ? ኢትዮጵያ ያለችበትን የችግር አረንቋ የማይረዱ፣ ድንገት ቡና ሲያምራቸው ስታርባክስ ሮጠው ማኪያቶ መጠቀም የሚችሉ ሰዎች ዓለም ሁሉ እንደዛ ይመስላቸዋል በመንግሥት በጀት ብቻ ሳይሆን ለምነንም ተለክተንም ሰርተን ገና ገና ነው።

ለምንድን ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አይነስውራን አካል ጉዳተኞችን ወይም አዛውንቶች በበዓል ቀን ምግብ የሚያበሉት እዚህ ያላችሁ መመገብ የምትችሉ ሰዎች እሳቸውን አይታችሁ እንድትመግቡ ጭምር ነው። ምክንያቱም በዚያ መመገብ ስርዓት ውስጥ አንድ ሺህ አስር ሺህ ሃምሳ ሺህ መቶ ሺህ ሰው በዛች እለት በልቶ ካደረ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ በረከት ስለሆነ ነው በሚታይም በማይታይም መንገድ እነዚያን ስራዎች ማየት ያለብን በዛው ሰአት ባላቸው ውጤት ብቻ አይደለም በሰው ባህል ውስጥ ልምምድ ውስጥ የሚያመጡትን አወንታዊ ተጽእኖ ማየት ያስፈልጋል። መቄዶኒያ በጣም ጥሩ ስራ ነው የምትሰሩት በርቱ መስፋታችሁም ጥሩ ነው እኔ ደግሜ ያልመጣሁት

ስራችሁን በጣም በቅርበት እሰማለሁ እከታተላለሁ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ስለሚመጡ ብዙ ስለምትታዩ ብዙም ስለ ሚድያም ችግር ስለሌለባችሁ የማይታዩትን ባይ ለማለት ነው እንጂ የናንተን ስራ በጣም ነው ማደንቀው፣ እንድትበረቱም እፈልጋለሁ ወደፊት ደግሞ ጊዜው ሲመች እናንተንም አገኛለሁ።

ሌሎች የእኛን ዘርፍ ብታገኝ የእኛን ዘርፍ ብታደርግ ያላችሁ አላችሁ በተቻለ መጠን ያው መገመት ትችላላችሁ ያለንበትን ነገር በተቻለ መጠን እንገናኛለን፣ እንዲህ ባለው መድረክ ልክ የምትጠይቁትን የምትናገሩትን እየሰማን ለማረቅ ለማስተካከል እንሞክራለን። በእናንተ በኩል ወይም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲገነዘብ የምፈልገው ግን አንደኛ ኢትዮጵያ እየተሰራች ነው። ሁለተኛ ኢትዮጵያን ከሰፈር ጨዋታ እናውጣት! በሰፈር ጨዋታ ስንያዝ ትክክለኛው ቦታችን የሚያስከትላቸውን ጣጣዎች መከላከል የማንችል እንዳንሆን፣ ብዙ አልባሌ ጨዋታዎችን እንጫወታለን አልባሌ ተራ ጨዋታዎች ይቺ ሀገር ቦታዋ አሁን ያለችበት አይደለም በአፍሪካ ሁለተኛው የህዝብ ቁጥር ያላት ሃገር ናት ስለዚህ አፍሪካ ውስጥ ብዙም ሊያስፈራራን የሚገባ ኃይል የለም ማለት ነው ወደዛ ለመሄድ፣ ወደዛ ለመሄድ ብዙ የቤት ስራዎች አሉብን ብዙ የሚሰሩ ስራዎች አሉ። ዘርዝሬ የማልጨርሳቸው ሙከራዎች አሉ፣ ብዙ ደግሞ ያልተሰሩ ስራዎች አሉ፣ ኢትዮጵያውያን ግድ የላችሁም፣ አሁን ያለው ትውልድ አስቀድሞ ጠፍቷል፣ የድህነት ሸለማት የተሸለመ ትውልድ ነው፣ ያ እንዳይሸጋገር እራሳችሁን ክዳችሁ፣ ራሳችንን ክደን ለልጆቻችን እንስራ። ያንን ካደረግን ያንን ካደረግን ቢያንስ ኢትዮጵያ በታሪክ ውስጥ በሚመጥናት ቦታ የምትጫወት ሀገር ትሆናለች፣ አሁን እያያችሁ ነው የተሰናዱ የተዘጋጁ የበረቱ ሀገራት እንዴት ብለው ጥቅማቸው እንደሚያስከብሩ ያልተዘጋጁ ሀገራት እንዴት እንደሚንኮታኮቱ ሳይነኩ፣ የሚጋጩት ሌሎች ሳይነኩ የሚንኮታኮቱበት ዋናው ምክንያት ዝግጅት ነው።

ለምሳሌ በምግብ ራስን እንቻል በቢጋ ስንዴ እናምረት ባንል ኖሮ እና የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት ሲቆም ምን እንሆን ነበር? የነዳጅ መኪና እናቁም ኤሌክትሪክ ነው የሚያስፈልገን ብለን ስንጀምር ታውቁታላችሁ የሄድንበትን መንገድ መጀመሪያ ያገለገለ የቆየ መኪና አይገባም ኢትዮጵያ ሲባል የቆየ ተሽከርካሪ ነጋዴዎች በጣም በጣም ተቆጡ ቀጥሎ የነዳጅ መኪና አይገባም ሲባል እንደዚሁ ተቆጡ፣ ተቆጥተውም አላበቁም ብዙውን ብልሹ እያዳረጉ፣ ስርዓት እያበላሹ ያስገባሉ። እዳው ግን እንደምታዩት ነው ቀድመን ብንዘጋጅ ቀድምን ብንሰራ ሰው ሰራሽ አስተውሎት የምንለው በኑክሌር ዘርፍ የምንለው ለኛ አይደለም ለልጆቻችን ነው። አሁን መሰረት ብናስቀምጥ ይሄ ቋንቋ ይቀየራል ለምሳሌ እዛ ካሉ ከያኒያን አንድ ሁለት ሶስቱ በዓለም እንደምናውቃቸው ከያኒያን ቢሆኑ

እና በድንገት መጥተው ተቀምጠው እዚህ አሁን የዕድገት እክል ላይ ትምህርት ቤት የለንም መጽሃፍ የለንም እንደዚህ የለንም ሲባል እጃቸውን አውጥተው “ግድ የለም ስንት ያስፈልጋቸዋል 20 ሚሊየን ነው እኔ አግዛችኋለሁ” ይሉ ነበር ምን ቢሆኑ ብናበቃቸው። እንደዛ አይነት ትውልድ እንዲፈጠር ከፈለጋችሁ አሁን እርሱት እኛ ከችግር ቋንቋ ልንወጣ አንችልም በጣም ብዙ ጣጣ አለብን ያን ተሸክመን አሸንፈን ለልጆቻችን ብንሰራ ግን መልካም ውጤት ቢያንስ እነሱ እንዲያዩ ማድረግ የምንችል ይመስለኛል።

ሲጠቀለል ከፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በትምህርት ዘርፍ ከሃ እስከ ፐ የተጀመረው ሙከራ፣ ጥረት እየተገኘ ያለው ውጤት ያስደንቃል። ይሄ ውጤት አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር ሲመራው ደግሞ የበለጠ ያስደንቃል። ልክ እንደዚህ እንዳንተ ኢትዮጵያን ወደው የኢትዮጵያን ፖሊሲ ተቀብለው ኢትዮጵያን በማገልገል እመርታ የሚያመጡ ሰዎች በዝተው ከተቃራኒ ፓርቲ አንድ ከሚታይ አንድ ሶስት የምናይበት ግን ሁሉም ለአንድ ዓላማ ለአንድ ሀገር እጃቸውን አጽድተው የሚሰሩበትን መንገድ ለመፍጠር ብንጥር ጥሩ ነው፣ ቲፎዞነታችን ለጥፋት ብቻ ባይሆን ልማት ስናይ መልካም ነገር ስናይ ማድነቅ የምንችል ቢሆን፣ ብንተባበር ይበልጥ አዋጭ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ለመንግሥት ሹመኞች የመጨረሻ መልዕክቴ እንደዚህ ያለው መድረክ በጣም ጠቃሚ ነው። አንዳንዶች ስራዎቻችሁን አድንቀዋል የጎደለ ጠይቀዋል። በተቋሞቻችሁ እቅድ ውስጥ አስገብታችሁ በጀት ካለ በበጀት፤ ከሌለ ለምናችሁ ማገዝ እንዲህ ባለው መድረክ ጊዜ ውስጥ የተስተካከለ ምስጋና የሚያስጥ ነገር ነው። ስለተሰጠኝ እድል እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። ለተሰራው አከብራለሁ ለጎደለው ደግሞ በጋራ እንድንሰራ ጥሪ አቀርባለሁ።

አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ


Huawei

በሁዋጂያን ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የተደረገ የፋብሪካዎች ጉብኝት

—ሚያዚያ 24፣ 2018 ዓ.ም

ባለፈው ሳምንት ያየነው የሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ በመንግሥት የተገነባ ነው። ሁዋጂያን እዚህ ያለው ኢንዱስትሪ ፓርክ ግን በግል የተገነባ ነው። በስፋት ደረጃ ስትወስዳቸው ሐዋሳና ይሄ ይተካከላሉ። ሁዋጂያን በግል የተገነባ ቢሆንም የጅማን ኢንዱስትሪ ፓርክ ሶስት እጥፍ ወይም ኮምቦልቻን ሶስት እጥፍ ይበልጣል፤ በስፋቱ በጣም ትልቅ ሲሆን 30 ሼዶች አሉት፤ ጅማና ኮምቦልቻ ግን ስምንት ስምንት ሼዶች ነው ያላቸው።

ሰፊና ያለ በርከት ያሉ ሰዎች የሚይዝ ለከተማም በጣም ቅርብ ስለሆነ በብዙ መልኩ የግል ዘርፉ በኢንዱስትሪ ረገድ ያለውን የኢንቨስትመንት ሚና አጉልቶ የሚያሳይ ነው ያም ሆኖ ግን ከአጎዋ በኋላ ጨርቃ ጨርቅ ላይ መሰረት ያደረገው ምርታችን አጎዋ ሲበለሻሽ ትንሽ ተደነቃቅፎ ነበር ያን ለመቀየር ማስፋፋት እናድርግ ብለን አሁን እንዳየኸው ሶላር፣ የኤሌክትሪክ ባጃጅ፣ ጫማዎች፣ ልብሶች የሚያመርት ኢንዱስትሪ ፓርክ ነው። ሠላሳውም ሼዶች የተለያየ ምርት የሚያመርቱ በመሆናቸው ተስፋፍቷል። ይህም አንዱ ገበያ ቢበላሽ በሌላው ለመቀጠል ዕድል የሚሰጥ ስለሆነ በጣም ጠቃሚ አካሄድ ነው።

ይሄኛው በቀደም ሐዋሳ ላይ እንዳነሳሁት የሶላር ሴል ማምረቻ ፋብሪካ ነው። የፋብሪካው ስም ጎበዝ ይባላል፤ ሁዋጂያን ውስጥ ያለ ፋብሪካ ነው። አሁን የሚያመርቱት ሁለት ጊጋዋት ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ ተጨማሪ ሁለት ጊጋዋት በቅርቡ የሚጀመር ሲሆን በሚቀጥለው ዓመት እሱም ያልቃል። ስለዚህ በዚህ ቦታ በአጠቃላይ አራት ጊጋዋት ይመረታል። የሶላር ሴል ማምረት የጀመርነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲሆን አጠቃላይ ሥራ ከጀመርን አንድ ዓመት ገደማ ቢሆነንም አሁን በጣም እየሰፋ ይገኛል።

አሁን የሚያስፈልገን ይሄንን ያሳካነውን ስኬት ብቻ ሳይሆን የሚቀሩትን ግብዓቶች እያወቅን እና የፍሰተ-ምርት ትስስር እየሠራን ከሄድን አብዛኛውን ምርት በሀገር ውስጥ ማምረት እንችላለን። ውድ ማዕድናት ስላሉን ከእነርሱ እያመረትን ፓነሎችን እያመረትን ከሄድን ውጤታማነቱ በጣም ያደገ ሊሆን ይችላል። አሁን የተገኘው ውጤት በጣም ማራኪ ነው፣ ቬትናም ያየነውን እና የተደመምንበትን ነገር በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ማድረግ ችለናል፣ ማስፋቱ ቀጣይ ስራ ይሆናል።

ሁዋጂያን ኢንዱስትሪ ፓርክ አዲስ አበባ የሚገኝ ስለሆነ በጣም በርካታ ሼዶች ስለሚይዝ ብዙ የውጭ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ እድል ያለው ተቋም ነው። የሰሩት ስራ በጣም

ማራኪ ነው። የኢንዱስትሪ ስራ በሰው ኃይል ቅጥር ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ለምሳሌ አየር መንገድ ኃይላችንን በመጠቀም በብዙ መንገድ ኢኮኖሚያችን ውስጥ ተጽዕኖ አለው። በሀገር የምንቀጥረው ብቻ ሳይሆን ከውጭ የምናመጣቸው ሙያተኞች ስላሉ የዕውቀት ሽግግር ለማካሄድ፣ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ስላለው ሁሉንም ጥቅሙን አሟጦ ለመጠቀም ያሳካነውን ካየን በኋላ የሚጎለንን ደግሞ እያወቅን መቀጠል ያስፈልጋል እና ኢትዮጵያ ታምርት የሚባለው እንቅስቃሴ በተግባር ውጤት እያመጣ ነው ያለው፣ የኢንዱስትሪ ሽግሽግ እያመጣ ነው ያለው፣ የሚቀሩን ነገሮች እያየን እየሞላን ከሄድን በሚቀጥሉት 5 እና 10 ዓመታት ኢትዮጵያ በብዙ መልኩ ራሷን የመቻል እድል እንዳላት ያመላክታል።

በርትተን ከሰራን፣ ጀምረን ነክሰን ከጨረስን፣ መጀመር ብቻ አይደለም ነክሰን ከጨረስን፣ መጨረስ ብቻ አይደለም ክፍተት እያዩ መሙላት ከጀመርን የማይቋረጥ ተከታታይ እድገት ስለሚያመጣ የምናስበው ውጤት ሊያመጣ ይችላል የሚል እምነት አለኝ። በጣም ጥሩ ስራ ነው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያገኘነው ውጤት ነው ይሄን እያሰፋን እያሳደግን የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ከሁላችን የሚጠበቅ ዐብይ ተግባር ይሆናል ብዬ አምናለሁ!

ባየሁት ደስ ብሎኛል እናንተም እንኳን ደስ አላችሁ!
አዲስ አበባ

የ2018 ዓ.ም ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ

ሚያዚያ 25፣ 2018 **ዓ.ም**

ክቡር አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣
የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ክቡር ቴዎድሮስ ምህረት፣
የፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ አደም ፋራህ፣
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር መላኩ አለበል፣
ክቡራን ሚኒስትሮች፣ የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ ክቡራን እንግዶች፣ ከሁሉ በላይ የኢትዮጵያ ታምርት ቤተሰቦች ፤ ለአራተኛ ዓመት የኢትዮጵያ ታምርት የኤክስፖ ፕሮግራም እና ለተገኘው ውጤት በጋራ ስላደረሰን እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እወዳለው!

“ማምረት ሉዓላዊነትን ያጎናጽፋል” ስንል አለማምረት በሰዎች ጣጣ በእኛ ላይ የሚደርሰውን ዳፋ፣ መከራ፣ ችግር ከግምት በማስገባት ነው፣ ኢትዮጵያ ማዳበሪያ ማምረት ካልቻለች የግብርና ምርትና ሂደቱ በሰዎች በጎ ፈቃድ ላይ የወደቀ መሆኑ አይቀርም። መብላት እስካለ ድረስ ለምግብ ግብዓት የሚሆኑ የማምረቻ መሳሪያዎች፣ ምርጥ ዘሮች፣ ማዳበሪያዎች በሀገር ውስጥ ማምረት የተሟላ የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ያግዛል።

ነዳጅ፣ ጋዝ ማምረት ባለመቻላችን ባለፈው አንድ ወር ሁለት ወር የገጠመንን ፈተና አይተናል፣ ኢትዮጵያ ብዙ የጋዝ፣ የነዳጅ ሀብት እንዳላቸው ሀገራት ከፍተኛ አቅም ያላት ቢሆንም እስከ ዛሬ ማምረት ባለመቻሏ የገጠማት ፈተና በኢንዱስትሪያሊስቶች፣ በሁላችሁም ዘርፍ የገጠመ ችግር ስለሆነ ይታወሳል፣ ይታወቃል። ነገር ግን ጋዝ ያላት ሃገር ያንን ሳታመርት በመቆየቷ ትራንስፖርት ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ደረጃ ሊታወክ ችሏል። ስለዚህም በሁሉም መስክ ማምረት ሉዓላዊነት ማረጋገጥ መሆኑን ማመን፤ ማመን ብቻ አይደለም ማቀድ፤ ማቀድ ብቻ አይደለም መስራት፤ ከዚያም መስፋት በሁሉም መስክ የሚጠበቅ ጉዳይ ይሆናል።

ከሉዓላዊነት ጋር ያለው ትስስር ቀጥታ ስለሆነ እርዳታ የሚቀበል ሀገር፣ ከሰዎች ምግብ የሚለምን ሃገር፣ አብዛኛው ፍላጎቱን ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ የተንተራሰ ሃገር ነጻ ነኝ፣ ሉዓላዊ ነኝ፣ ክብር ያለኝ ሀገር ነኝ ማለት አይችልም፣ ጥገኛ ነው፤ ለማኝ ጥገኛ ነው፣ እኛ ለማኝ ኢትዮጵያውያን ሰምታችሁኛል፣ እኛ ለማኝ ኢትዮጵያውያን ልመና በቃን እስካላለን ድረስ ጥገኞች ነን! ከጥገኝነት ያልተላቀ ማኅበረሰብ፣ ግለሰብ ደግሞ በነፃነት ማሰብ፣ በነፃነት ስለ ሃገሩ ስለ ልጆቹ ጥቅም መወሰን ይቸገራል። ያ እንዳይሆን ኢትዮጵያ

አምርታ ሉአላዊነቷን ማረጋገጥ እንድትችል ፣ ከሁሉ በላይ ይህ የገባው የኢትዮጵያ ታምርት ቤተሰብ ከፍተኛ ሀላፊነት እንዳለበት አምኖ አሁን በጀመራችሁት መንገድ በትጋት፣ በህብረት፣ በአንድነት መስራት ከቻልን፣ ኢትዮጵያን ሉዓላዊ፣ ነጻ፣ ክብሯን የጠበቀች ሃገር አድርገን ለልጆቻችን ማስረከብ እንችላለን። ይህ እንዲሆን ሁላችን በታላቅ ውሳኔና ቁርጠኝነት መስራት ይጠበቅብናል።

የዛሬ አራት ዓመት “ኢትዮጵያ ታምርት” ሲባል አሁን ባየነው ውጤት ልክ በፈጠነ ጊዜ የምርቱ አይነት ሰፍቶ፣ ጥራት አድጎ የኢትዮጵያን ፍላጎት በዚህ ልክ ይመልሳል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ጥቂቶች ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን የአምናውን፣ የካቻምናውን ኤክስፖ መጥቶ የጎበኘ ማንኛውም ሰው የዘንድሮውን ሲጎበኝ ኢትዮጵያ ምን ያህል በጥራት፣ በአይነት እያደገች እንዳለች ለመገንዘብ፣ ለመማር፣ ለማወቅ አይቸገርም።

በዚሁ አጋጣሚ ክቡር ሚኒስትር መላኩ 150 ሺህ ገደማ ሰዎች እንደሚጎበኙ ይጠበቃል ብሎ ነበር፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች፣ የሃይስኩል ተማሪዎችና መምህራን ይህ ኤግዚቢሽን እንዳያመልጣችሁ፤ በጣም በርካታ ትምህርት የሚገኝበት፣ ለመፍጠር፣ ሰው ለመሆን፣ ለማደግ፣ በውስጣችሁ የተደበቀውን ብቃት ለመቀስቀስ የሚያስችሉ ምርቶች ስላሉ የምትማሩ፣ የምታስተምሩ፣ መነገድ፣ ማምረት የምትመኙ፣ የምታስቡ ሰዎች በዚህ ስፍራ እየመጣችሁ የእነዚህን ድንቅ ኢትዮጵያውያን የአእምሮ እና የእጅ ስራ ብትጎበኙ በነጻ ዕውቀት ትገበያላችሁ ብዬ አምናለሁ። እኔም ዛሬ በጣም ብዙ ትምህርት አግኝቻለሁ ፤ እና 150 ሺህ ሰው በቂ ስላልሆነ በተቀናጀ መንገድ ተማሪዎች፣ መምህራን በስፋት መጥተው ሊጎበኙ እንደሚገባ በጽኑ አምናለሁ።

የ”ኢትዮጵያ ታምርት” እንቅስቃሴ ምንም እንኳን በዕድሜው ለጋ ቢሆንም ገና አራት ዓመት ቢሆንም ንቅናቄውን ከጀመርን በከፍተኛ ደረጃ ግን ምላሽ እያደረገ ነው። ዘንድሮ ሃገራችን ኢትዮጵያ የ10.2 በመቶ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት ታመጣለች። ይህ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት በቅርቡ የዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባ ሲደረግ 9.2 በመቶ እድገት ኢትዮጵያ ታመጣለች። ከአፍሪካ ቀዳሚው እድገት የኢትዮጵያ እንደሆነ ዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ተንበየዋል። ይህንን ትንበያ ኢንዱስትሪያሊስቶች በቀላል ማየት የለባችሁም።

በኢትዮጵያ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መካከል በዘመናት መካከል የአንድ በመቶ የትንበያ ልዩነት ኖሮ አያውቅም። እኛ 10 ስንል እነሱ ሰባት፣ ስድስት የሚሉት፤ ዘጠኝ ብለው እኛ አስር ካልን ምን ያክል የተቀራረበ ትንበያ እንዳለ ያሳያል።

የዘንድሮ የ10.2 በመቶ እድገት የሚረጋገጠው በዋናነት ኢንዱስትሪው እና “ኢትዮጵያ ታምርት” በፈጠሩት ንቅናቄ ስለሆነ ለዚህ እድገት የእናንተ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ!

ከማክሮ ኢኮኖሚክ ማሻሻያ በፊት በውጭ ምንዛሬ ግኝት ኢትዮጵያ የነበረባትን ፈተና ሁላችሁም ታውቃላችሁ፤ የዛሬ ሶስት ዓመት እና ከዚያ በፊት በነበሩ ዓመታት በሙሉ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ያላለፈ የወጪ ንግድ ገቢ ነበር ኢትዮጵያ የምታገኘው ሶስት ቢሊዮን ዶላር! ዘንድሮ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከካቻምናው በሶስት እጥፍ በልጠን ፣ 10 ቢሊዮን ዶላር ገደማ የወጪ ንግድ በዚህ ዓመት እናሳካለን። ይህ ትልቅ፣ ትልቅ ድል ነው፤ የዚህ ድል መሰረት ደግሞ ኢንዱስትሪ ነው፤ ለዚህም በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እወዳለው!

“ኢትዮጵያ ታምርት” ስንጀምር የአምራች ዘርፍ እድገት 4.7 በመቶ ነበር፤ ዘንድሮ 10.7 በመቶ ደርሷል የማኑፋክቸሪንግ እድገት ብቻ። ይሄ ሊመጣ የቻለው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በወጪ ንግዱ ያመጣው ውጤት፣ በተተኪ ምርቶች ያመጣው ውጤት፣ በተሟላ መንገድ እንዲሳካ አምራች ዘርፍ ያሳየው እድገት ነው። ለምሳሌ በተተኪ ምርቶች ብንወስድ ባለፉት አራት ዓመታት ከዚህ ቀደም በውጭ ምንዛሪ እናስገባ ከነበሩ ምርቶች መካከል 14.5 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ኢትዮጵያ በሃገር ውስጥ ማምረት ችላ ተክታለች። ይሄን እናንተ ባታመርቱ ኖሮ 14.5 ቢሊዮን ዶላር የምናገኝበት መንገድ አዳጋች፣ አታካች ስለሆነ በልጆቻችን ላይ የእዳ ቀንበር ከማጠናከር፣ ኢኮኖሚያችንን ከማዛባት ባልተረፍን ነበር ፤ ነገር ግን ስላመረታችሁ በአራት ዓመት ውስጥ 14.5 ቢሊዮን ገደማ የገቢ ንግድ መተካት ተችሏል።

በሚቀጥሉት አራት ዓመታት በብዙ እጥፍ እንደሚያድግ ምንም ጥርጥር የለውም፣ ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ 993 ኢንዱስትሪዎች በተለያየ ምክንያት ከዚህ ቀደም ቆመው የነበሩ ወደ ስራ ገብተዋል፣ ስራ ጀምረዋል፣ 1,000 ፋብሪካ ማለት ነው። ይሄ ምን ያክል የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ በወጪ ንግድ፣ በተኪ ምርት ሚናው ምን ያክል ሰፊ እንደሆነ ለእናንተ መንገር አስፈላጊ አይደለም። ባለፉት አራት ዓመታት “ኢትዮጵያ ታምርት” ካልንበት ጊዜጀምሮ 3,680 አዳዲስ ባለሃብቶች ወደዚህ ዘርፍ ተሰማርተዋል፣ 3,000 ተጨማሪ ኢንቨስተር መሳብ የቻለ ንቅናቄ የሚጎሉትን ነገሮች ለቅመን፣ ማረቅ፣ ማስተካከል ከቻልን ብዙ ሺህ ኢንዱስትሪያሊስቶችን መፍጠር እንችላለን ማለት ነው።

ከዚህም አንጻር የኢትዮጵያ ታምርት በወጪ ንግዱ፣ በሥራ መፍጠር ዘርፍ ካመጣው ውጤት በተጨማሪ፤ ተጨማሪ ሰዎች መፍጠር፣ መስራት፣ ፋብሪካ መትከል እንዲችሉ ያስቻለ ስራ ስለሆነ ለዚህ የስራ ስኬት ኢንዱስትሪያሊስቶች፣ የስራ አመራሮች፣ አጠቃላይ የተሳተፉ ባለ ድርሻ አካላት ላደረጉት ጉልህ አስተዋጽኦ በራሴ እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ስም የከበረ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ።

ክቡራት እና ክቡራን ካላመረትን ክብራችን፣ ነጻነታችንን መጎናጸፍ ስለምንቸገር ለማምረት ከናንተ ምን ይፈለጋል? ከመንግሥት ምን ይፈለጋል? በየደረጃው ካሉ የባለ ድርሻ አካላት ምን ይፈለጋል? የሚለውን የሚፈታ የኢንዱስትሪ አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁመን ላለፉት ዓመታት ስንሰራ መቆየታችን ይታወቃል። ይሁንና በመሬት፣ በኃይል፣ በመጠኑም ቢሆን በፋይናንስ ዘርፍ መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም በቅርቡ በነበረን ግምገማ የተገነዘብነው ነገር ዛሬም ለማየት እንደሞከርኩት አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ ፋይናንሻል ዘርፍ ለኢንዱስትሪው የሚያቀርቡት ብድር፣ ድጋፍ አነስተኛ ሆኖ አግኝተነዋል። በዚህም ምክንያት በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት፣ ምናልባት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ህግ እናወጣለን፣ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ሀብት ምን ያህል በመቶው ወደ ኢንዱስትሪ መፍሰስ እንዳለበት በግልም በመንግሥትም ባንክ ህግ ስለምናወጣ ከፋይናንስ ጋር ያለው ቻሌንጅ እንዳለ ይቀረፋል ብዬ መናገር ቢያስቸግረኝም፤ አሁን ግን ኢንዱስትሪው ሊያገኝ የሚገባውን ድርሻ እንዲያጣ ያደረጉ ሰው ፈጠር ችግሮች የሚቀረፉበት፣ ህግ ለማውጣት የኢትዮጵያ መንግሥት በስራ ላይ ስለሆነ ይህ ለእናንተ ትልቅ ብስራት ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እወዳለው!

ነገር ግን የኢትዮጵያ ሀብት የእናንተን ፍላጎት ሊመልስ አይችልም፤ መቶ በመቶ ያለንን ሀብት ለኢንዱስትሪ ማበደር ብንወስን እዚህ ውስጥ ካላችሁ 20/ 30 ሰዎች አያልፍም፤ ብዙ ሃብት ካልፈጠርን በቀር አሁን ያለው ሀብት በቂ አይደለም። ያለው ሀብት ግን በትክክለኛው መንገድ ለሁሉም ዘርፍ አግባብ በሆነ መንገድ ክፍፍል መፍጠር እንዲቻል ሁሉ ነገር ንግድ፣ ሁሉ ነገር ኮንትሮባንድ ብቻ እንዳይሆን በህግ የሚቀየር ይሆናል። ያ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም በኢትዮጵያ የሉዓላዊ ሀብት ፈንድ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በኩል እና በእናንተም ትስስር ሊሰራ የሚገባው አንድ ወቅታዊ ጉዳይ ብዬ ማስበው ነገር ከማምረት ባሻገር ያለ የንግድ ትስስር ነው።

ብዙ ምርቶች አሉ፣ አፍሪካ ውስጥ ባለው ገበያ ውስጥ ኩባንያዎች እየፈጠርን መሄድ አለብን፣ አንዱ እዚህ ያመርታል፣ አንዱ ከዛ ገዝቶ እዛ ያከፋፍላል፣ የኢትዮጵያን አምራቾች “አምርቱ፣ አምርቱ” ስትባሉ ነበር፣ አሁን ደግሞ ውጡ 5፣ 10፣ 15 ኩባንያ

ከቻለ በግል፣ ካልቻለ በህብረት፣ አልያም ከመንግሥት ጋር እየተቀናጀ ቢያንስ በተመረጡ አምስት፣አስር አፍሪካ ሃገራት የእኛ ኩባንያዎች መሄድ አለባቸው። ኢትዮጵያ ትልቅ ገበያ ያላት ሃገር ብትሆንም በአፍሪካ ውስጥ ያለውን ገበያ ለመቀራመት ከፍተኛ እድል ያላት ሃገር ስለሆነች አእምሯችሁን ማምረት ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ገበያ ለመሻማት በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፤ ከዚህም አንጻር መንግሥት የራሱን የቤት ሥራ የሚሰራ ይሆናል።

ከቡራን አምራቾች፣ ኢንዱስትሪያሊስቶች አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን ገብረው በአርበኝነት የኢትዮጵያን ነጻነት ለማረጋገጥ ይተጋሉ፣ አንዳንዶች እውቀታቸውን፣ አንዳንዶች ጉልበታቸውን፣ አንዳንዶች ጊዜያቸውን ይሰዋሉ። ከእናንተ ደግሞ የኢኮኖሚ አርበኝነት ይፈለጋል፣ እናንተ ካላመረታችሁ ወታደር ደሞዝ የለውም፣ እናንተ ካላመረታችሁ የምታዩት ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ ሊከናወን አይችልም፣ የኢኮኖሚ አርበኛ ለመሆን ደግሞ ግብር መክፈል ብቻ ሳይሆን ኮንትሮባንድ፣ ሌብነት፣ አጭር መንገድ በመንግሥትም በእናንተም በኩል ያለውን እያረቁና እያስተካከሉ መሄድ፣ የእውነተኛ አርበኝነትን ስሜት መላበስ ያስፈልጋል።

ከዚህ አንጻር በተሰራው የምንኮራ፣ የምናመሰግን ሲሆን ተጨማሪ ጥረት ከእናንተ ይፈልጋል፤ ከዚህ ጥረት ውስጥ አንደኛው እና ዋነኛው ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እየተመረቱ ካሉ ምርቶች በተጨማሪ 96 አይነት ምርቶች ተለይተዋል፣ ልናመርታቸው የምንችላቸው፣ ልናመርታቸው የሚገቡ፣ ልናመርት ስንችል ከውጪ የምናመጣቸው 96 ገደማ የምርት ዓይነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ መጀመር ይቻላል። ይሄን ለማድረግ ልየታው ስላለቀ በእናንተ በኩል መረጃውን ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በመውሰድ እነዚህ ዘርፎች በፈጠነ መንገድ በመተካት ከውጪ የምናመጣቸውን ምርቶች ማስቀረት ይኖርብናል። ለምሳሌ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በቅርቡ የሴራሚክስ ፋብሪካ እናስመርቃለን። ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት ድንጋይ ተሸክማ ትመጣ ነበር፣ ወደብ የሌላት ሃገር፣ ጠንካራ ሎጀስቲክ ሥርዓት የሌላት ሃገር፣ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ግብዓት እንዲሆን ድንጋይ ተሸክማ አምጥታ በሚፈለገው ልክ ግንባታን ማፋጠን አትችልም፤ አሁን ሴራሚክስ በሀገር ውስጥ በቅርቡ ይመረቃል ፤ ከአንድም ሁለት ይመረቃሉ። እነዚህ የኢትዮጵያን ፍላጎት መቶ በመቶ ይመልሳሉ ፤ እነዚህን የሴራሚክስ አምራቾች ወደ ፖርሲሊን፣ ግራናይት፣ ማርብል ማሳደግ አለብን፤ ድንጋይ መሸከም የለብንም፣ ለዚያ በቂ የሆነ ግብዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለ ያን እየለያችሁ ማምረት ከሁላችሁ የሚጠበቅ ይሆናል።

በማምረት ክብራችንን፣ ነጻነታችንን እና ተጨማሪ እድገት ማፋጠን እንችላለን። እናንተ ስራ ስለምታውቁ፣ ስራ ስለምትፈጥሩ፣ የስራም ጉዞ ስለሚገባችሁ በድፍረት ልነግራችሁ የምፈልገው ነገር የ10.2 በመቶ እድገት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ አስደናቂ በሆነ መልኩ በግብርናው፣ በማዕድን ፣ በኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም ከሁሉ በላይ ደግሞ በቴክኖሎጂ በጣም ፈጣን የሆነ እድገት እያሳየች ያለች ሃገር ናት ፤ በብዙ ምርቶች ለኛ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ገበያም ማቅረብ የቻለች ሃገር ናት።

ከመከላከያ አንጻር እንኳን ብንወስድ የዛሬ አራት አምስት ዓመታት ከውጭ እናስገባቸው የነበሩ ምርቶች፣ ጥቂት የማይባል የምርት አይነት ዛሬ ከስድስት በላይ የአፍሪካ ሃገራት እየሸጥን እንገኛለን። በመከላከያ ምርት ራስን መቻል እና መሸጥ ፤ በልብስ ራስን መቻል እና መሸጥ፤ በመድኃኒት ራስን መቻል እና መሸጥ፤ እነሱን ለማምረት የሚያስችሉ ማሽነሪዎች ማምረት እና መሸጥ እየቻልን ስንሄድ የምንወዳት ሀገራችን በተሟላ ቁመና የተሰራች ትሆናለች።ከኛ አንጻር ያቀድነው፣ የተለምነው፣ ያሰብነው ከሞላ ጎደል በሚያስደንቅ ሁኔታ በፈጣሪያችን እርዳታ እየተሳካልን ፣ ኢትዮጵያ እየተሰራች እንደሆነ በአይናችን፣ በአይናችሁ እያያችሁ ይመስለኛል።

በድፍን አፍሪካ ያለው ምኞት በኛ ልክ በሁሉም ዘርፍ የመጣ እድገት እና ሲሰራ የሚታይ ሀገር ማየት የብዙ ዜጎች ምኞት ነው፣ እኛ ይህን እድል እንጠቀም፣ እንተባበር፣ በጋራ እንስራ፣ ከጉድለት እንማር ፤ ለላቀ ውጤት፣ ለላቀ ስኬት በምቀኝነት መንፈስ ሳይሆን በትብብር መንፈስ አብረን እንቁም፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና በጋራ እናረጋግጥ። ኢንዱስትሪና ማምረት ለብልጽግና፣ ለነጻነት፣ ለክብር ወሳኝ መሰረቶች ስለሆኑ በጋራ ይሄን መሰረት እንድናቆም ጥሪ እያቀረብኩ ፤ ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት፣ በልጆቿ ምርት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ

በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሱሉልታ ወረዳ የስንዴ ማሳ ጉብኝት

ሚያዝያ 28፣ 2018 **ዓ.ም**

በግብርና ዘርፍ የጀመርነው ጣልቃ ገብነት እያስገኘ ያለው ውጤት በእጅጉ የሚያስደምም ነው። ይበልጥ እንድንበረታ፣ ይበልጥ እንድንተጋ፣ ይበልጥ አዲስ ሃሳቦች እንድንፈጥር፣ ይበልጥ አዲስ ነገሮች እንድንሞክር ጉልበት የሚሆን ስራ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ያው ሁላችሁም እንደምታስታውሱት ኮሮና እስከመጣበት ጊዜ ድረስ የበጋ እርሻ፣ የበጋ ስንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ አልነበረም። «መሬት ጦም ማደር የለበትም፤ ከልመና ራሳችንን መገላገል አለብን፤ ሊታረስበት፣ ሊመረትበት የሚችል መሬት አለን» የሚል ጽኑ እምነት ነበረን ስንጀምር፤ ማሳመኑም መከራ ነው የነበረው። አሁን ያለበት ደረጃ ግን በየጊዜው በራሱ ውጤት፣ ባስገኘው ውጤት ብዙኃንን እያሳመነ አስደማሚ ደረጃ ደርሷል።

እንግዲህ ስንዴ የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባ ብቻ ሳይሆን አነስተኛ ምርት ካላቸው ሀገሮች ተርታ የምትመደብ ናት። የዘንድሮውን እንኳን ብቻ ብንመለከት ባለፈው ክረምት ወደ 4.4 ሚሊዮን ሄክታር ነበር ያረስነው፤ የዘንድሮ በጋ 3.8 ሚሊዮን ሄክታር ገደማ ነው ያረስነው፤ በድምሩ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት አርሰናል፤ ያገኘነው ምርት ከ330 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ነው። ይሄ በአፍሪካ በስንዴ በማምረት ኢትዮጵያን በአንደኛ ደረጃ ያስቀምጣታል፤ ከፍተኛ ምርት ስለሆነ። አምናና ዘንድሮን እንኳን ብናስተያይ ወደ ሚሊዮን የሚጠጋ ሄክታር (950 ሺህ ገደማ ሄክታር) ጭማሪ አለው። ባለፈው ዓመት ክረምት እና በጋን 280 ሚሊዮን ሄክታር ገደማ ነበር ያመረትነው፤ በዚህኛው ዓመት ደግሞ 331 ሚሊዮን ኩንታል የምናመርተው። ይሄ የሚያሳየው የ50 ሚሊዮን ኩንታል ልዩነት ነው። በአንድ ዓመት ያመጣው ያ ልዩነት እንዴት መጣ ያላችሁ እንደሆነ ለምሳሌ አሁን ያለነው ሰሜን ሸዋ ውስጥ ነው፤ ይህ የከብቶች መዋያ መስክ ነው የነበረው በበጋ በዚህ ጊዜ ስትመጣ እንደዚህ ያለ አረንጓዴ ነገር የሚታይበት አልነበረም። እዚህ ጋ ትንሽዬ ወራጅ ወንዝ አለች፤ እሷን በየቦታው በመገደብ፣ በማስቀረት፣ የዘነበውን ዝናብ አስቀርተው ነው ይሄን እርሻ የሞከሩት።

አሁን ከዞኑ አመራር ጋር በነበረኝ ውይይት «በሚቀጥለው ዓመት በጣም ብዙ እናሰፋለን፤ ልምድ አግኝተናል፤ የማይቻል መስሎን ነበር፤ ተችሎ ስላየን አያሰጋም፣ የበለጠ ማደግ ይችላል» የሚል ሃሳብ ሰንዝሮልኛል። እና ሰሜን ሸዋ ውስጥ ይሄን የሚያክል ማሳ መገኘቱን፣ ወደ ማጎበረሰቡ ተደራሽነቱን በተግባር ብታይ... የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት ሰሜን ሸዋ ውስጥ ቢያንስ ቢያንስ አራት አምስት ወረዳዎች በሴፍቲኔት ይተዳደሩ ነበር፤

አራት አምስት ወረዳዎች አብዛኛው ቀበሌ ሴፍቲኔት ነበር። በዚህ ዓመት በሰሜን ሸዋ ውስጥ አንድም ቀበሌ በሴፍቲኔት የተያዘ የለም፤ መቶ በመቶ ራሳቸውን ነጻ አውጥተዋል በምን? በማምረት!

ሰሜን ሸዋ አራት አምስት ወረዳዎች በሴፍቲኔት ተይዞ የነበረው መቶ በመቶ ነጻ ወጣ ማለት በየቦታው በየሥነ-ምሕዳሩ፣ በየከባቢው የመሬት ጠባይና የአየር ጠባይ ጊዜ ጠብቀን የምናደርጋቸው ስራዎች ከሰራን በድፍን ኢትዮጵያ አምርቶ መብላት አሳሳቢ ጉዳይ አይሆንም ማለት ነው። ይህ አሁን በሰሜን ሸዋ የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት የነበረውን የገቢ ደረጃ ማንሳት ያሳርፋል፤ ዘንድሮ ግን በስምንት እና በዘጠኝ ቢሊዮን ገደማ መካከል ላይ ገቢ ይሰበስባል። ዞኑ ከስምንት እስከ 9 ቢሊዮን ባለው ውስጥ ዝቅተኛውን ብንወስድ 8 ቢሊዮን ሰበሰበ ብንል፣ የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት ኦሮሚያ እንደ ክልል የሚሰበስበው ገቢ 16-17 ቢሊዮን ብር ነበር፤ የኦሮሚያን የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት ገቢ ግማሽ የሚሆን አንዱ ዞን ብቻ ሰበሰበ ማለት ነው። በገቢ እድገት አለ፤ በሴፍቲኔት የታሰሩ ሰዎች ነጻ ወጥተዋል፤ ገንዘብ ደግሞ ብትወስድ ከሰሜን ሸዋ በቀን 500 ሺህ ሊትር ወተት ወደ ከተማ ይሄዳል። በዓመት ከወተት ብቻ 16 ቢሊዮን ብር ያገኛሉ፤ ከወተት ብቻ! እንቁላል በዚህ ዓመት ሶስት ሚሊዮን ጫጩት ነው ያባዙት፤ ያንሳል ብያቸዋለሁ።

እንቁላልና ወተት ላይ እንኳን በደንብ ቢሰራ፣ ለምሳሌ ወተቱ አምስት መቶ ሺህ የሆነው በጥቂት ዓመታት ውስጥ በሰው ሰራሽ መንገድ እያዳቀሉ ስለሆነ አንድ ሚሊዮን ሊትር ማምረት ቢችሉ በቀጥታ 30 ቢሊዮን ገቡ ማለት ነው በዓመት። ይሄ ግብይት በብዙ መልኩ የአርሶ አደሩን ህይወት ይነካል። ከእንቁላል፣ ከወተት፣ ከስጋ ምርት፣ ከእርሻ፣ ከእርሻ ከሚተርፍ ደግሞ መኖ ተያያዥ ነገር ነው። አንዱ አንዱ እየደገፈ ስለሚሄድ በከፍተኛ ደረጃ በምግብ ራስ መቻል ብቻ ሳይሆን የተሻለ የዘመነ ኑሮ እንድንኖር ያስችለናል።

ልጆች ከሞላ ጎደል ትምህርት ቤት ገብተዋል። ከኬጂ ጀምሮ ትምህርት ቤት ተስፋፍቷል፤ እየተማሩ ነው ያሉት። ታች ላይ የምንሰራው የትምህርት መስፋፋት በኋላ ለምናገኘው ውጤት ያግዛል። ልጆች የማይታረስ የነበረው ቦታ ሲታረስና ውጤታማ ሲሆን እያዩ ነው ያደጉት። ቴክኖሎጂ እየጨመሩ፣ ማሽነሪ እያስፋፉ፣ እየተጠቀሙ ያሳድጉታል እንጂ ወደ ኋላ አይመለስም። እንዳየኸው በዚህ ጊዜ እንግዲህ ግንቦት ሊገባ ነው አይደል? አሁን በዚህ ጊዜ ውስጥ ሰሜን ሸዋ እንደዚህ ያለ አረንጓዴ መስክ ማየት በጣም በጣም አስደሳች ነገር ነው። ሃገሩን ወቅትን ጊዜን አውቆ ለሚያይ ሰው የሚሰጠው ትርጉም ቀላል አይደለም። እንደዚህ አይነት ማሳ በዚህ ወራት ውስጥ መኖራቸው የበለጠ ብንገድብ፣ ውሃ ብንቆጥብ፣ እርከን ብናስፋፋ፣ ፓምፕ ብንጠቀም ድፍን ኢትዮጵያ ምን ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል።

አንደኛው እንግዲህ ክላስተር ነው። የተበጣጠሰ መሬት የሚባል የለም፤ የተበጣጠሰ አእምሮ ነው ያለው! መሬቱ ወጥ ነው። እኔ እና አንተ ከተደመርን፣ መሬታችንን ከደመርን «የተበጣጠሰ» የሚለው ቋንቋ በራሱ የሃሳብ እጥረት ነው። መሬቱን እንደምታየው ወጥ ነው። ሰዎች ናቸው በምናባዊ ድንበር እያበጁ የሸነሸኑት እንጂ ወጥ ነው። ክላስተር ስናደርግ እንደዚህ ያለ ወጥ መስክ ሆነ ማለት ነው። ትራክተር ሲጨመርበት፣ ግድብ ሲጨመርበት፣ ፓምፕ ሲጨመርበት በአንድ ጊዜ የንግድ እርሻ ቅርጽ ይይዛል።

እንግዲህ 330 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በዓመት ማምረት ማለት በቀላል የሚታይ አይደለም። በድፍን አፍሪካ በዚህ ደረጃ የሚያመርት ሃገር የለም። ይሄን ደግሞ ሳንዘናጋ አሁንም የቀሩ ቦታዎች ቴክኖሎጂ መጠቀም ብናሳድግ በአጭር ጊዜ ውስጥ አምስት መቶ ሚሊዮን ኩንታል መግባት እንችላለን ብዙ ሳንቆይ ማለት ነው። ያን ለማድረግ አሁንም አርሶ አደሩ፣ በግብርና ዘርፍ ውስጥ ያሉ የግብርና ማስፋፊያ ሙያተኞች፣ የዝናብ ወራትን ሲዘንብ ከዝናብ መሸሽ ሳይሆን ያንን ዝናብ እንዴት አድርገን እንደምናቆይ የሚያስቡ አመራሮች፣ አፈር ለመንካት ጭቃ ለመንካት ማሳ ውስጥ ገብቶ ለማየት ለማገዝ የሚተጉ አመራሮች እየተፈጠሩ ሲሄዱ ምርታማነት ያድጋል።

እንግዲህ ኢትዮጵያችን ተስፋ አላት! በግብርና ዘርፍ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አንዱ ዋና የእድገታችን መንገድ ነው ያልነው አዋጭ ሆኗል። ልክ እንደ ኢንዱስትሪው፣ ልክ እንደ ቱሪዝሙ፣ ልክ እንደ ማዕድን፣ ልክ እንደ ቴክኖሎጂው ግብርናውን እራሱን አስችሎ አመርቂ ውጤት እያመጣ ነው ያለው። አሁንም ብዙ የማደግ አቅም ስላለው እንበርታ፣ እንስራ፣ እንማር፣ እናሻሽል! ከትናንትናው እያረምን፣ እያረቅን፣ እያሻሻልን ከሄድን የምናስባትን ሃገር ለመፍጠር የሚያስችል መሰረት እንዳለ ያመላክታል።

ከሁሉ በላይ የሚያስደስተው የሃሳብ ጥራት ነው። መድፈር፣ መሞከር፣ መፍጠር! ከፈጠርን በኋላ መፍጠን፣ ማሰናሰል፣ ለትልቁ ነገር መጓዝ የሚለው ህልማችን እና እሳቤያችን ፍሬያማ እየሆነ ነው ያለው። በዚሁ እንድንበረታ፣ እንድንሰራ፣ እንዳንቆም፣ በጥረት፣ በልፋት፣ በላብ ብቻ የሚገነባ ሀገር እንድንመሰርት፤ ልጆቻችን ስንጥር፣ ስንለፋ፣ ስንተጋ እንዲያዩ ከዚያ የሚገኘውን ውጤት በጋራ መሰብሰብ እንድንችል ያንን ባህል መለማመድ ማሳደግ ያስፈልጋል። ሁሉም ቀን መጠቀም አለብን፣ ሁሉንም ወቅት መጠቀም አለብን ለማምረት፣ ለመልፋት፣ ለመስራት፣ እና ከዚያም ለመብላት ብቻ አይደለም፣ ለማብላትም ጭምር፣ ለመርዳትም ጭምር መጠቀም ይኖርብናል። በዚህ መንገድ የባህል ለውጥ፣ የአስተሳሰብ ለውጥ፣ የአሰራር ስርዓት ለውጥ፣ የስራ ባህላችን እየተቀየረ ሲሄድ፣ እንዳያችሁት የሚያስደስት ማሳ፣ የሚያስደስት ውጤት ኢትዮጵያ ውስጥ ማየት የተለመደ ይሆናል!

ዛሬ በሰሜን ሸዋ ባየሁት ስራ በእጅጉ ደስ ብሎኛል። ይሄ በሁሉም ዞኖች እንዲስፋፋ, በሁሉም ዞኖች እንዲበራከት መጪው ክረምት ከፍተኛ ስራ የሚጠበቅበት ወቅት ነው። ለዛ ሁሉም አርሶ አደሮች፣ የግብርና ማስፋፊያ ሙያተኞች የተሰናዱ፣ የተዘጋጁ እንዲሆኑ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ዓለም ያለችበት ሁኔታ የምናልፈው የምንሻገረው በልማት ብቻ ነው! ካረስን፣ የጀመርነውን ከጨረስን፣ ከበረታን እንሻገረዋለን። ከስራ ውጭ መሻገሪያ መንገድ እንደሌለ አስበን ጊዜያችንን በስራ፣ በልማት እንድናጠፋ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሰሜን ሸዋ ዞን ሱሉልታ ወረዳ

በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የቀረበ ሃሳብ

ግንቦት 7፣ 2018ዓ.ም

በመጀመሪያ ላለፉት ዓመታት የደከሙባቸውን፣ የሰሩባቸው፣ የመሯቸውን ስራዎች በዚህ መልክ ጥርት ባለ ሁኔታ ስላቀረቡልን ማመስገን እወዳለሁ። አስራ አንዱን ኮሚሽነሮችንም በታላቅ ትዕግስት፣ በሙያ ብቃት፣ በብዙ ፈተና ውስጥ እንዲህ ያለውን ሀገራዊ ሃላፊነት ለመወጣት ልክ እንደ ወታደር የገባችሁትን ቃል ለመፈጸም ላደረጋችሁት አስተዋጽኦ እንዲሁ ከፍተኛ ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ።

የውይይት ባህል እንደ ኢትዮጵያ ላለ ሀገር በእጅጉ አስፈላጊ ነው። የሲቪክ ባህል የምንገነባው ስንወያይ፣ ስንደማመጥ፣ ስንግባባ የውይይታችን ውጤትም ወደ ተግባር እንዲቀየር ከልብ ስንሻ እና ስንፈጽም ነው እና ይህ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ስራ በአፈጻጸም የሚያመጣቸው ውጤቶች ብቻ ሳይሆኑ በባህልም ጭምር ለውጥ የሚያመጣ ይመስለኛል። የምክክር ፣ የውይይትን ልምምድ እንደ ሃገር እንድናነለብት የሚያግዝ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ ያለ እድል ተገኝቶ አያቅም፤ ስናገኘው ሊራከስብን አይገባም! ይህ እድል እንዲገኝ ብዙዎች ታግለዋል፣ የህይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል፣ ጠይቀዋል፣ ታስረዋል፣ ተሰቃይተዋል እንወያይ በምክክር፣ በውይይት ጉዳያችን ይፈታ ሲሉ ብዙዎች የታገሉበትን አላማ ዛሬ እድል ሲገኝ ማደነቃቀፍ ተገቢ አይሆንምና መልካም መሰረት የሚጥል፣ አዲስ ባህል የሚገነባ ሂደት የሚሆን ይመስለኛል።

የምክክር ኮሚሽኑ አትኩሮት መሆን ያለበት ዋናው ጉዳይ በህግ የተሰጠውን ስልጣን ጠንቅቆ ማወቅና በዚያ ስልጣን ማዕቀፍ ውስጥ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት መወጣት ነው የመጀመሪያው ተግባር። ሁለተኛው ተግባር የሚሆነው በህግ ባይሰጥም በነበረው ሂደት የተገኙ እውቀቶች፣ የተገኙ ጠቃሚ ለፖሊሲ ግብአት የሚሆኑ ሃሳቦች ደግሞ ካሉ ደምሮ በጎንዮሽ መስራት ጠቃሚ ይሆናል። ዋናው ትኩረት ግን በህግ የተሰጠን ስልጣን ላይ ያተኮረ መሆን አለበት።

ይህ የምክክር አካሄድ አንደኛ በሥነ-ዘዴው፣ በተመረጠው ሥነ-ዘዴ፤ ሁለተኛ የኢትዮጵያን ባህል፣ የኢትዮጵያን ማኅበረሰባዊ ሃብት፣ የኢትዮጵያን ድልብ የማኅበረሰብ ዕውቀት ለመጠቀም የተሞከረበት ሁኔታ፤ ሶስተኛ አካታች፣ አሳታፊ ለማድረግ የተሞከረበት ሁኔታ ለብዙ ሃገራት ልምድ የሚሆን ለእኛም በእጅጉ የሚጠቅም ይመስለኛል። ሲጀመር ጀምሮ ከስር ወደ ላይ ይሁን ማኅበረሰቡ ይወያይ የተባለበት ምክንያት አልበርት

አንስታይን እንደሚለው ችግሩን በፈጠሩ አእምሮ መፍትሔ ማፍለቅ አስቸጋሪ ስለሆነ ጽንፈኛ አስተሳሰቦች በብሔር፣ በፖለቲካ፣ በጉርብትና አብሮ መኖር፣ አብሮ መብላት፣ አብሮ መስራት እንዲስተጓጎል ያደረጉ ኤሊት የሚባሉት መፍትሔ ያመነጫሉ፤ ብቻቸውን ብሎም በብዙ አፍሪካ ሃገር ያየነው ውጤት እኛ ሃገር ከመድገም ባሻገር የምናስበውን ነገር በተሟላ መንገድ አያመጣልንም፤ እነሱም ቢሆኑ ግን መገለል የለባቸውም አካታች ስለሆነ የእነሱም ሃሳብ ይደመጣል። የማጎበረሰብን ሃሳብ ማድመጥ ችግር ባልፈጠሩ ግን የችግሩ ገፈት ቀማሽ በሆኑ፣ የችግሩ ጣጣ የወደቀባቸውን ማጎበረሰብ ማድመጥ ደግሞ የተሻለ መፍትሔ ለማምጣት የሚያገዝ ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ የእድገት ችግር ከሞላ ጎደል ሁሉም ፖለቲከኛ መሆኑ ነው። የእኛ ህልም ሁሉም ፖለቲከኛ ከሚሆን ጥቂት ሳይንቲስት፣ ጥቂት ሀብት ፈጣሪ እና ስራ ፈጣሪ ሰዎችን ማብዛት ፖለቲከኞችም በዛው ልክ በጥልቅ ፍቅር፣ በፍላጎት የሚሳተፉ ሰዎች እየሆኑ ሲሄዱ እንደ ሌላው ሀገር ሁሉም በሙያው ለአንድ ታላቅ ርዕይ ማገልገል የሚያደርግበት አውድ ይፈጠራል። አሁን ግን ሁሉም ነጻና ቀላል የስራ መስክ ስለሆነ አብዛኛው ሰው በፖለቲካ ይሳተፋል፤ በዚያ ምክንያት ሌሎች ሙያዎች ቢገኙ ቢኖሩ ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦች ኢትዮጵያ ውስጥም እምብዛም እንዳይሰፉ አድርጓል።

የምሰጣቸው ሃሳቦች ፕሮፌሰር በደንብ ገልጸውታል ግን አሁንም ልምድ ይቀመር፣ በመጽሃፍ መልክ ይዘጋጅ ለልጆቻችን፣ ለሌሎች ሀገራት በእጅጉ አስፈላጊ ስለሆነ ይህንን ስራ አቅልለን ሳናይ መሰነዳችን መልካም ሆኖ ግን ደግሞ ሰዎች ጋር ደርሰው ሊያነቡት በሚችሉት አግባብ ተቀምሮ በመጽሃፍ መልክ ቢዘጋጅ ይጠቅማል ብዬ አስባለው። አንዱ ውጤትም ቢሆን ብዬ አስባለው። ሁለተኛ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ጨርሳችሁ አጀንዳ ለይታችኋል፣ ተወያይ ለይታችኋል አሁን እነዛን ሰዎች ጠርታችሁ ዋናውን ውይይት ማድረግ ሁለተኛው ምዕራፍ ነው የቀራችሁ። በጣም አስቸጋሪ የሚባለው ክፍል እስከአሁን የተሰራው ነው። ወደ እያንዳንዱ ወረዳ መሄድ፣ ከብዙ መቶ ሺህ ሰዎች ጋር መነጋገር፣ ውጪ ሀገር መዞር የሚጠይቀውን ክፍል ጨርሳችኋል።

ዛሬ ያደረጋችሁት ሪፖርት በዛሬው መድረክ ላይ ፌዴሬሽኑን ያቋቋሙ የፌደራል መንግሥታት አሉ፣ በፌደራል መንግሥት ሶስቱ የመንግሥት አካላት አሉ ከሞላ ጎደል መንግሥት ይሄ ነው፣ የፓርላማ ቋሚ ኮሚቴ አባላት አሉ፤ መንግሥትን በደንብ መወከል የሚችል ስብስብ ነው የዛሬው ስብስብ ነገር ግን ይሄ በቂ አይደለም። ነገ ከነገ ወዲያ የሃይማኖት አባቶችን አንድ መድረክ አግኝተው ይሄን ሪፖርት ቢሰሙ፣ የሚዲያ ሰዎች በመንግሥትም፣ በግል ዘርፉም ያሉ ተመርጠው ይሄንን ጉዳይ ቢሰሙ ታዋቂ ሰዎች፣

ይሄንን ጉዳይ ቢሰሙ። ምን ማለት ነው - ቢያንስ አምስት፣ ስድስት ቀን የተለያየ መድረክ እየፈጠራችሁ እስካሁን የሄዳችሁበትን ጉዳይ ሪፖርት በማድረግ ውስጥ ተጨማሪ ሃሳቦች ካሉ፣ የመረጃ እጥረት ካለም፣ ስራችሁን ወደ ህዝብ ለማድረስም ጠቃሚ ስለሚሆን በዛ አግባብ ቢሰራ መልካም ነው ብዬ አስባለው።

ህዝብ አዋቂ፣ አሳቢ፣ ፍላጎቱን የሚያውቅ፣ ፍላጎቱንም በባህል በስነ-ምግባር መግለጥ የሚችል መሆኑን ባያችሁት ሂደት ትምህርት የቀሰማችሁ ይመስለኛል። የሚናቅ ህዝብ የለም፤ የሚናቅ ሰው የለም። ሰው በተፈጥሮ ብዙ ነገር ይማራል በእድሜው ይማራል፤ እኛም ብንሆን በየወራቱ፣ በየዓመቱ እድሜያችን በጨመረ ቁጥር ከዚህ ቀደም እናውቀዋለን ብለን ከምናስበው ባሻገር ብዙ ዕውቀት ልምድ እያገኘን እንሄዳለን። የሰው ልጅ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ይቀየራል በየእድሜ ዘመኑ ይበልጥ ያስፈልገኛል ብሎ የሚያስባቸው ጉዳዮች እየተተኩ ሌላ አዳዲስ ፍላጎቶች እየተፈጠሩ ይሄዳሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የህዝብን ዕውቀት፣ የህዝብን ጥበብ፣ የህዝብን ሀገር መውደድ አራክሶና አናንቆ ማየት ተገቢ አደለም።

ከታች ጀምሮ የተደረገው ውይይት ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በተለየ መንገድ ለብዙ አፍሪካ ሃገራት ልምድ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ዋጋ የሚከፈለው ያ የምንንቀው ህዝብ ነው፤ እኛ እናቃለን፣ እንምከር፣ እንወያይ የምንለው አይደለንም፤ መጨረሻ ላይ ህይወቱን፣ እግሩን፣ እጁን፣ አይኑን ሰጥቶ ሀገር የሚያፀናው፤ የሚያቆየው ያ ለውይይት እንኳ አትበቃም የተባለው ማኅበረሰብ ነው። አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፤ የኢትዮጵያ ሰላም ጸንቶ እንዲቀጥል የሚያደርገው ያ የምንነቀው አርሶ አደር፤ አርብቶ አደር ነው። በእርሱ ላብ፣ በእርሱ ድካም፣ በእርሱ ያልተቆጠበ ትጋት ነው እናውቃለን የሚሉ ሰዎች የተሻለ ክፍያ፣ የተሻለ ጥቅም አግኝተው የሚኖሩት ስለዚህ ያንን ማኅበረሰብ ማክበር፣ ለእውቀቱ እውቅና መስጠት አስፈላጊ ይመስለኛል። ከስር ወደ ላይ ያለው ውሳኔ ትክክል መሆኑን ማረጋገጫ ካገኘሁባቸው አንዱ ዛሬ ያቀረባችሁት ሪፖርት ነው። ህዝብ እንደ ህዝብ ከራሱ ያለፈ ጥያቄ ማንሳት የሚችል መሆኑንም ማረጋገጫ አግኝቻለሁ።

በድጋሚ ዛሬ ላረጋገጥላችሁ የምፈልገው ጉዳይ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ አሁን ያለው መንግሥት ስልጣን ዘመኑን ሳይጨርስ የእናንተ ጉዳይ ከመጣ በተቻለ መጠን ሃሳቦቻችሁን ወደ መሬት ለማውረድ፣ ምክረ ሃሳቦቻችሁን ተጠቅመን ለማሻሻል እስከዛም ሂደቱ ደግሞ የተሳለጠ እንዲሆን ለማገዝ በእኛ በኩል ዝግጁ ነን። በዚህ ጉዳይ እንደ መንግሥት እንደ ፓርቲም ተወያይተን ጣልቃ መግባት የለብንም ሲያሻቸው ግን መደገፍ አለብን ብለን በወሰነው መሰረት ከኛ የሚያስፈልጋችሁን ድጋፍ እንሰጣለን፤ ከእናንተ በሂደት የተገኘ

ዕውቀት፣ የተገኘ ልምድ፣ የተገኘው ጥበብ ደግሞ ለቀጣይ ስራችን እንደ ግብዓት አድርገን ለመጠቀም በመንግሥት በኩል ዝግጁ መሆኑን መሆናችንን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። ይሄ ጥያቄ የመልስ መርሃ ግብር አይደለም እናንተ የሄዳችሁበት ርቀት ሪፖርት አቅርባችኋል፣ እኛ አድምጠናል፣ በሰራችሁት ስራ ኮርተናል! ልጆቻችን በታሪክ ማህደር ውስጥ የእናንተን ስራ፣ የእናንተን ጥረት እየመነዘሩ፣ እያዩ ብዙ ትምህርት እንደሚያገኙበት ጥርጥር የለውም።

እንደ እናንተ ያሉ ዕውቀትም፣ እድሜም፣ ልምድም ያላቸው ኢትዮጵያውያን መኖራቸው በራሱም ትልቅ እድል ነው። ለዚህም ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ኩራት እንደሚሰማቸው ተስፋ አደርጋለው ምክንያቱም በብዙ አፍሪካ ሃገራት ይህ ስራ የተሰራው እናንተ በለፋችሁበት መንገድ አይደለም። በጥቂት ሆቴሎች ውስጥ ያለቁ ስራዎች ናቸው። የጥቂት መንግሥታት ፍላጎት የፈለጉትን አንቀጽ ቀይረው ሕገ መንግሥት ተሻሽሏል ያሉበት ነው። የአብዛኛው የአፍሪካ ሃገራት የሕገ መንግሥት ማሻሻያ የተደረገው የመሪዎቹን የስልጣን ጊዜ ለማራዘም ነው። ሁለት ዙር ስላልበቃቸው ሶስት እናድርግላቸው፣ አራት እናድርግላቸው፣ የእድሜ ልክ እናድርግላቸው በሚል ነው ሕገ መንግሥትን የሚቀየረው። የእኛ ሕገ መንግሥት ደግሞ የሚቀየረው እድሜ ገደብ የሌለውን የስልጣን ከባቢዎች በጊዜ ለመገደብ ነው። ከስር ወደ ላይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ስልጣንን በህግ ለመገደብ ያለው እሳቤ በራሱ የተለያየ ነው።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርቲው እስካሸነፈ ድረስ እና መምረጥ እስከቻለ ድረስ የጊዜ ገደብ የለበትም አሁን ባለው ሕገ መንግሥት አሁን እዚህ እየተወያየን ያለነው ግን ያ አደገኛ ነው እንገድብ ብለን ነው። በብዙ ሃገራት ያለው ግን ከዚህ ተቃራኒ ነው። ይሄ በራሱ እሳቤው አልወያይም ብሎ የሚያስቡ ሰዎች ራሳቸውን እንዲጠይቁ የሚያስገድድ ይመስለኛል። እንዴት ነው መንግሥት ወዶ እና ፈቅዶ ህዝብ ተወያይቶ ስልጣኔ በህግ ተገድቦ የህዝብ ጥያቄዎችን በሕገ መንግሥት ተካተው እንዲሻሻሉ ፍቃድ አለኝ ሲል፤ ለዚያ መሻት የሚታገሉ ሰዎች አንወያይም እንዴት ይላሉ? ካልተወያዩ ለምን ፖለቲካ ይፈልጋሉ? ፖለቲካ በተቀዳሚነት ውይይት ነው፤ ይሄ ውይይት ያስፈልጋል! ለኢትዮጵያ ያስፈልጋል።

በኛ በኩል በዚህ ውይይት የመጡ ምክረ ሃሳቦች ተቀብለን ለማሻሻል፣ ለማስተካከል፣ የስራችን አካል ለማድረግ ዝግጁ ነን። በሕገ መንግሥቱ ማሻሻያ መሰረት የዚህ ሀገር መንግሥት የስልጣን ጊዜ እንዲገደብም ግንባር ቀደም ፈላጊዎች ነን፤ መገደብ አለበት ብለን እናምናለን። በዚህ ህግ መሰረትም እንዲፈጸም እንሰራለን። እስካሁን ባለው ሁኔታ ግን በህዝብ የተመረጠ ፓርቲ ወይም እሱ የወከለው ጠቅላይ ሚኒስትር እስከመቼውም

ማገልገል የሚያስችል ህገ መንግሥታዊ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። የፖለቲካ ፍላጎት፣ የስልጣን ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ይሄን ለማሻሻል እድል የሚሰጥ ውይይት ከመንግሥት በላይ ደስተኛ ሆነው መሳተፍ የሚጠበቅባቸው ይመስለኛል። ምክንያቱም መንግሥትማ ለሱ የሚጠቅም ለሱ የሚሻል አለው፤ የእርሱን ፍላጎት የሚቃረን ህግ ለማውጣት መንግሥት ከፈቀደ የስልጣን ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ደግሞ ያ ነገር እንዲሳካ ቢያደርጉት ተመራጭ ይመስለኛል። ነገር ግን በመቶ ሺዎች ህዝብ አወያይታችሁ፣ 4000 ተወካይ አወያይታችሁ፣ ከሺ በላይ ወረዳ አወያይታችሁ፣ በሁሉም ዓለም ከሞላ ጎደል ዲያስፖራ አወያይታችሁ እየመጣ ያለ ሀሳብ ነው።

እንደዚህ ያለ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ አናውቅም ጥቂት መቶዎች ተሰብስበው ነው ሕገ መንግሥትን የሰጡን ከዚህ ቀደም በሌላም ሃገር እንደዚህ አይነት ውይይት አይተን አናውቅም እና ከበቂ በላይ የኢትዮጵያን ፍላጎት መመለስ የሚችል ከ90 በመቶ በላይ ኢትዮጵያን ያሳተፈ ሂደት ስለሆነ ለምናስበው ለውጥ፣ ለምናስበው ማሻሻያ መሰረት መጣል የሚችል ይመስለኛል።

እያወራሁ ያለሁት አጠቃላይ የመንግሥት አካላትን ወክዬ ነው፤ በእኛ በኩል የምትጠይቁንን አቅም በፈቀደ መጠን እንመልሳለን፣ ድጋፍ እንሰጣለን፣ እንዲሳካላችሁ እንመኛለን። ስለነበራችሁ ትጋት፣ ጥረት እና ገለጻ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ቀጣዩ ጊዜ የተሳካ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ!
አዲስ አበባ

የገላን ጉራ የኢንዱስትሪ መንደር ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ግንቦት 8፣ 2018ዓ.ም

ክቡር አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣
ክቡር አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣
ክብርት ከንቲባ፣
ክቡራን ሚኒስትሮች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አባ ገዳዎች፣ ወጣቶች፣ የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች፤ እንኳን ደስ ያላችሁ!
ዛሬ ይህ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተመርቆ ስላየን ሳይሆን የዛሬ ሁለት ዓመት፣ አንድ ዓመት ተኩል ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት እመላለስ ነበር እና ይሄ መንገድ አልነበረም፤ ይሄ ሰፈር የዛሬ ሁለት ዓመት ገጠር ነበር። መኪና የማይደርስበት፣ ሰው የማይረግጥበት ገጠር ነበር። ይሄ መንገድ በሚሰራበት ወቅት ከዛኛው ጫፍ መጥተን ወደ ቦሌ መሻገር አንችልም ድልድይ አልነበረም። ዛሬ ግን በሚሊየን የሚቆጠር ችግኝ ተተክሎ፣ መንገዱ እንዲህ አምሮ፣ ቤቶች እየተገነቡ፣ እንደዚህ ያለው ፓርክ ተገንብቶ እውነት ለመናገር ለረጅም ጊዜ የምናውቀው የከተማይቱ ማዕከል አካባቢ ካሉት ቦታዎች አንጻር ሲነጻጸር በእጅጉ የተሻለ ከተማ ሆኗል አሁን።

አንደኛ በጣም ቆንጆ የእግረኛ መንገድ፣ መብራት አለው። ሁለተኛ ለከባቢ ብቻ ሳይሆን ከከተማም እየመጡ የሚጠቀሙበት ትልቅ ፓርክ የተገነባው በዚህ አካባቢ ነው። ሶስተኛ ለወጣቶች ስራ እንዲመች የኢንዱስትሪ ፓርኮች አሉ። የቤቶች ግንባታ አለው፣ ቦሌ እና ጎሮን፤ ቦሌ ለሚን እና ቦሌን በማገናኘት ረገድ በሲኤምሲ እና በጎሮ መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ከባቢ፤ አዲስ ሰፈር፣ አዲስ መንደር፣ አዲስ ከተማ የተለወጠ ሰፈር፤ የተለወጠ ፊት ያየንበት ስለሆነ ፈጣሪያችን እናመሰግናለን።

የእኛ ፍላጎት እና ህልም በተቻለ መጠን ከደህነት ከችግር የተላቀቀች ሃገር የሚፈጥር የሚሰራ ትውልድ፣ የሚረዳ ዜጋ መፍጠር ነው ሌላ አላማ የለንም። ይሄ ዜጋ ክርስቲያን እስላም የለውም፣ ይሄ ዜጋ አማራ ኦሮሞ የለውም፤ ኢትዮጵያዊ በሙሉ እራሱን ችሎ ከዚያ ሱማሊያን፣ ኬንያ፣ ዩጋንዳን ሌሎች ወንድሞቻችንን ማገዝ የምንችልበት ደረጃ ማድረግ እንፈልጋለን ፍላጎታችን ይሄ ነው። ለዚህ ፍላጎት የቀና ልብ ያለው ኢትዮጵያዊ በሙሉ ተባባሪ መሆን አለበት። ካለፋን ካልሰራን ሀገር አይለወጥም። እንዳያችሁት ነው እዚህ አካባቢ በተሰራው ስራ ብቻ ነው ለውጥ ያየነው። ሌላም የቀረ አካባቢ እንዲሁ እየሰራን ስንሄድ ሀገር ይቀየራል ሰው ይቀየራል። አርሶ አደር በዚህ እና በዚህ ሰርቶ፣ በፀሐይ እና በዝናብ ሰርቶ ያቀናው ሀገር ላይ አፈናቅለን የምንጥለው ከሆነ እሱ አቅም

የለውም አያቆምንም፤ አርሶ አደርን በሚጥል፣ ደሃን በሚጥል፣ እጅ አጠሮችን በሚገፋ መልክ የሚሰራ ልማት የትም አያደርስም ግን ህይወታቸውን የሚያሻሽል፤ አንድ ሰው ሽንት ቤት ሳይኖረው፣ ሰው ሲታመምበት ለመጠየቅ የማያስችል የኑሮ ዘዬ ውስጥ እየኖረ፣ ሰው ሲሞትበት ቦታ አጥቶ አስፓልት እየዘጋ ቆጥ ላይ እየኖረ ያን ነገር ለመቀየር የሚደረግ ጥረት መቃረን ተገቢ አይደለም።

በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ቤቶች ፈርሰዋል እየተባለ ይነገራል፤ ይሄን ነገር ከጊዜያዊ ፍላጎት፣ ከስሜት፣ ከፖለቲካ ወጣ ብሎ ማየት ጠቃሚ ነው። ኢትዮጵያን እንስራት ዓለም እየቀና እየተደነቀብን ባለ በዚህ ጊዜ ውስጥ እኛ አይናችን ከታወረ ለማደግ እንቸገራለን እና የነበርንበት የኑሮ ዘይ አስቀያሚ ነው፣ ችግር ደህንነት መጥፎ ነው፣ የሰው እጅ ማየት በግልም እንደ ሃገርም አስቀያሚ ነው፤ ከዛ ወጥተን እራሳችንን መቻል እንድንችል መተባበር፣ መስራት፣ መትጋት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ወደ ኢንዱስትሪው ስመለስ፤ ኢንዱስትሪ እንደ ግብርና አይደለም። ግብርና ሰኔ አርሰን መስከረም ይታጨዳል፣ ሃምሌ አርሰን ጥቅምት ይታጨዳል ይሄኛው ጊዜ ይፈልጋል። እንዳያችሁት እዚህ ቦታ ላይ መንገድ ሳንሰራ፣ ኤሌክትሪክ ሳናመጣ፣ ውሃ ሳናመጣ፣ ህንጻዎችን ሳንገነባ፣ ማሽነሪዎች ሳይሟሉ ኢንዱስትሪ መሆን አይችልም። እነዚህን ማሟላት ደግሞ ዓመታት ይፈልጋል መንገዱ እራሱ።

አሁን ዛሬ እዚህ ቦታ ያየሁት ነገር አንደኛ ወደኋላ መለስ ብዬ ስራዎቻችን እንድታዘብ እንደመረምር፣ ሁለተኛ ወደፊት አቅጣጫችን እንድመለከት በእጅጉ የሚያግዝ ስራ ነው። ሃዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስንሰራ ሰፊ ሼድ ገንብተናል በጣም በብዙ ገንዘብ ከዛ የውጭ ሰዎች መጥተው ኢንዱስትሪ ከፍተዋል። ችግር አጋጥሞን አጎዋ ሲባል ጥለውን ሄዱ ሰማንያ ዘጠና በመቶ ክፍት ቀረ። የተሰራው ፓርክ በብድር ነው፣ በጣም ብዙ ሃብት የወጣበት ነው የመጡት ጥለው ሄዱ፤ ያሉትስ? ታክስ አንከፍልም፣ ጊዜ ስጡን፣ ከውጭ ምናስገባውን እቃ አታስከፍሉን ጣጣው ብዙ ነው። እዚህ ዛሬ ያየናቸው ልጆች ግን የዛሬ አራት ዓመት፣ አምስት ዓመት፣ ስድስት ዓመት፣ ሰባት ዓመት ስራ ያልነበራቸው የተደራጁ በአነስተኛና ጥቃቅን ስራ የጀመሩ ዛሬ 40 ሰው፣ 50 ሰው፣ 60 ሰው ቀጥረው ነገ በሺህ እንቀጥራለን እያሉ ተስፋ ሲሰጡ ማየት በጣም በጣም አስደስታች ነገር ነው። በዚህ መደሰት ከሁላችን ይጠበቃል።

የኔ ተስፋ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያሊስት የሚፈልቁት እዚህ ውስጥ ነው። እነዚህ ልጆች ጭንቅላታቸው፣ ልባቸው፣ እጃቸው፣ ተሰናስሎ መልካም ነገር መፍጠር ይፈልጋሉ። ያስቸገራቸው ቦታ፣ ካፒታል፣ ድጋፍ ማጣት ነው። ያን በመጠኑ ስናመቻች እንዳያችሁት

በዚህ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለግብርና ስራ የሚውል ፓምፕ ይመረታል። እኛ ፓምፕ ከውጭ ለማስግባት መከራ እናያለን። በዚህ ኢንዱስትሪ ውስጥ የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካ ይመረታል፣ የመኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ይመረታል፣ የብሎኬት ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ይመረታል፤ ፋብሪካ ነው የሚመረተው። ፋብሪካን ማምረት የሚችሉ ወጣቶች ኢትዮጵያ መፍጠር ከቻለች ለእነዚህ የሚደረግ ማንኛውም ድጋፍ የሚባረክ ነገር ነው ጉዳት የለውም ጥቅም ብቻ ነው።

የዛሬውን ስራ ማየት ያለብን ልክ እንደ መዋለ ህጻናት ነው። መዋለ ህጻናት ሳንገነባ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳንገነባ ምንም አይነት ስለ ኢንዱስትሪ እና ፓርክ ቢወራ ዋጋ የለውም። መጪው መጥቶ የሚወስደውን ከወሰደ በኋላ ይሄዳል፤ ቀሪው የእኛ ሰው ነው። የእኛ ኢንዱስትሪ በኛ ሰዎች እንዲሰራ ማድረግ ያስፈልጋል። ያ ማለት የውጪውን እንግፋ አይደለም፤ ዕውቀት ያስፈልጋል፣ ካፒታል ያስፈልጋል ይምጡ ግን ተሰናስለን፣ ተባብረን፣ ተደምረን ሲሆን ነው አስተማማኝ ኢንዱስትሪ የሚገነባው። እና ይህ ስራ በጣም አስደሳች ስራ ነው ሁሉም ክልሎች ከዚህ ስራ መማር አለባቸው። በተናጠል ኢንዱስትሪ አያዋጣም፣ ኤሌክትሪክ አስቸጋሪ ነው፣ መንገድ አስቸጋሪ ነው፣ ውሃ አስቸጋሪ ነው፣ ሰብሰብ ሲል ለኢንዱስትሪያሊስቱ በጣም ስለሚቀል፣ ለገበያ ትስስር ስለሚመች መሰብሰብ ጠቃሚ ነው። አዲስ አበባ መጨመር አለበት፣ በክልል መጨመር አለበት፣ መበርታት አለብን።

ስንሰራ ግን ልክ ዛሬ እንዳየነው አርሶ አደሮች ቢያንስ ቢያንስ አንድ ሄክታር ሰጥተው 50 እና 60 ካሬ ላይ ሱቅ ቢኖራቸው ማን ይጎዳል በዚህ? እነርሱም ዜጎች ናቸው፣ እነርሱም ጭንቅላት አላቸው፤ እነርሱም ከታገዙ ይሄው ከኛ ጋር ተቀላቅለው መሸጥ መነገድ ይችላሉ። ይሄ የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢንዱስትሪያሊስት እሳቤ መሆን አለበት። ሲሰራ ደሃውን የኖረውን ሰው ባቀፈ እና ኑሮ ባሻለ መንገድ ከተሰራ በጣም በጣም መልካም ይሆናል። በብዙ መልኩ እየተሳካልን እየተከናወን እንገኛለን። የመከናወኑ ሚስጥር በንጹህ ልቦና ሀገርና ህዝብን ማገልገል ነው። በንፁህ ልቦና ሀገርና ህዝብን ስናገለግል ሁሉን ቻይ የሆነው ፈጣሪ ደግሞ ያግዛል። ያ ድጋፍ እንዲቀጥል እንዲበረታ እንዲፈጥን ጊዜ እንዳናባክን በአጠረ ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን ለውጠን ለማየት እንድንችል ዜጎች ብንበረታ ጥሩ ነው።

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ስንት ጎዳና የነበሩ ልጆች ሰልጥነው ስራ እንደያዙ ቁጥራቸውን ብታቁ፣ ስንት በየመንገዱ ያሉ እህቶቻችን በየቡና ቤት ያሉ እህቶቻችን ሰልጥነው ስራ እንደያዙ ብታቁ፣ ወጣቶች ስራ እንዲያገኙ የሚያስችል መድረክ ስንፈጥር የተረሱ የተዘነጉ

ሰዎች አካል ጉዳተኞችም ጭምር እድል እንዲያገኙ ስለሚያስችል ኢትዮጵያውያን ጓዳችን ሲገባ ሳይሆን በሰፈራችን ለውጥ ከመጣ የምናመሰግንና የምናግዝ መሆን አለብን። ዓለም እንዳያችሁት ነው መጤ አይፈልግም፣ የመጣበትን ያባርራል። ስንከዳትም ስንመጣባትም የማትሰለቸው እናት እቺው ናት፣ እሷን መጠበቅና ማልማት ያስፈልጋል።

በዚሁ አጋጣሚ ማንሳት የምፈልገው አንድ ጉዳይ በደንብ ጥናት ይፈልጋል፤ እናንተም ጠይቁ። ወንጪ የምናሰራው ቤተ-ክርስቲያን አለ። የወንጪ ቤተክርስቲያን ታሪካዊ ናት ወደ 800 ዓመት ቆይታለች ግን ስላረጀች እያሰራናት ነው። እሷን ለማየት ስሄድ ሰራተኛ የለም። ወንጪ አካባቢ ሰዎች ተጨማሪ ክፍያ ተከፍሎ ከአዲስ አበባ የተወሰዱት፤ ጅማ ስራ አለን ሰራተኛ የለም። ስኳር የምንሰራባቸው ቦታዎች ሰራተኛ የለም። በየቦታው ሰራተኛ ችግር ነው ይባላል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ስራ የለም ይባላል። አልገባኝም የቱ ጋር እንደሆነ ችግሩ? ቤት ሰራተኛ ማግኘት መከራ ሆኗል ታውቃላችሁ፣ ቤት ሰራተኛ የለም፣ ሾፌር ችግር ነው፣ የቀን ሰራተኛ የለም ስራ ደግሞ የለም ይባላል። ስራ ተርፏል፣ በቅቷል ብዬ አይደለም ግን ያልሸፈናቸው ቦታዎች አሉ። አንዳንድ ቦታ ከህንድ፣ ከፊሊፒን ከተለያየ ሀገርም ኢትዮጵያ ውስጥ ሰራተኞች ቻይና ብቻ ሳይሆን ብዙ ሃገር ማየት ተጀምሯል። ኬንያ፣ ናይጄሪያ ብዙ ነው የማገኛቸው።

ኢትዮጵያውያን ብንነቃ ጥሩ ነው። ዝም ብለን የሚባለውን መድገም፣ የተዘመረውን መዘመር፣ የተሰደበውን መስደብ ሳይሆን ችግሩ የት ነው ያለው? ስራ አለ ወይስ የለም? እኔም እናንተም ካልሰራን ላባችን ካልተንጠባጠበ ለውጥ አይመጣም። በስራ ብቻ ነው ለውጥ የሚመጣው፤ ለዚያ መትጋት ይኖርብናል። እርሻ ላይ ጥረት የሚያደርጉ ወጣቶች አይቻለው፣ ዘመናዊ በሆነ መንገድ በመስኖ፣ በአቀባዊ ግብርና የሚሰሩ ወጣቶች በጣም የሚገርሙ መብዛት አለባቸው። በቱሪዝም የጀመርናቸው ጉዳዮች ውጤት እያየንበት ነው። ሰዎች እየመጡ ነው፣ ሰዎች ከአውሮፓ እየመጡ፣ ከአሜሪካ እየመጡ በእናንተ ሃገር እድገት እየተደነቁ እየተደመሙ እናንተ አላየንም አልሰማንም አትበሉ ምክንያቱም በተቀዳሚነት የእናንተ ልፋት ውጤት ስለሆነ። እነሱን ካስደሰተ ይበልጥ ደግሞ በሚቀጥለው አዳዲስ ስራ እየሰራን እንድንጠብቃቸው ተነቃቅተን መሆን አለብን፣ ኃይልን ተሞልተን መሆን አለብን እንጂ ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም እንበርታ።

ኢትዮጵያ በቅርቡ ጉተሬሽ ሲናገር ሰምታችኋል 10.2 በመቶ የምታድግ ብቸኛ ሀገር ናት፣ በድፍን አፍሪካ 10.2 በመቶ እድገት የሚያድግ አንድም ሃገር የለም። ይሄንን እድገት እናፋጥን፣ ይበልጥ እናስፋ፣ እናሳድግ፣ ዜጎቻችን የሚጠቅም እናድርግ፣ እንዋደድ፣ እንከባበር ካሁን በኋላ መገፋፋት አያዋጣም። በእምነት፣ በቋንቋ፣ በሌላ ሌላ ጉዳይ

መከባበር፣ በጸታ መከባበር፣ ተከባብረን እራሳችን በምናከብረው ልክ ሌላውን አብረን መኖር ከቻልን ሃገራችን በጣም ውብ ለሁላችንም የምትበቃ ናትና እንበርታ እንስራ። እኛ በጣም ደስተኞች ነን። ጀምረን ያልጨረስነው፣ አስበን ያላሳካነው አንዳች ጉዳይ የለም። የገንዘብ እጥረት አልያዘንም፣ የሰዎች መለገም አልያዘንም፣ የጊዜ ማነስ አልያዘንም ማን እንደሚሰራው ባናውቅም እየተሳካልን ነው።

`ፈጣሪን በጣም እናመሰግናለን! የምትተጉ አመራሮች በጣም እናመሰግናለን! የምታግዙን ዜጎች በጣም እናመሰግናለን! አሁንም በስራ ውስጥ ያሉ ክፍተቶች ደግሞ ለይተን ማወቅ አለብን።

ይሄንን ስራ ስናደንቅ፣ ይሄ ስራ ሲሰራ ሌብነት ከነበረበት አያዋጣም። ሌቦች ጥንቃቄ ማድረግ ያለባችሁ ስራ እየሰራን እዛ ውስጥ አረም እንደማኖር ማለት ነው። ሌብነት እንዳይኖር፣ ትጋት ከልብ እንዲሆን ከእውነት እንዲሆን፣ ሰው እንዳንከፋፍል፣ ሁሉን አቅፈን እንድንይዝ ልቦናችን የቀና እና የተስተካከለ እንዲሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለው። በርቱ እንበርታ። የኢትዮጵያ ብልጽግና በጋራ እናያለን። ልጆቻችን በፍጹም አይለምኑም።

አመሰግናለሁ!
ገላን ጉራ ኢንዱስትሪ መንደር፣ አዲስ አበባ



የጎዴ የዩሪያ ማዳበሪያ ማምረቻ ግንባታ ፕሮጀክት ጉብኝት

ግንቦት 9፣ 2018ዓ.ም

ከጥቂት ወራት በፊት ከዳንጎቴ ጋር የነበረን ስምምነት የዳንጎቴ ሲሚንቶን ተጨማሪ ላይን የመጨመር እና ምርቱን ማሳደግ አንዱ ዋና የካፒታል ፍሰት የኢንቨስትመንት አንጓ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጎዴ የ3 ሚሊዮን ቶን ማዳበሪያ ፋብሪካ መገንባት ነው። ያኔ ለህዝባችን የገባነው ቃል ፋብሪካው በጀመረ በ40 ወራት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል ነበር። ይህንን ስራ ከጀመርን በኋላ በዓለም ላይ እንደሚታወቀው ማዳበሪያና ነዳጅ በጣም አስፈላጊ ከውጭ የሚገባ ሸቀጥ ሆነው ስለመጡ ጊዜውን ለማሳጠር ምን ማድረግ እንችላለን የሚለውን ከዳንጎቴ ጋር ስንመካከር ቆይተን ዛሬ ደግሞ ስራው ያለበትን ደረጃ እያየን ነው።

በተቻለ መጠን ከ40 ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ዕቅዱን፣ ፕሮጀክቱን ጨርሰን ለኛም ገበያ፣ ከኛ የሚተርፍ ካለም ለውጭ ገበያ ለመጠቀም ጥሩ ተስማምተናል። ስራውን ያኔ መጥተን ስናይ ያው ሃሳብ ነበር፤ ዛሬ እንደምታዩት ግን ስራው ተጀምሯል። ከሶስት ወር በኋላ ቢበዛ ከ4 ወር በኋላ እንመለሳለን። ከአራት ወር በኋላ ስንመጣ አብዛኛው መኖሪያ ቤት ግንባታ ይጠናቀቃል።

ለአምስት ሺህ ሰው የሚሆን መኖሪያ ቤት ግንባታ ትንሽዬ መንደር ነው የሚሰራው፤ መስከረም ላይ እሱ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ስራ ይጀምራል የሚል እምነት አለ። ውሃውን ካለበት ወደዚህ የማምጣት ስራ፣ ከፍተኛ ቦታዎችን ዝቅ የማድረግ፣ ዝቅተኛ ቦታዎችን የመሙላትና ለፋብሪካው የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ነው ያለው። በርካታ ግብዓቶች ተገዝተው እየመጡ ነው ያሉው፤ በአጠረ ጊዜ ውስጥ የማዳበሪያ ፋብሪካውን አጠናቀን የኢትዮጵያን አንዱን ቁልፍ ችግር እንፈታለን የሚል እምነት አለ። የዛሬ እዚህ ቦታ የእኛ መገኘት ዋናው ምክንያት ይህንን ፕሮጀክት በቅርበት የምንከታተለው፣ የምናየው፣ የምንመራው፣ ችግሮች ካሉ እየቀረፍን ባልነው ከተቻለም አፍጥነን ለመጨረስ ያለንን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው።

አሊኮ በጣም ቁርጠኛ ሰው ነው። በገባው ቃል መሰረት ገንዘቡን፣ ጊዜውንና ሙያተኞችን አፍስሷል። የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ አድርገን በማሳካት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ዋነኛውን ችግር እንፈታለን የሚል እምነት አለኝ፤ በጣም ደስ የሚል ስራ ነው ያየነው። እንግዲህ በዚሁ መልክ የክልሉ መንግሥት እና የፌደራል መንግሥት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እያደረጉ እንዲጠናቀቅ ካደረግን በጣም ትልቅ ችግር የሚፈታ ፕሮጀክት ይሆናል

የሚል ሙሉ እምነት አለኝ።በዚህ በጎዴ አካባቢ የምናደርጋቸው ኢንቨስትመንቶች አሁን የገለጽናቸውም ያልገለጽናቸውም ተደማምረው በኢትዮጵያ አየር መንገድ ደረጃ ከፍተኛ ገቢ ለኢትዮጵያ የሚያስገቡ ናቸው። ቀላል የካፒታል ፍሰት አይደለም፤ ዳንኑቴ ብቻ ከሶስት ቢሊዮን ወይም በላይ ነው እዚህ ቦታ የሚያፈስሰው። የቻይናዎቹም የካፒታል ፍሰት አለ እና በጣም ትልቅ የሀገርን መልክ፣ ቁመና እና የኢኮኖሚያዊ አቅም የሚቀይር ነገር ነው።

በምግብ ራስን መቻል ዋነኛ አጀንዳችን ነው። በምግብ ራስን ለመቻል መሬት ያስፈልጋል አለን፣ ውሃ ያስፈልጋል አለን፣ ሰው ያስፈልጋል አለን፣ ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ ላይ ደግሞ እየሰራን ነው ያለነው። እነዚህን ካሟላን ለኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የሚተርፍ ነገር ማድረግ ይቻላል ማለት ነው።

ይሄ ቦታ እንደምታዩት በጣም የተመቸ መስክ ነው፣ የተመቸ ሜዳ ነው። የሶማሌ ክልል አፈሩ ታርሶ አያውቅም፣ ውሃውም አለ። ይህንን ወደ መስኖ፣ ወደ ጠብታ መስኖ ሥርዓት ብናስገባ ሶማሌ ብቻ የምናርሰው ለብዙ ሊተርፍ ይችላል እና ስራ ይፈልጋል፣ ሀብት ይፈልጋል፣ ጊዜ ይፈልጋል፤ ያንን ካሳካን ግን ብዙ ችግሮቻችንን የሚፈታ ጉዳይ ይሆናል።

ጎዴ ፣ ሶማሌ ክልል

'የመረጃ ሉአላዊነት ለፖሊሲ ነፃነት' ጉባኤ

ግንቦት 10፣ 2018ዓ.ም

ዶክተር ፍጹም አሰፋ የፕላንና ልማት ሚኒስትር፣
ክቡር ዶክተር ከርሻሌ የስታትስቲክስ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈጻሚ፣
ክቡራን ሚኒስትሮች፣
የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት፣
የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ፤ እንኳን በሰላም መጣችሁ፣ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን እንዲህ ላለው ቀን በጋራ አደረሰን ለማለት እወዳለሁ።
ኢትዮጵያውያን ይህንን ቀን አቅልለን አንመለከተውም። በዚህ መንገድ መረጃን የመሰብሰብ፣ ከመረጃ በሚገኙ መረጃዎች ለውሳኔ ብቻ ሳይሆን ልካችን፣ ያለንን ለማወቅ ለመገልገል የበቃነው በብዙ ሙያተኞች ድካም፣ ጥረትና ልፋት ስለሆነ እነዚህን ሙያተኞች ለዚህ ቀን ስላበቁን አስቀድሜ ማመስገን እፈልጋለሁ።

ለምንድነው የመረጃ ጉዳይ ይሁነን ብለን አሰበን፣ ተቋምን ፈጥረን በዚህ መንገድ የምንነጋገርበት? የሚል ጥያቄ የአንድ ጤነኛ ሰው አእምሮ ቢያነሳ ተገቢ ይሆናል።
መረጃን እንደ ወርቅ፣ እንደ ሀብት ከስር ከመሰረቱ አይተን፣ ስለዚያ ጉዳይ ገዶን፣ መክረን፣ ዘክረን አውቀን ለመምራት የምንገለገልበት ዋናው ምክንያት ርዕያችን ጠንካራ ሀገረ መንግሥት መገንባት ነው። ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ለመገንባት ከሚያስፈልጉ ቁልፍ ቁልፍ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሉዓላዊነት ነው። ሉዓላዊነት ሲባል የኢትዮጵያን ድንበር መከላከል፣ አካላዊ አቅሞቻችንን መከላከል ብቻ ሳይሆን የመረጃ ሉዓላዊነት፣ የምግብ ሉዓላዊነት፣ የፖሊሲ ሉዓላዊነትና ሌሎችም ዘርፎች የሚጠቀሱ ሉዓላዊነቶች አሉ። ለምሳሌ የፖሊሲ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ መረጃ ሸምቶ ወይም መረጃ ተውሶ የፖሊሲ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ አይቻልም።

ለማንኛውም ፖሊሲ ዋነኛው ግብዓት መረጃ ስለሆነ ስላለ ብቻ ሸምተን ወይም ስላገኘን ብቻ ተውሰን ፖሊሲ ብንቀርጽ ያ ፖሊሲ በተሟላ መንገድ የእኛን መሻት፣ የእኛን ፍላጎት፣ የእኛን ትልም ሊያሳካ የሚችል ነው ብሎ መውሰድ ያስቸግራል። ስለዚህም የራስን መረጃ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ መተንተን መቻል ለፖሊሲ ሉዓላዊነት እንደ ትልቅ ግብዓት ይወሰዳል። ለምሳሌ አንድ ሰው በኪሱ የያዘውን የገንዘብ ልክ ቁጥሩን ባያውቅ፤ አስር ብር ወይም አንድ ሺህ ብር እንዳለው ቁጥሩን በትክክል ባያውቅ እና ወደ ምግብ ቤት ቢሄድ ቀጥሎ ለሚያደርገው ውሳኔ ይህ መረጃ በጣም ወሳኝ ነው። ጥብስ ነው የሚበላው ወይስ ሽሮ ነው የሚበላው ወይስ ዳቦ በሻይ ነው የሚበላው?

የሚወሰነው በኪሱ ባለ ገንዘብ ልክ ነው። በኪሱ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለ ያላወቀ ሰው ሁለት ችግር ይገጥመዋል። አንደኛው የተሻለ ነገር አዞ መጠቀም ሲችል ያለውን ባለማወቁ የማይፈልገውን እና የማይመቸውን ምግብ አዞ ሊበላ ይችላል። ሁለተኛ ደግሞ ያለውን በትክክል ሳያውቅ የተጋነነ ነገር አዞ በኋላ ባለዕዳ ሊሆን ይችላል።

በሀገር ደረጃ ደግሞ ስናየው ኢትዮጵያ ያላትን አቅም፣ ያላትን ሪሶርስ፣ ያላትን የማድረግ አቅም በቅጡ ካላወቅን ሌላው ቀርቶ አሁን ባለው በተለመደው ምዘና ሌሎች የሚመዝኑን በበቂ ለመገበያየት፣ በበቂ የውጭ የካፒታል ፍሰት ለመሳብ፣ በበቂ ለመበደር ሁሉ አዳጋች ይሆናል። ስለ እኛ ልክ፣ ስለ እኛ ብቃት የሚነግሩን ሁልጊዜም ሌሎች ከሆኑ እኛ ለዚያ ሂደት የምናዋጣው ምንም መረጃ ከሌለ ትክክለኛ መረጃ፣ ትክክለኛ ምዘና ላይሆን ይችላል። ቅድም እንደተገለጸው ሉዓላዊነት.. ሉዓላዊነት ስንል ራሱን የቻለ ነጻ እያልን አይደለም። ማንም ሀገር በተሟላ መንገድ ራሱን የቻለ መሆን አይችልም። ግን እርስ በእርስ የተደጋገፈ መሆን ይቻላል። እኛ የምንሰጠውን የምናውቅ፣ የምንቀበለውን የምናውቅ፣ ስንቀበል ወደን ፈቅደን ለሚያስፈልገን ጉዳይ መሆኑን ለይተን ከሆነ ያኔ ከየትም ምንጭ መረጃ ብንወስድ ለምን እንደምንጠቀምበት እናውቃለን። ከእኛ የሚወስዱም የእኛን የስራ ሂደት የሚገነዘቡ ከሆነ በተሟላ መንገድ አምነው የሚቀበሉንና የሚገለገሉበት ይሆናል።

የመረጃ ምንጭ አንድ ብቻ ሲሆን በመረጃ ጥራት ላይ የሚያስከትለው አደጋ አለ። ቅድም ሲገለጽ እንደነበረው የመረጃ ሰብሳቢዎች በአካል ሄደው መረጃ ሲሰበስቡ፣ በርቀት በሳተላይት መረጃ ሲሰበስብ፣ በድሮን መረጃ ሲሰበስብ፣ ለቀረቤታ መልክዓ-ምድራዊ መረጃ ሲታከልበት የዚያ መረጃ ጥራት ያደገ ይሆናል። ከብዙ የመረጃ ምንጮች በብዙ መንገድ መረጃ ሰብስበን ማመሳከር የማንችል ከሆነ ሙሉ ዕውቀት ከዚያ መረጃ ልናገኝ አንችልም። የመረጃ ምንጮችን ማብዛት እና ማመሳከር የጠራ መረጃ ለማግኘት ያግዛል። ዛሬ የስታቲስቲክስ አገልግሎት በሳተላይት፣ በድሮን፣ በአካል የላካቸውን ሰዎች እና መልክዓ-ምድራዊ መረጃዎችን ተጠቅሞ የእኛን ግብርና፣ የእኛን ጤና፣ የእኛን አጠቃላይ የማድረግ አቅም የለካበት መንገድ ለመላው ኢትዮጵያውያን እንደ ታላቅ ድል ሊወሰድ ይገባዋል።

በግሌ የስታቲስቲክስ አገልግሎት እና የፕላን ኮሚሽን ላለፉት በርካታ ወራት ብዙ ሺህ ሰው አሰማርተው የሰበሰቧቸው መረጃዎች፣ የተጠቀሙባቸው የአሰራር ስልቶች ለኢትዮጵያ ለቀጣይ እድገት እና ለምናስበው የሀገረ መንግሥት ግንባታ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን ስለማምን የተደረገውን ጥረት ብቻ ሳይሆን መረጃ ሰብስበው በመረጃ ማሳያ ሰሌዳ በቀለለ መንገድ ለተገልጋይ ማቅረብ መቻላቸው በኋላ ያለውን ጣጣ ባንገነዘብም

በውጤት ደረጃ እና በግብዓት ደረጃ ነገርየውን ለመረዳት የሚያግዝ እንደሆነ ሁሉ የሰሩትን ስራ በዚህ መልክ ባለድርሻ አካላት ባሉበት፣ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን በሚገባ በሚታይ መንገድ ማቅረብ መቻላችን ሌላ የኩራት ምንጭ ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ምን ያህላችሁ የተዘጋጀውን ኤግዚቢሽን እንዳያችሁ አላውቅም፤ እዚያ 30/40 ደቂቃ ስታሳልፉ ለምን ኩራት እንደሚሰማኝ እናንተም ያንን መንፈስ እንደምትጋሩ ምንም ጥርጥር የለውም። አስደናቂ ስራ! በጥቂት ሀገራት ብቻ የምናየውን የመረጃ አሰባሰብ፣ የመረጃ ትንተና እና የመረጃ አቀራረብ ዘዴ በሀገራችን በእኛው ልጆች ማየት መቻላችን ታላቅ ደስታ ስለሆነ በዚህ ስራ የተሳተፋችሁ ሁሉ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ። ቅድም አቅራቢዎች ሲገልጹ እንዳስቀመጡት መረጃ ሰብሳቢውም፣ መረጃ ተናጋሪውም፣ መረጃ አድማጩም በአንድ ስፍራ ያሉ ከሆነ የተግባራዊ የመረጃ ትንተና ብቃት አያጎናጽፍም። በአስተሳሰብ፣ በዕውቀት ደረጃ ስለዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ሊኖረን ይችላል። ነገር ግን በተግባራዊ መረጃ ትንተና ብቃት የሚሰጠን መረጃ ሰብሳቢዎች ለነገሩ ቀረብ ሲሉ ነው። ምን ማለት ነው? አንድ አርሶ አደር ከሶስት ሄክታር መሬት ላይ መኖ ኩንታል ስንዴ ሰበሰበ የሚለው መረጃ ለመረጃ ሰብሳቢውም ለመረጃ አድማጩም እኩል መሆን አይችልም። መረጃ ሰብሳቢው ያ ሶስት ሄክታር ምን አይነት መልክአ ምድር እንደሆነ፣ ውሃ በስንት ርቀት እንደሚገኝ፣ ምን አይነት የውሃ መሳቢያ እንደሚጠቀሙ፣ ምን አይነት ማሽነሪ እንደሚጠቀሙ፣ ሰብል በሚሰበስቡበት ሰዓት ምን ያህል ብክነት እንዳለ ብዙ ተጨማሪ መረጃዎችን በአካልና በቅርበት ስለሚያውቅ ከሚነግረን ባሻገር ስለዚያ አካባቢው የጠለቀ ግንዛቤና ዕውቀት ሊይዝ ይችላል።

በቅርቡ ባሌ ሀረና በሚባል ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ሰዎች ህገወጥ በሆነ መንገድ ወደ ብሔራዊ ፓርኩ እየገቡ ፓርኩ እየተጎዳ ስለነበር፣ ለሰዎቹ የኑሮ ማስኬጃ ቦታ ተመቻችቶላቸው ከዚያ ብሔራዊ ፓርክ እንዲወጡ ሲደረግ በዚያ ፓርክ ውስጥ የነበሩ አርሶ አደሮች በአማካይ እስከ 2000 ኩንታል የሚጠጋ ምርት ከእነሱ ቤት፣ ከእነሱ ጓሮ ተገኝቷል። ነገር ግን የእነዚያ አርሶ አደሮች የህይወት ዘይቤ ሲታይ 2000 ኩንታል ማምረት የሚችል አርሶ አደር የሚኖርበትን የኑሮ ደረጃ አይኖሩም። ቤታቸው የምታውቁት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ጎጆ ቤት ነው። የፀሐይ ብርሃን ኃይል የላቸውም፤ ቤታቸው የሚተኙበትና የሚመገቡበት የተለያየ ክፍል አይደለም። ምርታቸው እና ኑሯቸው አይመጣጠንም።በቅርበት በምናይበት ሰዓት በውጤት ደረጃ የዚያ መረጃ መሰብሰብና መተንተን የሚያመጣውን ፍሬ-ሃሳብ መረጃ ማግኘት ብቻ ሳይሆን ከውጤት ወደ ዘላቂ ለውጥ መሸጋገር አለበት። ያ መረጃ በፖሊሲ ተደግፎ፣ አመራር ተሰጥቶት በእያንዳንዱ

ዜጋ በቤተሰብ ደረጃ በህይወታቸው ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ማየት ካልቻልን እንዲሁ ምርት፣ እንዲሁ ሊታረስ የሚችል መሬት ስፋት ብቻውን በቂ አይደለም። እነዚያ መረጃዎች የሚያስፈልጉን የእያንዳንዱን ሰው ህይወት መንካት ሲችሉ፣ የህይወት ደረጃውን ማሻሻል ሲችሉ እና ውጤቱ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሲያመጣ ነው። ይህም አርሶ አደሩ አርሶ ማምረት ብቻ ሳይሆን ልጆቹን ትምህርት ቤት መላክ መቻሉን ስናረጋግጥ፣ ልጆች ትምህርት ቤት መሄዳቸው ብቻ ሳይሆን በሚያገኙት ምግብ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እንዳያጋጥማቸው እና ያም የኢንቨስትመንት አካል መሆኑን የሚገነዘቡ ዜጎች ሲበራከቱ ነው። ስለዚህ መረጃን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ በውጤት ደረጃ መረጃውን ከማከፋፈል፣ ከመስጠት ባሻገር፣ የሰውን ህይወት መለወጡን ማረጋገጥ በእጅጉ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ቴክኖሎጂ በተለይም ሰው ሰራሽ አስተውሎት አይተኬ ሚና አለው።

በእርግጥ ወርቁ እንዳቀረበው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየተቀናጁ ነው። የቁስ ሳይንስ፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ ባዮቴክኖሎጂ እና ሰው ሰራሽ አስተውሎት የምንላቸው ጉዳዮች አንዱን ከሌላው ለይተን ማየት በማንችልበት ደረጃ እየተቀናጁ ይገኛሉ። ለምሳሌ የስታትስቲክስ አገልግሎት የሚሰራቸው ስራዎች ከ60/70/ 80 በመቶ የሰው ሰራሽ አስተውሎት መጠቀም አስገዳጅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ስታትስቲክስን ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ውጪ ማሰብ ወደ ማንችልበት ደረጃ ደርሰናል። ግብርናን ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ውጪ ፣ ጤናን ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ውጪ ማሰብ አንችልም፤ ተቀናጅተዋል። እያንዳንዱ መስሪያ ቤት፣ እያንዳንዱ ተቋም፣ እያንዳንዱ የግል ኩባንያ ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ በቴክኖሎጂ መታገዝ ሲችል ጥራት፣ ስፋት፣ ውጤትና ተደራሽነት በእጅጉ ሊጎለብቱ ስለሚችሉ በእያንዳንዱ ተቋም ሰው ሰራሽ አስተውሎትን መጠቀም፣ በአጠረ ጊዜ መረጃ መሰብሰብ፣ በአጠረ ጊዜ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ማሳጠር የምንችለው ቴክኖሎጂን በብቃት ስንጠቀም ነው። ለዚህ የፕላን ኮሚሽን ጥሩ ማሳያ ይመስለኛል።

እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ እድሜ ጠገብና ጠንካራ ስራ ከሚሰሩ ተቋማት አንዱ የስታትስቲክስ አገልግሎት ነበር። አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደርሶ ትናንትና የነበረውን ስናይ ግን ቀን እና ማታ ማለት ነው። እንኳን በ50 እና በ60 ሺህ መረጃ ሰብሳቢዎች አይፓድ አስይዞ የት አካባቢ እንዳሉ አውቆ መከታተል ይቅርና፣ እያንዳንዱን መረጃ ያ ሰው በአካል ቦታው ተገኝቶ መሰብሰቡን ማረጋገጥ የሚችሉበት መንገድ እንኳ አልነበራቸውም። የመረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጫ መተንተኛው ከፍተኛ ትርጉም አለው። ያንን ለማድረግ አሁን እያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ በተሰጠው ቀጠና ውስጥ ሆኖ መረጃ እንደሚሰበስብ ማወቃቸው ብቻ ሳይሆን የመረጃ አሰባሰብ ስርዓቱ እንከን ካለበት፣ ስህተት ካለበት

ሲስተሙ እያገዘ ማረም መቻላቸው በእጅጉ አጋዥና ጠቃሚ ስራ ስለሆነ ሁላችንም፣ የግልም ሆነ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ቴክኖሎጂንና ሰው ሰራሽ አስተውሎትን መጠቀም፣ የራስን አቅም በትክክል ማወቅ፣ ያለማመንታት ለማደግ የምናደርገው ጥረት፣ መረጃ እና ወርቅን እኩል አስፈላጊ መሆናቸውን አምኖ በመቀበል በፖሊሲ ፣ በህግና በዕውቀት የሚመራ ማንኛውም ሀገርና መንግሥት ምንም ጥርጥር የለውም ብልጽግናን ያረጋግጣል።

እዚህ ያላችሁ ክቡራትና ክቡራን፤ ዛሬ ስለ መረጃ ወጣት የስራ ኃላፊዎች ያላቸውን ግንዛቤ፣ የደከሙበትን፣ የተጉበትን፣ የሰሩበትንና ለእኛ ያመላከቱበትን መንገድ ስንመለከት ኢትዮጵያ እንደተባለውም የማንሰራራት ጉዞ መጀመሯን ለሁሉም ሰው ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያመላክት አንድ ነገር ነው። ወርቅን በጥቂት ሚሊዮን ወይም 5 ቢሊዮን ዶላር መላክ የቻለች ሀገር ለመረጃ ግምት ካለመስጠት ወጥታ፣ መረጃን በብዙ ምንጮች መሰብሰብ፣ መተንተንና እና ለውሳኔ ሰጪው አካል በጥራትና በፍጥነት ማቅረብ የምትችል ሀገር ከሆነች፣ መረጃ ከወርቅ ያልተናነሰ ሀብት መሆኑን እየተገነዘብን እንደመጣን ያመላክታል። ይህ ጉዳይ መጠናከር አለበት፤ ይህ ጉዳይ የሁላችንንም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆን አለበት። ይህ ጉዳይ ይሁነን ብለን የምንገነዘበውና የምንመራው መሆን አለበት። ያ መሆን ከቻለ እያንዳንዱ ህግ፣ እያንዳንዱ ፖሊሲ፣ እያንዳንዱ የስራ ዝርዝር በመረጃ እና በዕውቀት ላይ ተንተርሰን ስለምንሰራ እድገታችንን ለማቀላጠፍ፣ የዜጎቻችንን ህይወት ለመንካት፣ ኢትዮጵያ የሚገባትን ልክ ለማረጋገጥ በእጅጉ የሚያግዝ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም።

ይህ ስራ እንዲሳካ በዕውቀት፣ በገንዘብና በጉልበት ያገዛችሁ፣ የተሳተፋችሁ ዜጎችና አጋሮቻችን በሙሉ እንኳን ደስ ያላችሁ፤ ታላቅ ስራ ሰርታችኋል። ይህ ስራ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ብልጽግና ሲረጋገጥ እንደ አንድ ታላቅ ስኬት ይህንን ቀን የምናወሳበት ጊዜ በቅርብ የሚደገም እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

ስለነበረን ጊዜ፤ ስላሳያችሁን ፤ ስለመረጃው ስለዕውቀቱ በእጅጉ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የላፍቶ ሆስፒታል ምረቃ ሥነ-ስርዓት

—ግንቦት 18፣ 2018ዓ.ም

ክቡር አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣
ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣
ክቡርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣
ክቡራን ሚኒስትሮች፣ ክቡራን እንግዶች፤ እንዲህ ያለውን ታላቅ ስራ ጀምረን ለመጨረስ፣ ለህዝባችን ስራ ለማስጀመር ስለበቃን፣ ስላበቃችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እወዳለሁ። በኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ ላለፉት አስርት ዓመታት ስንገለገልበት የነበረው ፖሊሲ ቅድሚያ ለመከላከል መስጠት ላይ ያተኮረ ነበር። ያንን ፖሊሲ ለማሻሻል ያስገደዱን ምክንያቶች አንደኛ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ሚገባ ጉዳይ በቂ ስራ አልተሰራም የሚል ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ሰው መከላከል ብቻ ሳይሆን ከዛ አልፎ በአደጋም በተለያየ ምክንያት ቢታመም ማከም መቻል አለብንና መከላከል እንደተጠበቀ ሆኖ ታመው ከመጡም ማከም የሚለው ሃሳብ መታከል አለበት የሚል ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር ተደርጎ ፖሊሲው ተሻሽሏል።

መከላከልን በሚመለከት ጤና ሁላችሁም እንደምታውቁት በጣም ውድ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ካላመመን አይገባንም፤ ሲያመን ወይም ሲታመሙብን ብቻ የምናቀው በጣም ወሳኝ ነገር ነው ልክ እንደ ሰላም። ልጆች ሲታመሙብን፣ ወላጆች ሲታመሙብን የት መውሰድ እንዳለብን ጭምር ነው ግራ የምንጋባው። አንዳንዴ ሰው ጭንቅላቱን ታሞ የልብ ሆስፒታል እንወስደዋለን፤ ሆዱን ታሞ የጭንቅላት እንወስደዋለን፤ ይህን ባለማወቅ ብቻ ህይወታቸው የሚያልፉ ዜጎች ብዙ ናቸው፤ የት መውሰድ እንዳለብን ካለመገንዘብ ብቻ! መከላከልን በሚመለከት ወንዞቻችን ቆሻሻ፣ የእግረኛ መንገድ የሌለበት ከተማ፣ የአካላዊ እንቅስቃሴ የማይደረግበት፣ ልጆች ማዋያ፣ መስክ፣ ኳስ ሜዳ ስላልተሰራላቸው ካለ እድሜያቸው ወደ ጫት፣ ወደ መጠጥ የሚሄዱበት፣ አዛውንቶች እግራቸውን ሊያፍታቱ ቢፈልጉ መውጫ ሰፈር የሌላቸው፣ ከወጡም በጨለማ ምክንያት አደጋ የሚያጋጥማቸው፤ እነዚህን ጉዳዮች ሳንፈታ መከላከል በተሟላ ሁኔታ ሊሳካ አይችልም። በሽታ ልክ እንደ ጦር ሰራዊት ውጊያ ይፈልጋል፤ ያ ውጊያ ደግሞ ትጥቅ ይፈልጋል፤ ትጥቁ ምግብ ነው።

በአዲስ አበባ በተለያየ ቦታ የመመገቢያ ማዕከል የተገነባው ቢያንስ ሰዎች ጎራ ብለው መብላት የሚችሉበትን ባህል ለማለማመድ፣ ማዕድ ማጋራት ልማድ እንዲሆን፣ በሁሉም

ሰዎች ሰው ካለው መክፈል፣ ማካፈል እንዲለምድ ያስፈለገበት ምክንያት በሽታን መከላከል ከተማችን ውስጥ ችግር ሆኖ ስለቆየ ነው። ከዚህ አንጻር መቶ በመቶ እንከና አልባ ስራ ሰራን ባይባልም ጅምር ሙከራዎች የሚናቁ አይደሉም። የምገባ ማዕከላት ተማሪዎች ቢያንስ በቀን ሁለቴ ትምህርት ቤት እንዲመገቡ ማድረግ፤ እንዲመገቡ ብቻ ሳይሆን ምታውቁ ታውቃላችሁ በሳምንት በድግግሞሽ የሚበሉ እና የማይበሉ ጉዳዮችም ተለይተው ማለት ነው። “አቅርበንልሃል እና ዳቦ በሻይ ብላ” ሳይሆን በተቻለ መጠን የተለያየ ምግብ ቀርቦላቸው የምግብ እጥረት እንዳያጋጥምም ጭምር ሙከራ እየተደረገ ይገኛል።

ይሄ በጣም ጠቃሚ ልምምድ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ማዕድ ማጋራት “ያን ያክል ያስፈልጋል ወይ?” ብለው የሚያስቡ ሰዎች እንዳሉ አቃለው፤ ግን ያስፈልጋል። የሚቸገሩ ሰዎች አሉ። አሁን ነገ አረፋ ነው ብዙ ሃብታሞች ያርዳሉ፣ ብዙ ደሃዎችን ማጋራት ካልቻልን፣ አንዳንዶቻችን ቤት ጠግበን የምንደፋው ቢኖርም፣ አንዳንዶቻችን ቤት ደግሞ ችግር አለ። ይሄንን በተሟላ ደረጃ ኢትዮጵያ ዜጎቿን መርዳት፣ መመገብ ስትችል ዜጎች በትብብር መንፈስ ያንን ችግር ማለፍ መቻል ይኖርባቸዋል። ያን እያደረግን ስንሄድ የተሟላ ጤንነት ያለው ትውልድ እና ማኅበረሰብ ይፈጠራል።

ከዚህ አንፃር በመከላከል ብቻ ሳይሆን የታመሙ ሰዎች በማከም ጭምር አዳዲስ አስተማማኝ ኢንቨስትመንት እንስራ ባልነው መሰረት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሲመረቁ የነበሩ ሆስፒታሎች አሉ። ዛሬም እንዳያችሁት ቴክኖሎጂን በበቂ የተላበሰ በጣም ጥሩ ሆስፒታል ተመርቋል፤ በሚቀጥሉት ወራትም የሚመረቁ አሉ። ለከተማ መስተዳድሩ ያለኝ መልዕክት ሁለት ነው፤ አንደኛው ተሳክቶላችኋል፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሚያስደንቅ ሁኔታ ከተማውን በትምህርት፣ በስፖርት ማዘውተሪያ፣ በጤና፣ በመሠረተ-ልማት፣ በኃይል ሊታሰብ የማይችል ስራ ሰርታችኋል። ለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ በሙሉ ያመሰግናችኋል። በሌላ መንገድ ግን የማኅበረሰብ ዘርፍ፣ ጤና፣ ትምህርት የመሳሰለው ዘርፍ በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ብቻ የሚፈታ ጉዳይ አይደለም፤ መንግሥታት ሙከራ ማድረግ አለባቸው፣ ክፍተት እያዩ መሙላት ይጠበቅባቸዋል፤ ግን የግል ዘርፉን መደገፍ በጣም ያስፈልጋል።

አዲስ አበባ ውስጥ ከምንገምተው በላይ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ሆስፒታል ለመስራት እና ያንን ክፍተት ለመሙላት የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል። ብዙ የሚደንቁ ሙያተኞች አሉ። ነገር ግን ብዙዎቹ ጋር ስንሄድ በቦታ እጥረት ምክንያት በቂ ድጋፍ ካለማግኘት፣ ሊሰሩ፣ ሊዘረጉ እየፈለጉ የታሰሩ ሰዎች አሉ። እነሱን ማገዝ ደግሞ ልክ

ከተማው አስደማሚ ስራ ሰርቶ እዚህ እንዳስደነቀን የግል ሆስፒታል እየሄዳችሁ፣ እያያችሁ፣ የሚጎላቸውን እየደገፋችሁ፣ ማስፋፊያ ካስፈለገ እየሰጣችሁ፣ ልክ እንደዚህ ያለውን ምርጥ ነገር በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በግልም እንድናይ የማድረግ ግዴታም፣ ሃላፊነትም አለባችሁ። ለምን? ለአዲስ አበባ ካልተጋነነ የዚህ ዓይነት 50 ካልተሰራ አይበቃም፤ በጣም ሰፊ ህዝብ ነው። እኛ ደግሞ ፈርዶብን "አንድ ለእናቱ" ለምደናል፤ አንድ ነገር እንሰራና እሱን እያወደስን መኖር እንጂ መደጋገም አናቅም።

በዚህ ምክንያት ከተማው በራሱ ገቢ ይህን የመሰለ ስራ ሰርቶ፣ ፈርቀዳጅ ስራ ሰርቶ፣ ላፍቶ አካባቢ ያሉ ሰዎች የዚህ ድል ተቋዳሽ እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉ ትልቅ ድል ሆኖ፣ በተለያየ ስፍራ ደግሞ እንዲበራከት የግል ዘርፉን መደገፍ፣ ማገዝ ያስፈልጋል። ስንደግፍ ከነ ግዴታው ሰተን "አምጣ፣ ውለድ፣ አቅርብ" ብለን እያገዝን ከሄድን የጤና ዘርፉ ኢትዮጵያ በጣም በርካታ ሀኪሞች ታፈራለች፣ መሠረተ-ልማት ትገነባለች፣ ዜጎችን አክሞ ማዳን በዛው ልክ ማደግ እንዲችል ማድረግ ይኖርብናል። ለጤና ተቋማት ሙያተኞች፣ ለጤና ቢሮ ያለኝ መልዕክት ደግሞ ዛሬ ድግስ ነው ከዚህ ቀደም "ድንጋይ ማስቀመጥ ስህተት ነው፤ አናስቀምጥ፤ ብለን እንጨርስ" ማለታችን ትክክል ነው፤ አሁን ደግሞ መቅረት ያለበት አንድ ባህል አለ።

ምርቃት ሲኖር ያምራል እንደምታዩት፤ የዛሬ ወር ስንመጣ መልሰን ይህንን ካላየን ዋጋ የለውም። ይሄ ሆስፒታል የተመረቀው ለኛ አይደለም፤ ይሄ ሆስፒታል የተመረቀው ለዜጎች ነው። ማጽዳት፣ አካባቢው ማሳመር የሁልጊዜ ልማድ መሆን አለበት እንጂ፣ ምርቃት ላይ ብቻ ከሆነ ዋጋ የለውም። ይሄ ደግሞ የጤና ቢሮ ስራ ይሆናል። እርግጠኛ ነኝ ከንቲባዋ፣ ምክትል ከንቲቦች፣ እኛም ብቅ ብለን ማየታችን አይቀርም። ዛሬ ያየነውን ነገር የዛሬ ወር፣ ሁለት ወር ካላየን ያው ባወደሰ አፋችን ደግሞ ወቀሳም ይከተላል ማለት ነው። ባህል መሆን አለበት፤ መርዳትም ከተጀመረ ባህል መሆን አለበት፤ መስራትም ባህል መሆን አለበት። አንድ ጊዜ አሳይተን እልም ከሆነ እንደ ኢትዮጵያ ሃገር መቀየር ያስቸግራል፤ እና ንጹህ መሆን አለበት። ሰዎች ሲመጡ የለመድነው "አይቻልም፣ አትገባም፣ ክልክል ነው፣ ሃኪም የለም፣ ስብሰባ ነው" በሽታ ላይ በሽታ ጨምረን ከምንሸኛቸው ቢያንስ "እረፍ፣ እስከዛ ዳቦ እና ሻይ እየበላህ ቆይ፣ አይዞህ" ከተባለ ሰው ይጽናናል፤ እና ያንን ባህል ማለማመድ፣ ማስለመድ፣ መለማመድ ያስፈልጋል።

በቅርቡ የጤና ሙያተኞች ስልጠና በኢትዮጵያ የሚሰጠውን ስናይ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ400 በላይ ከተለያዩ አፍሪካ ሃገራት እስፔሻላይዝ የሚያደርጉ ሬዝደንቶች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ብዙ አፍሪካ ሃገር ብትሄዱ ከምትገምቱት በላይ ብዙ አፍሪካ ሃገር ውስጥ

በተለያየ ዘርፍ ህክምና የሚሰጡ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ናቸው። ደቡብ አፍሪካም ብትሄዱ፣ ቦትስዋናም ብትሄዱ፣ የተለያየ ሀገር ብትሄዱ፣ ኢትዮጵያን ከዚህ አልፈው ሌላ ሃገር እየሄዱ ማከም የሚችሉ ሰዎች፣ እዚህ መጥተው መማር የሚችሉ አቅም ካለን፣ በዛው ልክ ዜጎች ማዳን፣ እርካታን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለምሳሌ በአገልግሎት እርካታዎች ይታያሉ፤ መሰብ ከመጣ በኋላ በጣም መሻሻል አለ፤ በህክምናም እንደዛ መሆን አለበት። እና ክብርት ከንቲባ በትምህርት ዘርፍ አዲስ አበባ ውስጥ በመዋዕለ-ሕፃናት ግንባታ፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ የነበሩ እድሳት፣ በትምህርት ቤት ምገባ፣ በአስተማሪዎች ብቃት ማሻሻል፣ የአስተማሪዎች ኑሮ ማሻሻል ላይ የተሰራው ስራ በእጅጉ ከተማውን ያስመሰግነዋል።

ልክ እንደዛ የሚቀጥሉት ዓመታት ግን በጤና ዘርፉ አገልግሎት ላይ ሳንቸገር መተን ታክመን "ቪአፒ" ተብሎ ሳይሆን ማንኛውም ዜጋ ታክሞ የሚሄድበትን መንገድ ለመፍጠር የእናንተ ቀጥተኛ አመራር ስለሚያስፈልግ ደግሞም እንደምትችሉ ስላሳያችሁን በጤናው ዘርፍ የሚጨበጥ ለውጥ ከተማችን ውስጥ መጥቶ ክልሎች ከዚህ ከተማ ትምህርት ወስደው መሰል ስራ እንዲሰሩ አበክራችሁ እንድትሰሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ሃኪሞች፣ እዚህ የሚሰሩ ነርሶች፣ የጤና ሙያተኞች እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንደዚህ ባለው ስፍራ መስራት በጣም በጣም እድለኛነት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ቀበሌና ሆስፒታል መሄድ በጣም ከባድ ነው፤ በንጹህ ፊት፣ በፈገግታ አገልግሎት መስጠት እንድንለማመድ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። በዚህ ስራ የተሳተፋችሁ አስደናቂ ስራ ሰርታችኋል፤ እንኳን ደስ ያላችሁ። ክብርት ከንቲባ እንኳን ደስ ያላችሁ።በርቱ፣ እንበርታ፣ እንስራ! የመለወጥ ትልቅ ተስፋ ያላት ሃገር ናት፤ እንደምታዩት በሁሉም ዘርፍ ውጤት እየመጣ ነው ያለው። ሳንኩራራ፣ ሳንረካ፣ ይሄኛውን ቶሎ ዛሬ ረስተን፣ አዲስ በመጀመር የምንዘረጋ ከሆነ ኢትዮጵያ ትለወጣለች። እርካታ በሽታ ነው፤ እርካታ ያስራል፤ እርካታ ወደ ኋላ ብቻ እንድናይ ያደርጋል "አምና እኮ እንትን ሰርቼ..." ወደ ኋላ ይወስዳል፣ መጥፎ በሽታ ነው። እና ክብርት ከንቲባ እኛ እንረካላችኋለን፤ እናንተ ስሩ፣ እንዳትቆሙ አደራ ለማለት ነው።

ስለነበረን ጊዜ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን፤ መልካም በዓል!
አዲስ አበባ

በምሥራቅ ቦረና የስንዴ ልማት ክላስተር ጉብኝት

—ግንቦት 19፣ 2018ዓ.ም

ዛሬ በቦረና ያየነው በቋንቋ መግለጽ አይቻልም፤ ተዓምር ነው። ቦረና የዛሬ ሁለት ሶስት ዓመታት በውሃ እጥረት ምክንያት ብዙ ከብቶች ያለቁበት፣ በተደጋጋሚ በረሃብ የሚጠቃ አካባቢ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት 90 በመቶው የዚህ አካባቢ ሰው፤ 90 በመቶው ሴፍቲ ኔት ነበር። በሴፍቲ ኔት ነው የሚጋባው ሰርግ የሚደረገው በእርዳታ እህል ነው 90 በመቶው፤ ዛሬ ዜሮ ነው፤ ቦረና ከእርዳታ እራሱን ነጻ አርጓል አርሶ። 250ሺህ ሄክታር ስንዴ ነው ያደረሱት ዘንድሮ! ቦረና በቂ ውሃ ካገኘ እስከ አንድ ሚሊየን ሄክታር መሄድ ይችላል። እራሱን መመገብ ብቻ ሳይሆን ለሌላውም አካባቢ ለገበያ ሊወጣ የሚችል ምርት ማምጣት ይችላል። ትልቁ ችግር ውሃ ነው።

ሰፊ ቦታ አለ፣ ለም መሬት አለ፣ ስራ ወዳድ ህዝብ አለ፤ ግን ውሃ አልነበረም። አሁን ውሃ ላይ ጣልቃ እየገባን ነው። ግን የሚያስደንቀኝ ነገር ሁለት ሶስት ዓመት በፊት ለረሃብ፣ ለችግር የመጣንበት ቦታ አሁን በዚህ ደረጃ ምርት!... ልክ ይሄኮ ባሌ፣ አርሲ ነው የሚመስለው። እንደዚህ አይነት ምርት ያለው ባሌ፣ አርሲ ብቻ ነው። በጣም በጣም በጣም ደስ ይላል፤ ፈጣሪ ይመስገን። ጥሩ ነገር ነው፤ አሁን እንበርታ፣ እንስራ፤ ይሄ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰፋ ይገባል። ኢትዮጵያ መራብ የለባትም፤ መለመን የለባትም።

ብንበረታ፣ ብንሰራ የተሰጠን ብዙ ነው!

የተሰጠንን አውቀን ከተጠቀምን ለውጥ ልናመጣ እንችላለን የሚለውን ነገር ሁሌ የምንለው ነገር በተግባር ያየንበት ነው። 90 በመቶ ተረጂ አምርቶ እራሱን መመገብ መቻል ማለት ደግሞ ይህ ተዓምር ነው፤ ምንም ሌላ ነገር ሊገልጸው አይችልምና ፈጣሪ ይመስገን።

የቦረናን ህዝብ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ!
ቦረና

የነገሌ ቦረና ገዳ አውሮፕላን ማረፊያ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

—ግንቦት 19፣ 2018ዓ.ም

ቦረና ታላቅ ህዝብ ነው፤ የኦሮሞን ማንነት፣ ባህል ያቆየ ህዝብ ነው። ከጉጂ፣ ከባሌ በከባቢው ካሉ ከኦሮሞዎች እና ከሌሎች ህዝቦች ጋር በትብብር የኖረ ህዝብ ነው። ከአዲስ አበባ ራቅ ያለ ከባቢ ነው። ይህ የአየር መንገድ ኤርፖርት በዚህ ስፍራ መሰራቱ በጣም ጥሩ ስራ ነው።

በኢትዮጵያ ደረጃ ከሞላ ጎደል በሶስት የሚከፈሉ ኤርፖርቶች አሉን፤ በአንደኛ ደረጃ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታዩ ኤርፖርቶች አዲስ አበባ፣ መቀሌ፣ ባህርዳር አሉን። በሁለተኛ ደረጃ ልክ በዚህ ደረጃ የሚታዩ ኤርፖርቶች ደግሞ በሰሜን አስር አሉን። ቅድም የጠቀስኳቸው ቦታዎች ኮምቦልቻ፣ ላሊበላ፣ መቀሌ፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ ሁመራ፣ መተማ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ አሁን ከሚሰራው ከደብረማርቆስ ጋር 10 ኤርፖርቶች በሰሜን ኢትዮጵያ ተገንብተዋል። ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ደረጃ የሚታዩ ናቸው።

በምስራቅ፡- ሰመራ፣ ጅጅጋ፣ ቀብሪዳሃር፣ ጎዴ፣ ድሬዳዋ አምስት አሉን። በምስራቅ የት ቀረ፣ ምን ብናሟላ የምስራቁን ህዝባችንን ከምዕራቡ ከሰሜን እናገናኛለን የሚል ስራ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጥናት ይሆናል ማለት ነው። በምዕራብ አሁን ከተሰሩት ጋር ሚዛን፣ ጅማ፣ መቱ፣ ጋምቤላ፣ ደምቢዶሎ፣ ነቀምት፣ አሶሳ ሰባት አለን በምዕራብ ኢትዮጵያ። በደቡብ ኢትዮጵያ ሃዋሳ፣ አርባ ምንጭ፣ ጂንካ፣ ያቤሎ፣ ነጌሌን ጨምሮ ስድስት አሉ።

አሁን ይህ የሚያሳየው በኢትዮጵያ ደረጃ በመካከል ያሉት የአየር ኃይል ጣቢያውን ጨምሮ፣ ቦሌን ጨምሮ ወደ 30 የሚጠጉ ኤርፖርቶች ያሉን ሲሆን የጎደሉን የት ናቸው የሚለውን ደግሞ እያየን መሙላት ያስፈልጋል። በደቡብ ኢትዮጵያ ጥቂት ቦታዎች የግድ የሚያስፈልጉበትን መለየት ያስፈልጋል። በምስራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁ መለየት ያስፈልጋል። ይሄንን በማመጣጠን ኢትዮጵያ ሁሉን ያቀፈች ለሁሉ በሁሉ እኩል የምታገለግል እንድትሆን ይሁነኝ ብለን አስበን መስራት ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ነገር እኩል ለዜጎች መድረስ እንዲችል ደግሞ ገበያን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን አስበን ካልሰራን በቀር እንደ ሀገር ጸንተን ለመቆየት እንቸገራለን። ፍትሃዊነት እና ሚዛናዊነትን ለማረጋገጥ የጎደሉ ነገሮች እያዩ መሄድ ያስፈልጋል። ለተሰራው በጣም

እናመሰግናለን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትልቅ ስራ ሰርቷል። ገና ብዙ ይጠበቅባቸዋል። የጀመራችሁት የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት መልክ ሲይዝ ግን የጎደሉ ቦታዎች እየለዩ ከመንግሥት ጋር እየተመካከሩ መሙላት ያስፈልጋል የሚለውን መልዕክት ነው ያስተላለፉት አቶ መስፍን። የቦረና ህዝብ፣ የጉጂ ህዝብ ይቅርታ እንዳይነፍገን ብንዘገይም እየደረስን ነው። ልማት ይመጣል፤ እናንተ የሰላም አባት ናችሁ፤ ሰላም ይቀጥላል፤ ተባብረን ኢትዮጵያን እናጽና፣ እናልማ ማለት እወዳለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
ቦረና



የእንጦጦ-ቀጨኔ መድኃኔዓለም የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ምረቃ

ግንቦት 25፣ 2018ዓ.ም

ዛሬ ግንቦት 25 ነው ትላንት በሃገር አቀፍ ደረጃ መላ ህዝባችን በሚያስደንቅ ትጋት እና ብርታት የዴሞክራሲ ስርዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ለማነጽ፣ ለመገንባት እስከ እኩለ ሌሊት ከዛም በላይ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በዚያ ሁሉ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ እንቢኝ ብሎ ስርዓቱን ለመገንባት ቁርጠኝነት አሳይቶ ሲመርጥ የዋለበት፣ ያመሸበት፣ ያደረበት ማለት ይቻላል እለት ነበረ። ይሄ ለኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንደ አንድ ታሪካዊ ጊዜ ሊወሰድ የሚችል ኩነት ነው። ሰላማዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ያሳየው ጥንካሬ ብርዱ፣ ውሀ ጥሙ፣ አልፎ አልፎ ዝናቡ በድምሩ አስደማሚ ነገር ነው። ይሄ ጉዳይ አያስተኛም ብዙ ማሰብ ፣ብዙ መበርታት በታመነው ልክ መገኘትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

እንግዲህ እኛም ትናንት ምርጫውን ስለጨረስን ዛሬ በቀጥታ መላው የመንግሥት አመራር በፌደራልም በክልልም ያሉ ወደ ስራ ገብተናል። ወደ ስራ እንድንገሰግስ፣ እንድንፈጥን ያደረገን አንዱ እና ዋነኛ ምክንያት በዚህ ዓመት ኢትዮጵያ ያቀደችው እድገት 10.2 በመቶ ወይም ከአፍሪካ ቀዳሚውን እድገት ለማረጋገጥ ነው። ይህ እድገት የሚረጋገጠው ደግሞ ሚባክን ጊዜ ከሌለን ነው። አሁን የቀረን አንድ ወር ከአምስት ቀን ነው፤ ሰኔ 30 የዚህ ዓመት የበጀት ስራ የሚከናወንበት የሚጠናቀቅበት ጊዜ ነውና ያ ጊዜ እንዳያልፈን ፈጥነን ወደ ስራ ለመግባት ሁላችንም እየሰራን እንገኛለን። እንጦጦ አስደናቂ ቦታ ነው ቀደም ሲል ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ እስከ ቦሌ ያለውን የውሃ ዳርቻ ስናለማ የሸገር ፕሮጀክት የሚባለው ይሄ ነው፤ በእግረኛ መግቢያ መንገድ ከግል ባለሃብቶች ጋር በመተባበር በጣም በርካታ ቡና መሸጫ ሬስቶራንቶች፣ የተለያዩ የንግድ መገበያያ ስፍራዎችን ለመስራት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ዛሬ ያየነው 9.6 ስድስት ኪሎ ሜትር ነው፤ ከእንጦጦ ቁስቋም አካባቢ ጀምሮ እስከ ቀጨኔ ያለው ለማመን ይከብዳል። አየሩም፣ አምና የተከልናቸው ዛፎች ያሉበት ሁኔታም እራሱ የውሃ ዳር ልማቱ በቀጥታ ነው እንጂ 9.6 ኪሎ ሜትር የምልህ የእግር ጉዞ መንገድ ሲጨምር በጣም በጣም ረዥም ነው እስከ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ብቻ ያለው ከዛ በኋላ ደግሞ ይቀጥላል ማለት ነው።

በዚህ ውስጥ ያስደነቀኝ ነገር እንጦጦ አካባቢ ስንጀምር የኢንጆሪ ልማት ሙከራ ተደርጎ ነበር እና ኢንጆሪ ልማት አዲስ አበባ ላይ በእንደዚህ ያለ ከፍታ ላይ እንደሚመረት ከዚህ ቀደም እምብዛም አናቅም ነበር። እንሞክር ተብሎ ነው የጀመርነው ዛሬ ያየነው ውጤት

ግን በጣም ይገርማል፤ ኢንጆሪው ደግሞ እንደሰማሁት ዛሬ በየሁለት ቀኑ የሚለቀም ነገር ነው እንደ ቡና ዓመት ጠብቀህ፣ እንደ ፓፓያ ወራት ጠብቀህ አይነት ሳይሆን በየቀኑ፣ በየሁለት ሶስት ቀኑ የሚለቀም ነገር ነው እና ይሄን ነገር ብናስፋፋ አዲስ አበባ እና አካባቢው ዋጋውም ውድነው ለሀገር ውስጥ ገበያ ለውጭም ልናውለው እንደምንችል የሚያመላክት ነገር አለ። ብርቱካን ተተክሏል፣ ሎሚ ተተክሏል፣ የደጋ ቡና ተተክሏል፣ ማር አይታችኋል ከእንጦጦ የተለየ መዓዛ ያለው ማር ማየት ችለናል። እንደዚህ አይነት የከተማ እርሻን የሚያሳልጡ ምግብ ለማምረት የሚያግዙ ውሃውን ለፍራፍሬ፣ ውሃውን ለሀገር በቀል ዛፎች፣ ውሃውን ለሚበሉ ነገሮች መጠቀም የምንችልበትን እድል የሚሰጥ ስራ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ባህር ዛፍ በተፈጥሮ በከፍተኛ ደረጃ ውሃ የሚመጥ ስለሆነ ድርቀት ያስከትላል። ባህር ዛፉን እያስወገድን ሀገር በቀል ዛፎች እያሰፋን ስንሄድ ተራራው ብዙ ውሃ የመያዝ እና ለታችኛው ተፋሰስ ደግሞ ውሃ የመልቀቅ አቅም እያሳደገ ይሄዳል። ቅድም እንዳያችሁት ባህርዛፍ የበዛበት እና ያነሰባቸው አካባቢዎች ይለያሉ ከወዲው እነዛ ሀገር በቀል ዛፎች ያሉበት ጥቅጥቅ ያሉ ሆነው የተለየ ግርማ፣ የተለየ ውበት አላቸው፤ ከውሃ በተጨማሪ እሱን ማስፋት ይፈልጋል። እንጦጦ ተራራ ላይ ያሉትን ባህር ዛፎች በሙሉ በማንሳት በሃገር በቀል ዛፎች መተካት ያስፈልጋል። ለመሬት ጥበቃውም ፣ ለዉሃ ማቆየቱም ለአጠቃላይ ለእርጥበት ማቆየትም ባህር ዛፍን እያስወገዱ ሃገር በቀል ዛፎች መተካት አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል።

በተለይ በተለይ ደግሞ የገረመኝ እና ያስደሰተኝ ነገር ተራራማ አካባቢ ስለሆነ አፈር ዝናብ ሲመጣ ተጠርጎ ስለሚሄድ ያን አፈር ለመከላከል የተሰሩ እርከኖች በኮንሶ ሙያተኞች ነው የተሰሩት ከውጭ ሀገር በመጡ ሰዎች አይደለም፤ የከተማ ጠበብቶች፣ ሳይንቲስቶች፣ አዋቂዎች አይደሉም በገጠር ያለው የሃገራችን ነዋሪ ለከተማም አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችለው ዕውቀት ብቃት እንዳለ ያየሁበት ነው። የኮንሶ እጅ ተራራ ላይ የሚሰሩትን የእርከን ስራ በምትመለከትበት ጊዜ በፍጹም ከማሽን ውጪ በዛ ጥንቃቄ ሰው ይገነባዋል ተብሎ አይታሰብም እና ኢትዮጵያ ውስጥ በግራ በቀኝ ስንሄድ የተለያዩ እውቀቶች አሉ፣ ብቃቶች አሉ እነሱን ማስተባበር፣ ማቃናት የከተማውን ለገጠር የገጠሩን ለከተማ ማምጣት ብንችል ምን ያክል ሀገራችንን ማስፋት፣ መለወጥ፣ ማሳመር እንደምንችል ያየሁበት ነው።

የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት ብዙ ጊዜ የተናገርንለት፣ አስፈላጊነቱን የገለጥነው ጉዳይ ቢሆንም ዛሬ ግን አንተም እኔም ስናየው እንደዚህ ያለው ስራ ለኢትዮጵያ ምን ያክል አስፈላጊ ምን

ያክል አስደማሚ ስራ እንደሆነ ማየት ችያለሁ። ስንጀምር እዚህ ወንዝ ዳርቻ ቅድም በስዕል እንዳያችሁት በጣም ብዙ የታጨቁ ቤቶች ነበሩ፤ በትክክል በእቅድ የተሰሩ፣ ሰዉ የታጨቁ ቤቶች ነበሩ እና እነዛ ቤቶች ክረምት ሲሆን ጎርፍ ሲመጣ ለአደጋ የሚጋለጡ ናቸው። ውሃው ይሸታል አኗኗራቸው ምንም አይነት መኪና አቅርቦት የለውም፤ ሰው ቢሞት፣ ሰርግ ቢኖር፣ ቢታመም ያንን ሰው ከዚህ አውጥቶ ወደ ህክምና መውሰድ የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም ያን ሁሉ ነገር የሚቀይር፣ አካባቢን የሚቀይር፣ የኑሮ ዘያችንን የሚያሻሽል፣ ሰዎች እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል አካባቢ መፈጠሩ በጣም አስደሳች ነው።

እኔ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች፣ ከሌላ ቦታ እየመጡ አዲስ አበባ ለሚጎበኙ ሰዎች ያለኝ መልዕእክት ጠዋት ጠዋት በሳምንት አንድ ቀን ወይም ሁለት ቀን ጂም ከምታሳልፉ ወይም ከምትተኙ ከ 12 ወይም 12፡30 ተኩል ከእንጦጦ ጀምሮ እስከ ቀጨኔ መድኃኔዓለም እስከ ፒያሳ 10-15 ኪሎ ሜትር ብትጓዙ አየሩ ቀዝቃዛ ስለሆነ የድካም ስሜት ሳይሰማችሁ፣ ብዙ ነገር እያያችሁ፣ አካላችሁን መገንባት ትችላላችሁ። ሃገራችሁን ለማወቅ፣ የሃገራችንን ውበት ለማድነቅ የቀረ የጎደለ ጉዳይ ካለም ለመሙላት ከማየት የዘለለ፣ በአካል ቦታው ላይ ከመገኘት የዘለለ ዕውቀት የሚገኝበት መንገድ ስለሌለ ማየት ማመን ነውና መጥታችሁ እዩ ማለት እፈልጋለሁ።

እንግዲህ በድምሩ ከእንጦጦ ጀምሮ እስከ ቦሌ ያለው የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት በአብዛኛው ተጠናቋል፤ ዛሬ ከምናስመርቀው ውጭ የሚቀሩን ስፍራዎች አሉ እነሱን በሚቀጥሉት ጊዜያቶች እያጠናቀቅን ስናስመርቅ በሚቀጥለው ሁለት ወር፣ ሶስት ወር ጊዜ ውስጥ እስከ ፒኮክ ያለው ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፤ ይህ ለከተማችን ህዝብ ትልቅ ብስራት ነው፣ ለኢትዮጵያ ትልቅ ብስራት ነው። ብዙዎች ሞክረውት ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ሞክረነው አልሰምር ያለውን ስራ በሃገር በቀል ልጆች በኛው ወጣቶች፣ በኛው አርቲስቶች በሚያስደንቅ ሁኔታ የውሃ አካባቢው የሚለውጥ ስራ ተሰርቷል፤ አሁንም ይበልጥ የማጥራት ውሃውን ወደ መጠጣት ወደ መገልገል የማሸጋገር ስራ ይቀረናል፤ ተጨማሪ ስራዎች ይቀራሉ ዛሬ ያየነው ግን አስደማሚ ስራ ነው።

እኔ ያለኝ መልዕክት እንበርታ፣ እንስራ ህዝባችን ስራ ይፈልጋል፣ ሀገራችን ስራ ትፈልጋለች ከበረታን ከሰራን የምናባክነው ጊዜ ከሌለ ምናስበውን እድገት፣ የምናስበውን ለውጥ ልንጎናጸፍ እንችላለን። እድገት፣ ልማት፣ ለውጥን ለመጎናጸፍ ያለው መንገድ ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነው፤ ተግቶ መስራት! ሳይሰንፉ ተግቶ መሮጥ! ያን ማድረግ ከቻልን በወንዝ ዳርቻ እንዳየነው በሌላው መስክ የተሳካ ነገር ማምጣት ይቻላል። ይህ የወንዝ ዳርቻ ስራ ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር፣ ከአፈር ጥበቃ አንጻር፣ ውሃን በንጽህና ከመያዝ

አንጻር፣ የሰውን የኑሮ ዘይቤ ከማሻሻል አንጻር፣ ለመንቀሳቀስ ምቹ ከመሆኑ፣ ለእይታ በጣም ማራኪ ከመሆኑ፣ አጠቃላይ ስራው በፈለገው መመዘኛ እጅግ የሚያኮራ ለብዙ የአፍሪካ ወንድምና እህቶቻችን ትምህርት የሚሆን ነው ብዬ አምናለሁ። በጣም ደስ ብሎኛል፣ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ





የቢሾፍቱ አየር መንገድ ግንባታ ጉብኝት

ሰኔ 8፣ 2018ዓ.ም

አሁን የምንገኘው የቢሾፍቱ አዲሱ ኤርፖርት ወይም በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቁ ፕሮጀክት ወይም በአፍሪካ ታሪክ አንድ ፕሮጀክት፣ ሲንግል ፕሮጀክት በስፋቱ፣ በሚፈስለት ሀብት፣ በሚያንቀሳቅሰው አጠቃላይ ማሽን በአፍሪካ ደረጃም ትልቁ ፕሮጀክት ነው። ዛሬ በቢሾፍቱ ኤርፖርት ግንባታ ከሌሎች አመራሮች ጋር ለማየት የመጣንበት ዋናው ምክንያት ፕሮጀክት ገንዘቡ ወይም የስራው ሃሳብ ብቻ በቂ አይደለም፤ ብዙ ሃገራት እኛም ሃገር ብዙ እናስባለን፤ አንዳንዴ አስፈላጊ ሀብት እንመድባላን። ነገር ግን የፕሮጀክት አመራር ችግር ስላለብን ፕሮጀክት መቼ ጀምረን መቼ እንደምንጨርስ፣ እንዴት ክትትል እንደምናደርግ በቂ ግንዛቤ ስለሌለ አንዳንዴ ይዘገያሉ፣ ተጨማሪ ሃብት ያስወጣሉ፣ አንዳንዴ ደግሞ ሳይከናወኑ ይቀራሉ።

እዚህ ቦታ ላይ ዛሬ ከ8000 በላይ ሰራተኞች አሉ፣ ከ3800 እስከ 4000 የሚጠጋ ማሽን እና መኪናዎች ይንቀሳቀሳሉ፤ ትንሽ ከተማ ማለት ነው እንቅስቃሴው። በ30 ኪሎ ሜትር ክልል ውስጥ ነው ይሄ ስራ የሚሰራው። እዚህ ቦታ በቀን 650ሺ በላይ ሊትር ነዳጅ በየቀኑ እንመግባለን ማሽኖቹን፣ በ10 ቀን ውስጥ ከ6.5 እስከ 7 ሚሊየን ሊትር ነዳጅ ለዚህ ቦታ ብቻ ይቀርባል። ነዳጁን ማቅረብ፣ ማሽነሪ ማቅረብ፣ መኪናዎች ማቅረብ ይሄን የመኪና መተረማመስ ማስተዳደር ደግሞ ስርዓት ይፈልጋል። ቅድም እንዳያችሁት ከመቆጣጠሪያ ማዕከሉ በቴክኖሎጂ ታግዞ በድሮኖች የእያንዳንዱን መኪና እንቅስቃሴ ቁጥጥር ይደረጋል።

እያንዳንዱ ድሮን የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች ብቻ ሳይሆኑ አንደኛው መኪና ከየት ተነስቶ የት እንደሚቆም፣ ስንት አፈር እንደሚሞላ ፣በቀን ምን ያክል እንደተሞላ ሁሉ ምስል እየወሰዱ ያን እያስተሳሰሩ ሪፖርት ያቀርባሉ። በመቆጣጠሪያ ሰሌዳው አማካኝነት በቀጥታ የስራውን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ ቴክኖሎጂው በእጅጉ አግዟል። ይሄን የሚያክል ማሽን የሚንቀሳቀስበት ስራ እንደ ሃገር መርተን አናቅም የመጀመሪያችን ነው።

በሀገር ደረጃ ኤርፖርቱን መስራት ብቻ ሳይሆን 4000 መኪና ነጥሮ ባልተለየ መንገድ ማስተዳደር መቻል በራሱ በቀን ምን ያክል የአፈር ብዛት ከየት ቦታ ተነስቶ የት ጋር እንደሚያርፍ ማወቅ በራሱ የአሰራር ስርዓቱን በደንብ መረዳት ለአመራሮች በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉን ስራዎች ሁሉ ከዚህ ስራ ያንሳሉ ግን ይዘገያሉ፣ ተጨማሪ ወጪ ያስወጣሉ፣ ባቀድነው ጥራት አያልቁም ለምን የሚለውን መልስ ለማግኘት

ይሄን የሚያክል ግዙፍ ፕሮጀክት በምን አይነት ኦፐሬቲንግ ስርዓት እንደምንሰራ መገንዘብ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ይሄንን ማሳካት ከቻልን ሌሎቹን ከዚህ በቀለለ ማኔጅ ማድረግ ይቻል ነበር ስርዓት ቢኖረን፣ ዳሽቦርድ ኖሮን በየቀኑ ስራዎቻችንን ማየት ብንችል፣ ቨርችዋሊ ምንቆጣጠርበት ስርዓት ብንዘረጋ አብዛኛው ፕሮጀክት በተጀመረለት ጊዜ እና ጥራት አልቆ የህዝብን እርካታ ሊያረጋግጥ ይችላል። እና ይህ የቢሾፍቱ ኤርፖርት ስራ በጣም ግዙፍ ነው ለኢትዮጵያን ትልቅ ክብር ነው።

ብዙዎች አትችሉም፣ ገንዘቡም አይገኝም፣ ስራውን መምራት አይሆንላችሁም፣ ይሄንም ያክል ግዙፍ ነገር ለምን ታስባላችሁ የሚል ምልከታ ያለው እሳቤ ሲያራግቡ ይሰማል። እውነታቸውን ነው ከነሱ አንጻር አይገባንም እኛ ደግሞ እንችላለን፣ ይገባናል፣ የሚመጥነን ትልቅ ነገር ነው እያልን ነው ማን እንደሚያሸንፍ ጊዜው ሲደርስ እናያለን። ይሄ ኤርፖርት ከዚህ ቀደም እንደነበረው ፕሮጀክት አይደለም በከፍተኛ ክትትል የሚመራ ነው፤ ባልነው ጊዜ እንጨርሰዋለን። የሚገጥሙ ፈተናዎች በጣም ብዙ ናቸው እነዚያን ፈተናዎች በቅርበት እየፈታን ፕሮጀክቱን በማሳካት ኢትዮጵያ ብቻ አይደለችም አፍሪካ ማሳካት እንደምትችል ማሰብ፣ ማቀድ፣ መስራት እንደምትችል ለአለም የምናሳይበት አፍሪካን የምናነቃቃበት ግዙፍ ስራ ነው።

በአፍሪካ ደረጃ የሚታሰቡ ሃሳቦች፤ ከሃሳብ ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ሙሉ በሙሉ ሂደቱን በቅርበት ለማወቅና ለመምራት በሚደረገው ጥረት አናሳ መሆን ምክንያት አንዳንዶች ውሽብልቅ ሆኖው እየገቡ ወደፊትም ወደኋላም እንዳይሄድ አንቀው የማስቀረት አቅም አላቸው። አንዱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ምንም አይነት ማሃከል ላይ በሽብልቅ ፎርም ገብቶ ስራውን የሚያደናቅፍ ነገር እንዳይኖር ገንዘብ ሊሆን ይችላል፣ ዕውቀት ሊሆን ይችላል ሌሎችም ጉዳዮች ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ማብሰር፣ መናገር የምፈልገው ነገር ለልጆቻችን የሚተርፍ፣ የሚያልፍ ትልቅ መሰረት እዚህ ቦታ እያስቀመጥን ነው።

ይሄ የኢትዮጵያን ገጽ፣ የኢትዮጵያን መልክ፣ የኢትዮጵያን ሃብት ይቀየራል። ይሄ ስራ በሚያልቅበት ሰዓት፣ ይሄ ሲንግል ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ጂዲፒ ውስጥ ያለው ሼር በጣም ከፍተኛ ነው የሚሆነው፤ የሚስባቸው ከፍተኛ የሆነ ቪርቪስ ኢንዱስትሪ አለ። አውሮፕላን ሲባል ብቻውን አይደለም በሚመጣው በሚሄደው ሰው ጭምር ከፍተኛ ሀብት ይንቀሳቀሳል። በቱሪዝም የምንሰራው ስራ አለ ያ ሁሉ ሀብቶቻችን መልስ የሚያገኙት ይሄ ኤርፖርት በደንብ ሲያልቅ ነው። ብዙዎች ሲመጡ፣ ብዙዎች ሲያድሩ፣ ብዙዎች ሲጠቀሙ፣ ሲገለገሉ እዚያ ውስጥ የብዙ ሰዎች ህይወትን የሚነካ ነገር ይፈጠራል። ዛሬ

8000 ሰው የቀጠረው ይህ ፕሮጀክት እያለቀ በሚሄድበት ሰዓት ከሚቀጥረው ባሻገር የሚነካቸው ዜጎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ይሆናሉ እና እንደዚህ ያለውን ሜጋ ነገር ማሰብ አተልቆ ማሰብ፣ አተልቆ መጀመር ፈጥኖ እና በጥራት መጨረስ እንደ አዲስ ልምምድ ኢትዮጵያ ውስጥ እየጀመርን ነው ያለነው፣ እየተማርን ነው ያለነው ይሄን ነገር አፍጥነን በማሰናሰል የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ማድረግ ያስፈልጋል።

ይሄ ወቅት የእኛ ጊዜ ነው፣ ይሄ ጊዜ የኢትዮጵያ ጊዜ ነው፣ ይሄ ጊዜ የአፍሪካ ጊዜ ነው ፣ይሄ ጊዜ የእኛ ጊዜ መሆኑን መናገር ብቻ ሳይሆን ያንን ለመተርጎም የሚያስችል ስራ መስራት ያስፈልጋል። ይሄ ጊዜ ካመለጠን መልሰን እንደዚህ ያለውን ነገር ለማሰብ እና ለመስራት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። እና ወቅቱ የእኛ ነው ጉብቶናል በትልቁ አስበን፣ በትንሹ ጀምረን፣ አሰናስለን፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ እየሰራን እንገኛለን፤ ትልቅ ብስራት ነው። ይሄን የተረማመሰ ማሸን ማየት በራሱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተስፋ ነው። ለነገሩ ተስፋ እንትከል ብለን አረንጓዴ ዐሻራን እየጀመርን ስለሆነ ሲደመር ዛሬ ያየሁት ነገር የጀመርነው መንገድ ትክክል መሆኑን፣ ኢትዮጵያ የሚመጥናት፣ የሚገባት እንደዚህ ያለ ግዙፍ ስራ መሆኑን ለማየት ችያለሁ።

ይህ ስራ እንዲከናወን በቅርበት የሚመራ ስትሪንግ ኮሚቴ አለ፤ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የሚመራ ስትሪንግ ኮሚቴውን ማመስገን እፈልጋለሁ፣ የቦርድ አባላትን ማመስገን እፈልጋለው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ማኔጅመንት አባላትን ማመስገን እፈልጋለሁ። ብዙ ወዳጆቻችን ከግራ ከቀኝ የስራውን ግዝፈት አይተው ለማገዝ፣ ለመደገፍ፣ የሚያደርጉትን ጥረት ማድነቅ ማመስገን እፈልጋለሁ። ከሁሉ በላይ በዚህ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች አርሶ አደሮች መኖሪያቸውን፣ ቦታቸውን፣ እርሻቸውን ለቀው እንደዚህ ያለው የሃገር ልማት እዚህ ቦታ እንዲሆን ላደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ። የእኛ መንግሥት እንደሚታወቀው አርሶ አደር ሲያነሳ እንደ ከዚህ ቀደሙ እነሱን ጥሎ ልማት አያመጣም 100 በመቶ የነሱ ህይወት መሻሻል እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፤ ቤት ገንብተናል፣ ቢዝነስ ተቋማት የሰራንላቸው ነው ፣ ማንም አርሶ አደር በዚህ ፕሮጀክት ምክንያት የሚጎዳ አይኖርም።

ይሄ ፕሮጀክት ለዚህ አካባቢ አርሶ አደሮች ትልቅ በረከት ነው፣ ለአዲስ አበባ እና ዙሪያዋ ትልቅ በረከት ነው፣ ለኢትዮጵያ ትልቅ በረከት ነው፣ ለምስራቅ አፍሪካ ትልቅ በረከት ነው፣ እውነት ለመናገር ለአፍሪካም ትልቅ በረከት ነው። በአፍሪካ ውስጥ እንደሚቻል ማሳያ ፕሮጀክት ነው፤ እንደሚቻል ማሳያ ብቻ ሳይሆን ብዙ ሃብት ወደ አፍሪካ የሚያመጣ ፕሮጀክት ነው። ሁሉንም ሰው ደረጃው ቢለያይም የሚጠቅም እንጂ ሚጎዳ

ፕሮጀክት አይደለም እና መባረክ ነው፣ መታደል ነው እንዲህ ያለውን ነገር ማድረግ መልካም ነው። ለዚህ ጉዳይ መተባበር ጥሩ ነው ብለን በአንድ መንፈስ፣ በአንድ ልብ አብረን እንድንቆም፣ እንድናሳካ፣ እንድንሰራ፣ እንደምንችል፣ በተግባር እንድንገልጥ፣ እንድናሳይ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። እንግዲህ አስደሳች ስራ ነው፣ አስደማሚ ስራ ነው፣ አስደናቂ ስራ ነው፣ ለልጆቻችን ትልቅ መሰረት ነው። ይሄንን መሰረት ከመጣል በላይ ለኛ ደሞ እንደ አገልጋይ የሚያስደስተን ነገር የለም።

ልጆቻችን ተስፋ አላቸው፣ ኢትዮጵያ ተስፋ አላት፣ ብልጽግናችንን እውን እናደርጋለን። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተባበረ ክንድ የኢትዮጵያን ድህነት ለመስበር፣ የጠለሸ ማንነት ለመቀየር የበለጸገች እና ያደገች ኢትዮጵያን በጋራ ለማየት፣ ለልጆቻችን ለማውረስ አንድ ላይ እንቁም፣ እንተባበር፣ እንስራ፣ ከስራ ከልፋት ውጪ ቁጭ ብለን በማውራት የምናመጣው ውጤት የለም፣ በስራ ብቻ ነው የሚቀየረው፣ ሰርተን እንቀይር የሚል መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል እንኳን ደስ አላችሁ!
ቢሾፍቱ



የ2018ዓ.ም አረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር

ሰኔ 8፣ 2018ዓ.ም

እንዴት ከረማችሁ?
Akkam jirtu? Nagaadha miti?
ክቡር አፈ ጉባዔ ታገሰ ጫፎ፣
ክቡር አፈ ጉባዔ አገኘው ተሻገር፣
ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣
ክቡር አቶ አደም ፋራህ የፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት፣
የተከበራችሁ የሁሉም ክልል ርዕሳን መስተዳድሮች፣ የሁለቱ ከተማ ከንቲባዎች ፣ ሚኒስትሮች፣ አባ ገዳዎች፣ ሀደ ሲንቄዎች፣ የቢሾፍቱ ፍልቅልቅ ከተማ ነዋሪዎች ሁላችሁም ለዚህ ታላቅ ቀን እንኳን በሰላም አደረሰን፣ እንኳን አደረሳችሁ።
የዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሃግብር በቢሾፍቱ እንዲጀመር ከተወሰነበት ዋነኛ ምክንያት አንዱ የቢሾፍቱ ከተማ የኮሪደር ስራ ብቻ ሳይሆን ዛፍ በመትከል፣ አበባ በመትከል፣ ችግኝ በማፍላት ለአዲስ አበባም ጭምር ትልቅ ግብአት ስለሆነችና የዚህ ዓላማ ስኬት ለነበራችሁ አስተዋጽኦ እና ለነበራቹ ድጋፍ ምስጋና ለማቅረብ ጭምር ነውና እንኳን ደስ አላችሁ።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በቀጥታ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ከማረጋገጥ፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና ከማረጋገጥ ህልማችን ጋር የሚተሳሰር አንኳር ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በምግብ ራስን በመቻል፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ድንበርን በማስጠበቅ፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ቅርሶቻችን በመጠበቅ፣የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መረጃችንን በመጠበቅ በብዙ መልኩ የሚገለጥ ሲሆን የአረንጓዴ ዐሻራና ሉዓላዊነት ያላቸው ትስስር ምን እንደሚመስል ለመረዳት እንዲያግዘን፤ የአንድ ሃገር ሉዓላዊነት ተደፈረ የሚባለው በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ነው። አንደኛው መንገድ ባዕድ አልሞ፣ አስቦ ታጥቆ ድንበር ጥሶ ሲገባብን ያኔ የሃገር ሉዓላዊነት ተደፈረ ይባላል። በዘመናት መካከል ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እንደዚህ ያለው መደፈር እንዳያጋጥም ህይወታቸውን፣ አጥንታቸውን፣ ደማቸውን፣ ማንነታቸውን በመገበር ነጻ ሃገር ሊያስረክቡን ችለዋል። ሁለተኛው ሉዓላዊነት የሚደፈርበት መንገድ ጠላት ከውጭ መጥቶ ሳይሆን የእኛ ሀብት፣ የእኛ ንብረት በዋዛ ፈዛዛ መልሰን የማንተካው እንደ አፈር ያለው ውድ ሀብት ድንበር ጥሶ ከክልላችን ሲወጣ ሌላ የሉዓላዊነት መደፈር መገለጫ ነው።

የመጣን መከላከል ብቻ ሳይሆን አለአግባብ የሚወጣን ጭምር ተከላክለን ማቆየት

የመጣን መከላከል ብቻ ሳይሆን አለአግባብ የሚወጣን ጭምር ተከላክለን ማቆየት ያስፈልግ ነበር፣ ያስፈልጋል ለዚህም ነው የምንሰራው። ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ በተሟላ ሁኔታ ሳትገነዘብ እና ሳታቅ ያጣችው የአፈር መጠን በገንዘብ ሊተመን አይችልም። ከፍተኛ ሀብት ስናጣ ቆይተናል። ያንን አፈር ከመሸርሸር፣ በነጻ ከመጓዝ ከምስጋና ውጭ ከመቀበል ተከላክሎ ማቆየት ሉዓላዊነትን የምንከላከልበት አንዱ መገለጫ ነው። መጥቶም ብንከላከል ሳያስፈቅድ ሲሄድም ብንከላከል ሁለቱም ለኢትዮጵያ ህልውና መቀጠል ወሳኝ ጉዳዮች ስለሆኑ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ከሚያስጠብቁ በአንዱ ጉዳይ እኔ እና እናንተ እየተሳተፍን እንደሆን አምነን ገብቶን ደስ ሊለን እና በደስታ ልንተክል እንደሚገባ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

የእኛ አባቶች ዐድዋ ላይ ገድል ሰርተዋል፤ እኔና እናንተ በአረንጓዴ ዐሻራ ሌላ ገድል እየሰራን ነው። ልጆቻችን ሁለት የሉዓላዊነት መገለጫ ያስባሉ፤ ዐድዋ ላይ ተዋግተው ከውጭ የመጣን ጠላት ተከላከሉ። በአረንጓዴ ዐሻራ ዘመን ደግሞ ተባብረው ችግኝ ተክለው የሚሸረሸር ተራራን፣ የሚጓዝ አፈርን፣ የሚነጥፍ ውሃን ተከላከሉ ብለው ሁለቱንም በእኩል ልጆቻችን ለማውሳት እንዲችሉ ስለሚያስችል በሰራችሁት ስራ ገናም በምንሰራው ስራ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ተሳካላችሁ ማለት እወዳለሁ።

የዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ መሪ ቃል “ተስፋን መትከል” ይላል፤ ተስፋን መትከል የነገን ብሩህ ታሪክ ዛሬ መጽሐፍ ነው። ተስፋን መትከል የተስፋችን ስሮች ወደ ታች ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ የብልጽግና ግንዶች ወደ ላይ እንዲያድጉ፣ የብልጽግና ቅርንጫፎች ወደ ጎን እንዲስፋፉ፣ የብልጽግና ፍሬዎች ከተከልነው ዛፍ የምንበላው የምንሸጠው ሀብት እንዲሆኑ የሚያስችል ነው። ለምን ተስፋን መትከል በተለየ መንገድ መረጣችሁ ያላችሁ እንደሆነ ተስፋ በጣም በርካታ ትርጓሜዎች አሉት። ለምሳሌ የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች በሰባተኛው ሀገራዊ ምርጫ ሙሉ ቀን በፀሐይ በውርጭ ሳይታክቱ ተሰልፈው መርጠዋል። የመረጡት ግን የቢሾፍቱ ከንቲባ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በቂ ስራ ሰሩልን ብለው ሳይሆን ሊሰሩልን ይችላል ብለው ተስፋ አድርገው ነው። ተስፋን ታጥቀው ተስፋን አድርገው ብንደግፍ፣ አብረን ብንቆም የተሻለ ልማት ሊመጣ ይችላል ብለው ነው። በዚህ ምርጫ የምታሸንፉ ሰዎች አስምራችሁ ልትገነዘቡ የሚገባው ነገር የኢትዮጵያ ህዝብ ተሰርቶለት ሳይሆን ተስፋ ሰንቆ ነው የመረጠው።

ይሄንን ተስፋ በተለያየ መንገድ ከዛሬው ኩነት ጋር አያይዞ ማየት ያስፈልጋል። ተስፋ አረንጓዴ መቀነት ነው፤ አረንጓዴ መቀነት ስለሆነ ሀገርን ያለብሳል፤ ቅድም እንዳያችሁት የገረጣን፣ የነጣን ስፍራ በአረንጓዴ በለምለም ልብስ ያለብሳል። ተስፋ አረንጓዴ ጸዳል

ነው፤ መንፈስ ያድሳል። እዚህ ቦታ የሚቀመጥ ማንም ሰው ይህንን ተራራ ይሄንን ሃይቅ አይቶ ውስጡ ደስታ የማይሞላ ሀሴት የማይላበስ እና የመረጋጋት ስሜት በውስጡ የማያድር ሰው አይኖርም፤ ተፈጥሮ እንደዚህ አይነት ጉልበት አለው የተረበሸ ማንነት የማከም ጉልበት አለው የአረንጓዴ ጸዳል መንፈስ ያድሳል። አረንጓዴ ወርቅም ነው ተስፋ፤ አረንጓዴ ወርቅ ቢዋቡት ጌጥ ነው፣ ቢነግዱ ቢሸጡበት ደግሞ ሀብት ነው። ቡናን ተመልከቱ ከ600 ሚሊየን ዘንድሮ ሶስት ቢሊየን ገደማ ኤክስፖርት እንደርሳለን። ስንረከብ 600 ሚሊየን ነበር፤ ዛሬ ሶስት ቢሊየን ደርሰናል። ይህ የአረንጓዴ ዐሻራ ውጤት ነው። ተስፋ አረንጓዴ ውርስ ነው፤ትውልድ የሚኮራበት ብሩህ ነገ ዛሬ የሚሳልበት፣ የሚጻፍበት ልጆቻችን ይህንን ባህል፣ ይህንን ልምምድ ይዘው ያደጉ እንደሆነ የበለጸገ አረንጓዴ የለበሰ ከጓሮ፣ ከማሳው የሚበላ፣የሚሸጥ፣ የሚሸመትበት ሀገር ስለሚረከቡ እንደኛ በድህነት፣ በችግር፣ በእርዳታ የሚታወቁ ሳይሆኑ በልተው፣ ጠግበው ማገዝ የሚችሉ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም።

የአረንጓዴ ዐሻራ እንቅስቃሴያችን በጀመርነው መንገድ ተቀናጅተን፣ ተደምረን በአንድ ልቦና መስራት መትከል እስካስቀጠልን ድረስ ኢትዮጵያ የተረጂነት ታሪካ ያ ክፉ ታሪክ እጥፋት ላይ ቆመን የእርዳታ የማገዝ ታሪካ በእኔና በእናንተ ዘመን እንደሚጀመር ምንም ጥርጣሬ የለኝም። ዛሬ የቢሾፍቱ ኤርፖርት ያለበትን የስራ ሁኔታ ከስራ ሃላፊዎች ጋር ለማየት እድል አግኝተን ነበር። የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች ይሄንን ስራ አልፎ አልፎ በእግርም ቢሆን እየሄዳችሁ ማየት አለባችሁ። ብዙ ስራ ፣ ብዙ ፕሮጀክት በተለያየ ሀገር ያየን ቢሆንም እኔ እና ጓደኞቼ ዛሬ የተግባባነው እስከዚህ ባለው እድሜያችን በቢሾፍቱ ኤርፖርት ደረጃ ማሽን የሚንቀሳቀስበት፣ ከፍተኛ ሰው የሚንቀሳቀስበት ስራ አይቼ አላቅም፣ አይተውም አያውቁም እናንተም አይታችሁ አታውቁም። ቅርብ ስላለ በዋዛ ፈዛዛ ማለፍ የለበትም ማየት አለባችሁ፣ መስራት አለባችሁ፣ ማገዝ አለባችሁ፣ መጠበቅ አለባችሁ።

አይችሉም ብለውን ነበር በአረንጓዴ ዐሻራ ችለን ዓለም ተደሚል፤ በኤርፖርት አትችሉም ብለዋል ችለን እናሳርፋቸዋለን!

ለዚህ ሳይሰራለት፣ በበቂ ሳይበላ፣ በበቂ ሳይታገዝ አምኖ በተስፋ ለመረጠ ህዝብ የሚቀጥለው ምርጫ ታላቁ ስጦታ የቢሾፍቱ ኤርፖርት የመጀመሪያውን ዙር መጨረስ ይሆናል፤ ይሄ ትልቅ ቁርጠኝነት ነው። ተመራጩ መንግሥት የሚቀጥለውን ምርጫ ለማድረግ ሲሰናዳ የቢሾፍቱ ኤርፖርት ካላለቀ አትምረጡ። አሁን በተስፋ መርጣችኋል፤ ነገ ግን በተግባር እና ስራን በማስረከብ መሆን አለበት።

የአረንጓዴ ዐሻራ ለምግብ ዋስትና ያለውን ፋይዳ ቅድም በዝርዝር ወንድማችን አቶ አዲሱ አረጋ አቅርቦታል፤ ዋና ጉዳይ አፈራችንን ከስደት ግድባችንን ከደለል መከላከል ስንችል የጎደሉ ሃይቆች ሲሞሉ፣ የጎደሉ ጅረቶች ሲሞሉ፣ ፓምፖች መጠቀም ስንጀምር የኢትዮጵያ ግብርና ምን መሆን እንደሚችል በግልጽ ማየት ተችሏል። ከዚያ በተጨማሪ በሄድንበት ዓለም ሁሉ የተለያዩ የአቮካዶ ዝርያ፣ የብርቱካን ዝርያ፣ የሎሚ ዝርያ፣ የሮማን ዝርያ ባየንባቸው ቦታዎች ሁሉ መጠነኛ ዘር አምጥተን ኢትዮጵያ ውስጥ ከ10 በላይ አዳዲስ የፍራፍሬ ችግኞች እያፈላን እየተከልን እንገኛለን። በሚቀጥሉት ዓመታት ኢትዮጵያ በካካዋ፣ በአዳዲስ የሮማን ዝርያዎች፣ በማካደሚያ፣ በተለያዩ ከዚህ ቀደም በማናውቃቸው ፍራፍሬዎች በገበያ የምናያቸው፣ በማሳችን የምናያቸው፣ ሽጠን የምንጠቀምባቸው ለምግብ ዋስትናችን ሁነኛ ሚና የሚጫወቱ ስለሚሆን ባገኘን ቁጥር ማፍላት፣ ማባዛት፣ መትከል በዚያ ውስጥ ደግሞ ስራን ማበራከት ከሁላችን የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል። ከስራ እድል አንጻር በጣም በርካታ ሰዎች ችግኝ በማፍላት፣ በመሸጥ፣ በማጓጓዝ፣ በመንከባከብ ስራ እያገኙ ይገኛሉ። ከዚያ ባሻገር ቡናው ዶላር ሆኗል፣ አቮካዶ ዶላር ሆኗል፣ የተከልነው ማፍራት ብቻ ሳይሆን ገንዘብ ሆኗል፤ አሁንም ምንተክለው ገንዘብ ይሆናል ሲደመር ልጆቻችን የጠገበች፣ የበለጸገች ሃገር እንዲረከቡ ስለሚያስችል ሳንታክት አብረን እንድንሰራ አደራ ልላችሁ እፈልጋለው።

ከቱሪዝም አንጻር ከዚህ ቀደም በኛ ስህተት ምክንያት የሸሹ የዱር አራዊቶች እየተመለሱ ነው፣ አዕዋፋት እየተመለሱ ነው፤ ሀይቆች ሲሞሉ አዕዋፋትም እየመጡ ነው። እዚህ በቢሾፍቱ ብቻ አሁን እያያችሁ ያላችሁት የአዕዋፋት መበራከት እና መመለስ የዚህ ከተማ ነዋሪዎች የምታስተውሉ ይመስለኛል እኔ ብዙ ቪዲዮ፣ ብዙ ፎቶዎች አሉኝ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ አስደማሚ፣ አስደናቂ የአዕዋፋት ዝርያዎች እንዳሉ ከምናይባቸው የኢትዮጵያ ቀጣናዎች አንዱ ከቢሾፍቱ እስከ አዋሽ ያለው ነው ። ልዩ ዝርያ ያለባቸው የሚያምሩ መደመርን በገሃድ የሚያሳዩ፤ ሲበሩ እንዴት መሰብሰብ ውበት እንደሆነ፣አብሮ መቆም አስፈላጊ እንደሆነ፣ አብሮ የሚሰበሰብ የሚቆምን ሀይል ሳትወዱ በግድ ቀና ብላችሁ ማየት አስገዳጅ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን እነዚህ አዕዋፋት ያሳያሉ። የዱር እንስሳትን ለማየት፣ ጫካዎቻችንን ለማየት፣ ሀይቆቻችንን ለማየት ሰዎች ደግሞ ገንዘብ አምጥተው ያፈሳሉ። በሁሉም መስክ አረንጓዴ ዐሻራ አዋጭ ስራ ነውና ተባብረን እናሳካው።

ባለፉት ዓመታት 48 ቢሊየን ችግኞች ተተክለዋል። በዚህ ዓመት እና በሚቀጥለው ዓመት የምንተክለው ተደምሮ 65 ቢሊየን ለመድረስ እቅድ አለ። ባለፉት ዓመታት ተክለን ቅድም ያየናቸውን የአፍሪካ የአየር ንብረት ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት ተችሏል። ኮፕ ከሰሃራ በታች ባሉ ሃገራት ሲዘጋጅ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ናት። በሚቀጥለው ዓመት በ2019 (2027

በፈረንጆች ህዳርና ታህሳስ) አካባቢ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ70 እስከ 80 ሺህ የሚጠበቁ የዓለም እንግዶች ይመጣሉ ያኔ ሙሽራ ቢሾፍቱ በሺህ የሚቆጠሩ እንግዶች ትቀበላለች። ይህ ስራ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዋነኛው ምክንያት ችለን ዓለም ያልቻለውን ሰርተን ስላሳየን ነው። 48 ቢሊየን በነፃ ህዝብ ተባብሮ የተከለበት አንድም ሃገር ዓለም ላይ የለም ታላቅ ታሪክ ነው። ዘንድሮ ከስምንት ቢሊየን በላይ እንተክላለን በዚያ ወደ 56 ወይም ከዛ በላይ ለመግባት እንሞክራለን። በሚቀጥለው ዓመት ከምንጨምረው ጋር 65 ቢሊየን ችግኝ ተክለን ነው ኮፕ የምናሰናዳው። ኮፕ ኢትዮጵያ ሲዘጋጅ 65 ቢሊየን ችግኝ መትከል የቻለች ሀገር የሚል ዜና ለመላው ዓለም የምናበስርበት ጊዜ ይሆናል።

ይህ እንዲሳካ ተመራቂዎች፣ ሙሽሮች በማንኛውም ሁኔታ የምንሰባሰብ ሰዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣አዛውንቶች፣ ታዳጊዎች ችግኝ መትከል የስራችን አካል መሆኑን፣ ችግኝ መትከል ለልጆቻችን አንድ ቁም ነገር ማቆየት መሆኑን አምነን ከዛሬ ጀምሮ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወደን ፈቅደን ጠዋት ማታ ቀን ሳንል በርብርብ እንድንተክል፤ ስብሰባዎች ችግኝ ሳንተክል እንዳንጀምር ቸርች፣ መስጊድ የምንሄድ ሰዎች ችግኝ ሳንተክል እንዳንጀምር፣ ችግኝ ስንተክል ተፈጥሮን ስንከባከብ መንከባከብ የሚገባንን ምድር ስንከባከብ ጸሎቱ ይደመጣል።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሚቀጥሉት ሁለት ሶስት ወራት ኑ እንደተለመደው ተስፋችንን እንትከል! ኑ ለኢትዮጵያ ወንድና ሴት ታዳጊዎች ተስፋን እንትከል! ኑ በትብብር የገረጣች የደኸየች ኢትዮጵያን አረንጓዴ እናልብስ! ኑ በትብብር ለዓለም ተባብረን ዐድዋ ላይ የፈጠርነውን ገድል ተባብረን አዲስ ገድል በማሳየት አፍሪካን፣ ዓለምን እናንቃ እንተባበር፣ እንችላለን፣ እንስራ፣ እናሳካለን ያ ሲሆን ፈጣሪያችንም ያግዘናል። ሁሌም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና ተከብራ ለዘላለም ትኑር።

ኢትዮጵያ ለምና ለዘላለም መኖር አትችልም፤ ኢትዮጵያ የሌሎችን ድጋፍ ጠይቃ አትችልም፤ በልጆቿ ጥረት ግን ታፍራ ተከብራ ለዘላለም ነጻ ሆና በልጽጋ ትኖራለች።

አመሰግናለሁ!
ቢሾፍቱ



የ2018 ዓ.ም የክረምት የበጎ ፈቃድ ዘመቻ ማስጀመሪያ

ሰኔ 11፣2018**ዓ.ም**

የክረምት በጎ ፈቃድ ስራዎቻችን ላለፉት ጥቂት ዓመታት ብዙ ውጤት አስገኝተዋል። የክረምት በጎ ፈቃድ ስንል የእጅ አጠር ሰዎችን ቤት እንጠግናለን፣ እናድሳለን፣ እንሰራለን፤ የቤት ልማት ላይ የምንሰራው ስራ አንድ የክረምት በጎ ፍቃድ ስራችን ነው። ሀገር በቀል ዛፎች እንተክላለን፣ ፍራፍሬዎችን እንተክላለን፣ በአንዳንድ ቦታ ደግሞ ባህር ዛፎችን እንቀንሳለን፤ ይሄም የክረምት በጎ ፈቃድ ስራችን አካል ነው። ከዚያ ውጪ የገጠር መንገዶች፣ በእጅ የሚሰሩ፣ ቀበሌን ከቀበሌ የሚያገናኙ፣ ሰፈርን ከሰፈር የሚያገናኙ መለስተኛ ድልድዮች በህዝብ አቅም የሚገነቡ ይሰራሉ፤ መድኃኒት መሸጫ ቤቶች ይገነባሉ፣ የህጻናት ማቆያ ትምህርት ቤቶች ይገነባሉ። በእነዚህ ሁሉ ስራ ውስጥ በመንግሥት በጀት የማይሸፈኑ ነገር ግን የማኅበረሰቡን የዕለት ተዕለት ችግር የሚፈቱ በርካታ ውጤታማ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል።

አሁንም ዘንድሮ ወሊሶ ላይ የእኛ መስሪያ ቤት እዚህ ስፍራ ላይ መጠነኛ ቤቶች ይገነባል፤ ልክ አምና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ እንደጀመርነው ስራ ማለት ነው። ታስታውሱ እንደሆነ ወልቂጤ ላይ፣ ስልጤ ወራቤ ላይ፣ ሃዲያ ላይ፣ ከምባታ ላይ ሰርተን ነበር፤ ይህን ስራ ደግሞ ዞኑ፣ ክልሉ፣ ወረዳው፣ ህዝቡ እያስፋፋው ቁጥሩ እያደገ የሚጨበጥ ውጤት እያመጣ ነው። ዘንድሮ ደግሞ እዚህ ወሊሶ ላይ አስጀምረናል። ተስፋችን በሁሉም ክልሎች፣ በሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም ወረዳዎች እያንዳንዱን ማኅበረሰብ ተባብሮ የእጅ አጠር ሰዎችን ቤት ይሰራል፣ ትምህርት ቤቶች ይገነባል፣ መለስተኛ በአከባቢው ሰው አቅም የሚገነቡ መንገዶች ይገነባል፣ ድልድዮች ይገነባል፣ መድኃኒት መሸጫ ቤቶች ይገነባሉ፣ ጤና ኬላዎች ይገነባል። እነዚህ ስራዎች ተሰናስለው መንግሥት በበጀት በእቅድ ከሚሰራቸው ጋር ሲደመሩ ነው የኢትዮጵያን ብልጽግና የሚያረጋግጡት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለው በጀት፣ ባለው የገንዘብ አቅም ብቻ ሊረጋገጥ የሚችል ብልጽግና የለም። ብልጽግና የሚረጋገጠው ያለን ትልቁ ሀብት ሰው ነው። መቶ ሰላሳ ሚሊየን ህዝብ ያላት ሃገር ናት። ይሄ ህዝብ ሲሰበሰብ ጉልበቱን፣ ሀብቱን፣ እውቀቱን ሲደምር በጣም በርካታ ችግሮች መፍታት ይችላል። ለምሳሌ ባለፉት አምስት ስድስት ዓመታት በሀገር ደረጃ ሰላሳ አምስት ሺህ መዋዕለ ሕጻናት ተገንብተዋል። ሰላሳ አምስት ሺህ መዋዕለ ሕጻናት መንግሥት አቅጄ ልስራ ቢል፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አይደለም የአፍሪካ መንግሥታት አቅደን እንስራ ቢሉ ለዓመታት ጊዜ ይፈጅባቸዋል። ሰላሳ አምስት ሺህ ተማሪ አይደለም ሰላሳ አምስት ሺህ ትምህርት ቤት ነው የተገነባው። በዚህ ውስጥ ከአራት ሚሊዮን በላይ ህጻናት ዛሬ በሀገር ደረጃ በመዋዕለ ሕጻናት ታቅፈው ትምህርት

ይማራሉ፤ ከዚህ ቀደም መዋዕለ ሕጻናት የማያውቁ፤ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው ታሪካቸውን፣ ባህላቸውን፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ መሰረታዊ የሚባሉ የትምህርት ስርዓት፣ አብሮ መዋልን ይማራሉ።

ይሄ በጣም በጣም ትልቅ ድል ነው። በመዋዕለ ሕጻናት ላይ የሚገነባ ማንኛውም ስራ ውሎ አድሮ ፍሬ ያፈራል። ከዚህ ቀደም የነበሩት ትምህርት ስርዓታችን ግን የሚያተኩረው አንደኛ ደረጃ ላይ ነው። አንደኛ ደረጃ ሲመጡ ከገጠር የመጡ ልጆች ምንም ነገር ሳይገባቸው ስለሚቀላቀሉ ብዙዎች ተመልሰው ይበተናሉ። መዋዕለ ሕጻናት ላይ በየመንደራቸው ቋንቋ፣ አብሮ መዋልን፣ አብሮ መስራት፣ መጣላት፣ መታረቅን እየተማሩ ያደጉ ልጆች፣ ማኅበራዊ ትስስር የፈጠሩ ልጆች አንደኛ ደረጃ ሲገቡ አቋርጦ የመውጣት መጠን በጣም በጣም ይቀንሳል። ልጅ የሚሰራው እስከ አስር ዓመት ነው፤ እስከ አስር ዓመት የሰጠነውን ማንኛውም ዕውቀት ነው በኋላ በተለያየ መንገድ በቋንቋ እያማረ፣ በተለያየ መንገድ የሚገለጠው እንጂ የሚገነባበት እድሜ እስከ አስር ያለው ነው። ከዚህ ውስጥ እስከ ሰባት ያለው ወይም አብዛኛውበመዶ በመዋዕለ ሕጻናት ውስጥ የሚሸፈን ይሆናል።ያንን ጊዜ ማሳለፍ የለብንም ብለን ነው የምንሰራው።

የክረምት በጎ ፈቃድ ስራዎቻችን አጠቃላይ በሃገር ደረጃ የምንሰራው ሃያ/ሰላሳ ሚሊየን ህዝብ የሚሳተፍበት፣ ብዙ ብር የሚዋጣበት፣ ብዙ ችግሮች የሚፈቱበት፣ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲ መጥተው ቁያቸው ሲውሉ የሚጨበጥ ውለታ ውለው የሚሄዱበት፣ ዛፍ ተክለው አጥር አጥረው፣ የድሃ ቤት ሰርተው፣ መንገዶች ቀይሰው፣ ከወጣቶች ጋር ተባብረው አቅመ ደካሞችን ደግፈው ስለሚመለሱ ወደ ዩኒቨርሲቲ ተመልሰው ፅንሰ-ሀሳብ ሲማሩ መሰረት አላቸው፣ ባህል አላቸው፣ የትብብር መሰረት አላቸው፣ የመተጋገዝ መሰረት አላቸው። ቁያቸውን፣ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን ያውቃሉ። ተነቅለው የተበጠሱ ሳይሆኑ መሰረት ላይ የቆሙ ናቸው።

እንደዚህ ያለው እድገት ነው ሙሉ እድገት የሚሆነው፤ የተነቀለ እድገት፣ ከማኅበረሰቡ የወጣ እድገት ዋጋ የለውም። ቀዬውን ያወቀ፣ የሸማግሌዎችን ተረት ያወቀ፣ የሸማግሌዎችን ምርቃት ያከበረ፣ ሽማግሌዎችን የደገፈ፣ እዚህ የጎደለውን ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ሄዶ የተማረ ሰው ሙሉ ሰው ነው። ያኔ ለሀገር የሚጠቅም፣ ለሀገር የሚበጅ፣ ዝም ብሎ የሚያወራ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ የሚሰራ ይሆናል። የማይሰራ እጅ በሚናገር አፍ ፍሬ አያፈራም፤ የሚሰራ እጅ በሚናገር አፍ፣ በሚያስብ ጭንቅላት የተደገፈ እንደሆነ ግን ብልጽግና ያረጋግጣል። አብዛኛው አሁን ያለንበት ችግር የማይሰሩ እጆች በሚናገሩ አፎች ብቻ ተይዘው ልማት የሚመጣ፣ ሰላም የሚመጣ፣ ብልጽግና የሚረጋገጥ ይመስላችኋል?

ያ መሆን አይችልም። የሚሰራ እጅ፣ የሚናገር አፍ፣ የሚያስብ አእምሮ ሲሰናሰሉ ነው ልማት ለውጥ የሚመጣው።

እና የከረምት በጎ ፍቃድ ስራዎቻችን ከበጀት በላይ ናቸው፣ ከልማት በላይ ናቸው፤ የሚያስተሳስሩ፣ የሚያስተባብሩ፣ የሚያዋህዱ፣ የሚያስተዋውቁ በመልካምነት በሰፈራችን በመንደራችን ቁም ነገር ሰርተን እንድናልፍ የሚያስችሉ ስለሆነ ወጣቶች፣ ጉልበት ያላቸው ልጆች እንደ ታላቅ የክብር ስራ መውሰድ አለባቸው። መትከልንም፣ ቤት መጠገንንም፣ አጥር መጠገንንም፣ እርሻ ማገዝንም፤ አዛውንቶች ደግሞ በዛ ውስጥ ባህልን፣ ቋንቋን ማስተማር፣ ተረትን ማስተማር፣ ጸሎትን ማስተማር፣ መሬት መርገጥን፣ አፈር መንካትን ወደ ሰማይ ሲያንጋጥጡ ለምስጋና እንዲሆን ደግሞ ማስተማር ያስፈልጋል።

ይህ በሚሆንበት ሰዓት ሙሉ ቅርጽ ያላት፣ ምትናበብ፣ ቁም ነገር የምትሰራ፣ ለራሷ የምትበቃ፣ ለሰፈሯ የምትተርፍ፣ ስመጥር የሆነች ኢትዮጵያን መገንባት ያስችላል። እንስራ፣ እንበርታ፤ ከስራ ከመበርታት ውጪ የሚገነባ ሃገር የለም። ተባብረን ከሰራን፣ ከበረታን ግን ምንም ጥርጥር የለውም ባሰብነው መንገድ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ይቻላል። ከፊታችን ያለው ዘመን ብዙ ድካም፣ ብዙ ስራ፣ ብዙ ውጤት የሚጠበቅበት፤ መሰረታዊ የሚባል የኢትዮጵያ ችግር መልክ የሚይዝበት ዓመት ነው ከፊታችን ያለው። በዚህ ጊዜ ውስጥ በጋራ በትብብር ቆመን ስራ እንድንሰራ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ክረምቱን እንጠቀምበት፣ ዝናቡን እንጠቀምበት፣ ጊዜውን እንጠቀምበት፤ ለኢትዮጵያ ብልጽግና አንዳንድ ጡብ የምናኖር መልካም ዜጎች ያድርገን ማለት እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።
በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን



ዲጂታል ለልህቀት ጉባዔ

ሰኔ 13፣2018ዓ.ም

ክቡራን አፈ ጉባዔዎች፣
ክቡር የፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት፣
ክቡራን የክልል ርዕሳነ መስተዳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ስራ ሃላፊዎች፣ እዚህ ቦታ የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ እንኳን ደህና መጣችሁ፣ እንኳን ደስ አላችሁ።

ባለፉት አስር/ሃያ ዓመታት በመንግሥት ስራ ውስጥ የነበራችሁ ሰዎች፣ በተለይም ቴክኖሎጂ ጋር የሚያያዝ ስራ የምትሰሩ ሰዎች የዛሬውን ቀን እንዴት እንደምታዩት መገመት ያስቸግራል፤ እኔ ግን ብዙ ነገር አስታወሰኝ። የአዲስ አበባ ከተማ አቶ መኩርያ ምክትል ከንቲባ እያሉ የአዲስ አበባ መሬት ይዘረፋል እና በካርታና መረጃ ቴክኖሎጂ የዘመነ እናድርገው የሚል ሃሳብ ምን ያክል ሲያጨቃጭቅ፣ ሲያካስስ እንደነበረ ሳስበው፣ የኢትዮጵያ ገቢዎች ገቢው አነስተኛ ነው አሰራሩ ይቀየር ስንል እስከ መንግሥት ድረስ ክስ ቀርቦ የመንግሥት መሪዎች ተሰብስበው ይሄ ጉዳይ ብለው የገመገሙበትን ጊዜ በጣም ያስታውሰኛል። ቢፒአር፣ ቢኤስ ኦቶሜት እናደርግ፣ ዘመን ተቀይሯል እንቀየር ሲባል የነበረው ትግል በሃገር መከላከያ ሚኒስቴር በተለመደዉ ባህላዊ መንገድ የምናደርገው ዝግጅት እና አካሄድ አያዋጣንም እንፍጠን እንዘጋጅ ያልንበትን ዘመን ያስታውሰኛል።

በነገራችን ላይ የዛሬ አስር/ አስራ አምስት ዓመት የኢትዮጵያ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ቴክኖሎጂ ላይ የነበረው ጭቅጭቅ ዌብሳይት ይኑራችሁ አይኑራችሁ ነው። ዌብሳይታችሁ መረጃ ማሻሻያ አያደርግም፣ ያሉት መረጃዎች የዋሉ፣ ያደሩ፣ የቆዩ ናቸው፤ ይሄን ማሻሻል አለባችሁ፣ አለብን ነበር ጭቅጭቁ። ከዚያ ወጥተን የሲቪል አገልግሎት የሚባለው የመንግሥት ቁልፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ህዝብን በብዙ መንገድ ያስምረረ፤ ተቀይሮ አሁን ባለበት ሁኔታ ዘመናዊነት ተላብሶ ማየት ለእንደኔ አይነት ሰው የሚሰጠውን ደስታ መገመት ትችላላችሁ። በዚያ ያለፋችሁ ሰዎች፣ በዚያ ጭቅጭቅ ያለፋችሁ ሰዎች ደግሞ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

መሶብ የምጣኔ ሃብት መሠረተ-ልማት ነው፤ ልክ መንገድ፣ አየር ማረፊያ እንደምንለው ለአንድ ምጣኔ ሃብት ቁልፍ መሠረተ-ልማት ነው። መሶብን በጥቅል ብቻ ሳይሆን በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል። አንድ ዜጋ መታወቂያ ለመውሰድ ሰላሳ ደቂቃ የሚወስድ አገልግሎት ቢሆን ያ ዘምኖ በአስር ደቂቃ ውስጥ መታወቂያውን ማግኘት ከቻለ ለዛ ዜጋ

በነፃ መንግሥት ሃያ ደቂቃ የሚያክል እድሜ ጨመረለት ማለት ነው። ያን ሃያ ደቂቃ ከፈለገ ሰርቶ ያተርፍበታል፣ አርፎ ተጨማሪ ጉልበት ያገኝበታል፣ ሌሎችም ቁም ነገሮች ሊሰራበት ይችላል። ሃያ ደቂቃ ከአንድ አገልግሎት ለአንድ ዜጋ ማትረፍ ማለት በብዙ አገልግሎቶች ሲሰላ በዚያ ሰው እድሜ ውስጥ ምን ያክል የነጠቅነውን ጊዜ፣ የነጠቅነውን ነጻ እድሜ መልሰን እንደሰጠነው ማሰብ ትችላላችሁ፤ ጊዜ በጣም ቁልፍ ሃብት ነው። ሰዎች መለስተኛ አገልግሎት ለማግኘት የምንነጥቃቸው ጊዜዎች ሲደመሩ መንግሥታት በነሱ ድክመት ምክንያት ዓመታትን ከዜጎች ሊወስዱ ይችላሉ፤ ያን የሚያክል ትርፍ የሚያስገኝ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማት ነው።

ሁለተኛው ሌብነት ነው እጅ መንሻ የሚጠየቅበት፤ ሰው አግኝተን ስቆ ሲያስተናግድ አልያም አዝኖ ሲያባርረን የሱን መከፋት እና ማዘን ወደኛ እያጋባው ያንን በሽታ፣ ያንን ሸክም ይዘን በብስጭት ወደ ቤታችን ሄደን ቤተሰብ ውስጥ ችግር የምንፈጥር ሰዎች እንደዚህ ያለው የገንዘብ ብቻ ሳይሆን አሉታዊ ሀይልን ተሸክመን ከመሄድ የሚያድን፣ ገንዘባችንን የሚቆጥብ፣ ጊዜያችንን የሚቆጥብ፣ ዜጎች ደስተኛ ሆነው በዚህኛው ስራ ደስታ የሚቀጥለው ነገር እንዲያሳኩ ያደርጋል። አስከፊው ሁኔታ ደግሞ ብንወስድ አንድ ሰው አገልግሎት ሊወስድ መጥቶ መታወቂያ ሰጪው አበሳጭቶት “ካልከፈልከኝ አልሰጥህም” ብሎት አስከፍቶት በብስጭት ሄዶ መኪና አስነስቶ ሊጋጭ፣ ሊገድል፣ ሊሞትም ይችላል።

ከብዙ ችግር የሚታደግ መሠረተ-ልማት ነው። ወደ መንግሥት ደግሞ ስንወስደው በተደጋጋሚ የመንግሥት ዋነኛ ስብራት “ተቋም ግንባታ ነው” ያልነውን አንድ ተቋም ወይም አንድ ሚኒስቴር ብቻውን ሳይሆን መንግሥት እንደ መንግሥት የተሰናሰለ፣ የሚናበብ አንድ አካል፣ አንድ ተቋም ያደርገዋል። ባንኮች፣ ገቢዎች፣ ፓስፖርት የሚሰጥባቸው ተቋማት የተለያዩ ተቋማት ሳይሆኑ እንደ መንግሥት አንድ ተቋም ሆነው ከአንድ ቦታ አገልግሎት ማቅረብ የሚችሉ ያደርጋቸዋል።

በዘመን ውስጥ ተወዳድረን የሚገባንን ነገር ለማግኘት ቴክኖሎጂ በጣም በጣም ወሳኝ ነገር ነው። ይህ መንግሥት የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ አምስት ቁልፍ ዘርፎችን ብሎ ከማዕድን፣ ከግብርና፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከቱሪዝም እኩል ቴክኖሎጂም አንዱ ዋናው ምሶሶ ነው ያለበትን ቀን እና ጊዜ ሳስበው ይገርመኛል፤ ምክንያቱም ያኔ እንደ እብደት ይቆጠር ነበር። ያኔ ስንወያይ ቴክኖሎጂ በዚህ ፍጥነት ኢትዮጵያ ውስጥ እያንዳንዱን ዜጋ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ይችላል ብሎ የሚያምን ሁለት ሶስት ሰው ማግኘት ከባድ ነበር።

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ከቦሌ እስከ ዋናው መስሪያ ቤት የክትትል ካሜራ እንዲያስገባ የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ ጥያቄ ቀርቦ ፌደራል ፖሊስ “ክፍያ መክፈል አልችልም” ብሎ በነጻ አገልግሎቱ ከቦሌ እስከ ፌደራል ፖሊስ ለመዘርጋት ለወራት የነበረውን ፍትጊያ ልነግራችሁ አልችልም። ከትናንትና ወዲያ ግን አንድ ሚገርም ነገር ገጠመኝ፤ የእኛ መስሪያ ቤት እንግዶች የሆኑ ሰዎች ለስራ መጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከውጭ ሃገር ኢትዮጵያ የመጡ ናቸው። ቀን ተዘዋውረው የወንዝ ዳር ልማት፣ የከተማ ኮሪደር አይተው በኢትዮጵያ ተደንቀው “እንዴት ምታምር ሀገር ናት? “ ብለው ማታ ላይ ከሃያት ሆቴል ወጥተው ሲራመዱ ሁለት ሶስት ሰዎች በጋራ ሄደው ሞባይላቸውን ይሰርቁባቸዋል። ቀኑ ሙሉ ሲያደንቁ ሲያመሰግኑ ነበር የዋሉት፤ በልጆቹ ማታ አራት ሰዓት ገደማ ሞባይል ተወሰደባቸው።

አራት ሰዓት ከአምስት፣ አራት ሰዐት ከአስር ለአዲስ አበባ ፖሊስ ተደውለላቸው፣ ብታምኑም ባታምኑም ዘጠኝ ሰዓት፣ (ከአምስት ሰዓት በኋላ) ዘጠኝ ሰዓት ላይ አንኳክቶ የአዲስ አበባ ፖሊስ ሞባይላቸውን መለሰላቸው። “ኢትዮጵያን በመንገድ ንጽህናዋ፣ በኮሪደሯ፣ በተከለችው ዛፍ ነበር ስናደንቅ የዋልነው፤ ይሄንን ተዓምር ግን አልጠበቅንም። እንኳን በነጻ አንኳክቶ በራችን የሚያመጣ ፖሊስ፣ ገንዘብ ተደራድረን ከፍለን እንኳን መልሰን ስልክ እናገኛለን ብለን አልገመትንም” ብለው ደስተኝነታቸውን ሲገልጹልኝ፤ የኔ እንግዶች ናቸው፤ እንኳንም ያኔ የደህንነት ካሜራ አጨቃጨቀን፣ እንኳንም ያኔ ለምነን ተለክተን ሰራነው፣ ለሌሎች አይደለም ለኔ መልሶ ከፈለኝ ነገርየው ማለት ነው እያየሁ።

በቅርቡ የቢሾፍቱ አየር ማረፍያ ስንሳበኝ በመቆጣጠሪያ ሰሌዳ አማካኝነት ፕሮጀክትን እንዴት በቀጥታ መከታተል እንደሚቻል እንዳየን ስንናገርም ሰምታቹ ይሆናል፤ እዛ ያስደነቀኝ አንድ ነገር በበግንባታው ዘርፍ ቴክኖሎጂ መጠቀም ከማሽነሪዎች ውጭ አስቸጋሪ ነው፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂን አይጠቀምም።

የቢሾፍቱ አየር ማረፍያ ስትሄዱ የምታዩት ግን የተለየ ነገር ነው፤ እያንዳንዱ ግሬደር፣ እያንዳንዱ ዶዘር እዛ ትላልቅ ማሽነሪዎች በሰው ሰራሽ አስተውሎት ይደገፋሉ። ለምሳሌ አንድ ጎርጓዳ ቦታ ያለው ኮትቻ አፈር ተነስቶ የተመረጠ ግብዓት የሚባለው ገብቶ ሲደመደም፣ ሲደለደል፣ በሙሌት ደረጃ ስራው ካለቀ ኮንትራክተሩ ስራውን አቁሞ ሌላ ተቆጣጣሪ ወይም ሌላ ኃይል መጥቶ በሚፈለገው ልክ ጥንካሬ መኖሩን፣ መጠቅጠቁን ያይ ነበር ታውቃላችሁ። ወደ መሰረት ኮርስም ሲያድግ እንደዚሁ፣ ንዑስ-መሰረትም ሲሆን እንደዚሁ ማጣሪያ ይደረጋል። አሁን ግን እራሱ ማሽኑ አፈር እየደለደለ፣ የት ጋር በበቂ ደረጃ እንደተጠቀጠቀ፣ የት ጋር ደግሞ እንደሚቀር እራሱ ትልቁ ማሽን ያውቃል።

“እዚህ ጋር አይበቃም” ብሎ በሰው ሰራሽ አስተውሎት እየታገዘ ይጨርሳል። ከዛ በኋላ ተጨማሪ ሰው መጥቶ አይቆጣጠርም። ምን ያክል ጊዜና ገንዘብ እንደሚቆጥብ ገምቱት። አብዛኛው የእኛ ስራ፣ የእኛ አስፓልት ጥራት የሚጎለው እና በየቦታው የሚቆፈረው የሚቆጣጠሩ ሰዎች እዚህ ጋር ፈትሸው፣ እዛኛው ጋር ሳይፈትሹ ያሳልፋሉ። ረዘም ያለ ስራ ሲሆን ማሽኑ ግን በእያንዳንዱ ሴንቲሜትር እራሱ እያየ “እዚህ ጋር የመጠቅጠቅ ደረጃው ያንሳል” ስለሚል አስፓልቶቻችን በዚያ ቴክኖሎጂ ቢሰሩ በአጠረ ጊዜ ውስጥ አይፈርሱም ማለት ነው፤ የማይነካው ነገር የለም። ከሳምንት በፊት አይታችሁ እንደሆነ አላውቅም፤ ኪራይ ቤቶች የጀመረው የስሪዲ (3D) ቤት አሰራር አለ፣ በማሽን ነው የሚሰራው። አንድ ቤት በስሪዲ (3D)እያተሙ መስራት የሚያስችል ቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ኢትዮጵያ ውስጥ አየን። የቤት ችግር ለኢትዮጵያ ስቃይ ነው። ስሪዲ (3D)ተጠቅመን ቤት የምናበራክት ከሆነ እያንዳንዱን ዜጋ እንነካለን።

የእኛ መሠረተ-ልማት ግንባታ ስርዓት ጥራት ያለው፣ ለትውልድ የሚሸጋገር አይደለም፤ እንደምታውቁት ይሰራል፣ ሽሮ ፈሰስ ባይሆንም ይፈራርሳል፣ ያን የሚቀይር ዘመናዊ ማሽኖች ኖረው፣ ጥራት ያለው መሠረተ-ልማት ከገነባን ሃያ/ሰላሳ ዓመት ያገለግለናል። ዜጎች ለመታወቂያ፣ ለፓስፖርት መከራ ከማየት ጊዜ እንዲቆጥቡ ያደርጋሉ።

በድምሩ ቴክኖሎጂ የማይነካው ዘርፍ የለም፤ ግብርናችንን እየነካ ነው፣ ኢንዱስትሪን እየነካ ነው፣ የማዕድን ዘርፍ እየነካ ነው፣ ቱሪዝም በጣም በብዙ የተሳሰረ ነው። የቴክኖሎጂ ዘርፍ የኢትዮጵያን የፋይናንሻል ዘርፍ ዛሬ ከሃምሳ አምስት ሚሊየን በላይ ሰዎች፣ ዜጎች በሞባይል ገንዘብ በትሪሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ግብይት ሲያደርጉ የምታዩ ሰዎች አቅላችሁ አትመልከቱት። የዛሬ አስራ ዘጠኝ/ አስራ ስምንት ዓመታት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘብ ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ በፋክስ በሚልክበት ዘመን አሰራሩን በቴክኖሎጂ እናዝምነው የሚለው ጥያቄ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ደረጃ ክስ ቀርቦ፣ ተከሰን፣ ተወንጅለንበት በመከራ ያሳካነው ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀላሉ ገንዘብ ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ እንዲተላለፍ ማድረግ የቻለበት ሂደት በዋዛ የመጣ አልነበረም። ያኔ በዘመኑ ብርቅ ነበር፣ አሁን ግን ሞባይል ገንዘብ መጣ፤ ሰው ከቤቱ ሳይወጣ፣ ባንክም ሳይሄድ ገንዘብ እንዲተላለፍ ማድረግ የሚያስችልበትን ተጽዕኖ ቴክኖሎጂ አምጥቷል። ይህ ዘርፍ አሁንም በዘገየነው ልክ ሳይሆን ተሸቀዳድመን በሚገባን ተርታ እንድንቆም የማድረግ ብቃቱ ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ በአፍሪካ ውስጥ አሁን ባለው ሁኔታ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት ሃገራት የቨርቿል አገልግሎት ወይም በአንዳንድ ማዕከል የሚሰጥ አገልግሎት አላቸው፤ መሰብ አይደለም።

ለምሳሌ ውጪ ጉዳይ ሄዳችሁ ውጪ ጉዳይ የሚመለከት የአሰራር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ያለባቸው ሃገራት አሉ፣ በጣም ጥቂት ናቸው። በአፍሪካ ደረጃ ልክ እንደ መሶብ የተቀናጀ ሁሉም አገልግሎት ከአንድ ቦታ የሚሰጥበት ሀገር ግን የለም።

ለአንድ ባለ ስልጣን፣ ለአንድ ሚኒስትሪ፣ ለአንድ ተቋም የሚሰጡ የሞከሩ አሉ፤ የእኛ የሚደንቀው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አንድ ብለን ጀምረን ሰባ ቅርንጫፍ መድረሳችን ነው። ሰባ ቅርንጫፍ በአፍሪካ ሳይሆን ልምድ መውሰጃ በሄድንባቸው ሃገራት በአስር/ አስራ አምስት ዓመታት ሰባ አልደረሱም። አስር/ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ነው የደረሱት ብዛቱ ይገርማል። ያ ደግሞ በተሟላ ሁኔታ ሳይጠናቀቅ ወደ ባስ ስንቀይረው፣ “ባስ የመሶብ አገልግሎት ይስጥ” ብለን ከጀመርን ሶስት ወር ገደማ ነው። የዛን ዕለት “ባስ መሆኑ ብቻውን በቂ አይደለም፣ ኤሌክትሪክ ባስ መሆን አለበት። የጋዝ፣ ጋዝ ስላወጣን የጋዝ ባስ መሆን አለበት” ብለን ነበር፤ ሶስት ወር ሳይሞላ አሁን ውጪ የጋዝ እና የኤሌክትሪክ መሶብ ማየት ይቻላል። ከሁሉም ሚደንቀው ደግሞ በአፍሪካ በሁሉም መስክ የመጀመሪያው የሆነው ዩኒፋይድ መሶብ መተግበርያ ነው።

በስልክ አንድ ማዕከል ሄዶ መገልገል አስደናቂ መሆኑን ተደንቀን ሳንጨርስ ዜጎች ከስልካቸው ላይ አንዳንድ ጉዳይ ካላቸው ከቢታቸው መገልገልን የሚያስችል መሶብን ከማዕከል፣ ከባስ ወደ ስልክ፣ ወደ ሞባይል ያስገባነው። ይህ በዓለም ደረጃ በጣም ጥቂት ሃገራት የደረሱበት ደረጃ ነው። ምክንያቱም በሁሉም በቴክኖሎጂ ባደጉ ሀገራት ውስጥ ትልቁ ችግር መረጃን ከአንድ ተቋም ወደ አንድ ተቋም ያለውን መቀያየር፣ መለዋወጥ እና የመረጃን ልውውጥ በበቂ ደረጃ መገልገል አለመቻል ነው፤ ብዙዎች ጋር መጥፎ ጎን ሆኖ ሚነገረው ። ይሄንን ነገር የሚፈታው ስልክ የተለያዩ ተቋማትን አገልግሎት በአንድ ስልክ መገልገል ከቻልን ቀጥሎ የሚጠበቅብን ጉዳይ እነዚህን መረጃዎች የምናከማችበት አንድ ቦታ መፍጠር ነው።

ከዚህ ቀደም ብየዋለሁ የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመረጃ ቋት እንድትገነባ የተሰጠውን አቅጣጫ ተቀብሎ ምናልባት በሚቀጥለው ዓመት የሚጠናቀቅ ይመስለኛል። በጣም ግዙፍ መረጃ ቋት እየገነባች ነው። አሁን የሚገነባው መረጃ ቋት በየተቋሙ ያለው መረጃ ማዕከል ተደምሮ የዛን መረጃ ቋት ግማሽ ያክል እንኳን አቅም አይኖረውም። ትልቅ አቅም ያለው፣ የመረጃ ሉዓላዊነት ያልነውን፣ የመረጃ ሉዓላዊነት እናረጋግጥ ያልነውን ጉዳይ የሚያሳካ ነው።

የመረጃ ሉዓላዊነት ሲባል ትንሽ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች “በመረጃ ምን ሉዓላዊነት አለ?” የሚል ጥያቄ ሲያነሱ ሰምቻለው። የመረጃ ሉዓላዊነት እንደ እኛ ቴክኖሎጂ ለጀመሩ ሃገራት ነው። ትክክለኛው የቴክኖሎጂ ሉዓላዊነት ነው። ወደዛ ዓላማ አድርገው የሚሰሩ ሀገራት አሉ። “ቴክኖሎጂን አንድ ሀገር ቢከለክለን በኛው መጠቀም የሚያስችል አቅም ያስፈልጋል” ብለው የቴክኖሎጂ ሉዓላዊነት የሚሉ ሃገራት አሉ። እኛ እዛ አልደረስንም፤ እኛ ያልነው የእኛን መረጃ በምናውቀው ስፍራ እናስቀምጥ፣ እነማን ተደራሽ እንደሚያደርጉ እንወቅ፤ የእኛን መረጃ የሚፈልጉ ሰዎችም ሲወስዱ በሚገባቸው ልክ ሚስጥራዊ መረጃን መውሰድ እንዳይችሉ እናድርግ ነው፤ ይሄ ይቻላል። ብዙ ሃገራት አድርገዋል፣ እኛም እናደርገዋለን፤ መረጃ ውድ ሀብት ስለሆነ።

ነገር ግን የመረጃ ሉዓላዊነት በብሄራዊ መረጃ ቋት ግንባታ ብቻ ሳይሆን፣ በካቢኔ ህግ አውጥተን ብቻ ሳይሆን፣ በየተቋሙ ይህ ጉዳይ እንዲተገብር ከጀመርነው ጎን ለጎን በቂ ስላልሆነ የሀርድዌር ምርት እንጀምር ብለን የሰው ሰራሽ አስተውሎት ተቋም ከሌላ ተቋም ጋር በመሆን የላፕቶፕ እና አይፓድ ማምረቻ ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ ጋር ደምሮ እየሰራ ይገኛል።

በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሶፍትዌር ላይ ያለን ብቃት፣ መረጃ ላይ ያለን ብቃት በሃርድዌር ደረጃም ላፕቶፕ እና አይፓድ ማምረት የሚያስችል ስራ እየተሰራ ይገኛል ኢትዮጵያ ውስጥ። ይሄ በሶፍትዌር ላይ ያመጣነው ብቃት የመረጃ ሉዓላዊነት እንድናልም ከረዳን፣ በሃርድዌር ደግሞ የጀመርናቸው ጉዳዮች እያደጉ ሄደው ከሆነ ዓመታት በኋላ ልጆቻችን “የቴክኖሎጂ ሉዓላዊነት” ማለት የሚያስችላቸውን አቅም ለመፍጠር መሰረት ይጥላል ማለት ነው። ቴክኖሎጂ በሁሉም መስክ ኢትዮጵያ ውስጥ እያመጣ ያለውን ነገር ለመገንዘብ እንዲያግዘን ሃምሳ አምስት ሚሊየን ሞባይል ተጠቃሚዎች የቴሌ ብር ይጠቀማሉ።

አምስት ሚሊዮን ኮደርስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰልጥነው በቨርቹዋል አገልግሎት፣ በቢፒዮ፣ በስታርትአፕ ለመቀጠር የሚያስችል መሰረት ይዘዋል። መሰብ አንድ ብለን በዓመት ሰባ ደርሰናል። ዲጂታል ፋይዳ ለብዙ ጊዜ የተናገርንበት ጉዳይ ቢሆን ዲጂታል መታወቂያ ፋይዳ በቅርብ ዓመታት ጀምረን አርባ አምስት ሚሊዮን በላይ ደርሰናል። የህግ አስከባሪ ተቋም በጥቅሉ እውነት ለመናገር አስደናቂ በሚባል ደረጃ ብቃታቸው እንዲዳብር አርገዋል። መጠቀም ብቻ አይደለም መፍጠር ጭምር። የዛሬ ስድስት ሰባት ዓመታት ከጀነራል መኮንኖቹ ጋር ስለ ድሮን ቴክኖሎጂ ስናወራ እንደ ቅዠት ይታይ ነበር።

ድሮን ቴክኖሎጂ ስናወራ እንደ ቅዠት ይታይ ነበር።መጠቀም ስንጀምር ለማየት የሚያጓጓ ነገር ነበር፤ አሁን በስፋት ኢትዮጵያ ታመርታለች። መናገር መጀመር ብቻ ሳይሆን ማምረት እንችላለን። እነዚህ ጉዳዮች ልጆቻችን በተለመደው ፍጥነት እንዳይጓዙ ብቻ ሳይሆን፣ የምንመኘውን ብልጽግና፣ የምንመኘውን ሉዓላዊነት፣ የምንመኘውን የጸና ሀገር ግንባታ ለማረጋገጥ በእጅጉ የሚያግዝ ጉዳይ ስለሆነ ሁላችንም ይሁነን ብለን ከልባችን ወስደን ልንሰራበት የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ በአንክሮ ማሳሰብ እወዳለው። እነዚህ ሁሉ ድሎች፣ እነዚህ ሁሉ አስደሳች ውጤቶች፣ እነዚህ ሁሉ አመርቂ ጅማሮዎች የእኔም፣ የእናንተም፣ የህዝባችንም ደስታ ናቸው። ነገር ግን የሚቀሩ ጉዳዮች ደግሞ አሉ፤ ልማድ ቶሎ አይለቅም፣ መሶብ ሰራን ብንልም አሁንም ዛሬም ሰዎች በእጅ መንሻ ምክንያት ዜጎች ይማረራሉ። በዘንድሮ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ከሌሊት እስከ ሌሊት ተሰልፎ ስለሀገሩ ያለውን ፍቅር፣ ስለ ሃገሩ ያለውን ክብር፣ ስለ ባንዳነት ያለውን ጥላቻ፣ ስለተቋማዊነትና ሰላም ብልጽግና ያለውን ጉጉት በተግባር ሲያሳይ፤ በአንድ ቋንቋ የተናገረው መልዕክት “እድል ብንሰጣቸው አገልግሎት አሻሽለው፣ ሌብነት ቀንሰው፣ ልማት አፋጥነው ልጆቻችን በበቂ ስራ እንዲይዙ ማድረግ ይችላሉ” የሚል እምነት በመያዝ ነው። ይሄንን እምነት በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት መያዝ ይኖርብናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ማክበር፣ ላከበረው ዋጋ መክፈል፣ ካልመሰለው ደግሞ የተቃረነውን ማድረግ ይችላል፣ አሳይቷል ይሄን። ስላከበረን አብዝተን ማክበር፣ ስላከበረን አብዝተን ማገልገል፣ ስላከበረን ባከበረን ልክ ታምነን መገኘት ካልቻልን አይቀጥልም ጉዳዩ። ያ እንዲሆን ሁሉም የስራ ሃላፊዎች በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት ድሮ ከምናረገው በላይ ውጤታማ መሆናችንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። አሁንም በአገልግሎት የሚማረሩ ዜጎች አሉ፤ አሁንም በሌብነት የሚማረሩ ዜጎች አሉ፤ አሁንም ስቆ ማስተናገድ ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር የሆነባቸው ቦታዎች በጣም ሰፊ ናቸው። እያንዳንዱ ተቋም እዚህ ያላችሁ ስማችሁ ይነሳል በዚህ ጉዳይ። ይሄን ፈትሾ ቴክኖሎጂን አስፋፍቶ እና ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ህዝብ ችግር መፍታት የእኔ፣ የእናንተ፣ የሁላችን ሃላፊነት እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል።

መሶብ ሰራን ማለት የህዝባችን እርካታ ጫፍ ደረሰ ማለት አይደለም! ጅማሮው ያስደንቃል ነው ያልነው። በዚህ ፍጥነት እድገታችን ያስደምማል ነው ያልነው እንጂ “በቃ በቃ” አላልንም። ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር፣ ለመሶብ ሃላፊ ያለኝ መልዕክት እስካሁን የሰራችሁት ስራ አስደማሚ ነው። ከአንድ ማዕከል ወደ ባስ፣ ከባስ ወደ ዩኒፋይድ መተግበሪያ ማደጋችሁ ደስ ይላል፤ ግን ይሄ እድገት ሌሎች አፍሪካ ሃገራት ላይ ማየት ስለምንፈልግ በሚቀጥለው ስንገናኝ ስንት ሀገር እንዳስተማራችሁ፣ ስንት ሀገር እንደሸጣችሁ፣ ስንት ብር ኢትዮጵያ እንዳመጣችሁ እንድትነግሩን እንፈልጋለን።

እዚሁ መስራት ብቻ አይደለም፣ ማስፋት ከዛ ደግሞ መሸጥ እና ገንዘብ ማምጣት መለመድ አለበት። ይሄን ጉዳይ መከላከያ አድርጎታል። ገዝቶ ተጠቀመ፣ "ሰራሁ" አለ፣ አሁን ሸጦ ብር እያመጣ ነው። ሸጣችሁ ብር ካላመጣችሁ እና ለብልጽግናው ጉዞ ካላበረከታቹ ደስታችን ሙሉ አይሆንም። ደስታችን ሙሉ እንዲሆን መጀመሪያ እንፍጠር፣ ህዝባችን እናገልግል፣ ከዚያ ደግሞ እዛ ያልደረሱ ሰዎችና ሀገሮች ስላሉ ሸጠን ገንዘብ እናምጣ። በሸጥን ቁጥር፣ በወጣን ቁጥር ብዙ ግብረ መልስ ስለሚመጣ ስራውን በየጊዜው እያደገ፣ እየዘመነ ለመሄድ እድል ይሰጣል። እኛ እየሄዱ መሸመት ብቻ ሳይሆን እየሄዱ መሸጥ፣ እኛ እየሄዱ መማር ብቻ ሳይሆን እየሄዱ ማስተማር ልማዳችን እንዲሆን የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና ሰራተኞች ቀጣይ ሃላፊነታችሁ ይሄ እንደሆነ አስባችሁ ወደ አፍሪካ ሃገራት እንድትወጡ አደራ እላችኋለሁ። የኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ፣ የመደመር ሰው ሰራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ በአፍሪካ የመጀመሪያው ነው።

ብዙ አፍሪካውያንን በነጻ የትምህርት እድል ተቀብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተምራል። እነዛ ተማሪዎች መሶብ ሄደው ይሰራሉ፣ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ይሰራሉ፣ ድሮን ማምረቻ ይሰራሉ፣ ላፕቶፕ ማምረቻ ይሰራሉ፤ ሃገራቸው ሲሄዱ በየሀገራቸው እንደዚያ ያለሙከራ ጅማሮ ያደርጋሉ። እነሱን ስናግዝ እንደ አህጉር በጋራ ተያይዘን ስንወጣ ነው አፍሪካ የማትደፈር፣ ሃብቷን ምትጠቀም፣ ከሌሎች የምትተጋገዝ የምትሆነው። "ሉዓላዊነት ሉአላዊነት" ስንል ከሌሎች አንማርም፣ አናስተምርም ማለት ሳይሆን አውቀን እንሰጣለን፣ አውቀን እንገዛለን ማለት ነው። እርስ በርስ መደጋገፍ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት ማለት ነው። ያን ማሳካት እንድንችል እንድንረባረብ አደራ ልላቹ እፈልጋለሁ።

እጅግ የተወደዳችሁ የስራ አመራሮች፣ የዛሬ ስድስት ዓመት "ስንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ ማምረት አለብን መግዛት የለብንም" ስንል የነበረን የስንዴ ማምረት ብቃት ውስን ነበር። ትልቋ ስንዴ አምራች አፍሪካ ውስጥ ግብጽ ነበረች፣ ዘጠኝ ነጥብ ሰባት ሚሊየን ቶን በዓመት ታመርታለች፤ እኛ በጣም እናንስ ነበር። ዛሬ ኢትዮጵያ ሰላሳ ሶስት ሚሊየን ቶን በዓመት ታመርታለች። ከሁለተኛዋ ግብጽ ከሶስት እጥፍ በላይ ትበልጣለች። የሞባይል ገንዘብ ስንጀምር ኤምፔሳ የኬንያው ከኛ በብዙ ይበልጥ ነበር፤ አሁን እኛ እንበልጣለን። ኮሪደር አዲስ አበባ ስንጀምር ታውቃላችሁ ፍትጊያውን፤ ዛሬ አርባ ምንጭ፣ ሃዋሳ፣ ጅጅጋ፣ ድሬዳዋ፣ ሃረር፣ ጅማ፣ ባህርዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር በየሄደበት በብዙ ከተሞች ቢሾፍቱ፣ አዳማ፣ ነቀምቴ በብዙ ከተሞች የሄደበት መጠንና ፍጥነት ብዙዎች "ገንዘቡን ከየት ታመጣላችሁ? በምን ገንዘብ ትሰራላችሁ?" የሚል ጥያቄ እስኪያስነሱ ድረስ ሰፊ ሆኗል። የብዙ አፍሪካ ሃገራት ልምድ የሚወስዱበት ጉዳይ ሆኗል።

በስንዴ፣ በከተማ፣ አሁን በመሶብ፣ በሰው ሰራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ በብዙ ጉዳዮች ኢትዮጵያ በአፍሪካ ተምሳሌ ትሆናለች ያልነውን ርዕይ ቅዠት ሳይሆን የሚጨበጥ እውነት ማድረግ ስለቻልን፣ ወደ ትክክለኛው ብልጽግና እስክንሄድ ድረስ ደግሞ የበለጠ ትጋት፣ የበለጠ ልፋት፣ የበለጠ ስራ ከኛ እንደሚጠበቅ አስበን በርብርብ እንድንሰራና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያን የኩራት ምንጭ እንዲሆኑ፣ የጸና፣ ለልጆቹ ድህንነትን የማያወርስ ሀገር እንዲሆን፣ ከዚያም አልፎ ለጸረ-ቀኝ ገዢ ትግል ለአፍሪካ ያደረገውን አስተዋጾ ለጸረ-ድህነት ትግልም ተመሳሳይ ድጋፍ ማድረግ የሚችል ሀገር እንዲሆን በጋራ እንድንረባረብ አደራ እያልኩ፤ ተስፋን ከመትከል እንዳትቦዝኑ።

ተስፋን ስንተክል መሶብን እንዴት ማሳደግ እንዳለብን፣ በምግብ ራስ መቻል እንዴት ማደግ እንዳለበት፣ የመረጃ ሉዓላዊነት መረጋገጥ እንዴት እንዳለበት፣ የከተሞች ስራዎቻችን እንዴት ማደግ እንዳለባቸው እያሰብን ተስፋን በክረምቱ እንተክላለን። ህዝብ የሰጠን አደራ ገምግመን ለይተን እራሳችንን እናጠራለን። በተሻለ ቁመና፣ በተሻለ ብቃት የሚቀጥለው አምስት ዓመታት ኢትዮጵያን በአስተማማኝ መሰረት ላይ የማስቀመጥ ስራ እንሰራለን። ይህ ደግሞ የሚሆነው በመደመር ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የሚሆነው አብሮ በመቆም ብቻ ነው። ይህ ደግሞ መሆን የሚችለው እስላም፣ ክርስቲያን፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አፋር አይደለም... ኢትዮጵያዊ በመሆን ነው። ያንን በማድረግ የኢትዮጵያን ብልጽግና በጋራ እንድናረጋግጥ፣ ተስፋ እንድንተክል አደራ ልላችሁ እፈልጋለው። ስለሆነው፣ ስላገኘነው ድል እጅግ አድርጌ ላመሰግናችሁ እፈልጋለሁ፤ የሚጠበቅብን ግን ከዚህ የበለጠ መሆኑን ደግሞ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ። እስካሁን የመጣው ድል የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚጠብቀው አንድ በመቶ ብቻ ነው፤ ለቀሪው በጋራ እንረባረብ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ



ከእንጦጦ እስከ ቀበና የወንዝ ዳርቻ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

—ሰኔ 21፣2018ዓ.ም

ዐይን ካላየ ግንባር ነው የሚባል ሀገርኛ ብሂል አለ። ዐይንን ገልጦ ማየት ካልተቻለ ልክ እንደ ግንባር ተልዕኮውን ዋነኛ ስራውን ያጣዋል። እኛ በበቂ ማየት ባለመቻላችን ለዘመናት በከተማችን ልናይ የሚገባንን ውበት፣ ልናይ የሚገባንን ሳቢ ቦታ ማየት ሳንችል ኖረናል። እንግዲህ እንደምታውቁት ኮከብ አጽባሃ የሚባለው በጣም እድሜ ጠገብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እዚህ ጋር ይገኛል። እዚህ የተማሩ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ። ቀበና ስመጥር ወንዝ ነው፤ ድልድዩ በጣም ይታወቃል። በዚህ አካባቢ ብቸኛው ድልድይ ስለነበረ በዚህ ድልድይ ያልተሻገረ፣ ይሄን አካባቢ የማያውቅ ብዙ ሰው የለም። አዲስ አበባ ቀበና አሁን ያለውን ቅርጽ፣ አሁን ያለውን መልክ፣ አሁን ያለውን ውበት ሊይዝ ይችላል ብሎ ማየት ያስፈልጋል፤ አስቀድሞ ማየት ሲቻል ስራ ይከተላል። ያው እንደምታስታውሱት ኮሪደር ስንጀምር ዋነኛ ስራችን የነበረው እንደ መሪ የወሰድነው ሶስት (ፒ) ነው። የመጀመሪያው ‘ፕሌስ’ ነው ቦታ፤ ቦታ ለይቶ አንጥሮ ማየት መቻል፣ ቦታ በበቂ መለየት መቻል ነው። ሁለተኛው ፒ ‘ፓተርን’ ነው፤ ቦታን ማየት ብቻ አይደለም፣ አጠቃላይ ጉዞውን ቀልጣፋ የሆነ ፓተርን ማልበስ ይፈልጋል። ሶስተኛው ‘ፒፕል’ ነው፤ ለሰዎች ምቹ እንዲሆን ቦታን አይተን፣ ፓተርን አስይዘን ዜጎች፣ ታዳጊ ልጆች ሃገራቸውን እየወደዱ በሃገራቸው እየቦረቁ ማደግ አለባቸው የሚል ቁጭትና እምነት መሻት የነበረ ነው።

ዛሬ እንግዲህ አዲስ አበባ ውስጥ መጠነኛ ባህር ዳር መዝናኛ አየን፣ ሃይቅ አየን፣ የውሃ ላይ ሞተር ሳይክል አየን፣ ትናንሽ ጀልባዎች አየን። የተጓዝነው 10 ኪሎ ሜትር ገደማ ነው። ከእንጦጦ ጫፍ ጀምሮ እስከ ቀበና 10 ኪሎ ሜትር፣ ከጣሊያን ኢምባሲ ጀርባ ጀምሮ እስከ ቀበና ሌላ ሶስት/ አራት ኪሎ ሜትር እንዳየኸው በሁለቱም ሳይድ የእግረኛ መንገድ አለው፤ በጣም ብዙ ቦታ ለልጆች መዝናኛ የሚሆን ቦታ አለው። ዛፎች፣ ፍራፍሬዎች ተተክለዋል። ከላይ ጀምሮ ፍራፍሬ በጣም ተተክሏል፤ የሚፈለገው ይሄ ነው፤ ወፎች መብላት እንዳይችገሩ ፍራፍሬ ካለ፣ መጠጣት እንዳይችገሩ ውሃ ካለ ይመጣሉ ታያችኋለው ተፈጥሮ ይጠራራል፤ ይጠራራና ትክክለኛው ውበቱን ይገልጣል። እና ያየነው ነገር እንደዚህ ያለውን ተስፋ፣ እንደዛ ያለውን የማሰብ አቅም፣ ሰርተን ጨብጠን ስናየው በእጅጉ ያስደስታል።

እንግዲህ መደመር ዋና እሳቤው ቦታ አንሰራም አለን፣ ውሃ አንፈጥርም ሰጥቶናል እሱ፣ ዛፎች አሉ፣ የሰው ጭንቅላት አለ፣ ሃብት አለ፣ በየቀኑ ደግሞ የደከሙ ገንቢዎች አሉ። የብዙ ሰዎች ድካም ውጤት ነው ይሄ። ያ ሲደመር እንደ ውጤት የሚፈጠረው ክሱትነት ነው።

መደመር ሂደት ነው፤ የሚከሰተው አዲሱ ጎልቶ እንዲወጣው የሚያደርገው ማንነት ደግሞ ውጤት ነው። ገንዘብን፣ ዕውቀትን፣ ጉልበትን፣ ሃሳብን፣ የአመራር ብቃትን፣ ክትትልን ስንደምር የዚህ ሂደት ውጤት የሚከሰተው አዲሱ ነገር ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርገው ነገር እንደዚህ ያለው ውበት ይሆናል። አሁንም ስንደመር፣ አሁንም ስንሰናሰል፣ አሁን ስንደጋገፍ ከዚህ የላቀውን ነገር ማድረግ እንችላለን።

በብዙ ደስ ያለኝ ቢሆንም አዲስ አበባ ከዚህ በላይ አቅም አላት። አሁንም አላየንም፣ አሁንም አልሰራንም። እውነት ለመናገር አሁንም አላየንም። ብዙ መታየት የሚገባቸው፣ ብዙ መስራት የሚገባቸው፣ መጨከን የሚገባን ጉዳዮች አሉ። የዚህ አካባቢ ሰዎች በደንብ ያውቁኛል እኔን፤ በሳምንት አንድ ቀን፣ ሁለት ቀን መጣለሁ። ጭቃውን እንዴት እንደምናጠፋው፣ ቆሻሻው እንዴት እንደምናነሳው ስመላለስ ያውቁኛል። የእነርሱን ህይወት እንዴት አስተካክለን ቤት ኖሯቸው ካከባቢው ይቀየራል የሚለው ጉዳይ በረጅም ጊዜ ሂሳብ የመጣ ነው። የሚገርመው የዚህን ቦታ የቀድሞ ሁኔታ እኔ እንደዛሬ አየዋለሁ፤ የሚያውቁት ያውቁታል። እናንተም ፎቶ እዩ። በጣም አሳዛኝ ቦታ ነበር። ዛሬ መጠነኛ ለውጥ አይቼበታለሁ። በእርግጠኝነት ልጆቻችን ይሄን እያዩ አድገው በብዙ አስበልጠው አልቀው እንደሚሰሩ ጥርጥር የለኝም። ባሰብነው ልክ ሰርተናል ብዬ አልገምትም። ብዙ ማየት ስላልቻልን፣ ብዙም ስለሚቸግር፣ ሰዎቻችንም ገብቷቸው ማገዝ ገና ስለሆነ በታየው ልክ አይደለም። ከዚህ በላይ ውብ መሆን ይችላል። በየቦታው ሃይቆች ያስፈልጋሉ፣ ፍራፍሬ ያስፈልጋል፣ ንጹህ ውሃን ማየት ያስፈልጋል፣ ወፎቹን ማየት ያስፈልጋል።

ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተን መኖር ካልቻልን፣ ተፈጥሮን መንከባከብ ካልቻልን፣ የተፈጥሮ ቅጣት ከባድ ነው። ዓለም ላይ ልክ እንደ የስነ-ልቦና ጦርነት እንደምንለው የሥነ-ምህዳር ጦርነት አለ። የሥነ-ምህዳር ጦርነት ውሃ ላይ፣ አፈር ላይ፣ የአየር ንብረት ላይ የሚሰራ ስራ ነው። ልክ በሌላው አስተሳሰብን ሌላ ቦታ ወስዶ መትከል፣ መንቀል እንደሚቻለው ሁሉ የሥነ-ምህዳር ጦርነትም አለ፤ ትውልድ መንቃት አለበት። ዝም ብሎ ከፊት ያለውን ብቻ እያየ ሲርቅ ከዓመታት በኋላ፣ ከአስርት ዓመታት በኋላ የሚያጋጥመንን አደጋ ቸል ማለት አያስፈልገውም። በጥልቀት ማየት፣ መገንዘብ፣ መተጋገዝ፣ መስራት ያስፈልጋል።እና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የሚገባቹ እንዲህ ያለው ነገር ነው። መቆሸሽ እኛ አይገባንም። መጠልሸት እኛ አይገባንም። ማነስ እኛ አይገባንም። ሌላ ቦታ እየሄዱ መቅናት እኛ አይገባንም። ሰርተን እንደምንችል ማሳየት ያስፈልጋል።

ይህንን ስል ለከተማችን ነዋሪዎች፣ በሌላም ዓለም ላሉ ዜጎች መናገር የምፈልገው ነገር ይሄንን ግድብ ስንጀምር አንድ አይደለም ሁለት ሶስት ሙያተኞች አትችሉም ብለውናል።

የምንሰራውን የኮሪደር ስራ አትችሉም የሚል ድምጽ ከግራ ከቀኝ ጠዋት ማታ እንሰማለን። ‘አትችሉም፣ አይሳካላችሁም፣ አትከናወኑም፣ ትጀምራላችሁ እንጂ አትጨርሱም’ የሚሉ ብዙ ድምጾች አሉ። የእኛዎቹ ይገርመኛል፣ ሌሎቹ ግን አይገባችሁም እያሉን ነው። የለም ይገባናል! የለም እንችላለን! ጥንታውያን ነበርን፤ በመሃል ጠፍተን ሊሆን ይችላል። ብንሰላሰል፣ ብንደመር፣ ብንተጋገዝ ውብ ሃገር አለን ፤ ከማናችሁም የማያንስ የሥነ-ምህዳር እኛም ተሰጥቶናል ብለን መናገር ብቻ አይደለም ሰርተን ማሳየት አለብን። የሚደንቀው ነገር ይህ ስራ ሲጀመር እዚህ አካባቢ ያስቸገሩን ሃይሎች ነበሩ። ዛሬ ዋና አድናቂዎች እነሱ ናቸው፤ ዋና ተጠቃሚዎችም እነሱ ናቸው። እና ዜጎች ማየት እንድንችል፣ መንቃት እንድንችል፣ መሰናሰል እንድንችል፣ መስራት እንድንችል፣ ልጆቻችን እኛ ባለፍንበት መከራና ችግር እንዳያልፉ በተገለጠ ማንነት አብረን መቆም እንድንችል አደራ ማለት እፈልጋለው።

ዐይናችን ግንባር እንዳይሆን፣ ዐይናችን ዐይን እንዲሆን ሃገራችንን ማየት አብልጦ መስራት የሚቻል ነገር እንደሆነ አንዱ ማሳያ ቀበና ነው። እና በጣም ደስ ይላል፤ ኑ እዩ፣ ተዝናኑበት፣ ያላየነውን እዩ፣ ያልሰራነውን ስሩ፣ አልቃችሁ አሳምሩና ለልጆቻችን በረከት እና ሃብት አድርጉላቸው ማለት እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ



በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን የልማት ስራዎች ጉብኝት

ሰኔ 25፣2018 **ዓ.ም**

ዛሬ ከጠዋት ጀምረን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን እንገኛለን። ጠዋት ዛሬ ያየነው በጣም አስደሳች ሥራ በምዕራብ አባያ ወረዳ የተጀመረው የገጠር ኮሪደር ሥራ ነው። አምና ታስታውሱ እንደሆነ የገጠር ኮሪደር በየቦታው እኛ ሞዴል ቤቶች እየሠራን ሰዎች ያንን ተከትለው እንዲሠሩ እናበረታታ ነበር። ዘንድሮ ብዙ ቦታ ተጀምሯል ግን እዚህ በምዕራብ አባያ ወረዳ ያየነው ሞዴል የገጠር ኮሪደር ሥራዎች ሙሉ በሙሉ የተገነቡት በአርሶ አደሩ ነው። እኛ የማሠልጠን፣ የጡብ ማሽነሪ የማቅረብ ዓይነት ድጋፍ ከማድረግ ውጭ ሙሉ በሙሉ ወጪው የተሸፈነው፣ ሥራው የተሠራው በአካባቢ አርሶ አደሮች ነው። ስለዚህ የእኛ አርሶ አደሮች ሙዝ ተክለው ከሸጡ በኋላ እንደዚህ ያለውን ቤት መሥራት ቢችሉ እንግዲህ በቤት ውስጥ እንዳያችሁት ቴሌቪዥን አላቸው፣ ስልክና ቻርጀር አላቸው፣ ከጓሮ ፍራፍሬዎች አሉ፣ ዶሮ አለ፣ አሳ አለ፣ ማር አለ፣ ፍየሎች አሉ።

አንድ አርሶ አደር በጓሮ ፍራፍሬ በተለያዩ መንገድ ማምረት የሚችል ከሆነ፣ ማርም ማምረት የሚችል ከሆነ፣ አሳ ካለው፣ ዶሮ ካለው፣ ፍየሎች ላሞች ካለው አንዱ እንኳን ቢጎድል አንዱ እየሞላ ቢያንስ ራስን ማኖር ጸዳ ያለ ኑሮ መኖር የሚባለው ጉዳይ ሊሳካ የሚችል መሆኑን ያመላክታል። ንጽህና ካለ ጤና አለ፤ ምግብ ካለ ጤና አለ፤ ሥርዓት ካለ ሰላም አለ፤ እነዚህ ጉዳዮች ከፍተኛ ግምት ሊሰጣቸው ይገባል። የዜጎቻችንን ሕይወት ይቀይራሉ፣ የአኗኗር ዘይቤያችንን ያሻሽላሉ፤ ኢትዮጵያን ወደምናስበው ከፍታ ወደምናስበው መሻሻል የመውሰድ አቅም አላቸው። ሰው መብራት ሲያገኝ፣ ስልክ ሲያገኝ፣ መረጃ መስማት መለዋወጥ ሲችል፣ በጓሮ ምግብ ማምረት ሲችል ብዙ ጉዳዮች እየቀለሉ ስለሚሄዱ አርሶ አደሮቻችን በጣም መልካም ጅማሮ ጀምረዋል፤ ሊበረታታ ይገባዋል፤ ሊስፋፋ ይገባዋል።

ከወጪ አንጻር እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ገደማ ብር ነው የፈጀባቸው እያንዳንዱ ቤት በዶላር ቢሰላ አስር ሺህ ገደማ ዶላር ማለት ነው። ስለዚህ በውጭ ሀገር ያሉ ዲያስፖራዎች አስር ሺህ ዶላር ለቤተሰቦቻቸው ቢልኩ እንደዚህ ያለውን ቤት መሥራት ይችላሉ ማለት ነው። በጣም በጣም ትንሽ ብር ነው ግን ቤቱ ረጅም ጣሪያ ነው ቅዝቃዜ አለው። መኝታ ቤትና ሳሎን የተለየ ነው፤ ማብሰያ ቤት የተለየ ነው ለኑሮ ምቹ ነው። እኛ ጋር የነበረውን ትልቁን ክፍተት የሚመልስ አሠራርና የኑሮ ዘይቤ ነው ያየነው። ይሄንን እናበረታታለን፤ እንደግፋለን፤ እንዲስፋፋ ከፍተኛ ፍላጎት አለ ተባብረን ማስፋፋት ይኖርብናል።

ትልቁ ገጥሞን የነበረው ፈተና ግን እዚህ ኢትዮጵያ ያመጡ የነበሩ ሰዎች በደቡብ አፍሪካ አምራቾች ነበሩ፤ ኢትዮጵያውያን ሆነው ደቡብ አፍሪካ ላይ ፋብሪካ አላቸው። ከደቡብ አፍሪካ እያመጡ እዚህ ይሸጡ ስለነበር የኢትዮጵያን የማራከስ፣ ጥራት የለውም የማለት፣ የእነርሱ ፋብሪካ እንዲያስገባ ፍላጎቶች ነበሩ።ያ ለምንድነው የሚለውን ስናይ ያው ሰዎች በተቻለ መጠን ዶላር ከሀገር ውስጥ ማውጣት፣ በዚያ ዶላር ደግሞ ሸቀጦች ማስገባት፣ የእነርሱን መክበር ቅድሚያ ሰጥተው ያያሉ ግን ጥሩ አይደለም። ለሀገር ለወል ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ያ ፋብሪካ ተነቅሎ ሊመጣ ይችላል ወደ ሌላ ገበያ ሊሄድ ይችላል። እኛ አንድ ፋብሪካ እዚህ ስንሠራ መቶ ሰው አንድ ሺህ ሰው የሚቀጥር ከሆነ ያ የሥራ ዕድል ጭምር ነው ኤክስፖርት የሚደረገው። ፋብሪካ ውጭ ሆኖ ከውጭ የምንገዛ ከሆነ ለሰዎቹም የምንከፍለው ዜጎቻችንን መቅጠር ሲገባን ማለት ነው። እና የገቢ ንግድን በመተካት በዚህ ዓመት አምስት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ነው ኢንዱስትሪዎቻችን ያመረቱት። በዚህ ብቻ አይደለም በሴራሚክ፣ በሸክላ፣ በሲሚንቶ በተለያዩ ምርቶች እያመረትን በገፍ እናስገባ የነበሩ ጉዳዮችን እየተካን ነው ያለነው።

ከዚያ ውጭ የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እዚህ አርባ ምንጭ አካባቢ ተጀምረዋል፤ እነሱ ሲያልቁ ፍራፍሬዎቹን ብቻ ሳይሆን ጁስ እያደረግን እንልካለን። ለሌማት የእርጎ ወተት ማቀነባበሪያዎች ተሠርተዋል እነሱም ሲቀናጁ ጥሬውን ከምንልክ የተመረተውን ምርት ለከተሞች ለማቅረብ ዕድል ይሰጣል፤ እና በግብርና ዘርፍ በፍራፍሬ ያየነው፣ በገጠር ኮሪደር ያየነው፣ ያን ወደ አግሮ-ኢንደስትሪ የመውሰድ ፍላጎትና ሙከራዎች ያየነው በጣም በጣም ተስፋ ሰጪ ነው። አርባ ምንጭ እንደ ወትሮው ታምራለች እና ጥሩ ጊዜ ነበረን።

ጋሞ ዞን



የአርባ ምንጭ የኮንፈረንስ ሪዞርት ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ሰኔ 27፣2018ዓ.ም

ክቡር አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣
ክቡር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቴዎድሮስ ምህረት፣
የክልላችን ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ጥላሁን፣
የዚህ ፕሮጀክት አስተባባሪና ዋናው አርክቴክት ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኘ፣ እንዲሁም የፕሮጀክቱ ምክትል አስተባባሪ በመሆን ባለፉት ጥቂት ወራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን፣ ምክትላቸው አቶ ለማ፣ በዚህ ስራ ላይ የተሳተፉ ኢትዮጵያውያን ሙያተኞች እና ኮንትራክተሩ ፎርሲ እንዲሁም የጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ የአርባ ምንጭ ነዋሪዎች፣ ይህ ስራ በታቀደለት በዚህ ልክ ተጠናቆ አርባ ምንጭ ከምናውቃት አሁን ወዳየናት ደረጃ ተሸጋግራ ለማየት ስለበቃችሁ፣ ስለበቃን እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ደስ ያለን ማለት እወዳለሁ።

አርባ ምንጭ በተፈጥሮ የነበራትን ውበት አንድ እርምጃ ወደፊት ከፍ የሚያደርገው ትላንት ያየነው ሳቅ ነው። ተራራዎች ይስቃሉ፣ አዛውንቶች ይስቃሉ፣ ህጻናት ይስቃሉ፣ አርባ ምንጭ ስቃ፣ ሳቅ አስተጋብታ ፍቅር ዘርታ የዋለችበትን የትላንትናውን ውሎአችንን ስንመለከት ጥቂት ስራ፣ ጥቂት ድካም፣ ጥቂት መልካም ዘር የዜጎቻችንን ልቦና በምን ያህል ደረጃ እንደሚነካ ያየንበት ሳቅ ደስታ የተጋራንበት እለት ነበረና በድጋሚ ሳቃችሁ እንዳይወሰድባችሁ ደስታችሁ እንዳይወሰድባችሁ በትላንትናው ሳትረኩ አዳዲስ ድል አዳዲስ ሳቅ ማምጣት የምትችሉ እንድትሆኑ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ሀገር ለስራ ጉዳይ ሄጄ ያረፍኩበት ሪዞርት ያጓጓ ነበር። እኔ ክፉ አመል አለኝ የሄድኩበት ስፍራ ስመለከት ቶሎ የመቅናትና ወደዚህ ሀገሬ የማምጣት መሻቴ ከፍተኛ ነው። እና የዚያን ሆቴል ባለቤት ወደ ኢትዮጵያ ጋበዝኩት። አርባ ምንጭ የሚባል ውብ ምድር አለ፣ የእግዜር ድልድይ የሚባል አስገራሚ ተፈጥሮ አለ፣ የደፈረሰውንና የጠራውን ውሃ ከፍሎ የያዘ፣ ነጭ ሳርን ከግርጌው ያስቀመጠ፣ ተራራዎቹ ተሰናስለው የእግዚአብሔርን የእጅ ስራ በአስደናቂ ሁኔታ የሚገልጥ ቦታ አለ። እዚያ ቦታ ላይ መጥተህ ልክ እዚህ ሀገር እንደሰራኸው አይነት የመዝናኛ ሪዞርት ብትሰራልን ብዬ ጋበዝኩት። እሱን መጋበዝ ብቻ ሳይሆን የአርባ ምንጭ ከተማ ከንቲባና አንዳንድ ሀላፊዎችም እዚያ ሄደው እንዲያዩ ተደረገ። ሰውየው መጥቶ አርባ ምንጭ አድሮ የእግዜር ድልድይን አይቶ ሲመለስ አገኘሁት። እና ምኞትህ ጥሩ ነው፣ ፍላጎትህ ጥሩ ነው፣ መንጠራራትህ ጥሩ ነው አርባ ምንጭ ግን ለዚህ ኢንቨስትመንት አልደረሰችም አለኝ።

አርባ ምንጭ አንድ ሆስፒታል የሌላት፣ አንድ ሱፐርማርኬት የሌላት፣ ለኔ ሪዞርት እንኳን በበቂ ደረጃ ግብዓት ማቅረብ የምትችል ከተማ አይደለችም። በዚህ ከተማ ውስጥ ኢንቨስት እንዳደርግ መጋበዝህን ባደንቅም ጊዜው የደረሰ አይመስለኝም አለኝ። ይህ በጣም መራርና ደግሞ እውነተኛ አስተያየት ነበር። ይህንን አስተያየት ስሰማ ምን ሊሰማኝ እንደሚችል እናንተ ገምቱት። ትላንት ማታ የነበረኝ ጉጉት ግን ያንን ሰው ደግሜ ጋብዤ አርባ ምንጭን እንዲያያት ነበረ።

እዚያ ያየሁት ሪዞርት እዚያ ያለውን ሪዞርት አያክልም። እዚያ ያለው ሪዞርት ከአንድ ሺህ በላይ ዘመናዊ ስብሰባ ማዕከል በተለየ ዲዛይን የተሰራ ቦታ የለውም። እዚያ ያየሁት ሪዞርት በውሃ ውስጥ በከፍተኛ ጥልቀት ገብቶ ሰማይ ላይ የወጣ፣ በሰማይ ላይ የሚሽከረከር፣ 360 ዲግሪ ተፈጥሮን ውበትን የሚያሳይ ሬስቶራንት እዚያ አላየሁም። ከዚህ ያነሰውን ጠይቄው አርባ ምንጭ አልደረሰችም አለኝ። ከዚያ የበለጠውን ሰርተን እንደምንችል፣ እንደሚገባን፣ ከማንም የሚያንስ ተፈጥሮና ብቃት እንደሌለን ለዚያ ሰውዬና መሰል እሳቤ ላላቸው ሰዎች በንግግር ሳይሆን በተግባር ማሳየት ጉጉቴ ነው ደግሞም ይመጣል።

የዚያ ሰውዬ ንግግር የሚያስቆጭ ቢሆንም፣ የሚያሳዝን ቢሆንም፣ የሚያስተምር ነገር ግን አለው። የተሰጣችሁን የማታውቁ ሀብታሞች ግን እንደ ደሃ የምትመላለሱ መስራት ስትችሉ በሚረባ በማይረባ የምትሻኮቱ ስለሆናችሁ እናንተ ጋር መጥቼ አልሰራም ነው ያለው በአጭሩ። እንደዚያ አለመሆናችንን ሰርተን ማሳየት፣ እንደዚያ አለመሆናችንን በተግባር መግለጽ ካልቻልን በንግግር ብቻ በልመና ብቻ ኢንቨስትመንት አይከናወንም። አርባ ምንጭ ላይ የተሰራው ይህ ሪዞርት ብቻውን በመንግስት ጣልቃ ገብነት ሳይሆን የግሉ ዘርፍ ወደዚህ ሀገር መጥቶ መስራት እንዲችል ስጋት የቀነሰና ለመምጣት እንዲበረታቱ ያደረገም ስራ ነው። ይህንን ኢንቨስትመንት ተከተሎ የኩሪፍቱ ሪዞርት ባለቤት በአርባ ምንጭ የሰራው ሪዞርት እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በግሉ ዘርፍ ከተሰሩ ስራዎች ሁሉ በሁሉም መመዘኛ የበለጠ ነው።

ለምንድነው አርባ ምንጭ ላይ ደረጃውን ከፍ ያለ ስራ የሰሩት ያለን እንደሆነ ሪዞርት ብቻ አይደለም መንገዶች ይገነባሉ፣ ጨለማው በብርሃን ይተካል፣ የተሻለ ሆስፒታል አለን፣ የነቃ የሚሰራ የሚተጋ ህዝብ አለን፣ የሚመጣን በደስታ የሚቀበል ህዝብ አለን፣ እዚህ ቦታ ኢንቨስት ብናደርግ እንደ ከዚህ ቀደሙ አልደረሳችሁም ሳይሆን እናተርፋለን የሚል ስነ-ልቦና እምነት በግሉ ዘርፍ ላይ ማሳደር በመቻሉ ነው። ለዚያም ስራ አቶ ታዲዎስ በድጋሚ እንኳን ደስ አለህ ብቻ ሳይሆን እጅግ አድርገን እናመሰግንሃለን።

ሰው በሀገሩ የሚገነባው ለዕለት አይደለም። ሰው በሀገሩ የሚሰራው ስራ በእሱ እድሜ የሚፈርስ ነገር አይደለም። ሰው በሀገሩ የሚገነባው ስራ ዐሻራ የሚሆን፣ የሚቆይ፣ ለልጆች የሚሸጋገር መሆን አለበት። ካልቻልን አንነካካ፣ ስንሰራ ግን የሚዘልቅ የሚሻገር የሚወረስ ነገር እንስራ። እንደዚያ ሲሆን በእኛ ዘመን እንኳን አትራፊ ባይሆን ልጆቻችን የአባቶቻቸውን ስም እያነሱ የሚያተርፉበት ስራ ይሆናል። በእርግጠኝነት አቶ ታዲዎስ በአርባ ምንጭ የሰሩት ሪዞርት ለልጆቻችን የሚሸጋገር ጥራት ያለው፣ የአርባ ምንጭን ህዝብ ያከበረ፣ ኢትዮጵያን ያከበረ ስራ መሆኑን ሁላችሁም ስታዩት የምትገነዘቡት ይሆናል። ይህ መልእክቴ ከዚህ ቀደም ለሰሩትም ከአሁን በኋላ ለሚሰሩትም ኢትዮጵያውያን ነው። ስንሰራ ለትውልድ የሚሸጋገር ስራ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የለብ ለብ ስራ፣ የዛሬ ማትረፍ ስራ ብቻ መሆን የለበትም። ለልጆቻችን የሚሸጋገር ጥራት ያለው የአካባቢውን ባህል የአካባቢ ስነ-ልቦና የሚገልጥ ስራ መሆን አለበት። ያ ሲሆን በዘላቂነት የተከበረ፣ በዘላቂነት የሚያተርፍ የተወደደም ስራ መሆን ስለሚችል የግሉ ዘርፍ የአቶ ታዴዎስን ፈለግ ተከተሎ የአርባ ምንጭ ስካይላይትን ፈለግ ተከተሎ መስራት ይጠበቅበታል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።

አርባ ምንጭ ስካይላይት በኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፋ ያለው የአየር መንገዳችን የሆቴል መዳረሻዎች አንዱ ነው። ስራ አስፈፃሚው፣ ምክትል ስራ አስፈፃሚው፣ በርካታ ባለሙያዎች በቅርብ ርቀት ከዋና የፕሮጀክት ሃላፊው ጋር በመሆን ይህንን ድንቅ ስራ ሰርተዋል። ለዚህም ምስጋና ይገባቸዋል። ክቡር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኘ ላለፉት ጥቂት ወራት በዚህ ስፍራ ላደረግከው ቆይታ፣ ትጋት፣ ልፋት ምስጋና ይገባሃል። እውነቱን ለመናገር ግን አርባ ምንጭ ከሚገባት አንድ በመቶ አልሰራችም።

በጣም የሚያሳስበኝ በጣም የሚያስፈራኝ ነገር ሳንሰራ በጣም የምንረካው ነገር ነው። የእርካታ መንፈስ ወደፊት እንዳንዘረጋ ያደርገናል። በቃ ይሄው ነው ልካችን ማለት ትላንት በነበርንበት የድህነት ልክ እንድንቆይ ያደርገናል። ከነበርንበት ከፍ ብለናል አይካድም እውነት ነው። ለዚያ ደስተኞች ነን። መድረስ የሚገባን ቦታ ግን ለመድረስ ገና ብዙ ትጋት፣ ብዙ ስራ፣ ብዙ ልፋት ይጠበቅብናል። በትንሹ የሚረኩ ሰዎች ማደግ አይችሉም። በትንሹ የሚረኩ ሰዎች ለልጆቻቸው የበለጠ የላቀ ነገር ማኖር አይችሉም። እርካታ አደገኛ በሽታ ነው። ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኘ ከሚጠበቅበት አንጂን በመቶ አርባ ምንጭ ላይ አስቀምጦ ቢሆንም ገና አዳዲስ ስራዎች ገና አዳዲስ ልማቶች የሚጠበቅብህ ወጣት ባለሙያ ስለሆንክ አርባ ምንጭ ላይ እንደጀመርክ፣ አርባ ምንጭ ላይ እንደተማርክ፣ አርባ ምንጭ ላይ ኢንጂነር የሚለውን ስም እንደተጎናጸፍክ አስበህ ስራህ ግን ከፊት እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል።

ተመልከቱ ተራራዎቻችንን ገና ስራ ይፈልጋል። ብዙ ከሚጠበቅብን አንድ አስቀምጠን በዚህ ፈሽታ የምንሰክር ከሆነ ማደግ አንችልም። ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፣ ማደግ የምትችል ሀገር ናት፣ ስራ የምትሻ ሀገር ናት። የጀመርነው ለኢትዮጵያም ለአፍሪካውያንም ምሳሌ የሆኑ ስራዎች ናቸው። ምሳሌ ማለት ግን ፍጻሜ ማለት አይደለም። ምሳሌንና ፍጻሜን መለየት ያስፈልጋል። ለሚቀጥለው ስራ ምልክት የሚሆን ነገር አቆየን እንጂ ወደ ፍጻሜ ገና አልተቃረብንም። ይህንን በልቦናችን አኑረን በትጋት በጋራ መቆም እንድንችል አደራ እያልኩ ለአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪዎች፣ ለደቡብ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች አራት መልዕክቶች አሉኝ።

አንደኛው ሌብነት ነው፤ ቱሪስቶች 365 ወይም 364 ቀን ተመላልሰው አድንቀው ተደስተው አክብረው አንድ ቀን ሞባይል ከጠፋባቸው አርባ ምንጭ ሄጄ ሞባይል ጠፋብኝ እንጂ አርባ ምንጭን አየሁ አይሉም። የአንድ ቀን ክፉ ስራ የዓመቱን መልካም ስራ ያጠለሸዋል። አንድ ሞባይል መስረቅ የዚያን ዜጋ የዚያን ግለሰብ ህይወት አይቀይርም። የብዙ ዜጎችን ስም ግን ያጠለሻል። ቱሪስቶች እኛ ከተማ ሲመጡ እንኳን ፈቅደን ወደን አቅደን መስረቅ ቀርቶ ቢወድቅባቸው ቢረሱ እንኳን አንስተን የምንመልስ ታማኞች ብንሆን ተመላልሰው ይመጣሉ። መልካም ስማችን እንደ መልካም መዓዛ በዓለም ሁሉ እንዲዳረስ ያደርጋሉ። በምድርም በሰማይም የከበረ ማንነት ይኖረናል። ሌብነት የምንለማመድ ከሆነ ግን ዜጎች አንዴ ይመጣሉ ደግሞ አይመጡም፣ ከመጡም ገንዘባቸውም ስልካቸውንም ጥላው ግራ ቀኝ እያዩ ራሳቸውን መጠበቅ አስቀድመው ስለሚመጡ ሌብነትና ቱሪዝም አብሮ ስለማይሄድ የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪዎች አደራ ማለት የምፈልገው የአርባ ምንጭ ወጣቶች ቱሪስቶች መጥተው በሌብነት ምክንያት መልካም ስማችን እንዳይጠለሽ ሁላችንም እንደ ፖሊስ ሁላችንም እንደ ጸጥታ አስከባሪ በጋራ ቆመን እንድንሰራ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው ሰላም ነው፤ መቼም አርባ ምንጭና አካባቢው በሰላም የሚታማ ህዝብ አይደለም በጣም ፍቅር የተሞላ ሰላማዊ ህዝብ ነው። አራት ሰዓት፣ አምስት ሰዓት፣ ስድስት ሰዓት ብንቀሳቀስበት የሚያሰጋ ነገር የለም። ይህ መለያችን፣ ሀብታችን የሚቀጥል መሆን አለበት። ሰዎች መጥተው የሚተኙ ሳይሆኑ ተንቀሳቅሰው ገንዘብ የሚያወጡ እንዲሆኑ የሰላም ጉዳይ ከምንም በላይ ጥንቃቄ ይሻል ቱሪስቶች ሰላም ከሌለ ወደዚህ ለመምጣት ስለማይደፍሩ።

ሶስተኛው ፅዳት ነው፤ ባለቤት ያለው ከተማ፣ ዜጎች ያሉበት ሀገር ወይም ባለቤቱ ራሱ የሚኖርበት ቤት አይቆሽሽም፣ ሰው የራሱን ቤት ውሃ ጠጥቶ በየቦታው ላስቲክ

አይወረውርም። ሶፍት ጠርጎ ሳሎን በየቦታው አይጥልም ቤቱ ነው ይጠብቀዋል ማፅዳት የሱ ስራ እንደሆነ ያውቃል። ዜጎቿ የሚኖሩባት ከተማም እንዲሁ ናት ሰው ዝም ብሎ አይጥልባትም የራሱን ከተማ ሰው አያቆሽሽም። መትከል ብቻ ሳይሆን ማፅዳት፣ አለማቆሸሽ፣ ይህን ተፈጥሮ መጠበቅ የአርባ ምንጭ ሰዎች መለያ መሆን አለበት። ኑሮአችን በሚፈለገው ልክ ያማረ ላይሆን ይችላል፣ ሀብታም ላንሆን እንችላለን፣ ዛፍ መትከልና ማፅዳት ግን ምንም አይከለክለንም። ፅዳቱና ዛፉ ብቻውን ያ ያነሰ ነገራችንን በተወሰነ ደረጃ የሚሸሽገው ብቻ ሳይሆን የበለጠ እንዲመጣ የሚጋብዝ ነው።

ሰላም፣ ፅዳት፣ ሌብነትን ማስወገድ፣ ቱሪስትን በበቂ ደረጃ ለማምጣት የሚያግዙን ጉዳዮች ስለሆኑ ሶስቱን የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪዎች፣ የአካባቢ ነዋሪዎች፣ የክልሉ ነዋሪዎችን አደራ የምላቸው ሲሆን፤ አራተኛውና ዋነኛው መልዕክቴ ግን ደቡብ ኢትዮጵያ አርባ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ከአንድ ሶስተኛ በላይ ብሄሮች የሚገኝበት ክልል ነው። ከ30 በላይ ብሄሮች የሚገኝበት ክልል ነው። ለተከበረው ለደቡብ ኢትዮጵያ ህዝብ አደራ እያልኩ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት ኮንሶ ከጋሞ አያንስም፣ ዳሰነች ከወላይታ አያንስም። ሁሉም ህዝብ እኩል ነው። እኔ እበልጣለሁ የሚል ስሜት፣ እኔ እሻላለሁ የሚል ስሜት፣ ካለ እኔ አንደኛ የለም የሚል ስሜት ለዘመናት ደሃ አድርጎ አቆይቶናል። መሻል በተግባር ነው። ጋሞ ሆኖ ጋሞን ከሚሰርቅ ዳሰነች ሆኖ ለጋሞ የሚሰራ ዜጋ ይሻለናል። በስም ብቻ የሰፈር ተወካይ ለመሆን የሚሞከረው ሙከራ አይጠቅመንም።

እኔ የአርባ ምንጭ ከተማ ተወላጅ አይደለሁም፣ ሀብታሙ ተገኘ የአርባ ምንጭ ከተማ ተወላጅ አይደለም፣ መስፍን ጣሰው የአርባ ምንጭ ተወላጅ አይደለም፣ ለማ የአርባ ምንጭ ተወላጅ አይደለም፣ ፎርሲ ቻይናዎች የአርባ ምንጭ ተወላጅ አይደሉም። ወደን ፈቅደን ተባብረን እንዲህ ያለውን ስራ መስራት ከፈለግን እኛ እንደ አንዱ መልካም ጋሞ ልንወሰድ ይገባል። እዚህ ተቀምጦ ደግሞ የአርባ ምንጭ ስብራት፣ የአርባ ምንጭ ድካም፣ የአርባ ምንጭ መጎዳት የማያመውና የማይተጋ ደግሞ ሰው ከሆነ ስሙ ብቻ የእኛ አያደርገውም። አደራ ልላችሁ የምፈልገው ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ እጅግ ሀብታም ክልሎች አንዱ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው። ብዙ ቋንቋ፣ ብዙ ባህል፣ ብዙ አስደናቂ ተፈጥሮ ያለው ክልል ነው። አላስፈላጊ ሽኩቻ ከልማት እንዳያስቀረን የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች አስመሳይና አንደኛ ብሄሮችን አትፈልጉ የሚሰሩ ሰዎችን ብቻ አበረታቱ።

አስመሳዮች አሉ የብሄር አንደኛ፣ የኦሮሞ አንደኛ፣ የአማራ አንደኛ፣ የትግራይ አንደኛ፣ የጋሞ አንደኛ በተግባር ግን ሌቦች የማይሰሩ፣ እንደዚህ ያለውን ክፉ ባህል ማስፋት ለልጆቻችን ድህነት ማኖር ስለሆነ ወላይታና ጋሞ፣ ጋሞና ጎፋ መተባበር ካልቻለ አብሮ

ለልጆቻችን ድህነት ማኖር ስለሆነ ወላይታና ጋሞ፣ ጋሞና ጎፋ መተባበር ካልቻለ አብሮ መቆም ካልቻለ ኢትዮጵያ እንዴት አብራ መቆም ትችላለች? ከማንም በላይ በችግር በመከራ አብሮ የኖረ ህዝብ መተባበርና በአርባ ምንጩ ለውጥ ሶዶ መሳቅ ካልቻለ፤ በሶዶ ለውጥ ጂንካው መሳቅ ካልቻለ ሌላው ሰውማ እንዴት ደስ ሊለው ይችላል? እናንተ ላይ መታየት አለበት ህብረቱ አንድነቱ መከባበሩ መዋደዱ አብሮ መቆም፣ መስራት፣ መልፋት፣ መሞከሩ። ይህንን ነገር በልባችሁ ማኖር አለባችሁ 30ውም ብሄር የተከበረ የተወደደ የሚችል ነው፤ አንዱ ከአንዱ በልጦ አንዱ ከአንዱ ልቆ እኔ አንደኛ ካልሆንኩ ብሎ የሚያስብ ከሆነ ማደግ አይቻልም። ትብብር ካለስ ልቀን ፈጥነን ማደግ እንችላለን።

የስዊድን ዜጎች አንድ ትምህርት ልጆቻቸውን ያስተምራሉ፤ ሲሰሙት ቀላል ግን ሲኖሩት በጣም አስፈላጊ ትምህርት ነው። ልጆቻቸውን አንተ ከማንም አትበልጥም ይሉታል። በትምህርት ስርዓታቸው ውስጥም እኔ ከማንም አልበልጥም እያለ ነው የሚያድገው። ያየውን ሰው ሁሉ በራሱ ልክ እያከበረ፣ ያየውን ሰው ሁሉ ከሱ የተስተካከለ ሰው እንደሆነ እያመነ ነው የሚያድገው። በዚህ ምክንያት ማንንም ሰው ቢያዩ ሰላማውያን ናቸው ራሳቸውን አንደኛ አድርገው ስለማያስቡ የመጣውን ሰው ሁሉ እኩል አስተካክለው የማየት ባህላዊ ልምምድ አላቸው። እዚህ ቦታ ይህንን ስናገር የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪዎች የጋሞ ነዋሪዎች ሰው ለመቀበል ስቆ ለመቀበል ያላችሁን ቀቅሎ ለማብላት ችግር አለባችሁ ማለት አይደለም ከሁሉም በላይ በፍቅር የተሞላ ህዝብ ብለን ከጠቀስን አንዱ የዚህ አካባቢ ህዝብ ነው፤ ፍቅርና ሰላም ያለው ህዝብ ነው።ነገር ግን ፖለቲከኞች ለኩብራ ብለው፣ ፖለቲከኞች ለነሱ ደሞዝ ብለው፣ አንተ ወላይታ ነህ፣ አንተ ጋሞ ነህ፣ አንተ ጎፋ ነህ ሲሉ የሚሰማ ትውልድ ግን መሆን የለባችሁም አጭበርባሪ በሏቸው አይጠቅመንም።

የጋሞ ቋንቋ፣ የጋሞ ባህል፣ የጋሞ ማንነት መከበር አለበት ለድርድር አይቀርብም የወላይታ ቋንቋ ባህሉ ማንነቱ የጎፋም የዳሰነችም ሌሎችም ብሄሮች እንደዚሁ መከበር አለበት። ልክ እንደኛ ባለቤት ያለው የሚወደድ የሚከበር መሆኑን ማመን አለብን። ነገር ግን እኛ አንደኛ ለመሆን እኛ የብሄር ተወካይ ለመሆን ሌላውን ማሳነስ ተገቢ አይደለም። ይህ ጉዳይ ጎድቶናል ይጎዳናል። ይህ እንዳይሆን የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ማንኛውም የሚሰራ ሰው ማንኛውም ባህላችንን የሚያከብር ሰው ከየትኛውም ጫፍ ይምጣ እንደኛ ቤተሰብ የሚወሰድ፤ የእኛ ሆኖ የሚያጭበረብር፤ የእኛ ሆኖ የሚሰርቅ ደግሞ ከሆነ የእኛ እንዳልሆነ የሚያስብ ልምምድ ማጎልበት ያስፈልጋል።

ቅድም እንዳልኩት የጀመርነው ትንሽ ነው የሚጠበቅብን ብዙ ነው። ያ የሚጠበቅብን ብዙ ሀብት፣ ብዙ ዕውቀት፣ ብዙ ጉልበት፣ ብዙ ትጋት ይፈልጋል። ያ ትጋት ምንጩ ደግሞ እነዚህ ብሄሮች ተደምረው እንደ አንድ ዜጋ አስበው የአርባ ምንጭ እድገት የሁላችን እድገት ብሎ ማሰብ ከቻሉ ብቻ ነው። ሲንጋፖር የምትባል ከተማ ሀገር ናት፤ የሲንጋፖር ከተማ ሀብት ከኢትዮጵያ ሀብት ይበልጣል። አርባ ምንጭ በልኳ ብታድግ፤ እንኳን ለደቡብ ኢትዮጵያ ተሻግራ ለኬንያ ለሌሎች ሀገሮች የምትተርፍ መሆን ስለምትችል እዚህ የምናየው ልማት በእጅጉ የሚጠቅመው ሁላችንንም እንደሆነ ማመን ያስፈልጋል። ባለፉት ዓመት ሁለት ዓመት ገደማ ምን ያህል ሰው ስራ እንደያዘ አስቡት፤ ስራው ሲሰራ አሁን በቋሚነት የሚሰሩ ሰዎች መንገድ ሲሰራ መብራት ሲሰራ አጠቃላይ መሠረተ-ልማት ሲቀየር ብዙ ወጣቶች ስራ አግኝተዋል።

ስራ ያልሰራችሁስ አይናችሁ አይቶ የማያውቀውን አዳዲስ ድንቅ ስራዎች ማየት ችላችኋል። በአርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ ትላንት የድሮን ሾው አይተናል። አናቃልለውም ምክንያቱም እንኳን በአርባ ምንጭ፣ እንኳን በኢትዮጵያ በአፍሪካም ብዙ የሚጠበቅ ነገር ስላልነበረ። ይህ ትላንት ያየነውን ሾው ግን አይተን የምናደንቅ ሳንሆን የምንፈጥር፣ የምንሰራ፣ የምናባዛ፣ የምናሳድግ መሆን እንድንችል ትብብር በእጅጉ ያስፈልጋል።

ላለፉት ሁለት ቀናት በአርባ ምንጭና አካባቢው በነበረኝ ቆይታ በገጠር ኮሪደር፣ በጨንቻ አካባቢ የዛሬ ዓመት ተኩል፣ ሁለት ዓመት ስንመጣ መንገድ በጣም ከባድ ነበር ዳገቱ፤ አሁን አስፋልት ተጀምሯል በሚቀጥለው ዓመት የሚያልቅ ይመስለኛል። እዚህ ቦታ ላይ 1190 ገደማ ሜትር ከባህር ጠለል በላይ ነው። 30 ደቂቃ ነድታችሁ ጨንቻ ሳትደርሱ 2300/2400 ይሆናል በእጥፍ ያድጋል እዚህ ይሞቃል እዚያ ይቀዘቅዛል። እዚህ ጋር የምታዩት የጨው ውሃ አይደለም፣ እዚህ ጋር የምታዩት የማይታረስበት ውሃ አይደለም። የጋሞን ተራራዎች እያጠበ መጥቶ የደፈረሰው ውሃ በውስጡ ምግብ ነው ያለው፤ ሀብት ነው። እነዚህን የማየት፣ የማድነቅ፣ የመስራት፣ የመተባበር ልምምዳችን ካደገ ደቡብ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ በረከት፤ ለኢትዮጵያ ፀጋ፤ ለኢትዮጵያ ማረፊያ የሚሆን ቦታ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለኝም። ሁለት ቀን ቆይተናል እውነት ለመናገር ዛሬ የምንሄደው በታላቅ ሀዘን ነው ብንቆይ ብንውል በጣም በጣም ደስ ባለን ነበር። ነገር ግን የእንጀራ ጉዳይ ነውና መሄድ ግድ ሆኖብናል።

ለመላ ኢትዮጵያውያን ሀምሌ፣ ነሃሴ፣ ክረምት ቁር የሚያስቸግር አካባቢ የምትኖሩ ዜጎች አርባ ምንጭ ሁለት እጁ ተከፍቶ በታላቅ ደስታና ሳቅ ልትቀበላችሁ ዝግጁ ስለሆነች አርባ ምንጭ ስትመጡ የሚታየው ተራራ ብቻ አይደለም የሚያምር ሪዞርት ብቻ አይደለም

የሚያስደንቅ ባህላዊ ምግቦች አሉ ስለ ምግብ አትጨነቁ ስንቅ አትያዙ ሙዝ አለን፤ ስኳር ድንች አለን፤ ጎደሬ አለን፤ ፍሩቶች አሉን። ኑ ከእኛ ጋር ደስታን ተጋሩ አርባ ምንጭ ኢትዮጵያውያንን የውጭ ዜጎችን ለመቀበል ዝግጁ ነች በጣም በጣም የሚያምር ቦታ ነው። ግን አደራ የምላችሁ ነገር ስትመጡ ሁለት ቀን ብላችሁ እንዳትመጡ ስትሄዱ ስለሚቆጫችሁ ሰፋ ያለ ጊዜ አስባችሁ ኑና ተዝናኑ። ተጨማሪ ልማቶች ተጨማሪ ሀብቶች ወደዚህ ከተማ እንዲፈሱ ብዙ ሰዎች መምጣት ይኖርባቸዋል ሰዎች እየመጡ ሲያዩ አዳዲስ ሀብት ይመጣል።

ትላንት የገጠመኝን ታሪክ ልንገራችሁ አንድ የውጭ ሀገር ዜጋ ከዚሁ ስራ ጋር በሚያያዝ የመጣ ዜጋ አለ፤ እና ከሱ ጋር ከዚህ ሪዞርት በቅርብ ርቀት የሃር ስራ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን አሉ የጋሞ ሰዎች አሉ። ይሄ የሃር ስራ ኢትዮጵያ ውስጥ እዚህ አርባ ምንጭ መደበቅ የለበትም ተጨማሪ ሀብት ዕውቀት ኢንቨስት ላድርግ ማሽን ላምጣ አብረን እንስራና እዚህም አዲስ አበባም ዱባይም ሱቅ ከፍተን ይህንን የሃር ስራ ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ እናሳድገው አለ።እንግዲ ትላንት ነው ይሄ... መጣ ሃር አየ በሚሊዮን ሚቆጠር ዶላር አፍስሼ አብረን እንደግ አለ። ሌላም ሰው ሲመጣ እንደዚሁ አዳዲስ ሀሳቦች ይመጣሉ ማለት ነው። ብር ያስፈልጋል፣ ዕውቀት ያስፈልጋል፣ ትስስር ያስፈልጋል። ሰው ሲመጣ ሊዝናና ብቻ አይመጣም ወይ አስተምሮን ወይ ገንዘብ አፍስሶ ወይ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ሀሳብ አመንጭቶ ስለሚሄድ የመጣውን ሰው ሁሉ ማክበር የመጣውን ሰው ሁሉ በዚህ መንፈስ ማስተናገድ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

መላው የኢትዮጵያ ዜጎች ኢትዮጵያ እያንሰራራች ነው የብልጽግና ጉዞዋን ጀምራለች፤ ለአፍሪካ ምሳሌ የሚሆኑ ስራዎች ጀምራለች። በዚህ ዓመት በአፍሪካ ውስጥ 10.2 በመቶ የሚያድግ ብቸኛው ሀገር የእናንተዋ ጥንታዊት ድንቅ ኢትዮጵያ ናት እንኳን ደስ ያላችሁ። እንደ ከዚህ ቀደሙ 10 በመቶ አድገናል ብቻ አይደለም፤ ማደጋችንን ለማወቅ አርባ ምንጭ ኑ፣ ማደጋችንን ለማወቅ ሀዋሳ ሂዱ፣ ሶዶ ሂዱ፣ ጂማ ሂዱ፣ ነቀምት ሂዱ፣ ባህር ዳር ሂዱ፣ ሐረር ሂዱ፣ ጅጅጋ ሂዱ፣ ድሬደዋ ሂዱ ይታያል ይዳሰሳል። እድገታችን ከጠራኋቸው ከተሞች አልፎ ያልነካቸው ከተሞች በጣም ብዙ ናቸው ጅማሮ ስለሆነ። እነዚህን አጠንክረን የቀረውን ጨምረን በመስራት የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ማድረግ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል።

በውጭ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ይደንቃችኋል ይገርማችኋል ኢትዮጵያ እያማረባት ነው። ወደ ቤታችሁ መመለስን ማሰብ የምትጀምሩበት ጊዜ ደርሷል። በማንኛውም መመዘኛ እያደገ ያለ ሀገርና እየወደቀ ባለ ሀገር ውስጥ ለመኖር ምርጫ የትኛው ተመራጭ እንደሆነ

አይመከርም። ከሚያድግ ልጅ ጋር መጓዝ ያስፈልጋል፤ የሚያድግ ልጅ ለሀጭ ፊቱ ላይ ሊታይ ይችላል ግን እየዋለ እያደረ ይፀዳል። ያረጀ ሰው ደግሞ የፀዳ ሊመስል ይችላል ግን ምርኩዝ ይፈልጋል። ኢትዮጵያ የምታድግ የምትበለጽግ ልጆቿን የምትሰበስብ የአንድነት፣ የሰላም፣ ምሳሌ የምትሆን ሀገር ናት። ይህ ከድካም፣ ከልፋት፣ ከስራ ውጭ የሚከናወን ነገር አይደለም። ፈተናዎች አሉ፣ ችግሮች አሉ፤ ወደ ኋላ እንድንጎተት የሚፈልጉ ሀይሎች አሉ እውነት ነው። ልማት ሰላም ብልጽግና የምናስብ ሰዎች እያሸነፍን ጉዟችን ወደፊት ይሆናል። ክፉ አሳቢ፣ ክፉ አላሚ መጨረሻው ሽንፈት፣ መጨረሻው ገሃነም ነው።

መልካም የምናስብና የምንሰራ ሰዎች በምድርም በሰማይም ቤታችን የለመለመ ነው። እኛ በኢትዮጵያ ስንኖር እናበለጽጋለን፤ ስንሄድም የሚጠብቀንን እናውቃለን።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አርባ ምንጭ



ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የአውሮፕላን ማረፊያ ምረቃ ሥነ-ስርዓት

—ሐምሌ 5 ፣2018ዓ.ም

ክቡር የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣
ክቡር የክልላችን ርዕሰ መስተዳደር አቶ አረጋ ከበደ፣
እንዲሁም የትልቁ አየር መንገዳችን ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው፣
የተከበራችሁ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎች፣ ለዚህ ታላቅ ቀን ለሳቅ፣ ለደስታ ስላበቃችሁ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። መንቆረር ብርዳማ እንደሆነች የሚነገር ቢሆንም፣ ዛሬ የዘመናት ጥያቄዋ ሲመለስላት ሰዉ ብቻ ሳይሆን ምድሩም በፀሐይ ስቆ ይታያል፤ ደስታው ከላይም ከታችም ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን።

ይህ አካባቢ ከረጅም ጊዜ በፊት መንቆረር ተብሎ ይታወቅ ነበር፤ በተለይም ደጃዝማች ጎሹ ጥቂት መንደር በነበረችበት ዘመን የመንቆረር አስተዳዳሪ እንደነበሩ በኋላም ወደ ከተማ ስታድግ ደጃች ተድላ ከፍ አድርገው በዚሁ መንቆረር ስም ሲያስተዳድሯት እንደነበረ ይነገራል። ኋላ ላይ የቀድሞ ራስ አዳል በኋላ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ደብረ ማርቆስ ብለው ይህንን ከተማ ስሙንና ግብሩን እሳቸውም ከሳቸው በኋላም ልጃቸው ከፍ አድርገው የጎጃም ክፍለ ሀገር መናገሻ፣ የወሎና የወለጋ ድልድይ ሆና ለረዥም ዘመናት ስመጥር ታዋቂ ከባቢ ሆና መቆየቷ ይታወቃል። በተለይም የጎጃም ክፍለ ሀገር መገኛ በነበረችበት ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ቀድመው ስልክ፣ ቴሌፎን፣ ቴሌግራፍ ከገባላቸው ከተሞች መካከል ደብረ ማርቆስ ግንባር ቀደም ነበረች።

በ1950 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩ ዘጠኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኘው እዚህ ደብረ ማርቆስ ነበር። በኢትዮጵያ ደረጃ ዘጠኝ ነበሩ፤ ከነሱም አንዱ እዚህ ይገኝ ነበር። በዚህ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማረው፣ ከፍተኛ ውጤት አምጥቶ ወደ አዲስ አበባ የመጣው፣ ዛሬ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሆነው አቶ መስፈን የተገኘው ከዚሁ ከተማ ነው። ለረጅም ዘመናት የኢትዮጵያን አየር መንገድ እንዲያገለግል መነሻው የሆነው ልጅ ሳለ ስትነሳ ስታርፍ የሚያያት ዳሽ ሲክስ በውስጡ ባኖረችው ምኞት መጨረሻ የዚያ መስሪያ ቤት አገልጋይ አሁን ደግሞ እንደምታዩት ዋና ስራ አስፈጻሚና ተወልዶ ባደገበት ከተማ የህዝቡን የዘመናት ጥያቄ ለመመለስ ስላበቃው አቶ መስፈን እንኳን ደስ ያለህ ለማለት እፈልጋለሁ።

እውነት ለመናገር አቶ መስፈን ብቻ ሳይሆን ክቡር ተመስገን ጥሩነህ የምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳሪ ሆነው ሲያገለግሉ ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ የዚህን የአየር መንገድ ጉዳይ በተለየ አንክሮ ያነሱ ነበር። ለረጅም ጊዜም እዚህ ቦታ ላይ ሲመላለሱ ከሚሰማቸው ከሚያሳዝናቸው አንደኛው የደብረ ማርቆስ አየር መንገድ ምላሽ ማጣቱ እንደሆነ በተደጋጋሚ ለኔም፣ ለጓደኞቻቸውም ያነሱ ነበር። እሳቸውም እዚህ አስተዳድረው፣ አማራን አስተዳድረው፣ አሁን የኢትዮጵያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ በሀገር ደረጃ ስራ ለመምራት ስላበቃቸው እንኳን ደስ ያላቸው ለማለት እፈልጋለሁ።

ዛሬ በመካከላችን ባይገኙም የቀድሞ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በተደጋጋሚ የዚህ አየር መንገድ ስራን በተመለከተ ሲያነሱልኝ ስለነበር እሳቸውም ምስጋና ይገባቸዋል። እንደምታውቁት መደመር ወደኋላ መለስ ሲል መልካም መልካሙን የሚያወሳ የሚያስታውስ ስለሆነ አቶ ደመቀ መኮንን ዘንግቶ አቶ ተመስገንን ቢያመሰግን ግማሽ ስለሚሆን ሙሉ እንዲሆን ሁሉንም በቅጡ፣ በወጉ፣ በስርዓቱ ማስታወስ ጠቃሚ ነገር ነው። በነዚህ ሁለቱ አመራሮች ብቻ ሳያበቃ የክልላችን ርዕሰ መስተዳድርም እንደምታውቁት የዚሁ አካባቢ ሰው ናቸውና ከዚህ የተነሱ ሰዎች ሀገር እየመሩ፣ ትላልቅ ተቋም እየገነቡ የህዝባቸውን የዘውትር ጥያቄ ለመመለስ ላለፉት ዓመታት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተው ዛሬ ከህዝባቸው ጋር፣ ከምድሪቱ ጋር መሳቅ ስለቻሉ ሁሉንም እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ደብረ ማርቆስ በ1951 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩ ሻል ሻል ካሉ 20 ከተሞች ተወዳድራ አንደኛ ወጥታ ነበር፤ የዛሬ ሰባ ዓመት ገደማ ማለት ነው፤ ትንሽ ያንሳል። ዛሬ ደብረ ማርቆስ ከ20 ከተሞች ጋር ተወዳድራ ያንን የቀድሞ ክብሯን ለማግኘት የሚያስችል ቁመና ላይ ነች ወይ የሚለውን ጥያቄ ማንም ደብረ ማርቆስን የሚያውቅ፣ የሚወድ፣ የሚቆረቆር ዜጋ ጥያቄ መሆን አለበት። ቀደም ሲል በነበሩ ግጥሞች «አትመጣም ወይ ማርቆስ ከተድላው ከተማ፣ ቢሻህ በአውሮፕላን ቢሻህ በሎንቺና» የተባለላት ከተማ ናት። አሁን ሎንቺናውም አውሮፕላኑም ላለፉት ጥቂት ዓመታት ችግር ሆኖ ነበር፤ ዛሬ ቢሻህ በአውሮፕላን ተመልሷል፣ ቢሻህ በሎንቺና ግን በኛ ጥረት መመለስ ይኖርበታል። ይሄንን የመሰለ ምድር ይዘን፣ መቼም እንዴት የሚያምር ሃገር እንደሆነ በውስጡ ያላችሁ ሰዎች ላይታወቃችሁ ይችላል።

እንደዚህ ያለውን ለምለም ሃገር ይዘን ተግባብተን፣ ተዋደን አገራችንን መስራት ሲገባን፣ ባንግባባ እንኳን ተወያይተን፣ ተከራክረን፣ ተነጋግረን ሳንጋደል አብረን መኖር ሲገባን፣

ክፉ ክፉውን የምንስብ መልካም መልካሙን የምንገፋ መሆን የለብንም። በዚህ ዘመን እውነት መስፈርያዋ በእጅጉ ስለቀጠነ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የዘር፣ የመከፋፈል፣ የጎጠኝነት፣ የጽንፈኝነት እሳቤ እየተንሰራፋ እንዲመጣ አንዱ የእውነት መቅጠን ምክንያት ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። ያ ባይሆን ኖሮ ትናንት ወሎንና ወለጋን አስተሳስሮ ድልድይ የነበረው ደብረ ማርቆስ፣ ካለምንም ጥርጥር ታሪክ እንደሚያወሳው እናንተም እንደምታውቁት ብዙ የደም መቀላቀል ያለበት የዚህ አካባቢ ሰው ለሌላው አርአያ እና አስተማሪ፣ ለሌላው መሰብሰብና አንድ መሆን ምልክት መሆን ነበረበት።

ከዚህ ከባቢ በላይ ከአፄ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ ከትግራዩም፣ ከኦሮሞውም፣ ከሌላውም ብሄር ተዋልዶ፣ ተዋህዶ የኖረ ህዝብ ያለ አይመስለኝም። የጅያግራፊ ቅርበት የራሱን አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም፣ ደብረ ማርቆስ በወሎ እና በወለጋ መካከል ድልድይ ሆና ንግድን፣ ሰውን ስታስተሳስር፣ እድገት ስታሳልጥ መኖሯ የማይታበል ሀቅ ነው። ይህንን ሀቅ ማስቀጠል አቅቶን በአባይ ሸለቆ አካባቢ አሊዶሮ አካባቢ የሸፈተውን እና ወደ አዲስ አበባ አላሻግርም ያለውን ሸፍታ በጋራ ታግለን ማስወገድ ሲገባን፣ ከዚህ ደጀን መሄድ እንዳንችል ተጨማሪ ሸፍቶች ማበራከታችን ተገቢ ጉዳይ አይመስለኝም። የትም ቦታ ያለውን ሸፍታ ተሰናስለን፣ ተደማምረን በማስወገድ የህዝባችንን ሰላምና ልማት ማረጋገጥ ሲኖርብን፣ ጭራሽ ወደ ቄያችን፣ ወደ ሰፈራችን ሸፍቶች እየተበራከቱ፣ ሰዎች በነጻነት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ስራ መስራት ወደማይችሉበት ደረጃ መድረሳችን ለሁላችንም አጠያያቂ፣ ጥዩፍ፣ የማይገባ፣ ልንማርበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል።

የተከበራችሁ የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎች የሃገር ሽማግሌዎች፤ ዛሬ የምታውቁትን አንድ እውነት ልንግራችሁ እፈልጋለሁ፤ አማራ እና ኦሮሞ እያለ የሚከፋፈል ማንኛውም ሰው ጎጃም እና ጎንደር ብሎ መከፋፈሉ አይቀርም። ምስራቅ ጎጃም እና ምዕራብ ጎጃም መባባሉ አይቀርም። የእኛ ቀዬ፣ የእነሱ ቀዬ መባባሉ አይቀርም። በመጨረሻም በእናት እንጂ በአባት አንድ አይደለም መባባሉ አይቀርም። ቤቱም ሲገባ የእናቱን ልጅ የአባቴ አይደለም ብሎ ከመከፋፈል አይቦዝንም። አንዴ እየወረደ፣ አንዴ እየተከፋፈለ የሄደ ማኅበረሰብ ማቆሚያ የለውም። ከላይ ሲጀምር ይመስላል፤ እየገባ ሲሄድ ግን ቤተሰብ የአንድ እናት ልጅ የሚከፍል በጣም ክፉ ልምምድ እና ባህሪ ነው። የሚሻለው፣ የሚበጀው የሚያለያየንን ነገር እየተወያዩ፣ ጥቃቅን ነገር እየረሱ በትልቁ ጉዳይ መሰብሰብ፣ መተባበር፣ ቢያንስ የሁላችንም የጋራ መሻት የሆነውን ሰላምና ልማት በጋራ ለማስፈጸም መጣርና መሞከር ይበልጥ ይበጃል። ከዚያ ውጪ ያለው አማራጭ ሀገራችንንና ህዝባችንን ከመጎዳት ባሻገር አንዳች ጥቅም ሊያስገኝ አይችልም።

ዛሬ ይህ አየር መንገድ ተመርቆ እንደተባለውም በቀን ሶስት ጊዜ ሰዎች የሚመላለሱበት በረራ መጀመሩ መልካም ነገር ነው። ነገር ግን ያንን መክፈል የማይችሉ ወይም የማይፈልጉ በትራንስፖርት ከዚህ ወደ ባህር ዳር ወይም ከዚህ ወደ አዲስ አበባ መሄድ ቢፈልጉ ያንን ጉዳይ ማድረግ እንዲቻላቸው፣ ሰዎች የነሱን ፕሮግራም፣ የነሱን መሻት እንዳያስተጓጉሉ ሰላም በእጅጉ አስፈላጊ ስለሆነ፣ መንግሥታችን ከህዝቡ ጋር በመተባበር ሊወያዩ፣ ሊነጋገሩ ለፈለጉ ማንኛውም ሰዎች በር ክፍት ነው፣ እጃችን የተዘረጋ ነው፣ ልባችን ክፍት ነው። እንቀራረብ፣ እንወያይ፣ እንነጋገር፣ ሀገራችንን ሰላም እናድርግ። የማያግባቡን ጉዳዮች ካሉ በሰላማዊ፣ በሰለጠነ የፖለቲካ አግባብ መነጋገር ይቻላል።

ከዛ ውጪ ያለው አማራጭ ኢትዮጵያን አይጠቅምም፣ አማራን አይጠቅምም፣ ጎጃምን አይጠቅምም፣ ምስራቅ ጎጃምን አይጠቅምም። ይህ ህዝብ በአፄ ዮሐንስ ጊዜ በነበረ ሁኔታ ምን እንደደረሰበት ያውቃል፤ በጣልያን ጊዜ ምን እንደደረሰበት ያውቃል። ትግል፣ ፍልሚያ፣ ውጊያ ለናንተ አዲስ ጉዳይ አይደለም፣ አባቶቻችሁ አልፈውበታል፤ በየዘመናቱ ግን ኪሳራ፣ ሞት፣ ድቀት እንጂ ጥቅም አልተገኘበትም። አሁን ሊበቃን ይገባል፣ ያንን በጋራ መወሰን አለብን። የምናየውን ትተን የምንሰማውን ብቻ እየወሰድን፣ የሚታየውን እየካድን የማይጨበጠውንና የሰማነውን ብቻ እየተቀበልን ብንለያይ ኪሳራው የበዛ ስለሚሆን፣ ወገኖቻችን በተከባበረ፣ በተደመረ መንፈስ ለልማት እንድንነሳ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ልማት በባህሪው ጊዜ ይፈልጋል። ይህንን የአውሮፕላን ማረፊያ ወሰንን ማለት በማግስቱ ሰራን ማለት አይደለም፤ ወስነን እስከምናሳካው ጊዜ የሚጠይቀው የራሱ የሆነ ሀብት፣ የራሱ የሆነ ጊዜ አለ።በሃገራችን «ሳይረግጡት አይሰበር፣ ሳይታገሱት አይበገር» ይባላል። አንድ ጫጩት ከእንቁላል ውስጥ ጫጩት ሆና እንድትወጣ ሙቀት ያስፈልጋታል፣ ጥበቃ ያስፈልጋታል፣ ጊዜ ያስፈልጋታል። ስለፈለግን ብቻ አሁኑኑ እንቁላሉን ብንሰብረው፣ በቂ ሙቀት ካላገኘች፣ ጊዜ ካላገኘች ጫጩት አይገኝም።እንደዚሁ ልማት ትብብር ይፈልጋል፣ ጥበቃ ይፈልጋል፣ ጊዜ ይፈልጋል፤ ተሳክቶ ሲታይ ፍሬው ግን እንደዚህ ለምድርም ለሰማይም ሳቅ ይሆናል። ጊዜ ለሚመልሰው ጉዳይ፣ ትዕግስት ለሚመልሰው ጉዳይ፣ ትብብር ለሚመልሰው ጉዳይ መለያየት፣ መገዳደል፣ አጓጉል ልምምድ ባህላችን እንዳይሆን ኢትዮጵያ ጥንታዊት፣ ታሪክ ጠገብ፣ ሰላምንም ጦርነቱንም የምታውቅ ሀገር ነች። የጎደላት ልማት ነው፣ የጎደላት ብልጽግና ነው፣ የጎደላት መደማመጥ፣ መከባበር፣ በታሪክ ላይ ቆሞ መልካም መልካሙን ወስዶ የቀረውን እየሞሉ ለልጆቻችን የተሻለ ሀገር ማስረከቡ ነው ችግር የነበረው ያንን ወቅታዊ ችግር ለመፍታት በጋራ እንድንቆም በታላቅ ትህትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ዛሬ ደብረ ማርቆስ ተገኝቼ ትክክለኛ ስሜቴን ለናንተ መግለጥ ባልችል፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት መጥቼ እንደተከልኩት ዛፍ ሳልተከል ብሄድ አጠቃላይ ምርቃቱ ሙሉ ስለማይሆን በጋራ ዛፍ በመትከል ዐሻራን በመተው አንድነት እንዲበቅል፣ እንዲያብብ፣ እንዲያድግ በማድረግ የነገይቱ ኢትዮጵያ ለልጆቻችን የተመቸች እንድትሆን በጋራ እንድንተጋ፣ እንድንሰራ፣ ከመስራት፣ ከመልፋት፣ ከመድከም ውጪ ውጤት እንደማይገኝ እንድናምን አደራ እያልኩ፤

ዛሬ በሆነላችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ለማለት እወዳለሁ!
ደብረ ማርቆስ ከተማ



ሀገራዊ ምክክር የማስጀመሪያ ሥነ-ስርዓት

—ሐምሌ 8 ፣2018ዓ.ም

እንዴት ከረማችሁ? እንዴት አደራችሁ?
ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ታሪካዊ ቀን በዚህ መልክ ለመሰባሰብ ያበቃንን ፈጣሪያችንን ለማመስገን እወዳለሁ።
ክቡር ቺፍ አሊሴንጎን አባሳንጆ የቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ፣ የአፍሪካ የሰላም አባት በመካከላችን ስለሚገኙ ጥሪያችንን አክብረው ስለተገኙልን ከፍ ያለ ምስጋና እንዳቀርብ ቢፈቀድልኝ።

የቀድሞ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክቡር ዶክተር ሙላቱ ተሾመ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ክቡር ታገሰ ጫፎ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ክቡር አገኘሁ ተሻገር፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣ ክቡር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቴዎድሮስ ምህረት፣ የፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ፣ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ ከሁሉ በላይ የዚህ መሰባሰብ ዋነኛ ባለቤት የሆኑት ኮሚሽነሮች፣ በተለይም ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ዋና ኮሚሽነር፣ ይህንን ታላቅ ኃላፊነት፣ ይህንን ብዙ ድምፆች ያሉበት አድካሚ ሥራ በነጻ፣ በርካቶቹ በማምሻ ዕድሜያቸው ሃገራቸውን በቅንነት በማገልገል ለልጆቻቸው መሠረት ለመጣል የወሰኑ አሥራ አንዱም ኮሚሽነሮች፣ በተለይም አባታችን ዘገዬ አስፋው በዚህ ሂደት ውስጥ ለነበራቸው ሚና ያለኝን ታላቅ አክብሮት በዚሁ መግለጽ እወዳለሁ።

የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፣ ሃደ ሲንቄዎች፣ ከምሥራቅ ከምዕራብ፣ ከደቡብ ከሰሜን የኢትዮጵያን ሕዝብ ወክላችሁ በዚህ ሥፍራ የተገኛችሁ የምትወያዩ አካላት፣ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በመወከል የተሰየማችሁ የዳያስፖራ አባላት፣ ከዚህ አዳራሽ ውጪ በመላው አገሪቱ የምትከታተሉ የኢትዮጵያ ዜጎች በሙሉ፤ ይህ ጉባዔ በቀላሉ የማይደገም፣ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ በስፋቱ፣ ባካሄዱ፣ በወሰደው ጊዜና ምናልባትም በሚያስገኘው ውጤት በእጅጉ የገዘፈ ዓላማ ያለው፣ የገዘፈ ተግባር የሚፈጽም፣ ለአፍሪካ በብዙ ምሳሌ የሚሆን የውይይት፣ የምክክር፣ የንግግር ሁሉን አቀፍ መድረክ ነውና በዚህ መድረክ ላይ ተገኝቼ የኢትዮጵያን መንግሥት አቋምና መልእክት እንዳስተላልፍ ዕድል ስለሰጣችሁኝ የከበረ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ።

ክቡራትና ክቡራን፤ አንዳንድ አጋጣሚዎች ከታሪክ ብዕርና ብራና ፊት ያቆሟችኋል።

ከታሪክ ብዕርና ብራና ፊት መቆም ብቻ ሳይሆን ያሻችሁን፣ የፈቃዳችሁን መጻፍ እንድትችሉ ብዕርና ብራና ያቀብሏችኋል። ይህ ዛሬ የምንገኝበት መድረክ ልባም ለሆኑ ሰዎች የታሪክን፣ የአጋጣሚን፣ የዕድልን ጠቃሚነት ማዝለቅ ለፈለጉ ሰዎች በዚያ ብዕር፣ በዚያ ብራና ላይ ሀገርን የሚታደግ፣ የሚጠቅም፣ የሚገነባ፣ ለዘመናት የሚታወስ ታሪክ ለመጻፍ ዕድል የሚሰጥ ነው። ይህንን የማይጠቀሙ፣ ይህንን የማይጠቀሙ ዕድል ደጋግሞ እንደማይገኝም የማይገነዘቡ፣ ታሪክ ብራናና ብዕር ቢያቀብላቸውም ሀገር ከሚጠቅም ይልቅ የሚጎዳ፣ ከሚገነባ ይልቅ የሚያፈርስ፣ ከሚያበለጽግ ይልቅ የሚያደኸይ፣ ከሚያሰፋ ይልቅ የሚያጠብ ታሪክ ጽፈው ያልፋሉ።

ያ ታሪክ ዛሬ በእኛ እንዳይደገም ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ተሰምቶን፣ በታላቅ አክብሮት ልንከውነው የሚገባ፣ እኛና ከእኛ በፊት የነበሩ ሰዎች ያጧቸውን ሊያሳኳቸው ሲገባ ያልቻሏቸውን ጉዳዮች ዳግም ልጆቻችን እንዳያጡ፣ በታላቅ ኃላፊነት እንድትሠሩ ደግሜ በትህትና ልጠይቃችሁ እወዳለሁ።

ዊልያም ሼክስፒር ከሠራቸው በርካታ ሥራዎች መካከል በአንዱ “በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ማዕበል አለ፤ ያንን ማዕበል ትክክለኛውን ጊዜ አውቆ የሚጠቀምበት ግለሰብ፣ የሚጠቀምበት ቡድን ካለ፣ ከጎርፉ ዳግም ወደማይገኝ ዕድል ሊያወጣው ይችላል” ይላል። መከራ ሁሉ መከራ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ዕድል አለው ማለት ነው፤ ችግር ሁሉ ችግር ብቻ ሳይሆን በውስጡ መፍትሔ አለው ማለት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በርከት ያሉ ችግሮች አሳልፈናል፤ በርከት ያሉ ያልተገቡ መከራዎች አሳልፈናል። ነገር ግን ይህንን መከራ ወደ ዕድል መቀየር ከቻልን፣ ይህንን ፈተና ወደ ዘላቂ መፍትሔ ማሻገር ከቻልን ልጆቻችን ከእኛ በተሻለ ሰላም፣ ከእኛ በተሻለ ብልጽግና፣ ከእኛ በተሻለ የኑሮ ዘይቤ መኖር ስለሚያስችላቸው ያንን የሚገባቸውን፣ ያማረ፣ የተዋበ የኑሮ ዘይቤ መከተል የሚችሉ ትውልዶች መፍጠር እንድንችል ይህንን መልካም አጋጣሚ፣ ይህንን የመከራ ወራትና ዘመን ወደ ዕድል መቀየር የምንችል፣ የምትችሉ እንድትሆኑ፣ እንድንሆን ምኞቴ ከፍ ያለ ነው። የወታደራዊ ጥበብ አዋቂው ሰን ዙ “ዕድሎች የሚበዙለት፣ ዕድሎች የሚበራከቱት በሚጠቀምባቸው ሰው ልክ ነው” ይላል። አንዳንድ ዕድል ይገኝና መጠቀም የሚሳነን ከሆነ ዳግም ያንን ዕድል ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል። ዕድል ሲገኝ በቅጡ፣ ዕድል ሲገኝ በኃላፊነት ስሜት፣ ዕድል ሲገኝ በመስጠት የምንጠቀምበት ከሆነ ዕድል ደጋግሞ፣ ደጋግሞ ወደ እኛ ይመጣል። ለምሳሌ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተገኘውን ዕድል፣ የተገኘችውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም የኢትዮጵያን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የወታደራዊ ሪፎርም ለማካሄድ፣ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ፣ ኢትዮጵያን በታሪክ ልክ

ለማቆም ባደረግነው ጥረት ውስጥ ዕድለኞች ነበርንና ዕድል መጠቀም እንችላለንና ቢያንስ በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ በነበራችሁ ቆይታ እንዳያችሁት ያን የቆሸሸ ከተማ አዲስ መልክ እንዲይዝ ማድረግ ችለናል።

ዛሬም የምናነኛትን እያንዳንዷን ደቂቃ፣ እያንዳንዷን ሰዓት፣ እያንዳንዷን ቀን እንደ ታላቅ ዕድልና ስጦታ በማመን፣ በመጠቀም የኢትዮጵያን ብልጽግና መሠረት ለመጣል ደከመን ሰለቸን ሳንል የምንተጋ መሆናችንን በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ይህ ምክክር ለምን አስፈለገ? ይህ ምክክር ከተለመደው ጥቂት ሰዎች ተሰብስበው ተመካክረው ከሚወስኑት አቅጣጫ በተለየ መንገድ በሙቶ ሺዎች በሁሉም አቅጣጫ ሴቶችና ወንዶች የኢትዮጵያ ልጆች በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ያሉ ዜጎች መክረው አራት ዓመት ሙሉ የፈጀ አድካሚ ጉዞ ለምን ማድረግ አስፈለገ? ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ እጅግ ታሪክ ጠገብ ጥንታዊት ሀገር ናት። በንግግሮች፣ በጽሑፎች፣ በሚታዩ በሚጨበጡ ቅርሶች፣ ከዚያም ባሻገር የሰው ልጅ መገኛ በመሆኗ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ባሉ ማረጋገጫዎች ሁሉ ጥንታዊነቷ አለ የማይባል የማይከራከር እውነት ነው።

ነገር ግን በዚህ ታሪካችን ውስጥ አንድ ስብራት አለ፣ አንድ ስንክሳር አለ፣ አንድ ውድቀት አለ፤ ያም በኃይል ቃል ጀምሮ በኃይል እርምጃ መደምደም ነው። ፖለቲካችን በኃይለ ቃል ይጀመራል፤ በኃይል እርምጃ ይደመደማል። ይህንን ስብራት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማቆም ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ከይፋት እስከ ግቤ፣ ከወላይታ እስከ ከፋ፣ ከወሎ እስከ ሸዋ፣ ከላስታ እስከ ትግራይ፣ ከአፋር እስከ ሶማሌ የኢትዮጵያን ሱልጣኔቶች፣ የኢትዮጵያን ሥርወ መንግሥት ብንፈትሽ በሁሉም ጊዜ የምናየው ስብራት በኃይለ ቃል ጀምሮ በኃይል መደምደም ነው። የኃይል እርምጃን የታሪካችን አካል ማድረግ ነው፤ ያንን ስብራት መቀየር ያስፈልጋል።

በእርግጥ በውስጣችን ያሉ ችግሮች እኛው ጀምረን እኛው የምንጨርሳቸው ብቻ አይደሉም። የጠንባሮ አባቶች አንድ አባባል አላቸው፡- “ከብት ሲገዛ የሌሉ አሞራዎች ከብት ሲታረድ በአካባቢው ያንጣብባሉ” ይላሉ። ከብት ስንገዛ ብር ያላዋጡ፣ ከብት ስንገዛ የትኛውን መግዛት እንዳለብን ለምርጫ ያላማከሩ አሞራዎች፣ ጭልፊቶች ከብቱ ሲታረድ ግን ያንጣብባሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ኮሽ ሲል ያደፈጡ፣ የሚነቁ፣ የዘመናት ያልተቋረጠ የጠላትነት ስሜት ያላቸው አገራት አሉ። የኢትዮጵያን ታሪክ ከጉንደት እስከ ጉራዕ፣ ከዐድዋ እስከ ማይጨው፣ ከካራማራ እስከ ባድመ እያንዳንዱን ብትፈትሹት ስንነነባ ያደፈጡ፣ ስንጨቃጨቅ ዕድል ጊዜ ጠብቀው ጣልቃ ሽብልቅ እየገቡ፣ መሻቶቻችን እንዳንከውን የሚያደርጉ ኃይሎች አሉ።

በዚህ የሽብልቅ ጉዞ በእኛ ስንፍና በእነሱ ጊዜን በመጠቀም የሽብልቅ ጉዞ የጥንቱን ታሪክ ብንተው በቅርቡ ቀይ ባሕርን ያጣንበት አጋጣሚ የዚህ እኩይ ታሪካዊ ክስተት አንዱ መገለጫ ነው። ኢትዮጵያ ለሺህ ዘመናት ያስተዳደረችውን፣ በባለቤትነት የያዘችውን፣ ለራሷም ለአካባቢውም መጠቀሚያ ያኖረችውን ቀይ ባሕር ያልተመረጠ መንግሥት፣ ያልተወያየ መንግሥት በሸፍጥ ኢትዮጵያን የጂኦግራፊ እስረኛ እንዲያደርግ ያደረገበት ዋናው ምክንያት በውስጥ ያለን ስንፍና እንጂ የኢትዮጵያን መሻትና ጥቅም ማስቆም የሚችል ኃይል ስለነበረ፣ ስላለ፣ ስለሚኖር አይደለም።

ሁልጊዜም ጥቅማችንን አሳልፈን የምንሰጠው ስንገነባ ያልነበሩ፣ ስንሻኮት ስንጣላ የሚያንጥብቡ አሞራዎች ስላሉ ነው። አሞራ ሲታረድ ይመጣል፤ ሲገነባ የለም። ህዳሴን ስንገነባ እኛ ጋር አልነበሩም፤ ከተሞቻችን ሲያሸበርቁ እኛ ጋር አልነበሩም፤ ልማት ስንጀምር እኛ ጋር አልነበሩም፤ እርስ በእርስ ስንጨቃጨቅ ግን ከየት መጡ ሳይባሉ ጥይት ሲያቀብሉ፣ ብር ሲያቀብሉ፣ በሚዲያ ፕሮፓጋንዳ ሲያደርጉ ይታያል። እጅግ የተከበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነገር ልብ እንዲል እፈልጋለሁ፤ ምንም ጉዳይ በውስጥ ቢያከራክረን፣ ምንም ጉዳይ በውስጥ ቢያጨቃጭቀን እንዲህ ባለው መድረክ መነጋገር፣ መወያየት፣ መፍታት ስለምንችል ለሌሎች ኃይሎች ጥቅም የኢትዮጵያን መሻት፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ፍላጎት አሳልፈን የምንሰጥ በታሪክ ውስጥ እንክርዳድ ሆነን የምንታይ ዜጎች ላለመሆን እያንዳንዳችን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ለሚያንጥብቡ አሞራዎች ያለኝ መልእክት፦ ከብቱን መርጠን የምንገዛ እኛ ነን፣ የቅርጫውን ባለቤት የምንወስን እኛ ነን፣ የተረፈንን የማንፈልገውን ካልሆነ በስተቀር የትኛውም አሞራ በጉልበት ከየትኛውም ቅርጫ መደብ ላይ አንዲት ኪሎ ሥጋ መውሰድ እንደማይችል ላረጋግጥላቸው እፈልጋለሁ። ስንፈልግ፣ ስንወድ ለማጋራት ዝግጁ ነን፤ ከፈቃዳችን ውጭ ግን ለሺህ ዓመታት የኖረች፣ የጸናች ኢትዮጵያ በቀላሉ በማይበጠስ ክር፣ በማይበጠስ ገመድ የተሳሰረች ኢትዮጵያ አሁን ባለው ፕሮፓጋንዳ ትዘነጋለች፣ ጥቅሟን አሳልፋ ትሰጣለች ብሎ መገመት ከንቱ ምኞት ስለሆነ ከወዲሁ የእኛን ታሪክ በትክክለኛው መንገድ አገላብጣችሁና አውቃችሁ ቀልባችሁን በመመለስ ለጋራ ጥቅም በጋራ እንድንሠራ ጥሪዬን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ታዲያ ኢትዮጵያ እንዴት ጸናች? የጽናታችን ሚስጥር ምንድን ነው? ያላችሁ እንደሆነ ሽምግልና፣ ንግግር፣ ይቅርታ፣ ካሳ የሚባሉ ሳይንስ በቀላሉ መርምሮ፣ ፈትሾ ሊመልሳቸው የማይችሉ ድልብ ሀብት በእኛ ሕዝብ ልምምድ ውስጥ ነበረ። ይጋጫል፤ ግን ይነጋገርና በይቅርታ፣ በካሳ ይፈታል። ይህ የንግግርና የይቅርታ

ባህላችን ኢትዮጵያን አጽንቷል። ይህ ውይይት፣ ይህ ምክክር፣ ይህ ንግግር በዚያ ባህላችን ላይ የሚንተራስ ከሆነ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥሉት በርካታ አሥርት ዓመታት የሚዘልቅ፣ የሚያቆይ መሠረት መጣል ይችላል። ከባህላችን፣ ከማንነታችን፣ ከታሪካችን ሳንነቀል ፈቅደን፣ ወደን፣ በደስታ፣ በፍቅር ስሜት፣ በኃላፊነት ስሜት ይህንን ውይይት የምናካሂድ ከሆነ ካለምንም ጥርጥር ልጆቻችን የበለጸገች፣ የጸናች ኢትዮጵያን መረከብ የሚችሉ ይሆናል።

ይህ ባህላችን በቀጥታ ከዋርካ ዛፍ ጋር የተሳሰረ ነው። ኢትዮጵያና ዋርካ ከፍተኛ ቁርኝት አላቸው። በዋርካ ሥር ሽምግልና እንቀመጣለን፤ በዋርካ ሥር ለትዳር ሽምግልና እንጠይቃለን፤ በዋርካ ሥር የሃይማኖት ትምህርቶች እንማራለን፤ በዋርካ ሥር አባቶች ዘር ያስቆጥሩናል፤ በዋርካ ሥር እንማማራለን፤ በዋርካ ሥር እናርፋለን።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ዋርካን የመቁረጥ ባህል ሲሰፋ ምክክሩ እየቀነሰ፣ ንግግሩ እየቀነሰ “አንተ ትብስ አንቺ ትብሺ” የሚለው ባህላችን “ከእኔ ወዲያ ማ፣ እኔ ብቻ፣ እኔ ካላልኩ፣ እኔ የምፈልገው ካልሆነ” የሚል አደገኛ ልምምድ ተቀየረ። ለዚህ ነው እንትከል፣ ተስፋን እንትከል፣ ዋርካን እንትከል፣ ምክክርን እንትከል፣ ውይይትን እንትከል፣ ይቅርታን እንትከል፣ በጋራ መቆምን እናጽና፤ በዚያ ብቻ ነው ሁላችን ተጠቃሚ፣ ሁላችን አሸናፊ የምንሆነው። የኦሮሞ አባቶች ሲተርቱ “አፋን ጋሪ፣ አፈ ጋሪ ጫላ” ይላሉ፤ መልካም ንግግር ከመልካም አልጋ የተሻለ ያሳርፋል ማለት ነው። ሰው በውስጡ ነገር ካለው ምንም አልጋው ያማረ ቢሆን ይገላበጣል እንጂ አይተኛም። ውስጡ ያረፈ ሰው ግን መደብ ላይም ቢሆን ድንጋይ ተንተርሶ መተኛት ይችላል። ውስጣችን ሰላም እንዲሆን፣ መልካም እንቅልፍ እንድንተኛ፣ ለሰፈሬ፣ እኔ ወገኔ ለምለው፣ ለእኔ አካባቢ ብላችሁ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ብላችሁ እንድትመክሩ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ለዛሬ አትምከሩ፤ ለነገ ምከሩ። ለእናንተ አትምከሩ፤ ለልጆቻችሁ ምከሩ። አሁን የምንመካከረው ስለ ትናንትናው አይደለም። የትናንትናውን ችግር ፈትተን ለነገ መልካም መሠረት ለማኖር ነውና እያንዳንዱ ተወያይ፣ እያንዳንዱ ተወካይ ልጆቹን እያሰበ ለመመካከር የወሰነ መሆን አለበት። ይህንን ስናደርግ ግን የአፋር አባቶች ምክር ከልባችን ማቆየት አለብን። አፋሮች “አንድ ቦታ ተቀምጠህ፣ አንድ ቦታ ሆነህ በዚያኛው ወገን ያለውን ችግር ልትረዳ አትችልምና ተነስ፣ ሂድ፣ ያኛው ወገን ምን እንደሚያስብ፣ ምን ጥያቄ እንዳለው አድምጥ፤ ሳትሄድ፣ ሳታዳምጥ፣ ሳትጠይቅ የወል የሆነ፣ የጋራ የሆነ መፍትሔ ልታመጣ አትችልም” ይላሉ።

ሶማሌዎች ጥያቄ አላቸው፤ አፋሮች አድምጧቸው። ትግራዮች ጥያቄ አላቸው፤ ወላይታዎች፣ ሲዳማዎች አድምጧቸው። ዳሰነች፣ አሌ ጥያቄ አለው፤ አሮሞዎች፣ አማሮች አድምጧቸው። በተለይ አሮሞዎችና አማሮች ዳሰነችን፣ ኮንሶን፣ አሌን ካላደመጣችሁ ኢትዮጵያን ልታጸኑ አትችሉም። ምንም ጥርጥር የለውም በቁጥር ትላልቅ ሕዝቦች ናችሁ፤ ትናንሾቹን ካላከበራችሁ፣ ትናንሾቹን ካላደመጣችሁ በቁጥር ብቻ 'የእኛ ፍላጎት ይሁን' ካላችሁ ይህ ውይይት አይሳካም። ይህ ውይይት የሚሳካው አሌ ጥያቄ ሲጠይቅ፣ ጋሞ የማይጎዳ ከሆነ ያ ጥያቄ የማይጎዳው ከሆነ አሌ መቀበል አለበት። አሌ ጥያቄ ሲጠይቅ ጥያቄው ጎፋን የሚጎዳ ከሆነ ግን አሌ ጥያቄውን መሳብ አለበት። ማንም ሳይጎዳ በጋራ መጠቀም የምንችልባቸውን ጉዳዮች አንስተን 'ለእኔ' ሳይሆን 'ለእኛ'፣ 'ለሰፈሬ' ሳይሆን 'ለኢትዮጵያ' ማለት ከቻልን ይህ ምክክር ፍሬያማ ይሆናል።

የደከሙ ኮሚሽነሮች በማምሻ ዕድሜያቸው ለኢትዮጵያ ልፋታቸው ምንዳቸው የዚህ ውይይት ውጤት ይሆናል። እንደዚህ ያለው መድረክ ማዘጋጀት ባለመቻላችን ለረዥም ዘመናት ዋጋ የከፈሉ፣ የሞቱ፣ የቆሰሉ ኢትዮጵያውያንም ቢያንስ በዓፀደ ገነት ሳሉ በሌላ ትውልድ በተሠራ ሥራ ዕረፍት ሊያገኙ ስለሚችሉ ያለፉትን፣ የደከሙትን፣ የሚመጡትን እያሰብን "አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሺ" ብለን ለኢትዮጵያ የሚበጃትን ውጤት እንድናመጣ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። በትግራይ አንድ ትልቅ አባባል አለ፡- "ምክሪ ሓደ ትሕቲ ምድሪ፣ ምክሪ ክልተ ልዕሊ ምድሪ፣ ምክሪ ሰለስተ ዘርኢ ምድሪ" ይላል ትግራይ፤ የአንድ ሰው ምክር ከምድር በታች እንደተቀበረ ነገር ነው ዋጋ የለውም፤ የሁለት ሰው ምክር ግን ከምድር በላይ ነው ይታያል፤ የሦስት ሰው ምክር ግን ምርጥ ዘር ነው ይበቅላል፣ ይለመልማል፣ "በዝታችሁ ምከሩ" ይላሉ።

ይህንን የትግራይ አባባልና ምክር ተቀብለን፣ አሜሪካኖች ሃምሳ አምስት ሰው ጠርተው ለመቶ ዓመታት የሚቆይ ሕገ መንግሥት የገነቡ ቢሆንም፤ ትግራዮች ከአንድ ሰው የሁለት ሰው፣ ከሁለት ሰው የሦስት ሰው ምክር ይሻላል ስለሚሉ አራት ሺህ ሰው ሰብስበናል። የአሜሪካ ሕገ መንግሥት በሃምሳ አምስት ሰው ቢሠራም ልባም ነበሩና ለመቶ ዓመታት የሚቆይ ሥራ ሠርተዋል። የእኛ አራት ሺህ ሰዎች ከእነሱ በላይ፣ ከእነሱ በተሻለ ጊዜ፣ ይበልጥ ልባም ሆነው ሁሉን ወገን፣ መላው ኢትዮጵያን የሚሰበስብ ምክክር ቢያደርጉ በቀጣይ የሚኖረን ሕገ መንግሥት ከዚህ ቀደም እንደለመድነው የመጣ ሁሉ የሚቀደው ሳይሆን እኛ በአራት ሺህ ጀምረናል፣ በአሥር ሺህ ምክክር ሳያደርግ አንድም ሰው መቀየር አይችልም ማለት ነው። እኛ አራት ዓመት ተመካክረናል፤ ስምንት ዓመት ሳይመካከር መቀየር አይችልም ማለት ነው።

ስለዚህም ዛሬን ሳይሆን ነገ ዘልቆ የሚሄድ፣ ለትውልድ የሚበጅ ምክክር፣ ውይይትና ውጤት እንድናመጣ አንድ ቁልፍ መልዕክት አለኝ። ይኸውም ቀፎዋን የጣለች ንብ ማር አትሰጥም፤ ማር ለመስጠት በቀፎ ውስጥ መቆየት ያስፈልጋል። ይህ አራት ሺህ ስብሰባ መልካም ነገር መስጠት የሚቻለው በዚህ ጉባዔ አዳራሽ ውስጥ ሐሳቡን፣ ልቡን ሰብስቦ ሌላኛውን ወገን ማዳመጥ ሲችል ነው እንጂ ማታ ማታ እየወጣ ፌስቡክ የሚያይ ከሆነ፣ ማታ ማታ እየወጣ ምክር የሚያዳምጥ ከሆነ፣ ማታ ማታ እየወጣ ይህንን ዐውድ ያልተገነዘቡ ሰዎች መልእክት የሚጭኑበት ከሆነ ያ ንብ ማር አይሰጥም። ቀፎው እዚህ ነው ያለው፤ ልባችን እዚህ ይሁን፤ አዕምሯችን እዚህ ይሁን።

ልባችንና አዕምሯችን እዚህ ቢሆንም አሜሪካ ያለውንም፣ ደቡብ አሞ ያለውንም፣ ባድመ ያለውንም፣ ጋምቤላ ያለውንም፣ ጎዴ ያለውንም፣ አሳይታ ያለውንም የሚያስብ ግን መሆን አለበት። ውይይታችን ከዚህ አዳራሽ ተነስቶ እንደ ፀሐይ ወደ መላው ኢትዮጵያ የሚያበራ ከሆነ ለሁላችን ይፈይዳል።

ሰዎች ብዙ ሐሳብ አላቸው፤ ብዙ መሻት አላቸው። ቅድም እንደተባለው ግን ምክክር፣ ውይይት፣ ማድመጥ አይፈልጉም፤ ማዘዝ ይፈልጋሉ። ያን ላለፉት መቶ ዓመታት አየነው። የልጅ ኢያሱን ዘመን ብታዩ፣ የአጼ ኃይለሥላሴን ዘመን ብታዩ፣ የደርግን ዘመን ብታዩ፣ የኢህአዴግን ዘመን ብታዩ፣ በመላው ጊዜ ውስጥ ለመደማመጥ እንዲህ ያለውን መድረክ መፍጠር ባለመቻላችን ምክንያት ጥቂቶች እየወሰኑ ለረጅም ዘመን የሚጠቅመንን ነገር ማቆየት ስላልቻሉ ይህ ጉባዔ በሰማይም በምድርም ታላቅ ኃላፊነት ያለበት፣ የመቶ ሠላሳ ሚሊዮን ዜጎች የዛሬ፣ የሁለት መቶ ሦስት መቶ ሚሊዮን ዜጎች የነገ ኃላፊነት ያለበት ዕድለኛ ስብስብ ነውና ይህንን የታሪክ ብዕርና ብራና ሳታባክኑ ለኢትዮጵያ መልካም፣ ለአፍሪካ አስተማሪ የሆነ፣ እጅግ አስደናቂ፣ ሁላችንን የሚሰበስብ፣ ሰላም የሚያጸና፣ ልማት የሚያመጣ፣ ለእያንዳንዳችሁ እርካታን የሚያጎናጽፍ፣ ለመላው ኢትዮጵያውያን ዕረፍት የሚሰጥ ውጤት እንድታመጡ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፤ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደ ትናንቱ ለአፍሪካ ምሳሌ ትሆናለች። ኢትዮጵያ ማዕበል መከራ አይኑር አትልም፤ ማዕበል መከራን ወደ ዕድል ትቀይራለች። ኢትዮጵያ በዚህ ጉባዔ መሠረት ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ባህልን ታጸናለች። የጀመርናቸውን መልካም ዘሮች እንዘራለን፣ እንከባከባለን፣ ዛፍ እናደርጋቸዋለን፤ ነገር ግን ከሚያፈሩት ፍሬ እኛ ሳንሆን ትውልድ እንዲጠቀም እናደርጋለን። ያሰብነው፣ የጀመርነው እንዲከናወን የልባችንን አይቶ ከሚገባን በላይ የረዳን ፈጣሪያችን የተመሰገነ ይሁን! ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

ኢትዮጵያ በታማኝ የምክክር ተወካዮች ለትውልድ የሚበጅ፣ የሚዘልቅ ሐሳብ እንድታመነጭ እያንዳንዱ የበኩሉን እንዲያደርግ ፈጣሪ እንዲያግዛችሁ ጸሎቴ ነው። ዛሬ የሃይማኖት አባትነት ሽታ ያላቸው፣ አገራቸውን የሚወዱ፣ የፖለቲካ የተደበቀ ዓላማ የሌላቸው፣ በብሔር የተደበቀ ዓላማ የሌላቸው ምርጥ ምርጥ አባቶች ጸሎት አድርሰውልናል። እነዚህ አባቶች ዛሬ እዚህ ብቻ ሳይሆን ሲመለሱ በየአብያተ ክርስቲያኑ፣ በየቤተክርስቲያኑ፣ በየመስጂዱ፣ በተለያየ የእምነት ቦታ ከውጭ ላሉ ሰዎች፣ እዚህ ላሉ ሰዎች ልቦና፣ ማስተዋል፣ ፍቅር እንዲሰጣቸው በጸሎት፣ በዱዓ እንድታስቧቸው አደራ እላችኋለሁ።

በመጨረሻም ላለፉት አራት ዓመታት በብዙ ችግርና ፈተና ውስጥ ይህ ጉዳይ ለዚህ እንዲበቃ ያደረጋችሁ የምክክር ኮሚሽን አባላት በሙሉ ለኢትዮጵያ ታላቅ ውለታ ውላችኋል፤ በጀግንነት በተሰጣችሁ ኃላፊነት ተፋልማችኋል፤ እንደወረደባችሁ ዱላ ቢሆን ባልተገኛችሁ ነበር፣ ተቋቁማችኋል። ለዚህ ሁሉ በጀግንነት የተሞላ ተግባራችሁ የኢፌዴሪ መንግሥት፣ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድና የነገው ትውልድ ያመሰግናችኋል። ጊዜያችሁ ያማረ፣ የሰመረ፣ ለትውልድ የሚተርፍ ያድርግላችሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!
አዲስ አበባ



የ2018ዓ.ም የአንድ ጀምበር ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር

ሐምሌ 27፣ 2018ዓ.ም

ባለፉት ሰባት ዓመታት በተከታታይ ሳናቋርጥ ክረምቱን በሙሉ ዛፍ መትከል፣ ኢትዮጵያን ለማልበስ፣ የኢትዮጵያን መሰረት ለመጣል መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል። የዚህ ጥረት ዋነኛ አላማ «ኢትዮጵያ መበልጸግ አለባት፣ ሙብላት አለባት፣ መለወጥ አለባት፣ ማደግ አለባት፣ መሰልጠን አለባት» የሚል ምኞት፣ ህልም፣ መሻት ብዙ ኢትዮጵያውያን አላቸው። እንደዚህ ያለው ትላልቁ ህልም ሊሳካ የሚችለው አስተማማኝ መሰረት ከተጣለ ብቻ ነው። በሥነ-ምሕዳር መሰረት አፈርን መጠበቅ፣ ውሃን መጠበቅ፣ ተራራን መጠበቅ ሲቻል ነው። ከህግ አንፃር መሰረት መጣል ማለት ህዝብ ተወያይቶ የጋራ የሆነ፣ አሳታፊ የሆነ አስተማማኝ ህግ ማስቀመጥ ሲችል ነው። እነዚህ መሰረቶች ሳይጣሉ እዚህ ላይ የሚገነባ ማንኛውም ግንብ በማንኛውም አጋጣሚ ፈራሽ ሊሆን ይችላል።

አሁን እየሰራን ያለነው ለልጆቻችን ነው! ተስፋ ነው የምንተክለው፤ ነገን ነው የምንተክለው፤ ኢትዮጵያን ነው የምናለብሰው! ይህ ደግሞ የሚሆነው በትብብር ነው፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ወጥቶ በሚያደርገው ጥረት ነው። ይህ ጥረት እንደከዚህ ቀደሙ ኢትዮጵያ የቀረ አይመስለኝም። ብዙዎች እውቅና ሰጥተውት የኢትዮጵያን ፋና ለመከተል፣ የኢትዮጵያን አካሄድ ለመከተል ጥረት እያደረጉ ይታያሉ። ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ላደረገችው ጥረት የዓለም መንግሥታት እውቅና ሰጥተው፣ ሽልማት ብቻ ሳይሆን ኮፕ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲዘጋጅ ወስነዋል! ኮፕ ማለት ከአለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ትልቁ አህጉራዊ/አለም አቀፋዊ ጉባኤ የሚካሄድበት መድረክ ነው ፤ ከ80 ሺህ እስከ 100 ሺህ ሰው የሚሳተፍበት፣ ቢያንስ እስከ 100 መሪዎች የሚሳተፉበት ማለት ነው። እንደዚህ አይነቱን ትልቅ በዓል ኢትዮጵያ አዘጋጅታ አታውቅም፤ ከሰሀራ በታች ያሉ ሀገራት አዘጋጅተው አያውቁም።

ለኛ ትልቁ ብስራት የሚሆነው ዓለም የለበሰች፣ ያማረች፣ እያደገች ያለች፣ ተስፋ ያላት፣ ኢትዮጵያን እድል ያላት ኢትዮጵያን ከብዙ ንግግር በላይ ገልጠን ለማሳየት፣ የእኛን ተጨባጭ ልምድ ለማካፈል ትልቅ መድረክ ነው። በዛው ልክ ደግሞ የምናገኘናቸው ጥቅሞች በርከት ያሉ ናቸው። እኛ ኮፕን አስታከን ዓመቱን ሙሉ ኢትዮጵያን እንገነባለን፣ እንተክላለን፣ እናጸዳለን፣ እናፈርሳለን፣ እንገነባለን። ኢትዮጵያን እየገነባን ምክንያት አድርገን በመጠቀም ለዓለም የተባበረ ህዝብ መሰረት መጣል እንደሚችል፣ የተባበረ ህዝብ ሀገር መገንባት እንደሚችል ጥሩ ማሳያ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ።

ይህንን ጉዳይ ስንሰራ ለልጆቻችን አንድ ማስታወሻ እየተውን፣ ለልጆቻችን አንድ ቁም ነገር እያስቀመጥን ቅርስ እያስቀመጥን እንደሆነ እያሰብን እንሰራ። ዛፍ ለዛሬ ትርጉም የለውም፤ ለነገ ግን ትርጉሙ ብዙ ነው። ምግብ ነው፣ ጥላ ነው፣ ውበት ነው። ከዚያም ባሻገር የሚሸረሸር፣ የሚጠፋ ሃብታችን ጠባቂ ዘብ ነው። ብዙ ትርጉም ስላለው ኢትዮጵያውያን በጀመርነው መንገድ ተባብረን ዛሬም በሚቀጥሉት ሳምንታትም በመትከል የዚህን ዓመት ግብ ማሳካት፣ የእለቱንም ግብ ማሳካት ዋነኛ ስራችን ይሁን የሚል መልዕክት ነው ያለኝ።

`እንግዲህ ዛሬ 800 ሚሊዮን ችግኝ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ለመትከል ከጥዋት ጀምሮ እየተረባረቡ ይገኛሉ። ደጋግመን በመትከል ይህ ያልነውን ቃል እንደምንፈጽም ሙሉ እምነት አለኝ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፤ በርቱ፣ ተስፋን ትከሉ ለማለት እወዳለሁ!
አዲስ አበባ

የባህር ዳር ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ አዲሱ ተርሚናል ምረቃ ሥነ-ስርዓት

ሐምሌ 30፣ 2018ዓ.ም

ክቡር አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣
ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣
የክልላችን ርዕሰ መስተዳደር እንዲሁም የአየር መንገዳችን ዋና ስራ አስፈጻሚ፣
የተከበራችሁ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የባህርዳር ከተማ ነዋሪዎች፣ በዚህ ታላቅ የምስራች የደስታ ቀን በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ የከተማችን ነዋሪዎች እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን!

ባህርዳር ታሪክ ከተፈጥሮ ሁለቱም ሳይሰስቱ ውበት ያበዙላት፣ ታሪክ ያጠገቧት፣ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ከኛም አልፎ ለአፍሪካውያን የልማት፣ የብልጽግና፣ የለውጥ፣ የእድገት ምሳሌ መሆን የምትችል ከተማ ነች። እቺ ከተማ አሁን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሳይሆን ከመቶ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ ንግድ ከመሃል ሃገር ከሸዋ ከወለጋ ወደ ጎንደር ወደ ሰሜን በሚደረገው ጉዞ ውስጥ ድልድይ ሆና የብዙ ንግድ መዘዋወርያ ማዕከል ሆና ለረዥም ጊዜ ያገለገለች አካባቢ ናት። ለዚያ አንዱ ማሳያ በጎንጎራና በባህርዳር መካከል ለነበረው የንግድ እንቅስቃሴ በጊዮርጊስ ጊቢ ማረፊያ ግንብ የተገነባው ቢያንስ ከ ሁለት መቶ ዓመት በፊት ነው። ይህ ስፍራ ጎርጎራን ከመሃል ሀገር የመጡትን ወደ ሰሜን በማሻገር ከፍተኛ የንግድ ማዕከል ሆኖ የቆየ አካባቢ ነው። በዚያ ታሪኩ ልክ ንግድ ተስፋፍቶ ሀገር ተለውጦ ለከተማውም ከከተማውም ባሻገር ልማት ሊያመጣ የሚችልበት ሁኔታ በቀጣይነት ባለመሰራቱ ባህርዳርን ማየት በሚገባን ልክ ሳናይ የቆየን ቢሆንም አሁን ታሪካችንን መለስ ብለን በመቃኘት መልካም ጅማሮ እንዳለ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጎርጎራ ሪዞርት ተገንብቶ እዚህም ፈለገ ጊዮን ባህርዳር ከተማ ውስጥ ተገንብቶ ሁለቱን ማገናኘት የሚችል የብዙ መርከቦች በተለይም ጣናነሽን የመሰለ በኢትዮጵያ ትልቋን መርከብ በዚህ አካባቢ ማምጣት የተቻለበት ዋናው ምክንያት በቱሪስት መስክ ባህርዳር ለኢትዮጵያ ማበርከት የምትችለው በጣም በርካታ ሀብቶች ስላሉ ነው። በዚህ እና ጎርጎራ መካከል ባሉ ቦታዎች ብዙ ታሪክ ጠገብ ውብ የኢትዮጵያ ቅርሶች፣ ታሪክ ማጥናት፣ ማወቅ፣ መማር ለሚፈልጉ ሰዎች በእጅጉ አስተማሪ የሆኑ ደሴቶች እንዳሉ ይታወቃል። እነዛን ደሴቶች ማየት፣ ታሪክ መማር ማጥናት የሚፈልግ ሰው

በባህርዳር እና ጎርጎራ መካከል የነበረውን ለረዥም ጊዜ የቆየውን የትራንስፖርት ሁኔታ አሻሽሎ በርከት ያሉ ሰዎች አንድ ጊዜ ከዚህ ወደዚያ ወይም ከዚያ ወደዚህ ለማምጣት በሚያስችል መንገድ ቱሪዝምን በሚያነቃቃ መንገድ የተሰራው ስራ ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት ባሻገር የግሉ ዘርፍ በባህርዳር ከተማ ያለቁ፣ የተጀመሩ፣ በቅርብ የሚጠናቀቁ በጣም በርካታ ስራዎች እንዳሉ ለማየት ችለናል።

ከለውጡ በኋላ ከቱሪዝም ባሻገር በኢንዱስትሪው መስክ ባህርዳር አንድ ትልቅ አቅም ያላት ከተማ ስለሆነች ኢንደስትሪያል ፓርክ በዚህ ከተማ ተገንብቷል። ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ከተሞች ምናልባትም ቀዳሚ በሆነ ደረጃ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በጥሩ ዲዛይን ከተሰራባቸው ከተሞች መካከል ከፍተኛውን ስፍራ የምትይዘው ባህርዳር ናት። በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በከባቢያችንም ጭምር በግዝፈቱ በጥራቱ ሊተካከለው የማይችል ድልድይ የተገነባው በባህርዳር ከተማ ነው። አሁን ደግሞ የኮሪደር ስራው በውስጥ ያላችሁ ሰዎች እንደምታዩት እኛም ዛሬ በከፍተኛ አድናቆት እንዳየነው በጣም ተስፋ ሰጪ፣ ይበልጥ ውበቷን መግለጥ የሚችል፣ ሰዎች ተቀብላ ለማስተናገድ የሀብት እንቅስቃሴ ማዕከል ለመሆን የሚያስችል ሁናቴ በባህርዳር መጀመሩን አይተናል።

ከዚህ ባሻገር እየተሰራ ያለው እስታድየም ሲጠናቀቅ ብዙ ሰዎች ከሀገር ውስጥ፣ ከአፍሪካ እየመጡ የሚሰነብቱበት፣ የሚከርሙበት፣ ውበት፣ ታሪክ፣ መልካም ማኅበረሰብ ተዳምሮ በብዙ መልኩ መጥተው የማይቆጩበት ከተማ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም። ከዚህ ባሻገር ዛሬ ያየሁት በጣም ተስፋ የሰጠኝ ነገር በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰራው ማሻሻያ ነው። የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ከቢሯቸው በመሆን በመላ ክልሉ ደረጃ የሚደረጉ ችሎቶችን ቨርቺዋሊ መከታተል የሚያስችል፣ ቅሬታ ማድመጥ የሚያስችል፣ ለክልሉ ህዝብ ፍትህ እና ርትዕ ለማረጋገጥ የሚያስችል አስደናቂ ስራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰርተው ማየቴ ከፍተኛ ምስጋና ላቀርብላቸው እፈልጋለው። እነዚህ መልካም ስራዎች በባህርዳር ከተማ ሲሰሩ በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ባለው ሁኔታ ከቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ቀጥሎ ትልቁ ሁለተኛው ተርሚናል የተገነባው ባህርዳር ከተማ መሆኑ ቅድም ለገለጽኳቸው የልማት ስራዎች ሁሉ ብስራት፣ ገበያ አምጪ፣ ለአየር መንገዱም፣ ለከተማውም፣ ለክልላችንም፣ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብም በእጅጉ የሚጠቅም መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ይህንን ታላቅ ስራ ለሰራው አየር መንገዳችን እና ዋና ስራ አስፈጻሚያችን እንኳን ደስ ያላችሁ ታላቅ ስራ ነው ለማለት እወዳለሁ።

ሁላችሁም እንደምታውቁት እንደዚህ ያለውን እድገት ለማስቀጠል ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች የግድ ሊሟሉ ያስፈልጋል። አንደኛው ቁልፍ ጉዳይ በገነባን ቁጥር በርከት ያሉ ሰዎች

እያመጣን ይበልጥ ገበያችን እያደገ ሌላ ልማት፣ ሌላ የልማት ስራ መስራት የሚያስችል የከተማውን ገቢ፣ የከተማውን አቅም ማሳደግ ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከቦሌ ቀጥሎ ትልቁ ተርሚናል አለ ብንልም፣ ትልቁ ድልድይ አለ ብንልም፣ ትላልቅ ሪዞርቶች ተገነቡ ብንልም፣ ስታድየም እያለቀ ነው ብንልም ዛሬ ባህርዳር ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ከተሞች ገቢዋ ሰባተኛ ደረጃ ነው። ይህ ገቢ ካልተሻሻለ በስተቀረ ከንቲባ ጎሹ ከተማን መቀየር አይችልም ብቻ ሳይሆን እስካሁን የሰራውን ጭምር ማስቀጠል አይችልም። ዛፎች ተተክለዋል፣ ሳር ተተክሏል፣ አበባ ተተክሏል ይሄ ሁሉ መጠገን እንክብካቤን ይሻል፤ ለዚያ ደግሞ ወጪ አለ። ለዚያ ወጪ እንዲሆን የከተማችን ገቢ አድጎ ባህርዳር እራሱን ችሎ እራሱን እያለማ እንዲሄድ፣ ለቱሪስቶች ምቹ፣ ለባለሃብቶች ምቹ፣ ወጥተው ለሚገቡ ሰዎች ምቹ፣ ሰዎች መጥተው በደስታ ገንዘባቸውን አፍሰውበት የሚሄዱበት ከተማ መሆን ይኖርበታል። ያ እንዲሆን መላው የከተማችን ነዋሪዎች፣ የክልላችን መንግሥት ከከንቲባችን ጋር በመረባረብ ባህርዳር የሚገባትን የገቢ ልክ ማመንጨት እንድትችል ተጨማሪ ስራ ያስፈልጋል።

ሁለተኛው ቁልፍ ጉዳይ ሰላም ነው። ባህርዳር ረዘም ያለ ጊዜ የቆያችሁ ሰዎች እንደምታውቁት ተስፋ ማደርገው አንድ ታሪክ አለ። እዚህ ከተማ ውስጥ አቶ አህመድ ወሎ የሚባሉ ወይም አባ ኑሮ የሚባሉ ዘይት ነጋዴ ነበሩ። የዘይት ንግዱ ስም ቅቤ ለምኔ ይባል ነበር። እኚህ ሰው የዘይት ነጋዴ ከመሆናቸው ባሻገር አንድ የሚታወቁበት ባህሪ አላቸው ከሳቸው አነስ ያለ ገቢ ያላቸውን ሰዎች ስራ እየፈጠሩ ያግዙ ነበር። ዘይት እየሰጡ እነዚያ እየቸረቸሩ ገንዘብ እንዲያመጡ፣ ሂወታቸው እንዲሻሻል ይደግፉ ነበር። በደግነታቸው የሚታወቁ ሰው ናቸው። እኚህ ሰው ከሚያግዟቸው ሰዎች መካከል አንዲት እናት ነበሩበት። እኚህ እናት ሁልጊዜ ሄደው ዘይት ይወስዳሉ። ሸጠው መጥተው ገንዘቡን ከፍለው ዘይት ይወስዳሉ። ሁሌ ሲመጡ ግን ያለቅሳሉ፤ እያለቀሱ ዘይት ከአቶ አህመድ ወሎ ወይም ከአባ ኑሮ እየተቀበሉ ይቸረችራሉ። እና አባ ኑሮ ለምንድን ነው በመጡ ቁጥር የሚያለቅሱት፣ የሚያዝኑት ብለው ይጠይቃሉ። እና እኚህ እናት፡- «ሁለት ልጆች አሉኝ፤ አንደኛው ልጅ ከእርሶ በብድር የምወስደውን ዘይት በትጋት ሸጦ ገንዘቡን ያመጣልኛል። አንደኛው ልጅ ጊዜ ጠብቆ አድብቶ፣ አድፍጦ ያን ገንዘብ ሰርቆ ያባክንብኛል። አንደኛው ልጅ ያግዘኛል፣ አንደኛው ልጅ ያዳክመኛል። በዚህ ምክንያት ውስጤ ሃዘን ገብቶ ነው በየጊዜው የማዝነው የማለቅሰው» ብለው ሴትዮዋ ሲመልሱ አቶ አህመድ ወሎ አንድ ግጥም ገጠሙ ይባላል፡- «ቀኙ የሰራውን ግራ እያፈረሰው፣ ሁሉም ጦም አዳሪ ሆነ የሀገሬ ሰው፤ አልቅሶ ከመኖር እድሜ ዘመኑን አይቆነጥጥም ወይ ቀኙ ግራውን» አሉት ይባላል። ቀኙ ግራውን መቆንጠጥ ካልቻለ፣ ቀኙ ግራውን ማሳረፍ ካልቻለ ያየናቸው ተስፋዎች፣ ያየናቸው ሙከራዎች ሊበላሹ ይችላሉ ። ጊዜ አይለፍብን፣ ዘመን አይለፍብን፣ ዕድል

ስናገኝ እንጠቀምበት፣ ዕድል ስናገኝ ልማት እንስራበት። ይህን ቦታ የሰራነው ከጅምሩ አቅደን ሳይሆን በዚያ ግጭት ምክንያት ጠላት ያኛውን ቀድሞ የነበረውን ያነሰውን አሮጌውን ተርሚናል ሲመታብን በዚያ ከምናላዝንና ከምናዝን ያንን ችግር ወደ ዕድል ቀይረን የተሻለ፣ የላቀ፣ ያማረ ለልጆቻችን የሚሻገር ነገር መገንባት ተችሏል። ይህ ነገር ልማድ እንዲሆን፣ ይህ ነገር እንዲደጋገም ባህርዳር በአፍሪካ ውስጥ ከጥቂት ሃገራት ውጪ ሻል ያለ ኤርፖርት ብቻ ሳይሆን እውነቱን ለመናገር ከሆነ ከብዙ የአፍሪካ ካፒታል ሲቲ የሚሻል፣ የሚልቅ፣ የሚበልጥ አቅም አላት። ይህ አቅም በኛ ትጋት፣ በኛ ጥረት፣ በኛ ልፋት፣ በኛ ስራ ልቆ ሊታይ የሚችል ስለሆነ መላው የከተማችን ነዋሪዎች ሰላም ውድ ስጦታ፣ ጊዜ ትልቅ ሃብት፣ ስራ ትልቅ ጸጋ፣ ትብብር በጋራ መቆምና ማልፋት ከምንም ጊዜም በላይ የሚያስፈልግበት ዘመን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የመጨረሻው መራር እውነት ባለፉት 30 ዓመታት ቢያንስ በቅርበት ባህርዳርን በማውቅበት ዘመን እንደዚህ እንደዛሬው ዘመን የአማራ ክልልም ሆነ ባህርዳር ራሱን በራሱ በተሟላ መንገድ የሚያስተዳድርበት ዘመን አልነበረም። ፕሬዝዳንታችን ከነሙሉ ክብራቸው እና ህግ ከሰጣቸው ስልጣን ጋር ያሻቸውን መወሰን የሚችሉ፣ የታመኑ፣ የተወደዱ፣ የተከበሩ፣ የሚሰሩ፣ የሚያሰሩ ፕሬዚዳንት ናቸው። እንተባበር፣ ባህርዳርን እናልማ! ካልተግባባን ደግሞ እንደ ጨዋ በንግግር እንጨቃጨቅ፤ ጊዜ ግን እንዳያልፍን እንጠንቀቅ !

አመሰግናለሁ!
ባህርዳር

ሞጆ ዘመናዊ የሎጂስቲክስ ማዕከል ማስፋፊያ የመጀመሪያ ምዕራፍ

—ጳጉሜን 5፣ 2018 ዓ.ም.

ባለፈው ዓመት በብዙ ድል፣ በብዙ መከናወን፣ በብዙ ስምረት ዓመቱን ጨርሰን አዲስ ዓመት በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ሞራል፣ በአዲስ ዝግጅት ለመቀበል ያበቃንን ፈጣሪያችንን እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። ከቡራት እና ከቡራን ዓመቱን ሙሉ የከወናቸውን አንጋፋ ሥራዎች ማንሳት ባያስፈልግም ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ በርከት ያሉ ፕሮጀክቶች አጠናቀን ያስመረቅንበት፣ አንጋፋ አንጋፋ ፕሮጀክቶች ለነገይቱ ኢትዮጵያ ስምረት መሠረት የሚጥሉ ሥራዎች ያስጀመርንበት፣ ከ50 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ወጥቶ “ይሁን” ብሎ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚያስተዳድረውን መንግሥት የመረጠበት፣ ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች የኢትዮጵያ ዜጎች በሙሉ ላለፉት ዓመታት የነበረባቸውን ጥያቄዎችና ስብራቶች መፍታት ይችሉ ዘንድ ከ4000 ሰው በላይ ከ40 ቀን በላይ መክሮ ዘክሮ የኢትዮጵያን መጻኢ ጉዞ ያሰመረበት ንግግር ጀምረን በሰላም የጨረስንበት ዓመት ነበረ።

ከዚያ ባሻገር ባለፉት የክረምት ወራት ብቻ ስምንት ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል አቅደን 8.2 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል ባለፉት ስምንት ዓመታት ኢትዮጵያ 56.2 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል መቻሏ ታላቅ ብስራት ነውና “እንኳን ደስ አላችሁ” ለማለት እወዳለሁ። እነዚህ የስምረት፣ የድል፣ የመከናወን ጉዞዎች ተሰናስለው እና ተደምረው በዚህ ዓመት ኢትዮጵያ ከ10.2 በመቶ በላይ እድገት ወይም ከፍተኛውን የአፍሪካ እድገት ማስመዝገብ ችላለች። በዚህ ዓመት ያገኘነው ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲቀጥል እንደዚህ ያለው ሥራ በእጅጉ ወሳኝ ነው። ሎጂስቲክስ ለአንድ አገር እድገት ከፍተኛ ጉልበት ሲሆን በቅጡ ሳይሠራ ሲቀር ደግሞ እድገትን የሚያንቅ ማነቆ ይሆናል።

እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በማደግ ላይ ላሉ፣ ግዙፍ ኢኮኖሚና ከፍ ያለ ህዝብ ቁጥር ላላቸው ሀገራት ሎጂስቲክስ የማይተካ ሚና ይጫወታል። ሎጂስቲክስ ሲባል ከባሕር በር እስከ እያንዳንዱ ቤትና ሱቅ ድረስ ያለውን እንቅስቃሴ አስተሳስሮ የያዘ ጉዳይ ነው። ትራንስፖርትን፣ የአየር መዳረሻን፣ የባቡሩ መስመርን፣ የወደብ አገልግሎትን እንዲሁም አጠቃላይ እነዚህን ጉዳዮች ለማሳለጥ የሚያግዙ አገልግሎቶችን በውስጡ የያዘ ሲሆን እነዚህ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ያነቁ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የፈለገው መንገድ እንዳይሄድ ያደረጉ ጉዳዮች መፈታት እንዲችሉ ይህ ዛሬ በሞጆ የምናስመርቀው ደረቅ ወደብ ወደዚያ ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች ውስጥ ምናልባት አንድ አሥረኛውን የሚሸፍን ይሆናል።

ይህ ፕሮጀክት ባለፉት ዓመታት ከውጭ ኢትዮጵያ ለምታስገባቸው ማንኛውም ዕቃዎች፣ የመቶ ብር ዕቃ ከሆነ 25 በመቶ (25 ብር) የምናወጣው ለሎጂስቲክስ ነው። የአራት ብር ዕቃ ከሆነ ፣ ብር የሚወጣው ለሎጂስቲክስ ነው። 25 በመቶ ለሎጂስቲክስ ማውጣት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠርና እድገት ለማሳለጥ በእጅጉ የሚያስቸግር ጉዳይ ስለሆነ ከዚህ ወደ ጅቡቲ የሚሄደውን ሃይዌይ አብዛኛውን ክፍል ጀምረናል። ባቡር ሥራ የጀመረ ቢሆንም የነበረውን አቅም ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል። ይህ ደረቅ ወደብ ያስተናግድ ከነበረው ግማሽ ሚሊዮን ኮንቴነር ወደ ፣ ሚሊዮን ኮንቴነር ማደግ ችሏል።

የቴክኖሎጂ አሰራር በዚህም በዚያም ጫፍ እንዲስፋፋ ተደርጓል። እነዚህ ጉዳዮች የሚጨበጥ ውጤትና የሥራ ስልጠት እንደሚያመጡ ይጠበቃል። ነገር ግን የኢትዮጵያ እድገት በቀጣይነት የተሟላ እንዲሆን ሎጂስቲክስ ከ25 ወደ 10 ከዚያም በታች ዝቅ እንዲል ከጫፍ ጫፍ ማገናኘት የሚገባን ሥራዎች ከፊታችን መኖራቸውን መዘንጋት አያስፈልግም። ኢትዮጵያ በአየር ትራንስፖርት የአፍሪካ መዳረሻ ማዕከል ለመሆን የጀመረችው ሥራ የተሟላ እንዲሆን ሞጆ፣ ቢሾፍቱ እንዲሁም ከዚያ ተሻግሮ የሚሠሩ ሥራዎች ተሰናስለው በቀጣይ ዓመታት እድገታችንን ወደምናስበው ደረጃ እንደሚያደርሱ ሙሉ እምነት አለኝ።

ክቡራት እና ክቡራን 2018 የብዙ ድል፣ የብዙ መከናወን፣ የብዙ ስኬት ዓመት ነበር። 2019 ከዚያ በላቀ፣ በከፍተኛ ውጤትና ድል ጀምረን የምንጨርስበት ዓመት ይሆናል። 2019 የምንሠራቸው ሥራዎች ዘንድሮ ከሠራናቸው በላቀ አፈጻጸምና ደረጃ ፕሮጀክቶች ያልቃሉ፤ የሀገራችን ሰላም ይሻሻላል፤ እድገታችን በተሻለ መሠረት ላይ ይቆማል። እድገታችንን፣ ጉዞአችንን የሚጠሉና ሊያቆሙን የሚተጉ ኃይሎች የማይቻል ተራራ ጋር የገጠሙ መሆኑን በተግባር እናሳያቸዋለን።

የሚቀጥለው ዓመት በብዙ ድል ጀምረን የምንጨርስበት ዓመት ስለሆነ እያንዳንዱ የሥራ ሃላፊ አምናና ካቻምና ከሠራው ባሻገር በብዙ እጥፍ ለኢትዮጵያ ለመስጠት፣ በታመነው ልክ ለመገኘት፣ ሕዝቡ ባከበረው ልክ በሥራና በውጤት ምላሽ ለመስጠት ቆርጦ እንዲነሣ፣ እንዲዘጋጅ፣ እንዲተሳሰር፣ እንዲደመር ከወዲሁ አደራ እያልኩ፤ ባለፈው ዓመት ያስጀመረንና ያስጨረሰን፣ በዚህ ዓመት የሚያስጀመረንና የሚያስጨርሰን ፈጣሪያችን ምስጋና ይግባው!

ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች! ያሰበችውን ታሳካለች! ጉዞዋን በፍጥነት ትቀጥላለች! የተባለው ሁሉ ይከወናል! እንበለጽጋለን! እናድጋለን! የአፍሪካ ማዕከል እንሆናለን! ይህን በልመና

ሳይሆን በሥራችን፣ በሥራችን የምናሳካው ጉዳይ ይሆናል። እናልማለን፣ እንተጋለን፣ እንፈጽማለን! እናልማለን፣ የሚቃረነን ሲኖር እንደ ጉዶ እየነቀልን ፍጥነታችንን ጨምረን ብልጽግናችንን እናረጋግጣለን! ልጆቻችን የተሻለ ሀገር እንዲረከቡ ያለብንን አደራ በሙሉ እምነትና ብቃት እንከውናለን። የኢትዮጵያ መጻኢ ዘመን እጅግ አስተማማኝ፣ እጅግ ተስፋ ሰጪ፣ ለብዙዎች አስተማሪ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም።

እንኳን አደረሳችሁ! እንኳን አደረሰን! መልካም በዓል! የድል ዓመት፣ የድል ዘመን ይሁንልን፣ ይሁንላችሁ!

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ
ሞጆ

መልእክቶች በአማርኛ

የ2018ዓ.ም አዲስ ዓመት መልእክት

ኢትዮጵያ ማንሠራራት በጀመረችበት እና ታላቁ የሕዳሴ ግድብ በተመረቀበት ጊዜ ለሚከበረው አዲስ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ። ያለፈው ዓመት ፈጣሪ ከጎናችን፣ ስኬት በደጃችን መሆኑን ያየንበት ዓመት ነበር። በግብርና፣ በቱሪዝም፣ በማዕድን፣ በአምራችነት እና በአይሲቲ ዘርፎች ያስመዘገብናቸው ውጤቶች ይሄንን ይመሰክራሉ። ኢትዮጵያን ያህል ሀገር፣ ኢትዮጵያውያንን ያህል ሕዝብ ይዘን በትጋት ከሠራን፣ ከዚህ በላይ ድል ልናሳካ እንደምንችል ምስክራችን የሕዳሴ ግድብ ነው።

ከእርግዝና ወራት ሁሉ እጅግ አስቸጋሪዎቹ፣ እጅግ አስፈሪዎቹ እና እጅግ ፈታኞቹ የመጨረሻዎቹ ሰዓታት ናቸው ይባላል። በሕዝብ ልብ ውስጥ ለዘመናት የተጸነሰውን የሕዳሴውን ግድብ ኢትዮጵያ እንድትወልደው ብዙ ፈተናዎችን መሻገር ግድ ነበር። ብዙ አስቸጋሪ ጊዜያትን ማለፍ ይገባ ነበር። አያሌ አስፈሪ ተግዳሮቶችን መቋቋም ወሳኝ ነበር። በተለይም የመጨረሻዎቹ ጊዜያት ወገብን አሥሮ፣ ሐሞትን አምርሮ፣ ወኔን ቋጥሮ፣ ወጥመድን ሰብሮ፣ ሞትን ተሻግሮ መሄድ የሚያስፈልግባቸው ጊዜያት ነበሩ። ከፈጣሪ ጋር፣ በሕዝባችን ጽናት፣ በፕሮጀክት ሠራተኞቻችን ብርታት፣ በጸጥታ አባሎቻችን መሥዋዕትነት ያን ሁሉ አልፈን ለምርቃቱ በቅተናል።

የምናከብረው የዓመትን መለወጥ ብቻ አይደለም። የታሪክን መለወጥ ጭምር ነው። የኢትዮጵያ ገጽታ፣ የኢትዮጵያ ትርክት፣ የኢትዮጵያ ጂኦ ፖለቲካዊ ቁመና ተቀይሯል። ቀደምቶቻችን ሲመኙት፣ አያቶቻችን ሲያስቡት፣ አባቶቻችን ሲጠብቁት፣ እኛ ስንታገልለት የነበረው የኢትዮጵያ ማንሠራራት እውን ሆኗል። ይሄ ለሺ ዘመን የከፍታ ጉዟችን መነሻ እንጂ መዳረሻ አይደለም። ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። እኛ በዐቅምና በአቋም ከተደመርን፣ ሀገራችን ባለ ብዙ ጸጋ ናት። ለአፍሪካ እና ለዓለም የሚተርፍ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ተፈጥሯዊ ሀብት ሞልቷታል።

2018 የኢትዮጵያን ማንሠራራት የበለጠ ሥር እና መሠረት የምናስይዝበት ዓመት ነው። በአንድ እጃችን ፈተናዎቻችንን እየተቋቋምን፣ በሌላው እጃችን ታሪካችንን እየቀየርን እንጓዛለን። ንሥር ከምድር ሲነሣ ብዙ ወፎች እና ነፍሳት አብረውት ሊነሡ ይችላሉ። ለተወሰነ ጊዜም አብረውት ይበራሉ። የተወሰነ ሰዓትም ሊሸፍኑት ይደርሳሉ። የበለጠ ወደ ላይ በመጠቀ ቁጥር ግን ብዙዎቹ ወደታች ይቀራሉ። በመጨረሻም በሕዋው ላይ የሁሉንም ታሪክ እየተመለከተ ንሥር በድል መጓዙን ይቀጥላል። እኛም ለኢትዮጵያ ንጋት እና ምጥቀት ያስፈልገናል። 2018 የኢትዮጵያ ታላቅነት የበለጠ እየነጋ፣ የበለጠ እየበራ፣ የበለጠ እየፈካ የሚሄድበት ነው። የሕዳሴ ግድብን ባየን ቁጥር የኢትዮጵያን

የኢትዮጵያን አይበገሬነትና ቻይነት እናስታውሳለን። ሐይቁን ባየን ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያን ንጋት እናስባለን። "ንጋት ሐይቅ" የተባለውም ለዚህ ነው። ግድቡ እስካሁን የነበረውን ይናገራል። ሐይቁ ከዚህ በኋላ የሚመጣውን ያበሥራል። ንሥር ከትንሽ ከትልቁ ጋር በሆነ ባልሆነው አይከራከርምም፤ አይነጋገርም። ወደላይ በመጠቀ ቁጥር ፈተናው እየቀነሰ፣ ዐቅሙ እየጨመረ፣ ታሪኩ እየተቀየረ እንደሚሄድ ያውቀዋል። ስለዚህም ከግራ ከቀኝ የሚወረወረው እየቻለ ወደ ላይ ይመጥቃል። እኛም ወደ ላይ ከፍ ባልን ቁጥር ፈተናችን እየቀረ፣ ድላችን እየተጨመረ እንደሚሄድ ዐውቀን፣ አእምሯችንን እና እጆቻችንን ለሥራ ማሰለፍ አለብን። ኢትዮጵያን የሚቀይራት የልጆቿ ፍጥነትና ፈጠራ ነው። የዓባይን ታሪክ የቀየረው ሥራ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ የሚቀይረውም ሥራ ነው። በየቢሮው፣ በየእርሻው፣ በየግንባሩ፣ በየድርጅቱ፣ በየትምህርት ቤቱ፣ በየተቋማቱ ያለን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ልባችንን፣ ሐሳባችንን፣ ዕውቀታችንን እና ጉልበታችንን ለኢትዮጵያ ብልጽግና እናውለው። ስንሠራ ምን እንደምንቀይር ከሕዳሴው ግድብ አይተናል። እኛ ለስኬት ስንረባረብ ፈጣሪ ምን ያህል እንደሚረዳን እኛው ምስክር ነን። የሺ ዘመናትን ጥያቄ እንድንመልስ ኃይል የሰጠ ፈጣሪ፣ የዓመታትንና የወራትን ጥያቄ ለመመለስ አይሳነውም። 2018 ዓመት ይሄንን ይበልጥ የምናረጋግጥበት እንደሚሆን አምናለሁ።

ዛሬ ዓይኖቻችን ያዩትን ለማየት፣ ጆሮዎቻችንም የሰሙትን ለመስማት እንዲችሉ መሥዋዕትነት ለከፈላችሁት ሁሉ እጅ እንነሳለን። በሁሉም መስክ የተሳተፋችሁትን ሁሉ ኢትዮጵያ ታከብራችኋለች። ከጎናችን የነበራችሁትን ወዳጅ ሀገሮች እና ሕዝቦች ሁሉ በኢትዮጵያ ስም እናመሰግናችኋለን። እድገትና ብልጽግና የቅብብሎሽ ውጤት ነው። የጀመራችሁ፣ ያስቀጠላችሁ፣ ለፍጻሜ የታገላችሁ ስማችሁን በሕዳሴ ግድቡ ላይ ጽፋችኋል። በገንዘብ፣ በዕውቀት፣ በጉልበት፣ በሚዲያ፣ በዲፕሎማሲ፣ በሞያ፣ ወዘተ. የምትችሉትን ያበረከታችሁ ሁሉ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ሆናችሁ በታሪክ ሠፍራችኋል። ይህ ተጋድሏችን፤ ይህ ትብብራችን፤ ይህ ለብሔራዊ ጥቅም በአንድነት መቆማችን፤ ይህ ለራሳችን፣ በራሳችን፣ ከራሳችን መሥራታችን ነገም መቀጠል አለበት። ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ ይገባታል። ኢትዮጵያ ከዚህም በላይ ታላላቅ ሥራዎች ይጠብቋታል። ይሄንንም አብረንና ተባብረን ልናሳካላት ይገባል።

አዲሱ ዓመት የኢትጵያ ማንሠራራት የበለጠ መሠረት የሚይዝበት እንደሚሆን አምናለሁ በድጋሚ መልካም አዲስ ዓመት ይሁን ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ጳጉሜን 5፣ 2017 ዓ.ም

እንኳን ለመስቀል በዓል አደረሳችሁ!

የመስቀል በዓል ሲታሰብ እውነት ተቀብራ እንደማትቀር እናስባለን። መስቀሉ የተቀበረበት ቦታ ተራራ ሠርቶ ነበር። የቀበሩት ሰዎች ከዚህ በኋላ እንደማይወጣ ደምድመው ነበር። አንዳንድ አማኞችም ተስፋ ቆርጠው ነበር። ጊዜው በረዘመ ቁጥር ቀባሪዎቹ ያሸነፉ መስሏቸው ተደሰቱ። የተቀበረው መስቀልም ታሪክ የሆነ መሰለ።

ብርቱ ሰዎች፣ እውነት ፈላጊ ሰዎች፣ አቧራውን የሚገልጡ፣ ቆሻሻውን የሚያነሡ ሰዎች፣ ሲመጡ ግን መስቀሉ ከተቀበረበት ወጣ። እውነት አይቀበርም። ጊዜው ሲደርስ አቧራውን አንሥቶ ዐሻራውን ያሳያል። ሐሰቱን እንደ ጉም አትንኖ፣ ሐቁን እንደ ዐለት አግንኖ ያሳያል።

የኢትዮጵያም እውነት እንደሁ ነው። የአውራ ዶሮዎች ጩኸት የፀሐይን መውጣት አያስቀረውም። የሌሊት ወፎች ክንፍ የፀሐይን ንጋት አያግደውም። በዚህም ተባለ በዚያ ፀሐይ ትወጣለች። የኢትዮጵያ እውነት እንደ መስቀሉ ሁሉ አቧራውን ጥሶ፣ አፈሩን አፍልሶ ፣ ቆሻሻውን ደርምሶ ይገለጣል። የወጓት ያዩዋታል። ከላይ ሆነው እንዳዩዋት ሁሉ፤ ከታች ሆነው ይገረሙባታል።

በመደመር ደመራ እየተመራን፣ በትጋት እየቆፈርን፣ የኢትዮጵያን ብልፅግና እናወጣዋለን። ይህ ዓመት የኢትዮጵያ ብርሃን ሲወጣ የምናይበት ይሆናል።

በድጋሚ መልካም የደመራና የመስቀል በዓል ይሁንልን። ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
መስከረም 16፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለኢሬቻ መልካ በሰላም አደረሳችሁ!

ኢሬቻ የኦሮሞ የምስጋና ስርዓት ነው፡፡ ኦሮሞ የሰው ዘር አፍርቶ የሚባዛው የተዘራው ሞቶ በመነሣት ፍሬ የሚያፈራው በፈጣሪ ድጋፍና እርዳታ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ለዚህ ነው ኢሬቻ ሲደርስ ኦሮሞ ልበ ንፁህ የሆነውን ታላቅ ፈጣሪ ላደረገለት ሁሉ በማመስገን ለሚመጣው ጊዜ ደግሞ ምህረትን በመለመን ውዳሴ ያቀርባል፡፡

በጥንት የኦሮሞ ፍልስፍና ውስጥ ኦሮሞ ለውሃ ትልቅ ስፍራ አለው፡፡ ውሃ የንጽህና ምንጭ ፣ የፍጥረትና የህይወት መሠረት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ለዚህም ነው ሲፀልይ ፈጣሪ አምላክ ፣ የፍጥረታት አምላክ ፣ የቡርቃ ወላቡ (የወላቡ ምንጭ) አምላክ ብሎ ነው የሚፀልየው፡፡ የዘንድሮው ኢሬቻ ኢትዮጵያ የዜጎቿን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት የዓባይን ወንዝ በመገደብ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ባስመረቀችበት ማግስት የሚከበር መሆኑ ደስታችንን ድርብ ያደርገዋል፡፡ እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን!

ኦሮሞ መልካ የሌለው ህዝብ ራስ እንደሌለው ህዝብ ነው እንደሚል የባህር በር የሌላት ሀገር ኑሮ የሌላት ሀገር ናት ብለን ለህዝባችን ብልጽግና ስንል በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የባህር በር ለማግኘት እየሠራን እንገኛለን፡፡ በዚህ ረገድ እያደረግን ያለነው እንቅስቃሴ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘት ላይ ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት አዲስ እሳቤ በሆነው የመደመር ፍልስፍና በመመራት ሀገር ያላትን ሀብት፣ ልምድና ዕውቀት ከህዝባችን ጋር በመሆን ቁርጠኛና በሳል አመራር በመስጠት ፣ ፈጣሪም አግዞን በበርካታ ችግሮች ውስጥ ሆነን አስደናቂ ለውጦችን አስመዝግበናል፡፡ በ2018 ዓመተ ምህረትም የኢሬቻ እሴቶች የሆኑትን ሰላም፣ ምህረትና አንድነትን አጥብቀን በመያዝ የአገራችንን ማንሠራራት ለማረጋገጥ በፈተናዎች ሳንበገር ተግተን እንድንሠራ አደራ ለማለት እወዳለሁ፡፡

በድጋሚ የመከናወን ኢሬቻ ይሁልን እላለሁ! መልካው ሰላም ይሁን! ገዳው የጥጋብና የስኬት ይሁን! ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ፣ በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ!
መስከረም 23፣ 2018ዓ.ም

እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ!

ዘንድሮ የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት የምናከብረው የተነገረው የተስፋ ቃል መድረሱን፣ የለውጥ ብርሃን መፈንጠቅ መጀመሩን፣ የመሻገር ዘመን መቅረቡን እያመንን ነው። ጉዟችን በውጣ ውረድ የተሞላ ነበር፤ ተስፋ አስቆራጭ መከራዎችን አስተናግደናል። ከእንግዲህ ፈተናው ጨርሶ አይጎበኘንም ባንልም፣ ተስፋችን የሚወለድበት የዋዜማው ዕለት ላይ ደርሰናል። የፍዳው ዘመን ላይመለስ ተሸኝቶ፣ የማንሠራራት ዘመን እንደመጣ በልበ ሙሉነት መናገር እንችላለን።

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ትናንትን የዋጀ፣ ነገን የታደገ ነው። ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት የተከናወነው ሁሉ ዋጋ ያገኘው በክርስቶስ መወለድ ምክንያት ነው። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው የሰው ልጅ ሕይወት ቀና የሆነው በክርስቶስ ምክንያት ነው። ክርስቶስ በትላንትና እና በነገ መካከል “ዛሬ” ሆኖ ሁለቱን አስታርቋቸዋል። ለዚህ ነው የክርስቶስን መወለድ በታላቅ ክብር የምናከብረው።

ክርስቶስ ባይወለድ ኖሮ ትንቢት የተናገሩ ነብያት፣ መሥዋዕት ያቀረቡ ካህናት፣ ቃል ኪዳን የተቀበሉ አበው፣ ተስፋ ያደረጉ የሰው ልጆች ሁሉ ሥራቸው ታሪክ ብቻ ሆኖ ይቀር ነበር። ዋጋ ከፍሎ ህያው ያደረጋቸው ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ባይወለድ ኖሮ የሰው ልጅ ወደፊት የሚያከናውናቸው የሥልጣኔ፣ የጽድቅ እና የበጎነት ሥራዎች ሁሉ የደኅንነት ቅኝት አይኖራቸውም ነበር። ትላንትን የቀደሰው፤ ነገንም የዋጀው፣ ዛሬ የተወለደው ክርስቶስ ነው።

ይሄንን ታላቅ ትምህርት እናስተውል ዘንድ ይገባናል። ትናንት የቱንም ያህል ታላቅ ታሪክ፣ ታላቅ ቅርስ እና ታላቅ ዕሴት ቢኖረንም ዛሬያችን ከተበላሸ ዋጋ የለውም። ባቢሎን እና ፋርስ፣ አቴና እና ሮም፣ ሱሜር እና ሜሶፖታምያ - ዛሬ በጥንቱ ክብራቸውና ታላቅነታቸው የሉም። እነርሱ ትናንት ነበራቸው። ያጡት ዛሬን ነው። ዛሬን በማጣታቸው ደግሞ ትላንታቸው ትዝታ፣ ነጋቸው ሕልም ሆኗል። ትውስታ እንጂ እመርታ የላቸውም።

ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ነበረች። የታላላቅ ሥልጣኔዎች ሀገር ነበረች። የታላላቅ መንግሥታትና የታላላቅ ሕዝቦች ሀገር ነበረች፤ የታላላቅ ባህሎች እና የአስደናቂ ቅርሶች ሀገር ነበረች። ጥያቄው “ዛሬስ” የሚለው ነው። ዛሬ በድህነት፣ በኋላ ቀርነትና በረሃብ የምንሰቃይ ከሆነ፣ ታሪካችንን አልዋጀነውም ማለት ነው። ትናንትን የሚዋጀው ዛሬ ነውና። ትናንት የሚቃኘውና የሚተረጎመው በዛሬ መንፈስ ነው። የዛሬ ከፍታ ትላንትን ጨምሮ ከፍ ያደርገዋል። የዛሬ መዋረድ ደግሞ ትላንትን ጨምሮ ያወርደዋል።

የሀገራችንን ታላቅነት የሚገነዘብ ትውልድ አሁን ተፈጥሯል። ትውልዱ የድህነትን በትር ደጋግሞ ቀምሷል፤ የኋላቀርነትን አስቀያሚ መልክ እስኪበቃው አይቷል። የትናንት ስሕተት ያስከተለውን ፍዳ ትከሻው እስኪጎብጥ ለመሸከም ተገድዷል። የመልክዓ ምድር እሥረኝነት ዓይን አፍጥጦ፣ ጥርስ አግጥጦ ሲመጣ የታዘበ ትውልድ ነው። የችግሩን ልክ መዝኖ መረዳት ብቻ ሳይሆን የመሻገሪያ መርከቡን መገንባት የሚያውቅ ትውልድ ነው። የትናንት ኩስመናን በዛሬ ትጋት እንደሚያሸንፉ የሚያምኑ ዜጎች ቁጥራቸው በጨመረ ቁጥር የነገ ቁመናችን እንደሚሻሻል ጥርጥር የለውም።

የነቢያት ጽድቅና ትንቢት የቀጠለው የነቢያት አምላክ ክርስቶስ ትንቢታቸውን ፈጽሞ ስለተወለደ ነው። የትንቢት መጻሕፍት ዋጋ ያገኙት በወንጌል መጻሕፍት የተነሣ ነው። ብሉይ ኪዳን ጥቅም ያገኘው በሐዲስ ኪዳን ምክንያት ነው። ሁሉንም ትናንቶች የዋጀቸው ዛሬ ነው። ትላንታችን ዋጋ እና ክብር እንዲኖረው ከፈለግን ዛሬ ተግተን እንሥራ። ብዙ ጊዜያችንን በትላንት ትዝታ እና ትውስታ ውስጥ ከምናሳልፍ፣ በዛሬ ትግልና ውጣ ውረድ ላይ እናጥፋ። ዛሬያችን የተስተካከለና የተቃና ከሆነ፣ ያለ ጥርጥር ትላንትናችን ተገቢውን ክብር ያገኛል።

ክርስቶስ ባይወለድ ኖሮ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው ዘመን አዲስ ዘመን አይሆንም ነበር። “ነገን ለመተንበይ የተሻለው መንገድ፣ ነገን ራሱን መፍጠር ነው” ይባላል። የሰው ልጆችን ነገ ክርስቶስ ጀመረው፤ ክርስቲያኖች ደግሞ ተራመዱበት። ዛሬ የተሻለ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ነገን የተሻለ አድርገው ይፈጥሩታል። ዛሬን በዋዛና በፈዛዛ፣ በክፋትና በሤራ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ ነገን የባሰ አድርገው ያበላሹታል።

የኢትዮጵያ ነገ በዛሬ ሥራና ተጋድሎ እንጂ በዛሬ ምኞትና መሻት ብቻ አይመጣም። አንዳንዶች የኢትዮጵያን ነገ ለማበላሸት ዛሬ በክፋት ሥራዎች ተነክረዋል። እኛ ግን የኢትዮጵያን ነገ ለማቅናት ስንል ነገን በሚዋጁ ሥራዎች ተጠምደናል። ነገን የሚዋጀው ዛሬ መሆኑን ስለምናውቅ፣ ነገን ተቀምጠን አንጠብቀውም። ሠርተን እንደርስበታለን እንጂ።

ከቤተልሔም በረት እስከ ቀራንዮ አደባባይ የሰው ልጆች ትላንት ሲቀደስ፣ የሰው ልጆች ነገ ሲሠራ መልከ ብዙ ምላሽ ነበረው። የተኙ ነበሩ። የናቁ ነበሩ። ገዳዮች ነበሩ። አሳዳጆች ነበሩ። ሤረኞች ነበሩ። ወሬኞች ነበሩ። አደናቃፊዎች ነበሩ። ነቃፊዎች ነበሩ። በሌላ በኩል ደግሞ ገብቷቸው የተከተሉ፤ ነገን ለመሥራት የተባበሩ፤ እውነት ለመንገር የደፈሩ፤ ለእውነት ለመሠዋት የቆረጡ፤ ጥቂቶች ቢሆኑም ብዙዎችን ለማፍራት የሚተጉ ነበሩ።

የኢትዮጵያ ነገ ሲሠራም ምላሹ ልዩ ልዩ ነው። የሚያሸንፉት ግን ተግተው የሚሠሩት ናቸው። ቪክቶር ሁጎ “ጊዜው የደረሰን ሐሳብ ለማስቆም የሚችል ኃይል በዓለም ላይ የለም” ብሎ ነበር። የኢትዮጵያ ብልጽግና ጊዜው የደረሰ ሐሳብ ነው። ማንም ሊያስቆመው አይቻለውም። የኢትዮጵያ ታላቅነት ጊዜው የደረሰ ሐሳብ ነው። ሊገታው የሚችል ምንም ኃይል የለም።

እኛ ዛሬ የቆምነው በትናንት እና በነገ መካከል ነው። ትናንትን በዛሬ ሥራችን ዋጋ እንዲያገኝ እናደርገዋለን። ነገን ደግሞ በዛሬው ሥራችን አሣምረን እንገነባዋለን። የክርስቶስን የልደት በዓል ይሄንን ታሪካዊ ኃላፊነታችንን እያሰብን እናከብረዋለን።

በድጋሚ መልካም የልደት በዓል ይሁንልን!! ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ታኅሣሥ 28፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን!

በክርስቲያኖች ዘንድ ጥምቀት አንድም የመገለጥ፣ ሁለትም የእርቅና ዳግም የመወለድ ምልክት ነው፡፡ በቀደመው ዘመን አዳምና ሔዋን በፈጸሙት ሐጥያት የሰው ልጅ ከአምላኩ ተቀያይሞ የፍዳ ዘመናትን አሳልፏል፡፡ ዳሩ ግን ሰው በሐጥያቱ ልጅነቱን ቢነጠቅም እስከወዲያኛው ጠፍቶ አልቀረም፤ አባቱን ያስከፋ ሥህተት ቢሰራም እስከመጨረሻው ተረግሞ አልኖረም፡፡ አጥቶ የነበረውን የልጅነት ጸጋ በክርስቶስ ዳግም ተቀብሏልና፡፡ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ የተገኘው እሱ ራሱ ሐጥያት ኖሮበት አይደለም፤ ይልቁንም በሐጥያት እድፍ ለቆሸሸው የሰው ልጅ የእርቅ መንገድ ለመሆን እንጂ፡፡

ሥርዓተ-ጥምቀቱን ስናከብር የጥፋት መፍትሔው ይቅርታ፣ የጸብ መድሃኒቱ እርቅ እንደሆነ እያሰብን መሆን አለበት፡፡ ጸብ አይቀሬ ተፈጥሯዊ ሁነት ነው፡፡ በአባትና በልጅ፣ በፈጣሪና በፍጡር፣ በሕዝብና በሕዝብ መካከል ጸብ ይኖራል፡፡ ነገር ግን ይቅርታና እርቅም አይቀሬ የተፈጥሮ ሁነቶች ናቸው፡፡ ጸብ በአንድ አጋጣሚ የሚከሰት ድንገቴ ክስተት እንደሆነ ሁሉ፤ እርቅ ደግሞ ልዩ ልዩ ሁነቶችን ያቀፈ ጊዜ ወሳጅ ሂደት ነው፡፡ በፈጣሪና በሰው ልጅ መካከል የተፈጠረው የጸብ ግድግዳ መፍረስ የጀመረው በቃል ነው። አምላክ “ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ” ብሎ ሲናገር የእርቅ ሂደቱም ያኔ ጀምሯል፡፡ የተቋጨው ግን ክርስቶስ በቤተልሄም ተወልዶ፣ በዮርዳኖስ ተጠምቆ፣ መስቀሉን ተሸክሞ ከተሰቀለ በኋላ ነው፡፡

በአምላክና በሰው ልጅ መካከል የተፈጠረው ጸብ በክርስቶስ ፍጻሜውን እንዳገኘ ሁሉ፤ እንደ ሀገር ያሉብንን አለመግባባቶች በጠረጴዛ ዙሪያ ልንፈታቸው፣ የዘመናት የልዩነት እዳዎቻችን ፍጻሜ ሊያገኙ ከጫፍ ደርሰናል፡፡ የሀገራዊ ምክክር ኮምሽኑ ከተቋቋመ ወዲህ ባለፉት ሦስት ዓመታት ሰፊ ቁጥር ያላቸው ዜጎቻችን የተካፈሉበት፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፉ እና የልዩነት አጀንዳዎችን ያሰባሰቡ ሰፋፊ መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡ ተቃርኖዎቻችን በዘላቂነት መፍትሔ የሚያገኙት በምክክራችን ፍጻሜ ነውና እንደሂደቱ ሁሉ ለፍጻሜው ርብርብ እንድናደርግ በዚሁ አጋጣሚ አደራ እላለሁ፡፡

ሥርዓተ-ጥምቀቱ የመገለጥም ምልክት ነው፡፡ ከጥምቀቱ እለት በፊት ክርስቶስ የሚታወቀው በጥቂቶች ብቻ ነበር። በልደቱ የተገለጠውን ብርሃን ለማዳፈን የሞከሩ ሄሮድስን የመሰሉ አካላትም የተሳካላቸው መስሏቸው ነበር። ከሠላሳ ዓመታት በፊት በቤተልሔም የታየው የሰው ልጅ ተስፋ መልሶ የጠፋ መስሎም ነበር። ታይቶ እንደሚጠፋ ኮከብ፤ መጥቶ እንደሚሄድ ዘመን፣ ተከሥቶ እንደሚሠወር መብረቅ የቆጠሩትም ነበሩ።

በጥምቀት ዕለት ግን እውነት ለዓለም ሁሉ ተገለጠች። ከሰማይ እና ከምድር ምስክር መጣ። እንደ ቤተልሔም በጥቂቶች ፊት ብቻ ሳይሆን፣ በአደባባይ በብዙዎች ፊት ተገለጠ። “እርሱን ስሙት” የሚለው ቃልም ከሰማይ መጣ። ከዚህ በፊት ለእረኞች ብቻ ነበር የተነገረው። ዛሬ ግን ጆሮ ላላቸው ሁሉ ተነገረ። ያኔ በበረት ውስጥ ነበር፤ አሁን ግን በሄኖም ሸለቆ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ፣ በዓለም ፊት ሆነ።

ጊዜው ደርሶ የተገለጠ ነገር በዓላማው ፈጻሚዎች እና በዘናው ሰሚዎች መካከል የተለያየ አካሄድ አለው። የዓላማው ፈጻሚዎች ከየት፣ ለምን፣ እንዴት እንደመጣ ያውቃሉ። ወዴት፣ እንዴት እንደሚሄድ ይረዳሉ። ለምን ዓይነት ግብ እንደመጣ ይገነዘባሉ። ስለዚህም ምንም ዓይነት መሥዋዕትነት ለመክፈል ይዘጋጃሉ። አንድ ሆኖ የበራው ሻማ፣ ቀስ እያለ እልፎችን ሲያቀጣጥል ይታያቸዋል። በደመናት ውስጥ የፈነጠቀው ፀሐይ፣ ቀስ እያለ ደመናውን ሲገላልጥ ይታያቸዋል። ከአንድ እንጨት የተለኮሰው እሳት፣ ቀስ እያለ ሲንቦገቦግ ይታያቸዋል።

ዜናውን የሚሰሙት ግን እንደዚያ አይደሉም። ሂደቱን የሚገመግሙት ባገኙት መረጃ መሠረት ብቻ ነው። ዜናው የቀዘቀዘ ሲመስላቸው ጠፍቷል ብለው ያምናሉ። ዜናው የሞቀ መስሎ ሲሰማቸው ደግሞ አለ ብለው ይገምታሉ። የነገሩን መነሻ፣ ሂደትና ግብ በቅርበት አያውቁም። በቤተልሔም የሉም፤ በዮርዳኖስ አልቆሙም። አየን ያሉ ይነግሯቸዋል፤ ሰማን ያሉ ያወሯቸዋል። በዚህም የተነሣ ውሳኔያቸውና ብያኔያቸው በዕለት ክሥተት ላይ የተመሠረተ ነው። ክርስቶስ በሚያስተምርበት ወራት በየተአምራቱ፣ በየክሥተቱና በየኩነቱ ይገኙ እንደነበሩ ሰዎች ዓይነት። በጥብርያዶስ ዳር ሲመግባቸው “እናንግሥህ” ይላሉ፤ በጲላጦስ አደባባይ ሲቆም “ስቀለው” ብለው ይፈርዳሉ።

ዛሬ በዚህ የበዓሉ መንፈስ ውስጥ ሆነን የኢትዮጵያን የመገለጥ ጉዞ እንድንመረምር እጋብዛለሁ። የኢትዮጵያ ዕሴቶች፣ የኢትዮጵያ ሀብቶች፣ የኢትዮጵያ አቅሞች፣ የኢትዮጵያ ክንዶች፣ የኢትዮጵያ ውበቶች፣ የኢትዮጵያ ክብሮች፣ የኢትዮጵያ ከፍታዎች - እየተገለጡ ናቸው። ለውጡ ከመጣ ጀምሮ ላለፉት ጥቂት ዓመታት መሠረቱን ስንሠራ ነበር። የብሉዩን ዘመን ስናድስ፣ የሐዲሱን ዘመን ስንረስስ ነበር። የኦሪቱን ዕዳ ስንደመስስ፣ የሐዲሱን ምንዳ ስናስስ ነበር። የያዘንን ትብታብ ስንበጥስ፣ የለያየንን ግንብ ስናፈርስ ነበር። የፈነጠቀው እስኪፈካ፣ የተወጠነው እስኪሳካ ጠብቀን ነበር። ያልገባቸው እስኪረዱ፣ የገባቸው እስኪራመዱ ዕድል ሰጥተን ነበር።

አሁን ያ ሁሉ አልፎ የኢትዮጵያ የመገለጥ ዘመን መጥቷል። የግብርና አቅሟ ተገልጦ ሕዝቦቿን ይመግባል። የማዕድን ዐቅሟ ተገልጦ ዕድገቷን ያፋጥናል። የቱሪዝም ዐቅሟ

ተገልጦ ዓለምን ያስደምማል። የቴክኖሎጂ ዐቅሟ ተገልጦ ልማቷን ያቀላጥፋል። የዲፕሎማሲ ዐቅሟ ተገልጦ ተጽዕኖ ፈጣሪነቷን ያጸናል። የአምራችነት አቅሟ ተገልጦ የዓለምን ገበያ ይሻማል።

አሁን የኢትዮጵያ ምስክሮች ከላይም ከታችም እየተሰሙ ናቸው። በቤተልሔም ለጥቂቶች ተገልጦ የነበረው የኢትዮጵያ ታላቅነት፣ ዛሬ በዮርዳኖስ ለዓለም ሁሉ እየታየ ነው። ከእንግዲህ የተገለጠችውን ኢትዮጵያን መስማት የግድ ነው። በዮርዳኖስ ስንገለጥ እያዩ በምኩራብ የቀሩት አካላት ብዙ ቢናገሩ አይገርመንም። እኛ የሐዲስ ሰዎች ነን። ብዙ ነገሮችን ቀይረናል፤ አድሰናል። እነርሱ የኦሪት ሰዎች ናቸው። ባልታደሱ ጎዳናዎቻቸው፣ ባረጁ ከተሞቻቸው፣ በደከሙ ቅጥሮቻቸው ውስጥ ይኖራሉ። ኢትዮጵያ እንደሆነች ከቤተልሔም ወደ ዮርዳኖስ፤ ከዮርዳኖስ ወደ ቆሮንጦስ - ከቆሮንጦስ ወደ ደብረ ታቦር - ከደብረ ታቦር ወደ ቀራንዮ - ከቀራንዮ ወደ ደብረ ዘይት እያለች መጓዟን ትቀጥላለች። ከእንግዲህ እያረገች ትሄዳለች እንጂ ወደ አሮጌ መንደሮቿ አትመለስም። የፈርዖን አስማተኞች የሚፈጥሩት አስማትና መተት ከእንግዲህ አያስፈራትም። ባሕር እንዴት እንደሚከፈል በዮርዳኖስ አይታለችና።

ይህ ዘመን ያለ ጥርጥር የኢትዮጵያ ዘመን ነው። ከኢትዮጵያ እውነት ጋር የሚራመዱ ሁሉ ከኃይል ወደ ኃይል ይራመዳሉ። ይሄን የተረዱ ብዙዎች ከውጭም፣ ከጫካም ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ነው። ኢትዮጵያም እየተቀበለቻቸው ነው። የቀሩት ብዙዎች ደግሞ የጊዜ ጉዳይ እንጂ እንደሚመጡ እናምናለን። ከጥፋት ልጅ በቀር ማንም ከኢትዮጵያ እውነት አይቀርም።

እምነታችን፣ ሥርዓታችን፣ ባህላችን፣ ቋንቋችን፣ ዜማችን፣ በአጠቃላይ ጎብረ ብሔራዊ አንድነታችን በአደባባይ ለሚገለጥበት የኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል በድጋሚ እንኳን አደረሳችሁ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ጥር 10፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለ130ኛው የዐድዋ ድል በዓል አደረሳችሁ!

የዐድዋ ድል የኢትዮጵያውያንን የማይቀየር ዐቅምና ዐቋም ያሳየ ድል ነው። ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ብሔራዊ ጥቅም፣ ነጻነትና ሉዓላዊነት ላይ የማይቀየር አቋም አላቸው። ይሄንን አቋማቸውን በጽኑ መሠረት ላይ ለመትከል ደግሞ ሁሉንም አቅማቸውን ይጠቀማሉ። ሥርዓታትና መሪዎች ሊቀያየሩ ይችላሉ፤ በአንዳንድ ጉዳዮች ልዩነቶች ይኖሯቸው ይሆናል፤ ስለ ሀገራቸው ያላቸው አቋምና ለሀገራቸው የሚያወጡት ዐቅም ግን አይቀየርም።

ወደ ዓድዋ የዘመቱ ጀግኖቻችን ሁሉ በሁሉም ነገር የተስማሙ አልነበሩም። አንድ ዓላማ ነበራቸው እንጂ አንድ ዓይነት አልነበሩም። አንድ ሀገር ነበራቸው እንጂ አንድ ባሕልና እምነት አልነበራቸውም። በዚያ ጊዜ ሀገራቸውን ከድተው ከጠላት ጋር ያበሩ ባንዳዎች ነበሩ። ለጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ ዘላቂ የሀገራቸውን ጥቅም የሸጡ ምንደኞችም ነበሩ። ከባዳ ጋር ወግነው ወገናቸውን ያስጣሙ ደላሎችም ነበሩ።

ጀግኖች እናቶቻችን እና አባቶቻችን የተዋጉት ከወራሪው የጣሊያን ጦር ጋር ብቻ አልነበረም። ከባንዳዎች፣ ከምንደኞች እና ከሀገር ደላሎች ጭምር እንጂ። አርበኝነት ማለት ባዳና ባንዳን ማሸነፍ ማለት ነው። አርበኝነት ማለት ለሀገር ጥቅም ሲባል የግል ጥቅምን ማሸነፍ ማለት ነው። አርበኝነት ማለት ለሀገር ክብር ሲባል የራስን ክብር መሰዋት ነው። የዓድዋ ድል በዓል እነዚህን ሁሉ የምናስታውስበት ነው። የዓድዋ ድል በዓል የኢትዮጵያውያንን አቅምና አቋም እንደገለጠው ሁሉ ዛሬም በጸና አቋም ፣ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ አቅም የምንገልጥበት ጊዜ ነው። በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም፣ በማዕድን እና በዲጂታል ሀገራችን ያላትን አቅም መግለጥ አለብን። የዓድዋን ድል በሁሉም ዘርፍ ለመድገም የኢትዮጵያ አቋም ጽኑ መሠረት ሊኖረው ይገባል።

ሀገርን አቅም ያሳድጋታል፤ አቅም ይገነባታል። ሀገርን አቅም ይሰራታል፤ አቋም ያጸናታል። ሀገርን አቅም ያራምዳታል፤ አቋም ያሻግራታል።

የዓድዋ ድል በዓላችን የኢትዮጵያን አቅም ይበልጥ የምንገነባበት፤ የኢትዮጵያውያንን አቅም ይበልጥ የምናጸናበት እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
የካቲት 22፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል አደረሳችሁ፤ አደረሰን!

በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ ዒድ አል ፈጥር የበረከት በዓል ተደርጎ ይታመናል። የመዳንም የአላህ (ሱወ) ደግነት የሚገለጥበት፤ ውድ ስጦታዎችን ለሰው ልጆች የሰጠበት ወር ነው። ቁርዓን ወደ ምድር የወረደበት፤ ጀሃነም ተዘግቶ የጀነት በሮች የሚከፈቱበት፤ ሁሉም እንደ እምነቱ ጽናትና እንደ አላህ (ሱወ) አዛኝነት ምህረቶችን የሚያገኙበት ወቅት በመሆኑ ሕዝበ ሙስሊሙ ዘወትር የረመዳንና ዒድ አል ፈጥርን በጉጉት ይጠብቃል።

በዒድ አል ፈጥር ከፈጣሪ በረከት የሚቸራቸው የረመዳን ወር በፆምና በዱዓ ያሳለፉ ናቸው። በበዓሉ መምጣት የሚደሰቱትም ረመዳንን በመልካም ተግባር ለማሳለፍ የበረቱ ናቸው። የተቀደሰው ወር ከክፉት የተቆጠቡ፤ ለድሆችና አቅመ-ደካሞች ዘካት የሰጡ፤ የበደሏቸውን ይቅር ለማለት የደፈሩ፤ በሐሴትና በመንፈሳዊ ኃይል ተሞልተው ለዒዱ ይደርሳሉ። በተቃራኒው ለዱዓ የሰነፉና ለመስጠት የሰሰቱ ከፈጣሪ በረከት አያገኙም። ከፊታችን ግንቦት ላይ የሚካሄደው ምርጫ ሀገራችን የዴሞክራሲ ድል የምትቀዳጅበት፤ ወደ ቀጣይ ብሩህ ዘመንዋ የምትሸጋገርበት በር ነው። እንደ ሀገር ለዓመታት ዴሞክራሲን ስንናፍቅ ኖረናል። ጉዟችን አልጋ በአልጋ አልነበረም። ነገር ግን ከፈተና በሁዋላ በረከት፤ ከብርታት በኃላ ሐሴት እንዳለ ከረመዳን ፆምና ከዒድ አል ፈጥር በዓል እንማራለን።

መልካም የዘራ ሰው መልካም ምርት እንደሚያጭድ ሁሉ፤ እሾህ የዘራውም አሜኬላ ያበቅላል። ስለተመኘን ብቻ አሜኬላው በመልካም ሰብል አይለወጥም። በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ ጉዳዮች ውስጥ ዘርና ምርት የተቆራኙ ናቸው። ስለዴሞክራሲም ስና ስብ ይህንን ሐቅ መዘንጋት የለብንም። የምንገነባው ሕጋዊና ሕዝባዊ መንግሥት የሚወሰነው በቅድመ ምርጫ ተሳትፏችን ልክ ነው። ተሳትፏችን ከጠየመ ዴሞክራሲያችንም ይጠይማል። ደካም ተሳትፎ አድርገን ጠንካራ ዴሞክራሲ ለማዋለድ መመኘትም ሞኝነት ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በባዶ መሬት አይበቅልም፤ በግጭትና ሥርዓት አልበኝነትም አይገነባም። ይልቁንም ስክነትን፤ ለትብብርና ቅንጅት ልብን ክፍት ማድረግን፤ በጨዋታው ሕግ መመራትን ይጠይቃል።

ረመዳን ቤተሰብ የሚገናኝበት፤ ጎሊና የሚሰበሰበበት ፤ ሰውነት የሚገራበት እና መንፈስ የሚቀናበት ወር ነው። ዒድ አል ፈጥር ደግሞ የሰው ልጅ ጤናማ ግንኙነቶች የሚያመለክት በዓል ነው። የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር፤ ከራሱ ጋር እና ከወገኑ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ ጠቅላላ ሕይወቱ ጤናማ አይሆንም። በረመዳን ወቅት ፆሙ ሰዎችን ከራሳቸው ጋር ያገናኛቸዋል። ሰላትና ዱአ ደግሞ ከፈጣሪያቸው ጋር

ያገናኛቸዋል። አፍጣርና ዘካት ደግሞ ከማህበረሰቡ ጋር ያገናኛቸዋል። ኢትዮጵያውያን ጤናማ ሕይወትን መምራት እንድንችል እነዚህን ሦስቱን ጤናማ ማድረግ አለብን።

ሰው ከፈጣሪው እና ከራሱ ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ ለማህበረሰቡም ለሀገርም ጠንቅ ነው። ሰው ከራሱ ጋር እየተጋጨ ከኖረ ከሁሉም ጋር ይጋጫል። ዛሬ ጦርነትን ባህል፤ ዝርፊያን ልማድ፤ ጥፋትን ዕሴት፤ ውድመትን ክብር አድርገው የሚኖሩት ሰዎች የመጀመሪያው ችግራቸው ከፈጣሪያቸውና ከራሳቸው ጋር አለመስማማት ነው። ውስጣዊ ባህሪያቱ ያልተስማሙለት ሰው ከማንም ጋር አይስማማም። ዕርቅ፤ ሰላም፤ ፍቅር፤ ይቅር፤ መግባባት እና መስማማት የሚባሉት ነገሮች አይገቡትም።

ሰው ከፈጣሪውና ከራሱ ጋር ከተስማማ፤ ከማንም ጋር መስማማት ይችላል፤ ከእንስሳትም ጋር ሳይቀር። “ለድንቢጥ እንኳን ቢሆን የራራ ሰው፤ በፍርድ ቀን (ቂያማህ) አላህ ይራራለታል” ሲሉ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያስተማሩት ለዚህ ነው።
የእስልምና ዋናው መሠረቱ ሰላም የሆነው ለዚህ ነው። ሰላም ማለት ከራሱ ከአካባቢ ጋር በጤናማ ግንኙነት ለመኖር መቻል ማለት ነውና።

የዘንድሮውን የዒድ በዓል ስናከብር በዓለማችን ስለ ሰላም የሚነገረውን ያህል የዓለም ህዝቦች በሰላም መኖር ለምን አልቻሉም ብለን እንጠይቅ? የግጭትና የጦርነት ድንጋይ እየደጋገመ ለምን ይመታናል? ከአዛኝ ይልቅ ገዳይን እንደ ጀግና የሚያየው ልምምዳችን ለምን ገናና ሆነ? የሰው ልጅ ከግጭትና ከጦርነት ያተረፈው ድህነትና ኋላ ቀርነት መሆኑን እያየን ለምን አልተማርንም? ሠልጥኗል በምንለው ዓለም የሚኖሩ ወገኖቻችን እንዴት ግጭትንና ጦርነትን የሚያበረታቱ ሆኑ? ይህ ትውልድ እነዚህን ጥያቄዎች በሚገባ አጢኖ ምላሽ ሊያገኝላቸው ይገባል።

ከራሳቸው ጋር ሰላም ያጡ አካላት የማህበረሰቡን ሰላም እንዲረብሹ ልንፈቅድላቸው አይገባም። ከረመዳን ዕሴቶች ጋር የተጣሉ ሰዎች ዘመኖቻችንን እንዲረብሹ ልንፈቅድላቸው አይገባም። በዐሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መኖር ቀደሞ መገኘት ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንደ ዐሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን መኖር ግን መረገም ነው። መግደል፤ ማገት፤ የገበሬውን እርሻ ማቃጠል፤ ሴቶችን መድፈር፤ ማህበራዊ ተቋማትን መመዝበር፤ ቅርጽና ታሪክን ማበላሸት፤ መመንጠር፤ ጠመንጃን የሁሉም ነገር መድኃኒት አድርጎ መውሰድ፤ እነዚህ ሁሉ ከ800 ዓመታት በፊት ያነበሩ የሰው ልጅ ጠባያት ናቸው።

ዜጎች ሲሰማሙ የብልጽግና ጉዞዋ ይሰምራል። የኢትዮጵያም መበልጸግ የሌላ ሳይሆን የእኛ መበልጸግ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ እንድትበለጽግ የሚፈለግብን መስዋዕትነት ሁሉ የመክፈል ኃላፊነት የእኛ ነው። የእኛ ልፋት ከዛሬ አልፎ ለትውልድ ይተርፋል። ሀገር መውደዳችን የሚታወቀው እና መልካም ዜግነታችን የሚገለጠው በሥራችን ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) “ምርጥ ሰዎች ማለት ሌሎችን ለመጥቀም የበረቱ ሰዎች ናቸው” ብለው ያስተማሩትም ለዚህ ነው። ይሄን የሚድ አል ፊጥር በዓል እነዚህን መልካም ዕሴቶች እያሰብን፤ ሦስቱን ጤናማ መስመሮችንም እያጸናን እንድናከብረው አደራ እላለሁ።

በድጋሚ መልካም የሚድ አል ፊጥር በዓል ይሁን! ዒድ ሙባረክ! ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
መጋቢት ፲፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል አደረሳችሁ፤ አደረሰን!

የትንሣኤ በዓል በክርስቲያኖች ዘንድ ልዩ ቦታ ያለው በዓል ነው። ሞት የተሻረበትና ሕይወት ዋስትና ያገኘበት ነው። ከሞት ባሻገር ሕይወት፤ ከመቃብር ባሻገር ትንሣኤ መኖሩ የታወጀበት ነው። ሞት መጨረሻ፤ መቃብር መድረሻ አለመሆናቸው የተረጋገጠበት ነው። በአዳም ምክንያት ወደ ምድር የወረደው ሰው፤ በክርስቶስ ምክንያት ወደላይ የወጣበት ነው።

የዘንድሮውን ትንሣኤ የምናከብረው ሀገራችን ኢትዮጵያ በሚያልፍ ፈተና ውስጥ እንዳለች እያሰብን ነው። መንገዳችን ረጅም፤ ጉዟችን ፈታኝ መሆኑን እናውቃለን። ብርሃን እንዳናይ የሚጋርዱ፤ በጥልቁ ጨለማ ጠፍተን እንድንቀር አሥረው ለመያዝ የሚሞክሩ ወጥመዶች ብዙ ናቸው። ወደ ተስፋ ምድር እንዳንሻገር የሚጎትቱ ሰበቦች ሞልተዋል። ዳሩ ግን ከሕማማቱ ወዲያ ትንሣኤ፤ ከዕንቅፋቱ ባሻገር ስኬት እንደሚጠብቀን አምነን እንታገላለን።

በትንሣኤው ዋዜማ፤ እርግጠኞች፣ ተስፈኞች፣ ተስፋ ቆራጮች፣ ወሬኞች፣ ተስፋ አስቆራጮች፣ ተጠራጣሪዎች ነበሩ። እርግጠኞች የሕማማቱ ፈተና እንደሚያልፍ እርግጠኞች ነበሩ። የዕለተ ስቅለት መከራ፤ ለዕለተ ትንሣኤ ዋዜማ ለመሆኑ እርግጠኞች ነበሩ። የድንጋዩ በር፣ የበሩ ማኅተም እና የመቃብሩ ጠባቂዎች ትንሣኤውን እንደማያሰናክሉት እርግጠኞች ነበሩ። የሚናፈሰው ወሬ እና የሚሠራጨው አሉባልታ እድሜው አጭር መሆኑን እርግጠኞች ነበሩ። እርግጠኞችም ስለሆኑ መስዋዕትነትን ለመክፈል ዝግጁዎች ነበሩ። እውነቱን ለመመስከር ቆራጦች ነበሩ። በመስቀሉ ሥር ለመገኘት ደፋሮች ነበሩ።

ተስፈኞች የእርግጠኞቹን ያህል ሳያዩ የሚያምኑ አልነበሩም። ግን አንዳች መልካም ነገር ይጠብቁ ነበር። የተሰጠውን ትምህርት፣ የተደረገውን ተዓምራት ሰምተዋል፤ አይተዋል፤ አንዳች ነገርም ጠብቀዋል። ነገር ግን ተገቢውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁዎች አልነበሩም። እውነትን ለመድፈር ቆራጦች አልነበሩም። ሐሰቱን ለመጋፈጥ ዐቅም አላገኙም። ቢያንስ ግን አንደበታቸውን ከክፉ ከልክለዋል።

ተጠራጣሪዎች አጥር ላይ የነበሩ ናቸው። በጥብርያዶስ ይበላሉ፤ በጎልጎታ ይክዳሉ። በሆሳዕና ይዘምራሉ፤ በሊቶስጥራ ይሸሻሉ፤ ተአምር ለማየት ይመጣሉ፤ መከራ ለማየት ይሳቀቃሉ፤ ከደስታው አውጡልኝ፤ ከመከራው ጦመኛ ነኝ የሚሉ ናቸው። ተስፋ ቆራጮች በሚያዩትና በሚሰሙት ቶሎ የሚወሰዱ ናቸው። በእውነትና በሐሰት፤ በፍርሃትና በጽናት

መካከል ያለው ድንበር የጠፋባቸው ናቸው። ሕማማቱ ሲመጣ በቶሎ ወደ ትዝታ ገቡ። ሁሉንም ነገር የትናንት ታሪክ ብቻ አድርገው ወሰዱት። ሁሉንም ነገር "ልጡ የተራሰ፤ መቃብሩ የተማሰ" አድርገው ቆጠሩት። ከግራ ከቀኝ የሚሰሙት አሉባልታ፤ ከፊት ከኋላ የሚመጣው ጫጫታ፤ ከወዲህ ከወዲያ የሚመጣው እሳት፤ ከዚህም ከዚያም የሚያዩት መዓት አስፈራቸው። ነገን አስረሳቸው። በዚህ የተነሣ ተስፋ ቆርጠው ወደ ኋላ ተመለሱ። ወሬኞች ድሮም ወሬ ስቧቸው የመጡ ናቸው። ምን አለ? ምን ተባለ? ብለው የተሰባሰቡ ናቸው። የሰሙትንም ያልሰሙትንም፤ የሚያውቁትንም የማያውቁትንም፤ እውነቱንም ሐሰቱንም እያደባለቁ ኢየሩሳሌምን በወሬ ሞሏት። ቢያንስ ከትንሣኤው 15 ዓመት በኋላ ወንጌሉን የጻፈው ማቴዎስ፤ እስከዚያ ዘመን ድረስ ወሬው ብዙ ተቀባይ እንደነበረው ገልጧል።

ተስፋ አስቆራጮች ዓላማቸው ሰውን ሁሉ ከትንሣኤ መንገድ ማራቅ ነበር። እነርሱም አይሄዱ፤ ሰውም አያስኬዱ። ከመጀመሪያው አልተቀበሉትም፤ በኋላም አልፈለጉትም። ብዙ ሰዎች እንደተከተሉት ሲያውቁ ደግሞ ቅናት አቃጠላቸው፤ ክፋት አንገበገባቸው። ክርስቶስን ከሰሱ፤ ራሳቸው ምስክር ሆኑ፤ በመጨረሻም ራሳቸው ፈረዱ። መቃብሩን ዘጉ፤ ጠባቂ አስቀመጡ። በማኅተም አሸጉ። ነገር ያለቀና የተቆረጠ መሰላቸው።
የትንሣኤ በዓል የእነዚህን ሁሉ እውነተኛ ማንነት የገለጠ ነው። እርግጠኞች የቆራጥነታቸው ውጤት በትንሣኤ አገኙ። ተስፈኞች እንዲህ ለሚያልፍ ጊዜ ባለመጽናታቸው አዘኑ። ተስፋ ቆራጮች አሻግሮ ማየት አቅቷቸው ከቦታቸው በመጥፋታቸው ተፀፀቱ። ወሬኞች በትንሣኤው እውነት የተነሣ ያ ሁሉ ወሬ እንደ ናቡከደነፆር ሐውልት ሲፈረካከስ አዩት። ተስፋ አስቆራጮች የገደሉት ክርስቶስ ሲነሣ፤ የዘጉት መቃብር ሲከፈት፤ ያተሙት ማኅተም ሲቀደድ፤ የመደቧቸው ጠባቂዎች ሲሸሹ በዓይናቸው በብረቱ አዩ። ትንሣኤው የሚነገር ሐቅ፤ የሚታይ እውነት ሆነ። ተጠራጣሪዎች ግን አሁንም አጥራቸው ላይ ሆነው ከግራም ከቀኝም ሳይሆኑ ቀሩ።

የኢትዮጵያችንም ነገር እንዲሁ ነው። በኢትዮጵያ ለውጥ እርግጠኞች የሆኑት ዋጋ ይከፍላሉ፤ እርግጠኝነትን ፈርተው ተስፈኞች የሆኑት ቢያንስ አንደበታቸውን ከክፉ ይጠብቃሉ። ተስፋ ቆራጮች ነገን ማየት ስለሚሳናቸው መንገዳቸውን ይቀይራሉ። ወሬኞች አውርቶ አዳሪዎች በመሆናቸው የወሬ እንጀራ ይጋግራሉ። ተስፋ አስቆራጮች "ወተቱን አጥቁረው፤ ማሩን አምርረው" የዋሑችን አታለሏቸው። ተጠራጣሪዎች አንዴ ትኩስ አንዴ ቀዝቃዛ ሲሆኑ፤ ለብ ብለው ቀሩ።

ኢትዮጵያችን ግን ትንሣኤዋን እያየች ነው። መግነዙን ፈትታዋለች፤ መቃብሩን

ከፍታዋለች፤ ማኅተሙን ቀዳዋለች። ወሬኞች ከመቃብር ጠባቂዎች ጋር ተማክረው የሚያወሩትን ወሬ የምትሰማበት ጆሮ የላትም። ትንሣኤዋን አይለውጠውምና። እሷ ከዚህ በኋላ የምትጠብቀው ዕርገትን ነው። የምትጓዘው ኃይል እንደሚወርድላት አረጋግጣ ነው። ወደኋላ መመለስ የለም። ሕማማት አልፏል፤ ዓርብም አልፏል፤ ቅዳሜም አልፏል። ትንሣኤ መጥቷል። በትንሣኤ ሌሊት የተኙ አልሰሙ ይሆናል። በተስፋ አስቆራጮች ተታለው የሄዱ ዜናው አልደረሳቸው ይሆናል። ትንሣኤ ግን እውን ሆኗል።

ከቻላችሁ አጥር ላይ ያላችሁ ውረዱ። ተስፈኞች ርግጠኞች ሁኑ። ተጠራጣሪዎች እመኑ። ወሬኞች ከአፍ ወደ መዳፍ ተለወጡ። ምክንያቱም - ኢትዮጵያ ወደ ትንሣኤ ተቃርባለች። የኢትዮጵያ ትንሣኤ ከሚበሰርባቸው ምዕራፎች አንዱ ግንቦት ላይ የሚካሄደው ምርጫ ነው። ትንሣኤን ያለ ሕማማት እንደማናስበው ሁሉ ዴሞክራሲንም ከውጣ ውረድ ነጥሎ ማየት አይቻልም። በዓለም ላይ በደልዳላ መንገድ ተጉዞ ዴሞክራሲን የገነባ ሀገር የለም። ዴሞክራሲና ብልጽግና ያለ ጽናት አይሳኩም። ከእኛ በፊት ዐመጻውን በትዕግሥት የመከቱ ተሻግረዋል፤ ሑካታውን በጽናት ያለፉ አሳክተዋል። ብንመኝም ፈተናውን አናስቀርም፤ መጽናት ግን እንችላለን። ከድህነት መውጫው ብርታታችን፤ ወደ ዴሞክራሲ መድረሻችን ትዕግሥታችን እንደሆነ አምነን ለኢትዮጵያ ትንሣኤ በሙሉ ልባችን እንትጋ!! በድጋሚ መልካም የትንሣኤ በዓል ይሁንልን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ሚያዝያ 03፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለ85ኛው የጀግኖች አርበኞች በዓል አደረሳችሁ!

ሚያዝያ 27 ቀን ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አርበኞች የፋሽስትን ወረራ የቀለበሱበትና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ሙሉ በሙሉ ያስከበሩበት በዓል ነው። አርበኝነት ማለት ለሀገር ያለ ዋጋ የሚከፈል ከራስ ወዳድነት የነጻ መሥዋዕትነት ነው። ዓላማውም ሀገርንና ሕዝብን ብቻ ማዕከል ያደረገ ነው። ለግል ወይም ለቡድን በተለየ የሚገኝ ነገር የለውም። ለሀገር ከሚገኘው ነጻነት፣ ሉዓላዊነት እና ክብር ከሚደርስ የዜጋ ድርሻ በቀር። እናትና አባት አርበኞች ከፋሺስት ጋር የተዋጉት ለሀገር እና ለወገን ብለው ነው። በግል ጥቅም ለማግኘትማ ከአርበኝነት ይልቅ ባንዳነት አቋራጭ ነበር። ግን አላደረጉትም።

የአርበኝነት ትግሉ ከሦስት ጠላቶች ጋር የተደረገ ነበር። ከራስ ፍላጎት፣ ከባንዳና ከወራሪ ፋሺስት ጋር። አርበኝነት የራስን ጥቅም ለሀገር ጥቅም ሲባል መተው ነው። አርበኝነት የግል ክብርን፣ የግል ሥልጣንን እና የግል ጥቅምን መሠዋት ነው። ይሄንን ለመቀበል ከጠላት በፊት ራስን ማሸነፍ ይጠይቃል። ባንዳዎች ማለት ራሳቸውን ማሸነፍ ያቃታቸው ናቸው። የግል ጥቅምንና ክብርን ማሸነፍ ሲያቅታቸው የሀገራቸውን ክብርና ጥቅም ይሸጣሉ። ባንዳነት ማለት ሀገርን ለራስ ጥቅም በመሸጥ የሚከናነቡት የውርደት ካባ ነው። አርበኞች ከባንዳዎች ጋር ታግለዋል። ባንዳዎች በአንድ በኩል ሀገራችሁን ሸጣችሁ እንደኛ በግል ተጠቀሙ ይሏቸዋል። በሌላ በኩል መንገድ እየመሩ ወራሪውን ያመጡባቸዋል። ያም አልሆን ሲላቸው ሕዝቡን በሐሰተኛ ወሬ ልቡን ይሰልቡባቸዋል።

ዛሬም ሦስቱም ጠላቶች አሉ። መልኩና ስም ብቻ ቀይረዋል። በሌላም በኩል ዛሬም በየመስኩ የተሠማሩ ኢትዮጵያውያን አርበኞች አሉ። የኢትዮጵያ ብልጽግና እንዲሳካ ብሔራዊ አርበኞችን ይፈልጋል። የራስ ፍላጎትን፣ ባንዳነትን እና ወራሪን እምቢ የሚል አርበኝነት። የኢንዱስትሪ አርበኞች፣ የግብርና አርበኞች፣ የጸጥታ አርበኞች፣ የፖለቲካ አርበኞች፣ የንግድ አርበኞች፣ የዲፕሎማሲ አርበኞች፣ የመንግሥት አገልጋይ አርበኞች፣ የሕክምና አርበኞች፣ የትምህርት አርበኞች፣ ወዘተ. ያስፈልጉናል። ይሄንን በዓል የምናከብረው የየራሳችንን የአርበኝነት ደረጃ በመገምገም ነው።

ለኢትዮጵያ ምን ያህል አርበኞች ነን? ዛሬም የግል ፍላጎት የሚያሸንፋቸው ደካሞች አሉ። ሀገርን አፍርሰው የግል ቤት መሥራት የሚመኙ። ትልቁን መርከብ አፍርሰው ትንንሽ ታንኳዎችን ለመሸጥ የሚመኙ። ለቅንጥብጣቢ ነገር ውርደትን ለመሸከም የማይሰቀቁ።

ዛሬም ወራሪዎች አሉ። በአካል ሀገርን ለመውረር ካሰፈሰፉት በተጨማሪ ድህነት፣

ኋላቀርነትና ሌብነት የሚባሉ እንደ ሰርዶ ሀገርን ወርረው ሸባ የሚያደርጉ ጠላቶች አሉ። ሀገርን ለባዳ ከሚሸጡት ባንዳዎች እኩል፣ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የሚሸጡ ባንዳዎች አሉ። አገልግሎትንና የሕዝብን ሀብት የሚሸቅጡ ባንዳዎች አሉ።

ብሔራዊ አርበኝነት ማለት እነዚህን ሦስት ጠላቶች ታግሎ ማሸነፍ ማለት ነው። ዛሬ የምናየውን የኢትዮጵያ ለውጥና እድገት ማስመዝገብ የተቻለው ብሔራዊ አርበኞች በየአካባቢው በመኖራቸው ነው። ብሔራዊ አርበኞች ሦስቱን ጠላቶች እያሸነፉ ቢሆንም ገና ሙሉ በሙሉ ድልን አልተቀዳጁም።

ድሉ እንደ ሚያዝያ 27 የሚታወጀው ኢትዮጵያ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌትስትሆን ነው። ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ከሚገኙ ኃያል ሀገሮች አንዷ ስትሆን ነው። ይሄንን ድል እውን ለማድረግ ኢትዮጵያን የሚወዱ የኢትዮጵያ አርበኞች ሁሉ እንዲነሡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ሚያዝያ 27፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለ1447ኛው የሚድ አል አድሐ በዓል አደረሰን፣

ስለሚድ አል-አድሐ “ዐረፋ” በዓል ስናስብ ሦስት ነገሮች ቀድመው ይታወሱናል። መስዕዋትነት፣ መታዘዝ እና መተጋገዝ። አባት ልጁን ለመስዕዋት ያቀረበበት፤ ልጅ የአባቱን ትዕዛዝ የፈጸመበት፤ ሙስሊሞች የመተጋገዝን እሴት ለዓለም የገለጡበት በዓል ስለሆነ “ዐረፋ” በሕዝበ-ሙስሊሙ ዘንድ ትልቅ ትርጉም አለው።

እስማኤል ለነብዩ ኢብራሒም የመጀመሪያ እና ተወዳጅ ልጃቸው ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ይሄን ተወዳጅና የመጀመሪያ ልጅ እንዲሠዉለት ሲጠይቃቸው ታዘዙ እንጂ ወደኋላ አላሉም። ለመታዘዝ የሞከሩት ነገሩ ቀላል ሆኖ አይደለም። ልጅን ያህል ነገር መስዕዋት ማድረግ ምኑ ይቀላል? የአባትነት ስሜት ይተናነቃል። የሰይጣን ሹክሹክታ ይፈታተናል። የቤተዘመድን ወቀሳ እና የጎረቤትን አስተያየት መቋቋምም ይከብዳል። ነብዩ ኢብራሒም በዚህ ሁሉ አጣብቂኝ ውስጥ አንድ ሐቅ ተገልጦላቸዋል። ከራስ ስሜት፣ ከሰው ሐሜት እና ከወዳጅ ፍላጎት የሚልቅ ታላቅ ዓላማ እንዳለ አምነዋል። ስለዚህም በፈተና ውስጥ ጸንተው ቆሙ፤ ቆራጥነታቸውም በተግባር ታየ።

ሀገር የምትገነባው ከራስ ጥቅም በላይ በሚያስቡ እና ከግላዊ ፍላጎታቸው በላይ ለመፈጸም በቆረጡ ዜጎች ነው። የሚወዱትን ነገር እንኳን ሳይቀር ለመሠዋት ዝግጁ የሆኑ ዜጎች ሲበዙላት ሀገር ትበረታለች። እስማኤላቸውን ለመስጠት የማያመነቱ ዜጎች የሞሉባት ሀገር ጽኑ ናት።

የለመድናቸው፣ የምንወዳቸው፣ የራሳችን ገንዘብ ያደረግናቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ። ከእነዚህ የሚበልጥ ዓላማ ግን አለ፤ እሱም “ሀገርነት እና ሉዓላዊነት” ይሰኛል። ሀገርነት የሚገነባው ከመውሰድ ይልቅ በመስጠት ነው። ሉዓላዊነት የሚጸናው በፈተና ሳይወድቁ በመቆም፤ በወጀብ ሳይናወጡ መጓዝ በመቻል ነው።

የእውነት ኢትዮጵያ ሲያልፍላት ማየት የምንሻ ከሆነ ምኞታችን በተግባር ይገለጥ። የሀገር ኩስመና ካሳሰበን ለግዘፈቷ እንድከም። ያጎበጣትን የድህነት ቋጥኝ ለመሸከም ትከሻችንን እናመቻች። ጎተራዋ እንዲሞላ እጃችን አፈር ይንካ። የጠየመ ገጽዋ እንዲፈካ በሥራ ሌት-ተቀን እንሰለፍ። የተቀማ ክብሯ እስኪመለስ ድርሻችንን እንወጣ። ሀገር መውደዳችን ከልብ ከሆነ መስዕዋት ለመሆን አናመንታ።

የዐረፋ በዓል የመታዘዝና የመስዕዋት ብቻ ሳይሆን የመደጋገፍና የመተጋገዝ በዓል ጭምር ነው። በዐረፋ ከሚከናወነው እርድ አንድ ሦስተኛው ለምስኪኖች እንዲሰጥ የእስልምና

አስተምህሮ ያዛል። በዐረፋ ሕዝበ-ሙስሊሙ ደስታና ሐዘኑን እየተጋራ በዓሉን ያከብራል። የዐረፋ እለት አንድም ሰው ተከፍቶ አያሳልፍም፤ በዐረፋ ሰሞን ማንም ሰው ተርቦና ተጠምቶ አያድርም። በዓሉ ትርጉም የሚሰጠው ሕዝበ-ሙስሊሙ ያለውን ተካፍሎ ሲያከብረው ነው። ሰዎች አስቸጋሪ ሁኔታን የሚሻገሩበት መፍትሔው መተሳሰብና መተጋገዝ እንደሆነ ከዐረፋ እንማራለን። ሀገርም ከፈተናዎችዋ በላይ እንድትሆን እነዚህ እሴቶች ወሳኝ ናቸው።

ዐረፋ ማኅበረሰባዊ በዓል የሚባለው ለዚህ ነው። ሰዎች በግላቸው የሚያከብሩት አይደለም። ቤተሰቡ፣ ጎረቤቱ፣ ሠፈሩ፣ ከተማው የሚያከብረው በዓል ነው። ያላቸውና የሌላቸው፤ የሚችሉና የማይችሉ፤ ታላላቆችና ታናናሾች፤ ባለ ሥልጣናትና ተራ ዜጎች፣ በአንድነት የሚያከብሩት በዓል ነው። ሰው የሚኖረው በቤቱ ውስጥ አይደለም። በማኅበረሰቡ ውስጥ ነው።

ማኅበረሰባዊ ትሥሥርና ትብብር ለዜጎች እና ለሀገር ደኅንነት ወሳኝ ናቸው። ማኅበረሰባዊ ትሥሥር ስለሌሎች እንድናስብ፣ ስለሌሎች እንድንሠራ እና ስለ ሌሎች ዋጋ እንድንከፍል ያደርገናል። ራሳችንን በሌሎች ጫማ ላይ አቁመን እንድናይ ያስችለናል። የሁላችንም ሰላም፣ የሁላችንም ደኅንነት እና የሁላችንም ጥቅም ካልተከበረ በቀር የግላችንን ብቻ ልናስከብር እንደማንችል ያስገነዝበናል። ስለዚህም ማኅበራዊ ግዴታን እንደ ዜግነት ግዴታ ወስደን እንድንሠራ ያደርገናል።ምርጫ ማኅበራዊና የዜግነት ግዴታዎችን ከምንወጣባቸው የዴሞክራሲ መገንቢያ መሳሪያዎች መካከል ዋነኛው ነው። ያለ ሕዝብ ተሳትፎ ዴሞክራሲ አይሳካም። ያለ ምርጫም የሕዝብ ተሳትፎ ምሉዕ አይሆንም። የዴሞክራሲያችን መሰረት ጥንካሬው የሚለካው በተሳትፏችን መጠን ነው።

የዘንድሮ ሀገራዊ ምርጫ ሀገረ-መንግሥታዊ ሥርዓታችን የሚጠነክርበት መሰረት ነው። የዴሞክራሲ ልምምዳችን አንድ ደረጃ ከፍ የሚልበት፤ የቀጣይ ዓመታት የሀገራችንን እጣ-ፈንታ የምንበይንበት፤ ከምንም በላይ ብዝሃ-ድምጽ የሚሰማበት የሕግ መወሰኛ ምክርቤት የምንመሰርትበት ወሳኝ አጋጣሚ ነው። በመሆኑም በዓሉን ስናከብር የዜግነት ግዴታችንን ለመወጣት ብቻ ሳይሆን በካርዳችን ዴሞክራሲያዊ መብታችንን ለማረጋገጥ እየተዘጋጀን እንዲሆን ጥሪዬን አቀርባለሁ። በድጋሚ መልካም የዐረፋ በዓል እንዲሆን እመኛለሁ! ዒድ ሙባረክ!!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ግንቦት 18፣ 2018 ዓ.ም

እንኳን ለ1501ኛው የነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) የመውሊድ በዓል አደረሳችሁ

የነቢዩ መሐመድ ታሪክ ትውልድን ለበጎ ከሚቀርጹ ታሪኮች መካከል አንዱ ነው፡፡ የተጠሩበትን ዓላማ ማክበር፤ ለተጠሩበት ዓላማ ዋጋ መክፈል፤ የተጠሩበትን ለሌሎች ማካፈል፤ የተጠሩበትን አክብሮ መኖር - እነዚህ ሁሉ ሺ መጻሕፍት የሚወጧቸው ትምህርቶች ናቸው፡፡

ነቢዩ የተጠሩበትን ዓላማ በሚገባ ስለተገነዘቡ አክብረው ኖረዋል፡፡ የተጠሩት ለተራና ርካሽ ነገር እንዳልሆነ ተገንዝበዋል፡፡ የተጠሩት ትውልድን ለመቅረጽና ታሪክን ለመቀየር መሆኑን አምነዋል፡፡ ያንንም በቃላቸው፣ በሥራቸውና በኑሯቸው አክብረውት ኖረዋል፡ ። ለታላቅ ሀገራዊ ዓላማ ተጠርተናል ብለን የምናምን ከሆነ ይህ የነቢዩ ሕይወት ታላቅ ትምህርት ይሆነናል፡፡ የተጠራንበትን ዓላማ በንግግራችን፣ በሥራችንና በሕይወታችን እንግለጠው፡፡ነቢዩ ለተጠሩበት ዓላማ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ ከቦታቸው ተሰደዋል፤ ምግብና መጠለያ ተነፍገዋል፤ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተዋል፡፡ ለሞት በሚያበቁ ፈተናዎች ውስጥ አልፈዋል፡፡ ጦርነት ተከፍቶባቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁሉንም በአላህ ኃይል አሸንፈዋል፡፡ ክብር ያለ መከራ አይገኝምና፡፡ እውነተኛ ሰው ለዓላማው እንደ ነቢዩ መሐመድ(ሰዐወ) ዋጋ ይከፍላል፡፡ ዓላማው የሚያስገኘውን ክብርና ጥቅም ብቻ ሳይሆን ዓላማው የሚያስከፍለውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ይሆናል፡፡

ነቢዩ መሐመድ(ሰዐወ) ከአላህ የደረሳቸውን መልእክት ለራሳቸው ብቻ አላስቀሩም። የተጠሩበትን ለሌሎች ለማካፈል ተግተዋል፡፡ መጀመሪያ በጣት ለሚቆጠሩ ሰዎች፣ በኋላም ለቅርብ ሱሐባዎች፣ በመጨረሻም ለዓለም መልእክቱን አዳርሰዋል ፡፡ እሳቸው የዘሩት ዘር እያፈራና እየጎመራ ተጉዟል፡፡ ዓላማችንን እኛ ማወቃችንና ማመናችን ብቻ ጥቅም የለውም፡፡ ሌሎች እንዲያውቁና እንዲያምኑ ልክ እንደነቢዩ ተግተን መድከም አለብን፡፡ የነቢዩን መውሊድ ስናከብር ከሕይወታቸው እየተማርን፤ የተማርነውንም ለሀገረ መንግሥት ግንባታችን እየተጠቀምን እንዲሆን አደራ እላለሁ፡፡ በድጋሚ መልካም የመውሊድ በዓል ይሁንልን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ነሐሴ 19፣ 2018 ዓ.ም

የ2019ዓ.ም አዲስ ዓመት መልዕክት

ዘመን ከፈጣሪ ለሰው የተሰጠ የመሥሪያ መጽሐፍ ነው። ይህ የመሥሪያ መጽሐፍ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጡ የተወሰኑ ገጾች አሉት። የመጨረሻው ገጽ ተጠናቅቆ የማጠቃለያው ሽፋን እስኪከደን ድረስ የፈለግነውን የመጻፍ መብት በእጃችን ነው። አንዳንዶች ዓለምን የቀየሩ ሐሳቦችንና ሥራዎችን፤ ሌሎች ታሪክን የቀየሩ ዕሳቤዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ጽፈውበታል። በተቃራኒው ዓለምን ያወደሙ፤ ሕዝብ የከፋፈሉና የጨረሱ፤ ተፈጥሮን ያዛቡ፤ ክፋትንና ጭካኔን ያስተማሩ ሐሳቦችንና ተግባራትን የጻፉበትም ጥቂት አይደሉም። ስንፍናንና ድንዛዜን፣ ዕንቅልፍንና ሐኬትን የጻፉም አሉ።

ኢትዮጵያውያን በዚህ የዘመን መጽሐፍ ውስጥ ምን እየጻፍን ነበር? አሁንስ ምን እየጻፍን ነው? ወደፊትስ ምን ለመጻፍ እናስባለን? ከኋላችን ያሰናበትነው አሮጌ ዓመት እና ከፊታችን የምንቀበለው አዲስ ዓመት እነዚህን ጥያቄዎች እንድንመልስ ያስገድዱናል። ዓለምን ያስደነቁ የንግድ፣ የግብርና፣ የሥነ ሕንጻ፣ የዘመን አቆጣጠር፣ የሥነ ከዋክብት፣ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር፣ ሥነ ሥዕልና ሥነ ዜማ፣ ሃይማኖትና ፍልስፍና - በዘመን መጽሐፋችን ውስጥ የጻፍንባቸው የዘመን ገጾች አሉን። በተቃራኒው ረሃብና ቸነፈር፣ ጦርነትና እልቂት፣ መከፋፈልና መለያየት፣ ማነስና መድከም፣ የጻፍንባቸው የዘመን ገጾችም አሉን።የትናንቱ ዘመን ጠባሳውንም ዐሻራውንም፣ ዕዳውን ምንዳውንም ሰጥቶን አልፏል። አሁን ወሳኙ ነገር በቀሩን ዘመናት ምን ቁም ነገር እንሰራለን? የሚለው ነው።

ኢትዮጵያውያን ዛሬ ለትውልድ የሚተርፍ አስደናቂ ታሪኮችን እየሰራን ነው። አረንጓዴ ኢኮኖሚን በአረንጓዴ ዐሻራ፤ ቱሪዝምን በገበታ ፕሮጀክቶች፤ የምግብ ሉዓላዊነትን በበጋ ስንዴና በሌማት ትሩፋት፤ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን በኢትዮጵያ ታምርት እየገነባንና እያጸናን ነው። የኢነርጂ ዐቅማችንን በተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክትና ኑክሌር ቴክኖሎጂ ለማሳደግ፤ የአፈር ማዳበሪያ ግብአቶችን በሀገር ውስጥ ለመሸፈን፤ የአየር መንገድ አድማሳችንን በግዙፉ የቢሾፍቱ አየር ማረፊያ ፕሮጀክት ለማስፋት፣ ነገን አስበን ዛሬ እየተጋን ነው።

የሕዳሴ ግድብን ፍጻሜ፤ የመስኖ ግድቦችን ፍሬ፤ የሩዝ ምርትን ከፍታ፤ የፍራፍሬ ምርትን ተአምር፤ የወጪ ንግድን ጭማሬ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያችንን ውጤት፤ በአፍሪካ የፈጠርነውን የኢነርጂ ትሥሥር፤ ዲጂታል 2030ን ስኬት፤ የኮሪደር ልማታችን የኢትዮጵያን ሀብትና ውበት መግለጥ፤ የዘመን መጽሐፋችን እየመዘገበ ነው። የወንዝ ዳርቻ ልማታችን አፈራችንንም፣ ከተማችንንም፣ ጤናችንንም፣ ውኃችንንም እየጠበቀ መሆኑን፤ መድኃኒት የማምረት ደረጃና ዐቅማችንም እያደገ መሄዱን፤ የማዕድን ፍለጋችን፣

ምርታችንና ሽያጫችን የዘመናት ስብራትን እየጠገነ መምጣቱን፤ የባሕር በር አጀንዳችን ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ማግኘቱን፤ የኢትዮጵያ የተጽዕኖ አድማስ መስፋቱን - የዚህ ዘመን የመጽሐፉ ገጾች እያሠፈሩ ናቸው።

እነሆ የዘመን መጽሐፋችንን የ2019 አዲስ ምዕራፍ የምንጀምረው ሀገራዊ ምክራችንን በስኬት አጠናቅቀን ነው። ይሄንን ምክክር ለዘመናት ኢትዮጵያውያን ይጠይቁት ነበር። ችግራችንን በጦርነት ከመፍታት ይልቅ ለምን አንመካከርም ይሉ ነበር። በየብሔረሰቡ ያለውን የመነጋገርና የመመካከር ባህል ለምን ወደ ፖለቲካው አናመጣውም ይሉ ነበር። የዘመን መጽሐፍ ገጾችን ስናነባቸው ይሄን ጥያቄ ያቀረቡ ወገኖች ብዙ ዋጋ መክፈላቸውን ያስነብቡናል። እኛ ግን ሐሳቡን አመንበት፤ አምነንም ተቀበልነው፤ ተቀብለንም ተገበርነው። ማመናችንና መተግበራችን ትክክል እንደሆነ የሚያሳዩ ውጤቶችንም ምክክሩ አስገኝልን። የመጀመሪያው ውጤት “የጠላት ሚርት መክሸፉ” ነው። ኢትዮጵያውያን ሊመካከሩ አይችሉም፤ ቢመካከሩም ወደ ተቀራራቢ ሐሳብ አይደርሱም የሚለውን ሚርት አክሽፈነዋል። ለመመካከር እንደምናቅድ፤ አቅደን እንደምንጀምር፤ ጀምረን እንደምንጨርስ በሀገራዊ ምክክር አስመስክረናል። ብዝሃ ሐሳቦቻችን በሀገር ጉዳይ የጋራ አቋም ከመያዝ እንደማያግዱን በተግባር አይተናል።

